# የክርስትና ትምህርቶች
# እና
# የእምነት መግለጫዎች

# CATECHISMS, CREEDS
# AND
# CONFESSIONS

የኮምፒዩተር ጽሑፍ
ፍቅርተ ጸጋዬ

## የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በሉተራውያን የእምነት መግለጫዎች ላይ ያላትን አቋም በመተዳደሪያ ደንቧ እንደሚከተለው ገልጻለች፡፡

5.1 ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን፤ ማለትም የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የማይሻሩና የማይለወጡ የመጨረሻ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ታምናለች፤

5.2 ቤተ ክርስቲያኒቱ በቀደምት አባቶች ተዘጋጅተው በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያገኙትን የሐዋርያትን፣ የኒቂያን፣ የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫዎችን ትቀበላለች፡፡

5.3 ቤተ ክርስቲያኒቱ ያልተለወጠውን የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫና የሉተር ካቴኪዝምን የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ ማብራሪያ አድርጋ ትቀበላለች፡፡

## The Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus mentioned her stand on Lutheran Confessions and Creeds in her Constitution as follows:

**5.1** **the Church (EECMY) believes and professes that the Holy Scriptures of the Old and the New Testaments are the Holy Word of God and the only source and infallible norm of all Church doctrine and practice.**

**5.2** **the Church adheres to the Apostles' Creed, the Nicene Creed, and the Athanasian Creed, which were formulated by the early Fathers' and accepted by ancient church.**

**5.3** **the Church sees in the Unaltered Augsburg Confession, which was worded by the Church Reformers, as well as in Luther's Catechisms, as a pure exposition of the Word of God.**

# ማውጫ
# Contents


መንደርደሪያ ሐሳብ ........................................ 5

**Forward**........................................ **6**

መቅድም ........................................ 7

**Preface**........................................ **7**

ሦስቱ ዓለም ዐቀፍ የእምነት መግለጫዎች ........................................ 10

**The Three Ecumenical Creeds**........................................ **11**

የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ........................................ 24

**The Augsburg Confession** ........................................ **25**

ትንሹ የክርስትና ትምህርት........................................ 88

**The Small Catechism** ........................................ **89**

ትልቁ የክርስትና ትምህርት ........................................ 146

**The Large Catechism**........................................ **147**

የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ (በከፊል) ........................................ ***328***

**Formula of Concord (partly)** ........................................ **328**

# ለክርስትና ትምህርቶች እና ለእምነት መግለጫዎች መጽሐፍ
# መንደርደሪያ ዐሳብ

ቡክ ኦፍ ኮንኮርድ በአማርኛ ተዘጋጅቶ በቅርቡ ስለታተመ በኢትዮጵያ የሚገኙትን ሉተራውያን ምእመናንን እንኳን ደስ አላችሁ ስል በታላቅ ደስታ ነው፡፡ ይህ እጅግ ጠቃሚ የሆነውና የሉተራውያንን መሠረተ እምነት የሚያብራራው መጽሐፍ ለአያያዝና ለንባብም በሚመች ሁኔታ ተዘጋጅቶ እንደገና መታተሙ ቄሶች፣ ተማሪዎች እንዲሁም ፍላጎት ያላቸው ምእመናን ሁሉ በቀላሉ ስለሚያነቡትና በውስጣቸውም በ16ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት የእምነት አባቶች ያስተላለፉልንን ሥነ መለኮት በጥልቀት እንዲያጠኑት ስለሚረዳቸው ጌታን እናመሰግናለን፡፡

ዛሬ ማንም ሰው ወደየትኛውም የዓለም ክፍል ቢጓዝ፣ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጹትን የጌታን ትምህርቶች የሚያዛቡ የስህተት ትምህርቶች ወጥመድ ሆነው ያጋጥሙታል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ እንደምንገነዘበው ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ምስክር ሆና ለመቆም በምትጥርበት ጊዜ ሁሉ እንዲህ ያለው ፈተና ይገጥማታል፡፡ ስለዚህ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፈ ስምምነት ውስጥ የሚገኙትን የተሟሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሌሎች ሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ማካፈላቸው እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የሰውን ውድቀት፣ ከኃጢአተኛ ሁኔታው የተነሳ መዳንን ለማግኘት በራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል መገንዘብና ትኩረት መስጠት አለብን፡፡ እውነተኛው የወንጌል ትምህርት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በማርቲን ሉተር እንደገና በተገኘ ጊዜ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ በጸጋ እንደሚድን ተገለጸ፡፡ ትክክለኛው ትምህርት ለጠፉባቸውና እውነትን ለሚፈልጉ ሁሉ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው ይህን ነው፡፡

በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሚዙሪ ሲኖዶስ [ሉ.ቤክሚሲ] የታወቀውና አገልግሎት ሰጪ የሆነው ሉተራን ሄሪቴጅ ፋውንዴሽን የተሰኘው ድርጅት መጽሐፈ ስምምነትን በብዙ ቅጂ ለማሳተም እድሉን በማግኘቱ ክብር ይሰማዋል፤ ለዚህም የልግስና ስጦታ ያበረከቱትን ያመሰግናል፡፡ መጽሐፈ ስምምነት በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት የወደፊት ጉዞአቸው ጽኑ መሠረትን እንዲጥል ጸሎታችን ነው ምክንያቱም መሰረቱ የእግዚአብሔር ቃል ነውና፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙት ሉተራውያን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለቅዱሳን ስለተሰጠ ሃይማኖት ሲጋደሉ ጌታችን እርሱ ይባርካቸው፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ ይሁን፡፡

ቄስ ማቲው ደብሊው. ሄይሴ
ዳይሬክተር
ጥር 2007 ዓ.ም.

## Forward to Amharic and English Catechisms, Creeds and Confessions

It is with great joy that I congratulate my fellow Lutheran believers from Ethiopia upon the printing of the Catechisms, Creeds and Confessions book in side-by-side Amharic and English. We thank the Lord that these valuable expositions of the Christian faith have been printed so that the Church might evangelize and teach its youth from the heritage that has been passed down to us through the ages.

No matter where one travels in the world today, false teaching lays traps that can divert us from our Lord's teaching as expressed in Holy Scripture. Throughout the history of the Church, this has often been the case as the Church strives to be a faithful witness to our Lord Jesus Christ. It is therefore essential that the Lutheran Church share with others the solid, biblical teachings that are found in these texts. We need to acknowledge man's fallen, sinful condition and emphasize that he can do nothing to achieve salvation. The rediscovery of the Gospel by Martin Luther in the 16th century confesses that man is saved by grace through faith alone in Jesus Christ. That is the teaching of the Church that Lutherans can share gladly with those who are lost and are seeking the Truth.

The Lutheran Heritage Foundation, a recognized service organization (RSO) of The Lutheran Church-Missouri Synod (LCMS), is honored and privileged to help print this volume along with the Amharic Book of Concord. We are very thankful to the generous donor who provided the funds to print these books. Our prayer is that these building blocks of the faith will lay a firm foundation for the future of Lutheran churches in Ethiopia because they are based upon the Word of God.

May our Lord bless the Lutherans of Ethiopia as they contend for the faith that was once for all delivered to the saints (Jude 1:3). Soli Deo Gloria!

Rev. Matthew W. Heise
Executive Director
January 2015

# ለክርስትና ትምህርቶች እና ለእምነት መግለጫዎች መጽሐፍ

## መቅድም

ሉተራዊ ማንነትን አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ከሆኑ ወጣቶችም ሆነ ከሌሎች ዘንድ አያሌ ጥያቄዎች ይቀርቡልናል፡፡ የልጆችና ወጣቶች አገልግሎት መምሪያም ይህንን በሚመለከት ያዘጋጃቸው ትምህርቶች፣ ስልጠናዎች፣ ትምህርታዊ ሴሚናሮችና ኮንፍራንሶች ቢኖሩም በቂ ናቸው የሚል እምነት የለንም፡፡ ይህንን ነገር በአጥጋቢ መልኩ ሊመልስና ወጣቱን ስለ እምነቱ በደንብ ሊመግብ የሚችል መጽሐፍ ለማዘጋጀት በምናስብበት ጊዜ ከመጽሐፈ ስምምነት የተሻለ ሌላ መጽሐፍ ማግኘት አልቻልንም፡፡

መጽሐፈ ስምምነትን በዛ አድርጎ ለማሳተምና ለማሰራጨት ሐሳቡ ቢኖረንም መጽሐፉ ተለቅ ያለ መሆኑና በቀላሉ ለመንቀሳቀስ የማያመች መሆኑ ትንሽ ስጋት ሆኖብናል፡፡ ምንም እንኳን ከመጽሐፉ ውስጥ ሊቀነስ የሚገባ ነገር ባይኖርም አሁን የሚነሱትን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመድረስ የሚችልና ወጣቱ በቀላሉ ይዞት ሊንቀሳቀስ የሚችል አነስ ያለ መጽሐፍ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ እንደሆነ በመረዳት ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅተናል፡፡

መቼም ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀቱ የሚጠይቀው የሰው ኃይልና ወጪ ቀላል እንደማይሆን የታወቀ ነው፡፡ በዚህ በኩል ቤተ ክርስቲያንን ለመደገፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካቸው ለማለት እወዳለሁ፡፡ በተለይም ደግሞ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሚዙሪ ሲኖዶስንና የሉተራን ሄሪቴጅ ፋውንዴሽንን ላደረጉልን ድጋፍ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና እያቀረብኩ፤ ደግሜ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ፡፡

ውድ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ይህንን መጽሐፍ በአግባቡ በመጠቀም ሌሎችን ደግሞ በማስተማር ትውልዱ ስለ እምነቱ እንዲያውቅ፣ እግዚአብሔርን እየፈራና እያከበረ እንዲመላለስ አድርጉ፡፡

ፀጋሁን አሰፋ
የልጆችና ወጣቶች አገልግሎት መምሪያ ዳይሬክተር
ጥር 2007 ዓ.ም.

## Perface for the Catechisms, Creeds and Confessions

We have received so many questions regarding Lutheran identity that we conducted trainings, academic seminar and conferences on it. We still don't think that this is enough. To give answers for the above mentioned questions, the best material we found is the Book of Concord.

Though we had a plan to print the Book of Concord in large number, its size and volume is not comfortable to carry as our Holy Bible. This made us to select some items from the book of concord that go in line with many questions that our youth ask (there is nothing that we can throw away from the book of concord). By this we can print a book that is easy to carry everywhere and quench the thrust of the youth.

It is as clear as crystal that preparing this book demands manpower and incurs huge cost. On behalf of the children and the youth of the church, I would like to extend my heartfelt thank to them. May the Lord bless them. My special appreciation goes to the Lutheran Church of Missouri Synod and Lutheran Heritages Foundations

Dear esteemed fellow ministers, please use this book to teach the others and guide them to grow with fear of God.

Tsegahun Assefa

Director of Children and Youth Ministry Department

January 2015

## ምሕፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| [ ] | በመጀመሪያው ጽሑፎች ውስጥ የሌለውን ሐተታ ያመለክታል |
| ANF | *The Ante Nicene Fathers: Translation of the Fathers down to A.D. 325*፣ 10 ጥራዞች፣ ድጋሚ እትም ግራንድ ራፒድስ፣ ኤርድማንስ 1978 |
| AP | Apology of the Augsburg Confession (የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ መከላከያ) |
| BC | ቡክ ኦቭ ኮንኮርድ (መጽሐፈ ስምምነት) |
| BSLK | *Die Bekenntnisschriften der evangelisch-lutherischen Kirche.* 11th ኤድ ጎቲንገን፡- ቫንደንሆክ እና ሩፕሪችት 1992 |
| *BSRK* | *Die Bekenntnisschriften der reformierten Kirche: In authentischen Texten mit geschichtlicher Einleitung und Register.* አርታኢ ኢ.ኤፍ.ኬ.ሙለር ላይፕዚግ፡- ኤ. ዴይች 1903፤ ድጋሚ እትም ዙሪክ፡- ቲዎሎጂስኬ ቡካንድሉንግ 1987 |
| *CA* | ኮንፌሲዮ ኦግስታና (የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ) |
| *CR* | *Corpus Reformatorum.* ጥራዞች 1-28፡- *Philippi Melanthonis Opera Quae Supersunt Omina.* ሃሌ እና ብራንስዊክ፡- ሲ ኤ ሽዌትሽኬ 1834-60 |
| *CSEL* | *Corpus Scriptorum Ecclesiasticorum Latinorum.* 91 + ጥራዞች ቪያና ጌሮልድ 1866 -፡፡ |
| *Enchiridion* | ማርቲን ኬሚኒዝ *Ministry, Word, and Sacraments: An Enchiridion,* ተርጓሚ ሉተር ጠይሎት ሴይንት ሉዊ ኮንኮርዲያ 1981 |
| *EP* | ኢፕቶም ኦቭ ዘ ፎርሙላ ኦቭ ኮንኮርድ (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ማጠቃለያ) |
| *Essays* | ኡልሪች ዝዊንግሊ *On Providence and Other Essays,* አርታዒያን ሳሙኤል ማኩሌ ጃክሰን እና ዊሊያም ጆን ሂንኬ፤ ፊላደልፊያ 1922፤ ድጋሚ እትም፡- ዱርሃም ኤን ሲ ላቢሪንዝ 1983 |
| *Examination* | ማርቲን ኬሚኒዝ፡- *Examination of the Council of Trent,* ተርጓሚ ፍሬድ ክራመር 4 ጥራዞች ሴይንት ሉዊ ኮንኮርዲያ 1971-86 |
| FC | ፎርሙላ ኦቭ ኮንኮርድ (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ) |
| *GCS* | *Die griechischen christlichen Schrifsteller der ersten drei Jahrhunderte.* ላይፕዚግ፡- ጄ. ሲ ሂንሪችስ 1897-፡፡ |
| *JPH* | ኢያን ዲ ቡንቲንግ ትርጉም «ዘ ኮንሴንሰስ ቲጉሪኑስ» *Journal of Presbyterian History* 44 (1966): 45-61. |
| LC | Large Catechism (ትልቁ የክርስትና ትምህርት) |
| Lenker | *Sermons of Martin Luther* አርታኢና ተርጓሚ፡- ጆን ኤን ሌንከር 8 ጥራዞች፤ ድጋሚ እትም፡- ግራንድ ራፒድስ ቤከር 1989 |
| *Loci* 1521 | ሜላንክተን፣ ፊሊፕ *Loci communes theologici 1521.* የእንግሊዝኛ ትርጉም በሜላንክተንና በቡሰር አርታዒ ዊሊያም ጠክ ፊላደልፊያ፡- ዌስትሚኒስተር 1969 |
| *Loci* 1543 | ሜላንክተን፣ ፊሊፕ *Loci communes rerum theologicarum* 1543. የእንግሊዝኛ ትርጉም፡- *Loci communes* 1543 - ተርጓሚ፡- ጄ ኤ ኦ ፕሪዮስ ሴይንት ሉዊ ኮንኮርዲያ 1992 |
| *LW* | *Luther's Works* የአሜሪካ እትም 55 ጥራዞች፡- ፊላደልፊያ፡- ፎርትረስ፣ ሴይንት ሉዊስ፣ ኮንኮርዲያ 1955-86፡፡ |
| *MBW* | *Melanchthons Briefwechsel* አርታዒ ሄንዝ ሼብሌ 10 + ጥራዞች ስቱትጋርት ፍሮማን/ሆልዝቡግ 1977 |
| *MPG* | *Patrologiae cursus completus: Series Graece.* 161 ጥራዞች ፓሪስ እና ተርናውት 1857-66 |
| *MPL* | *Patrologiae cursus completus: Series Latina* 221 ጥራዞች ፓሪስ እና ተርናውት 1859-1963 |
| *NPNF* | *የኒቅያና ድኅረ ኒቅያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የተመረጡ ቤተ መጻሕፍት፡፡* አርታዒ፡- ፊሊፕ ሻፍ 28 ጥራዞች በሁለት ተርታዎች ድጋሚ እትም፣ ግራንድ ራፒድስ፡- ኤርድማንስ 1980-83 |
| NRSV | New Revised Standard Version of the Bible |
| RSV | Revised Standard Version of the Bible |
| SA | Smalcald Articles (የስማልካልድ አንቀጾች) |
| SC | Small Catechism (ትንሹ የክርስትና ትምህርት) |
| SD | Solid Declaration of the Formula of Concord (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ሙሉ መግለጫ) |
| *Six Sermons* | ጃኮብ አንድሪያ *Six Christian Sermons on the Division Which Have Continued to Surface among the Theologians of the Ausburg Confession from 1548 until This Year 1573,* በ*Andreae and the Formula of Concord: Six Sermons on the Way to Lutheran Unity* በሮበርት ኮልብ ሴይንት ሉዊ ኮንኮርዲያ 1977. 58-134 |
| *STh* | ቶማስ አኩዊናስ *Summa Theologiae* |
| Tr | ትሪታይስ ኦን ዘ ፓወር ኤንድ ፕራይሜሲ ኦቭ ዘ ፖፕ (በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሥልጣንና የበላይነት ላይ የቀረበ ጽሑፍ) |
| *Two Natures* | ማርቲን ኬምኒዝ *The Two Natures in Christ,* ተርጓሚ ጄ. ኤ. ኦ ፕሪዩስ፡- ሴይንት ሉዊ፡- ኮንኮርዲያ 1971 |
| WA | ሉተር፣ ማርቲን *Luthers Werke: Kritische Gesamtausgabe [Schriften.]* 65 ጥራዞች ዌማር ኤች ቦህላው 1883-1993 |
| WABr | ሉተር፣ ማርቲን *Luthers Werke: Kritische Gesamtausgabe. Briefwechsel.* 18 ጥራዞች ዌማር፣ ኤች ቦህላው 1930-85 |
| WADB | ሉተር፣ ማርቲን *Luthers Werke: Kritische Gesamtausgabe. Bibel.* 12 ጥራዞች ዌማር፣ ኤች ቦህላው 1906-61 |
| WATR | ሉተር፣ ማርቲን፣ *Luthers Werke: Kritische Gesamtausgabe. Tischreden* 6 ጥራዞች ዌማር፣ ቦህላው 1912-21፡፡ |

# ሦስቱ

# ዓለም አቀፍ የእምነት መግለጫዎች

## ለሦስቱ ዓለም አቀፍ የእምነት መግለጫዎች

## የአርታዒያን መግቢያ

መጽሐፈ ስምምነቱ ከጥንት ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች አንጻር ራሱን መርምሮአል። በመጽሐፈ ስምምነቱ ያሉት የሉተራውያን የእምነት መግለጫ ሰነዶች እያንዳንዳቸው ቢያንስ ከሦስቱ ዓለም አቀፍ የእምነት መግለጫዎች አንዱን ይጠቅሳሉ ወይም ያነሣሉ። የሰነዶቹ ጸሐፊዎች ከመላዋ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር መዋሐዳቸውን ተረድተዋል። የመጽሐፈ ስምምነቱ የራሱ አዘጋጆች የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫን እንደ እምነት መግለጫ ተረድተውታል፤ ወይም፣ በሦስቱ ዓለም አቀፍ የእምነት መግለጫዎች የሚገኘውን ያንኑ እምነት በማንጸባረቅ፣ የግሪኩንና የላቲኑን ቃል በመጠቀም የእነርሱን ዘመን «ምልክት» መርጠዋል።[1] የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ራሱ እንኳ ከእግዚአብሔርና ከፍጥረት (ኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ I-II) ወደ ክርስቶስ (ኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ III-IV)፣ መንፈስ ቅዱስ (ኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ V-VI) ፣ በመጨረሻም ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ ወደ ቅዱሳት ምሥጢራት፣ እንዲሁም ወደ ትንሣኤ (ኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ VII-XV፣ XVII) በመንቀሳቀስ በአጠቃላይ የእምነት መግለጫውን ቅደም ተከተል ይከተላል።[2]

ዓለም አቀፍ የእምነት መግለጫዎችን በዐሥራ ስድስተኛ ክፍለ ዘመን የመሠረተ እምነት መጻሕፍት ማካተት ቢያንስ ለሳክሶኒ ግዛት ዋና የመሠረተ እምነት ጽሑፍ ወደ ሆነው የፊልፕ ሜላንክተን ጽሑፎች ስብስብ፣ የ1560ው *Cropus doctrinae Philppicum* ኮርፐስ ዶክትሪኔ ፊሊፒከም ዘመን ይደርሳል።[3] ይህ ልምምድ በኋለኛ የሉተራን ስብስቦችም ቀጥሎአል። የእነርሱ መካተት በወንጌላውያን የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል ለነበረው ጥልቅ የሆነ ጽኑ እምነት ትኩረት የሰጠው ተሐድሶው ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከመለያየት ይልቅ የዓለም አቀፍዋ ቤተ ክርስቲያን እምነት ዋና አስተምህሮዎችን ደግፎአል፤ መልሶ ግልጽ አድርጐአል። የእምነት መግለጫዎቹ ራሳቸው እንደሚሰጡት ምስክርነት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ ሰዎች ለዚያ ወንጌል መስክረዋል።

## የሐዋርያት የእምነት መግለጫ

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ጽሑፍ በስምንተኛው ክፍለ ዘመን የአሁኑን ቅርጹን ያዘ። ይህም መጀመሪያ በቀደምቱ የሦስተኛው ክፍለ ዘመን በምዕራቡ (ቤተ ክርስቲያን) የተረጋገጠውን የጥንቱን የሮማ የእምነት መግለጫ የመጨረሻ እትም

---

[1] Ep, Rule and Norm, 4, እንዲሁም SD, Rule and Norm, 5. ተመልከት። ቀደም ብሎ ሩፊነስ የእምነት መግለጫ አባባሎችን ለመግለጽ ሲምቦሎን የሚለውን የግሪኩን የተውሶ ቃል ተጠቅሞአል። ቅጽርያኑስ በሥሉስ አምላክ ያሉትን እምነትን የሚመለከቱትን የጥምቀት ጥያቄዎች በመጥቀስ ተጠቅሞበት ነበር።

[2] ተመሳሳይ፣ የእምነት መግለጫ ቅደም ተከተልን በስማልካልድ አንቀጾች ደግሞ ማግኘት ይቻላል።

[3] ይህም የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫንና መከላከያውን፣ እንደዚሁም የሜላንክተንን የሥነ መለኮት መማሪያ መጽሐፍ፣ የ1543ቱ *Loci communes* ሎሲ ኮምዩንስን፣ እንዲሁም እርሱ አቀናብሮአቸው የነበሩ ሌሎች ጽሑፎችን አካትቶአል።

ይወክላል፤ የላቲንዋ ቤተ ክርስቲያን የጥንቱን የሮማ የእምነት መግለጫ እንደ ጥምቀት የእምነት መግለጫ ተጠቅማበታለች።[4] ይዘቱና ተግባሩ በሮማው ንጉሠ ነገሥት ግዛት ሁሉ በነበሩ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ ከዋሉ ተመሳሳይ የእምነት መግለጫዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ነበር። የዚህ የቆየ የእምነት መግለጫ ክፍሎች ፈጣሪ አምላክ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት መሆኑን፣ የክርስቶስን በሥጋ መወለድ፣ ሥነ ስቅለትን፣ እንዲሁም «የሥጋ» ትንሣኤን በማጉላቱ ቀጥተኛ ክርስትናን በተቃወሙ በአንዳንድ የኖስቲክ አማራጮች ተቃውሞ ደርሶበት ወይም እርሱ እነርሱን ተቃውሞ ነበር።

የጥምቀት የእምነት መግለጫዎች ቀስ በቀስ ለኒቅያ የእምነት መግለጫ ስፍራ ከለቀቁበት ከምሥራቁ ቤተ ክርስቲያን በተለየ ሁኔታ በምዕራብ የጥምቀት ቅዳሴዎች ውስጥ በነበረው ስፍራ ተደግፎ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ሥልጣኑንና ሰፊ አጠ ቃቀሙን ጠብቆ ቆይቶአል። በ404 ምናልባትም ቀደም ብሎ በነበረው የሩፊነስ ጥንታዊ የሮማ የእምነት መግለጫ ማብራሪያ ወቅት፣ እያንዳንዱ ሐዋርያ የተለየ አንቀጽ ያቀረበበት፣ የእምነት መግለጫው ሐዋርያዊ አመጣጥ አፈ ታሪክ ተሠራጭቶ ነበር። ይህ ታሪክ ከዚህ ቀደም በዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጥቃት ደርሶበት ነበር። የእምነት መግለጫው የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ አስተምህሮ አጠቃቀም ያንጸባርቃል ማለት ይበልጥ ትክክል ነው።

## የኒቅያ የእምነት መግለጫ

በ325 እንደ እስክንድርያው አትናቴዎስና አርዮሳውያን በመሳሰሉት ጳጳሳት መካከል ትምህርተ ክርስቶሳዊ ክርክር ባስነሣው በቤተ ክርስቲያን መለያየት የታወከው ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ አንድ ወጥ ምላሽ ለማዘጋጀት በኒቅያ እንዲሰበሰብ የጳጳሳት ሲኖዶስን ጠራ። ጉባኤው በቂሣርያው አውሳብዮስ ከቀረበው ወይም ከኢየሩሳሌም የእምነት መግለጫ ከሁለቱ አንዱ ጋር ተመሳሳይ ወደ ሆነው የጥምቀት የእምነት መግለጫ የተወሰኑ ፀረ አርዮሳዊ ሐረጎችን ጨምሮአል።[5] በ381 የቊስጥንጥንያው ጉባኤ Pneumatomachians የኒውማቶማኪያውያን የመንፈስ ቅዱስን ሙሉ መለኮታዊነት ተቃውሞ ለመቋቋም የተወሰኑ ማሻሻያዎችን አክሎአል፤ እንዲሁም ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ክፍል አስፋፍቶአል።[6] የኤፌሶን (431) እና የኬልቄዶን (451) ጉባኤዎች በአጠቃላይ የኒቅያ የእምነት መግለጫ በመባል የሚታወቀውን፣ ይህንን «የኒቅያ ቊስጥንጥንያዊ የእምነት መግለጫ» እንደ ገና አረጋግጠዋል። በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያንና፣ በይበልጥ እያደር በምዕራቡ፣ የእምነት መግለጫው በሥጋ ወደሙ ቅዳሴ ውስጥ ማዕከላዊ ቦታ ይዞአል።

ሦስቱን የሥላሴ አካላት እኩልነት ያጐላው የአውግስጢኖስ ሥላሴያዊ ሥነ መለኮት ባሳደረው ተጽእኖ፣ የምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን፣ በስፔይን በመጀመር፣ በምዕራብ ተጽእኖ ማሳደር የቀጠለውን አርዮሳዊነት በመቃወም በኋላ ላይ («ከአብና

---

[4] ያ ማለት፣ በሥሉስ አምላክ፦ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማመንን በሚመለከት በጥምቀት ቅዳሴ ላሉት ሦስቱ ጥያቄዎች መልሶችን ሰጥቶአል። ይህ ውይይት እንዲህ ላሉ የእምነት መግለጫዎች ስያሜ የሆነው ሲምቦሉም ወይም ምልክት የሚለው ቃል መገኛ ነው። የእምነት መግለጫው የሥላሴ ምልክትና የእርሱ ክርስቲያናዊ ማስታወቂያ ነበር።

[5] ስለ ወልድ አርዮሳውያን «እርሱ ያልነበረበት [ጊዜ] ነበረ» ብለዋል። ለዚህ የኒቅያ የእምነት መግለጫ «ከአብ ጋር አንድ የሆነ» እና «ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ» የሚሉትን በመሳሰሉ ቃላት ምላሽ ሰጥቶአል።

[6] «ኒውማቶማኪያውያን» በአራተኛው ክፍለ ዘመን የመንፈስ ቅዱስን ሙሉ መለኮታዊነት ለካዱ የተሰጠ ስም ነበር። በ370ዎቹ የቂሣርያው ባሲል ተቃውሞአቸዋል።

ከወልድ ይሠርጻል») የሚለውን *filioque* ፊሊዮኬ ሐረግ በሦስተኛው አንቀጽ ላይ አክሎአል።[7] በዐሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን በታላቁ ክፍፍል ጊዜ፣ ይህ በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አወዛጋቢ ጉዳይ ሆኖ ነበር። የፊተኛው (የምሥራቁ) በመጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ የሦስቱን አካላት ልዩነት ጠብቆ ማቆየቱን አጉልቶአል። የኋለኛው (የምዕራቡ) ፊሊዮኬ እውነተኛውን የሥላሴ አንድነት በግልጽ ማንጸባረቁን አጉልቶአል።

## የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ

በእርግጥ አዳሾቹ አሁንም እንጻሰቡት፣ በአትናቴዎስ ያልተጻፈው ይህ የላቲን የእምነት መግለጫ፣ የመካከለኛው ዘመን ልማድን ተከትሎ፣ ከምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶአል፤ የአውግስጢኖስና የአምብሮዝ ሥላሴያዊ ሥነ መለኮትንም ያንጸባርቃል። በመጀመሪያ መስመሩ ምክንያት ብዙ ጊዜ *Quicunque vult* ኩዊኩንኩዩ ቩልት ተብሎ የሚጠራው፣ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን በደቡባዊ ጋውል (ፈረንሳይ) በእጅጉ የተከሠተና በምዕራብም በቻርልማኝ ጊዜ ታዋቂነትን ያገኘ ይመስላል (በዚሁ ጊዜ፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫና *Te Deum* ቴ ዴዩም የመሳሰሉ ሌሎች ጠቃሚ ጽሑፎች ደግሞ በምዕራብ የበላይነትን እያገኙ ነበር።) የእርሱ ረጅም አጻጻፍ የኑፋቄ አስተምህሮን ከሚቃወሙ የተሟሉ ውግዘቶቹ ጋር ቀላል ቅርጽ ካላቸው ከሌሎቹ ሁለት የእምነት መግለጫዎች የተለየ መልክ ያለውና በተለዩ ሥነ መለኮታዊ ጉዳዮች ወይም የእምነት መግለጫ ላይ ይበልጥ የተስፋፉ አስተያየት ይመስላል።

ይህ ትርጉም አስፈላጊ ልዩነቶች በሚከሰቱበት በመጽሐፈ ስምምነት ጥቅም ላይ የዋሉትን የጀርመንኛና የላቲን እትሞች የሚጠቅሱትን በመጀመሪያዎቹ ቋንቋዎች የተጻፉትን የእምነት መግለጫ ጽሑፎችን ይጠቀማል።

[7] ይህ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በቻርልማኝ አገዛዝ በሰፊው ተሠራጭቶል። በተለይ በሻልሣዊ ሌዎ ጊዜ፣ በሮም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ለሁለት ክፍለ ዘመናት ገደማ ይህንን እንቅስቃሴ ተቃውማለች።

## I.
## ሦስቱ ዋና የእምነት መግለጫዎች[1]

## ወይም
## በአብያተ ክርስቲያናት በአንድ ስምምነት ጥቅም ላይ የዋሉ በክርስቶስ የሆኑ የእምነት መግለጫዎች

የመጀመሪያው የእምነት ማሳወቂያ ወይም መግለጫ የክርስትና እምነት መሠረት የተጣለበት፣ የሐዋርያት የጋራ የእምነት መግለጫ ነው። እርሱም እንደሚከተለው ይነበባል፦[2]

1 እኔ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፣ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።[3]

2-3 ደግሞም[4] በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣[5]
4 በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣[6] በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሲኦል
5 በወረደ፣[7] በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፣[8] ወደ ሰማይ በወጣ፣[9] ሁሉን በሚችል
6 በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣[10] በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

7 ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት[11] የሁሉም በሆነች ቤተ ክርስቲያን፣[12]
8 በቅዱሳን አንድነት፣[13] በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣[14] በዘላለም ሕይወት
አምናለሁ።[15] አሜን።

---

[1] ሲምቦሉ፦ «ምልክቶች፣» ከግሪኩ በተውሶ የተገኘ፣ ለእምነት መግለጫ የሚሆን ሙያዊ ቃል።

[2] በእንግሊዝኛ ተናጋሪ ሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ብዙ የተለያዩ የዚህ የእምነት መግለጫና አሁን በጋራ ጥቅም ላይ የዋለው የኒቅያ የእምነት መግለጫ ትርጒሞች አሉ፦ የቆየው (*Lutheran Worship* [St. Louis: Concordia, 1982], 141-43 ተመልከት), የInternational Consultation on English texts ትርጒም (*the Lutheran Book of Worship* [Minneapolis: Augsburg Fortress, 1978], 64-65), ተመልከት፣ እንዲሁም the English Language Liturgical Consultation (*With One Voice: A Lutheran Resoruce for Worship* [Minneapolis: Augsburg Fortress, 1995], 54-55 ተመልከት)። የአሁኑ ትርጒም የጀርመንኛ ትርጒምና እንደ ሮማ የጥምቀት የእምነት መግለጫ አጠቃቀሙ ወደ ሦስተኛው ወይም ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን የሚመለሰው የጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ ተብሎ በሚጠራው በላቲንና በግሪክ ትርጒሞች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በመገንዘብ በመጽሐፈ ስምምነት ጥቅም ላይ በዋለውና መጀመሪያ ከ753 በፊት በተረጋገጠው (*BSLK 21*) በላቲኑ አጻጻፍ ላይ የተመሠረተ ነው።.

[3] ይህ የመጨረሻ ሐረግ በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ ይጐድላል።

[4] ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጒሞች በዚህ አንቀጽ መጀመሪያ አቋም የተወሰደበት «እኔ አምናለሁ»ን በግልጽ ያካትታሉ።

[5] የጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ «ከመንፈስ ቅዱስና ከድንግል ማርያም የተወለደ» ተብሎ ይነባባል።

[6] በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኝም።

[7] በላቲኑ የመጽሐፈ ስምምነት ትርጒም *Ad inferna* በአብዛኞች ሌሎች የላቲን ትርጒሞች *ad inferos* እነዚህ ቃሎች በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኙም። መጀመሪያ የታዩት በአራተኛው ክፍለ ዘመን በስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ውስጥ ነው። በዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ሐረጉ ለሲኦል ስያሜ በመሆን በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ አግኝቶ ነበር። FC IX ተመልከት። በእውነቱ፣ ቃል በቃል የታችኛው ዓለም የሚል ትርጒም ያለው ይህ ቃል፣ ለገሃነም፣ ለሙታን ስፍራ የግሪኩ ትርጒም ነው። ስለ ሆነም፣ የEnglish Language Liturgical Consultation ጽሑፍ «ወደ ሙታን ወረደ» በማለት ይነበባል።

[8] በዘመናዊው የእንግሊዝኛ ትርጒሞች «ከሙታን» የሚሉት ቃሎች አይገኙም።

[9] የጀርመንኛና የእንግሊዝኛ ትርጒሞች ነጠላ ቊጥሩን ይጠቀማሉ።

[10] «ሁሉን የሚችል» የሚለው ቃል በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኝም በዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጒሞችም ጥቅም ላይ አልዋለም።

[11] እነዚህ ቃሎች በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኙም።

[12] ካቶሊካ፦ ከጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ ብዙ ጽሑፎች የጐደለው ይህ ቃል (አስቀድሞ ከተሐድሶ በፊት) በሁለቱም በጀርመንኛው እና በቆየው የእንግሊዝኛ ትርጒም «ክርስቲያን» ተብሎ ተተርጒሞአል።

[13] *communio Sanctorum:* በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኝም (አዳሾቹ ደግሞ ያውቁት የነበረ እውነት፤ LC, Creed, 47) ተመልከት፣ «አንድነት ወይም በቅዱሳት ነገሮች መሳተፍ፣» ማለት፣ በቅዱሳት ምሥጢራት ተብሎ ሊተረጐም ደግሞ ይችላል።

[14] Carnis: «ሥጋ፣» የጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫን ተከትሎና ጀርመንኛው ተከትሎት። በሉተራን እምነት መግለጫ 60 የሉተርን አስተያየት ተመልከት። የነፍስ ሕያውነትን በሚመለከት የተወሰኑ የኖስቲክ የጥንት እምነት አፈ ታሪኮችን ለመቋቋም ይህ ቃል ታክሎአል። የእንግሊዝኛ ትርጒሞች «አካል» በማለት ይተረጒሙታል።

[15] ጀርመንኛ፦ «የዘላለም ሕይወት» ይህ ሐረግ በጥንቱ የሮማ የእምነት መግለጫ አይገኝም።

## ሁለተኛው የእምነት መግለጫ

## ወይም የኒቅያ የእምነት መግለጫ[16]

1 ሁሉን በሚችል[17] ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡[18]
2 እንዲሁም[19] እርሱ ብቻ[20] የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር[21] ከአብ[22] በተወለደ፣
3 ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ
አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ በሆነ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ሁሉ በእርሱ
4 በሆነ፣[23] ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ደኅንነታችንም ከሰማይ በወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል
5 ማርያም[24] ሥጋ ነሥቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመንም ስለ እኛ በተሰቀለ፣
መከራ በተቀበለ፣ በሞተ፣ በተቀበረም፣ በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደ ተጻፈ በሦስተኛው
ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፣ ወደ ሰማይም[25] በወጣ፣ በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና
6 በሙታንም ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው[26] በአንድ
ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡
7 እንዲሁም[27] ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚከበር፣ ከአብና ከወልድ[28] በሚሠርጽ፣ በነቢያት በተናገረ፣ የሕይወት ሰጪና ጌታ በሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ፡፡
8 በአንዲት[29] የሁሉም በሆነች[30] ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንም አምናለሁ፡፡
9-10 ለኃጢአት ማስተስሪያ በአንዲት ጥምቀትም አምናለሁ፡፡ የሙታንን ትንሣኤና ገና የሚመጣውን ዓለም[31] ሕይወትም እጠባበቃለሁ፡፡ አሜን፡፡

---

[16] የመጽሐፈ ስምምነቱ የላቲን ጽሑፍ የሮማን Missal ያንጸባርቃል፡፡ በሌላ መንገድ ካልተመለከተ በስተቀር ይህ ትርጕም በግሪኩ ጽሑፍ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

[17] በኒቅያ፣ በቊስጥንጥንያ፣ እንዲሁም በኬልቄዶን የጉባኤ ዐውድን የሚያንጸባርቅ፣ መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪኩ ንባብ፡፡ ይህ በመካከለኞቹ ዘመናት በላቲኑ ትርጕም «እኔ አምናለሁ» ወደሚለው ተለውጦአል፣ የእምነት መግለጫውን የቅዳሴ አጠቃቀም ያንጸባርቃል፡፡ ይህ ኋለኛ ንባብ በጀርመንኛና በቆዩት የእንግሊዝኛ ትርጕሞች ደግሞ ይገኛል፡፡

[18] ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጕሞች፡- «አብ፣ ሁሉን ቻይ» ተብለው ይነበባሉ፡፡ ጀርመንኛው «በአንድ ሁሉን ቻይ አምላክ፣ አብ» ተብሎ ይነበባል፡፡

[19] ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጕሞች ውሳኔ ላይ የተደረሰበትን «እናምናለን» የሚለውን በግልጽ ያካትታሉ፡፡

[20] የጀርመንኛና ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጕሞችን ተከትሎ፡፡ ግሪኩና ላቲኑ ደግሞ «የእግዚአብሔር ልጅ፣ አንድያ ልጁ» ወይም «አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡

[21] የግሪኩንና የላቲኑን ጽሑፎች ተከትሎ፡፡ ጀርመንኛው «ከመላው ዓለም በፊት» ተብሎ ይነበባል፣ እንዲሁም የቆዩት የእንግሊዝኛ ትርጕሞች «ከዓለማት ሁሉ በፊት» ተብለው ይነበባሉ፡፡ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጕሞች «ለዘላለም» ተብለው ይነበባሉ፡፡

[22] በላቲኑ፣ በጀርመንኛው፣ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ትርጕሞች ግሪኩ እነዚህን ቃሎች ያስቀራል፡፡

[23] በግሪኩ (*homoousion:* አንዱ ዐይነት ህልውና)፣ በጀርመንኛው (*Wesen*)፣ እንዲሁም በዘመናዊው የእንግሊዝኛ ትርጕሞች ንባብ፡፡ ላቲኑና የቆየው እንግሊዝኛ እንደ ቀደም ተከተላቸው፣ «የአንዱ ዐይነት መሠረታዊ ባሕርይ» ተብለው ይነበባሉ፡፡

[24] የጀርመንኛው፣ የላቲኑ፣ እንዲሁም የቆየው የእንግሊዝኛ ትርጕሞች «የ[ላቲን፡-*de*] መንፈስ ቅዱስ፣ ከ[ላቲን፡-*ex*] ድንግል ማርያም» ተብለው ይነበባሉ፡፡ በእንግሊዝኛ ጽሑፎች ላይ የተካሄደው የዓለም አቀፉ ምክክር ትርጕም «በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከድንግል ማርያም ሥጋ ለባሽ ሆነ» ተብሎ ይነበባል፡፡

[25] የጀርመንኛውና የእንግሊዝኛው ትርጕሞች ነጠላ ቊጥሩን ይጠቀማሉ፡፡

[26] የእንግሊዝኛው ትርጕሞች፡- «መንግሥቱ ፍጻሜ አይኖረውም» በማለት ይነበባሉ፡፡

[27] ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጕሞች ውሳኔ ላይ የተደረሰበትን «እናምናለን» የሚለውን በግልጽ ያካትታሉ፡፡

[28] *filioque* እየተባለ የሚጠራው በማናቸውም የግሪክ የጽሑፍ ረቂቆች አይገኝም፤ ነገር ግን የምዕራቡን የሥላሴ አካላት ግንኙነት ግንዛቤን ያንጸባርቃል፡፡ መጀመሪያ በተርቱሊያን ተግባራዊ የሆነው፣ ይህ ዐስተሳሰብ በአውግስጢኖስ ተደግፎአል በአትናቴዎስ የእምነት መግለጫም ተካትቶአል (ከዚህ በታች ተመልከት)፡፡ ከምእት ዓመታት በኋላ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሌዎ ሣልሣዊ የተነቀፈው ዐዲስ ነገር፣ መጀመሪያ በ589 በቶሌዶው ጉባኤ በኒቅያው የእምነት መግለጫ የላቲን ጽሑፍ ውስጥ ገብቶል፡፡

[29] ግሪኩን፣ ላቲኑን፣ እንዲሁም ጀርመንኛውን ተከትሎ፡፡ የእንግሊዝኛ ትርጕሞች ሁሉ ውሳኔ ላይ የተደረሰበትን «እናምናለን» የሚለውን በግልጽ ያካትታሉ፡፡

[30] የጀርመንኛውና የእንግሊዝኛው የቆዩ ትርጕሞች «ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ፡፡

[31] ግሪኩንና ላቲኑን ተከትሎ፡፡ የጀርመንኛውና የእንግሊዝኛው ትርጕሞች «ዓለም» የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ፡፡

# ሦስተኛው የእምነት መግለጫ

## ወይም አርዮሳውያን ተብለው የሚጠሩ መናፍቃንን በመቃወም ያዘጋጀውና እንደሚከተለው የሚነበበው የቅዱስ አትናቴዎስ[32] የእምነት መግለጫ ተብሎ የሚጠራው፡-[33]

1-2 ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች[34] የቤተ ክርስቲያንን
እምነት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበል ያስፈልገዋል። ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሁሉ
ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል።
3 በሦስትነቱ[35] አንድነቱን፣ በአንድነቱም ሦስትነቱን አምነን አንድ አምላክን
4 እናመልካለን። ይህም እውነተኛ የክርስትና እምነት ነው። ይህንንም የምናደርገው አካላቱን
ሳንደባልቅ መለኮታዊ ህልውናውንም ሳንከፍል ነው።[36]
5 ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው፣ የወልድ ለብቻው፣ የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው
6 ስለ ሆነ ነው፤ ሆኖም፣ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ ነው፤ ክብሩ
ሥልጣኑም እኩል ሆኖ ይኖራል።
7-8 ወልድ በህልውናው እንደ አብ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው። አብ
9 አልተፈጠረም፤ ወልድ አልተፈጠረም፣ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም። አብ ወሰን
10 የለውም፤ ወልድ ወሰን የለውም፤ መንፈስ ቅዱስም ወሰን የለውም። አብ ዘላለማዊ ነው፤
11 ወልድ ዘላለማዊ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ ነው። ቢሆንም፣ ዘላለማዊ የሚሆን አንድ
12 እንጂ ሦስት አይደሉም። ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው ሦስት እንዳልሆነ እንደዚሁም
13 ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ ነው። እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ነው፤ ወልድ
14 ሁሉን የሚችል ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው። ቢሆንም፣ ሁሉን የሚችል
አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።
15-16 ስለዚህ አብ አምላክ ነው፤ ወልድ አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው።
17 ሆኖም፣ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም። ስለዚህ አብ ጌታ ነው፤ ወልድ
ጌታ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው። ሆኖም፣ አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች
18-19 አይደሉም። ምክንያቱም የክርስትና እምነት እውነተኛነት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ
መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ የክርስትና እምነት ሦስት አማልክት ወይም
ሦስት ጌቶች እንዳንል ይከለክለናል።
20-21 አብ በማንም አልተሠራም፤ አልተፈጠረም፤ አልተወለደምም። ወልድ ከአብ ብቻ
22 የተገኘ ነው። አልተሠራም፤ አልተፈጠረም፤ ነገር ግን አንድያ ልጁ ነው። መንፈስ ቅዱስ
አልተሠራም፤ አልተፈጠረም፤ አልተወለደምም፤ ነገር ግን ከአብና ከወልድ የሚሠርጽ ነው።
23 ስለዚህ አብ አንድ ስለ ሆነ ሦስት አብ አይደለም፤ ወልድም አንድ እንጂ ሦስት ወልድ
24 አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት አይደለም። ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሌላው
ቀዳሚነት ወይም ደኃሪነት የለውም፤ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ
25 አይደለም። ስለ ሆነም፣ ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው። ከዚህ
የተነሣም (ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው) ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት፣ አንድ አምላክም
26 በሦስቱ አካላት፣ በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል። ለመዳን
የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሴ እንደዚሁ ማሰብ ይገባዋል።

[32] በ0ሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የአትናቴዎስ ጸሐፊነት፣ ፈታኝ ሁኔታ አልገጠመውም። አሁን ይህ ከአምስተኛ ክፍለ ዘመን መገባደጃ የጋሊክ ቤተ ክርስቲያን ያልታወቀ ጸሐፊ ሥራ እንደ ሆነ ታስቦአል።

[33] የ *BSLK* ላቲኑን ተከትሎ። ስለ ሌሎች ትርጒሞች *Lutheran Book of Worship,*54ን እንዲሁም *Lutheran Worship, 134ን* ተመልከት።

[34] የጀርመንኛውና የእንግሊዝኛው የቆዩ ትርጒሞች እዚህና ሙሉ በሙሉ «ክርስቲያን» የሚለውን ይተካሉ።

[35] ወይም፡- «በሦስት አካላት።»

[36] መሠረታዊ ባሕርይ፡- መለኮታዊ ህልውና።

ከዚህም ሌላ የዘላለምን ድነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን አምነን ማስታወቅ ነው:: እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ[38] ከአብ የተወለደ[37] አምላክ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው:: የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ[39] የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው:: በአምላክነቱ ከአብ የተካከለ፣ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው::

አምላክም ሰውም ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት ክርስቶስ አይደለም::[40] አንድ ነው ስንል ግን የሰውን ሥጋ ለበሰ እንጂ መለኮትን ወደ ሥጋ አልለወጠም:: በእርግጥ አንድ የሆነውም በባሕርያት መደባለቅ ሳይሆን፣ በአካል አንድ በመሆኑ ነው:: ምክንያቱም የሚያስብ ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደ ሆኑ ሁሉ አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ ናቸው::

እርሱም ለድነታችን ሲል መከራ የተቀበለ፣ ወደ ሲኦል[41] የወረደ፣ ከሙታን የተነሣ፣ ወደ ሰማይ የወጣ፣ በአብ ቀኝ የተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ፤ በመምጣቱ ጊዜም ሰዎች ሁሉ በሥጋ ተነሥተው ስለ ሥራቸው መልስ ይሰጣሉ:: መልካም የሠሩ ወደ ዘላለም ሕይወት፣ ክፉ የሠሩም ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ::

ይህ እውነተኛው የክርስትና እምነት[42] ነው:: ይህን የማያምንና አጥብቆ የማይዝ ሊድን አይችልም::

---

[38] በዚህ አረፍተ ነገር *saeculum* እንደ «ዘመን» (ጊዜ) ወይም «ዓለም» ሊተረጐም ይችላል::

[37] መሠረታዊ ባሕርይ:- ህልውና:: ጀርመንኛ:- ባሕርይ::

[39] *carne:* ሥጋ

[40] መሠረታዊ ባሕርይ:- ህልውና፣ ባሕርያት::

[41] *ad inferos.* እላይ ቀኑ 7ን ተመልከት::

[42] ጀርመንኛ:- «እውነተኛ የክርስትና እምነት::»

# የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ

## ለኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የአርታዒያን መግቢያ

በ1521 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) የቅድስት ሮማ ንጉሠ ነገሥት ቻርለስ አምስተኛ በወርምስ የንጉሠ ነገሥቱ ጉባኤ ላይ ማርቲን ሉተርንና ትምህርቱን ሕገ ወጥ አድርጎ ፈረጃቸው፤ ደግሞም በሉተር የተሐድሶ መርሐ ግብር መሠረት ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ በግዛቱ የሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ እንዲታገዱ አዘዘ። በ1520ዎቹ መሳፍንትና ከተሞች ከንጉሣዊውና ከሮማ ካቶሊክ ኀይላት ጋር ለፖለቲካ ሥልጣን ሲሉ ያንን መርሐ ግብር በኑረምበርግ (1522፣ 1523) እና በስፔየር (1526፣ 1529) ንጉሠ ነገሥታዊ ጉባኤዎች ውስጥ ለማስተዋወቅ ቈርጠው ነበር። የጀርመን መሳፍንት በራሳቸው ሕሊና ወርምስ በተባለው ጉባኤ የተላለፈውን ውሳኔ ለመተግበር ቃል በገቡበት ስፍራ በ1526 ዓ.ም. በስፔየሩ ጉባኤ በተላለፈው አሻሚ ውሳኔ ምክንያት፣ ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት መራጮች መካከል አንዱ የሆነው መስፍን የሳክሶኑ ዮሐንስ በአካባቢው ከሚገኝ የሮማ ካቶሊክ ጳጳስ ፈቃድ ውጪ በግዛቱ የሚገኙ ሰበካዎችን መደበኛ በሆነ መንገድ ይጐበኛቸው ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘ በማርቲን ሉተርና በዊተንበርጉ መሪ ቄስ ዮሐንስ ቡገንሃገን እየተረዳ ፊሊፕ ሜላክንተን «በጎብኚዎች የተዘጋጁ መመሪያዎች» በሚል ርእስ በሳክሶኒ ለሚገኙ ቄሶች የሚሆኑ የመሠረተ እምነት ትምህርት መመሪያዎችን በ1528 አሳተመላቸው። በ1529 በተደረገው የስፔየሩ ጉባኤ እየተስፋፋ ባለው የሉተራውያን ተሐድሶ ላይ ያነጣጠረውንና አሻሚ የሆነውን የቀድሞ ውሳኔ ቻርለስ አርሞት ነበር። ይህም ከሉተር መሳፍንታዊ ደጋፊዎች ሕጋዊ አቤቱታን ወይም «ፕሮቴስታቲዮ» (ምስክርነት ወይም የእምነት መግለጫን) አስከትሎአል።

ቻርለስ በ1529 ቪየናን ከብበው ከነበሩት ከቱርክ ንጉሠ ነገሥታዊ ኀይላት ጋር ለሚያደርገው ጦርነት ርዳታን መሰብሰብ ፈልጎ ነበር፤ ከፈረንሳይ ጋር ግጭት ውስጥ ስለ ነበረ፣ አንጻራዊ በሆነ መልኩ በዚያ ባሉ የአካባቢ መሳፍንት መሥዋዕትነት በጀርመን የራሱን ኃይል ለማጠናከርና ለማዋቀር ይሻ ነበር። ደግሞም ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይጨነቅ ነበር፤ ግብረ ገባዊና ተቋማዊ ተሐድሶን የማስፋፋት ፍላጎትም ነበረው። በዚያኑ ጊዜ ሉተር ሲያካሄደው የነበረውን የመሠረተ እምነት ተሐድሶ አጣጥሏል። ስለዚህ፣ በጥር ወር 1530 ዓ.ም. ቦሎኛ ውስጥ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቀሌምንጦስ ሰባተኛ ጋር በተደረገ ድርድር በኦጉስቡርግ ከተማ በፀደይ ወቅት መጨረሻ ላይ በተጠራ ንጉሠ ነገሥታዊ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ሃይማኖታዊ መርሐ ግብራቸውን ለጉባኤው እንዲያስረዱ ሉተራውያን መሳፍንትንና ከተሞችን ጠራ። ለዚህ ጉባኤ በመዘጋጀትም ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት መራጮች መካከል አንዱ የሆነው የሳክሶኑ ዮሐንስ በሉተርና በሜላንክተን የሚመሩ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን፣ በሉተር ትምህርት የተማረኩ የሳክሶን እና ሌሎች የአካባቢው ቤተ ክርስቲያኖችን ወደ ተሐድሶ በመሩ ጕዳዮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲያዘጋጁ ኀላፊነትን ሰጣቸው። ቶርጋው ተብለው በሳክሶን ከተማ ስም የተሰየሙት አንቀጾች የካህናት ጋብቻን፣ በጌታ እራት ስላሉት ስለ ሁለቱ ዓይነቶች (ስለ ኅብስቱና ወይኑ)፣ ስለ ቅዱስ ቍርባን ሥነ ሥርዓት መሥዋዕት፣ ስለ ኑዛዜ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ኀላፊነት፣ ስለ ቅስና ማዕርግ፣ ስለ ምንኵስና መሐላ፣ ለቅዱሳን ስለሚቀርብ ልመና፣ በአምልኮ ጊዜ በአካባቢ ቋንቋ ስለ መጠቀም በሚናገሩ ተከታታይነት ባላቸው ረቂቆች መልክ ጐለበቱ።

ሉተር በ1521 ዓ.ም. በንጉሠ ነገሥቱ ሕግ ተላላፊ ተደርጎ በመወገዙ ምክንያት፣ በእርግጠኝነት ሊያዝ ምናልባትም በቻርለስ አምስተኛ ኀይላት ሊሰቀል ወደሚችልበት ወደ ኦግስቡርግ አልተጓዘም። በዚህ ፈንታ፣ ወደ ጉባኤው የሄዱ የሳክሶን ሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን ሜላንክተን መራቸው። በኦግስቡርግ፣ ሜላንክተንን ያጋጠመው፣

በኢንጎልድስታት ከፍተኛ መምህር የነበረው ደግሞም በጀርመን ካሉ የሮማ ካቶሊክ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል ብሩህ ዐስተሳሰብና ጉልህ ስፍራ የያዘው፣ በዚያም ወቅት የዊተንበርጋውያን ቀንደኛ ጠላት በነበረው በዮሐንስ ኤክ የታረመው ዐጺስ እትም ነው። ይህ ጉባኤ ከሉተር ሥራዎች፣ ከሜላንክተንና ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ሥራዎች ከተወሰዱ ጥቅሶች፣ ቤተ ክርስቲያንን ከሚተቹ ወገኖች በተወሰዱ ብዙና ልዩ ልዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሁም የሥላሴን ትምህርት ከሚቃወሙና ዳግም አጥማቂያን ከሆኑ፣ ደግሞም ኡልሪች ዝዊንግሊ እና እንደ እርሱ፣ እውነተኛው የክርስቶስ ሥጋ በጌታ እራት እንደሚገኝ ከሚክዱ ወገኖች ተውጣጥተው ከተወሰዱ ጥቅሶች የተገኙ አራት መቶ አራት ዐሳቦች በጣምራ የቀረቡበት ነው። ኤክ፣ እነርሱን ከዊትንበርግ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ጋር በመመደብ፣ የሳክሶን ሥነ መለኮት ለቤተ ክርስቲያን የታወቁ ብዙ ኑፋቄዎችን አጽንቶአል የሚል አስተያየት ሰጠ። ሜላንክተን ሉተራውያን ከተሐድሶ ያለፈ ጉዳይ ሊያነሡ እንደሚገባ ተገንዝቧል። ደግሞም ሉተራውያን የራሳቸውን ቀጥተኛነትና የሁሉም መሆናቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል። ስለዚህ «አፖሎጂያ» (መከላከያ) የሚለውን የእምነት መግለጫ፣ ስሙን «ለሃያ አንድ አንቀጽ የመሠረተ እምነት ትምህርቶች ርእሶችና ለባለ ሰባት አንቀጽ የተሐድሶ ጥረቶች» ብሎ በመለወጥ የእምነት መግለጫ አዘጋጀ። ይህን በማድረጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን በመግለጽ፣ ደግሞም በሮማ ካቶሊክ ተቃዋሚዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን የሐሰት ትምህርቶች በማውገዝ በዊተንበርግ የተሰጠው የሥነ መለኮት ትምህርት ለካቶሊክ ወግ እውነተኛ ሆኖ መቀጠሉን ለማሳየት ፈለገ። ለዚህ የእምነት መግለጫ የሚሆኑ መሠረተ እምነታዊ አቋሞችን በ1529 ክረምት ለሉተራውያን ማኅበር አስተዳደሮች ከተዘጋጀው ከሸዋባህ አንቀጾች ወስዶ (በተለይ በCAXX) በማስፋፋት፣ ኤክ የሚያቀርባቸውን እጅግ ጠንካራ ክሶች ለማስተባበል እንዲችሉ አድርጎ አቀረበ። የእምነት መግለጫውን መሠረተ እምነት ዝግጅት ለማጠናቀቅ በጥቅምት 1529 በዊተንበርጋውያንና በሌላ ወገን የዙሪኩ ኡልሪክ ዝዊንግሊ ከስዊዘርላንዳውያን ባልደረቦቹ ጋር ያደረጉት ውይይት ውጤት ሆነው ከተዘጋጁት የማርቡርግ አንቀጾች፣ *Confession concerning Christ's Supper* ኮንፌሽን ኮንሰርኒንግ ክራይስትስ ሳፐር ከተሰኘው የሉተር የራሱ የእምነት ማጠ ቃለያ ሦስተኛ ክፍል (1528) እና *Instruction by the Visitors* ኢንስትራክሽን ባይ ዘ ቪዚተርስ ከሚለው ጽሑፍ ወስዶ ተጠቅሞባቸዋል። በእነዚህ ሰነዶች ላይ ተመሥርተው በተዘጋጁት የመሠረተ እምነት አንቀጾች ላይ ተሐድሶ የሚፈልጉ ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶችን በሚመለከት ከሳክሶናውያን ቀደምት ረቂቅ ጽሑፎች የተሻሻለ እትም አክሎባቸዋል።

በኦግስቡርግ ዝዊንግሊ ራሱ በማርቲን ቡሰር መሪነት የራሱን *Ratio fidei* ራቲዮ ፊዴ (የእምነት መሠረት) ላከና ለንጉሡ ነገሥቱና ለአራቱ ከተሞች ስትራስቡርግ፣ ሜሚንገን፣ ሊንዳው እና ኮንስታንስ *Confessio Tetrapolitana* ኮንፌሲዎ ቴትራፖሊታና የተባለውን አቀረበ።

ከብዙ ሳምንታት በኋላ የሮማ ካቶሊክ ወኪሎች ከሆኑ መሳፍንት፣ ከጳጳሳትና ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ጠንካራ ድርድር ከተደረገ በኋላ ሰባቱ ሉተራውያን መሳፍንትና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በሰኔ 25 ቀን 1530 ጉባኤ ላይ የሜላንክተንን የእምነት መግለጫ ደገፉና ለንጉሡ ነገሥቱ፣ በጉባኤው ላይ ለተገኙ መሳፍንትና ለንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ከተሞች ወኪሎች አቀረቡ። ከጀርመን ንጉሡ ነገሥት መራጮች መካከል አንዱ የሆነው የዮሐንስ ግዛት የበላይ ኀላፊ የሆነው ክርስቲያን ባየር የእምነት መግለጫውን ለጉባኤው አነበበው፣ ድምፁም ጐላ ከማለቱ የተነሣ ወደ ውጪ በመንገዱ ላይ በደንብ ይሰማ ነበር። ደግሞም ሜላንክተን በንጉሣዊው ትእዛዝ መሠረት በዚያኑ ጊዜ ለቻርለስ ያስረከበውን የላቲኑን ቅጂ አዘጋጅቶ ነበር።

ቀጣይ ድርድሮች ቀጠሉ፡፡ በዚያኑ ጊዜ የሮማ ካቶሊክ ሥነ መለኮት ዐዋቂዎች በንጉሠ ነገሥቱ ታዘው የዚህን እምነት መግለጫ «ማስተባበያ» አዘጋጁ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም ይህን ሰነድ በመቀበል ሉተራውያኑ ያቀረቡትን የሕጋዊነት ጥያቄ አልተቀበለውም፡፡ በስብሰባው መጨረሻም የሉተራውያን ግዛቶች እስከ ሚያዝያ 15 ቀን 1531 ለሮማ ወደ መታዘዝ እንዲመለሱ አዘዘ፣ አለበለዚያ ተጽእኖ እንደሚገጥማቸው አስታወቀ፡፡

የአጉስቡርግ የእምነት መግለጫ ጽሑፍ በ1531[1] ታተመ፡፡ ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እንደ «ተልእኮ መግለጫ» ተደርጎ ተቀባይነትን በማግኘቱ ምክንያት ሜላንክተን ማሻሻሉን የመቀጠል ግዴታ እንዳለበት ተሰማው፤ በሁለተኛው እትምም (1533) በጀርመንኛው ጽሑፍ ላይ ልዩነቶች መታየት ጀመሩ፡፡ በሦስተኛው (1540) እና በአራተኛው (1542) እትሞች የላቲኑ ጽሑፍ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ተለወጠ፡፡ በ1560ዎቹ እነዚህ ለውጦች አከራካሪ ሆኑ፤ ይህም የእርሱ በጄኔቫውያን ተጽዕኖ አማካይነት የጌታን እራት መሠረተ እምነት መንፈሳዊ ያደረጉበትን ጥረት እውነታነት ለማረጋገጥ ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት መራጮች መካከል አንዱ የፖላቲኔቱ ፍሬደሪክ ሦስተኛ፣ የዚህን “Confessio Augustana Variata” «*ኮንፌሲዮ አውጉስታና ቫሪያታ*» የተለወጠው የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ዐሥረኛ አንቀጽ እንደ ማስረጃ አድርጎ በተጠቀመበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ይህንን አቋም የተቃወሙ “Confessio augustana Invariata,” «*ኮንፌሲዮ አውግስታና ኢንቫሪያታ*» ባልተለወጠው የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ላይ አተኰሩ፤ ይህም የ1531 *editio princeps* ኢዲቲዎ ፕሪንሴፕስ የመጀመሪያው ጽሑፍ ነው፡፡

---

[1] ፊልፕ ሜላንክተን በኅዳር ወር አጋማሽ ላይ በ1530 በተጻፈው፣ ደግሞም በግንቦት 1531 በታተመው በ1531 የመጀመሪያው እትም ላይ የሚከተለውን መቅድም (MBW 1103 = CR 2:445047) አከለበት፡፡ «ይህ የእምነት መግለጫ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀረቡት መሳፍንት ሳያውቁ በአንድ ስግብግብ አታሚ፣ ከስድስት ወር በፊት ታተመ፡፡ በብዙ ስፍራዎች ላይ ሆን ተብሎ የተደረገ ስሕተትን ይዞ በሚታይበት ሁኔታ ታትሟል፡፡ ይሁን እንጂ፣ መሳፍንቱ ቢፈልጉ እንኳ፣ ከሕዝቡ እጅ ሊነጥቁት የማይችሉ በመሆኑ፣ ደግሞም እነዚያ የመጀመሪያው እትም ጉድለቶች ዐዲስ የሐሰት ክሶችን የሚያመጡ ሆነው መገኘታቸው አደገኛ በመሆኑ፣ ሊታረም፣ በድጋሚ ሊመረመርና ሊስተካከል ተገቢ ሆነ፡፡ ለዚህም ስሕተቶች የሆኑ የዚህ ዓይነት ጽሑፎች በዋናነት ርእሳቸውን ይዘው በስፋት እንዳይሰራጩ ማድረግ፣ የመሳፍንቱ ክብር ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት ጉዳይም ነው፡፡ ስለዚህም አሁን እኛ ከ«እውነተኛ» ቅጂዎች በትክክልና በትጋት የተጻፈ የእምነት መግለጫ አሳትመናል፡፡ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠ መከላከያንም አክለንበታል፡፡ ምክንያቱም ወደ ፊት የእምነት መግለጫው አሁን ካለበት ባነሰ መልኩ ይታረማል ብለን ፈርተን ነበር፡፡

«ይሁን እንጂ፣ ባላንጣዎቻችን ከቀኣጣቸው መብረድ የማይፈልጉ ቢሆኑ እንኳ፣ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያሉ፣ እነዚህን መጻሕፍት የሚያነቡ መልካምና አርቆ ዐሳቢ ሰዎች ሁሉ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንና የሁሉም ከሆነችም ቤተ ክርስቲያን የተለየ ቀኖና እንዳልያዝን እንደሚረዱልን ያለ ጥርጥር ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በዚህ ፈንታ የእኛ ሰዎች ባላቸው የተሻለ መብት ጥቂት የተበላሹ አሠራሮችን ይተቻሉ፣ ደግሞም በዚህ ጊዜ እጅግ በጣም ጠንቀኛ በሆኑ ዐስተሳሰቦች የደበዘዙ የክርስትና መሠረተ እምነት ርእሶች ላይ ብርሃናቸውን ይፈነጥቃሉ፡፡ የእምነትን ጽድቅ በተመለከተ እስከ አሁን ድረስ አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ በእርግጥም የዘመኑ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መጻሕፍት ሁሉ ጸጥ ብለዋል፡፡ በንስሐ መሠረተ እምነት ውስጥ [Poenitentia: fee CA XII, n. በ65 ተመልከት]፣ ለሕሊናዎች እርግጠኛና የጸኑ መጽናናቶች በየትኛውም ስፍራ አልተላለፉም፡፡ የኃጢአት ዕዳ ክፍያ መሠረተ እምነት ሕሊናዎችን እየጨፈጨፈ ነበር፡፡ ቅዱሳት ምሥጢራት «ኤክስ ኦፔሬ ኦፔራቶ» (ሥርዓቱን በመፈጸም ብቻ) ያጸድቃሉ የሚለውን ዐስተሳሰብ አንድ ጊዜ በመቀበል ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ አርክሰዋል [CAXIII, n. 75 ተመልከት]፡፡ በውጤቱም ይህ ዐስተሳሰብ የእምነትን መሠረተ እምነት ዘርፈ ብዙ የጣዖት አምልኮ ልምምድንም ፈጥሮአል፡፡ የሰው ወጎች ገደብ በሌለው መልኩ የሚፈጠሩ ስለሆኑ፣ ከመደበኛ ሕጎች ይልቅ በልጠዋል፡- ይህም በከፊል አይሁዳዊ በሆነ የአጉል እምነት አተረጓጐም የሚከሰት ሲሆን፣ በከፊል ደግሞ በጭቈና አገዛዝ የሚመጣ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ፣ የወጎች መላላት ቅር ከመሰኘት ጋር ተነጻጽሮአል፡፡ የቤተ ክርስተያንን አስተዳደር ለማጥፋት ሳይሆን፣ ነገር ግን ወንጌልን ወደ ቀደመው ንጽሕናው ለመመለስና ደግሞም ቀና ሕሊናዎችን ያጽናኑ ዘንድ የእኛ ሰዎች እነዚህን መጥፎ ተግባራት ተችተዋል፡፡

«እንግዲህ 'ክርስቶስ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ' (ማቴ 10፡32-33) ስለሚል፣ ለእውነት ጥብቅና መቆምን ከንቱ አያደርጉም፡፡ ስለዚህ ጽሑፎቹን ደግሞም በሚገርሙ ማሳሳቻዎችና ማታለያዎች እውነትን ለመጋረድ የሚሞክሩትን የባላንጣዎቻችንን ጫጫታ መሠረት በማድረግ ብቻ እንዳይፈርዱብን፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ እጅግ በጣም ተገቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ጉዳዩ የእግዚአብሔርን ክብር ሃይማኖትን፣ ደግሞም የነፍሳትን መዳን የሚመለከት በመሆኑ ምክንያት፣ እኛንም ጭምር እንዲያደምጡን፣ ጉዳዩን በሙሉ እንዲመረምሩ፣ ማንም ዐላዋቂ እንዳይሆን፣ መልካም ሰዎችን ሁሉ እንማጸናለን፡፡»

# የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ

## የላቲን ጽሑፍ

## በኦግስቡርግ ከተማ በ1534 ለማይበገረው ንጉሠ ነገሥት፣ ቻርለስ አምስተኛ፣ ለአውግስጦስ ቄሣር የቀረበ የእምነት መግለጫ

**መዝሙር 119[፡46]**

*«በነገሥታት ፊት ምስክርህን እናገራለሁ፣ አላፍርምም»*[8]

## መቅድም

1 እጅግ የማይበገሩ ንጉሠ ነገሥት፣ አውግስጦስ ቄሣር፣ እጅግ ቸር ለሆኑት አለቃ፡፡
ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ በመጀመሪያ፣ እጅግ በጣም አስፈሪ፣ የክርስትና ስምና
ሃይማኖት፣ ጥንታዊ ጠላት የሆነውን ቱርክን ለመቃወም የሚያስችል፣ እንዲሁም ቀጣይና
2 የተባበረ የጦርነት ዝግጅት በማድረግ ቍጣውን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል፣ ሁለተኛም
ቅዱስ በሆነው ሃይማኖታችንና የክርስትና እምነታችን ላይ በመካከላችን ያሉ የተለያዩ
ጎራዎች የሚኖሯቸው ዐሳቦችና አቋሞች እንዲደመጡ፣ ተገቢ ስፍራ እንዲሰጣቸው፣
በቅንነትና በትሕትና እንዲሁም የጋራ በሆነ ቸርነት ነገሮችን ለማየት በሚበጅ መልኩ
ለመምከር የንጉሠ ነገሥት ግዛትዎ አጠቃላይ ስብሰባ በኦግስቡርግ እንዲደረግ ጥሪ
3 አስተላልፈዋል፡፡ በዚህ መንገድ፣ በሁለቱ ጎራዎች ጽሑፎች ውስጥ በተለያየ መልኩ የታዩ
ነገሮችን በማረም ሁሉንም በአንድ ላይ በመሰብሰብ ወደ አንድ ነጠላ እውነትና ክርስቲያናዊ
4 ስምምነት መመለስ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም፣ በዚህ ዓይነት አንዱን ንጹሕና እውነተኛ
ሃይማኖት ማገልገል እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ልክ በአንዱ በክርስቶስ የምንኖርና የምንዋጋ[9]
እንደ ሆንን፤ እንዲሁ ሁላችን በአንድነትና በስምምነት በአንዷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን
5 መኖር እንችላለን፡፡ እኛ ፊርማችን ከዚህ በታች የሚገኘውና በተጨማሪም ሌሎች ድምፅ
ሰጪዎች፣ መሳፍንትና ግዛቶች፣ አስቀድሞ ወደ ተነገረው ጉባኤ እንደ ተጠራን ሁሉ፣
የንጉሠ ነገሥቱን መመሪያ በመታዘዝ ወደ ኦግስቡርግ መጥተናል፡፡ በእርግጥ አስቀድመው
ከደረሱት መካከል እኛ እንገኛለን ብለን ሳንኩራራ መናገር እንችላለን፡፡
6 ይሁን እንጂ፣ በዚህ የኦግስቡርግ ጉባኤ ላይ ግርማዊነትዎ፣ ከሌሎች ነገሮች
መሐል፣ በጀርመንና በላቲን የየራሳቸውን አስተያየትና ውሳኔ እንዲያቀርቡ ለጀርመን ንጉሠ
ነገሥት መራጮች፣ ለመሳፍንትና ለሌሎች የንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች ጥያቄ አቅርበው ነበር፣
7 በንጉሣዊው ትእዛዝ መሠረት፣ በእኛ በኩል በቂ ውይይት ካደረግን በኋላ ባለፈው ረቡዕ
ለግርማዊነትዎ እንዳስታወቅነው በሚቀጥለው ዓርብ የእምነት መግለጫችንን እናስረክባለን፡፡
8 በዚህም መሠረት፣ እንደ ግርማዊነትዎ መሻት በዚህ ጉዳይ[15] የምናስረክበው የእምነት
መግለጫ ስለ ሃይማኖታችን፣ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በሰባኪዎቻችን በኩል የምናስተምረው
መሠረተ እምነት ሲሆን ይህም በቅዱሳት መጻሕፍትና በንጹሑ የእግዚአብሔር ቃል ላይ
የተመሠረተ ነው፡፡
9 እንግዲህ ሌሎች የንጉሠ ነገሥት መራጮች፣ መሳፍንት፣ እንዲሁም ንጉሣዊ
10 ግዛቶች፣ እላይ በተባለው የግርማዊነትዎ ዐሳብ መሠረት ሃይማኖትን በተመለከተ በላቲንና

---

[8] ይህ ርእስ በ1531 *editio princeps* እና በስድስት ረቂቆች ውስጥ ይገኛል፡፡ ሁለቱ ይህን ማስታወሻ ይጨምራሉ፡- «ከቁርስ በኋላ ከመጥምቁ ዮሐንስ ክብረ በዓል (ማለትም፣ ከሰኔ 25) ቀጥሎ ባለው ቅዳሜ በጉባኤ መካከል አንብብ» ከመዝሙረ ዳዊት 119 የሚጠቀሰው ጥቅስ፣ ሉተር በጊዜው ያደርገው ከነበረው ደብዳቤ መጻጻፍ ጋር የመጣ መሆኑ በአያሌው ይመስላል፤ ለምሳሌ ከኮንራድ ኮርዳተስ የመጣው ደብዳቤ፣ ቀኑ ሐምሌ 6/1530 መሆኑ ተዘግቧል፡፡ (WABr 5:441-42: *LW* 49:353-56)፡፡

[9] በአንቀጽ 1 ላይ እንደ ተመዘገበው፣ ለንጉሠ ነገሥቱና ለአብዛኛው የጀርመን ሕዝብ በኦግስቡርግ ጉባኤ ላይ እጅግ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ሆኖ ውይይት እንዲደረግበት የሚፈለገው ከኦቶማን ቱርክ ጋር የሚደረገው ጦርነት ነበር፡፡ ቀደም ባለው የበልግ ወቅት የቱርክ ኀይላት ቪየናን ከብበው የንጉሠ ነገሥቱን ግዛት እምብርት ለመውረር ዝተው ነበር፡፡

[15] *ካውሳ* (*Causa*) ለሕጋዊ ሂደት የሚሆን ቃል፡፡

በጀርመን መግለጫ አዘጋጅተው ከሆነ ለግርማዊነትዎ ባለን ተግባራዊ መታዘዝ፣ አስቀድሞ
ከተጠቀሱት መሳፍንት፣ ከወዳጆቻችንና ከግዛቶች ሁሉ ጋር በመከባበር እንዲደረግ ተገቢና
ተቀባይነት ባለው አቀራረብ ለመወያየት፣ በዚህም ያለምንም ጥላቻ ከሁለቱም ወገን
ያለመግባባት በታየባቸው ጉዳዮች የሚቀርቡ ጽሑፎችን በመጠቀም ልንስማማ እንድንችል
አንድ እውነተኛ የተቀናጀ ሃይማኖት እንዲገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ይህ መከፋፈል
እንዲቆም ውይይት ለማድረግ መዘጋጀታችንን ቸር ለሆኑ አለቃችን እናቀርባለን፡፡
11 ምክንያቱም በግርማዊነትዎ ትእዛዝ መሠረት ሁሉንም ነገር ወደ እግዚአብሔር እውነት
መምራት ይቻል ዘንድ ሁላችን በአንዱ በክርስቶስ ልንኖርና የእምነትን ገድል ልንጋደል፣
እንዲሁም አንዱን ክርስቶስን ልንመሰክር ይገባል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ እንዲረዳንና
ሰላምንም እንዲሰጥ እጅግ ልባዊ የሆነ ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን፡፡

12 ይሁን እንጂ፣ በግርማዊ ንገሠ ነገሥትነትዎ ትእዛዝ ቀደም ተከተል መሠረት እንደ
ሌላው ወገን የጀርመን ንጉሠ ነገሥት መራጮችን፣ መሳፍንትን፣ እንዲሁም ግዛቶችን
የሚመለከተውን ጉዳይ በዚህ መንገድ ማስተናገድ እርምጃ የማያሳይ፣ እንዲሁም ፍሬ
13 የማያፈራ ከሆነ፣ በእግዚአብሔርና በበጎ ሕሊና ሊደረግ እስከ ቻለ ድረስ፣ በእርግጥ እኛ
በማንኛውም መንገድ የታረቀ የክርስትና አንድነት ዓላማን ሊያገለግል የሚችል ማንኛውንም
14 ነገር ቸል የማንል ነን፡፡ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥትነትዎ ከሌሎች የጀርመን ንጉሠ ነገሥት
መራጮችና የንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች እንዲሁም ይህን ጉዳይ በተከፈተ አእምሮ ከሚሰሙ፣
በታማኝነትና በፍቅር እውነተኛውን ሃይማኖት ለመያዝ ከሚፈልጉ ሁሉ ጋር እነዚህን ነገሮች
ከዚህ ለእኛና ለሰዎቻችን ከሚሆን የእምነት መግለጫ ለማወቅና ለመረዳት በቸርነት ተገቢ
በሆነ መንገድ ዝግጅት ያድርጉ፡፡

15 ደግሞም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ አንድ ጊዜ ሳይሆን በተደጋጋሚ ለንጉሠ
ነገሥቱ መራጮች፣ ለመሳፍንትና ለንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች፣ እንዲሁም በስፔየር በተደረገው
16 ጉባኤ ማለትም በጌታችን ዓመት በ1526፣ በገሃድ በተላለፈውና በተነበበው ትእዛዝም በዚያ
ለተጠቀሱ ጥቂት ምክንያቶች ሲባል፣ ሃይማኖትን በሚመለከተው ጉዳይ ውሳኔ
እንደማያስተላልፉ፣ ነገር ግን ከሮማው ጳጳስ ጋር በመሆን እንደሚሠሩና ጉባኤ እንደሚጠሩ
17 ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ ገልጸዋል፡፡ ይህ እንዲያውም ይበልጥ ሰፋ ባለ መልኩ ከአንድ
18 ዓመት በፊት በስፔየሩ የመጨረሻ ጉባኤ የተገለጸ ነበር፡፡ እዚያ፣ ከሌሎች ነገሮች መካከል፣
ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ ወዳጃችንና ቸር አለቃችን በሆኑት በቦሂሚያና በሃንጋሪ ንጉሥ፣
ፈርዲናንድ፣ ከዚያም በግዛትዎ ቃል አቀባይ ሹማምንት በኩል እነዚህ ነገሮች በመመሪያ
እንዲገለጹ አድርገዋል፡- ጠቅላላ ጉባኤ መጥራትን በተመለከተ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ
በሬገንስበርግ ተሰብስበው የነበሩት፣ ይኸውም፣ በንጉሠ ነገሥት ግዛቱ የመላው ግዛትዎ
አስተዳዳሪ፣ ፕሬዚዳንቱና የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አማካሪዎች፣ እንዲሁም የሌሎቹ
ግዛቶች አምባሳደሮች ያደረጉትን ውይይት ተረድተዋል፤ ከግምት ውስጥም አስገብተዋል፤
እንዲሁም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ፣ ጉባኤ መጥራት ጠቃሚ መሆኑን ወስነዋል፤
19 በቅርቡም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎና በሮማው ጳጳስ መካከል ስምምነት የተደረገባቸው
ጉዳዮች ሰላምንና ክርስቲያናዊ እርቅን ለማምጣት የተቃረቡ ነበሩ፡፡ የሮማው ጳጳስ ይህን
መሰል ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂዱ ማሳመን መቻሉን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ አልተጠ
20 ራጠሩም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሮማው ጳጳስ በመጀመሪያ ደረጃ ይፋ የሆኑ
ደብዳቤዎች በመላክ ለሕዝብ መገለጽ ያለበትን ስብሰባ ለመጥራት ይስማሙ ዘንድ፣ ግርማዊ
ንጉሠ ነገሥትነትዎ እንደሚሠራ በቸርነትዎ አመልክተዋል፡፡

21 ከዚህም የተነሣ፣ ጉዳዩ ይህ ከሆነ፣ በእኛና በሌላው ወገን መካከል ያለው
አለመግባባትም በመግባባት የማይፈታ ከሆነ፣ በንጉሠ ነገሥቱ መራጮች፣ በመሳፍንትና
በንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች ሁሉ ዘንድ፣ በሁሉም የንጉሠ ነገሥት ግዛት ጉባኤዎችና
በግርማዊነትዎ የግዛት ዘመን ዘወትር በትልቅ ስምምነትና እጅግ ላቅ ባለ የውይይት
መንፈስ እንደሚደረግ ሁሉ፣ ለግርማዊነትዎ ባለን ሙሉ መታዘዝ ከምንጠየቀው በላይ እንኳ

ቢሆን እንደዚህ ላለ ክርስቲያናዊ፣ ነጻና አጠቃላይ ጉባኤ እንዘጋጃለን፤ ይህም
22 እንዲፈቀድልን እንለምናለን። በዚህ እጅግ ክብደት ባለው ጉዳይ ላይ እንደዚህ ያለ ጉባኤ
እንዲጠራ ተገቢ በሆነ መንገድና ሕጋዊ በሆነ መልኩ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥትነትዎን
23 አስቀድመን ጠይቀን ነበር። ጉዳያችን መግባባት ባለበት መልኩ እስካልተሰማና ውይይት
እስካልተደረገበት እንዲሁም ክርስቲያናዊ ስምምነት እስካልመጣ ድረስ፣ በዚህም ሆነ
በሌሎች የዕርቅ ድርድሮች ውስጥ ይህንን ልመና ልንተወው ዐላሰብንም፤ አንችልምም፤ እስከ
24 አሁንም ለዚህ ልመና እጃችንን ሰጥተናል። ይህ እንግዲህ ከዚህ በታች ደግሞ በይፋ
የምናውጀው[25] ነው።

## ዋና የእምነት አንቀጾች

### *[I. (1) ስለ እግዚአብሔር]*

1 በእኛ ዘንድ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ስለ መለኮታዊ ባሕርይ አንድነትና ስለ
ሦስቱ አካላት የኒቅያው ጉባኤ ውሳኔ እውነት እንደ ሆነ ያለ ምንም ጥርጥር ሊታመን
2 እንደሚገባ በሙሉ ስምምነት ያስተምራሉ። ይህም አንድ መለኮታዊ ባሕርይ ያለ ሲሆን
እርሱም እግዚአብሔር ይባላል ማለት ነው። እግዚአብሔር፡- ዘላለማዊ፣ ግዑዝ አካል አልባ
የሆነ፣ የማይከፋፈል፣ ሊለካ የማይችል ኀይል፣ ጥበብ፣ መልካምነት ያለው፣ ሁሉን ነገር
3 ማለትም፣ የሚታዩትንና የማይታዩትን ሁሉ የፈጠረና የሚጠብቅ ነው። ሆኖም በአንድነት
ዘላለማውያን የሆኑ፣ አንድ ባሕርይና ኃይል ያላቸው ሦስት አካላት አሉ፡- እነርሱም አብ፣
4 ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በዚህ ረገድ፣ «አካል» የሚለው ቃል የቤተ ክርስቲያን
ጸሐፊዎች ለተጠቀሙበት ትርጒም የሚውል ነው፡- ይህም በሌላው ውስጥ የሚገኝ የአንድን
ነገር ክፍል ለማመልከት ሳይሆን፤ ነገር ግን በራሱ ብቻ የሚቆም መሆኑን ለማመልከት
ነው።
5 ይህንን የእምነት መግለጫ በመቃረን የተነሡ ኑፋቄዎችን ሁሉ፣ ለምሳሌም ልክ
አንዱ መልካም ሌላው ክፉ የሆኑ ሁለት መመሪያዎች አሉ ብለው የሚያስተምሩ እንደ
ማኒያውያን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ቫሌንቲናውያን፣ አርዮሳውያን፣ ዩኖሚያውያን፣
6 መሐመዳውያንና እንደ እነርሱ ያሉ ሌሎችን ሁሉ ያወግዛሉ።[36] አንድ አካል ብቻ ነው
ያለው በማለት የሚከራከሩና በብልሃትና እንዲሁም በአጉል ድፍረት፣ ቃልና መንፈስ ቅዱስ
ለየቅል የሆኑ አካላት አይደሉም፤ ነገር ግን ያ «ቃል» ንግግራዊ ቃልን የሚያመለክት ሲሆን
«መንፈስ» ደግሞ የተፈጠረን እንቅስቃሴ አመልካች ነው ሲሉ የሚከራከሩትን የጥንቶቹንና
የአሁኖቹን ሳሞሳታውያንን ደግሞ ያወግዟቸዋል።

### *[II. (2)ስለ ውርስ ኃጢአት]*

1 በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከአዳም ውድቀት ጀምሮ በተፈጥሮ መሠረት የተዋለዱ የሰው
ልጆች ሁሉ በኃጢአት ማለትም፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ሳይኖራቸው፣ በእግዚአብሔር
2 ባለመታመንና በክፉ ምኞት የተወለዱ ናቸው ብለው ያስተምራሉ። እንዲሁም ይህ በሽታ
ወይም የውርስ በደል[43] በእርግጥ ኃጢአት እንደ ሆነ፣ አሁንም እንኳ በጥምቀትና በመንፈስ
ቅዱስ ዳግም ባልተወለዱት ላይ ኩነኔና የዘላለም ሞት እንደሚያመጣባቸው ያስተምራሉ።

---

[25] *ፕሮቴስታሙር* (*Protestamur*) ሕጋዊ አቤቱታን ያመለክታል።

[36] በእነዚህና በCA I-XXI ባለው የላቲን ትርጒም በአጠቃላይ «ያስተምራሉ» ደግሞም «ያወግዛሉ» የሚሉት «በእኛ ዘንድ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን *CA* I.1 ያመለክታሉ።

[43] *vitium originis.*

3 የውርስ በደል ኃጢአት መሆኑን የሚክዱትንና የክርስቶስን የክብሩን ሥራና ትሩፋት ለማሳነስ፣ ሰዎች በራሳቸው አመክንዮአዊ ችሎታ በእግዚአብሔር ፊት ሊጸድቁ ይችላሉ በማለት የሚከራከሩትን ጴላግዮሳውያንንና ሌሎችን ያወግዛሉ፡፡[44]

*[III. (3)ስለ እግዚአብሔር ልጅ]*

1 በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል፣ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ በብጽዕት
2 ድንግል ማርያም ማኅፀን ውስጥ የሰውን ባሕርይ ነሣ ብለው ያስተምራሉ፤ በዚህም ሁለት
ባሕርያት፡- መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያት ሳይለያዩ፣ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው
ሆኖ፣ «ከድንግል ማርያም በተወለደው፣» እርሱም በእርግጥ «መከራ በተቀበለው፣
3 በተሰቀለው፣ በሞተውና በተቀበረው» በአንድ አካል፣ በአንድ ክርስቶስ በአንድ ላይ
ይኖራሉ፡፡ በዚህም አብን ከእኛ ጋር ሊያስታርቅና ለውርስ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን
ለሰው ልጆች የግብር ኃጢአት ሁሉ ደግሞ መሥዋዕት ሊሆን ነው፡፡ ደግሞም «ወደ ሲኦል
4 ወረደ፤ በሦስተኛው ቀን» በእውነት «ተነሣ፡፡» ከዚያ በኋላ «በአባቱ ቀኝ ለመቀመጥ» «ወደ
ሰማይ ዐረገ፤» ደግሞም ለዘላለም ይነግሣል፤ በፍጥረታት ሁሉ ላይም የበላይ ይሆናል፡፡
5 የሚገዛቸውን፣ የሚያጽናናቸውን፣ ሕያዋን የሚያደርጋቸውን፣ እንዲሁም የዲያብሎስንና
የኃጢአትን ኃይል የሚከላከልላቸውን መንፈስ ቅዱስን ወደ ልባቸው በመላክ በእርሱ
6 የሚያምኑትን ይቀድሳቸዋል፡፡ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ እንደሚለው አንዱ ክርስቶስ
«በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በግልጽ ይመለሳል ...፡፡»

*[IV. (4) ስለ መጽደቅ]*

1 በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሰዎች በራሳቸው ኃይል፣ ምግባር ወይም መልካም ሥራ
2 በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅ እንደማይችሉ ያስተምራሉ፡፡ ነገር ግን በጸጋ[52] ተቀባይነትን
ባገኙና በሞቱ የኃጢአት ዕዳ ክፍያን[53] ከፈጸመው ከክርስቶስ የተነሣ ኃጢአታቸው ይቅር
3 በተባለላቸው ጊዜ እንደ ስጦታ[45] ከክርስቶስ የተነሣ በእምነት ይጸድቃሉ፡፡ እግዚአብሔር
ይህንን እምነት ጽድቅ አድርጎ ይቈጥረዋል (ሮሜ 3[፡21-26] እና 4[፡5])፡፡

*[V. (5)በቤተ ክርስቲያን ስላለ አገልግሎት]*

1 እንግዲህ ይህን እምነት መቀበል እንድንችል፣ ወንጌልን የማስተማርና የቅዱሳት
2 ምሥጢራት አገልግሎት ተቋቁሞአል፡፡ ምክንያቱም በእነዚያ ወንጌልን በሰሙት ሰዎች ውስጥ፣
3 ይህም ማለት እግዚአብሔር በራሳችን ሥራዎች ሳይሆን፣ ነገር ግን ከክርስቶስ የተነሣ፣ ያመኑት ሰዎች በጸጋ ተቀባይነትን እንደሚያገኙ የሚያምኑትን እንደሚያጸድቅ በሰሙት ሰዎች ውስጥ፣ በመሣሪያዎች እንደሚሆን በቃሉና በቅዱሳት ምሥጢራት አማካይነት እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝበት ቦታና ጊዜ እምነትን የሚፈጥር መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ገላትያ 3[፡14]፡- «እንግዲህ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንቀበላለን፡፡»[54]

4 ያለ ውጫአዊው የእግዚአብሔር ቃል በራሳቸው ዝግጅትና ሥራ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰዎች ይመጣል ብለው የሚያስቡትን ዳግም አጥማቂዎችንና ሌሎችን ይቃወማሉ፡፡

---

[44] *rationis:* በሜላንክተን ለ*liberum, arbitrium* (ነጻ ፈቃድ) በተመሳሳይነት ጥቅም ላይ የዋለ፡፡

[52] ለ*gratiam recipi*: እዚህና በV.3, IX2, XX.9, XXVI.5, እና XXVII.37 ሉተርና ሜላንክተን *gratia* የሚለውን ቃል የተረዱት የሮተርዳሙ ኤራስመስ በዐዲስ ኪዳን ማብራሪያው እንደ መለኮታዊ ሞገስ ወይም ምሕረት በመጀመሪያ ባቀረበው መሠረት ነበር፡፡

[53] *Satisfecit*: ካሳ ተፈጽሞአል፡፡

[45] *gratis*: ያለክፍያ፣ በነጻ በቸርነት፡፡

[54] ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ በእጅ ከተጻፉ ከብዙ ቅጂዎችና ከ1531 *editio princeps* ጐድሎአል፡፡

*[VI. (6)ስለ ዐዲሱ መታዘዝ]*

1 በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ይህ እምነት መልካም ፍሬን ከማፍራት ጋር የተቆራኘ ነው፤
ደግሞም ይህ እምነት ከእግዚአብሔር ፈቃድ የተነሣ በእግዚአብሔር የታዘዙትን መልካም
ሥራዎችን ማድረግ ይሻል እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን ለማግኘት በእነዚህ ሥራዎች
2 እንድንታመንባቸው አይደለም የሚለውን ያስተምራሉ። ምክንያቱም የክርስቶስም ትምህርት
[ሉቃስ 17፡10] «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ በምታደርጉበት ጊዜ ...
የማንጠቅም ባሪያዎች ነን» በሉ በማለት እንደሚመሰክረው፣ የኃጢአት ይቅርታና መጽደቅ
በእምነት ይጨበጣሉ። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊዎችም ይህንኑ ያስተምራሉ።
3 ምክንያቱም አምብሮስ፡- «ማንም በክርስቶስ ቢያምን ያለ ሥራ፣ በእምነት ብቻ የኃጢአትን
ይቅርታ እንደ ስጦታ በመቀበል፣ ይድናል የሚለው በእግዚአብሔር የጸና ነው» ይላል።

*[VII. (7)ስለ ቤተ ክርስቲያን]*

1 በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች
የሚለውን ያስተምራሉ። ቤተ ክርስቲያን ወንጌል በንጽሕና የሚሰበክባት፣ ቅዱሳት
2 ምሥጢራትም በትክክል የሚከናወኑባት የቅዱሳን ጉባኤ ናት። ደግሞም እውነተኛ የቤተ
ክርስቲያን አንድነት እንዲኖር የወንጌል ትምህርትንና የቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎትን
በተመለከተ መስማማት በቂ ነው። በሰዎች የተቋቋሙ ሰብአዊ ወጎች፣ ሥርዓቶች ወይም
3 ሥነ ሥርዓቶች በሁሉም ስፍራ አንድ ዓይነት መሆናቸው አስፈላጊ አይደለም። ጳውሎስ
4 «አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ አምላክ፣ የሁሉም አባት...» ይላል [ኤፌ
4፡5፣6]።

*[VIII. (8)ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?]*

1 ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን በትክክለኛ አነጋገር፣ የእውነተኞች አማኞችና የቅዱሳን
ጉባኤ ብትሆንም፣ ነገር ግን በዚህ ሕይወት ብዙ ግብዞችና ክፉ ሰዎች ከእነርሱ ጋር
ተቀላቅለው የሚገኙ በመሆናቸው አንድ ሰው በክፉ ሰዎች የሚከናወኑ ቢሆኑም እንኳ
በቅዱሳት ምሥጢራት ሊጠቀም ይችላል። ይህ ክርስቶስ በ[ማቴ 23፣2] «ጻፎችና
2 ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል ...» ብሎ ከተናገረው ጋር ይስማማል። በክፉ ሰዎች
በሚከናወኑበት ጊዜ እንኳ፣ ቅዱሳት ምሥጢራትና ቃሉ ሁለቱም በክርስቶስ ድንጋጌና
ትእዛዝ ምክንያት ይሠራሉ።
3 የክፉ ሰዎች አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ሊጠቅም ይችላል የሚለውን
የሚቃወሙትንና የክፉ ሰዎች አገልግሎት የማይጠቅምና ዋጋ ቢስ ነው ብለው የሚያስቡትን
ዶናተሳውያንንና እንደ እነርሱ ያሉ ሌሎችን ይቃወማሉ።

*[IX. (9)ስለ ጥምቀት]*

1-2 ጥምቀትን በተመለከተ የእግዚአብሔር ጸጋ በጥምቀት የሚሰጥ በመሆኑ ለድነት
አስፈላጊ ነው፤ ስለዚህም ሕፃናት መጠመቅ ይገባቸዋል ሲሉ ያስተምራሉ። ሕፃናት
በጥምቀት ለእግዚአብሔር በሚቀርቡበት ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ይሆናሉ።
3 የሕፃናትን ጥምቀት የማይቀበሉትና ሕፃናት ያለ ጥምቀት ይድናሉ የሚሉትን
ዳግም አጥማቂያንን ይቃወማሉ።

*[X. (10)ስለ ጌታ እራት]*

1 የጌታ እራትን በተመለከተ የጌታን እራት ለሚበሉ የክርስቶስ ሥጋና ደም በእውነት
2 እንደሚገኙና እንደሚታደሉ ያስተምራሉ። ከዚህ ውጪ የሚያስተምሩትን አይቀበሉም።

*[XI. (11)ስለ ኃጢአት ኑዛዜ]*

1 የኃጢአት ኑዛዜን በተመለከተ ጥፋትን ሁሉ መዘርዘር የማያስፈልግ ቢሆንም፣
ለሚናዘዙቱ በግል የሚሆን ከኃጢአት የመፍታት አዋጅ በአብያተ ክርስቲያናት መያዝ
2 እንዳለበት ያስተምራሉ። ምክንያቱም በመዝሙር [19፡2] «ስሕተትን ማን ያስተውላታል?»
በሚለው መሠረት ስሕተትን መዘርዘር የማይቻል ነው።

*[XII. (12)ስለ ንስሐ]*[68]

1 ንስሐን በተመለከተ ከጥምቀት በኋላ በኃጢአት የወደቁት ምን ጊዜም ወደ ንስሐ[69]
2 በሚቀርቡበት ጊዜ የኃጢአት ይቅርታ መቀበል ይችላሉ፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያን ወደ
3-4 ንስሐ የተመለሱትን ልትፈታቸው ይገባል የሚለውን ያስተምራሉ። እንግዲህ በትክክል
ለመናገር፣ ንስሐ ሁለት ክፍሎችን ይይዛል፦ አንደኛው ጸጸት ወይም ኃጢአት
በሚታወቅበት ጊዜ ሕሊናን የሚነካ ፍርሃት፣ ሌላው በወንጌል ወይም ከኃጢአት በመፍታት
5 በኩል ሕያው የሚሆን እምነት ነው። ይህ እምነት ከክርስቶስ የተነሣ የኃጢአት ይቅርታ
6 እንደ ተደረገ ያምናል፤ ሕሊናን ያጽናናል፤ እንዲሁም ከፍርሃት ነጻ ያወጣል።[70] በዚህም
የንስሐ ፍሬ የሆኑ መልካም ሥራዎች መከተል አለባቸው።
7 አንድ ጊዜ የጸደቁ መንፈስ ቅዱስን ሊያጡ ይችላሉ የሚለውን ትምህርት
8 የሚክዱትን ዳግም አጥማቂዎችን፣ ደግሞም በዚህ ሕይወት አንዳንዶች ኃጢአትን
የማይሠሩ ሆነው በፍጹምነት ይቀጥላሉ ብለው የሚከራከሩትን ይቃወማሉ።
9 ከጥምቀት በኋላ የወደቁትንና ወደ ንስሐ የተመለሱትን መፈታትን ለመስጠት
ፈቃደኛ ያልሆኑት ኖቫቲያውያን ደግሞ የተወገዙ ናቸው።
10 የኃጢአት ይቅርታ በእምነት እንደሚመጣ የማያስተምሩት፣ ነገር ግን በራሳችን
የኃጢአት ዕዳ ክፍያ ጸጋን እንድንቀበል የሚያዙን ደግሞ ተቀባይነት የላቸውም። *ዘላለማዊ
ቅጣትን ወይም የሙታን ነፍስ ጊዜያዊ ማቆያ ቅጣትን ለማስወገድ ቀኖናዊ የኃጢአት ዕዳ
ክፍያ ያስፈልጋል ብለው የሚያስተምሩም ተቀባይነት የላቸውም።*[79]

*[XIII. (13)ስለ ቅዱሳት ምሥጢራት አጠቃቀም]*

1 የቅዱሳት ምሥጢራትን አጠቃቀም በተመለከተ ቅዱሳት ምሥጢራት የተቋቋሙት
በሰዎች ዘንድ የሃይማኖት ምልክቶች እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ከዚያ በበለጠ
እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፈቃድ እንዲያመለክቱና እንዲመሰክሩ፣ በሚጠቀሙባቸውም
2 ሰዎች ውስጥ እምነትን እንዲቀሰቅሱና እንዲያጠናክሩ ነው ብለው ያስተምራሉ። በዚሁ

---

[68] *poenitentia.*

[69] *convertuntur*: የመጀመሪያ መለወጥንና የየዕለቱ ንስሐን በአንድነት ለማመልከት ሉተራውያን የተጠቀሙበት ቃል።

[70] ይህ ቃል ከሁለት ይልቅ ሦስት ክፍሎችን፦ ጸጸትን፣ ኑዛዜንና ከኃጢአት መፍታትን እንዲሁም የኃጢአት ዕዳ ክፍያን ከሚይዘው ከሮማ ካቶሊክ ምሥጢረ ንስሐ ልዩነቱን የበለጠ ግልጥ ያደርጋል። Gratian, *Decretum II*, chap. 33, q. 3; *De poenitentia*, dist 3 chap. 8; and *Instructions for the visitors* (1528) (WA 26:220, 1-19; LW 40:293-97) ተመልከት።

[79] ዘመም ባሉ ፊደላት የተጻፈው ክፍል በመጀመሪያ በ1531 *editio princeps* የተጨመረና ደግሞ በ1580 እና በ1584 በመጽሐፈ ስምምነት የተገኘ ነው።

መሠረት፣ ቅዱሳት ምሥጢራት ጥቅም ላይ የሚውሉት በቅዱሳት ምሥጢራት አማካይነት
የተሰጡና የተገለጡ ተስፋዎችን የሚያምን እምነት እንዲያድግ ነው፡፡
3 *ስለዚህ ቅዱሳት ምሥጢራት* ex opere operato (ኤክስ ኦፔሬ ኦፔራቶ) (*ሥርዓቱን*
*በመፈጸም ብቻ*) *እንደሚያጸድቁ የሚያስተምሩትንና በቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎት*
*የኃጢአት ስርየት እንደሚገኝ የሚያምን እምነት እንደሚያስፈልግ የማያስተምሩትንም*
*ያወግዛሉ፡፡*[80]

*[XIV. (14)ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት]*

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትን በተመለከተ በትክክል ካልተጠራ በቀር ማንም ሰው በቤተ ክርስቲያን በይፋ ማስተማር ወይም ቅዱሳት ምሥጢራትን ማከናወን የለበትም ብለው ያስተምራሉ፡፡[81]

*[XV. (15)ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓቶች]*

1 የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓቶችን በተመለከተ ያለ ኃጢአት ሊጠበቁ የሚችሉትና
በቤተ ክርስቲያን ለሰላምና ለመልካም ሥርዓት አስተዋጽኦ የሚያደርጉት፣ ለምሳሌ አንዳንድ
በዓላት፣ ዐውደ ዓመት፣ የመሳሰሉት ሥርዓቶች መከበር አለባቸው ብለው ያስተምራሉ፡፡
2 ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ዓይነት አምልኮ ለደኅንነት አስፈላጊ እንደ ሆነ አድርገው
በሰው ሕሊና ላይ ሸክም እንዳይጭኑ ለሰዎች ማሳሰቢያ ተሰጥቶአቸዋል፡፡
3 ደግሞም የእግዚአብሔርን ሞገስ ለማግኘት፣ ጸጋን ለማትረፍ እንዲሁም የኃጢአት
ዕዳ ክፍያን ለመፈጸም የተቋቋሙት የሰው ወጎች ወንጌልንና የእምነትን ትምህርት
4 የሚቃወሙ እንደ ሆኑ ማሳሰቢያ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ ምግቦችንና ቀናትን፣ ወዘተ በተመለከተ
ጸጋን ለማትረፍና የኃጢአት ዕዳ ክፍያን ለመፈጸም የተቋቋሙት መሐላዎችና ወጎች
የማይጠቅሙና የወንጌል ተቃራኒ የሆኑት ለዚህ ነው፡፡

*[XVI. (16)ስለ ዜግነት ጉዳዮች]*

1 የዜግነት ጉዳዮችን በተመለከተ ሕጋዊ የዜግነት ድንጋጌዎች የእግዚአብሔር
2 መልካም ሥራዎች መሆናቸውንና ክርስቲያኖች የመንግሥት ሥልጣንን ለመያዝ፣ በሕግ
ችሎቶች ለመሥራት፣ በንጉሣዊና በጊዜው ባሉት ሌሎች ሕግጋት ጉዳዮችን ለመወሰን፣
ፍትሐዊ ቅጣቶችን ለመጣል፣ ፍትሐዊ ጦርነትን ለማወጅ፣ በውትድርና ለማገልገል፣ ሕጋዊ
ውሎችን ለመዋዋል፣ ንብረት ለማፍራት፣ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በሚፈልጉበት ጊዜ
ቃለ መሐላ ለመፈጸም፣ ጋብቻ ለመፈጸም እንደሚችሉ መፈቀዱን ያስተምራሉ፡፡[89]
3 ክርስቲያኖች እንዲህ ያሉ የመንግሥት ኃላፊነቶችን እንዳይዙ የሚከለክሉትን ዳግም
አጥማቂዎችን ያወግዛሉ፡፡
4 ወንጌል ዘላለማዊ የሆነ የልብን ጽድቅ ስለሚያስተላልፍ፣ እግዚአብሔርን
በመፍራትና በእምነት ሳይሆን ከመንግሥት ኃላፊነቶች ራስን በማግለል መንፈሳዊ ፍጽምና[90]
5 ይገኛል የሚሉትን ደግሞ ያወግዛሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ወንጌል መንግሥትን ወይም
ቤተሰብን የሚንቅ ሳይሆን ነገር ግን ሁለቱም እንደ እግዚአብሔር ድንጋጌና የፍቅር
6 ልምምድ በእነዚህ ትእዛዛት በፍጹም እንዲጠበቁ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ኃጢአት እንዲሠሩ

---

[80] (ከቀኁ.79 ጋር ተመሳሳይ ነው)
[81] *Rite vocatus* ማለት በመደበኛ ሁኔታ ተገቢ በሆኑ ባለ ሥልጣናት የተጠራ ነው፡፡ ይህም «ሥርዓትን የመፈጸም» ጉዳይ አይደለም፡፡
[89] *ducere uxorem, nubere*: እንደ ቅደም ተከተላቸው በላቲን የወንዶችንና የሴቶችን ጋብቻ የሚመለከት ነው፡፡
[90] *perfectio evangelica*, ለምንኵስና ሕይወት የሚሆን ቴክኒካዊ (ሙያዊ) ቃል ነው፡፡ CA XXVII. 49-55 ተመልከት፡፡

ካልታዘዙ በቀር ክርስቲያኖች ለመንግሥት ባለ ሥልጣናትና ለሕግ መገዛት ይጠበቅባቸዋል፡፡
7 ምክንያቱም ኃጢአት እንዲሠሩ ከታዘዙ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ይበልጥ ሊታዘዙ
ይገባል (የሐዋ 5[፡29])፡፡

*[XVII. (17)ስለ ክርስቶስ ለፍርድ መመለስ]*

1 በዓለም ፍጻሜ ክርስቶስ ለፍርድና ሙታንን ሁሉ ሕያዋን ለማድረግ ይገለጣል ብለው
2 ደግሞ ያስተምራሉ፡፡ ለጻድቃንና ለተመረጡት የዘላለምን ሕይወትና ፍጻሜ የሌለውን ደስታ
3 ይሰጣል፤ ነገር ግን ዓመፀኞችንና ዲያብሎስን ፍጻሜ በሌለው ሥቃይ ይፈርድባቸዋል፡፡
4 ለተኮነኑ ሰዎችና ለዲያብሎስ ቅጣት ፍጻሜ አለው ብለው የሚያስቡትን ዳግም
አጥማቂዎችን ያወግዛሉ፡፡
5 ከሙታን ትንሣኤ አስቀድሞ ቅን የሆኑ ሰዎች የዓለምን መንግሥት ሲይዙ፣ ክፉዎች
ደግሞ በየስፍራው ሁሉ ይጨቈናሉ እያሉ የአይሁድን ዐስተሳሰብ የሚያሠራጩትን ሌሎችን
ደግሞ ያወግዛሉ፡፡

*[XVIII. (18)ስለ ነጻ ፈቃድ]*

1 ነጻ ፈቃድን በተመለከተ የሰው ፈቃድ ሕዝባዊ ጽድቅን ለመሥራትና ለአመክንዮ
2 የሚገዙ ነገሮችን ለመምረጥ የተወሰነ ነጻነት አለው ብለው ያስተምራሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያለ
መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ወይም መንፈሳዊውን ጽድቅ ለመሥራት ኃይል
አይኖርም፤ ምክንያቱም «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና
3 አይቀበለውም» [1ቆሮ 2፡14]፡፡ ነገር ግን ይህ ጽድቅ በልብ ውስጥ የሚፈጠረው ሰው በቃሉ
4 አማካይነት መንፈስ ቅዱስን በሚቀበልበት ጊዜ ነው፡፡ አውግስጢኖስ *ሂፖግኖስቲኮን*
(*Hypognosticon*) በተሰኘው 3ኛ መጽሐፍ በብዙ ቃላት ይህንን ይላል፡- «ሰዎች ሁሉ
የአመክንዮ ዳኝነት ያለው ነጻ ፈቃድ አላቸው ብለን እንመሰክራለን፡፡ ነገር ግን ያለ
እግዚአብሔር ለአሁኑ ሕይወት ብቻ የሚሆኑ መልካም ወይም ክፉ ሥራዎችን ከመሥራት
በስተቀር፣ እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ሥራዎችን ሁሉ ሊፈጽሟቸው ቀርቶ ሊጀምሯቸው
5 እንኳ አይችሉም፡፡ 'መልካም ሥራዎች' ያልኩት በተፈጥሮ ውስጥ ካለ በጎነት
የሚመነጩትን፣ በእርሻ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆንን፣ መብላትንና መጠጣትን፣
ጓደኛ ማፍራትን፣ ልብስ መልበስን፣ ቤት መሥራትን፣ ማግባትን፣ ከብት ማርባትን፣ ጠ
ቃሚ የሆኑ የተለያዩ ክህሎቶችን መማርን፣ ወይም የአሁኑን ሕይወት የሚመለከቱ
6 ማናቸውንም መልካም ሥራዎች መሥራትን ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዳቸውም ያለ
መለኮት ምሪት አይሆኑም፤ በእርግጥም እነርሱ የሚገኙትና የሚኖሩት ከእርሱና በእርሱ
7 ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ 'ክፉ ሥራ' ያልኩት ጣዖትን ለማምለክ፣ ሰውን ለመግደል ወዘተ.
ያለውን ፍላጎት ነው፡፡
8 ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ በተፈጥሮ ኃይል ብቻ እግዚአብሔርን ከሁሉ ነገር
አብልጠን ልንወድደው እንችላለን፤ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት «በተግባራቱ
ባሕርይ መሠረት»[100] ልንጠብቅ እንችላለን እያሉ የሚያስተምሩትን ጴላጊዮሳውያንንና
9 ሌሎችንም[101] ያወግዛሉ፡፡ ተፈጥሮ በተወሰነ ደረጃ ውጫአዊ ሥራዎችን እንደ ስርቆትና

---

[100] *ኩአድ ሰብስታንቲያም አክቱም* (*Quoad substantiam actuum*):- ሰው ተቀባይነት የሚያስገኝለት (*gratia gratum faciens*) የተለየ የጸጋ «ባሕርይ» እንዲሠርጽበት በተደረገ ጊዜ ብቻ ሕጉ በእውነት መፈጸም እንዳለበት በሚጠይቅ በእግዚአብሔር፣ «በሕግ ሰጪው ዓላማ መሠረት ሳይሆን» እንደ ፊደሉ ብቻ የመለኮት ትእዛዛትን ለመፈጸም ሰው ላለው ተፈጥሮአዊ ችሎታ ጥቅም ላይ የሚውል ፍልስፍናን ማዕከል ያደረገ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ሙያዊ ቃል፡፡ እንደ ኃጢአተኞች የሰው ልጆች ያለ ጸጋ ሕጉን የመፈጸም ችሎታ እንዳላቸውና ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደሚያስገኝላቸው አጽንዖት ለመስጠት ይህ ልዩነት በጆን ዱንስ ስኮተስ *Commentary on the Sentences* III, 27 እና በገብርኤል ባይኤል *Commentary on the Sentences* II, 28B ይደገፉ ነበር፡፡

[101] እንደ ገብርኤል ባይኤል ያሉ፡

*ግድያ ያሉትን ከመፈጸም እጆችን መሰብሰብ ቢችልም ነገር ግን እግዚአብሔርን እንደ መፍራት፣ በእግዚአብሔር እንደ መታመን፣ እንደ ትዕግሥት ወዘተ. ያሉትን ውስጣዊ መነሣሣቶችን ሊሠራ አይችልም።*[102]

*[XIX. (19)ስለ ኃጢአት መንሥኤ]*

የኃጢአት መንሥኤን በተመለከተ እግዚአብሔር ፍጥረትን ቢፈጥርና ቢጠብቅም፣ የኃጢአት መንሥኤ የክፉዎች፣ ማለትም የዲያብሎስና የዓመፀኞች ሰዎች ፈቃድ ነው ብለው ያስተምራሉ። ክርስቶስ በዮሐንስ 8[:44] «[ዲያብሎስ] ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል» ሲል እንደሚገልጸው ፈቃዳቸው በእግዚአብሔር እስካልታገዘ ድረስ ከእግዚአብሔር ርቆአል።

*[XX.] (20)ስለ እምነትና መልካም ሥራ*

1-2 የእኛ ሰዎች መልካም ሥራን ይከለክላሉ በማለት በሐሰት ይከሰሳሉ። ምክንያቱም
በዐሥርቱ ትእዛዛት እና በሌሎችም በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጁት
ጽሑፎቻቸው ሁሉንም የሕይወት ዓይነትና አካሄድ በሚመለከት፣ ማለትም ምን ዓይነት
የአኗኗር ዘይቤና በየትኛውም የሥራ መስክ የትኛዎቹ ተግባራት እግዚአብሔርን ደስ
3 እንደሚያሰኙ፣ ጠቃሚ መመሪያ እንደ ሰጡ ይመሰክሩላቸዋል። በቀደሙት ጊዜያት
እንደነዚህ ስላሉ ነገሮች ሰባኪያን ያስተምሩ የነበረው እጅግ አነስተኛ ነበር። በዚህ ፈንታ፣
ስለ ተወሰኑ በዓላትና አጽዋማት፣ ስለ ወንድማማችነት፣ ስለ ሃይማኖታዊ ጉዞ፣ ስለ ቅዱሳን
አምልኮ፣ ስለ መቁጠሪያዎች፣ ስለ ምንኩስናና ስለ መሳሰሉት፣ እዚህ ግቡ ስለማይባሉና
4 ስለማያስፈልጉ ሥራዎች አጥብቀው ያሳስቡ ነበር። ባላጋራዎቻችን ስለ እነዚህ ነገሮች
እንዲያስታውሱ በመደረጋቸው አሁን እየተዉአቸው ሲሆን በቀደሙት ጊዜያት ያደርጉት
5 የነበረውን ያህል እንደነዚህ ያሉ እርባና ቢስ ሥራዎችን እየሰበኳቸው አይደለም። ከዚህ
በፊት አስገራሚ በሆነ ዝምታ ይታለፍ የነበረውን እምነትን ማንሣት ደግሞ ጀምረዋል።
6 በሥራ ብቻ እንደማንጸድቅ ያስተምራሉ፣ ነገር ግን በሁለቱም እንጸድቃለን በማለት
7 እምነትንና ሥራን ያጣምራሉ። ይህ ትምህርት ከፊተኛው ይልቅ ሊታገሡት የሚቻልና
ከቀድሞው ትምህርታቸው ይልቅ መጽናናትን መስጠት የሚችል ነው።
8 ስለዚህ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋና መሆን የሚገባው እምነትን የሚመለከተው
ትምህርት ለረጅም ጊዜ በመደብዘዝ ተዳክሞ ቆይቶአል፦ ይኸውም በእምነት የሚገኘውን
ጽድቅ በተመለከተ በስብከት ውስጥ ብርቱ ዝምታ እንዳለ፣ በአንጻሩ ደግሞ ስለ ሥራዎች
የሚሰጠው ትምህርት ብቻ በቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋ እንዳለ ሁሉም ሰው ሊቀበለው
ይገባል፦ የእኛ ሰዎች ስለ እምነት በሚከተለው መንገድ አብያተ ክርስቲያናትን
አስተምረዋል፦
9 ለመነሻ ያህል፣[105] ሥራችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅ ወይም ጸጋንና
የኃጢአት ይቅርታን ሊያስገኝ እንደማይችል፣ ነገር ግን በእርሱ አማካይነት ከአብ ጋር ዕርቅ
ከተደረገበት፣ እርሱ ብቻ መካከለኛና የማስተሰሪያ መሥዋዕት ከተደረገው ከክርስቶስ የተነሣ
ወደ ጸጋ እንደምንገባ ባመንን ጊዜ ይህንን በእምነት ብቻ እንደምናገኝ አብያተ
10 ክርስቲያናትን ዐሳስበዋል። ስለዚህ፣ በሥራ ጸጋን እናገኛለን ብለው የሚተማመኑ ሁሉ
የክርስቶስን ሥራና ጸጋ ይንቃሉ፤ ክርስቶስ ስለ ራሱ [ዮሐ 14፡6] «እኔ መንገድና እውነት

---

[102] የ1531 *ኤዲቲዮ ፕሪንሴፕስ (editio princeps)* እና የ1580 እና የ1584 *የመጽሐፈ ስምምነት የላቲን ትርጒሞች ዘመም ባሉ ፊደላት የተጻፉትን ቃላት ይጨምራሉ።*

[105] *ይህ ማጠቃለያ ሦስት ክፍሎች አሉት፦ አንቀጽ* 9-22፣ 23-26 እና 27-34።

ሕይወትም ነኝ» ብሎ ሳለ፣ ያለ ክርስቶስ በሰው ኃይል ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰንን
መንገድ ይፈልጋሉ።
11 ይህ እምነትን የሚመለከት ትምህርት ጳውሎስ በሁሉ ስፍራ የሚያነሣው ነው። ኤፌ
2[፡8-9] «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም . . . ከሥራ አይደለም።»
12 ደግሞም በጳውሎስ ትምህርት ላይ ዐዲስ ትርጒም በማታለል እንደ ፈጠርን አድርጎ
13 ማንም እንዳይተቸን፣ ይህ አጠቃላይ አካሄድ በአበው ምስክርነት የሚደገፍ ነው። የሥራን
መንፈሳዊ ትሩፋት በመቃወም አውግስጢኖስ በብዙ መጻሕፍት ለጸጋና በእምነት ለሚገኘው
14 ጽድቅ ይሟገትላቸዋል። አምብሮስም (*Concerning the Calling of the Gentiles*) *ኰንሰርኒንግ ዘ
ኰሊንግ ኦፍ ዘ ጀንታይልስ*[106] በሚለው ጽሑፍና በሌሎችም ስፍራዎች ተመሳሳይ ነገሮችን
ያስተምራል። *ኰንሰርኒንግ ዘ ኰሊንግ ኦፍ ጀንታይልስ* (*Concerning the Calling of the
Gentiles*) በሚለው ጽሑፍ፡- «በጸጋ የሚገኘው ጽድቅ አስቀድሞ በሚፈጸም በጎ ምግባር
የሚገኝ ከሆነ፣ በክርስቶስ ደም መዋጀት ዋጋ አይኖረውም፤ ለሰው ሥራዎች ቅድሚያ
መስጠትም ለእግዚአብሔር ምሕረት የቀዳሚነትን ስፍራ አይሰጥም። ምክንያቱም የሰጪው
ነጻ ስጦታ መሆኑ ቀርቶ የሠራተኛው ደመወዝ ስለሚሆን ነው» ይላል።
15 በተጨማሪ፣ ምንም እንኳ ይህ ትምህርት የሕይወት ልምምድ በሌላቸው ሰዎች
ቢናቅም፣ ለታመኑና ለትጉሃን ጎሊናዎች ግን እጅግ በጣም ከፍ ያለ መጽናናትን
እንደሚሰጥ በልምምድ ይደርሱበታል። ምክንያቱም ጎሊናዎች ከክርስቶስ የተነሣ ዕርቅ
ያደረገ አምላክ እንዳላቸው እርግጠኞች በሚሆኑበት ጊዜ በእምነት ብቻ ሊያርፉ ይችላሉ
16 እንጂ በማንኛውም ሥራ አይደለም። ጳውሎስ በሮሜ 5፡[1] እንደሚያስተምረው፡- «እንግዲህ
17 በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ … ሰላምን እንያዝ።» ይህ ትምህርት በሙሉ፣
ከዚያ ከተሸበረ ጎሊና ትግል ጋር መታየት አለበት፣ ከዚያ ትግል ተለይቶም ሊታወቅ
18 አይችልም። ለዚህ ነው ክፉዎችና ልምምድ የሌላቸው ሰዎች ክፉኛ የሚፈርዱበት።
ምክንያቱም የክርስቲያን ጽድቅ ማኅበራዊና ፍልስፍናዊ ጽድቅ እንጂ ምንም እንዳልሆነ
ያስባሉ።
19 በቀደሙት ጊዜያት፣ ጎሊናዎች በበጎ ሥራ መሠረተ እምነት ይበሳጩ ነበር፤
20 ከወንጌል መጽናናትን አልሰሙም። ጸጋን ለማግኘት ተስፋ ወደ አደረጉባቸው ስፍራዎች ወደ
ምድረ በዳ፣ ወደ ገዳማት በምንኵስና ለመኖር እንዲገቡ ጎሊና አንዳንዶችን
21 አስገድዶአቸዋል። አንዳንዶች ጸጋን ለማግኘትና የኃጢአትን ዕዳ ለመክፈል ሌሎችን
22 ሥራዎች ዐቅደዋል። በዚህ ምክንያት የተጨነቁ ጎሊናዎች መጽናናትን እንዳያጡ ነገር ግን
በክርስቶስ በማመን ጸጋና የኀጢአት ይቅርታ እንደሚገኝ ያውቁ ዘንድ በክርስቶስ የማመንን
ትምህርት ማስተላለፍና ማደስ እጅግ አስፈላጊ ነበር።
23 ደግሞም በዚህ ስፍራ «እምነት» የሚለው ቃል ክፉ ሰዎችና ዲያብሎስ
እንደሚኖራቸው ዓይነት ታሪካዊ ዕውቀትን ብቻ የሚያመለክት እንዳልሆነ፣ ነገር ግን
ታሪኩን ብቻ ሳይሆን ውጤቱንም ማለትም አንቀጹ የሚገልጸውን የኃጢአትን ይቅርታ
በክርስቶስ አማካይነት ጸጋን፣ ጽድቅንና የኃጢአት ይቅርታን አግኝተናል የሚለውን
እምነት የሚያመለክት እንደ ሆነ ሰዎች እንዲገነዘቡ ተደርጓል።
24 እንግዲህ በክርስቶስ አማካይነት ከአብ ጋር እንደታረቁ የሚያውቁ ሁሉ[110] በእውነት
እግዚአብሔርን ያውቃሉ፣ እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅላቸው ያውቃሉ፤ ወደ እርሱም
25 ይጸልያሉ። በአጭሩ እንደ አረማውያን እግዚአብሔር የሌላቸው አይደሉም። ምክንያቱም
ዲያብሎስና ክፉ ሰዎች የኃጢአት ይቅርታን አንቀጽ ሊያምኑ አይችሉም። በመሆኑም
እግዚአብሔርን እንደ ባላጋራ ይጠሉታል፤ እርሱንም አይጠሩትም፤ ከእርሱም ምንም
26 መልካም ነገር አይጠብቁም። አውግስጢኖስም «እምነት» ስለሚለው ቃል በዚሁ መንገድ

---

[106] *De vocatione [omnium] gentium* I, 17 (*MPL* 51: 670)። በዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመንም ይህ በራሪ ወረቀት በአምብሮስ እንደ ተጻፈ ይታሰብ ነበር። አሁን ግን የአክዮታይኔው ተወላጅ የፕሮስፐር ሥራ እንደ ሆነ ይታመናል።
[110] በላቲኑ በነጠላ ቊጥር ነው።

አንባቢዎቹን ያሳስባል፤ በቅዱሳት መጻሕፍትም «እምነት» የሚለው ቃል የተሸበረን አእምሮ
እንደሚያጽናና እና እንደሚያደፋፍር መታመን[111] እንጂ ከእግዚአብሔር ውጪ የሆኑ ሰዎች
እንዳላቸው ዓይነት ዕውቀት[112] እንዳልሆነ ያስተምራል።
27 ከዚህም ባሻገር፣ በእነርሱ አማካይነት ጸጋን እናገኛለን በሚል ተስፋ ሳይሆን
የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ሆነ፣ መልካም ሥራዎችን መሥራት አስፈላጊ እንደ ሆነ የእኛ
28 ሰዎች ያስተምራሉ። ነገር ግን የኃጢአት ይቅርታና ጸጋ የሚገኙት በእምነት ብቻ ነው።
29 በተጨማሪ፣ መንፈስ ቅዱስ በእምነት አማካይነት የሚሰጥ በመሆኑ መልካም ሥራዎችን
መሥራት ይችል ዘንድ የሰዎችን ልብ ያድሳል፤ ዐዲስ ፍቅርንም[113] በውስጡ ይፈጥራል።
30 አምብሮስም፦ «እምነት የመልካም ፈቃድ እና የጽድቅ ተግባር እናት ናት» ይላል።[114]
31 ምክንያቱም ያለ መንፈስ ቅዱስ የሰው ችሎታዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆነውን
በመወደድ የተሞሉና በእግዚአብሔር ፊት መልካም ሥራዎችን ለመሥራት እጅግ ደካሞች
32 በመሆናቸው ነው። ከዚህም ሌላ፣ ወደ ልዩ ልዩ ኃጢአት፣ ቅንነት ወደ ጐደላቸው
ዐስተሰሰቦች፣ እንዲሁም ግልጽ ወደ ሆኑ ወንጀሎች ሰዎችን አስገድዶ በሚመራ በዲያብሎስ
33 ሥልጣን ሥር ናቸው። ይህም ደግሞ፣ ምንም እንኳ በታማኝነት ለመኖር ቢጥሩም ዳሩ ግን
ባልቻሉና፣ በብዙ ግልጽ ወንጀሎች በረከሱ፣ ፈላስፋዎች ሁኔታ ሊታይ የሚችል ነገር ነው።
34 የሰው ልጆች ያለ እምነት ወይም ያለ መንፈስ ቅዱስ ባሏቸው ሰብአዊ ችሎታዎች ብቻ
ራሳቸውን በሚመሩበት ጊዜ ድካማቸው ይህን ያህል ነው።
35 ስለሆነም፣ ማንም ሰው ይህን ትምህርት መልካም ሥራን የሚከለክል ነው ሲል
መንቀፍ እንደማይገባው በቀላሉ መታወቅ አለበት። በተቃራኒው፣ መልካም ሥራን እንዴት
36 ልንሠራ እንደምንችል በማሳየቱ ሊመሰገን የሚገባው ነው። ምክንያቱም ያለ እምነት ሰው
በባሕርይ የመጀመሪያውንም ሆነ የሁለተኛውን ትእዛዛት ሥራዎች መሥራት አይችልም።
37 የሰው ባሕርይ ያለ እምነት የሰውን እርዳታ ይፈልጋል፤ በእርሱም ይታመናል እንጂ ወደ
እግዚአብሔር አይጸልይም፤ ከእግዚአብሔር ምንም አይጠብቅም፤ ወይም መስቀል
38 አይሸከምም። ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ማመንና መታመን ሲጠፉ ሁሉም ዓይነት ብርቱ
39 ፍላጎትና የሰው ዕቅድ ልብን ይገዛሉ። ለዚህ ነው ክርስቶስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ
40 አትችሉም» (ዮሐ 15[:5]) ያለው። ቤተ ክርስቲያንም፦ የአንተ የመለኮት ፈቃድ ከሌለበት
(በሰው ውስጥ ምን ተገኝቶበት) ቅኖች ሁሉ ጠፍተዋልና ብላ ትዘምራለች።[115]

### *[XXI. (21) ቅዱሳንን ስለ ማምለክ]*

1 ቅዱሳንን ማምለክን በተመለከተ በጥሪያችን መሠረት የእምነታቸውንና የመልካም
ሥራቸውን ፈለግ ለመከተል ቅዱሳንን ስለ ማሰብ ያስተምራሉ። ስለሆነም ቱርኮችን
ከትውልድ አገራችን ለማባረር በሚደረግ ጦርነት ንጉሡ ነገሥቱ የዳዊትን አርዓያ መከተል
2 ይችላሉ። ምክንያቱም ሁለቱም ነገሥታት ናቸው። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ
ቅዱሳን እንድንጸልይ ወይም እንዲረዱን እንድንማጸናቸው አያስተምርም። ምክንያቱም
ክርስቶስን ብቻ መካከለኛ፣ የኃጢአት ማስተሰሪያ መሥዋዕት፣ ሊቀ ካህናትና አማላጅ
3 አድርጎ ያቀርብልናል። ሊጸለይ የሚገባው ወደ እርሱ ነው፤ ጸሎታችን እንደሚሰማም ተስፋ
4 ሰጥቶናል። በተጨማሪም ከሁሉ በላይ ይህንን አምልኮ፣ ይኸውም በመከራ ሁሉ ወደ እርሱ

---

[111] *ፊዱሲያ (fiducia)*
[112] *ኖቲቲያ (notitia)*
[113] *አፌክቱስ (affectus)*:- በሜላንክተን የሥነ መለኮት መዝገበ ቃላት ቴክኒካዊ (ሙያዊ) ቃል ሲሆን የሰው ፈቃድ ከፍተኛው የጥልቅ ስሜቱ መነሳሳት ወይም መንቀሳቀስ ማለት ነው። የእርሱን *Loci* 1521:23-29 ተመልከት።
[114] የአክዮታይኔው ፕሮስፐር፣ *De vocatione omnium gentium* I, 25 (*MPL* 51: 676).
[115] «መንፈስ ቅዱስ ና» ከሚለው ከመካከለኛው ዘመን መዝሙር (Veni Sancte Spiritus)። የራይ ፖልመር የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ትርጒም *The Lutheran Hymnal* (St. Louis: Concordia, 1941), no. 227 and *Service Book and Hymna1* (Philadelphia United Lutheran Publication House, 1958), no. 121 ውስጥ ይገኛል።

*መጻለይን አጥብቆ ይደግፋል፡፡ «ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን ...»*
1ኛ ዮሐንስ 2[፡1]፡፡

*[የክፍል አንድ ማጠቃለያ]*

1 ይህ በአብዛኛው በእኛ መካከል ያለው ትምህርት ሙሉ ማጠቃለያ ነው፡፡ በግልጽ
ማየት እንደሚቻለው፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ወይም ከሁሉን አቀፍዋ ቤተ ክርስቲያን፣
ወይም ከጸሐፊዎቿ ለመረዳት እንደምንችለው ከሮማ ቤተ ክርስቲያን የሚያፈነግጥ ምንም
ነገር የለም፡፡ ጉዳዩ እንደዚህ ስለ ሆነ፣ የእኛ ሰዎች መናፍቃን እንደ ሆኑ የሚቈጥሩ ሰዎች
2 ሁሉ ፍርዳቸው የጭካኔ ፍርድ ነው፡፡ አጠቃላዩ ውዝግብ ያለ ተገቢ ሥልጣን ወደ ቤተ
ክርስቲያን ሾልከው የገቡ የተወሰኑ ብልሹ አሠራሮችን የሚመለከት ነው፡፡ ምንም እንኳ
በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች የነበሩ ቢሆንም፣ አሁን ዝርዝር ማብራሪያ ከሰጠ
ንበት የሃይማኖት መግለጫ የተነሣ ተቻችለን ለመሄድ ጳጳሳቱ በጣም ለዘብ ማለት
ነበረባቸው፡፡ ምክንያቱም ቀኖናዎቹ እንኳ በሁሉም ስፍራ ሥርዓቶች አንድ ዓይነት መሆን
3 አለባቸው ብለው እስከ መጠየቅ ድረስ እጅግ የከረሩ አይደሉም፤[121] የሁሉም አብያተ
4 ክርስቲያናት ሥርዓቶችም አንድ ዓይነት ሆነው ዐያውቁም፡፡ ሆኖም ግን የጥንታውያኑ
ሥርዓቶች በአብዛኛው፣ በእኛ ዘንድ በትጋት ይጠበቃሉ፡፡ ምክንያቱም በአብያተ
ክርስቲያናችን ሁሉም ሥነ ሥርዓቶችና ጥንታውያን ሥርዓቶች እንደ ተወገዱ የሚቀርበው
5 ክስ ሐሰት ነው፡፡ እውነቱ፣ የተወሰኑ ብልሹ አሠራሮች ከተለመዱት ሥርዓቶች ጋር
በመደባለቃቸው ሕዝባዊ ተቃውሞ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ ብልሹ አሠራሮች በበጎ ሕሊና
ተቀባይነት ሊያገኙ ያልቻሉ በመሆናቸው በተወሰነ ደረጃ እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡

## እርማት ስለ ተደረገባቸው ብልሹ አሠራሮች
## ትኩረት የተሰጠባቸው አንቀጾች

1 ዐዲስ የሆኑትንና ከቀኖናዎቹ ዓላማ በተቃራኒ ከጊዜ በኋላ ከተፈጠረ ስሕተት
የተነሣ ተቀባይነት አግኝተው የነበሩትን ጥቂት ብልሹ አሠራሮች ከመቃወም በስተቀር
በእኛ መካከል ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በየትኛውም የእምነት አንቀጽ የሁሉ ከሆነችው
ቤተ ክርስቲያን የተለየ አመለካከት ያላራመዱ በመሆኑ፣ ሕዝቡ ሕሊናውን ጥሶ እነዚህን
ብልሹ አሠራሮች እንዲጠብቃቸው እንዳይገደድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ መልካም
ፈቃድዎ ሆኖ ስለ ለውጦቹና ለእነርሱም ስለምናቀርባቸው ምክንያቶች እንዲያደምጡን
2 እንለምናለን፡፡ በእኛ ሰዎች ላይ የሌሎችን ጥላቻ ለማባባስ አስደንጋጭ የሆኑ የሐሰት ክሶችን
በሕዝቡ መካከል የሚያሠራጩትን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ ሊያምኗቸው አይገባም፡፡
3 በመጀመሪያ የመልካም ሰዎችን አእምሮ በመራራ ዐስተሳሰብ በመሙላት ላለመግባባቱ
4 ዕድል ሰጥተዋል፡፡ አሁንም በተመሳሳይ ዘዴ ግጭቱን ለማባባስ እየጣሩ ነው፡፡ ምክንያቱም
በመካከላችን ያለ የትምህርት ዓይነትና ሥነ ሥርዓቶች እነዚህ ጠማማና መሰሪ ሰዎች
ከሚሉት ይልቅ ይበልጥ ተስማሚ እንደ ሆነ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትነትዎ ያለ ጥርጥር
5 ይደርስበታል፡፡ በእርግጥ እውነት ከሕዝብ አሉባልታ ወይም ከጠላቶቻችን እርግማን
6 ልትገኝ አትችልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የሥነ ሥርዓቶችን ክብር ለመጠበቅና በሕዝቡ መካከል
ከበሬታንና ቅድስናን ለማሳደግ በአብያተ ክርስቲያናት ሥርዓቶችን በአግባቡ ከማካሄድ በላይ
የላቀ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ምንም እንደሌለ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

[121] Gratian, *Decretum* I, dist. 12, chaps. 3, 10, 11.

## *[XXII]. (22)ስለ ሁለቱም ዓይነቶች*[128]

1 ይህ አጠቃቀም «ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ» (ማቴ 26[፡27])፣ የሚል የጌታ ትእዛዝ
ያለው በመሆኑ፣ በጌታ እራት ምሥጢር ሁለቱም ዓይነቶች [ኅብስቱና ወይኑ]
2 ሳልቀሰሱትም ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ስፍራ ክርስቶስ ሁሉም ሊጠጡት ስለሚገባው ጽዋ
ያስተምራል፡፡

3 ይህ ቀሳውስቱን ብቻ የሚመለከት ነው በሚል ማንም እንዳይከራከር ጳውሎስ
በ1ቆሮንቶስ [11፡21] መላዋ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱንም ዓይነቶች ትጠቀም እንደ ነበር
የሚታይበትን ምሳሌ ይጠቅሳል፡፡ ይህ አጠቃቀም በቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመን
4 ቀጥሏል፡፡ ምንም እንኳ ካርዲናል ሱሳነስ መቼ በአግባቡ ተቀባይነት እንዳገኘ ቢጠቅስም፣
5 መቼና በማን ሥልጣን መጀመሪያ እንደ ተቀየረ አይታወቅም፡፡ ቅጽርያኑስ በተለያዩ
6 ቦታዎች ደሙ ለሕዝቡ ይሰጥ እንደ ነበር ይመሰክራል፡፡ ጄሮም፡- «ቀሳውስቱ ሥጋ ወደሙን
7 ይሰጣሉ፣ የክርስቶስንም ደም ለሕዝቡ ያድላሉ» በማለት ተመሳሳይ ነገር ይመሰክራል፡፡
8-9 በእርግጥ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ገላሲየስ ቅዱስ ምሥጢሩ ሊነጣጠል አይገባም ሲል ያዛል
*ኮንሰርኒንግ ኮንሴክሬሽን ምዕ. «ዊ ዲስከቨር» ክፍል 2* (dist 2, *Concerning, Consecration*,
chap, "We Discover")፡፡ ከዚህ በተለየ መንገድ የሚያምነው የቅርብ ጊዜ ልማድ ብቻ ነው፡፡
ይሁን እንጂ፣ ቀኖናዎቹ እንደሚመሰክሩት ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ተቃራኒ ሆኖ የገባ
ልማድ ሊፈቀድ እንደማይገባ ግልጽ ነው (ክፍል 8 ምዕ. ኰንሰርኒንግ ዘ ትሩዝ) (dist 8፣
10 chap Concerning the Truth»[132] እንዲሁም ተከታዮቹ ምዕራፎች)፡፡ በእርግጥ፣ ይህ ልማድ
ተቀባይነት ያገኘው የእግዚአብሔርን ቃል ችላ በማለት ብቻ ሳይሆን ጥንታውያኑን
11 ቀኖናዎችና የቤተ ክርስቲያንን ምሳሌነት በመቃወምም ነው፡፡ በዚህ መሠረት፣ በቅዱስ
ምሥጢሩ ሁለቱንም ዓይነቶች ለመጠቀም የመረጡ ሰዎች ሕሊናቸውን በመጣስ ከዚህ
12 የተለየ ነገር እንዲያደርጉ መገደድ የለባቸውም፡፡ ቅዱስ ምሥጢሩን መነጣጠል ከክርስቶስ
ድንጋጌ ጋር ስለማይስማማ፣ እስካሁን ድረስ ልማድ የሆነው የቅዱስ ቊርባን አክብሮታዊ
ሰልፍ ከእኛ ዘንድ እንዲወገድ ተደርጎአል፡፡

## *[XXIII] (23)ስለ ካህናት ጋብቻ*

1 ራሳቸውን የማይገዙትን ካህናት መጥፎ አርዓያነት በሚመለከት ሕዝባዊ ጩኸት
2 አለ፡፡ ከዚህ የተነሣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓየስ ቀሳውስቱ ጋብቻ የተከለከሉባቸው ጥቂት
ምክንያቶች ቢኖሩም፣ ነገር ግን ጋብቻ እንዲፈቀድላቸው የሚያደርጉ ብዙ ይበልጥ ክብደት
3 ያላቸው ምክንያቶች አሉ ሲል እንደ ተናገረ ተዘግቦአል፡፡ ፕላቲናም እንዲሁ ይጽፋል፡፡
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመካከላችን ያሉ ቀሳውስት ይህን ገሃዳዊ ቅሌት ለማስወገድ
ከመፈለጋቸው የተነሣ፣ በሚከተሉት ምክንያቶች አግብተዋል፤ ማግባታቸውም አግባብ ያለው
4 መሆኑን አስተምረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ጳውሎስ «ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ
ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣» ደግሞም «በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና»
5 [1ቆሮ 7፡2፣ 9]፡- ይላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዲባዙ የፈጠራቸው
በመሆኑ (ዘፍ 2[፡28]) ክርስቶስ ሁሉም ሰው ያለ ጋብቻ ለመኖር የተገባ እንዳልሆነ
ባስተማረበት ስፍራ «ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም» [ማቴ 19፡11]
6 ይላል፡፡ ያለ እግዚአብሔር ስጦታና ሥራ በሰው ችሎታ ተፈጥሮን መቀየር የማይቻል ነው፡፡
7 በዚህ መሠረት ሳያገቡ ለመኖር ያልተሰጣቸው ሰዎች ማግባት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም
8 የሰው የሆነ ሕግ ወይም መሐላ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ትእዛዝና ድንጋጌ ሊሽር

---

128 *ስፒሽስ (species)*፣ ቃል በቃል «ዓይነት» ማለት ሲሆን በጌታ እራት ውስጥ ለሚገኙ ጥንተ ነገሮች የቆመ ሙያዊ ቃል ነው፡፡
132 *De veritate*, in Gratian, *Decretum* I, dist. 8, Chap. 4.

9 አይችልም:: ከእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ ቀሳውስታችን ሚስቶችን ማግባታቸው አግባብነት
ያለው እንደ ሆነ ያስተምራሉ::
10-11 በጥንት ቤተ ክርስቲያንም ቄሶች ያገቡ እንደ ነበር ግልጽ ነው:: ምክንያቱም
12 ጳውሎስ ያገባ ሰው ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ሊመረጥ ይችላል ይላል [1ጢሞ 3:2]:: ከአራት መቶ
ዓመታት በፊት በጀርመን አገር ቄሶች ሳያገቡ ለመኖር አይገደዱም ነበር:: በእግርጥ፣
የማኢንዝ ሊቀ ጳጳስ በዚህ ጉዳይ የሮምን ጳጳስ አዋጅ ሊያሳትም በነበረ ጊዜ ከፍተኛ
ተቃውሞ ባስነሡ በተቈጡ ቀሳውስት ለሞት ጥቂት እስኪቀረው ድረስ ተደብድቦ ነበር::
13 ምንም እንኳ ይህ በመለኮታዊና በሰብአዊ ሕግጋት ሁሉ፣ እንዲሁም በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና
እጅግ በተከበሩ ጉባኤዎች የተዘጋጁትን ቀኖናዎች የሚቃረን ቢሆንም፣ የወደፊቱን ጋብቻ
በመከልከል ብቻ ሳይሆን አሁን ያሉትም ጋብቻዎች እንዲፈርሱ በመደረጉ ጉዳዩ እንደዚህ
ባለ ዓመፅ የሚካሄድ ነበር::
14 ዓለም ዕድሜዋ እየገፋ የሰው ልጅ ባሕርይም እየደከመ የሚሄድ እንደ መሆኑ መጠን
ብዙ ዓመፅ ወደ ጀርመን ሰርጎ እንዳይገባ አርቆ አስተዋይነትን መለማመድ ተገቢ ነው::
15 በተጨማሪም እግዚአብሔር ጋብቻን ያቋቋመው ለሰብአዊ ድክመት መፍትሔ
16 እንዲሆን ነው:: ቀኖናዎቹ ራሳቸው የቆየው ጽኑ ሕግ ከሰው ድካም የተነሣ አልፎ አልፎ
መላላት አለበት ሲሉ ይገልጻሉ፤ ይህም ይህንን በተመለከተ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው
17 ነው:: ለረጅም ጊዜ ጋብቻ ከተከለከለ ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ የቄሶች እጥረት
የሚያጋጥማት ይመስላል::
18 ነገር ግን የእግዚአብሔር ትእዛዝ አሁንም አለ፤ የቤተ ክርስቲያንም ልማድ በሚገባ
የታወቀ ነው፤ ደግሞም ንጽሕና የሌለው ሳያገቡ መኖር በርካታ አሳፋሪ ድርጊቶችን፣
ዝሙትን፣ እንዲሁም በጥሩ ዳኞች ቅጣት የሚገባቸው ሌሎች ወንጀሎችን ያስከትላል:: ያም
ሁሉ ሆኖ፣ የካህናት ጋብቻን በተመለከተ እንዲህ ያለ ብርቱ ተቃውሞ እስከ አሁን መኖሩ
19 በእጅጉ የሚያስገርም ነው:: ጋብቻ በአክብሮት እንዲያዝ እግዚአብሔር አዝዞአል::
20 በሥርዓት የሚመሩ ሕዝቦች ሕግጋት፣ በአረማውያንም ቢሆን እንኳ፣ ለጋብቻ ከሁሉ የላቀ
21 ክብር ይሰጡታል:: አሁን ግን ከቀኖናዎቹ ዐሳብ በተቃረነ መልኩ በማግባታቸው ብቻ
22 የሞት ቅጣት ተደንግጓል፤ ለካህናቱም እንደዚሁ! ጳውሎስ ጋብቻን መከልከልን የአጋንንት
23 ትምህርት ብሎ ይጠራዋል (1ጢሞ [4:1 እና 3]):: የጋብቻ ክልከላው እንዲህ ባሉ
ቅጣቶች ጥበቃ የተደረገለት በመሆኑ ይህን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል::
24 ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መሻር የሚችል የሰዎች ሕግ እንደሌለ
25 ሁሉ፣ ያንን ሊያደርግ የሚችል መሐላም የለም:: ከዚህ የተነሣም፣ ቅጵርያኑስ ለንጽሕና
የገቡትን ቃል መጠበቅ ያልቻሉ ሴቶች ማግባት አለባቸው ሲል መክሮአል:: (በሁለተኛው
መልእክት አንደኛ መጽሐፍ) እነዚህ የእርሱ ቃላት ናቸው:- «ነገር ግን ፈቃደኞች ባይሆኑ
ወይም ጸንቶ መቆም ቢያቅታቸው፣ በምኞታቸው እየተቃጠሉ ወደ እሳት ከመውደቅ
ቢያገቡ ይሻላቸዋል፤ በእርግጥም ለወንድሞቻቸውና ለእኅቶቻቸው ማሰናከያ መሆን
አይገባቸውም::»
26 በተለምዶ እስከ አሁን ድረስ ሲደረግ እንደ ነበረው፣ ከተገቢው ዕድሜአቸው በፊት
መሐላ ለገቡ ሰዎች ቀኖናዎቹም እንኳ በተወሰነ ደረጃ አግባብነት ያለውን ሚዛናዊነት
ያሳያሉ::

## *[XXIV]. (24)ስለ ቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት*

1 የእኛ አብያተ ክርስቲያናት የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓትን አስወግደዋል በሚል
2 በሐሰት ተከሰዋል:: እንዲያውም፣ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት በእኛ ዘንድ በታላቅ ክብር
እየተጠበቀና እየተከበረ ይገኛል:: የጀርመንኛ መዝሙሮች ሕዝቡን ለማስተማር ሲባል

በላቲኑ መዝሙሮች እዚህና እዚያ ጣልቃ ከመግባታቸው በስተቀር ሁሉም የተለመዱት
3 ሥርዓቶች ተጠብቀው ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ሥነ ሥርዓቶች በተለይ ዕውቀት የጎደላቸውን
4 ሰዎች ለማስተማር ሲባል ያስፈልጋሉ፡፡ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ሕዝቡ የሚገባው ቋንቋ
5 ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ይመክራል [1ቆሮ 14፡2፣9]፡፡ ሕዝቡም፣ ማለትም ይህንን
ለማድረግ የበቁ ሁሉ፣ ቅዱስ ምሥጢሩን በጋራ ወደ መቀበል ደርሰዋል፡፡ ይህም ደግሞ
6 ለሕዝባዊ ሥነ ሥርዓቶች ከበሬታና ውዳሴን ይጨምራል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ወደዚህ
7 የሚቀርቡት በመጀመሪያ ሊመረመሩና ሊደመጡ ዕድሉ ካላቸው ብቻ ነው፡፡ ሕዝቡም
በእግዚአብሔር ማመንን እና መልካሙን ሁሉ ከእግዚአብሔር መጠበቅንና መጠየቅን ይማሩ
ዘንድ ስለ ቅዱስ ምሥጢሩ ክብርና ጥቅም ማለትም ለተሸበሩ ሕሊናዎች ታላቅ መጽናናትን
8 እንደሚሰጥ እንዲያስታውሱ ይደረጋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ እግዚአብሔርን ደስ
ያሰኛል፣ ደግሞም እንዲህ ያለው የቅዱስ ምሥጢሩ አጠቃቀም ለእግዚአብሔር የሚኖረውን
9 አክብሮት ያዳብራል፡፡ እንግዲህ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቱ ከእኛ ዘንድ ይልቅ
በተቃዋሚዎቻችን ዘንድ በበለጠ ታማኝነት መያዙ አይታይም፡፡
10 ይሁን እንጂ፣ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶች በአሳፋሪ ሁኔታ በመርከሳቸውና
ለትርፍ በመዋላቸው ለረጅም ጊዜ በአደባባይ ጠንከር ያለ የደጋግ ሰዎች ጩኸት ነበረ፡፡
11 እንደዚህ ዓይነት ተገቢ ያልሆነ አድራጎት በሁሉም የአምልኮ ስፍራዎች እንዴት በሰፊው
እንደ ተሠራጨ፣ ምን ዓይነት ሰዎችም ለገቢ ወይም ለአበል ሲሉ ብቻ የቅዱስ ቊርባን
ሥነ ሥርዓቶችን እንደሚፈጽሙ፣ ምን ያህሉ ደግሞ ቀኖናው ከከለከለው ተቃራኒ በሆነ
12 መንገድ ያከበሩት መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ «ሳይገባው ይህን
እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት» [1ቆሮ
11፡27] ባለ ጊዜ ሥጋ ወደሙን ባልተገባ ሁኔታ የሚመለከቱትን ሰዎች በጥብቅ ያስጠ
13 ነቀቃል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ ለትርፍ ተብሎ ከሚሰጥ በስተቀር ምንም የግል ቅዱስ ቊርባን
የሚሰጥ ስላልነበረ በእኛ ዘንድ ያሉ ካህናት ይህንን ኃጢአት በተመለከተ ትምህርት
ከተቀበሉ ጊዜ ጀምሮ የግል የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት በእኛ ዘንድ ተቋርጦአል፡፡
14 ጳጳሳቱም እነዚህን ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶች የማያውቁ አልነበሩም፡፡ በጊዜው
15 አርመዋቸው ቢሆን ኖሮ አሁን ያለው አለመግባባት ጋብ ባለ ነበር፡፡ በቸልተኝነታቸው
በርካታ መጥፎ ልማዶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተሳቡ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል፡፡
16 እንግዲህ፣ ይህ ሁካታ መቼም ቢሆን በትዕግሥት ሊታለፉ በማይችሉ በእጅጉ እየተገለጡ
በመጡ በእነዚያ ተገቢ ባልሆኑ ተመሳሳይ አድራጎቶች ሳቢያ የመጡ ሆኖ ሳለ፣ እነርሱ
17 አሁን ገና በቤተ ክርስቲያን ስላለ አደጋ ማማረር ጀምረዋል፡፡ የቅዱስ ቊርባን ሥነ
18 ሥርዓትን፣ ማለትም ቅዱስ ምሥጢሩን በተመለከተ ታላላቅ አለመግባባቶች ተነሥተዋል፡-
ሊያርሟቸው በሚችሉና በተገባቸው በእነዚያው ሰዎች፣ በቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት
በዝምታ ሲታለፍ በቆየው እንዲህ ባለው የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ዘላቂ ርኩሰት
19 ምክንያት ምናልባትም ዓለም እየተቀጣች ነው፡፡ ምክንያቱም በዐሥርቱ ትእዛዛት
«እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና» [ዘጸ 20፡7] ተብሎ
20 ተጽፎአል፡፡ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እንደ ቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ያለ በጣም
በትጋት ለትርፍ የተፈጸመ መለኮታዊ ጉዳይ ያለ አይመስልም፡፡
21 የሚከተለው አመለካከት ማለቂያ የሌላቸው የግል የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶችን
22 አብዝቶአል፡- ክርስቶስ በሥቃዩ ለውርስ ኃጢአት ዕዳ ክፍያን ፈጸመ፤ እንዲሁም ሞት
ለሚገባቸውና ቀላል ለሆኑ ለየቀኑ ኃጢአቶች መሥዋዕት ሊቀርብ የሚችልበትን የቅዱስ
ቊርባን ሥነ ሥርዓት አቋቋመ፡፡ ከዚህም ሁኔታ ሥርዓቱን በመፈጸም ብቻ (*ኤክስ ኦፔሬ
ኦፔራቶ*) (*ex opere operato*) የሕያዋንንና የሙታንን ኃጢአት የሚያስወግደው የቅዱስ
23 ቊርባን ሥራ ነው የሚል የጋራ አመለካከት መጣ፡፡[150] ለብዙዎች የተደረገ አንድ የቅዱስ

[150] ተግባርን በመፈጸም ብቻ፡፡ *CA* XIII, በ 75 ተመልከት፡፡

ቊርባን ሥነ ሥርዓት ለግለ ሰቦች የሚደረጉ ልዩ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶችን ያህል
ተገቢነት ይኖረው ይሆን ወይ የሚል ክርክር እዚህ ላይ ጀምሯል፡፡ ይህም ክርክር ለቊጥር
የሚያታክቱ ማለቂያ የሌላቸው ብዙ የቅዱስ ቊርባን ሥርዓቶችን አፍርቶአል፡፡
24 እነዚህ አመለካከቶች ይልቁኑ የክርስቶስን የመከራውን ክብር ያቃልላሉ እንጂ
25 ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንደማይስማሙ ሰዎቻችን አስጠንቅቀዋል፡፡ ምክንያቱም
26 የክርስቶስ መከራ ለሁሉም ዓይነት ሌሎች ቀሪ ኃጢአቶች ደግሞ እንጂ ለተወረሰ
ኃጢአተኝነት ብቻ የተሰጠና የተከፈለ አይደለም፤ በዕብራውያን [10፡10፣14] ላይ
እንደተጻፈው «የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል»
27 እንዲሁም፣ «አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና፡፡»
28 በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በክርስቶስ በሆነ እምነት በኩል በእግዚአብሔር ፊት የጸደቅን
29 መሆናችንን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል፡፡ እንግዲህ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት
የሕያዋንንና የሙታንን ኃጢአት *ex opere operato* (ኤክስ ኦፔሬ ኦፔራቶ)[151] (ሥርዓቱን
በመፈጸም ብቻ) የሚያስወግድ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ጽድቅ ከእምነት ሳይሆን የእግዚአብሔር
ቃል ካልፈቀደው ከቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ሥራ ይመጣል ማለት ነው፡፡
30 ነገር ግን ክርስቶስ ለእርሱ መታሰቢያ እንዲደረግ አዝዞአል፡፡[152] ስለዚህ፣ የቅዱስ
ቊርባን ሥነ ሥርዓት የተቋቋመው በቅዱሳት ምሥጢራት የሚጠቀሙ ሰዎች እምነት
በክርስቶስ በኩል የተቀበሉአቸውን ትሩፋት እንዲያስታውሱ እንዲሁም የተሸበረ ሕሊናን
31 እንዲያበረታቱና እንዲያጽናኑ ነበር፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስን ማሰብ ትሩፋቱን ማሰብና
32 በእውነትም ለእኛ የተሰጡ መሆናቸውን መገንዘብ ነው፡፡[153] ታሪክን ማስታወስ በቂ
33 አይደለም፤ ምክንያቱም አይሁድና ክፉዎችም ደግሞ ያንን ማስታወስ ይችላሉ፡፡ አምብሮስ፦
«ሁልጊዜ ስለምበድል፣ ሁልጊዜ መድኃኒቱን መውሰድ አለብኝ»[154] እንዳለው፣ የቅዱስ
ቊርባን ሥነ ሥርዓት መጽናናትን ለሚፈልጉ ሰዎች ቅዱሳት ምሥጢራትን ለማቅረብ
ዓላማ መዋል አለበት፡፡
34 የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ቅዱሳት ምሥጢራትን የሚያካፍል እስከ ሆነ ድረስ
በእኛ ዘንድ በማንኛውም የበዓል ቀን አንድ የጋራ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል፤
35 እንዲሁም የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ በሌሎች ቀናት ደግሞ ይካሄዳል፡፡ ይህም ልማድ በቤተ
ክርስቲያን ዐዲስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከጎርጎርዮስ[155] ዘመን በፊት የነበሩ የጥንት
መምህራን የግል የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶችን አይጠቅሱም፤ ነገር ግን ስለ ጋራ የቅዱስ
36 ቊርባን ሥነ ሥርዓት አዘውትረው ይናገራሉ፡፡ ዮሐንስ አፈወርቅ (ክሪሶስቶም) (Chrysostom)
ካህኑ በየቀኑ በመሠዊያው አጠገብ እየቆመ አንዳንዶችን ወደ ቅዱስ ቊርባን ሲጋብዝ
37 ሌሎችን ደግሞ ያቆያቸዋል ብሎአል፡፡ እንዲሁም ከጥንታዊ ቀኖናዎች ግልጽ እንደ ሆነው
አንድ ሰው የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓትን ሲያካሂድ፣ የቀሩት ሽማግሌዎችና ዲያቆናት
38 የክርስቶስን ሥጋ ከእርሱ ይቀበላሉ፡፡ ምክንያቱም የኒቅያው ቀኖና ቃሎች እንዲህ
ይነበባሉ፦ «ዲያቆናት ቅዱስ ቊርባንን በቅደም ተከተል ከሽማግሌዎቹ ቀጥለው ከጳጳሱ
39 ወይም ከሽማግሌው ይቀበሉ»፡፡ ጳውሎስም ደግሞ ቅዱስ ቊርባንን በተመለከተ [1ቆሮ
11፡33] የጋራ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖር ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዲጠባበቁ ያዛል፡፡
40 ስለዚህ፣ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት እኛ እንደምንፈጽመው በራሱ የቤተ
ክርስቲያን ምሳሌነት፣ የእግዚአብሔር ቃልና የአባቶች ድጋፍ ያለው ስለ ሆነ፣ በተለይ
ልማዳዊ የሆኑት ይፋዊ ሥነ ሥርዓቶች በአብዛኛው ስለ ቀጠሉ፣ ሊነቀፍ እንደማይቻል
እርግጠኞች ነን፡፡ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶች ብዛት ብቻ የተለየ ነው፤ ደግሞም ከፍ

[151] ተግባርን በመፈጸም ብቻ፡፡ *CA* XIII, በ 75 ተመልከት፡፡
[152] 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡25
[153] ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ የሜላንክተን ፅንሰ ዐሳብ his *Loci* 1521, p. 21f. ተመልከት፡፡
[154] አምብሮስ፣ ቅዱሳት ምሥጢራትን በመተለከተ (*De sacramentis*) V, 4, 25 (*MPL* 16:464; *CSEL* 73:58,12)
[155] ጳጳስ ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ፡፡

ካሉትና ከተገለጡት ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶች የተነሣ እነርሱን ውሱን ማድረግ መልካም
41 መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ምክንያቱም በቀድሞ ዘመን የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት እጅግ
በሚዘወተርባቸው አብያተ ክርስቲያናት እንኳ በየቀኑ አይደረግም ነበር፤ *የትራይፖርታይት
ሂስትሪ* (*Tripartite History*) ዘጠነኛው መጽሐፍ እንደሚመሰክረው፦ «ነገር ግን እንደ ገና
በእስክንድርያ ቅዱሳት መጻሕፍት ረቡዕና ዓርብ እየተነበቡ መምህራኑ ደግሞ
ይተረጕሙአቸዋል፤ እንዲሁም ከተከበረው የጌታ እራት (መስዋዕት)[159] በቀር ሁሉም ነገር
ይደረጋል።»

*[XXV] (25)ስለ ኑዛዜ*

1 ኑዛዜ ከአብያተ ክርስቲያናታችን አልተወገደም። ምክንያቱም አስቀድሞ ለተፈተኑና
ከኃጢአታቸው እንደ ተፈቱ ለታወጀላቸው ካልሆነ በቀር የክርስቶስን ሥጋ ማደል
2 የተለመደ አይደለም። ሕዝቡ ደግሞ ከዚህ በፊት ታላቅ ዝምታ ሰፍኖበት ስለ ነበረው፣
ከኃጢአት በመፈታት አዋጅ ቃል ማመንን በተመለከተ በከፍተኛ ሁኔታ በትጋት
ተምረዋል። ከኃጢአት የመፈታት አዋጅ የአምላክ ድምፅ ስለሆነና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ
3 ተከትሎ የተነገረ በመሆኑ ሕዝቡ በእጅጉ እንዲጠቀሙበት ተምረዋል። እንዲህ ያለውን
ከኃጢአት የመፈታት አዋጅ ከሰማያት እየደጋገመ እንደሚያስተጋባ እንደ ራሱ እንደ
4 እግዚአብሔር ድምፅ እናምነው ዘንድ እግዚአብሔር እምነትን ስለሚጠይቅና ይህም እምነት
በእውነት የኃጢአት ይቅርታን የሚያገኝና የሚቀበለው ስለ ሆነ፣ የካህናቱ ሥልጣን እንዲህ
ያለውን ታላቅ መጽናናት ለተሸበሩ ሕሊናዎች የሚያመጣ በመሆኑ የተመሰገነና የሚታሰብ
5 ነው። በቀድሞ ዘመን የኃጢአት ዕዳ ክፍያዎች ከሚገባው በላይ ይወደሱ ነበር፤ ስለ
እምነት፣ ስለ ክርስቶስ ሥራ፣ ወይም በእምነት ስለሆነው ጽድቅ ምንም ነገር አይነሣም
ነበር። በዚህ ነጥብ ላይ አብያተ ክርስቲያናታችን እምብዛም የሚወቀሱ አይደሉም።
6 ምክንያቱም ኑዛዜን በተመለከተ የተሰጠው ትምህርት በእጅጉ በጥንቃቄ የተተነተነና
በትክክል ወደ ብርሃን የወጣው በሕዝባችን እንደ ሆነ ባላጋራዎቻችንም እንኳ ቢሆኑ
ለመቀበል ይገደዳሉ።
7 ከዚህ ባሻገር፣ ኑዛዜን በተመለከተ ስሕተቶችን መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም፤
እንዲሁም ሕሊናዎች ስሕተቶቻቸውን ሁሉ በመቍጠር ጭንቀትን መሸከም የለባቸውም
በማለት ያስተምራሉ። ምክንያቱም ሁሉንም ስሕተት በቃል መድገም የማይቻል ነው፤
8-9 መዝሙሩ «ስሕተትን ማን ያስተውላታል?» [19፡12] ብሎ እንደሚመሰክረው፣ ደግሞም
ኤርምያስ፦ [17:9] «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው» ይላል። ነገር
ግን ከፍ ባለ ድምፅ በመደጋገም ልንቈጥራቸው ከምንችለው የሕሊና ኃጢአቶች በቀር ሌላ
ኃጢአት ይቅር የማይባል ቢሆን ኖሮ ሕሊናችን ፈጽሞ ሰላምን ሊያገኝ አይቻለውም።
10 ምክንያቱም ብዙ ኃጢአቶች ሊታዩ ወይም ሊታወሱ የማይችሉ ናቸው። የጥንት
11 ጸሐፊዎችም ደግሞ እንዲህ ያለ ዝርዝር አስፈላጊ እንዳልሆነ መስክረዋል። ምክንያቱም
ዮሐንስ አፈወርቅ (ክሪሶስቶም) (Chrysostom) በቀኖናዎቹ ጠቅሶ እንደሚለው፦ «በአደባባይ
መገለጥ አለባችሁ ወይም ራሳችሁን በሌሎች ፊት መክሰስ አለባችሁ አልልም፣ ነገር ግን
'መንገድህን በእግዚአብሔር ፊት ግለጥ' [መዝ 37፡5 ሹልጌት] ብለው ለተናገሩት ለነቢያቱ
እንድትታዘዙ እፈልጋለሁ። ስለዚህ፣ ኃጢአትህን በጸሎት፣ ለእውነተኛው ፈራጅ፣
ለእግዚአብሔር ተናዘዝ። ኃጢአትህን በአንደበትህ ሳይሆን ነገር ግን በሕሊናህ በማሰብ
12 ግለጽ»። *ኮንሰርኒንግ ኮንፌሽን* (*Concerning Confession*) በሚለው ውስጥ የጎዳጉ ማስታወሻ
(ክፍል 5 ምዕ. «ኮንሲደር» "Consider") ኑዛዜ የሰብአዊ ሕግ ጉዳይ መሆኑን ይቀበላል።

[159] *Oblatio.* እዚህ ላይ ስለ ጌታ እራት እንደ ቴክኒካዊ (ሙያዊ) ቃል ጥቅም ላይ ውሎአል።

13 የሆነ ሆኖ፣ ኑዛዜ ከታላቅ ትሩፋቱ የተነሣ የኃጢአት ስርየትን ስለማስታወቅና ለሕሊና
ስለሚሆኑ ሌሎች ዕድሎች ሲል በእኛ ዘንድ የሚቀጥል ነው።

*[XXVI] (26)ስለ ምግብ ልዩነት*

1 ይህም ስለ ምግብ የተደረገው ልዩነትና ተመሳሳይ ሰብአዊ ልማዶች ጸጋን
ለማግኘትና የኃጢአት ዕዳ ክፍያን ለማድረግ ጠቃሚ ሥራዎች ናቸው የሚለው አጠቃላይ
ግንዛቤ፣ የሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በአብያተ ክርስቲያናት የሚያስተምሩትም ሰዎች
2 ጭምር ነበር። በየቀኑ ዐዳዲስ ሥርዓቶች፣ ዐዳዲስ ትእዛዛት፣ ዐዳዲስ በዓላትና ዐዳዲስ
አጽዋማት በመፈጠራቸውና እንዲሁም መምህራን በአምልኮ ስፍራ እነዚህ ሥራዎች ጸጋን
ለማግኘት አስፈላጊ የአምልኮ አካል እንደ ሆኑ አድርገው በግድ ስለሚጠይቁና ሰዎች
ከእነዚህ መካከል ማንኛቸውንም ሳይፈጽሙ ከቀሩ በጭካኔ ሕሊናቸውን በማሸበራቸው
3 ዓለምም ይህንን ትክክል ነው ብሎ እንደሚያስብ ለመረዳት ይቻላል። ወጎችን በተመለከተ
ከዚህ ጽኑ እምነት የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ብዙ መጥፎ ነገር ተከትሎአል።
4 በመጀመሪያ ደረጃ፣ ይህ የወንጌሉ ዋነኛ ክፍል የሆነውንና በቤተ ክርስቲያን ሊኖርና
ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባውን ከሥራዎችና ከሌሎች የአምልኮ ተግባራት በላይ በሚገባ
ይታወቅና ይከብር ዘንድ የሚገባውን ጸጋንና ከእምነት የሆነውን ጽድቅ በተመለከተ ያለውን
5 የክርስቶስን ሥራ ትምህርት አደብዝዞአል። ጳውሎስ ለዚህ አንቀጽ እጅግ ታላቅ ክብደት
የሰጠውና የክርስቲያን ጽድቅ ከእንዲህ ዓይነት ሥራዎች የተለየ ነገር መሆኑን ለማሳየት
ሕግንና ሰብአዊ ወጎችን ያስወገደው ለዚህ ነው። የክርስቲያን ጽድቅ ከክርስቶስ የተነሣ
6 በጸጋው ተቀባይነት ያገኘን መሆናችንን የሚያምን እምነት ነው። ይህ የጳውሎስ ትምህርት
ጸጋና ጽድቅ ከምግብ በመታቀብና በተመሳሳይ የአምልኮ ተግባራት ይገኛል ብሎ
7 በሚያስተጋባው አመለካከት፣ ሙሉ በሙሉ በወጎች ተጻፍኖ ነበር። ከንስሐ ልምምድ ጋር
ስላለው እምነት ምንም ነገር አልተጠቀሰም፤[164] እነዚህ የኃጢአት ዕዳ ክፍያ ሥራዎች ብቻ
ቀርበዋል። መላው ንስሐ እነርሱን ብቻ የያዘ እንደ ሆነ ይታሰብ ነበር።
8 በሁለተኛ ደረጃ፣ ወጎች ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ይልቅ በእጅጉ ስለሚመረጡ፣
እነዚህ ወጎች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አደብዝዘዋል። ክርስትና በመላው የተወሰኑ የበዓላት
9 ቀናትን፣ ሥርዓቶችን፣ አጽዋማትንና፣ አልባሳትን ማክበር እንደ ሆነ ይታሰብ ነበር። እነዚህ
የሕግ ሥነ ሥርዓቶች አጠባበቅ «መንፈሳዊ ሕይወት» እና «ፍጹም ሕይወት» ስለ ነበሩ
10 እጅግ የተለዩ ማዕረጎችን ይዘው ነበር። ይህ በእንዲህ እያለ የአንድን ሰው ጥሪ
የሚመለከቱት፡- የቤተ ሰቡ ራስ ልጆችን ማሳደግ አለበት፤ እናትም ልትሸከማቸው ይገባል፤
አንድ መስፍንም አገሩን ማስተዳደር አለበት የሚሉት የእግዚአብሔር ትእዛዛት
አልተመሰገኑም። እነዚህ ድንቅ ከሆነው የሥነ ሥርዓቶች አጠባበቅ በጣም ዝቅ ያሉ እንደ
11 «ዓለማዊ»ና «ፍጹም እንዳልሆኑ» ሥራዎች ተደርገው ይቈጠሩ ነበር። ይህ ስሕተት
መንፈሳዊ ሕሊናዎችን በእጅጉ አሰቃይቷል። ፍጹም ባልሆነ ዓይነት ሕይወት፡- በጋብቻ፣
በመንግሥት፣ ወይም በሌሎች ሕዝባዊ ተግባራት በመታሰራቸው አዝነዋል። መነኩሳትንና
እንደ እነርሱ ያሉትን ሌሎችን አድንቀዋል፤ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የሥነ ሥርዓቶች አጠ
ባበቅም እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ በሐሰት ገምተዋል።
12 በሦስተኛ ደረጃ፣ ሁሉንም መጠበቅ የማይቻል ስለ ነበረ ወጎች ለሕሊናዎች ታላቅ
አደጋን አምጥተዋል፤ ሆኖም ግን ሰዎች እነዚህን ሥነ ሥርዓቶች አስፈላጊ የአምልኮ
13 ተግባራት ናቸው ብለው ፈርጀዋቸዋል። ጌርሶን ብዙዎች ወጎችን መጠበቅ ስለ ተሳናቸው
ተስፋ መቍረጥ እንደ ደረሰባቸው፣ አንዳንዶችም ደግሞ የራሳቸውን ሕይወት እንኳ
እንዳጠፉ ይጽፋል። ይህ በእንዲህ እያለ በእምነት የሆነውን ጽድቅና ከጸጋ የሚመጣውን

[164] *poenitentia. CA* XII, በ 65 ተመልከት።

14 መጽናናት ጨርሶ ሰምተው ዐያውቁም፡፡ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች
ወጎችን አሰባስበው፣ ለሕሊናዎች አግባብነት ያለውና ጨዋ የሆነ መፍትሔ[171] እንደሚፈልጉ
እናያለን፡፡ ሁሉም በአንድ ላይ አልተሳካላቸውም፤ ይልቁንም በሂደቱ የበለጠ ሕሊናዎችን
15 ተበተቡ፡፡ በዚህ ፈንታ ትምህርት ቤቶችና[172] ስብከቶች ወጎችን በመሰብሰብ በእጅጉ ጊዜ
ስላጠራቸው እምነትን፣ መስቀሉን፣ ተስፋን፣ የሕዝባዊ ጉዳዮችን ክብርና በአስቸጋሪ ፈተና
ውስጥ ያለ የሕሊና መጽናናትን በተመለከተ ያሉትን ጠቃሚ ትምህርቶች ለመፈለግና
16 የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሶ ለማስተማር ጊዜ አልነበራቸውም፡፡ ስለሆነም፣ ጌርሶንና
የተወሰኑ ሌሎች የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች በወጎች ላይ በሚደረጉ በእነዚህ ንትርኮች
17 ተውጠው ወደ ተሻለ ትምህርት ሊመለሱ ስላልቻሉ በጽኑ ቅር ተሰኝተዋል፡፡ አውግስጢኖስም
እንደዚህ ባሉ ሥርዓቶች የሰውን ሕሊና መጫንን በመከልከል እነዚህ ነገሮች ባልተፈቀዱ
ወይም ባልተከለከሉ ጉዳዮች ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ጃንዋሪዮስን በጥበብ ያሳስበዋል፤
እርሱም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡
18 ስለዚህ፣ ሰዎቻችን ይህንን ሰበብ በአጋጣሚ እንደ ወሰዱ ወይም አንዳንዶች ጳጳሳትን
ይጠላሉ ብለው በስሕተት እንደሚጠረጥሩአቸው መታየት የለባቸውም፡፡ አብያተ
ክርስቲያናትን ከእነዚያ ወጎችን በተሳሳተ መንገድ ከመረዳት ከመነጨ ስሕተቶች ለማስጠ
ንቀቅ እጅግ በጣም ያስፈልግ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በገዛ ራሳቸው ምርጫ ሥነ
ሥርዓቶችን በመጠበቅ ጸጋን እንደሚያገኙ የሚያስቡ ከሆነ ከቶ ሊረዱት የማይቻለውን
የጸጋንና የእምነትን ጽድቅ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን በጽናት እንድንሰጥ ወንጌሉ
ያስገድደናል፡፡
21 እንግዲህ የሰውን ወግ በመጠበቅ ጸጋን ማግኘት ወይም የኃጢአት ዕዳ ክፍያን
መፈጸም እንደማንችል ያስተምራሉ፡፡ በዚህ ምክንያት እንደነዚህ ዓይነት ወጎችን መጠበቅ
22 አስፈላጊ የአምልኮ ተግባራት ሆነው እንደሚቈጠሩ መታሰብ የለበትም፡፡ ከእግዚአብሔር
ቃል ማስረጃ ይጨምራሉ፡፡ ምንም እንኳ ገለልተኛ ነገርና፣[176] ከመንጻት ሕግ ጋር
ተያያዥነት ያለው ተደርጎ ቢቈጠርም፣ በማቴዎስ 15[፡1-20] ክርስቶስ ሐዋርያት የተለምዶ
ወግን አለመጠበቃቸውን ይደግፋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በ[ማቴ 15፡9]፡- የሰውም ሥርዓት የሆነ
ትምህርት እያስተማሩ «በከንቱ ያመልኩኛል» ይላል፡፡ በመሆኑም ከንቱ የሆነ የአምልኮ
23 ተግባርን የግድ አይልም፡፡ ከዚህ በኋላ ጥቂት አለፍ ብሎ በ[ማቴ 15፡11]፡- «ሰውን
24 የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም» ይላል፡፡ እንዲሁም ሮሜ 14[፡17]፡-
25 «የእግዚአብሔር መንግሥት … መብልና መጠጥ አይደለችምና» ይላል፡፡ ቈላ 2[፡16]፡-
«እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም … ስለ ሰንበት ማንም
26 አይፍረድባችሁ፡፡» *እንደገና [ቈላ 2፡20-21]፡- «ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ
ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፣ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት፡- 'አትያዝ፣ አትቅመስ፣
27 አትንካ' ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ?»*[177] ጴጥሮስ
በሐዋርያት ሥራ 15[፡10-11]፡- «እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን
ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለ ምን
ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ
28 እናምናለን» ይላል፡፡ እዚህ ላይ ጴጥሮስ የሙሴንም ሆነ የሌሎችን ተጨማሪ ሥርዓቶች
29 በሕሊናዎች ላይ መጫንን ይከለክላል፡፡ እንዲሁም 1ጢሞቴዎስ 4[፡1-3] የመብል ክልከላውን
የአጋንንት ትምህርት ብሎ ይጠራል፤ ምክንያቱም በእነርሱ በኩል ጸጋን ለማግኘት በማሰብ

---

[171] *epieikeia.*
[172] *scholae: universities* (ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት)፡፡
[176] *media res*:- የላቲኑ ተመሳሳይ adiaphora (ጽድቅም ሆነ ኩነኔ ያስከትላሉ ተብለው በጽሑፍ ያልተቀመጡ ነገሮች) ሲሆን፣ ኅሊናን ሳይጎዱ ሊደረጉ ወይም ሊተዉ የሚችሉ ነገሮች ማለት ነው፡፡
[177] የ1531 *edito princeps* እና የ1580ውና የ1584ቱ የላቲን የመጽሐፈ ስምምነት እትሞች ዘመም ባሉ ፊደላት የተጻፉትን ቃላት ይጨምሩበታል፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ነገሮችን መደንገግ ወይም መፈጸም፣ ወይም ያለ እነዚህ የአምልኮ
ተግባራት የክርስቲያን ጽድቅ ሊኖር እንደማይቻል ማሰብ ከወንጌል ጋር ይጻረራል።
30 እዚህ ላይ ባላጋራዎቻችን የእኛን ሰዎች እንደ ጆቪኒያን (Jovinian) ሥጋን
መግራትንና መጒሰምን ይከለክላሉ ብለው ይከስሳሉ። ነገር ግን በእኛ ሰዎች ጽሑፎች ውስጥ
31 ከዚህ የተለየ ነገር ማግኘት ይቻላል። ምክንያቱም መስቀልን በተመለከተ ክርስቲያኖች
32 ሁልጊዜ መከራን መቋቋም እንዳለባቸው አስተምረዋል። በተለያዩ መከራዎች መግራትና
ከክርስቶስ ጋር መሰቀል፣ ማስመሰል የሌለበት እውነተኛና የምር የሆነ ጒሰማ ነው።
33 በተጨማሪ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ከመጠን በላይ የሆነ ጫናም ሆነ ሥራ ፈትነት ወደ
ኃጢአት እንዳይስባቸው በአካላዊ ቊጥጥር ወይም በአካላዊ እንቅስቃሴና የጉልበት ሥራ
ራሳቸውን ማሠልጠንና መቈጣጠር አለባቸው ብለው ያስተምራሉ። ነገር ግን በእነዚህ
ልምምዶች የኃጢአት ይቅርታን እንደምናገኝ ወይም የኃጢአት ዕዳ ክፍያን እንደምንፈጽም
34 አያስተምሩም። እንደዚህ ያለው ሥጋን መግራት ዘወትር ሊበረታታ የሚገባው ሲሆን፣
35 ይህም በተወሰኑ ጥቂት ቀናት ብቻ መገደብ የለበትም። ክርስቶስ በ[ሉቃስ 21፡34]፡- «ነገር
ግን ልባችሁ ... ስለ ትዳር በማሰብ እንዳይከብድ ... ተጠንቀቁ» ብሎ እንደሚያዘው ነው።
36 እንዲሁም [ማርቆስ 9፡29]፡- «ይህ ወገን [ርኩስ መንፈስ] በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም
37 ሊወጣ አይችልም» ይላል። እንዲሁም ጳውሎስ፡- «ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ» ይላል
38 [1ቆሮ 9፡27]። እዚህ ላይ ሥጋውን የጎሰመው በዚህ ድርጊቱ የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት
ሳይሆን ሥጋውን ለመግዛት፣ ለመንፈሳዊ ነገሮች ራሱን ለማዘጋጀትና በተጠራበት ጥሪ
39 መሠረት ኃላፊነቱን እንደሚገባ መወጣት ይችል ዘንድ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ስለዚህ፣
ጾም በራሱ የተወገዘ አይደለም፤ ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ሥራዎች ለአምልኮ ተግባራት
አስፈላጊ የሆኑ ይመስል፣ ኅሊናን በሚጎዳ መልኩ አንዳንድ ቀናትንና ምግቦችን የሚወስኑ
ወጎች የተወገዙ ናቸው።
40 ሆኖም ግን፣ በቤተ ክርስቲያን መልካም ሥርዓትን ለማጽናት ተስማሚ የሆኑ፣
በቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት እንዳሉት ንባቦች፣ በዓላት፣ ወዘተ. ያሉ በርከት ያሉ ወጎች
41 በእኛ ዘንድ ይጠበቃሉ። ነገር ግን በተመሳሳይ መልኩ፣ እንዲህ ያሉ የአምልኮ ተግባራት
በእግዚአብሔር ፊት እንደማያጸድቁና ሌላውን በማያሰናክል መልኩ ሳይደረጉ ቢቀሩ፣
42 የሚያስቀጣ ኃጢአት እንዳልሆኑ ለሰዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። የሰው ሥርዓትን
በሚመለከት እንደዚህ ዓይነቱ ነጻነት በቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ያልታወቀ
43 አልነበረም። ምክንያቱም በምሥራቅ የትንሣኤ በዓል የሚከበረው ከሮም በተለየ ጊዜ ነበር፤
ደግሞም በዚህ ምክንያት የምሥራቁን መከፈል በመቃወም ሮማውያን በከሰሱ ጊዜ፣
እንደዚህ ዓይነት ልማዶች በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ መሆን የለባቸውም ተብለው በሌሎች
44 ደግሞ ተገሥጸዋል። ኢራንዮስ፣ «ስለ ጾም ያለው አለመግባባት የእምነትን አንድነት
አያፈርስም» ይላል፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጎርጎርዮስም[183] (ክፍል 12) እንደዚህ ዓይነቱ ልዩነት
45 የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አያፋልስም ሲል ያመለክታል። *Tripartite History*
(በትራይፓርታይት ሂስትሪ)፣ 9ኛ መጽሐፍ፣ የማይመሳሰሉ ሥርዓቶችን በተመለከተ በርከት
ያሉ ምሳሌዎች ተሰባስበዋል፤ የሚከተለው መግለጫም ይገኛል፡- «የሐዋርያት ዓላማ
የየበዓላቱን የአከባበር ሥርዓት መደንገግ ሳይሆን፣ በሕዝቡ መካከል መልካም ምግባርንና
እግዚአብሔርን መምሰልን ለመስበክ ነበር።»

## *[XXVII.] (27)ስለ ምንኩስና መሐላ*

1 የምንኩስና መሐላን በተመለከተ በእኛ ዘንድ የሚሰጠውን ትምህርት በተሻለ መልኩ
መረዳት የሚቻለው የገዳማቱ ሁኔታ እንዴት እንደ ነበረና በገዳማቱ ውስጥ በየቀኑ

[183] ምናልባትም ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጎርጎርዮስ 1ኛ *Letters,* bk. 9. ep. 12 (*MPL* 77: 955-58; *NPNF* 13:8-9) የተወሰደ።

ቀኖናዎቹን የሚጻረሩ ምን ያህል ድርጊቶች እንደሚከናወኑ ሲታወስ ነው። በአውግስጢኖስ
2 ዘመን ገዳማት የበጎ ፈቃድ ማኅበራት ነበሩ። በኋላ ግን ሥነ ሥርዓቶች እየተበላሹ
በሄዱበት ስፍራ ሁሉ፣ በጥንቃቄ እንደ ታቀደ እስር ቤት፣ ሥነ ሥርዓቶቹን ወደ ነበሩበት
ለመመለስ ሲባል መሐላዎቹ ተጨመሩ።

3-4 ቀስ በቀስ ብዙ ሌሎች ሕጎች በነባሮቹ መሐላዎች ላይ ተጨመሩ። በተጨማሪ፣
እነዚህ ሰንሰለቶች ቀኖናዎቹን በሚጻረር መልኩ፣ በሕግ ተጠያቂ ወደሚሆኑበት የዕድሜ
5 ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት በብዙዎች ላይ ተጭነው ነበር። ብዙዎች ወደዚህ ዓይነት
ሕይወት የገቡት በስሕተት ነበር፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ ዕድሜአቸው ለዚህ የበቃ
6 ቢሆንም የራሳቸውን ጥንካሬ አላጤኑትም ነበር። ምንም እንኳ አንዳንዶች ወደ ቀኖናዎቹ
ሸሽተው ነጻ መሆን የሚችሉ ቢሆኑም በዚህ ዓይነት ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ የገቡት
7 እዚያው እንዲቆዩ ተገደዋል፤ ምንም እንኳ ደካማው ጾታ የበለጠ የመትረፍ ዕድል የነበረው
8 ቢሆንም፣ ጫናው ከወንዶቹ ይልቅ በሴቶቹ ገዳማት የበረታ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ የከረረ
መመሪያ ከእኛ ዘመን በፊት የነበሩ ብዙ በጎ ሰዎችን ያሳዘነ ነበር። እነርሱም ሴቶችና
ወንዶች ልጆች በሕይወት ለመቆየት ሲሉ ወደ ገዳማት እንደ ገቡ ዐይተዋል። እነርሱም
እንዲህ ዓይነቱ ተገቢ ያልሆነ ዝግጅት ያስከተላቸውን ዐሳዛኝ ውጤቶች፣ ምን ዓይነት
አስነዋሪ ድርጊቶችን እንደ ፈጠረ፣ እንዲሁም ምን ዓይነት ወጥመድ በሕሊናዎች ላይ እንደ
9 ዘረጋ ዐይተዋል። በዚህ እጅግ አደገኛ ጉዳይ የቀኖናዎቹ ሥልጣን ፈጽሞ ችላ በመባሉና
10 በመናቁ አዝነዋል። ይባስ ብሎ መሐላዎቹ የነበራቸው ስም ትንሽ የተሻሉ ብልሆች የነበሩ
የቀድሞ መነኮሳትን በግልጽ አሳዝኗል።

11 ሰዎች መሐላዎች ከጥምቀት ጋር እኩል ናቸው ብለዋል፤ እንዲሁም በዚህ ዓይነት
ሕይወት መሐላዎች የኃጢአት ይቅርታንና በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅን እንደሚያስገኙ
12 አስተምረዋል። በእርግጥ የምንኩስና ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን ከማስገኘት
ያለፈ ነገር እንዳለው ጨምረው ገለጹ፦ እርሱም ትእዛዛትን ብቻ ሳይሆን የወንጌልንም
13 ምክር መጠበቅ ነው። በዚህ መንገድ የምንኩስና ሥራ ከጥምቀት እጅጉን የተሻለና የገዳም
ሕይወትም ሰው ሠራሽ የሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ሳይጠብቁ በጥሪአቸው ለእግዚአብሔር
ትእዛዝ ከሚገዙ ባለ ሥልጣናት፣ ቀሳውስትና ከመሳሰሉት ሕይወት የበለጠ ዋጋ ያለው ነው
14 ብለው አምነው ነበር። ከእነዚህ ነገሮች የትኞቹም ቢሆኑ የሚካዱ አይደሉም፤ ምክንያቱም
ሁሉም በመጽሐፎቻቸው ይገኛሉ።

15 ኋላ ላይ በገዳማቱ ውስጥ ምን ተፈጠረ? በቀድሞ ዘመን እነርሱ የቅዱስ ቃሉና
ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ሌሎች ትምህርቶች የሚሰጡባቸው ትምህርት ቤቶች ነበሩ፤
ጳጳሳትና ቀሳውስት የሚወሰዱት ከዚያ ነበር። አሁን ሁሉም ነገር ተለውጧል፤ እንዲሁም
16 በሚገባ የሚታወቀውን ነገር መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም። በቀድሞ ዘመን ምቹ የመማሪያ
ቦታዎች ነበሩ። እንግዲህ ሰዎች እንደዚህ ዓይነቱ ኑሮ የተመሠረተው ጸጋንና ጽድቅን
ለማስገኘት ነው ብለው ያስባሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የፍጹምነት ሁኔታ ነው ብለው
ያውጃሉ፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ከመሠረታቸው ከሁሉም የአኗኗር ዓይነቶች እጅግ
17 የበለጠ አድርገው ይመርጡታል። በዚህ ምክንያት ምንም ነገር በተንኮል ሳናጋንን፣ ይህንን
ጉዳይ በተመለከተ የሰዎቻችን ትምህርት ይበልጥ እንዲታወቅ ለማድረግ እነዚህን ነገሮች
ዘርዝረን ተናግረናል።

18 በመጀመሪያ ደረጃ፣[192] የሚያገቡትን ሰዎች በተመለከተ የእኛ ሰዎች ሳያገቡ ለመኖር
ተስማሚ ያልሆኑ ቢያገቡ ሕጋዊ እንደ ሆነ ያስተምራሉ፤ ምክንያቱም መሐላ
19 የእግዚአብሔርን ድንጋጌና ትእዛዝ አይሽርም። ከዚህ በተጨማሪ፣ ይህ የእግዚአብሔር
ትእዛዝ ነው [1ቆሮ 7:2]፦ «ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት
20 ትኑረው» ይላል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻም አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልዩ

[192] ሁለተኛው ዐሳብ/መረጃ በአንቀጽ 36 ላይ ይጀምራል።

ሥራ ምክንያት ጋብቻ የማይመለከታቸው ካልሆኑ በስተቀር የእግዚአብሔር ፍጥረትና
ድንጋጌ፡- «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» በሚለው በዘፍጥረት 2[:18]
21 መሠረት ወደ ጋብቻ ይመራቸዋል። ከዚህ የተነሣ ይህንን ትእዛዝና የእግዚአብሔርን
ድንጋጌ የሚፈጽሙ ኃጢአት የለባቸውም።
22 ለዚህ ምን ተቃውሞ ሊነሣ ይችላል? ማንኛውም ሰው አሁንም የመሐላን ግዴታ
ምንም ያህል የሚያጋንን ቢሆን፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲሽር ማድረግ አይቻልም።
23 ቀኖናዎቹ ማንኛውም ቃለ መሐላ ለበላይ ሥልጣን ተገዢ ነው ብለው ያስተምራሉ።
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚቃረኑ መሐላዎች ምንኛ ያነሰ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው!
24 እንግዲህ የመሐላዎቹ ግዴታዎች በምንም ምክንያት ሊቀየሩ የማይችሉ ከሆነ፣
የሮማ ጳጳሳት ልዩ ፈቃድ መስጠት ባልቻሉ ነበር። ምክንያቱም በግልጽ በመለኮታዊ
25 ሥልጣን የተቀመጠን ግዴታ መሻር ለሰው ልጅ ሕጋዊ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ የሮማ
ጳጳሳት እንዲህ ዓይነቱ ግዴታ አግባብ ባለው መንገድ ሚዛናዊነት መስተናገድ እንዳለበት
26 ወስነዋል። ብዙ ጊዜ ከመሐላ ነጻ እንዳደረጉ የምናነበው ከዚህ የተነሣ ነው። በእርግጥ
ከገዳም እንዲመለስ የተደረገው የአራጎን ንጉሥ ታሪክ በደንብ የሚታወቅ ነው፤ በእኛም
ዘመን ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎች አይታጡም።
27 ከዚህም በተጨማሪ፣ ባላጋራዎቻችን ስለ መሐላው ባሕርይ፣ ማለትም በፈቃደኛነት፣
28 በነጻ ምርጫና ሆን ተብሎ መደረግ ያለበት ስለ መሆኑ ምንም ሳይሉ፣ የመሐላውን ግዴታ
ወይም ውጤት የሚያጋንኑት ለምንድን ነው? ሆኖም ግን ዘላቂ የሆነ ንጽሕና እስከ ምን
29 ደረጃ ድረስ በሰው ችሎታ እንደሚሆን ዐይታወቅም። ቃለ መሐላውን በፈቃደኝነትና ሆን
ብለው በምርጫቸው የፈጸሙት ስንቶቹ ናቸው? ሴቶችና ወንዶች ልጆች በራሳቸው መወሰን
ወደሚችሉበት የዕድሜ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት በማግባባት አንዳንዴም ተገደው
30 መሐላውን እንዲፈጽሙ ተደርገዋል። በፈቃደኝነት ወይም ሆን ተብሎ ያልተገባን የተስፋ
ቃል እንዲፈጽሙ መገደድ ከመሐላው ባሕርይ ጋር የሚቃረን መሆኑን ሁሉም ሰው
የሚስማማበት ሆኖ ሳለ በግዴታዎቹ ላይ በጠባብ አስተሳሰብ አጥብቆ መከራከሩ ተገቢ
የማይሆነው ለዚህ ነው።
31 ብዙ ቀኖናዎች ከዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በፊት የሚደረጉትን መሐላዎች
ይሽራሉ፣ ምክንያቱም ከዚህ ዕድሜ በፊት ሰው ስለ ቀሪ ሕይወቱ ወይም ሕይወቷ ተገቢ
32 ውሳኔ የመስጠት አቅም እንዳለው ወይም እንዳላት ዐይታሰብም። ሌላው ቀኖና፣ የሰውን
ደካማነት ይበልጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዐሥራ ስምንት ዓመት በፊት መሐላ
33 መፈጸምን ስለሚከለክል፣ ጥቂት ዓመታትን ይጨምራል። ነገር ግን አንዱን ወይም ሌላውን
ብንከተል እጅግ በጣም የሚበዙቱ መሐላውን የፈጸሙት ወደዚህ ዕድሜ ከመድረሳቸው
በፊት በመሆኑ፣ ገዳማቱን ለቀው ለመውጣት ምክንያት አላቸው።
34 በመጨረሻ፣ ምንም እንኳ መሐላውን መጣስ ምናልባት እንዲታገድ ቢደረግም፣
35 የእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋብቻ እንዲፈርስ ሊያደርግ አይችልም። ምክንያቱም
አውግስጢኖስ በ(ክ. 27 ጥ. 1 ምዕ. «ኦቭ ሜሪየጅስ» "Of Marriages" እንደ ተጠቀሰው)
እነዚህ ጋብቻዎች መፍረስ እንደሌለባቸው ይገልጻል። ምንም እንኳ ሌሎች የኋላ ኋላ
ከእርሱ የተለየ አቋም የያዙ ቢሆንም፣ የእርሱ ሥልጣን በቸልታ የሚታለፍ አይደለም።
36 በተጨማሪ፣ ምንም እንኳ ጋብቻን በሚመለከት የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብዙዎችን
ከመሐላቸው ነጻ የሚያደርጋቸው ቢመስልም፣ የእኛ ሰዎች መሐላዎች ተቀባይነት
የማያገኙበትን ሌላም ምክንያት ያቀርባሉ፡- ጽድቅንና ጸጋን ያስገኛል ተብሎ ያለ
እግዚአብሔር ትእዛዝ በሰው የተደነገገና የተመረጠ ማንኛውም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ
አገልግሎት ልክ ክርስቶስ በ[ማቴ 15:9]፡- «የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ
37 በከንቱ ያመልኩኛል» እንደሚለው ከመንፈሳዊነት የራቀ ነው። ጳውሎስም በሰዎች
የተፈጠሩ የአምልኮ ተግባራትን በመጠበቅ ጽድቅን መሻት እንደማይገባ፣ ነገር ግን

ከክርስቶስ የተነሣ እግዚአብሔር ወደ ጸጋው የተቀበላቸው መሆኑን ለሚያምኑ በእምነት
እንደሚገኝ በየቦታው ያስተምራል።
38 ይሁን እንጂ፣ መነኮሳቱ የእነርሱ በሰው የተፈጠሩ የሃይማኖት ሥነ ሥርዓቶቻቸው
መጠበቅ የኃጢአት ዕዳ ክፍያን ይፈጽማል፤ ጸጋንና ጽድቅንም ሊሰጥ ይችላል ብለው በግልጽ
አስተምረዋል። ይህ ከክርስቶስ ክብር ከማስቀረት፣ የእምነትን ጽድቅ ከመሸፈንና ከመካድ
39 ውጪ ምን ሊሆን ይችላል? ስለዚህ፣ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የተለምዶ መሐላዎች
ከመንፈሳዊነት የራቁ የአምልኮ ተግባራት በመሆናቸው ተቀባይነት የሌላቸው ይሆናሉ።
40 ምክንያቱም መንፈሳዊ ያልሆነ መሐላ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለሚቃረን ተቀባይነት
የለውም። ምክንያቱም ቀኖናዎቹ እንደሚሉት ማንኛውም መሐላ የኃጢአት እስራት መሆን
የለበትም።
41 ጳውሎስ በ[ገላ 5፡4]፦ «በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ
42 ከጸጋው ወድቃችኋል» ይላል። ስለዚህ በመሐላ ለመጽደቅ የሚፈልጉ ከክርስቶስ ወድቀዋል፤
43 ከጸጋውም ተለይተዋል። ምክንያቱም መጽደቅ ከመሐላ የተነሣ ነው የሚሉ፣ ለክርስቶስ
44 የሚገባውን ክብር ለራሳቸው ሥራ ይሰጡታል። መነኮሳቱ የጸደቁትና የኃጢአት ይቅርታ
ያገኙት በመሐላው አማካይነትና ሕጉን በመጠበቃቸው እንደ ሆነ በግልጽ ማስተማራቸው
ሊካድ አይችልም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሥራዎቻቸውን ለሌሎች ማስተላለፍ እንደሚችሉ
45 በድፍረት በሚኩራሩበት ጊዜ በዚህ ላይ የበለጠ አሳፋሪ ነገሮችን ጨምረዋል። ማንም
ከጥላቻ የተነሣ ይህንን ማጋነን ቢፈልግ መነኮሳቱ ራሳቸው የሚያፍሩባቸው እንዴት በርካታ
46 ነገሮች ሊሰበስቡ በቻሉ ነበር! በተጨማሪ፣ የእነርሱ ሰው ሠራሽ ሕጎች ወደ ክርስትና
47 ፍጹምነት ደረጃ ሊያደርሱ እንደሚችሉ ሰዎችን አግባብተዋል። ታዲያ ይህ፣ መጽደቅን
በሥራ ማድረግ አይደለምን? ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጪ አንዳንድ ሰው ሠራሽ የአምልኮ
48 ተግባራትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሰዎች ማቅረብና እነዚህ የአምልኮ ተግባራት ሰውን
ያጸድቃሉ ብሎ ማስተማር ቀላል የማይባል አሳፋሪ ድርጊት ነው። ምክንያቱም እነዚህ
የሚያስደንቁ መልአክ የሚመስሉ ሥርዓቶች እና አስመሳይ የሆኑ የድኽነት፣ የትሕትና፣
እንዲሁም ሳያገቡ የመኖር አስመሳይነት ሕዝብን በማሳወር የእምነት ጽድቅ በቤተ
ክርስቲያን ውስጥ ከሁሉ በላይ ሊማሩት የሚገባ ሆኖ እያለ ተሸፍኗል።
49 ከዚህ በተጨማሪ፣ በፍጽምና ደረጃ የሚገኙት መነኮሳቱ ብቻ ናቸው የሚለውን
ዐሳብ ሰዎች በሚሰሙበት ጊዜ የእግዚአብሔር ትእዛዛትና እውነተኛው የእግዚአብሔር
አምልኮ ይሸፈናሉ። ምክንያቱም ለክርስቲያን ፍጽምና ማለት ከልብ እግዚአብሔርን
መፍራት፣ ከዚህም ጋር ትልቅ እምነት ያለው መሆን፣ ከክርስቶስ የተነሣ ቸር አምላክ
እንዳለን መታመን፣ ከጥሪያችን ጋር በተያያዘ ልንሸከማቸው ለሚገቡን ነገሮች ሁሉ
ከእግዚአብሔር እርዳታን መለመንና በእርግጠኝነት መጠበቅ፣ ይህ በእንዲህ እንዳለም፣
50 ለሌሎች በትጋት መልካም ማድረግና በጥሪያችን መሠረት ማገልገል ነው። እውነተኛ
ፍጽምናና እውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያጠቃልል እንጂ
ሳያገቡ መኖርን፣ ልመናን ወይም የተጎሳቈለ ልብስ መልበስን የሚያመለክት አይደለም።
51 በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ከእንደዚህ ዓይነት የውሸት የገዳም ኑሮ ሙገሳ ጎጂ የሆነ ውጤት
52 ያላቸው ብዙ አስተያየቶችን ይፈጥራሉ። ሳያገቡ መኖር ያለማቋረጥ ሲወደስ ይሰማሉ፤
53 ስለዚህም በጋብቻ ሕይወታቸው ሕሊናቸውን እያስጨነቁ ይኖራሉ። ለማኞች ብቻ ፍጹማን
እንደ ሆኑ ይሰማሉ፤ ስለዚህም ጥሪታቸውን የሚይዙት ወይም ሥራቸውን የሚያከናውኑት
54 በተጨነቀ ሕሊና ነው። አለመበቀል የወንጌል ምክር እንደ ሆነ አድርገው ይሰማሉ፤
ስለዚህም ይህ በምክር እንጂ በትእዛዝ የተከለከለ አይደለም ተብሎ ስለ ተነገራቸው
55 አንዳንዶች በግል ሕይወታቸው ለመበቀል አይፈሩም። ሌሎች ከዚህም ያለፈ ስሕተት
ይፈጽማሉ፤ ምክንያቱም ሁሉም የመንግሥት አካላትና ሕዝባዊ ቢሮዎች (ኃላፊነቶች)
ለክርስቲያኖች የማያስፈልጉና ከወንጌል ምክር ጋር የሚጋጩ ናቸው ብለው ይደመድማሉ።

56 ትዳራቸውን ጥለውና የመንግሥት አስተዳደር ተሳትፎአቸውን ትተው ወደ ገዳም
57 የገቡ ሰዎችን ታሪክ ማንበብ ይቻላል። ይህንንም «ከዓለም መሸሽ» እና «የቅድስና ሕይወት
ፍለጋ» ብለውታል። ሰዎች በፈጠሩአቸው ትእዛዛት ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ
58 ባስተላለፋቸው ትእዛዛት ሊገለገል እንደሚገባው አልተረዱም። መልካምና ፍጹም የሆነ
59 አኗኗር የእግዚአብሔር ትእዛዝ ያለው ነው። ሰዎች በእነዚህ ጉዳዮች መመሪያ
ማግኘታቸው አስፈላጊ ነበር።
60 ከእኛ ዘመን በፊት ጌርሶንም ፍጽምናን በተመለከተ የመነኮሳትን ስሕተት ገሥጾአል፤
በእርሱ ዘመንም የገዳም ኑሮ የፍጽምና ሁኔታ ነው መባሉ ያልተለመደ እንደ ነበረም
መስክሯል።
61 ስለዚህ ከመሐላዎች ጋር የተያያዙ ብዙ ቀና ያልሆኑ ዐስተሳሰቦች አሉ፡- ያጸድቃሉ፤
ክርስቲያናዊ ፍጽምናን ያስገኛሉ፤ መነኮሳት ምክሮችንና ትእዛዛትን ይጠብቃሉ፤ ደግሞም
62 እነርሱ ከሚፈለገው በላይ መልካም ሥራ ይሠራሉ የሚሉ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ
ሐሰትና ፍሬ ቢስ በመሆናቸው፣ መሐላዎችን ተቀባይነት የሌላቸው ያደርጋሉ።

## *[XXVIII.] (28)ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን*

1 በቀድሞ ዘመን፣ አንዳንድ ሰዎች ያለ አግባብ የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣንና የሰይፍን
2 ሥልጣን በመደባለቃቸው የጳጳሳትን ሥልጣን በተመለከተ ከባድ ውዝግቦች ነበሩ። ከዚህም
ግራ መጋባት የተነሣ ታላላቅ ጦርነቶችና ዐመፆች ተከስተዋል። ጳጳሳቱ በክህነት ሥልጣን
ተመክተው ዐዳዲስ የአምልኮ ዓይነቶችን በመደንገግ፣ ጉዳዮችን በይደር በማቆየትና ከባድ
ውግዘት በማስተላለፍ የሕሊና ጫና በመፍጠር ብቻ ሳይገደቡ ምድራዊ መንግሥታትን
ለመሻርና ለመሾም የሚሞክሩና የነገሥታትን የመግዛት መብት የሚቀሙ ነበሩ።
3 ለእግዚአብሔር ያደሩና የተማሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ እነዚህን መጥፎ ምግባሮች
4 ከረጅም ጊዜ ጀምሮ አውግዘዋቸዋል። ስለዚህ ነው የእኛ ሰዎች ሕሊናዎችን ለማስተማር
ሲሉ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና በሰይፍ ሥልጣን መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት
የተገደዱት። እነርሱ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ምክንያት ሁለቱም በምድር ላይ እግዚአብሔር
የሰጣቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ በረከቶች እንደ ሆኑ ተደርገው በኃይል መከበርና መያዝ
እንዳለባቸው አስተምረዋል።
5 ይሁን እንጂ፣ እነርሱ፣ በወንጌሉ መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያን ወይም የጳጳሳቱ
ሥልጣን ወንጌሉን ለመስበክ፣ ኃጢአትን ይቅር ለማለትና ለመያዝ እንዲሁም ቅዱሳት
ምሥጢራትን ለማካሄድ በእግዚአብሔር የተሰጠ አደራ ሥልጣን መሆኑን ያምናሉ፤
6 ምክንያቱም ክርስቶስ ሐዋርያቱን በዚህ ትእዛዝ ልኮአቸዋል [ዮሐንስ 20፡21-23]፡- «አብ
እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ... መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር
7 ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል።» ደግሞም በማርቆስ
16[፡15]፡- «ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ...» አላቸው።
8 ይህ ሥልጣን የሚተገበረው በግለ ሰቡ ጥሪ መሠረት ለብዙኃን ወይም ለግለ ሰቦች
ወንጌልን በማስተማር ወይም በመስበክ እንዲሁም ቅዱሳት ምሥጢራትን በማካሄድ ብቻ
ነው። ምክንያቱም የሚሰጡት ሥጋዊ ነገሮች ሳይሆኑ፣ ነገር ግን ዘላለማዊ ነገሮች፣
ዘላለማዊ ጽድቅ፣ መንፈስ ቅዱስና፣ ዘላለማዊ ሕይወት ስለ ሆኑ ነው። ጳውሎስ [በሮሜ
9 1፡16]፡- «በወንጌል አላፍርምና ... ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና»
እንዳለው፣ እነዚህ ነገሮች በቃሉና በቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎት አማካይነት ካልሆነ
10 በቀር ሊገኙ አይችሉም። ደግሞም መዝሙር 119[፡50]፡- «ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና»
ይላል። ስለዚህ፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ዘላለማዊ ነገሮችን የሚሰጥ ስለሆነና ይህም
ተግባራዊ የሚሆነው በቃሉ አገልግሎት በኩል ብቻ በመሆኑ፣ በምድራዊ መንግሥት

አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ ገብነቱ የዝማሬ ጥበብ በእርሱ ውስጥ ጣልቃ የመግባቱን ያህል
11 ትንሽ ነው። ምክንያቱም ምድራዊ መንግሥት የሚመለከተው ከወንጌል ውጭ ያሉትን
ነገሮች ነው። ምክንያቱም የሕግ ባለ ሥልጣን አእምሮን ሳይሆን ሥጋዊ አካልንና
ቊሳቊሶችን ግልጥ ከሆነ ጉዳት የሚጠብቅና የሰዎችንም ድርጊት የሚገድበው ሰይፍን
በማንሣትና በአካላዊ ቅጣት ስለ ሆነ ነው። ወንጌሉ አእምሮን መንፈሳዊነት ከጐደለው
ዐስተሳሰብ፣ ከዲያብሎስና ከዘላለማዊ ሞት ይጠብቃል።

12 ከዚህም የተነሣ፣ የቤተ ክርስቲያንና የምድራዊ መንግሥት ሥልጣን መደባለቅ
የለባቸውም። የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ወንጌልን ለመስበክና ቅዱሳት ምሥጢራትን
13 ለማካሄድ የራሱን ኀላፊነት የያዘ ነው። የሌላውን ሥራ መቀማት፣ ምድራዊ መንግሥታትን
ማሸጋገር፣ የሕግ ባለ ሥልጣንን ሕግ መሻር፣ ለተፈቀደው ነገር መታዘዝን ማስቀረት፣
ምድራዊ ሥነ ሥርዓቶችን ወይም ስምምነቶችን በሚመለከት ረገድ በፍርድ ጉዳይ ጣልቃ
መግባት፣ መመሥረት ያለበትን የመንግሥት ዓይነት በሚመለከት ረገድ ለሕግ ባለ
14 ሥልጣናት ሕግጋትን መቅረጽን በተመለከተ ጣልቃ መግባት የለባትም። ክርስቶስ [በዮሐንስ
15 18፡36]፡- «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም»፤ እንደ ገናም [በሉቃስ 12፡14]፡- «ፈራጅና
16 አካፋይ በላያችሁ እንድሆን ማን ሾመኝ?» እንደሚለው ነው። ቅዱስ ጳውሎስም በፊልጵስዩስ
17 3[፡20]፡- «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና»፤ ደግሞም በ2 ቆሮንቶስ 10[፡4]፡- «የጦር ዕቃችን
ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው» ይላል።

18 በዚህ ዓይነት እንግዲህ የእኛ ሰዎች የሁለቱን ሥልጣናት ተግባር ይለያሉ፤ ደግሞም
ሁለቱም በክብር መያዝና እንደ እግዚአብሔር ስጦታና በረከት መታየት ይገባቸዋል ብለው
ያዝዛሉ።

19 ጳጳሳት ሰይፍ ለማንሣት ሥልጣን የሚኖራቸው ከሆነ ይህን ሥልጣን በወንጌል
ትእዛዝ ያገኙት ሳይሆን፣ ነገር ግን ለአገራቸው ምድራዊ አስተዳደር በነገሥታትና በንጉሠ
ነገሥታት አማካይነት በሰብአዊ መብት የተሰጣቸው ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ ከወንጌል
አገልግሎት የተለየ ተግባር ነው።

20 ስለዚህ፣ አንድ ሰው ስለ ጳጳሳት ሥልጣን በሚጠይቅበት ጊዜ፣ የፖለቲካ አገዛዝን
21 ከቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ለይቶ ማየት ይኖርበታል። ከዚህም የተነሣ በወንጌሉ መሠረት፣
ወይም እነርሱ እንደሚሉት፣ ጳጳሳት እንደ መሆናቸው በመለኮት ሥልጣን፣ ይህ ሥልጣን
ለጳጳሳት የተሰጣቸው (ማለትም፣ የቃሉና የቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎት ለተሰጣቸው)፣
ኃጢአትን ይቅር ለማለት፣ ወንጌሉን የሚቃወም ትምህርትን ለማስወገድና ፈሪሃ
እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች ክፉ ሥራቸው በግልጽ ሲታወቅ ከቤተ ክርስቲያን የቅዱስ
22 ቊርባን ማዕድ ለማግለል ነው። ይህንንም የሚደርጉት በሰው ሥልጣን ሳይሆን በቃሉ
ሥልጣን ነው። ይህንን በሚመለከት «የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል» እንደ ተባለው [ሉቃስ
10፡16]፣ አብያተ ክርስቲያናት ለጳጳሳት እንዲገዙ በመለኮት ሥልጣን ታዘዋል።

23 ይሁን እንጂ፣ ከወንጌሉ ተቃራኒ የሆነ አንዳች ነገር በሚያስተምሩ ወይም
በሚመሠርቱ ጊዜ፣ አብያተ ክርስቲያናት ለዚህ እንዳይታዘዙ የሚከለክል ከእግዚአብሔር
24 የሆነ ትእዛዝ አላቸው። ማቴ 7[፡15]፡- «ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።» ገላትያ 1[፡8]፡-
«እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ
25 የተረገመ ይሁን!» 2ቆሮንቶስ 13[፡8፣10]፡- «ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም
ለማድረግ አንችልምና፣» ደግሞም «ጌታ ለማፍረስ ያይደለ ለማነጽ እንደ ሰጠኝ ሥልጣን»
27 ይላል። ቀኖናዎቹም በክፍል II፣ ጥ.7፣ ምዕራፎች «ፕሪስትስ» እና «ሺፕ» “Priests” and
28 “sheep” የተባሉት ተመሳሳይ ነገር ያዝዛሉ። አውግስጢኖስም ጴጢሊያንን ተቃውሞ በጻፈው
ደብዳቤ ላይ የሁሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ምናልባት ቢሳሳቱና በቀኖናዎቹ
ውስጥ ካሉት የእግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍት ተቃራኒ የሆነ አንዳች ነገር ቢይዙ አንድ
ሰው ከእነርሱ ጋር መስማማት የለበትም ይላል።

29 ውሳኔ ለመስጠት (ለምሳሌ ጋብቻን ወይም ዐሥራትን ወዘተ በሚመለከት) ከዚህ
ሌላ አንዳች ኃይል ወይም ሥልጣን ቢኖራቸው ይህንኑ ያገኙት በሰው ሥልጣን ነው።
እነዚህ የበላይ ጠባቂዎች እነዚህን ነገሮች መሥራት ቢተዉ መሳፍንት ያለፈቃዳቸው
ቢሆንም እንኳ የሕዝብን ሰላም ለማስጠበቅ ሲሉ ለዜጎቻቸው ፍትሕን ለማስፈን ይገደዳሉ።
30 በተጨማሪ፣ ጳጳሳት ወይም ቀሳውስት በቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓቶችን
የማቋቋምና እንዲሁም ምግብን፣ የበዓላት ቀናትን፣ የአገልጋዮችን ማዕረጎች ወይም
ደረጃዎች ወዘተ የሚመለከቱ ሕግጋትን የማውጣት መብት ያላቸው መሆኑ አከራካሪ ነው።
31 ይህንን መብት ለጳጳሳት የሚሰጡ ሰዎች የሚጠቅሱት ማስረጃ [ዮሐንስ 16:12-13]፦
«የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፤ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ
የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» የሚለውን ቃል ነው።
32 ደግሞም [በሐዋርያት ሥራ 15:20-29] ከደምና ከታነቀ ነገር መራቅን ያዘዙትን፣
የሐዋርያትን ምሳሌነት ይጠቅሳሉ። ከዐሥርቱ ትእዛዛት ተቃራኒ የሚመስለውን ወደ እሑድ
33 የተለወጠውን ሰንበት ደግሞ ይጠቅሳሉ። ከዚህ የሰንበት ለውጥ ይልቅ ብዙውን ጊዜ
የሚቀርብ ምሳሌ የለም። ቤተ ክርስቲያን በዐሥርቱ ትእዛዛት ላይ ለመወሰን የሚያበቃ
ታላቅ ሥልጣን አላት! ሲሉ ይከራከራሉ።
34 ይሁን እንጂ፣ ይህንን ጥያቄ በሚመለከት፣ እላይ እንደ ተገለጠው፣ የእኛ ሰዎች
ጳጳሳት ከወንጌል ተቃራኒ የሆነ አንዳች ነገር ለመመሥረት ሥልጣን የላቸውም ሲሉ
35 ያስተምራሉ። ቀኖናዎቹም በክፍል 9 በሙሉ ይህንን ይገልጣሉ። በተጨማሪም፣ እነርሱን
በመጠበቅ የኃጢአትን ዕዳ ክፍያ መፈጸምና ጽድቅን ማግኘት እንችል ዘንድ አንዳንድ
36 ወጎችን ማቋቋም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ነው። ምክንያቱም እንደዚህ ያሉትን
ነገሮች በመጠበቅ እንጸድቃለን ብለን በምናስብበት ጊዜ የክርስቶስን ሥራ ክብር ማርከስ
37 ነው። ይሁን እንጂ፣ በዚህ ዐስተሳሰብ ምክንያት እምነትና የእምነትን ጽድቅ የሚመለከተው
ትምህርት ተጨቍኖ ቍጥር ስፍር የሌላቸው ወጎች በቤተ ክርስቲያን እንደ ተከሰቱ
የተረጋገጠ ነው። ምክንያቱም ተጨማሪ የበዓላት ቀናት በተደጋጋሚ ተፈጥረዋል፤
አጽዋማት ታውጀዋል፤ እንዲሁም ዐዳዲስ ሥነ ሥርዓቶችና ትእዛዞች ተቋቁመዋል፤
ምክንያቱም የእነዚህ ነገሮች መሥራቾች በእነዚህ ተግባራት አማካይነት ጸጋን እናገኛለን
38 ብለው ስለ ገመቱ ነው። ስለዚህ የንስሐ ቀኖናዎች በቀድሞ ዘመን እየጨመሩ የሄዱ ሲሆን፣
አሁንም እኛ የእነርሱን ርዝራዦች በኃጢአት ዕዳ ክፍያዎች ውስጥ እናገኛቸዋለን።
39 እንደ ገናም፣ የወጎቹ መሥራቾች ኃጢአትን ከምግብ፣ ከቀናትና ከመሳሰሉ ነገሮች
ጋር በማያያዛቸውና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሕግ እስራትን በመጫናቸው ጽድቅን ለማግኘት
እነዚህን ማቋቋም በዘሌዋውያን እንደሚታዩት ያሉ የአምልኮ ተግባራት በክርስቲያኖች
መካከል ሊኖሩ ይገባ ይመስል፣ ደግሞም እግዚአብሔር እነዚህን እንዲያቋቁሙ
ሐዋርያትንና ጳጳሳትን ያዘዘ ይመስል፣ ይህን ሲያደርጉ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር
40 በተቃረነ መልኩ መንቀሳቀሳቸው ነው። ምክንያቱም አንዳንዶች በዚህ መንገድ ጽፈዋል፤
41 ጳጳሳቱም በሙሴ ሕግ ምሳሌነት በተወሰነ ደረጃ የተታለሉ ይመስላሉ። ከዚህም የሚከተሉት
ሸክሞች ተፈጠሩ፦ ሌሎችን ባያስቀይምም እንኳ በበዓላት ቀኖች የጉልበት ሥራ መሥራት
ሞት የሚገባው ኃጢአት እንደ ሆነ፣ አንዳንድ ምግቦች ሕሊናን የሚያረክሱ እንደ ሆኑ፣
ጾም ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ጻሩ ግን አካላዊ ሥቃይን በሚያስከትልበት ጊዜ እግዚአብሔርን
የሚያስደስት ሥራ እንደ ሆነ፣ ቀኖናዊ ሰዓታትን ማስተጓጐል ሞት የሚገባው ኃጢአት
እንደ ሆነ፣ ምንም እንኳ ቀኖናዎቹ ራሳቸው የሚናገሩት በደልን ስለ መያዝ ሳይሆን የቤተ
ክርስቲያንን ቅጣቶች ስለ መያዝ ቢሆንም፣ ጉዳዩን ከያዘው ሰው ፈቃድ ውጭ በተያዘ
ጉዳይ ላይ ኃጢአትን ይቅር ለማለት አይቻልም የሚሉት ናቸው።
42 ጳጳሳት ሕሊናን ለማጥመድ እንደዚህ ያሉትን ወጎች በቤተ ክርስቲያን ላይ
የመጫንን መብት ከወዴት አገኙ? ጴጥሮስ በደቀ መዛሙርት ላይ ቀንበር መጫንን
የከለከለበት ሐቅ እያለ፣ እንዲሁም ጳውሎስ ለማፍረስ ያይደለ ነገር ግን ለማነጽ ሥልጣን

የተሰጣቸው መሆኑን እየተናገረ፣ እነርሱ በእንደዚህ ያሉ ወጎች አማካይነት ኃጢአትን
የሚጨምሩት ለምንድን ነው?
43 የሆነ ሆኖ፣ የእግዚአብሔርን ቍጣ ለማብረድ ወይም ለድነት አስፈላጊ እንደ ሆኑ
44 አድርጎ ወጎችን መመሥረትን የሚከለክሉ ግልጽ የሆኑ ምስክሮች አሉ። ጳውሎስ በቈላስይስ
2[፡16፣20-23]፡- «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር
45 መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ»፤ ደግሞም «ከዓለማዊ ከመጀመሪያ
ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት አትያዝ፤
አትቅመስ፤ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ
ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና፤ ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም
46 በመጨቈን ጥበብ ያለው ይመስላል» ይላል። ቲቶ 1[፡14]፡- «ስለዚህ ምክንያት የአይሁድን
ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ ...» ይላል።
47 ክርስቶስ በማቴዎስ 15[፡14] ወጎችን ስለሚፈልጉ ሰዎች፡- «ተዉአቸው፤ ዕውሮችን
48 የሚመሩ ዕውሮች ናቸው» ይላል። ደግሞም «የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ
ይነቀላል» [ማቴዎስ 15፡13] በማለት እንዲህ ያሉትን የአምልኮ ተግባራት ይቃወማል።
49 ጳጳሳት ሕሊናዎችን እንደዚህ ባሉ ወጎች ለመጫን መብት ካላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ
ወጎች መመሥረትን እንደዚህ በተደጋጋሚ የሚከለክለው ለምንድን ነው? ለምንስ የአጋንንት
ትምህርቶች ብሎ ይጠራቸዋል? መንፈስ ቅዱስስ ስለ እነርሱ ያስጠነቀቀው በከንቱ ነውን?
50 ስለዚህ፣ አስፈላጊ ናቸው ተብለው፣ ወይም ጽድቅን ያስገኛሉ በሚል ዐስተሳሰብ
የሚቋቋሙ ሥርዓቶች ከወንጌሉ ጋር የሚጋጩ ስለ ሆነ፣ እንደነዚህ ያሉትን የአምልኮ
ተግባራት ማቋቋምም ሆነ አስፈላጊ እንደ ሆኑ አድርጎ መደንገግ ለጳጳሳት ሕጋዊነት
51 የለውም ማለት ነው። ምክንያቱም በገላትያ [5፡1]፡- «እንደ ገናም በባርነት ቀንበር
52 አትያዙ» ተብሎ እንደ ተጻፈው በሕግ መታሰር ለመጽደቅ አስፈላጊ አይደለም የሚለውን
የክርስትናን ነጻነት የሚመለከተውን ትምህርት በአብያተ ክርስቲያናት አጥብቆ መያዝ
አስፈላጊ ነው። ጸጋን የምናገኘው በክርስቶስ በማመን እንጂ አንዳንድ ሥርዓቶችን በመፈጸም
ወይም በሰዎች በተቋቋሙ የአምልኮ ተግባራት አማካይነት አይደለም የሚለውን የወንጌልን
ዋና አንቀጽ አጥብቆ መያዝ አስፈላጊ ነው።
53 ስለዚህ፣ አንድ ሰው በአምልኮ ስፍራዎች ስለ እሑድና ተመሳሳይ ሥርዓቶች ማሰብ
የሚገባው ምንድን ነው? ለዚህ ጕዳይ የእኛ ሰዎች ሲመልሱ በእነርሱ አማካይነት
የኃጢአታችንን ዕዳ ክፍያ ለመፈጸም ወይም የሰው ሕሊና ለአምልኮ ተግባር አስፈላጊ
እንደሆኑ አድርጎ እንዲቀበላቸው ለማስገደድ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ማንኛውም ነገር
በሥርዓት እንዲካሄድ ጳጳሳትና ቀሳውስት ሥርዓቶችን ማቋቋማቸው ተገቢ ስለሆነ ነው
54 ይላሉ። ስለ ሆነም ጳውሎስ ሴቶች በማኅበር ራሳቸውን እንዲሸፍኑ አዘዘ [1ቆሮ 11፡5]፤
ደግሞም በቤተ ክርስቲያን የሚተረጐሙ ሥርዓት ባለው መንገድ ሊደመጡ ይገባል
ብሎአል [1ቆሮ 14፡30]።
55 አብያተ ክርስቲያናት ለፍቅርና ለጸጥታ ሲባል ለእነዚህ ሥርዓቶች መታዘዛቸው
ደግሞም ሌሎችን እስካላሰናከሉ ድረስ መጠበቃቸው ተገቢ ነው። ስለ ሆነም፣ በአብያተ
ክርስቲያናት ሁሉም ነገር በማያደናግር መልኩ ሥርዓት ባለው መንገድ መከናወን አለበት፤
56 ዳሩ ግን ሕሊና እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን ለድነት አስፈላጊ ናቸው ብሎ በማሰብ፣ ወይም
ያለ ማሰናከያ እነርሱን በሚተላለፍበት ጊዜ ኃጢአት አድርጌአለሁ በማለት
በማይጨነቅበት መንገድ መሆን አለበት። ልክ አንዲት ሴት ማንንም በማያስቀይም ሁኔታ
ራስዋን ሳትሸፍን ከቤት ብትወጣ ኃጢአት አደረገች ብሎ ማንም እንደማይናገር እንደዚሁ
ነው።
57 እሑድን፣ ፋሲካን፣ በዓለ ሃምሳንና የመሳሰሉትን በዓላትና ሥርዓቶች የመጠበቅም
58 ጕዳይ እንደዚሁ ነው። ምክንያቱም፣ በሰንበት ምትክ እሑድን የማክበር አስፈላጊነት በቤተ

ክርስቲያን ሥልጣን የተቋቋመ ነው ብለው የሚፈርጁ ሰዎች ተሳስተዋል፡፡ ሰንበትን
59 ያስቀረው የእግዚአብሔር ቃል እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፡፡ ምክንያቱም ወንጌል
60 ከተገለጠ በኋላ ሁሉም የሙሴ ሥነ ሥርዓቶች ሊወገዱ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕዝቡ
መሰብሰብ የሚችሉበትን ቀን ያውቁ ዘንድ አንድ ቀን መመደብ አስፈላጊ እንደ መሆኑ
መጠን ቤተ ክርስቲያን ለዚሁ ዓላማ እሑድን የመደበች ይመስላል፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ ሰዎች
ለክርስትና ነጻነት አንድ ምሳሌ ሊኖራቸውና ሰንበትንም ሆነ ሌላን ቀን ማክበር አስፈላጊ
እንዳልሆነ ሊያውቁ ስለሚችሉ ይህ የሚያስደስት ነገር ነበር፡፡
61 አሁንም የሕጉን መለወጥ በሚመለከት፣ የዐዲሱን ሕግ ሥነ ሥርዓቶች በሚመለከት፣
የሰንበትን መለወጥ በሚመለከት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አምልኮ እንደ ሌዋውያን
አምልኮ ዓይነት መሆን አለበት ከሚል የተሳሳተ ዐስተሳሰብና ክርስቶስ ለድነት አስፈላጊ
የሆኑ ዐዳዲስ ሥርዓቶችን እንዲቀርጹ ሐዋርያትንና ጳጳሳትን ሾሞአቸዋል ከሚል ዐስተሳሰብ
62 የመነጩ ከፍተኛ የሆኑ ክርክሮች አሉ፡፡ እነዚህ ስሕተቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርገው
63 የገቡት በእምነት የሆነ ጽድቅ በበቂ ግልጽነት በማይሰበክበት ጊዜ ነበር፡፡ አንዳንዶች
እሑድን ማክበር እንደ መለኮት ሥልጣን «የሚቈጠር» እንጂ «በእርግጥ» የመለኮት
ሥልጣን አይደለም ብለው ይከራከራሉ፡፡ ደግሞም ሰዎች በበዓላት ቀኖች ምን ያህል ሥራ
64 መሥራት እንደሚፈቀድላቸው ይደነግጋሉ፡፡ እነዚህን የመሰሉ ክርክሮች ለሕሊና ወጥመዶች
እንጂ ሌላ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ምክንያቱም እነርሱ ምንም እንኳ ለወጎች ፍትሕን
ለማስገኘት የሚሞክሩ ቢሆንም[222] አስፈላጊ ናቸው የሚለው ዐስተሳሰብ እስካለ ድረስ ፈጽሞ
ሚዛናዊነት ሊገኝ አይችልም፡፡ በእምነት የሆነው ጽድቅና የክርስትና ነጻነት ቸል በሚባልበት
ቦታ ሁሉ ይህ ዐስተሳሰብ ጸንቶ ይኖራል፡፡
65 ሐዋርያት ከደም፣ ወዘተ. መራቅ እንደሚገባ አዝዘዋል፡፡ አሁን ይህን ትእዛዝ የሚጠ
ብቅ ማን ነው? ይህንን የማይጠብቁ ሰዎች ኃጢአት እየሠሩ ነው ለማለት እንደማይቻል
የተረጋገጠ ነው፡፡ ምክንያቱም ሐዋርያት እንደዚህ ባለ እስራት አማካይነት ሕሊናን
ለመጫን ፍላጎት ስላልነበራቸው ነው፡፡ ገደቡን ያወጡት ለጊዜው ማሰናከያን ለማስቀረት
66 ነበር፡፡ ምክንያቱም የወንጌሉ አጠቃላይ ዐሳብ ከዚህ ድንጋጌ ጋር ተያይዞ መታየት አለበት፡፡
67 ዳሩ ግን ከቀኖናዎቹ ማንኛውም ቢሆን በተጻፈው መሠረት እምብዛም አይጠበቅም፡፡
68 ስለ ወጎች በሚሟገቱ ሰዎች መካከል እንኳ ከእነዚህ ብዙዎቹ በየቀኑ ይዘነጋሉ፡፡ ይህ
የሚዛናዊነት መለኪያ ካልተጠበቀ በስተቀር ሕሊናን መምከር የሚቻል አይደለም፡፡ ከዚህ
የተነሣ፣ አስፈላጊ እንደሆኑ ተደርገው እስካልተቈጠሩና በዚህ ጉዳይ የሰዎች ልምምድ
ቢለወጥም ሕሊናን እስካልጐዱ ድረስ ወጎች ሊጠበቁ እንደሚችሉ እናውቃለን፡፡
69 ይሁን እንጂ፣ ጳጳሳቱ በበጎ ሕሊና ሊጠበቁ የማይችሉ ወጎችን እንዲፈጽሙ
70 ካላስገደዱ በስተቀር ተገቢነት ያለውን መታዘዝ በቀላሉ ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ እንግዲህ ሳያገቡ
መኖርን በሰው ላይ ይጭናሉ፤ ደግሞም ንጹሑን የወንጌል ትምህርት እንደማያስተምር
71 መሐላ ካልፈጸመ በቀር ማንንም ሰው አይቀበሉም፡፡ ምንም እንኳ መልካም እረኞች
ሊያደርጉት የሚገባ ነገር ቢሆንም፣ ጳጳሳት ክብራቸውን መሥዋዕት በማድረግ ስምምነትን
72 እንዲያስገኙ አብያተ ክርስቲያናችን አይጠይቁም፡፡ የሚጠይቁት ጳጳሳቱ ተገቢ ያልሆኑትንና
ዐዲስ የሆኑትን እንዲሁም የሁሉ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልማድ በተቃራኒው ተቀባይነት
73 ያገኙትን ሸክሞች እንዲያረግቡ ብቻ ነው፡፡ ምናልባት በመጀመሪያ ለእነዚህ ሥርዓቶች
ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ነበሩ፤ ዳሩ ግን እነርሱ ለኋለኛው ዘመን የሚስማሙ
74 አይደሉም፡፡ ደግሞም አንዳንዶቹ በስሕተት ተቀባይነትን ያገኙ ይመስላል፡፡ ስለዚህ፣ ጳጳሳት
እነርሱን በማቅለል ርኅራኄአቸውን ሊያሳዩ ይገባል፤ ምክንያቱም እንደዚህ ያለው ለውጥ
ለቤተ ክርስቲያን አንድነት አስጊ ሊሆን አይችልም፡፡ ለምን ቢባል ቀኖናዎቹ እንደሚያሳዩት
75 ዘመናት እያለፉ ሲሄዱ ብዙ የሰዎች ወጎች ስለ ተለወጡ ነው፡፡ ዳሩ ግን ያለ ኃጢአት

[222] *epiikeizare* የ220ን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

ሊጠበቁ የማይቻሉትን ሥርዓቶች ለማርገብ አስቸጋሪ ከሆነ ከሰዎች ይልቅ ለእግዚአብሔር
መታዘዝ ይገባናል ለሚለው የሐዋርያት ማስጠንቀቂያ መገዛት ተገቢ ይሆናል [የሐዋ
5፡29]፡፡
76 ጴጥሮስ ጳጳሳት አብያተ ክርስቲያናትን በኃይል እንዳይገዙና እንዳያስገድዱ
77 ይከለክላል፡፡ የአሁኑ ጉዳይ ጳጳሳት ሥልጣናቸውን መጠቀም እንዲተዉ የሚያደርግ
አይደለም፤ ነገር ግን የተጠየቀው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ይኸውም ወንጌሉ በንጽሕና
መሰበኩን እንዲፈቅዱና ያለ ኃጢአት ሊጠበቁ የማይችሉትን እነዚያን ጥቂት ሥርዓቶች
78 እንዲያረግቡ ነው፡፡ ይህንን የማያደርጉ ከሆነ በግትር አቋማቸው ለመለያየት ሰበብ በመፍጠ
ራቸው በእግዚአብሔር ፊት ምን ምክንያት ማቅረብ እንዳለባቸው ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

*[መደምደሚያ]*

1 አከራካሪ ናቸው ተብለው የታሰቡትን ዋና ዋና አንቀጾች ዘርዝረናል፡፡ ምንም እንኳ
ከዚህ የበለጡ ሌሎችም በርካታ አግባብነት የሌላቸው ነገሮች ሊጠቀሱ ቢችሉም፣ ብዙ
2 መንዛዛትን ለማስወገድ ዋና ዋናዎቹን ብቻ አካትተናል፡፡ ስለ ስርየት ማግኛ ሽያጭ ጽሑፍ፣
ስለ ሃይማኖታዊ ጉዞዎችና ውግዘትን ያለ አግባብ ስለ መጠቀም ከባድ ስሞታዎች ነበሩ፡፡
ሰበካዎች የስርየት ማግኛን ጽሑፍ በሚሸጡ ሰባኪዎች ተበሳጭተዋል፡፡ በቄሶችና በመነኮሳት
መካከል የሰበካ መብቶችን፣ ኑዛዜዎችን፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቶችንና ስፍር ቍጥር የሌላቸው
3 ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ያልተቋረጠ ጠብ ሲካሄድ ቆይቶአል፡፡ ቀደም ሲል በአጭሩ
የቀረቡት ዋና ዋና ነጥቦች በይበልጥ በቀላሉ ይታወቁ ዘንድ እንደዚህ የመሳሰሉትን ጉዳዮች
4 ትተናቸዋል፡፡ በዚህ ውስጥ ማንንም ለመሳደብ የተነገረ ወይም የተወሳ አንድም ነገር የለም፡፡
5 ሊባሉ ይገባቸዋል ተብለው የታሰቡ ነገሮች ብቻ ተዘርዝረዋል፡፡ ይህም የተደረገው
ከእግዚአብሔር ቃል ወይም የሁሉ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ የሆነ ትምህርትም
ሆነ ሥርዓት በእኛ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ነው፡፡ ምክንያቱም ዐዲስ
የሆነ ወይም መንፈሳዊነት የጐደለው ምንም ዓይነት መሠረተ እምነት በአብያተ
ክርስቲያናችን ሠርጎ እንዳይገባ በከፍተኛ ትጋት የተጠነቀቅን መሆናችን የተገለጠ ስለ ሆነ
ነው፡፡
6 በግርማዊነትዎ ትእዛዝ መሠረት እላይ የተጠቀሱትን አንቀጾች ለማቅረብ ፈልገናል፡፡
እነርሱም የእኛን የእምነት መግለጫ የሚያሳዩና የአስተማሪዎቻችንን መመሪያ ማጠቃለያ
7 የያዙ ናቸው፡፡ በዚህ የእምነት መግለጫ አንዳች የጐደለ ነገር ቢገኝ እግዚአብሔር ከፈቀደ
በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ከዚህ የበለጠ መረጃ ለማቅረብ ዝግጁዎች ነን፡፡

የግርማዊነትዎ ታማኞችና ትሑታን [ተገዥዎች]
ጆን፣ የሳክሶን መስፍን የንጉሠ ነገሥት መራጭ
ጆርጅ፣ የብራንደንበርግ [አንስባህ] ጦር መሪ
ኧርነስት፤ የኑረምበርግ መስፍን
ፊሊፕ የሄሴ አገረ ገዥ
ጆን ፍሬዴሪክ፣ የሳክሶን መስፍን
ፍራንሲስ፣ የሉኔበርግ መስፍን
ዎልፍጋንግ የአንሃልት መስፍን
የኑረንበርግ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልና ከንቲባ
የሬውትሊንገን ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል

# ትንሹ የክርስትና ትምህርት

## ለትንሹ የክርስትና ትምህርት የአርታዒያን መግቢያ

የሉተር ትንሹ የክርስትና ትምህርት መሠረት ከጥንት የቤተ ክርስቲያን ዘመን ይጀምራል። *ካቴኮ* katecho የሚለው የግሪኩ ቃል እንደ ገና ማስተጋባት ወይም ከላይ በሚል ዐሳብ የክርስትና ትምህርትን ለማመልከት አስቀድሞ በጳውሎስ ጥቅም ላይ ውሎአል (ገላ 6፡6)። በሁለተኛው ክፍለ ዘመን፣ የቅድመ ጥምቀት የክርስትና ተማሪዎችን መመሪያ የሚያሳይ ሆኖአል። አውግስጢኖስ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትን ለማመልከት መጀመሪያ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ የሆነውን የላቲን ብቸኛ ቃል፣ በመዋስ *ካቴኪስመስ* catechismus የሚለውን ስም ተጠቀመ። በመካከለኞቹ ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት ብዙ ጊዜ ወደ ዐሠርቱ ትእዛዛት፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ፣ እንዲሁም የጌታ ጸሎት አጠቃላዋለች። ሉተር በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ቃሉን በዚህ መንገድ ተጠቅሞአል። በመካከለኞቹ ዘመናት መጨረሻ ለክርስትና ትምህርት ማስተማሪያ የተጻፉ ትናንሽ መጻሕፍት በምሥጢረ ንስሐ፣ ቅዱስ ምሥጢር፦ የእምነትና የጸጸት ዝግጅት ሥራዎች፣ የኑዛዜ ምሉእነት፣ ተተኪ የኃጢአት ዕዳ ክፍያ ሥራዎች (በተለይም ጸሎት፣ ጾም፣ ምጽዋት መስጠት)፣ በመጨረሻም ለጥሩ አሟሟት መዘጋጀት ላይ አተኩረዋል።

ሉተር አስቀድሞ ከቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በፊት በዊተንበርግ በምትገኘው የቅድስት ማርያም የከተማ ቤተ ክርስቲያን በሰባኪነት ተግባር በነበረው ድርሻ በክርስትና ትምህርቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ላይ ስብከቶችን አቅርቦአል።[1] መጀመሪያ በ1522 ለብቻ ታትመው፣ በግል የጸሎት መጽሐፉ በመድበልነት ታተሙ።[2] ምንም እንኳ ይህ ትንሽ መጽሐፍ በራሱ የክርስትና ትምህርት ባይሆንም፣ ሉተር ለ1526ቱ ቅዳሴው፣ ለጀርመንኛው ቅዳሴ በጻፈው መቅድም ትናንሽ የትምህርት መጻሕፍት እንዲጽፉ አብረውት ለሚሠሩ ቀሳውስትና ሰባኪያን ልመና አቅርቦአል ለሥራቸው እንደ መነሻ ነጥብም የግል የጸሎት መጽሐፉን እንዲጠቀሙ አሳስቦአቸዋል።[3] በብዙ የመካከለኛው ዘመን የክርስትና ትምህርቶች ከሚገኘው ቅደም ተከተል የተለየው፣ ይህ አነስተኛ የጸሎት መጽሐፍ ትእዛዛቱን በማብራራት ጀምሮ ከዚያም በመጀመሪያ ወደ እምነት ክፍሉ በመጨረሻም ወደ ጸሎት ተሻግሮአል።[4]

አስቀድሞ በ1525 እርዳታ ፈልጎ ለሉተርና ለሳክሶኑ ፍርድ ቤት አቤቱታ ባቀረበው በዝዊካኢው ቄስ በኒኮላስ ሐውስማን Zwickau Nicholas Hasumann መሪነት ለመሠረታዊ የክርስትና ትምህርት የሚሆኑ መርጃዎች እንዲያዘጋጁ በዊተንበርግ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ላይ የነበረው ጫና እየጨመረ ነበር። በዊተንበርግ የነበረው የመጀመሪያው ቡድን በውጥኑ ላይ ለመሥራት በዊተንበርግ በተሰበሰበ ጊዜ፣ አግሪኮላ ወደ አይስሌበን በመንቀሳቀሱ ምክንያት ዮሐንስ አግሪኮላና ጁስተስ ዮናስ ከፍጻሜ ላይ ሊያደርሱት አልቻሉም፣ ሉተር ራሱ በውጥኑ ላይ ለመሥራት ቃል ገባ። ሉተር የገባውን ቃል ወዲያውኑ ባልፈጸመ ጊዜ፣ ውጥኑን ሌሎች ሠሩት። ምናልባት (በኋላ በዝዊካኡ የከተማ ጸሐፊ በሆነው) በእስጢፋኖስ ሮት የተዘጋጀ ከሉተር የግል የጸሎት መጽሐፍም ምንባቦችን የያዘ ይህን የመሰለ አንድ የታተመ መጽሐፍ በ1525 መጨረሻ ላይ ታትሞአል።[5] መግቢያው ሦስት የቈዩ የክርስትና ትምህርቱ ክፍሎችን፣ ነገር ግን ደግሞ ለቅዱስ

---

1 በዚህ ቅጽ የትልቁን የክርስትና ትምህርት መግቢያ ተመልከት።

2 WA 10/2: 375-406; LW 43:5-45.

3 WA 19:77, 12; LW 53:66.

4 ለሉተር የዚህ መዋቅር ማብራሪያ WA 10/2: 376, 12-377, 13 (LW 43:13-14) ተመልከት።

5 የምእመናንና የልጆች አነስተኛ መጽሐፍን ተመልከት።

ጥምቀትና ለጌታ እራት የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የያዘ ያልቀሰሱ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ የሚጠራውን አካትቶአል፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አምስቱ «ዋና ዋና ክፍሎች» በሙሉ በአንድ ላይ ታትመዋል። በአይስሌበን ያለው የላቲን ትምህርት ቤት ኀላፊ፣ ዮሐንስ አግሪኮላን ጨምሮ ሌሎች ሰባኪያንና አስተማሪዎች በዛም አነስ የዊተንበርግ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮን ያንጸባረቁ የክርስትና ትምህርቶችን ደግሞ አዘጋጁ።[6]

በ1528 የብራውንሽዌግ Braunschweig ከተማን በማሻሻል ሊረዳ ከሄደው ከዊተንበርግ ዋና ቄስ ከዮሐንስ ቡገንሃገን ጋር ሉተር እንደ ገና የክርስትና ትምህርቱን መስበክን ተረከበ። ከረጅም ማብራሪያዎች በተጨማሪ በእነዚህ ስብከቶች ብዙውን ጊዜ የአንድ የተለየ የክርስትና ትምህርቱ ክፍል ትርጉምን ወደ አንድ አረፍተ ነገር ለመቀነስ ሞክሮአል። አጠ ያያቂ በሆኑት በሌሎች የክርስትና ትምህርቶች ሥነ መለኮትና የማስተማር ዘዴ ጥናት ተበረታትቶና በሳክሶኒ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ባደረገው ይፋ ጉብኝት አጭር ልምምዱ ተነሣሥቶ፣ በ1528 መጨረሻ ወይም በ1529 መጀመሪያ ትንሹን የክርስትና ትምህርት መጻፍ ጀመረ። እያንዳንዳቸው በቤተ ሰብ ኀላፊዎች አድራሻ የተጻፉ፣ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ክፍሎች በተለዩ ሰፋፊ ወረቀቶች ላይ በጥር 1529 ታትመው ነበር። ከበድ ያለ ሕመም እንቅስቃሴዎቹን ከቀነሰበት በኋላ፣ ከቅዱሳት ምሥጢራቱ ማብራሪያዎችና ለቤተ ሰብ ጸሎቶች በሚሆኑ አጫጭር ቅደም ተከተሎች ጋር ውጥኑን በፀደይ ወራት ላይ ከፍጻሜ አደረሰው።

ሉተር ለዊተንበርጉ አትም ለተራ ቀሳውስትና ሰባኪያን አድራሻ የተጻፈ መቅድም አቀረበና እነዚህ የመጀመሪያ ሰፋፊ ወረቀቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ በትንሽ መጽሐፍ መልክ ደግሞ ታተሙ። በዊተንበርግ ያሉ ተከታታይ ኅትመቶች ሁሉ ከእንጨት በተፈለፈሉ ሥዕሎችና በመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች የተገለጹ ሁለት ተጨማሪ ጽሑፎችን፡- የጋብቻው ጀርመንኛ ትርጒምና የጥምቀት አገልግሎት የሉተር መግቢያዎችን የያዙ ነበሩ። የተለያዩ የቤተ ሰብ ጸሎቶችንና ለቤተ ሰብ የሚሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሠንጠረዥ (አንዳንድ ጊዜ «የግዴታዎች ሠንጠረዥ» ተብሎ የሚጠራውን) ደግሞ አካትተዋል። በ1531 ሉተር በአራተኛው የቅዱስ ጥምቀት ጥያቄ ላይ ለግል ኑዛዜ ከሚሆን ቅደም ተከተል ጋር አጭር የኃጢአት ኑዛዜ ወይም ውይይት በማያያዝና ለጌታ ጸሎት መግቢያ ማብራሪያ በመጨመር ትንሹን የክርስትና ትምህርት በመጠኑ አሻሻለ።

የሉተር ትንሹ የክርስትና ትምህርት *Was ist das?* ዋስ ኢስት ዳስ? (ይህ ምንድን ነው?) የሚል ቀላል ጥያቄ ያነሣል፣ እንዲሁም ሌሎች ጥያቄዎችን አልፎ አልፎ ብቻ ያነሣል (ይህ እንዴት ይሆናል? ይህ ምን ማለት ነው? ይህ ምንን ያመለክታል?) ያ ጥያቄ ያስከተለው ቀላሉ የክርስትና ትምህርት ጽሑፎች ማብራሪያ ከሕግ (ዐሠርቱ ትእዛዛት) ወደ ወንጌል (የእምነት ክፍልና የጌታ ጸሎት) ባለው የመሸጋገር ጽናት እንዲሁም የቅዱስ ጥምቀትና የጌታ እራት ማብራሪያዎችን ለማካተት በቁዩ የክርስትና ትምህርቶች የሚገኝ ጽሑፍን በማስፋፋት የተመጣጠነ ነው። ለማዕድ ጊዜያትና ለጥዋት፣ እንዲሁም ለመኝታ ጊዜ የሚሆኑ ጸሎቶች ከቈዩ ምንጮች የተገኙ ናቸው። ለቤተ ሰብ የሚሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ዝርዝር በዕለት ተዕለት ኑሮ ያሉ ግንኙነቶች፣ በራስ ምርጫ የሚሆን አንዳንድ መንፈሳዊነትን ሳይሆን የክርስትናን ሕይወት ይይዛሉ የሚለውን የሉተርን እምነት ያንጸባርቃል።

በ1580 በድሬድሰን በተዘጋጀው በመጽሐፈ ስምምነት፣ ትንሹ የክርስትና ትምህርት እላይ የተገለጹትን ክፍሎች ሁሉ አካትቶአል። ይሁን እንጂ፣ የጠላቲኔቱ ሉድዊግ ስድስተኛን ጨምሮ አያሌ መሳፍንት፣ እንዲሁም የሥነ መለኮት ዐዋቂዎቻቸው የሉተርን

[6] የዮሐንስ አግሪኮላን One Hundred Thirty Questions for the Girl's School in Eisleben ተመልከት። አግሪኮላ በክርስትና ትምህርቱ ያለውን የሕግንና የወንጌልን ቅደም ተከተል ተወና በራሱ «ፀረ ሕግ» ሥነ መለኮትን ማጒልበት መሠረት ሕጉን አሳነሰ።

የጥምቀት አገልግሎት አጋንንትን ከማስወጣት ማጣቀሻዎቹ ጋር ተቃውመውታል፡፡ ከዚህ የተነሣ፣ ምንም እንኳ ከያዕቆብ አንድሬአ ልመናዎች ቢቀርቡም፣ ሁለቱ ተጨማሪ ጽሑፎች በሌላ ቦታ በአንድ ጊዜ ከተዘጋጁ እትሞችና በድሬድሰደን ከታተሙ ተከታታይ ቅጂዎች ተወግደዋል፡፡ ይህ ቈርጦ ማውጣት በሉተራውያን መካከል በጥምቀት ባሕርይ ላይ የተደረገ ረጅም ክርክር ክፍል ነበር፣ በተለይም ሉተራውያን ያለ እምነት ድርጊቱን በመፈጸም ብቻ ጥምቀትን እንደ ውጤታማ ይረዱታል በማለት በአንዳንድ ተሐድሶአውያን የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ተጽዕኖ ሥር በነበሩት የተመሩ እነዚያ ስጋት አደረባቸው፡፡ እዚህ የተካተቱት ሁለቱ ተጨማሪ ጽሑፎች እንዲሁም ሉተር በሕይወት በነበረ ጊዜ በአብዛኛው በዊተንበርግ ከተዘጋጀ ከእያንዳንዱ እትም ጋር አብረው የሄዱ የመጀመሪያዎቹ ሥዕላዊ መግለጫዎች ቀለል ያሉ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

## መመሪያ መጽሐፍ[1]
## [የዶክተር ማርቲን ሉተር]
## ትንሹ የክርስትና ትምህርት
## ለተራ ቀሳውስትና ሰባኪያን[2]

## [የዶክተር ማርቲን ሉተር መቅድም]

*ማርቲን ሉተር፣[3]*
*ታማኞችና ልበ ቅኖች ለሆኑ ቀሳውስትና ሰባኪያን ሁሉ።*
*በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረት፣ እና ሰላም ይሁን።[4]*

1 ጉብኝት ላይ በነበርኩበት ጊዜ[5] በቅርቡ ያጋጠመኝ አሳዛኝና እጅግ መጥፎ ክልከላ
ይህንን የክርስትና ትምህርት፣ ወይም የክርስትና መግሪያ[6] እንዲህ ባለ አጭር፣ ግልጽና
2 እንዲሁም ቀለል ባለ መልክ እንዳዘጋጅ አሳምኖኛል አስገድዶኛልም። ውድ አምላኬ፣ ምን
ጉስቀሉልና ነው ያየሁት! በተለይም በመንደሮቹ ያለው፣ ተራው ሰው ስለ ክርስትና እምነት
ፈጽሞ ምንም ዐያውቅም፣ እንዲሁም በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ቀሳውስት ፈጽሞ ያልሠለጠ
3 ኑና ብቃት የሌላቸው አስተማሪዎች ናቸው። ሆኖም ግን ለምናልባቱ ምንም እንኳ የጌታን
ጸሎት፣ የእምነት መግለጫዎችን፣ ወይም ዐሠርቱን ትእዛዛት ባያውቁም ሁላቸውም
ክርስቲያን የሚለውን ስም ይዘዋል፣ ተጠምቀዋል፣ ቅዱስ ቊርባንም ይቀበላሉ![7] ከዚህ
የተነሣ፣ እንደ ተራ ከብት ወይም ማሰብ እንደማይችሉ አሳማዎች ይኖራሉ ደግሞም
ወንጌል መመለሱ እውነት ቢሆንም እንኳ ነጻነታቸውን ሁሉ ያለ አግባብ የመጠቀምን ጥበብ
ጠንቅቀው ተክነውታል።
4 እናንተ ጳጳሳት ሆይ! በጣም በሚያሳፍር ሁኔታ ሕዝቡን ችላ ብላችኋልና ለአንድ
ሰከንድም እንኳ የአገልግሎት ድርሻችሁን አልተገበራችሁምና፤ ለክርስቶስ እንዴት መልስ
5 ትሰጡታላችሁ? በዚህስ ከቅጣት ታመልጣላችሁን! ሕዝቡ የጌታን ጸሎት፣ የእምነትን
ክፍል፣ ዐሠርቱን ትእዛዛት፣ ወይም አንድን የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ያወቀ እንደ ሆነ
ለመጠየቅ ከቶ ሳትጨነቁ እንኳ በጌታ እራት ጽዋውን [ለምእመናን] ትከለክሉና የራሳችሁን
ሰብአዊ ሕግጋት በመጠበቅ ትጸናላችሁ። ለዘላለም ልታፍሩ ይገባል![8]
6 ስለዚህ፣ ቀሳውስት ወይም ሰባኪያን የሆናችሁ ውድ ጌቶቼና ወንድሞቼ፣
አገልግሎታችሁን በድፍረት እንድታነሡ፣ አደራ ለተሰጡአችሁ ሕዝባችሁ እንድታዝኑ፣
እንዲሁም የክርስትና ትምህርትን ለሕዝቡ፣ በተለይም ለወጣቶች እንድናመጣ እንድትረዱን
ስለ እግዚአብሔር ብዬ ሁላችሁንም እለምናችኋለሁ። በተጨማሪ፣ ምንም የተሻለ ሊያደርጉ

[1] Enchiridion.
[2] ሉተር ለሁለቱም ዓይነት የጀርመን ቀሳውስት ገልጾአል፦ የመጋቢነት እንክብካቤና በማኅበራኑ ምእመናን የሚካሄድ አምልኮ ዋና ኀላፊነት የተሸከሙ ቀሳውስት (Pfarrherr)፣ እንዲሁም ሰባኪያን (Prediger)።
[3] ይህ መቅድም ሰፋ ባሉት ወረቀቶች ከታተሙት ከመጀመሪያዎቹ ጽሑፎች በስተቀር በሁሉም የክርስትና ትምህርቱ እትሞች ይገኛል።
[4] 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡2 እና 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡2 አነጻጽር።
[5] ሉተር ምርጫ ይደረግባት በነበረችው ሳክሶኒና ሜይሰን ከጥቅምት 22 ቀን 1528 እስከ ጥር 9 ቀን 1529 ይፋ ጉብኝቶች አድርጎአል። ገጠመኞቹ ኅዳር 11 ቀን 1528 ለኒኮላስ ቮን አምስዶርፍ በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾአል (WABr 4:597; LW 49:213-14).
[6] LC, "Short Preface" 1-2 ተመልከት።
[7] በሉተር ዘመን «የክርስትና ትምህርት» የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ በመካከለኛው ዘመን መጨረሻው የሚገኙትን መምሪያዎች እዚህ ላይ በቅደም ተከተል የተጠቀሱትን እነዚህን ሦስት ክፍሎች አመልክቶአል።
[8] በ the Instruction of Visitors (1528) (WA 26195, 4-201, 7; LW 40:269-73) የሉተር ጳጳሳቱን መተቸት አነጻጽር።

ያልቻሉ እነዚህን ሠንጠረዦችና እትሞች[9] እንዲያነሡና በሚከተለው አኳኋን ለሕዝቡ ቃል
በቃል እንዲያነብቡአቸው እጠይቃለሁ፦
7 *በመጀመሪያ ደረጃ፣* ሰባኪው ከሁሉም በላይ በጽሑፉና በዐሠርቱ ትእዛዛት፣ በጌታ
ጸሎት፣ በእምነት ክፍል፣ በቅዱሳት ምሥጢራት፣ ወዘተ. እትም ያሉትን ለውጦችና
ልዩነቶች ለማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ አንድን እትም
መቀበል፣ በእርሱ መጽናት፣ እንዲሁም መቀበል፣ እንዲሁም ሁልጊዜ ያንኑ ከዓመት ወደ
ዓመት መጠቀም አለበት። ምክንያቱም ወጣቶችና ያልተማሩ ሰዎች አንድ፣ የተወሰነ
ጽሑፍና እትም መማር አለባቸው። አለበለዚያ፣ አንድ ሰው አሁን በአንድ መንገድ፣
በሚቀጥለው ዓመት በሌላ መንገድ ቢያስተምር፦ ለመሻሻል ቢባልም እንኳ፦ ሕዝቡ በጣም
በቀላሉ ግራ ይጋባሉ፣ እንዲሁም ጊዜውና የተደረገው ጥረት ሁሉ ከንቱ ይሆናል።
8 የተወደዱት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ደግሞ ይህንን በሚገባ ተረድተዋል። ለጌታ
ጸሎት፣ ለእምነት መግለጫ፣ እንዲሁም ለዐሠርቱ ትእዛዛት አንድ መንገድ ተጠቅመዋል።
ስለዚህ፣ እኛ ደግሞ የአንዱንም ክፍለ ቃል ሳንለውጥ ወይም ከአንድ ዓመት ወደ ቀጣዩ
ዓመት በተለየ መንገድ ሳናቀርብና ሳንደግም እነዚህን ክፍሎች ለወጣቶችና ማንበብ
9 ለማይችሉ ሰዎች ማስተማር አለብን። ስለዚህ፣ እስከ ወዲያኛው በየትኛው እትም መጽናት
እንደምትፈልግ ለራስህ ምረጥ። እርግጠኛ ለመሆን፣ ለተማሩና ለዐዋቂ ሰዎች
በምትሰብክበት ጊዜ፣ ያኔ ዕውቀትህን ልታሳይና እነዚህን ክፍሎች በብዙ ውስብስብነትና
በተቻለህ መጠን በብዙ ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ልትወያይባቸው ትችላለህ። ወጣቶችን
10 በሚመለከት ግን፣ በተወሰነ፣ በማይለወጥ እትምና መንገድ ጽና። ለመጀመር ያህል፣
እነዚህን ክፍሎች፦ ለአንተ ደግሞ እንዲደግሙልህና በቃል እንዲያጠኑት ጽሑፉን ቃል
በቃል በመከተል ዐሠርቱ ትእዛዛትን፣ የእምነት ክፍልንና የጌታ ጸሎትን፣ ወዘተ.
አስተምራቸው።
11 እነዚህን ነገሮች ለመማር የማይፈልጉ፣ ክርስቶስን እንዴት እንደሚክዱና
ክርስቲያኖች እንዳልሆኑ ሊነገራቸው የሚገባ ወደ ቅዱስ ቊርባን ደግሞ ሊቀርቡ አይገባም፣
በጥምቀት ሕፃናትን አቅራቢዎች መሆን የለባቸውም፣ ማንኛውንም ዓይነት የክርስቲያናዊ
ነጻነት መለማመድ የለባቸውም፣[10] ነገር ግን በዚህ ፈንታ በቀላሉ ወደ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና
ባለ ሥልጣናቱ፣[11] ከእነርሱ ጋርም ወደ ዲያብሎስ ወደ ራሱ ተመልሰው መላክ አለባቸው።
12 በተጨማሪ ወላጆቻቸውና አሠሪዎቻቸው ምግብና መጠጥ ሊከለክሉአቸውና እንዲህ የመሰሉ
ልበ ደንዳና ሰዎችን ከአገሪቱ እንዲያባርር የመስፍኑ ዐሳብ መሆኑ ሊነግሩአቸው ይገባል።
13 ምንም እንኳ እንዲያምን[12] ማንንም ሌላን ሰው ማስገደድ ባይችል ወይም ባይገባውም፣
የሆነ ሆኖ አብረዋቸው ለመኖር፣ ለመብላት፣ እንዲሁም ኑሮን ለመግፋት በሚፈልጉአቸው
መካከል ትክክልና ስሕተት የሆነውን እንዳወቀ አንድ ሰው መጽናትና ብዙኀኑን በዚህ
መያዝ አለበት።[13] ለምሳሌ፣ ሰዎች በአንዲት በተለየች ከተማ ለመኖር ቢፈልጉ፣ የሚያምኑ
ወይም ወሮበሎችና ተንኰለኞች ቢሆኑ ጥበቃ የሚያገኙባትን ከተማ ሕግ ማወቅና በእርሱም
መኖር ይገባቸዋል።
14 *በሁለተኛ ደረጃ፣* ሕዝቡ አንድ ጊዜ ጥቅሱን በሚገባ ከተማሩት፣ ያኔ ምን ማለት
እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ፣ እንዲገባቸው ደግሞ አስተምራቸው። እንደ ገና በእነዚህ ሠንጠ
ረዦች የቀረበውን መንገድ ወይም ይሻላል የምትለውን ሌላ አጭር መንገድ ተጠቀም።
15 ከዚያም ልክ እላይ ጽሑፉን በሚመለከት እንደ ተገለጸው፣ አንድም ክፍለ ቃል ሳትለውጥ

[9] ቃል በቃል፣ ገበታዎች (Tafeln) እና ቅጾች (Forme)። Tafel የሚለው ቃል ማውጫዎቻቸው መጀመሪያ ሰፋ ባሉ ወረቀቶች ታትመው የነበሩትን አነስተኛ ጽሑፎች ያመለክታል።

[10] LC, "Short Preface," 1-5 ደግሞ ተመልከት።

[11] አስተዳደራዊ፣ ሥነ ሥርዓታዊና የጋብቻ ጒዳዮችን የወሰኑ የሀገረ ስብከት ዳኞች።

[12] መጋቢት 17 ቀን 1522 ለኒኮላስ ሐውስማን የተጻፈ ደብዳቤ (WABr 2:474-75; LW 48:399-402); ለጐብኚዎቹ የሚሆን መመሪያ መቅድም (1528) (WA 26:200, 21-201, 7; LW 40:273); እንዲሁም በታኅሣሥ 1528 ለክርስትና ትምህርት ስብከቶች የሉተር ማስታወቂያ (WA 30/1:157, 14-28; LW 51:136).

[13] ነሐሴ 26 ቀን 1529 ለቶማስ ሎሽከር የተጻፈ ደብዳቤ (WABr 5:137; LW 49:232-34) እንዲሁም LC "Short Preface," 2.

16 ተከተለው:: በተጨማሪም፣ ክፍሎቹን ሁሉ በአንድ ጊዜ ማንሣት ስለማያስፈልግህ ነገር ግን
በዚህ ፈንታ አንድ በአንድ እንድታከናውናቸው በቂ ጊዜ ይኑርህ:: ሕዝቡ የመጀመሪያውን
ትእዛዝ በሚገባ ከተረዱ በኋላ፣ ሁለተኛውን፣ ከዚያም ቀጥሎ ያለውን አንሣ:: አለበለዚያ
በጣም ይበዛባቸውና አንድም ነገር ማስታወስ ሳይችሉ ይቀራሉ::
17 *በሦስተኛ ደረጃ፣* እንደዚህ ያለውን አጭር የክርስትና ትምህርት ለሕዝቡ ካስተማርህ
በኋላ፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ረዘም ያለውን የክርስትና ትምህርት[14] አንሣና
በጣም የበለጸገና የተሟላ ግንዛቤ አስተላልፍላቸው:: እንዲህ ያለውን የክርስትና ትምህርት
በመጠቀም በጣም ብዙ በሆኑ ትናንሽ መጻሕፍት በስፋት ተተንትኖ እንደምታገኘው፣
በተናጠል እያንዳንዱን ትእዛዝ፣ ጸሎት፣ ወይም ክፍል ከተለያዩ ሥራዎቹ፣ ጥቅሞቹ፣
18 እንዲሁም በረከቶቹ፣ ጉዳትና አደጋ ጋር አብራራ:: በተለይ፣ ሰዎችህ ከሁሉ የላቀ ፍላጎት
በሚለማመዱበት በዚያ ትእዛዝ ወይም ክፍል ላይ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ትኩረት አድርግ::
ለምሳሌ፣ ለዕደ ጥበብ ባለሙያዎችና ለባለ ሱቆች እንዲሁም ለገበሬዎችና ለቤት ሠራተኞች
እንኳ ስለ ስርቆት የሚናገረውን ሰባተኛውን ትእዛዝ በጽናት አጉላው፣ ምክንያቱም እንዲህ
ባሉ ሰዎች መካከል ሁሉም ዓይነት እምነት ማጉደልና ሌብነት ከቁጥጥር ውጪ በሆነ
ሁኔታ በብዛት ይገኛሉ::[15] በተመሳሳይ መልኩ፣ ሥርዓት ያላቸው፣ ታማኞች፣ ታዛዦች፣
እንዲሁም ሰላማዊ[16] ይሆኑ ዘንድ አራተኛውን ትእዛዝ ለልጆችና ለአብዛኛው ሰዎች ማጉላት
አለብህ:: እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ ሰዎችን የቀጣባቸው ወይም የባረከባቸው ብዙ
ምሳሌዎችን ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል አቅርብ::
19 በተለይ በዚህ ስፍራ[17] የሚያስተዳድሩ ባለ ሥልጣናትንና ወላጆችን ደግሞ በሚገባ
እንዲያስተዳድሩና ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ አደፋፍር:: እንዲህ
እንዲያደርጉ እንዴት እንደሚገደዱና ባያደርጉ ምን ዓይነት ሰይጣናዊ ኃጢአት እየፈጸሙ
እንደሆነ አመልክት፣ በዚያም ምክንያት ከሁሉ በጣም የከፉ የእግዚአብሔርና የሰው ልጅ
ጠላቶች ሆነው ሁለቱንም የእግዚአብሔር መንግሥትንና የዓለምን መንግሥት
20 እንደሚገለብጡና እንደሚጥሉ ይገንዘቡ:: ልጆችን እንደ ቀሳውስት፣ ሰባኪያን፣ የመንግሥት
ሠራተኞች፣[18] ወዘተ.፣ ለማሠልጠን እገዛ በማያደርጉበት ጊዜ ምን ዓይነት አስከፊ ጉዳት
እንደሚያደርሱ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ አብራራ፣ እንዲሁም ስለዚህ እግዚአብሔር
አሰቃቂ በሆነ መንገድ እንደሚቀጣቸው ንገራቸው:: ምክንያቱም በእኛ ጊዜና ዘመን ስለ
እነዚህ ነገሮች መስበክ አስፈላጊ ነው:: ወላጆችና የሚያስተዳድሩ ባለ ሥልጣናት በእነዚህ
ጉዳዮች አሁን ኃጢአት እየሠሩ የሚገኙበት መጠን ሙሉ ገለጻን በግልጽ ይቃወማል::
ዲያብሎስ ደግሞ፣ በዚህ ሁሉ፣ አስከፊ ነገር ለማድረግ ያቅዳል::[19]
21 በመጨረሻ፣[20] የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አምባገነናዊነት በመወገዱ ምክንያት፣
ከእንግዲህ ሰዎች ቅዱስ ምሥጢሩን ለመቀበል አይፈልጉም፣ ደግሞም ይህንን በንቀት
ይመለከቱታል:: ቅዱስ ምሥጢሩን እንዲያምን ወይም እንዲቀበል ማንንም ማስገደድ
እንደሌለብንና ምንም ሕግ ወይም ጊዜ ወይም ስፍራ መወሰን እንደማይገባን በማስታወስ
22 ይህን ደግሞ በተደጋጋሚ ልናተኩርበት ያስፈልጋል:: በዚህ ፈንታ፣ ሰዎቹ ያለ እኛ ሕግ
እንዲመጡና በቀሳውስትነታችን ቅዱስ ምሥጢሩን እንድናከናውንላቸው ዝም ብለው

---

[14] በሉተር ዐሳብ የነበረው ሌሎች ትልቁ የክርስትና ትምህርት ብለው የጠሩት የራሱ Deutsch Katechismus ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን ሌሎች የክርስትና ትምህርት መጻሕፍት ደግሞ ነበሩት::

[15] LC, "Ten Commandments," 225-26 ተመልከት::

[16] LC, "Ten Commandments," 105-66 ተመልከት::

[17] ይህ አንቀጽ የሉተርን የአራተኛው ትእዛዝ ማብራሪያ ይቀጥላል:: LC, "Ten Commandments," 167-78, እንዲሁም Treatise on Good Works (1520) (WA 6:253, 32-258, 13; LW 44:85-100) ተመልከት::

[18] Schreiber: ቃል በቃል ለሰነድ ሕጋዊ ማረጋገጫ የሚሰጡ የመንግሥት ሹማምንት ወይም ጸሐፊዎች::

[19] LC, "Ten Commandments," 174-77; To the Councilmen of All Cities in Germany That They Establish and maintain Christian Schools (1524) (WA 15:27-53; LW 45:339-78); እንዲሁም A Sermon on Keeping Children in School (1530) (WA 30/2: 517-88; LW 46:207-58) ተመልከት::

[20] ይህ የእምነት ማጽኛ ተማሪዎችን በቃል የማስተማር አራተኛ ደረጃን ሳይሆን የክርስትና ትምህርቱ እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ የመጨረሻ ምሳሌን ያስተዋውቃል:: LC, "Lord's Supper," 39-87 ተመልከት::

ሊያስገድዱን በሚችሉበት መንገድ መስበክ አለብን። እጅግ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ
ያህል ቅዱስ ምሥጢሩን የማይፈልግ ወይም የማይቀበል ማንም ሰው ቢሆን ቅዱስ
ምሥጢሩን የሚንቅና ልክ ወንጌልን የማይሰማ ወይም የማያምን ክርስቲያን እንዳልሆነ ሁሉ
ክርስቲያን አለመሆኑን ማሰብ ይኖርባችኋል ብሎ ለእነርሱ በመናገር ይህ ሊከናወን
ይችላል። ምክንያቱም ክርስቶስ፣ «ይህን አስቀሩ፣» ወይም «ይህንን ናቁ» አላለም፣ ነገር ግን
በዚህ ፈንታ፣ «... በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ አድርጉት» [1ኛ ቆሮ 11፡25] ብሎአል። በእርግጥ
እንዲደረግ እንጂ በፍጹም እንዲቀር ወይም እንዲናቅ አይፈልግም። «አድርጉት» ይላል።
23 ቅዱስ ምሥጢሩን በከፍተኛ ክብር የማይዙ እነርሱ[21] ኃጢአት እንደሌለባቸው፤
ሥጋ፣ ዲያብሎስ፣ ዓለም፣ ሞት፣ አደጋዎች፣ ሲኦል እንደሌሉ ያመለክታሉ። ያ ማለት፣
ምንም እንኳ በእነርሱ ቢዘፈቁና አንዴ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሁለት ጊዜ የዲያብሎስ
ቢሆኑም፣ ከእነዚህ ነገሮች አንዱም እንደሌለባቸው ያምናሉ። በሌላ በኩል፤ ጸጋ፣ ሕይወት፣
ገነት፣ መንግሥተ ሰማይ፣ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር፣ ወይም ሌላ ምንም ነገር
እንደማያስፈልጋቸው ያመለክታሉ። ምክንያቱም በጣም ብዙ ክፋት ያለባቸውና በጣም ብዙ
መልካም ነገር እንዳስፈለጋቸው ካመኑ፣ እንዲህ ያለ ክፋትን የሚቃወም እርዳታ
የሚቀርብበትንና በጣም ብዙ በጎ ነገር የሚሰጥበትን ቅዱስ ምሥጢር ቸል አይሉም። ቅዱስ
ምሥጢሩን እንዲቀበሉ በማንኛውም ሕግ ሊገደዱ አያስፈልግም። በዚህ ፈንታ ወደ እርሱ
እየተጣደፉና እየሮጡ ራሳቸው ይመጣሉ፤ ለመምጣት ራሳቸውን ያስገድዳሉ፣ እንዲሁም
ቅዱስ ምሥጢሩን እናንተ እንድትሰጡአቸው ይወተውታሉ።
24 በእነዚህ ምክንያቶች፣ እናንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንዳደረገው ምንም ሕግ
ማውጣት አያስፈልጋችሁም።[22] በዚህ ቅዱስ ምሥጢር ያለውን ጥቅምና ጉዳት፣ ፍላጎትና
በረከት፣ አደጋና ድነት ብቻ በግልጽ አጕሉ። ያኔ ያለ ምንም ጥርጣሬ እና ግዴታ
በራሳቸው ይመጣሉ። የማይመጡ ከሆነ፣ ተዉአቸውና ትኵረት የማይሰጡ ወይም ከፍ ያለ
ችግራቸውና የእግዚአብሔር ቸር እርዳታ የማይሰማቸው የዲያብሎስ መሆናቸውን
25 ንገሩአቸው። ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለ ተሳትፎ ካላደፋፈራችሁ ወይም ሕግ ወይም መርዝ
ካላደረጋችሁት፣ ያኔ ቅዱስ ምሥጢሩን ቢንቁ የእናንተ ጥፋት ነው። እናንተ ከተኛችሁና
ዝም ካላችሁ ከሚንቁት በቀር ምን ማድረግ ይችላሉ?
26 ስለዚህ፣ ቀሳውስትና ሰባኪያን ልብ በሉ! የአገልግሎት ኀላፊነታችን በርእሰ ሊቃነ
ጳጳሳቱ ሥር ከነበረበት ጊዜ ይልቅ አሁን ፍጹም የተለየ ሆኖአል። አሁን አስፈላጊና ጠቃሚ
ሆኖአል። ስለ ሆነም፣ አሁን ብዙ ድካምና ሥራ ብዙ አደጋዎችና ጥቃቶች[23] አሉበት፣
27 እንዲሁም በተጨማሪ በዐለም ትንሽ ሽልማት ወይም ምስጋና አለው። ነገር ግን በታማኝነት
እስከ ሠራን ድረስ፣ ክርስቶስ ራሱ ሽልማታችን ይሆናል። በክርስቶስ፣ በጌታችን ለዘላለም
ውዳሴና ምስጋና የሚገባው የጸጋ ሁሉ አባት እርሱን ይስጠን። አሜን።

---

[21] የጀርመንኛው ጽሑፍ የሦስተኛውን መደብ ነጠላ ቍጥር ይጠቀማል።
[22] በ1215 እያንዳንዱ ክርስቲያን በፋሲካና ለሥጋ ወደሙ ክብር በሚከበረው ከሥላሴ ቀጥሎ ባለው ሐሙስ መካከል የጌታን እራት መቀበል እንዳለበት አራተኛው የላተራን ጉባኤ ወስኖአል። Receiving Both Kinds in the Sacrament (1522) (WA 10/2: 24, 14-27; LW 36:249)ተመልከት።
[23] Anfechtung.

## ዐሠርቱ ትእዛዛት፦

### *የቤተ ሰብ ኀላፊ በቀላል መንገድ ለቤተ ሰቡ የሚያቀርባቸው*[24]

1 ### የመጀመሪያው[25] [ትእዛዝ][26]

ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።[27]

ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

2 ከሁሉም ነገሮች በላይ እግዚአብሔርን መፍራት፣ መውደድ፣ እንዲሁም ማመን አለብን።

3 ### ሁለተኛው[28] [ትእዛዝ]

የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ።[29]

4 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ፣[30] ስላለብን[31] እንዳንምል፣[32] ጥንቈላ/አስማት እንዳንለማመድ፣ እንዳንዋሽ፣ ወይም የእግዚአብሔርን ስም በመጠቀም እንዳናታልል፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ በችግር ጊዜ ሁሉ እንድንጠራው፣ ወደ እርሱ እንድንጸልይ፣ እንድንወድሰው፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ምስጋና እንድናቀርብ ይገባናል።

5 ### ሦስተኛው[33] [ትእዛዝ]

የሰንበትን ቀን ትቅድሰው ዘንድ ዐስብ።[34]

6 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ ስላለብን ስብከትን፣ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል እንዳንንቅ፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ያንን ቃል እንድንቀድስና በደስታ እንድንሰማው እንዲሁም እንድንማረው ነው።

---

[24] ለእያንዳንዱ የትንሹ የክርስትና ትምህርት የሚሆኑ አርእስት ከ1529ኙ ሰፋፊ ወረቀቶች የሚመነጩና በተከታታይ እትሞች የቀጠሉ ናቸው። የ1529 የላቲኑ ትርጒም የትምህርት ቤት መምህራንና ተማሪዎችን ያመለክታል።

[25] በሉተር የሕይወት ዘመን በትንሹ የክርስትና ትምህርት እትሞች እያንዳንዱ ትእዛዝ፣ የእምነት አንቀጽ፣ የጌታ ጸሎት ልመና፣ እንዲሁም ቅዱስ ምሥጢር ከእንጨት በተፈለፈለ ሥዕልና በመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች የታጀበ ነበር። በትንሹ የክርስትና ትምህርት ጥቅም ላይ ከዋሉት ጋር የሚመሳሰሉ የእንጨት ፍልፍል ሥዕሎች በትልቁ የክርስትና ትምህርት ዋነኛ እትሞች ተካትተዋል (WA 30/1:133-210). እዚህ ያለው ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፦ ሙሴ ዐሠርቱን ትእዛዛት ሲቀበልና እስራኤላውያን ከወርቅ በተሠራው ጥጃ ዙሪያ ሲጨፍሩ። (እዚህና ከ1536ቱ እትም ሙሉ ለሙሉ) የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፦ «ይህ ገላጭ ስዕል ከዘጸአት 32» የተወሰደ ነው።

[26] በ1529-35 እትሞች የጐደለው ይህ ቃል፣ በትንሹ የክርስትና ትምህርት ሌሎች እትሞች ሁሉና በ1580ው መጽሐፈ ስምምነት ይገኛል።

[27] ሉተር በተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ከዘጸአት 20ም ሆነ ወይም ከዘዳግም 5 ጽሑፎች ጋር ሁልጊዜ የማይመሳሰለውን የዐሠርቱ ትእዛዛት የተለመደ አጻጻፍ ሉተር ይጠቀማል። ከዚህ የተነሣ፣ የ1531ዱ እና የ1558ቱ የኑረምበርግ እትሞችን ጨምሮ አንዳንድ ኋለኛ እትሞች፣ እዚህና በሌላም ስፍራ ያለውን ጽሑፍ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጽሑፍ መሠረት ያርማሉ።

[28] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል የሰሎሚት ልጅ እግዚአብሔርን መስደብ። የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፦ «ይህ ገላጭ ሥዕል በዘሌዋውያን 24 [:10-16] ተመዝግቦአል።»

[29] የ1529-35 እትሞች «የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» የሚለው አላቸው። የ1531ዱ እና የ1558ቱ የኑረምበርግ እትሞች እንዲህ ይነበባሉ፦ «የጌታ አምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውም።»

[30] ለእነዚህ ግሦች አጠቃቀም፣ Instruction of the visitors (1528) (WA 26:203, 17-37; LW 40:276-77) እንዲሁም LC, (Ten Commandments," 321-27) ተመልከት።

[31] daB. በአጻጻፍ ሆነ («... ባለ ማድረግ ...») ወይም በሚያስከትለው ነገር («... በማናደርገው ውጤቱ ...») ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

[32] እዚህ ላይ Schweren በሐሰት መሐላዎች ስሜት ጥቅም ላይ ውሎአል። LC, "Ten Commandments," 66 ተመልከት።

[33] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፦ በፊት ለፊት ሰባኪ ከማኅበረ ምእምናን ጋር፤ መደቡ አንድ ሰው እንጨት ሲለቅም። የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፦ «ገላጭ ሥዕሉ ከዘኍልቁ 15[:32-36]» የተወሰደ ነው።

[34] Feiertag; ቃል በቃል፣ «የዕረፍት ቀን» (እንደ ዕብራይስጡ ቃል ሰንበት)፣ በአጠቃላይ ግን ለእሑድ።

7 ## አራተኛው[35] [ትእዛዝ]

አባትህንና እናትህን አክብር፡፡
8 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-
ወላጆቻችንንና በሥልጣን ላይ ያሉ ሌሎችን፣[36] እንዳንንቅ ወይም እንዳናስቈጣ፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ እንድናከብራቸው፣ እንድናገለግላቸው እንድንታዘዛቸው፣ እንዲሁም ተገቢ ክብር በመስጠት እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን ማለት ነው፡፡

9 ## አምስተኛው[37] [ትእዛዝ]

አትግደል፡፡
10 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-
የባልንጀሮቻችንን ሕይወት አደጋ ላይ እንዳንጥል ወይም እንዳንጐዳ፣[38] ነገር ግን በዚህ ፈንታ ለሕይወት በሚያስፈልጉአቸው ነገሮች ሁሉ እንድንረዳቸውና እንድንደግፋቸው፣ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን ማለት ነው፡፡

11 ## ስድስተኛው[39] [ትእዛዝ]

አታመንዝር፡፡
12 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-
በቃልና በሥራ ንጽሕና የጨዋነት ሕይወት እንድንመራ፣ እንዲሁም ከእኛ እያንዳንዱ የትዳር ጓደኛውን ወይም ጓደኛዋን እንዲወድድና እንዲያከብር፣ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን ማለት ነው፡፡

13 ## ሰባተኛው[40] [ትእዛዝ]

አትስረቅ፡፡
14 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-
የባልንጀራችንን ገንዘብ ወይም ንብረት እንዳንወስድ ወይም በማታለልና በማጭበርበር የራሳችን እንዳናደርጋቸው፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ንብረታቸውንና ገቢያቸውን ያሻሽሉና ይጠብቁ ዘንድ እንድናግዛቸው፣ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን ማለት ነው፡፡

15 ## ስምንተኛው[41] [ትእዛዝ]

በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡
16 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

---

[35] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፡- የኖኅ ሰካራምነት፡፡ የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፡- «ገላጭ ሥዕሉ ከዘፍጥረት 9[፡20-27] የተወሰደ ነው፡፡»

[36] Herrn; ቃል በቃል፣ «ጌቶች፣» ነገር ግን ብዙ ጊዜ በጀርመንኛ በሥልጣን ላይ ያሉትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎአል፣ ለምሳሌ፣ Landesherren (መሳፍንት) ወይም Pfarrherrm (ቀሳውስት) ፡፡

[37] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፡- ቃየን አቤልን ሲገድል፡፡ የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፡- «ገላጭ ሥዕሉ ከዘፍጥረት 4[፡1-16] የተወሰደ ነው፡፡»

[38] እዚህና በሚከተሉት ማብራሪያዎች፣ «ባልንጀራ» የሚለው ቃል በጀርመንኛው ነጠላ ቊጥር ነው፡፡

[39] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፡- ዳዊትና ቤርሳቤህ፡፡ የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፡- «ይህ ገላጭ ሥዕል በ2ኛ ሳሙኤል 11 ተመዝግቦአል፡፡»

[40] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፡- የአካን ሌብነት፡፡ የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፡- «ይህ ገላጭ ሥዕል በመጽሐፈ ኢያሱ 7 ተመዝግቦአል፡፡»

[41] ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፡- የሶስና ታሪክ፡፡ የሥዕል ሥር የጽሑፍ መግለጫ፡- «ገላጭ ሥዕሉ ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 13 የተወሰደ ነው፣ እንዲሁም ደግሞ በአዋልድ መጻሕፍት፣ ዳንኤልን በሚመለከተው ክፍል ይገኛል፡፡» በእርግጥ ምዕራፍ 13 የዳንኤል አዋልዳዊ ክፍል ነው፡፡

ስለ ባልንጀራችን ሐሰት እንዳንናገር፣ እንዳናማው ወይም ስሙን እንዳናጠፋ፣ ወይም ዝናውን እንዳናጐድፍ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን። በዚህ ፈንታ ልንከላከልለት፣ ስለ እርሱ መልካም ልንናገር፣ እንዲሁም የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር በተሻለ መልክ ልናብራራ ይገባናል ማለት ነው።

17 ## ዘጠነኛው[42] [ትእዛዝ]

የባልንጀራህን ቤት አትመኝ።

18 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

የባልንጀሮቻችንን ውርስ ወይም ንብረት ለማታለል እንዳንሞክር ወይም ሕጋዊ መብት አለን ብለን ልናገኘው እንዳንሞክር፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ የእነርሱ የሆነውን በመጠበቅ እንድናግዛቸውና እንድናገለግላቸው እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ አለብን ማለት ነው።

19 ## ዐሥረኛው[43] [ትእዛዝ]

የባልንጀራህን ሚስት፣ ወንድ ወይም ሴት ሠራተኛ፣ ከብት፣ ወይም የእርሱ የሆነ ማንኛውንም ነገር አትመኝ።

20 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን የባልንጀሮቻችንን የትዳር ጓደኞች፣[44] የቤት ሠራተኞች፣ ወይም ከብቶች ማባበል፣ ማስገደድ፣ ወይም መስረቅ ሳይሆን በዚህ ፈንታ እነርሱ ከባልንጀሮቻችን ጋር ጸንተው እንዲቆዩና ግዳጃቸውን እንዲፈጽሙ መገፋፋት ይኖርብናል።

21 ታዲያ እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ሁሉ ትእዛዛት ምን ይላል? መልስ፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ። በሚጠሉኝ ሰዎች ላይ ስለ አባቶች ኃጢአት እስከ ሦስትና እስከ እስከ አራት ትውልድ ድረስ በልጆቻቸው ላይ ቅጣትን የማመጣ ነኝ። ዳሩ ግን ለሚወዱኝና ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ መልካምን አደርጋለሁ»።[45]

22 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛት የሚጥሱትን ሁሉ እንደሚቀጣ ያስጠነቅቃል። ስለዚህ የእርሱን ቍጣ እንድንፈራና ትእዛዛቱን እንዳናፈርስ መጠንቀቅ አለብን። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛት ለሚጠብቁት ሁሉ ጸጋንና ማንኛውንም መልካም ነገር ለመስጠት ተስፋ ይሰጣል። በመሆኑም እኛም ደግሞ እርሱን መውደድና መታመን እንዲሁም በደስታ ትእዛዛቱን መፈጸም ይገባናል።

---

42 ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፦ ያዕቆብ ከላባ በጎች ጋር። የሥዕል ግርጌ የጽሑፍ መግለጫ፦ «ይህ ገላጭ ሥዕል ከዘፍጥረት 30[፡25-43] የተወሰደ ነው።»

43 ከእንጨት የተፈለፈለ ሥዕል፦ ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት። የሥዕል ግርጌ የጽሑፍ መግለጫ፦ «ይህ ገላጭ ሥዕል ከዘፍጥረት 39 የተወሰደ ነው።»

44 ቃል በቃል ትርጒም «ሚስቱን»።

45 ይህ ጽሑፍ ሉተር በተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተተረጐመው ዘጸአት 20፡5-6ን ወይም ዘዳግም 5፡9-10ን አይከተልም።

# የእምነት መግለጫው:-

## *ቀላል በሆነ መንገድ የቤተ ሰቡ መሪ ለቤተ ሰቡ የእምነት መግለጫውን የሚያቀርብበት ሁኔታ*

## 1 የመጀመሪያው[46] አንቀጽ:- ስለ አፈጣጠር

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድር በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፤

ይህ ምን ማለት ነው? መልስ:-

2 እግዚአብሔር አሁን ካለው ነገር ሁሉ ጋር አብሮ እንደ ፈጠረኝ አምናለሁ፤ እግዚአብሔር ሥጋና ነፍስን ሰጥቶኛል እንዲሁም እነርሱን ይጠብቃቸዋል:- ዓይን፣ ጆሮ፣ እጅና እግሮቼን ሁሉ፣ እንዲሁም ስሜቶችን፤ የማመዛዘን ችሎታንና የአእምሮ ክፍሎችን ሁሉ ሰጥቶኛል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ጫማና ልብስ፣ ምግብና መጠጥ፣ ቤትና እርሻ፣ የትዳር ጓደኛ[47] እንዲሁም ልጆች፣ የእህል ማሳንና ከብቶችን እንዲሁም ንብረቶችን ሁሉ ለዚህ ሥጋና ለሕይወት የሚያስፈልጉትን ነገሮችና ምግብን ሁሉ ጨምሮ አትረፍርፎ ይሰጣል።[48] እግዚአብሔር ከማንኛውም አደጋ ይጠብቀኛል፤ እንዲሁም ከክፉ ሁሉ ይጋርደኛል፣ ያድነኛልም። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ንጹሕ ከሆነ ከአባታዊና ከመለኮታዊ በጎነቱና ቸርነቱ የተነሣ እንጂ ፈጽሞ ከእኔ መልካም ሥራና የተገባ ከመሆን የተነሣ አይደለም። ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ማወደስና ለእርሱም መታዘዝ ይገባኛል።[49] ይህ ፍጹም እውነት ነው።[50]

## 3 ሁለተኛው[51] አንቀጽ:- ስለ መቤዡት

ደግሞም[52] በአንድ ልጁ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሲኦል በወረደ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፣ ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

4 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ:-

እውነተኛ አምላክ የሆነው፣ በዘለዓለማዊነት ከአብ የተወለደው፣ እንዲሁም ደግሞ እውነተኛ ሰው የሆነውና ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዬ መሆኑን አምናለሁ። እርሱም እኔን የጠፋሁትንና ኰነኔ የተፈረደብኝን ሰው ተቤዥቶኛል። በወርቅና በብር ሳይሆን ዳሩ ግን ቅዱስ፣ ክቡር በሆነው ደሙ እንዲሁም ያለ ኃጢአቱ[53] በተቀበለው መከራና በሞቱ ከኃጢአት፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ኃይል ገዝቶኝ ነጻ አውጥቶኛል። ይህን ሁሉ ያደረገው እኔ የእርሱ ገንዘብ እንድሆን፣ በመንግሥቱ ውስጥ በእርሱ ሥር እንድኖር፣

---

[46] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል:- እግዚአብሔር በእንስሳት ተከብቦ፣ እንዲሁም በደመናዎችና በአራቱ ነፋሳት ታጅቦ በረከት እንደሚሰጥ ጢማም ሰው ተገልጾአል።

[47] ቃል በቃል ትርጉም «ሚስት»። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ የለም።

[48] ብዙ ዘመናዊ አስተያየት ሰጭዎችና ተርጓሚዎች «ጫማ … ንብረት» የሚሉትን ቃላት ቀደም ሲል ካለው አረፍተ ነገር ጋር ያያይዙአቸዋል፣ ይሁን እንጂ፣ የ1529ኙ የላቲን ትርጉም፣ በመጀመሪያው ጽሑፍ ውስጥ «በተጨማሪ» (ዳዙ) (*Dazu*) የሚለው ቃል በትላልቅ ፊደላት መጻፉና በዚህ መግለጫ ውስጥ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር መጨረሻ ግሥ መቀመጡ ከሚቀጥለው ጋር የተካተተ መሆኑን የሚደግፍ ነው።

[49] *schÜldig*

[50] ሐረጉ ቲቶ 3፡8ን ለመተርጐም ጥቅም ላይ የዋለበትን በትንሹ የክርስትና ትምህርት «የጌታ ጸሎት» 21 እና «ቅዱስ ጥምቀት» 9 ተመልከት።

[51] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል:- ክርስቶስ በመስቀል ላይ፤ በደመናና በኪሩቤል የተከበበ። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ የለም።

[52] ጽሑፉ ከ1529ኙ ትንሹ የክርስትና ትምህርት ጋር የሚመሳሰል ነው።

[53] Un *schÜldingen:-* ቃል በቃል ትርጉም «ባለ ዕዳ ያልሆነ» ወይም «በደለኛ ያልሆነ» ማለት ነው።

እንዲሁም እርሱ ከሞት እንደ ተነሣና ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንደሚገዛ እኔም በዘለዓለማዊ ጽድቅ፣ ንጽሕናና[54] ብፅዕና እንዳገለግለው ነው። ይህ ፍጹም እውነት ነው።

5 ## ሦስተኛው[55] አንቀጽ፦ ቅዱስ ስለ መደረግ[56]

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን አንድነት፣[57] በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣ በዘለዓለም ሕይወት አምናለሁ።

6 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

በራሴ ዕውቀትና ብርታት በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን እንደማልችል፣ ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ያለችውን መላዋን ቤተ ክርስቲያን[58] እንደሚሰበስብ፣ እንደሚያበራላትና ቅዱስ እንደሚያደርጋት፣ እንዲሁም በአንዱ የጋራ በሆነው እውነተኛ እምነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አጽንቶ እንደሚጠብቃት ሁሉ እኔንም እርሱ በወንጌል አማካይነት እንደ ጠራኝ፣ በስጦታዎቹ እንደ አበራልኝ፣ ቅዱስ እንዳደረገኝና በእውነተኛው እምነት እንደ ጠበቀኝ አምናለሁ። መንፈስ ቅዱስ በዚህች ቤተ ክርስቲያን በየቀኑ የእኔንና የሁሉንም አማኞች ኃጢአት በሙላት ይቅር ይላል። በመጨረሻው ቀን መንፈስ ቅዱስ እኔንና የሞቱትን ሁሉ አስነሥቶ ለእኔና በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጣል ይህ ፍጹም እውነት ነው።

## የጌታ ጸሎት፦

### *ቀላል በሆነ መንገድ የቤተ ሰቡ መሪ ለቤተ ሰቡ<br>የጌታን ጸሎት የሚያቀርብበት ሁኔታ*

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ።[59]

1 *[60]ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦*

2 *በእነዚህ ቃሎች አማካይነት እግዚአብሔር፣ አፍቃሪ የሆኑ ልጆች አፍቃሪ የሆነውን አባታቸውን እንደሚጠይቁ ሁሉ እኛም እርሱን በድፍረትና በፍጹም ልበ ሙሉነት ልንጠይቀው እንችል ዘንድ[61] እርሱ እውነተኛ አባታችን መሆኑንና እኛም በእውነት የእርሱ ልጆች መሆናችንን እንድናምን ሊያደፋፍረን ይፈልጋል።*

3 ## የመጀመሪያው[62] ጸሎት[63]

ስምህ ይቀደስ[64]

---

[54] Un *schÜld* ፦ ቃል በቃል ትርጉም «ዋጋ የማይሰጥ» የሚል ነው።

[55] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፦ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከሚንበለበል የብርሃን አክሊልና ከሚገላበጥ ደመና ሥር በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉና የእሳት ልሳን ከአፋቸው ሲወጣ። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ የለም፣ የሐዋ 2 እና ራእይ 11፡5 ተመልከት።

[56] «መቀደስ» የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በመንፈስ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ ተግባር መካከል ያለውን የቋንቋ ትስስር ለይቶ የሚገልጽ አይደለም፣ በLC. ውስጥ «የእምነት መግለጫ» 35 ተመልከት።

[57] ቃል በቃል ትርጉም «ቅዱሳን የሆኑት»።

[58] *Christenheit*፦ ከሉተር ቀደም ሲል የነበሩት የጀርመንኛ ቅጂዎች ብዙ ጊዜ ይህን ቃል የሚጠቀሙበት *ኤክለሺያ ecclesia* (ቤተ ክርስቲያን) የሚለውን ቃል ለመተርጎም ነው።

[59] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፦ ሰባኪ ለተለያዩ አባሎች ከምስባክ ስብከት ሲያደርግ። ከጌታ ጸሎት ቀጥሎ በዊተንበርግ የነበረውን የተለመደ ቅርጽ እንጂ በሉተር በተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቅጂ አይደለም።

[60] ሉተር ይህንን ዘመም ባሉ ፊደላት የተጻፈውን መግለጫ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1531ዱ እትም መግቢያ ጨመረው።

[61] *Bitten* ማለት መጠየቅና መጸለይ ማለት ነው።

[62] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራው ሥዕል ቀደም ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፦ «ይህ ሥዕል ከዘጸአት 20፡8፣11፣19 የተወሰደ ነው»።

[63] Bitbe, ቃል በቃል ትርጉም «መጠየቅ» ማለት ነው።

[64] *Geheiliget*፡ ቃል በቃል «ቅዱስ መደረግ» ወይም «መቀደስ» ማለት ነው።

4 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

የእግዚአብሔር ስም በራሱ ቅዱስ መሆኑ እውነት ነው፣ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው እርሱ በእኛና በእኛ መካከል ደግሞ ቅዱስ ይሆን ዘንድ ነው፡፡

5 ይህ የሚሆነው እንዴት ነው? መልስ፡-

የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽነትና በንጽሕና ስናስተምርና እንዲሁም እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን በእርሱ መሠረት በቅድስና ስንኖር ነው፡፡ ውድ የሰማይ አባታችን ሆይ ይህን እንድንፈጽም እርዳን! ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው ውጪ በሌላ መንገድ የሚያስተምርና የሚኖረ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ስም በመካከላችን ያረክሳል፡፡ የሰማይ አባታችን ሆይ ከዚህ ጠብቀን!

## 6 ሁለተኛው[65] ጸሎት

*መንግሥትህ ትምጣ፡፡*

7 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

በእርግጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ያለ እኛ ጸሎት በገዛ ራስዋ ትመጣለች፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው እርሷ ወደ እኛ እንድትመጣ ነው፡፡

8 ይህ የሚሆነው እንዴት ነው? መልስ፡-

እኛ በእርሱ ጸጋ ቅዱስ ቃሉን እንድናምንና በዚህ ዓለም እንዲሁም በሚመጣውም ዓለም ለዘለዓለም የተቀደሰ ኑሮ እንኖር ዘንድ የሰማይ አባታችን መንፈስ ቅዱሱን ሲሰጠን ነው፡፡

## 9 ሦስተኛው[66] ጸሎት

*ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን*

10 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

በእርግጥ የእግዚአብሔር በጎና ቸር ፈቃድ ያለ እኛ ጸሎት ትመጣለች፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው በእኛና በመካከላችን እንድትመጣ ነው፡፡

11 ይህ የሚሆነው እንዴት ነው? መልስ፡-

የእግዚአብሔርን ስም እንድንቀድሰው የማይፈልጉ የእርሱን መንግሥት መምጣት የሚከለክሉትን - በዲያብሎስ፣ በዓለምና በሥጋችን ፈቃድ የሚገኙትን - ማናቸውንም ክፉ ሤራና ፈቃድ እግዚአብሔር በሚሰብርበትና በሚያግድበት ጊዜ፣ እንዲሁም በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ እኛን በቃሉና በእምነት በሚያጠነክርበትና በሚያጸናበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም የእርሱ ቸርና በጎ ፈቃድ ነው፡፡

## 12 አራተኛው[67] ጸሎት

*የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን*

13 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

---

[65] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- ከእምነት መግለጫው ሦስተኛ አንቀጽ መግለጫ ጋር የሚመሳሰል ነው፤ የሥዕል መግለጫው፡- «ይህ ሥዕል በሐዋ 2 የተመዘገበው ነው፡፡

[66] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ከሥሩ ሲወድቅና በወታደሮች ሲደበደብ ያሳያል፤ የሥዕል ግርጌ መግለጫ ጽሑፍ፡- «ይህ ሥዕል ከዐዲስ ኪዳን የተወሰደ ነው፤ ማቴዎስ 27 ከቀኍ. 31 ጀምሮ፡፡»

[67] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- ኢየሱስ ከብላቴናው ጋር አምስት ሺውን ሲመግብ፤ የሥዕል ግርጌ መግለጫ፡- ይህ ሥዕል በዐዲስ ኪዳን የተመዘገበ ነው፣ ዮሐንስ 6፡1-15፡፡

በእርግጥ እግዚአብሔር ያለ እኛ ጸሎት ለክፉዎች ሰዎች ሁሉ እንኳ የዕለት እንጀራን ይሰጣል፤ ጻሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው እኛ የዕለት እንጀራችን ምን እንደ ሆነ እንድንገነዘብና እርሱንም በምስጋና እንድንቀበለው ያደርገን ዘንድ ነው።

14 እንግዲያውስ «የዕለት እንጀራ» ማለት ምን ማለት ነው? መልስ፡-

ማንኛቸውም ለሥጋችን ፍላጎትና እርካታ[68] የሚሆኑት እንደ ምግብ፣ መጠጥ፣ ልብስ፣ ጫማ፣ ቤት፣ እርሻ፣ ሰብሎች፣ ከብቶች፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ መልካም[69] የትዳር ጓደኛ፣ መልካም ልጆች፣ መልካም የቤተ ሰብ አባሎች፣[70] መልካምና ታማኝ አስተዳዳሪዎች፣ መልካም መንግሥት፣ መልካም የአየር ጠባይ፣ ሰላም፣ ጤንነት፣ ጨዋነት፣ ክብር፣ መልካም ጓደኞች፣ ታማኝ ጐረቤቶችና የመሳሰሉት ናቸው።

## 15 አምስተኛው[71] ጸሎት

በደላችንን ይቅር በለን፣[72] እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል

16 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

በዚህ ጸሎት የምንለምነው ሰማያዊ አባታችን ኃጢአታችንን እንዳይቈጥርብን ወይም እነዚህን ጸሎቶች እምቢ እንዳይለን ነው፤ ምክንያቱም እኛ ስለምንለምነው ነገር ምንም የማይገባንና ወይም የሥራችን ዋጋ ስላልሆነ ነው። በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በጸጋው እንዲሰጠን እንለምናለን፣ ምክንያቱም እኛ በየቀኑ ብዙ ስለምንበድልና በእርግጥ ቅጣት ብቻ የሚገባን በመሆናችን ነው። ስለዚህ በሌላ በኩል እኛም ደግሞ የበደሉንን በእውነት ከልብ ይቅር ለማለትና ለእነርሱም በደስታ መልካም ለማድረግ እንፈልጋለን።

## 17 ስድስተኛው[73] ጸሎት

ወደ ፈተናም አታግባን

18 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

እግዚአብሔር ማንንም እንደማይፈትን የታወቀ ነው፣ ጻሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው ዲያብሎስ፣ ዓለምና ሥጋችን እንዳያታልሉን፣ ወይም ወደ ተሳሳተ እምነት፣ ወደ ተስፋ መቍረጥ፣ ወደ ታላቅ ሀፍረትና መጥፎ ምግባር እንዳይመሩን፣ እንዲሁም ምንም እንኳ በእነርሱ ብንጠቃ[74] በመጨረሻ እኛ የበላይነትን እንድናገኝና ድልን እንድንቀዳጅ እግዚአብሔር እንዲያበረታንና እንዲጠብቀን ነው።

## 19 ሰባተኛ[75] ጸሎት

ከክፉ አድነን እንጂ

20 ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፡-

---

[68] SC «የሐዋርያት የእምነት መግለጫ» 2 ጋር አነጻጽር።

[69] *frumm*፡- ይህ ቃል በ0ሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ቀጥተኛ፣ ጨዋ፣ ብቃት ያለው፣ ችሎታ ያለው፣ ጥሩ ጠባይ ያለው፣ አስተዋይ ማለት ነበር፤ ጻሩ ግን በዛሬው አጠቃቀም ቅን፣ ወይም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው እንደ ማለት አይደለም።

[70] *Gesinde*፡ የቤት አገልጋዮችና ሠራተኞች። በሉተር ዘመን ቤተ ሰብ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ማዕከል ነበር።

[71] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- ይቅርታ ያላደረገው አገልጋይ ምሳሌ፤ የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፡- «ይህ ከዐዲስ ኪዳን የተወሰደ ነው፤ ማቴዎስ 18፡23-25»።

[72] *Schulde.*

[73] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- የክርስቶስ ፈተና፣ ክርስቶስ ከበጎቹ ጋር ዲያብሎስ ደግሞ ከተከፉላ ጋር ሆኖ የሚያሳይ ሥዕል፤ የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፡- «ይህ ሥዕል ከዐዲስ ኪዳን የተወሰደ ነው፤ ማቴዎስ 4፡1-11።»

[74] *angefochten, የAnfechtung* ግሳዊ አጻጻፍ

[75] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከሲሮፊንቂያዊቱ ሴትና ከሴት ልጇ ጋር ፊት ለፊት ሲተያዩ። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፡- ይህ ሥዕል ከዐዲስ ኪዳን የተወሰደ ነው፤ ማቴዎስ 15፡21-28።»

የሰማይ አባታችንን በዚህ ጸሎት እንደ ማጠቃለያ የምንለምነው - ሥጋን ወይም ነፍስን፣ ንብረትን ወይም መልካም ስምን ከሚጐዱ - ከማናቸውም ክፉ ነገሮች እንዲያድነን፣ እንዲሁም በመጨረሻው ቀናችን የተባረከ ፍጻሜን እንዲሰጠንና ከዚህ የልቅሶ ሸለቆ በጸጋው ወደ ራሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲወስደን ነው።

21 አሜን[76]

ይህ ምን ማለት ነው? መልስ፦

እንደዚህ ያሉ ጸሎቶች በሰማይ አባታችን ዘንድ ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸው ስለ መሆኑ እርግጠኛ እንድንሆን ነው፣ ምክንያቱም በዚህ ዓይነት እንድንጸልይ እርሱ ራሱ ስለ አዘዘንና እንደሚሰማንም ተስፋ ስለ ሰጠን ነው። «አሜን፣ አሜን» ማለት «አዎን፣ አዎን፣ ልክ እንደዚሁ ይሆናል» ማለት ነው።

## የቅዱስ ጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር፦

### *ቀላል በሆነ መንገድ የቤተ ሰቡ መሪ ለቤተ ሰቡ ቅዱስ ጥምቀትን የሚያቀርብበት ሁኔታ*

1-2 ### አንደኛ[77]

ጥምቀት ምንድን ነው? መልስ፦

ጥምቀት እንዲሁ ባዶ ውሃ ብቻ አይደለም፣ ይልቁንስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ውስጥ የታቀፈና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተጣመረ ውሃ ነው።

3 ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር ቃል የትኛው ነው? መልስ፦

4 ጌታችን ክርስቶስ በማቴዎስ 28፡19፦ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ[78] በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» የሚለው ነው።

### ሁለተኛ

5-6 ጥምቀት ምን ዓይነት ስጦታዎችን ወይም ጥቅሞችን ያስገኛል? መልስ፦

የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ይቤዣል፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያውጀው በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የዘለዓለምን ድነት ይሰጣል።

7-8 እነዚህ የእግዚአብሔር ቃሎችና ተስፋው የትኞቹ ናቸው? መልስ፦

ጌታችን ክርስቶስ በማርቆስ 16፡16 «ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን የፈረድበታል» የሚለው ነው።

---

[76] ከሉተር ሞት በኋላ የታተሙት አንዳንድ የክርስትና ትምርቱ የኋለኞቹ እትሞች የውዳሴውን መዝሙር ይጨምራሉ። ምንም እንኳ በኢራስመስ የግሪክ ዐዲስ ኪዳን እትሞችና በሉተርም የጀርመንኛ ትርጒም የሚገኝ ቢሆንም ሉተር ራሱ በክርስትና ትምህርት የመካከለኛውን ዘመን አጠቃቀም አዘውትሮ በመከተል እርሱን አስወግዶታል።

[77] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፦ የአንድ ሕፃን ጥምቀት። ቄሱ በአንድ እጁ በጐድጓዳ ሳህን ባለ ውሃ ላይ ፊቱን ያጐነበሰ ራቁቱን የሆነ ሕፃን ይዞ በሌላው እጁ ውሃ ሲጨልፍ ያሳያል። አንድ ዲያቆን እርሱ እንዲያነበው የተከፈተ መጽሐፍ ይዞለት ሦስት ያልቀሰሱ ሰዎች ሲጸልዩ ያሳያል፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ሆኖ በትዕይንቱ ላይ ያንዣብባል። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፦ «ሥዕሉ ከማቴዎስ 28፡16-20 የተወሰደ»።

[78] Heiden: or, heathen.

9-10 ### ሦስተኛ

ውሃ እንደዚህ ያሉትን ታላላቅ ነገሮች እንዴት ሊፈጽም ይችላል? መልስ፡-

ውሃ ብቻውን ይህን ሊያደርግ እንደማይችል ግልጽ ነው፣ ጳሩ ግን ከውሃው ጐን ለጐን ያለው የእግዚአብሔር ቃልና በውሃው ውስጥ ያለውን ይህን የእግዚአብሔር ቃል የሚያምነው እምነት ይህን ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር ቃል ከሆነ ውሃው እንዲሁ ውሃ ብቻ ነው እንጂ ጥምቀት አይደለም፤ ጳሩ ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከሆነ ጥምቀት ይሆናል፣ ማለትም ጸጋን የተሞላ የሕይወት ውሃና «ለዐዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ» እንደ ተባለው ይሆናል፣ ይኸውም ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ በምዕራፍ 3፡[5-8] «... ለዐዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፣ ያን መንፈስም *በጸጋው ጸድቀን*[79] በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ በእርግጥ[80] የታመነ ነው» እንዳለው ነው፡፡

11 ### አራተኛ

12 ታዲያ እንደዚህ ያለው የውሃ ጥምቀት ምን ፋይዳ አለው? መልስ፡-

በእኛ አሮጌው ፍጥረት[81] ከኃጢአቱና ከክፉ ምኞቱ ሁሉ ጋር በየቀኑ በሚደረገው ጸጸትና ንስሐ[82] መቀበር እንዳለበትና፣ በሌላ በኩል ደግሞ በየቀኑ ዐዲስ ሰው መውጣቱንና በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅና በንጽሕና ለዘላለም እንዲኖር መነሣቱን የሚያመለክት ነው፡፡

13 ይህ የተጻፈው የት ነው? መልስ፡-

14 ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 6፡4፣ «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በዐዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» ይላል፡፡

15 *ያልተማሩ ሰዎች የኃጢአት ኑዛዜን እንዴት እንደሚማሩ፡፡*[83]

16 *ኑዛዜ ምንድን ነው? መልስ፡-*

*ኑዛዜ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ አንዱ ኃጢአታችንን መናዘዝ ነው፡፡ ሌላው የኃጢአት ይቅርታን አዋጅ መቀበል ሲሆን ይኸውም ከንስሐ አባት (ኑዛዜ ከሚቀበለው) የምንቀበለውን የይቅርታ አዋጅ ከራሱ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ በመቊጠር በዚሁ አማካይነት በሰማይ አምላክ ፊት ኃጢአታችን ይቅር ስለ መባሉ በምንም ዓይነት ሳንጠራጠር በጥብቅ ማመን ነው፡፡*

17 *አንድ ሰው የሚናዘዘው የትኞቹን ኃጢአቶች ነው?*

18 *በእግዚአብሔር ፊት አንድ ሰው፣ በጌታ ጸሎት እንደምናደርገው ሁሉ የማናውቃቸውን እንኳ ቢሆን፣ በሁሉም ኃጢአቶች በደለኛ መሆኑን ማመን አለበት፤ ይሁን እንጂ በንስሐ አባት (ኑዛዜ በሚቀበለው) ፊት የምንናዘዘው የምናውቃቸውንና የሚያስቸግሩንን ኃጢአቶች ብቻ ነው፡፡*

---

[79] «ጻድቃንና» ሉተር ከተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ከ1536 በፊት የነበሩት እትሞች «የጸደቀ» የሚሉ ናቸው፡፡

[80] «በእርግጥ» የሚለው ቃል ከ1536 በፊት አልነበረም፡፡

[81] ቃል በቃል ትርጉም አሮጌው አዳም፡፡

[82] የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ XII,3.

[83] በ1531 አንቀጽ 15-29 የጥምቀቱን መጽሐፍ በመከተል በዚህ ነጥብ ላይ በ1529 በትንሹ የክርስትና ትምህርት በአንድ የላቲን እትም ውስጥ የነበረውንና በ1529 በትንሹ የክርስትና ትምህርት በአንድ የጀርመንኛ እትም ውስጥ ቀደም ሲል የነበረውን *አጭር የኑዛዜ ሥነ ሥርዓት* የሚለውን አስወግዶታል (1529) (WA 30/1: 343-45; LW 53:116-18)፡፡ ሉተር በፍራንክፈርት ለነበረው ለከተማው ጉባኤና ለማኅበረ ምእመናን «ግልጽ ደብዳቤ በፍራንክፈርት ኦን ዘ ሜይን ላሉት 1533» በሚል ርእስ በጻፈው ደብዳቤ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ይህን ጭማሪና የግል ኑዛዜን ጠብቆ አቆይቶታል፡፡ ትርጉም ጆን ዲ ቬከር፣ *Concordia Journal* 16 (1990)፡ 333-51 (WA 30/3: 567-71) .

19 *እነዚህ ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው?*

20 *በዚህ ውስጥ በዐሥርቱ ትእዛዛት አንጻር የሕይወታችሁን አካሄድ መመርመር አለባችሁ*[84]*:- አባት፣ እናት፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ ጌታ፣ እመቤት፣ አገልጋይ መሆናችሁን፤ የማትታዘዙ፣ የማትታመኑ፣ ሰነፎች*[85] *መሆናችሁን፤ በቃል ወይም በሥራ አንድን ሰው መጉዳታችሁን፤ አንድን ነገር መስረቃችሁን፣ ቸልተኛነታችሁን ማባከናችሁን፣ ወይም መጉዳታችሁን ማሰብ አለባችሁ።*

21 *እባክዎ አንድ አጭር የኑዛዜ ዓይነት ያቅርቡልኝ! መልስ*[86]*:-*

*ለንስሐ አባት (ኑዛዜ ለሚቀበለው) እንዲህ ማለት አለብህ:-*

*«የተከበሩ ውድ ጌታዬ ኑዛዜዬን እንዲያዳምጡኝና በእግዚአብሔር ስም የኃጢአት ይቅርታን እንዲያውጁልኝ እለምንዎታለሁ»*[87]

*«ቀጥል።»*

22 *«እኔ ምስኪን ኃጢአተኛ በሁሉም ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ መሆኔን እናዝዛለሁ።*[88] *እኔ በእርስዎ ፊት በተለይ የምናዘዘው ምንም እንኳ አገልጋይ፣ ወዘተ ብሆንም ጌታዬን በታማኝነት አለማገልገሌን ነው። ምክንያቱም በዚህና በዚያ ወቅት የነገሩኝን ነገር አልፈጸምሁም። እነርሱን አስቈጥቼ እንዲራገሙ አድርጌአቸዋለሁ፤ ሥራዬን ቸል ብዬ ጉዳት እንዲደርስ አድርጌአለሁ። ደግሞም በንግግርና በተግባር ብልግናን ፈጽሜአለሁ። ከእኩያዎቼ ጋር ተጣልቼአለሁ፤ በእመቤቴም ላይ በማጒረምረም ተሳድቤአለሁ፤ ወዘተ. በዚህ ሁሉ አዝናለሁ። ጸጋ ያስፈልገኛል፣ ለማሻሻል እፈልጋለሁ።»*

23 *ጌታ ወይም እመቤት የሚከተለውን ለማለት ይችላሉ:-*

*«እኔ በተለይ የምናዘዘው ልጄን፣ የቤተ ሰቤን አባሎች፣ የትዳር ጓደኛዬን*[89] *ለእግዚአብሔር ክብር በታማኝነት ያልተንከባከብሁ መሆኔን ነው፤ ተራግሜአለሁ፣ በብልግና ቃላትና በተግባር መጥፎ ምሳሌ ሆኛለሁ፣ በባልንጀሮቼ*[90] *ላይ ጉዳት አድርሼአለሁ፤ በእነርሱ ላይ ክፉ ተናግሬአለሁ፤ ከተገቢው በላይ አስከፍያቸዋለሁ፤ መናኛ ዕቃዎችንም ሸጬላቸው የጐደለ መልስም ሰጥኋቸው»። ሌሎችንም ማንኛቸውንም ከእግዚአብሔር ትእዛዛትና ከሕይወት ተግባራቸው ወዘተ ውጭ የፈጸሙአቸውን መናዘዝ ይችላሉ።*

24 *ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ግለሰቦች*[91] *በእነዚህ ወይም በታላላቅ ኃጢአቶች ምክንያት ሸክም ካልተሰማቸው መጨነቅ የለባቸውም፤ ወይም ሌሎች ኃጢአቶችን በመፈላለግና በመፍጠር ኑዛዜን ወደ ሥቃይ*[92] *መለወጥ የለባቸውም። በዚህ ፈንታ እናንተ የምታውቁትን አንድ ወይም ሁለት ኃጢአት ከዚህ እንደሚከተለው መጥቀስ ትችላላችሁ:-*

*«በተለይ የምናዘዘው አንድ ጊዜ ተሳድቤአለሁ፤ እንዲሁም አንድ ጊዜ ባለማስተዋል ተናግሬአለሁ፣ አንድ ጊዜ ይህንን ወይም ያንን ወዘተ. ቸል ብዬአለሁ»። ማለቱ ይበቃል።*

25 *ጭራሹን ምንም ኃጢአት ያልተሰማችሁ ከሆነ (ይህም በእውነት የማይመስል ቢሆንም) ምንም የተለየ ኃጢአት መጥቀስ የለባችሁም፤ በዚህ ፈንታ በንስሐ አባት ፊት በምታደርጉት አጠቃላይ ኑዛዜ*[93] *መሠረት ይቅርታን መቀበል ትችላላችሁ።*

---

[84] Stand

[85] መጽሐፈ ስምምነት (1580) የ1535ቱ የዊተንበርግ እትሞች «ሰነፍ» ከሚለው ቀጥሎ «ቀኊጡ፣ ዐመፀኛ ጠበኛ የሚሉትን ቃላት ዘልለዋቸዋል።

[86] የዚህ መልክ አብዛኛው ክፍል በመካከለኛ ዘመን ልምድ ላይ የተመሠረተ ነው።

[87] ሉተር በዚህና በሁሉም መደበኛውን መልክ ይጠቀማል።

[88] ይህ ከታች በአንቀጽ 25 የተጠቀሰው አጠቃላይ የኑዛዜ ዓይነት ነው፤ በዚህ ለተለየ ኑዛዜ እንደ መቅድም ያገለገለ ሲሆን በአንቀጽ 23 እና 24 መጀመሪያ በውስጠ ታዋቂነት ይገኛል። በሌሎች ሁኔታዎች «አጠቃላይ ኑዛዜ» በአምልኮ ጊዜ በስብከቱ መደምደሚያ ላይ የሚነገሩትን ቃሎች የሚያመለክት ነው። Cf. SA III, 3, 13.

[89] በጀርመንኛ:- «ሚስት»።

[90] በጀርመንኛ:- ነጠላ ቍጥር።

[91] በጀርመንኛ:- ነጠላ ቍጥር።

[92] A Discussion on How Confession Should Be Made (1520) (WA 6:157-69; LW 39:27-47) እና CA XXV, 7-12 ተመልከት።

[93] እላይ ቍ 88 ተመልከት፤ ሉተር ይህንን ከመልእክት በኋላ በሰባኪው ከሚነገሩት የአደባባይ አጠቃላይ የኑዛዜ ቃላት ጋር ለማስፋት አስቦ ሊሆን ይችላል።

26 *በዚህ ጊዜ የንስሐ አባቱ (ኑዛዜ የሚቀበለው) እንዲህ ይበል፡-*
*«እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልህ፣ እምነትህንም ያጠንክርልህ፣ አሜን።*
27 *በተጨማሪም የንስሐ አባቱ (ኑዛዜ የሚቀበለው) እንዲህ ይበል፡-*
*«የእኔ ይቅርታ የእግዚአብሔር ይቅርታ መሆኑን ደግሞ ታምናለህን?»*
28 *መልስ፡- «አዎን፣ ውድ ጌታዬ»።*
*ያኔም እንዲህ ይበል*
*«'እንደ እምነትህ ይሁንልህ[94] እንዲሁም እኔ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት[95] ኃጢአትህን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይቅር ብዬሃለሁ፣ አሜን፣ በሰላም ሂድ»።[96]*
29 *በእርግጥ የንስሐ አባቱ (ኑዛዜ የሚቀበለው) ተጨማሪ የእግዚአብሔር ቃል ምንባቦችን በመጠቀም ከባድ የሕሊና ሸክም ያለባቸውን ወይም በሐዘንና በመጠቃት[97] ላይ ያሉትን ማጽናናትና ማበረታታት ይችላል። ይህ ላልተማሩ ሰዎች ብቻ የሚሆን ተራ የኑዛዜ ዓይነት ነው።*

## የመሠውያው ቅዱስ ምሥጢር፡-

### *ቀላል በሆነ መንገድ የቤተ ሰቡ መሪ ለቤተ ሰቡ አባላት የሚያቀርብበት ሁኔታ[98]*

1-2 **የመሠውያው ቅዱስ ምሥጢር ምንድን ነው? መልስ፡-**
**ይህ እኛ ክርስቲያኖች እንድንበላውና እንድንጠጣው በራሱ በክርስቶስ የተመሠረተ በኅብስትና በወይን መልክ የቀረበ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ነው።**
3 **ይህ የተጻፈው የት ነው? መልስ፡-**
4 **ቅዱሳን ወንጌላውያኑ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይጽፋሉ፡- «ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመስግኖ፤ ቈርሶም 'እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት' አለ፤ እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸውና፤ 'ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፣ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት'»[99] አለ።**
5-6 **እንደዚህ ያለው መብላትና መጠጣት የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው? መልስ፡-**
**«ለእናንተ የተሰጠ»፣ «ለኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የፈሰሰ»[100] የሚሉት ቃላት በእነዚህ ቃላት አማካይነት በቅዱስ ምሥጢሩ ለኃጢአት ይቅርታ[101] ሕይወትና ድነት የተሰጡ መሆናቸውን ያሳዩናል፣ ምክንያቱም የኃጢአት ይቅርታ ባለበት ሕይወትና ድነት ደግሞ አለ።**

---

[94] ማቴዎስ 8፡13።
[95] ማቴዎስ 16፡19፤ 18፡18፤ ዮሐንስ 20፡23።
[96] ማርቆስ 5፡34፤ ሉቃስ 7፡50፤ 8፡48።
[97] *angefochten.*
[98] ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ ሥዕል፡- የጌታ እራት ሲታደል። ከመሠውያው በላይ በመጨረሻው እራት ክርስቶስ ይሁዳን ሲያቈርብ ያሳያል። የአገልጋይ ሸሚዝ የለበሰ ቄስ ለተንበረከከ ሰው ኅብስት ሲሰጥ አንድ ረዳት ደግሞ ለተንበረከከች ሴት ጽዋውን ሲሰጥ። በመሠውያው ግራና ቀኝ ሌሎች ቅዱስ ቍርባን ለመውሰድ ይጠባበቃሉ። የሥዕል መግለጫ ጽሑፍ፡- ይህ ሥዕል በማቴዎስ 26፡26-28 የተመዘገበ ነው።»
[99] ከ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23-25፤ ከማቴዎስ 26፡26-28፤ ከማርቆስ 14፡22-24፤ ከሉቃስ 22 ከቍ 19 ጀምሮ ካሉት ምንባቦች የተውጣጣ ነው፤ ከL.C, Sacrament of the Alter," 3 ጋር አነጻጽር። ይህ ጽሑፍ በጀርመኑ የቅዱስ ቍርባን ሥነ ሥርዓትና የአገልግሎት ሥርዓት የመመሥረቻ ቃሎች (1526) (WA 19:97, 12-99:4; LW 53:80-81) ወይም ከትልቁ የክርስትና ትምህርት «አጭር መቅድም» 23 ጋር የሚመሳሰል አይደለም።
[100] በዚህና በሚቀጥሉት ጥያቄዎች በጀርመንኛው አንድ ጊዜ ብቻ የተጠቀሰው «ለእናንተ» የሚለው ቃል ለሁለቱም ሐረጎች የሚያገለግል ነው።
[101] ከ1536ቱ ትንሹ የክርስትና ትምህርት እትም ጀምሮና በመጽሐፈ ስምምነቱ «ኃጢአቶች» ተብሎአል።

7-8 *አካላዊ መብላትና መጠጣት እንዲህ ያለውን ታላቅ ነገር እንዴት ሊፈጽም ይችላል?*[102] *መልስ፡-*

በእርግጥ መብላትና መጠጣት ብቻ ይህን ሊያደርግ አይችልም፣ ዳሩ ግን «ለእናንተ የተሰጠ» እና «ለኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የፈሰሰ» በማለት የተጻፉት ቃላት ናቸው፤ እነዚህ ቃላት አካላዊ ከሆነ መብላትና መጠጣት ጋር ከተያያዙ በቅዱስ ምሥጢር በጣም ዋና ነገሮች ናቸው። እነዚህንም ቃላት የሚያምን ማንም ሰው እነርሱ የሚያውጁትንና የሚገልጹትን፣ ማለትም «የኃጢአት ይቅርታን» ያገኛል።

9-10 *ታዲያ ይህን ቅዱስ ምሥጢር በተገቢነት የሚቀበል ማን ነው? መልስ፡-*

በእርግጥ ጾምና አካላዊ ዝግጅት መልካም ውጫዊ ሥነ ሥርዓቶች ናቸው፣ ዳሩ ግን «ለእናንተ የተሰጠ» እና «ለኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የፈሰሰ» የሚሉትን እነዚህን ቃላት የሚያምን ሰው በእውነት የተገባና በሚገባ የተዘጋጀ ነው። ይሁን እንጂ፣ እነዚህን ቃላት የማያምን ወይም እነርሱን የሚጠራጠር ሰው ያልተገባና ያልተዘጋጀ ነው፣ ምክንያቱም «ለእናንተ» የሚለው ቃል የሚያምን ልብ ስለሚጠይቅ ነው።

## *የቤተ ሰቡ መሪ ለቤተ ሰቡ አባላት የጧትና የማታ ጸሎት እንዴት ማስተማር እንዳለበት*[103]

### [የጧት ጸሎት]

1 በማለዳ ከመኝታህ እንደ ተነሣህ በቅዱስ መስቀሉ ምልክት በማማተብ እንደዚህ ትላለህ፡-

2 «እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ጠብቀኝ። አሜን»።»

ከዚያም በመንበርከክ ወይም በመቆም የሐዋርያትን የእምነት መግለጫና የጌታን ጸሎት ጸልይ። ከፈለግህ ይህችን ትንሽ ጸሎት ደግሞ በተጨማሪ ለመጸለይ ትችላለህ፡-

«የሰማይ አባቴ ሆይ፣ በዚህች ሌሊት ከማንኛውም ጉዳትና አደጋ ስለ ጠበቅኸኝ በውድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አመሰግንሃለሁ፤ እንዲሁም በዛሬው ቀን ደግሞ ሕይወቴና ተግባሬ ሁሉ አንተን ፈጽሞ ያስደስት ዘንድ እንድትጠብቀኝ እለምንሃለሁ። ራሴን በእጆችህ ላይ አደራ አስቀምጣለሁ፡- ሥጋዬን፣ ነፍሴንና ያለኝን ሁሉ አስረክባለሁ። ክፉው ጠላቴ በእኔ ላይ ሥልጣን እንዳይኖረው የአንተ ቅዱስ መልአክ ከእኔ ጋር ይሁን። አሜን።»

3 (ለምሳሌ ዐሥርቱ ትእዛዛትን የሚመለከት)[104] ወይም ሌላ ማንኛውንም የአንተን የጸሎት ጊዜ የሚመለከት አንድ መዝሙር ከዘመርህ በኋላ በደስታ ወደ ሥራህ መሄድ ትችላለህ።

### [የማታ ጸሎት]

4 ማታ ወደ መኝታ በሄድህ ጊዜ በቅዱስ መስቀሉ ምልክት በማማተብ እንዲህ በል፡-

«እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ጠብቀኝ። አሜን»።

5 ከዚያም በመንበርከክ ወይም በመቆም የሐዋርያትን የእምነት መግለጫና የጌታን ጸሎት ጸልይ።

---

[102] ከ1540ው ትንሹ የክርስትና ትምህርት እትም ጀምሮና በመጽሐፍ ስምምነቱ ውስጥ «ታላላቅ ነገሮች» ተብሎአል።

[103] ሉተር ይህንን ጽሑፍ በሮማውያኑ በየሰዓቱ ከሚነበቡ ጸሎቶች፣ ከሚዘመሩ መዝሙሮች፣ ከዳዊት መዝሙሮች መጽሐፍ ላይ የወሰደው ነው፤ «ባርኮት ስጡ» (Sich Segenen) የሚለው መግለጫ በሉተር ዘመን «በመስቀሉ ምልክት ማማተብ» የሚል ዐሳብ ነበር።

[104] ትልቁ የክርስትና ትምህርት «አጭር መቅድም» 25 እና ዐሥርቱ ትእዛዛት ላይ የተጻፈውን የራሱን የሉተርን መዝሙሮች (WA 35:426-28; LW 53:277-81) ተመልከት።

እንዲሁም ከፈለግህ ይህችን ትንሽ ጸሎት መድገም ትችላለህ፡-

«ሰማያዊ አባቴ ሆይ፣ በውድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነትህ ዛሬ ስለ ጠበቅኸኝ ለአንተ ምስጋና እሰጣለሁ፤ እንዲሁም የሠራሁትን መተላለፍ፣ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ፤ ደግሞም በቸርነትህ በሚመጣው ሌሊት እንድትጠብቀኝ እለምንሃለሁ። ራሴን፣ ሥጋዬን፣ ነፍሴንና የእኔ የሆነውን ሁሉ በእጅህ አሳልፌ እሰጣለሁ። ክፉው ጠላት በእኔ ላይ እንዳይሠለጥንብኝ ቅዱስ መልአክህ ከእኔ ጋር ይሁን። አሜን።»

ከዚያ በኋላ በፍጥነትና በደስታ ለመተኛት ትሄዳለህ።

6 *የቤተ ሰብ ኃላፊው የማዕድ ጸሎትና ምስጋና ለማቅረብ የቤተ ሰቡን አባላት እንዴት እንደሚያስተምር*[105]

## [የማዕድ ጸሎት][106]

7 ሕፃናቱና የቤተ ሰቡ አባላት በታማኝነት ወደ ማዕዱ መጥተው እጆቻቸውን አጣጥፈው እንዲህ ይደግማሉ፡-

«የሁሉ ዓይኖች አንተን ተስፋ ያደርጋሉ፤ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ዘርግተህ፣ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ።»[107]

8 አስተያየት፡- «መልካም» ማለት ሁሉም እንስሳት ደስተኞች እንዲሆኑና በቂ ምግብ እንዲቀበሉ ማድረግ ነው፣ ምክንያቱም ጭንቀትና ስስት እንዲህ ዓይነት ደስታን ያስቀራሉ።

9 ከዚያም የጌታን ጸሎትና የሚከተለውን ጸሎት መድገም አለባቸው፡-

«ሰማያዊ አባት፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ እኛንና በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከተትረፈረፈው በጎነትህ የምንቀበላቸውን እነዚህን ስጦታዎችህን ባርክ። አሜን።»

10

## ምስጋና[108]

በተመሳሳይ መልኩ፣ ከበሉ በኋላ በዚያው ዓይነት እጃቸውን አጣጥፈው በልብ መድገም አለባቸው፡- «ቸር ነውና፣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ ለሚጠሩት ለቁራዎች ጫጩቶች ለእንስሶችም ምግባቸውን ይሰጣል። የፈረስን ኀይል አይወድድም፣ በሰውም ጭን አይደሰትም። እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱም በሚታመኑ ይደሰታል።»[109]

11 ከዚያም የጌታን ጸሎትና የሚከተለውን ጸሎት ይድገሙ፡- በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁሉ ጥቅሞችህ ለዘላለም ለምትኖርና ለምትነግሥ ለአባታችን ጌታ እግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን። አሜን።»

---

[105] በዚህ ክፍል ያለው ጽሑፍ ቀደም ሲል በ1525 ከነበረው የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት ከሮማውያን መጽሐፍ የተወሰደ ነበር። *Das Buchlin für die Leyen und kinder* (ለተራ ሕዝብና ለሕፃናት የተዘጋጀ መጽሐፍ) ሉተር ደስታ በሚለው ቃል ላይ የሕፃናቱን ባሕርይና ቃሉን ማንጸባረቅን የሚገኘውን ደስታ በተመለከተ መመሪያዎችን ይጨምራል።

[106] ይህ ርእስ *Benedictio mensae* በሚለው በላቲኑ ብቻ ይገኛል።

[107] መዝሙር 145፡15፣16። ተከታዩ ማብራሪያ ከዚህ ጽሑፍና ከሉቃስ 2፡14 ጋር ስለ ተያያዘው ደስታ ስለሚለው ቃል (*Wohlgefallen*) (*ዎልግፎለን*) ሉተር በተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ካሉት የሉተር አስተያየቶች ጋር ይተካከላል።

[108] ሉተር የ1525ቱን የዊተንበርግ ክርስትና ትምህርት ተከትሎ Gratias የሚለውን የላቲን ቃል ይጠቀማል።

[109] መዝሙር 106፡1፤ 136፡1፣26፤ 147፡9-11። ጽሑፉ ሉተር በተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን ትርጒሞች ይከተላል።

1 # የአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የቤተ ሰብ ሠንጠረዦች[110]

## *በሁሉም የአገልግሎት እርከንና የሕይወት ጉዞ ላይ ያሉ አገልጋዮችና ምእመናን በተለይ ለአገልግሎታቸውና ለሥራቸው አግባብነት ባለው መንገድ የሚገሠጹበት ትምህርት*[111]

2 ## ለጳጳሳት፣ ለቄሶችና ለሰባኪያን

«እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፣ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባ የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣[112] ነገር ግን ገር የሆነ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፣ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ ዐዲስ ክርስቲያን አይሁን፡፡»[113] 1ኛ ጢሞ 3[፡2-6]፡፡[114]

4 ## ስለ መንግሥት ባለ ሥልጣናት

«ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ፡፡ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፣ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፣ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ፡፡ በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡» ሮሜ 13[፡1-2፣4ለ]፡፡[115]

6 ## ለባሎች

«ባሎች ሆይ፣ [ደካማ][116] ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወት ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው፡፡» 1ኛ ጴጥ 3[፡7] «መራራም አትሁኑባቸው» ቈላ 3[፡19]፡፡

---

[110] Die Haustafel አንዳንድ ጊዜ «የተግባር ማዕድ» በሚል ተተርጕሞአል፡፡ (እዚህ ካለው አጠቃቀም የተወሰደ የቃሉ ትርጕም)፣ ይህ ክፍል በዮሐንስ ጌርሰን Tractatus de modo virendi omnium fidelium ለሉተር የተሰጠ ሊሆን ይችላል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም ምንባቦች እዚህ ላይ ጽሑፎቹ በሉተር በራሱ በተዘጋጁበት ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

[111] ሉተር ስለ ምንኩስና ሕይወት የዚህን ቃል የተለመደ አጠቃቀምና ሦስቱንም ግዛቶች፡ Ordo ecclesiasticus, politicus and oeconomicus (ቤተ ክርስቲያን፣ መንግሥትና ቤተ ሰብ) በማመልከት ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ SA, «መቅድም»፣ 14፣ እንዲሁም the confession concerning Christs's supper (1528) (WA 26:503, 17/35-505, 28; LW 37:363-65 ተመልከት፡፡

[112] የኋለኛውን የሉተር ጀርመንኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም በመጠቀም የ1536ቱ ትንሹ የክርስትና ትምህርትና መጽሐፈ ስምምነት ዘመም ተደርጎ በተጻፈው ጽሑፍ «እፍረት የሌለው ትርፍ ለሚለው ስስትን» ተክተዋል፡፡

[113] ከቲቶ 1፡9 ምንባብን በመጠቀም ዘመም ተደርጎ የተጻፈው ጽሑፍ በ1540ው የትንሹ የክርስትና ትምህርት እትምና በመጽሐፈ ስምምነት ላይ ተጨምሮ ነበር፡፡ ቀደምት እትሞች  በቀላሉ ወዘተ. በሚለው ተደምድመዋል፡፡

[114] የ1540ው የትንሹ የክርስትና ትምህርት እትም «ክርስቲያኖች ለመምህራንና ለቀሳውስት [seelsorger] ማድረግ ያለባቸው» የሚል ርእስ ያለውን ክፍል ይጨምራል እንዲሁም ከሉቃስ 10፡7፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡14፤ ገላትያ 6፡6-7፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡17-18፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-13 እና ዕብራውያን 13፡17 ጽሑፎችን ያካትታል፡፡ ይህ ጽሑፍ በትንሹ የክርስትና ትምህርትና በመጽሐፈ ስምምነት በጥንቱ እትሞች አይገኝም፡፡ ከሉቃስና ከ1ኛ ተሰሎንቄ ምንባቦችን የሚያስቀረው በምሕፃረ ቃል መልክ የቀረበው፣ ያለ ሉተር ዕውቅና ወይም ስምምነት ተስማሚ በመሰለው ሁሉ በ1529 የላቲን ትርጕሞች ተገኝቷል፡፡

[115] የ1542ቱ የትንሹ ክርስትና ትምህርት እትም «ምን ዓይነት ትምህርቶች ለባለ ሥልጣናት ሊሰጡ ይገባል» የሚል ርእስ ይጨምራል፣ እንዲሁም ከማቴዎስ 22፡21፤ ሮሜ 13፡1፣5-7፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2፤ ቲቶ 3፡1 እና ከ1ኛ ጴጥሮስ 2፡13-14 ጽሑፎችን ያካትታል፡፡ ይህ ጽሑፍ በጥንቱ ትንሹ የክርስትና ትምህርትም ሆነ በመጽሐፈ ስምምነት እትሞች አይገኝም ፡፡ የማቴዎስ 17፡24-27 ጽሑፍን ሳይሆን ማጣቀሻን የሚያካትት ተስማሚ በመሰለው ሁሉ ያለ ሉተር ዕውቅና ወይም ስምምነት በ1529 የላቲን ትርጕሞች ተገኝቶአል፡፡

[116] ከ1536 በፊት፡- »ደካማ፡፡»

7

## ለሚስቶች

«ሚስቶች ለጌታ እንደሚገዙ፣ ለባሎቻቸው ይገዙ፣ ሣራም ለአብርሃም ጌታ ብላ እየጠራች እንደታዘዘችለት እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ ናችሁ።»[117] 1ኛ ጴጥ 3[፡1፣6]።[118]

8

## ለወላጆች

«እናንተም አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቈጡአቸው» ኤፌ 6[፡4]።

9

## ለልጆች

«ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት» ኤፌ 6[፡1-3]።

10

## ለሴትና ለወንድ ባሪያዎች፣ ለቀን ሠራተኞች፣ ወዘተ.

«ባሪያዎች[119] ሆይ፣ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ[120] ተገዙ፣ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና።»[121]

11

## ለጌቶችና ለኀላፊዎች[122]

«እናንተም ጌቶች ሆይ፣ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና።» ኤፌ 6[፡9]።

12

## ለወጣቶች ባጠቃላይ

«እንዲሁም ጎበዞች ሆይ፣ ለሽማግሌዎች ተገዙ፣ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ።» 1ኛ ጴጥ 5[፡5-6]።

---

[117] ዘመም ተደርጎ የተጻፈው ጽሑፍ በመጀመሪያ በ1536 በትንሹ የክርስትና ትምህርት እትም ተጨምሮ ነበር። የጥንቱ እትሞች «ማንኛውንም የሚያሸብር ነገር መፍራት» ተብለው ይነበባሉ። በዚህ ጥቅስ ካቀረበው ከ1522 የሉተር ስብከት WA 12:341, 11-345,27 (LW 30:87-91) ተመልከት።

[118] «ለጌታ እንደ» የሚሉት ቃሎች ከኤፌሶን 5፡22።

[119] Knecht:- በጀርመን ቤተ ሰብ ወንዱ አገልጋይ።

[120] ከ1536 በፊት የዊተንበርግ የጥንት መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ትንሹ የክርስትና ትምህርት፡- «በመታዘዝ» ተብሎ ይነበባል።

[121] ኤፌሶን 6፡5-8።

[122] Hausheua und Hausfrauen: የቤተ ሰብ ኃላፊዎች ጌታና የበላይ የሚሉት ቃላት በጀርመንኛ አንድ ናቸው።

13 ## ለባልቴቶች

«ብቻዋንም ኖራ በእውነት ባልቴት የምትሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርጋለች ሌትና ቀንም በልመና፣ በጸሎትም ጸንታ ትኖራለች፤ ቅምጥሊቱ ግን በሕይወቷ ሳለች የሞተች ናት።» 1ኛ ጢሞ 5[:5-6]።

14 ## በማኅበረ ሰቡ ላሉ ሁሉ[123]

«ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቃልሎአል።» ሮሜ 13[:9] እንግዲህ [እግዚአብሔርን] በመምሰል ጸሎት ስለ ሰዎች ሁሉ እንዲደረግ እመክራለሁ።» 1ኛ ጢሞ 2[:1]።[124]

15 ትምህርቶቻቸውን ሁሉ በጥንቃቄ ይማሩ፣
ለቤተ ሰቡ እንዲሳካለት ጥረት አድርጉ።[125]

## ለቄሶች የሚሆን የጋብቻ መመሪያ[126]
## ማርቲን ሉተር

1 የተለመደው ምሳሌ፣ «በጣም ብዙ መሬት፣ በጣም ብዙ ቀረጥ» ይላል። በዚህ ምክንያት ሥርዓችና የተጋቡት ሁኔታ የዓለም ጉዳዮች ስለ ሆኑ፣ ይህ «መንፈሳውያን»[127] የሆንነው፣ ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በምንም መንገድ ለማዘዝ ወይም ጋብቻን በተመለከተ ማንኛውንም ነገር ለማስተላለፍ እንደማይችሉ፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ለእያንዳንዱ ከተማና አገር አሁን በጥቅም ላይ የዋሉትን ልምዶቻቸውን እንዲቀጥሉ መፍቀድ ነው። አንዳንዶች ሙሽራውን ማታና ጧት ሁለት ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ፣ አንዳንዶች አንድ ጊዜ ብቻ ያመጣሉ። አንዳንዶች ከሁለት ወይም ከሦስት ሳምንት አስቀድሞ በግልጽና ጽሑፍ በማሳተም ከምስባክ ያስታውቃሉ። እነዚህን ሁሉ እንደሚፈልጉት እንዲያከናውኑ ለመስፍኑና ለከተማ ምክር ቤት እተዋለሁ።

2 ይሁን እንጂ፣ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ፊት ወይም በቤተ ክርስቲያን እንድንባርካቸው፣ እንድንጸልይላቸው ወይም ጋብቻ እንድንፈጽምላቸው እንኳ በሚጠይቁበት ጊዜ ይህን እንድናደርግ እንገደዳለን። ስለዚህ፣ ምናልባትም ይህን የተለመደ ትእዛዝ ከእኛ ለሚፈልጉት ምንም ነገር በተሻለ ሁኔታ ለማያውቁት እነዚህን የምክር ቃላት ትእዛዝ ልሰጥ ፈልጌአለሁ። አለበለዚያ፣ የተሻለ የሚያደርጉት (ማለትም በፍጹም ምንም ማድረግ የማይችሉና ሁሉን እንደሚያውቁ የሚያስቡት) በሚገባ ካላሻሻሉትና ካላስተካከሉት በስተቀር ይህ አገልግሎቴ አያስፈልጋቸውም። እንደ ሌሎቹ ተመሳሳይ ልምምድ እንዳይከተሉ በእርግጥ ታላቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። አንድ ሰው ከሌላ ስፍራ አንዳች ነገር እንደ ተማሩ ሊያስብ ይችላል! ይህ ነውር አይሆንምን?

3 ምክንያቱም እስካሁን ድረስ ሰዎች ወንድና ሴት መነኮሳት በሚለይበት (ምንም እንኳ ሁኔታቸው[128] እና ሕልውናቸው ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት በመጽሐፍ ቅዱስ

---

[123] Gemeine: ይህ ቃል «ማኅበረ ምእመናን»፣ «ማኅበረ ሰብ» ወይም «ሁሉም በኅብረት» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። Cf. Confession Concerning Christ's Supper (1528) (WA 26:506, 30-507; LW 37:367-68).

[124] ቀላል ማብራሪያ።

[125] ይህ የሉተርን የራሱን አባባል ለመምሰል የቀረበ ነው። WA 35:580 ተመልከት።

[126] በ1529 እንደ ተለየ በራሪ ወረቀት ደግሞ የታተመው ይህ ጽሑፍ በ1529 ተጀምሮ፣ እንዲሁም በ1580 በታተመ ቢያንስ በአንድ የመጽሐፈ ስምምነት እትም በሉተር የሕይወት ዘመን በታተሙ የትንሹ የክርስትና ትምህርት አብዛኞቹ እትሞች ተካትቶአል። ይህ ትርጉም የተመሠረተበት የእንግሊዝኛ ትርጉም በLW 53:110-15 (WA 30/3: 74-80) ይገኛል።

[127] Geistliche: ሉተር ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መነኮሳት የተለመደ ቃል ይጠቀማል።

[128] እዚህና በዚህ በራሪ ጽሑፍ ውስጥ ሁሉ መጽናት፣ «የሕይወት መንገድ» ማለት ነው።

ምንም መሠረት የሌለው የሰው ፈጠራ ቢሆንም) እንዲህ ያለ ትልቅ ትዕይንት ስለ አደረጉ፣ እግዚአብሔር የወደደውን ይህንን የጋብቻ ጥምረት ምን ያህል አብልጠን ልናከብረው፣ ልንጸልይለትና ከፍ ባለ ክብር ልናስውበው ይገባናል። ምክንያቱም ምንም እንኳ ምድራዊ ቢሆንም፣ ከጐኑ የእግዚአብሔር ቃል አለው፤ እንዲሁም እንደ መነኮሳቱ የሰው ፈጠራ ወይም ተቋም አይደለም።[129] ስለዚህ በሥጋና በደም የተፈጠረና የተቋቋመ፣ እንዲሁም ፍጹም ከዓለማዊ አእምሮና ማስተዋል ውጪ በመሆኑ ምክንያት፣ በእርግጥ ዓለማዊና ሥጋዊ ከሆኑት ነገሮች ሁሉ በላይ ሆኖ መቈጠር ስለ አለበት በቀላሉ ከምንኵስና ሥርዓት ይልቅ መቶ ጊዜ ብልጫ ያለው መንፈሳዊ ተደርጎ መቈጠር አለበት።

4 ወጣቶች ይህን ሥርዓት አጥብቀው የሚከታተሉበትን ሁኔታ ለመማር እንዲችሉ፣ ይህንን ባልተለመዱ መንገዶች በሳቅ፣ በማሾፍ፣ በማፌዝና በመሳሰለው ቅብጠት ሳይሆን በከፍተኛ ክብር እንደ መለኮታዊ ሥራና ትእዛዝ እንዲይዙ ማድረግ አለብን። ጋብቻ መፈጸም ወይም ሰርግ መደገስ ቀልድ ወይም የሕፃናት ጨዋታ ይመስል እስካሁን ድረስ የተለመደ ሆኖአል። በመጀመሪያ ሙሽራንና ሙሽሪትን ወደ ቤተ ክርስቲያን የማምጣትን ልማድ የመሠረቱ ሰዎች በእርግጥ እንደ ቀልድ ቈጥረውት ሳይሆን እንደ ጥብቅ ጒዳይ አድርገውት ነበር።[130] ምክንያቱም የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበልና የማኅበረሰቡን ጸሎት[131] ፈልገው እንጂ፣ ነገር ግን ለጨዋታ ወይም ለአረማዊ ቀልድ እንዳልመጡ ጥርጥር የለውም።

5 ሥነ ሥርዓቱ ራሱ ይህንን ግልጽ ያደርጋል። ምክንያቱም ከቄሱ ወይም ከጳጳሱ[132] ጸሎትና ቡራኬ የሚፈልጉ ሁሉ በጣም በግልጽ ቢናገሩትም ወይም ባይናገሩትም፣ በዚያ ምክንያት፣ ለምን አደጋና ችግር ራሳቸውን እያጋለጡ እንደ ሆኑና እየገቡበት ላሉት ሁኔታ የእግዚአብሔርን በረከትና የማኅበረ ሰቡን ጸሎት ምን ያህል እንደሚፈልጉ ያመለክታሉ። ምክንያቱም በየቀኑ ዲያብሎስ ምን ያህል በጋብቻ ሁኔታ ላይ በምንዝርና፣ ታማኝነትን በማጒደል፣ በብጥብጥና በሁሉም ዓይነት ችግር ምክንያት እየፈጠረ ሰላም እንደሚነሣ በልምድ እናያለን።

ስለዚህ (በሚፈልጉበትና በሚጠይቁበት ጊዜ) ሙሽሪትዋንና ሙሽራውን በሚከተለው መንገድ ለማስተናገድ እንፈልጋለን።

6 በመጀመሪያ ከምስባኩ በሚከተሉት ቃላት የጋብቻ ሥርዓትን[133] አውጅ፦

«ዮሐንስና ማርያም[134] በእግዚአብሔር ድንጋጌ መሠረት ወደ ቅዱስ ጋብቻ ለመግባት፣ በእነርሱ ፊንታ በእግዚአብሔር ስም ይጀምሩትና ይሳካላቸው ዘንድ የምእመናንን ጸሎት ይፈልጋሉ። እንግዲህ ማንም ሰው ይህንን በመቃወም የሚለው አንዳች ነገር ካለ፣ እርሱ ወይም እርስዋ በዚህ ጊዜ ይናገሩ ወይም ከዚህ በኋላ ጸጥ ይበሉ። እግዚአብሔር በረከቱን ይስጣቸው። አሜን።»

7 በቤተ ክርስቲያን ፊት በሚከተሉት ቃላት የቃል ኪዳን መሐላ[135] ይለዋወጡ፦

«አንተ ዮሐንስ፣ ማርያም የቃል ኪዳን ሚስትህ እንድትሆን ትፈልጋለህ?»

«አዎን» ብሎ ይመልስ።

«አንቺ ማርያም፣ ዮሐንስ የቃል ኪዳን ባልሽ እንዲሆን ትፈልጊአለሽ?»

---

129 ለተመሳሳይ ትችት፣ The Estate of Marriage (1522) (WA 10/2: 275-304; LW 45:17-49) እና The Judgement of Martin Luther on Monastic Vows (1521) (WA 8: 573-669; LW 44:245-400) የሚሉትን ደግሞ ተመልከት።

130 ከ"Sermon at Marriage of Sigismund Von Lindenau" (1545) (WA 49:802, 11-22; LW 51:363f.) ጋር አነጻጽር።

131 ሉተር የሚያስበው በማኅበረ ሰብ አምልኮ የሚደረገውን አጠቃላይ ጸሎት ነው።

132 ሉተር በከተማ ያለውን ዋና ቄስ ጳጳሱ ነው ብሎ ጠርቶአል። ለምሳሌ፦ 1Timothy (1528) (WA 26:49, 5-51, 9; LW 28:281-84); Answer to the Hyperchristian ... Book (1521) (WA 7:630,10-632,19; LW 39:154-56); and Instruction of the Visitors (1528) (WA 26:196,1-197, 10; LW 40:269-71), እንዲሁም SC, «መቅድም» 1 እና «የቤተ ሰብ ሠንጠረዥ» 2 የሚሉትን ደግሞ ተመልከት።

133 ሉተር ስለ መተጫጨት ስላለው ዐስተሳሰብ፣ On Marriage Matters (1530) (WA 30/3:224, 32-225, 29; LW 46:290 እና ተከታዩን) የሚሉትን ተመልከት።

134 ጽሑፉ Hans und Greta ተብሎ የሚነበበው ለባልና ሚስት የተለመደ ስም ነው፣ የሉተር የራሱ ወላጆችም ስም ነው።

135 ከመተጫጨት በኋላ ወዲያው ጋብቻ እንዲፈጸም ሉተር አምኖአል። የቃል ኪዳን ልውውጥ የመንግሥት ሕግ እንደ ሆነ ይቈጠር ስለ ነበር፣ በቤተ ክርስቲያን በር ላይ ይፈጸም ነበር።

«አዎን» ብላ ትመልስ፡፡

8 እዚህ ላይ የቃል ኪዳን ቀለበቶቻቸውን ሲለዋወጡ ቀኝ እጃቸውን ያጣምሩ፣ እንዲህም በላቸው፡-

«እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው፡፡»[136]

9 ከዚያ በኋላ ቄሱ ለተሰበሰቡት ሁሉ እንዲህ ያስታውቅ፡-

«ስለዚህ ዮሐንስና ማርያም እርስ በርሳቸው በጋብቻ ስለ ተፈላለጉና ይህንኑ እዚህ በእግዚአብሔርና በዓለም ፊት በይፋ ስለ መሰከሩ፣ ይህንንም፣ ለማጽናት እርስ በርሳቸው እጆቻቸውንና የቃል ኪዳን ቀለበት ስለ ተሰጣጡ፣ እኔ በእግዚአብሔር አብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በጋብቻ መጣመራቸውን አስታውቃለሁ፡፡ አሜን፡፡»

10 «በመሠዊያው[137] ፊት ቄሱ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘፍጥረት 2[፡18፣21-24] በሙሽራውና በሙሽሪት ዘንድ ያንብብ፡፡

«እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት[138] እንፍጠርለት፡፡ እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍን ጣለበት አንቀላፋም ከጐኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው፡፡ እግዚአብሔር አምላከም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት፡፡ አዳምም አለ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል፡፡ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡»

11 ከዚያ በኋላ ቄሱ ወደ ሁለቱ ዞሮ እንዲህ ይበል፡-

«እናንተ ሁለታችሁም በእግዚአብሔር ስም ወደ ጋብቻው ጥምረት ገብታችኋልና
12 ይህንን ጥምረት በሚመለከት ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስሙ፡- ቅዱስ
ጳውሎስ[139] እንዲህ ይላል፡-

«ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን[140] እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፣ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት[141] የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ፡፡ እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል፡፡ የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፣ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፣ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል ይከባከበውማል፡፡

13 «ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፣ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፡፡ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፡

14 ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር በዚህ የጋብቻ ጥምረት ላይ[142] የጫነውን መስቀል ደግሞ ስሙ፡- ለሴቲቱም እግዚአብሔር አለ፡-

«በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጂያለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል እርሱም ገዢሽ ይሆናል፡፡»

እንዲሁም ለወንዱም እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡-

---

[136] ማቴዎስ 19፡6፡፡

[137] ይህ የአምልኮ አገልግሎት መጀመርን ያመለክታል፡፡

[138] ከ1536ቱ የሉተር የክርስትና ትምህርት እትም ጋር ጽሑፉ ሉተር የተረጎመው የ1534ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ እትም ይከተላል፡፡ ቀደምት ጽሑፎች «የእርሱ ጓደኛ የሚሆነው» ተብለው ይነበባሉ፡፡

[139] ኤፌሶን 5፡25-29፤ 5፡22-24፡፡

[140] Gemiene ቃል በቃል «ማኅበረ ምእመናን» የሚለው የጀርመንኛ ቋንቋ በምንባቡ ሁሉ ይዘልቃል፡፡

[141] ከ1536 በፊት፡- «ለራሱ ክብርት ቤተ ክርስቲያንን አቀረበ፡፡»

[142] ዘፍጥረት 3፡16-19፡፡

«የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ካንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ እሾህና አሜከላን ታበቅልብሃለች የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና።»

15 ሦስተኛ፣ ይህ የጋብቻ ጥምረትህ በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል እንደሚያስደስትህና እንደሚባርክህ ስታውቅና ስታምን መጽናኛህ ይሆናል። እንዲህ ተጽፎአልና።[143]

«እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ። በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።» «እግዚአብሔርም ዐየ፤ የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደ ሆነ ዐየ።»

ስለዚህ ሰሎሞን ደግሞ እንዲህ ይላል፡-[144] *«ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ፣ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል።»*

16 እዚህ ላይ ቄሱ በእነርሱ ላይ እጆቹን ዘርግቶ እንዲህ ይጸልይ፡-[145] ጌታ እግዚአብሔር፣ ወንድንና ሴትን የፈጠርህና ለጋብቻ ጥምረት የመደብህ በሆዳቸውም ፍሬ የባረክሃቸውና በውድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ምሥጢርና የእርሱ ሙሽራ በሆነችው ቤተ ክርስቲያንህ[146] ያመለከትህ፡- ይህ የአንተ ፍጥረት፣ ድንጋጌ፣ እንዲሁም በረከት እንዲወገድ ወይም እንዲበላሽ እንዳትፈቅድ፣ ነገር ግን በቸርነትህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመካከላችን እንድትጠብቀው ከቶ የማያልቀውን መልካምነትህን እንለምናለን። አሜን።

## በጀርመንኛ የተተረጎመውና በዐዲስ መልክ የተሻሻለው[147]
## የጥምቀት ሥነ ሥርዓት መጽሐፍ

### ማርቲን ሉተር

*ለክርስቲያን አንባቢያን ሁሉ ፡- በጌታችን በክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይሁን።*

1 በሁሉም ረገድ ስላለው ትኩረት ያለ መስጠት ሁኔታ ምንም ሳይባል፣ ሰዎች በምን ግዴለሽነትና እርጋታ በጐደለው አኳኋን እዚያ የተገኙት በከፊል ምን እየተባለና እየተደረገ እንዳለ ምንም ያለ መረዳታቸው እውነት ነው ብዬ አምናለሁ፣ ከፍተኛውን፣ ቅዱሱን፣ እንዲሁም የሚያጽናናውን የጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር ለሕፃናት እንደሚያከናውኑ በየዕለቱ የማይና የምሰማ ስለ ሆነ፣ አገልግሎቱን በጀርመንኛ ማካሄድ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ መሆኑን ደግሞ ወስኛለሁ። በዚህ ምክንያት በጀርመንኛ ማጥመቅን ለመጀመር፣ አቅራቢዎቹና

---

[143] ዘፍጥረት 1፡27 እና 1፡31።

[144] የምሳሌ 18፡22 ማብራሪያ። ከ1536 በፊት ጽሑፉ «ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ፣ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል» በማለት ይነበባል።

[145] የሚከተለው ጸሎት በሉተር ጊዜ ከሠርግ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት የተወሰደ የተለምዶ ጸሎት ነው።

[146] Kirchen. ሉተር ጋብቻን እንደ ቅዱስ ምሥጢር አልተመለከተውም፣ ነገር ግን ቃሉ ኤፌሶን 5፡32ን በመጥቀስ ቩልጌት የግሪኩን Mysterio በwith sacramentum በሚተረጕምበት በተለምዶ ጸሎት የሚገኘውን ይጠቀማል። WA 6:550, 22-552, 27 (LW 36:92-95) ተመልከት።

[147] በመካከለኛው ዘመን የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ላይ የተመሠረተው የጥምቀት መጽሐፍ በመጀመሪያ በ1523 (WA 12:42-48; LW 53:95-103 የታተመ ነበር። እዚህ ላለው ጽሑፉ መሠረት የሆነው በ1526 ሁለተኛ እትም ተዘጋጅቶ ነበር (WA 19:537-41; LW 53:106-9 ከ 101-3 ጋር)። በ1529 የትንሹ የክርስትና ትምህርት እትም በሁለተኛ ጊዜ እና ሉተር በሕይወት እያለ በዊተንበርግ በታተሙ ተከታታይ እትሞች ጠቅላላ ሂደት ላይ፣ እንዲሁም በአንዳንድ የ1580 የመጽሐፈ ስምምነት እትሞች ተካትተዋል። ይህ ትርጕም በLW 53 ላይ የተመሠረተ ነው።

ሌሎች የተገኙ በይበልጥ ለእምነትና ልባዊ ለሆነ ታማኝነት እንዲነሣሡ እንዲሁም የሚያጠ
ምቁት ቀሳውስት ለአድማጮቹ ሲባል የበለጠ ትጋት ያሳዩ ዘንድ በላቲን[148] ሲባሉ የነበሩትን
እነዚያን ክፍሎች ተርጕሜአለሁ።
2 ክርስቲያናዊ በሆነ ራስን የመስጠት ስሜት የሚያጠምቁ፣ ሕፃናትን[149] ለሚያቀርቡ
ወይም ጥምቀትን ለሚመሰክሩ እዚህ ያለውን ታላቅ ሥራና መረጋጋት ልብ እንዲሉ አቤቱታ
አቀርባለሁ። ምክንያቱም እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ የጸሎት ቃሎች በማዘንና
በቅንንነት በፊቱ በመናዘዝ በእነዚህ በማይለወጡና ጥርጣሬ በሌለባቸው ቃላት ሕፃኑ በሰይጣን
ከተያዘበት የኃጢአትና የቍጣ ልጅ ከሆነበት በጥምቀት ይፈታና የእግዚአብሔር ልጅ ይሆን
ዘንድ እርዳታና ጸጋ በመለመን እንዴት ወደ እግዚአብሔር እንደምታቀርበው ትሰማለህ።
3 ስለዚህ፣ እንዲህ ዓይነት ኃይለኛና የዕድሜ ልክ ጠላት የሆነውን ዲያብሎስን የመቃወም
እርምጃ መውሰድ እምቦቃቅላውን ሕፃን ከእርሱ መንጠቅ ብቻ ሳይሆን በሕፃኑ አንገት ዙሪያ
ወዲያና ወዲህ ማለቱ ቀልድ አለመሆኑን መረዳት ይገባሃል። በመሆኑም በፍጹም ልብህና በጠ
ንካራ እምነት ከልጁ ጋር መቆም እጅግ አስፈላጊ ነው፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በእነዚህ
የጸሎት ቃላት መሠረት ሕፃኑን ከዲያብሎስ ሥልጣን ነጻ እንደሚያወጣ ብቻ ሳይሆን ሕፃኑን
እንዲያጠነክረው ልጁ በሕይወትና በሞት እርሱን በኃይል እንዲቋቋመው በትልቅ ታማኝነት
4 መማለድ ያስፈልጋል። ከጥምቀት በኋላ ሰዎች ክፉኛ ወደ ኋላ ይመለሳሉ የሚል ስጋት አለኝ፣
ምክንያቱም በእንዲህ ዓይነት ቀዝቃዛና ግዴለሽ በሆነ መንገድ ለእነርሱ የነበረን አያያዝና
በጥምቀታቸው ጊዜ ያለ ውስጣዊ ተነሣሽነት ጸሎት አድርገንላቸዋል።
5 ደግሞም ልብ በል፣ በጥምቀት ጊዜ ከዓይኑ በታች እፍ ማለት፣ በመስቀል ምልክት
ማማተብ፣ በአፉ ጨው ማድረግ ወይም መትፋትና በጆሮና በአፍንጫ ሽክላ ማድረግ፣ ጡትና
ትከሻን ዘይት መቀባት፣ ራስን ቅባ ቅዱስ መቀባት፣ የክርስትና ልብስ ማልበስ፣ የሚበራ ሻማ
በሕፃኑ እጅ ማድረግ፣ ጥምቀትን ለማስጌጥ በሰው የተጨመረ ማንኛውም ነገር የመሳሰሉት
ውጪአዊ ሥነ ሥርዓቶች ይህን ያህል አስፈላጊ አይደሉም። ምክንያቱም ከእነዚህ ነገሮች
አንዱም ሳይኖር በእርግጥ ጥምቀት ሊከናወን ይችላል፤ እንዲሁም ዲያብሎስ የሚያፈገፍግባቸው
ወይም የሚሸሽባቸው እውነተኛ መሣሪያዎች አይደሉም። እርሱ ከእነዚህ የሚበልጡትን ትልልቅ
ነገሮች እንኳ ያንኳስሳል! እዚህ ላይ በእውነት ለነገሮች ክብደት ሊሰጣቸው ይገባል።
6 በዚህ ፈንታ፣ በእውነተኛ እምነት እዚያ መገኘትህን፣ የእግዚአብሔርን ቃል
መስማትህን፣ እንዲሁም ከልብ መጸለይህን አረጋግጥ። ምክንያቱም የትም ቢሆን ቄሱ
«እንጸልይ» ሲል፣ ከእርሱ ጋር እንድትጸልይ እያደፋፈረህ ነው። በተጨማሪ፣ አቅራቢዎቹና
በዚያ የተገኙት ሁሉ በልባቸው ከእርሱ ጋር የጸሎቱን ቃሎች ለእግዚአብሔር መናገር
7 ይኖርባቸዋል። በዚህ ምክንያት፣ አቅራቢዎቹ የሕፃኑን ፍላጎት ከሙሉ ልብ በእግዚአብሔር ፊት
ይዘው በመቅረብ፣ በሕፃኑ ስም ባላቸው ኃይል ሁሉ ዲያብሎስን በመቃወም፣ እንዲሁም
ለዲያብሎስ ቀልድ ላልሆነው ነገር ክብደት መስጠታቸውን በማሳየት ሊሰሙአቸውና
ሊረዱአቸው ይችሉ ዘንድ፣ እንዲሁም ደግሞ በልባቸው በአንድ ዐሳብ ከቄሱ ጋር መጸለይ
ይችሉ ዘንድ ቄሱ እነዚህን ጸሎቶች በግልጽና በዝግታ መናገር አለበት።
8 በዚህ ምክንያት ሰካራሞችና ምግባረ ብልሹ ቀሳውስት እንዳያጠምቁ ወይም ምንም
የማይጠቅም የክርስትና አባት እንዳይመርጡ መከልከል ትክክልና ተገቢ ነው። በዚህ ፈንታ፣
ይህ ከፍተኛ ቅዱስ ምሥጢር ለዲያብሎስ ማላገጫ እንዳይተውና በዚህ ቅዱስ ምሥጢር ሰፊና
የጸጋው የተትረፈረፈ ብልጽግና በእኛ ላይ የሚያሳየውን የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያጎድል፣
በጥብቅና በእውነተኛ እምነት ጉዳዩን ለማከናወን የሚጠበቁ መልካም፣ ግብረገብ ያላቸው፣
ጥብቅ፣ ትክክለኛ ቀሳውስትና የክርስትና አባቶች ሊመረጡ ይገባል። እርሱ ራሱ «ዐዲስ
ልደት»[150] በማለት ይጠራዋል፤ በእርሱም ከዲያብሎስ አገዛዝ ነጻ የምንወጣበትና ከኃጢአት፣

---

[148] ዘመም ተደርጎ የተጻፈው ጽሑፍ የሚገኘው በ1523ቱ እትምና በመጽሐፈ ስምምነት ብቻ ነው። የትንሹ የክርስትና ትምህርት እትሞች በቀላሉ «እነዚህ ነገሮች» አሉአቸው። በሮማውያን ሥነ ሥርዓት ብቻ ለአቅራቢዎች ጥያቄዎችና መልሶቻቸው በላቲን አልነበሩም።

[149] Kinder heben: በቀጥታ ትርጕም ሕፃናትን ከማጥመቂያ ማውጣት። ከዚህ በታች ያለውን የአገልግሎት ደንብ ተመልከት። ቄሱ የጥምቀት ልብስ ለሕፃኑ ሲያለብስ አቅራቢዎቹ ሕፃኑን በማጥመቂያው ላይ መያዝ አለባቸው።

[150] ዮሐንስ 3፡3-5።

ከሞትና ከሲኦል የምንፈታበት፣ ሕያዋን ልጆች፣ የእግዚአብሔር ርስት ሁሉ ወራሾች፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የክርስቶስ ወንድሞችና እኅቶች እንሆናለን።[151]

9 ውድ ክርስቲያኖች፣ ቃል የማይገልጸውን ይህንን ስጦታ በግማሽ ልብ እንደ ዋዛ አንቀኊጠረው ወይም አናስተናግደው። ምክንያቱም ጥምቀት መጽናኛችንና ለእግዚአብሔር ንብረቶች ሁሉ እንዲሁም ለቅዱሳን አንድነት በር ነው። ለዚህ ዓላማ እንድንበቃ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

11 አጥማቂው እንዲህ ይላል፡-[152]

«አንተ ርኲስ መንፈስ ሂድ፣ ለመንፈስ ቅዱስም ስፍራውን ልቀቅ።»

12 ከዚህ በኋላ በራስ ላይና በጡት ላይ በመስቀል ምልክት አማትቦ እንዲህ ይላል፡-

«በራስ ላይና በጡት ላይ ይህን ቅዱስ የመስቀል ምልክት ተቀበል።»

«እንጸልይ፡-»

13 «ሁሉን ቻይና ዘላለማዊ አምላክ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የጥምቀትህን ስጦታ በሚለምነውና በመንፈሳዊ ዳግም ልደት ዘላለማዊ ጸጋህን በሚፈልገው በዚህ አገልጋይህ በ ..... ስም ወደ አንተ እጣራለሁ፣ ጌታ ሆይ፣ ተቀበለው[153] እንዲሁም፣ «ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ፣ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል»[154] እንዳልከውም ይህንን የሰማያዊ መታጠብ[155] ዘላለማዊ በረከት ያገኝና በጌታችን በክርስቶስ በኩል ተስፋ የተሰጠውን መንግሥት ይቀበል ዘንድ ለሚለምንህ አሁን በረከትህን ስጠው፣ መዝጊያን ለሚያንኳኳም ክፈትለት። አሜን።

«እንጸልይ፡-

14 በጥብቅ ፍርድህ የማያምነውን ዓለም በጥፋት ውሃ የኰነንህና በታላቅ ምሕረትህ የሚያምነውን ኖኅንና የቤተ ሰቡን ሰባት አባላት ያዳንህ፣ እንዲሁም ፈርዖንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር የጣልህ ሕዝብህንም እስራኤልን በዚሁ ባሕር በየብስ መርተህ ያሻገርህ፣ በዚያ ምክንያት ይህን መታጠብ ለቅዱስ ጥምቀት ምሳሌ ያደረግህ፣ በውድ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዮርዳኖስንና ውሃን ሁሉ የተባረከ ሞልቶ የሚፈስስ እንዲሆን የቀደስህና የከፈልህ እንዲሁም ከኃጢአት መታጠብን ያደረግህ ሁሉን ቻይ ዘላለማዊ አምላክ፡- ሞልቶ በሚፈስሰው በዚሁ በአንዱ ማዳን ከአዳም በእርሱ የተወለደው ሁሉና በዚያ ላይ እርሱ የጨመረው ማንኛውም ነገር በእርሱ ይሰጥምና ይዘቅጥ ዘንድ፣ ከማያምኑት ቊጥር በመለየትም በቅዱሱ የቤተ ክርስቲያን መርከብ ደረቅና ዋስትና ያለው ሆኖ ይጠበቅ ዘንድ፣ በተስፋህ ከሚያምኑ ሁሉ ጋርም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት የተገባ ይሆን ዘንድ፣ ስምህን ለማገልገል ሁልጊዜ በመንፈስ የሚቃጠልና በተስፋ ደስ የሚለው እንዲሆን .......ን በቸርነትህና ወሰን በሌለው ምሕረትህ እንድትመለከተውና በእውነተኛ እምነት በመንፈስ ቅዱስ እንድትባርከው እንለምንሃለን። አሜን።

15 «አንተ ርኲስ መንፈስ፣ ከዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ከ...... እንድትወጣና እንድትሄድ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አዝሃለሁ።[156] አሜን።

«የቅዱስ ማርቆስን ቅዱስ ወንጌል እንስማ፡-[157]

16 «እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው።[158] ኢየሱስ ግን ዐይቶ ተቈጣና፡- ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ

---

[151] በቀጥታ ትርጒም፡- «ወንድሞች።»

[152] ይህ ክፍል በትንሹ የክርስትና እምነት «በቅዱስ ጥምቀት ምሥጢር» ፊት ጥቅም ላይ በዋለው በተመሳሳይ ከእንጨት ተፈልፍሎ በተሠራ ሥዕል የታጀበ ነው።

[153] ሉተር በሁሉም ስፍራ ለሚጠመቀው ሰው በተባዕታይ ተውላጠ ስም ይጠቀማል።

[154] ማቴዎስ 7፡7።

[155] ቲቶ 3፡5።

[156] የመስቀሉ ምልክት በሕፃኑ ላይ ሦስት ጊዜ ተማትቦአል።

[157] ማርቆስ 10፡13-16። ለመጀመሪያ ጊዜ ሉተር የተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1536 እትም ጋር ጽሑፉ ይስማማል። እስከዚያ ድረስ ጽሑፉ በትንሹ የክርስትና ትምህርት ነጻ ትርጒም ነበር፣ ምናልባትም በላቲን ቩልጌት ላይ የተመሠረተ ነበር።

[158] መጽሐፈ ስምምነትና የ1536ቱ እትም «ተወሰደ» በማለት ይነበባሉ።

የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው፡፡ አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው፡፡»

17 ከዚያ በኋላ ቄሱ እጁን በሕፃኑ ራስ ላይ ጭኖ ከተንበረከኩት አቅራቢዎቹ ጋር የጌታን ጸሎት ይጸልያል፡- «አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፡፡ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፡፡ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ፡፡» አሜን፡፡

18 ከዚህ በኋላ ሕፃኑ ወደ ማጥመቂያው[159] ይመጣና ቄሱ እንዲህ ይላል፡-

«ጌታ መግባትህንና መውጣትህን ይጠብቅ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፡፡»[160]

19 ከዚህ በኋላ ቄሱ በአቅራቢዎቹ በኩል ሕፃኑን እንዲህ በማለት ዲያብሎስን እንዲክድ ያደርጋል፡-

20 «ስም.....! ዲያብሎስን ትክዳለህን?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

21 «ሥራዎቹን ሁሉ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

22 «መንገዶቹን ሁሉ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

ከዚያም እንዲህ ይጠይቃል፡-

23 «ሁሉን በሚችል፣ ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ ታምናለህ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

24 «በተወለደና መከራ በተቀበለ፣ በአንዱ ልጅ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ታምናለህ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

25 «በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን አንድነት፣[161] በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣ ከሞት በኋላ ባለ በዘላለም ሕይወት ታምናለህ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

26 «ለመጠመቅ ትፈልጋለህ?»

መልስ፡- «አዎን፡፡»

27 በዚህን ጊዜ ሕፃኑን ወደ ማጥመቂያው ወስዶ በማጥመቅ እንዲህ ይላል፡-

28 «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ፡፡»

29 ከዚያም አቅራቢዎቹ ሕፃኑን በማጥመቂያው ላይ ይይዛሉ፤ ካህኑም የጥምቀት ልብሱን ለሕፃኑ እያለበሰው እንዲህ ይላል፡-

30 «ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በውሃና በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ የወለደህ፣ ኃጢአትህን ሁሉ ይቅር ያለህ ለዘላለም ሕይወት በጸጋው ያበርታህ፡፡ አሜን፡፡

31 «ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን፡፡»

መልስ፡- «አሜን፡፡»[162]

---

159 በመካከለኛው ዘመን ሥነ ሥርዓት መሠረት፣ ሰይጣንን ማውጣት በቤተ ክርስቲያን በር ላይ፣ እንዲሁም የቀረው አገልግሎት በማጥመቂያ ላይ ይደረጋል፡፡

160 መዝሙር 121፡8፡፡

161 በቀጥታ ትርጉም፡- «ቅዱሳን፡፡»

162 የተለያዩ የትንሹ ክርስትና ትምህርት እትሞች ደግሞ ሌላ ጽሑፍን ይጨምራሉ፡፡ በሉተር ሕይወት ዘመን በዊተንበርግ የታተሙ እትሞች በ1529 ተካተዋል፡- The German Litany (WA 30/3: 29-36; LW 53:163-69); በ1536, 1537, እንዲሁም 1539: the German Te Deum and the Magnificant (WA 35:458-59; LW 53:171-79); በ1543: A Prayer against the Turks (WA 51:608, 6/24-610, 15/34; LW 43:232-33).

# ትልቁ የክርስትና ትምህርት

## ለትልቁ የክርስትና ትምህርት የአርታዒያን መግቢያ

በትልቁ የክርስትና ትምህርት ውስጥ የሚገኙት ጽሑፎች ሉተር ስለ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በሰበካቸው ስብከቶች የተገኙ ናቸው። አስቀድሞ ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአንዳንድ የጀርመን ክልላዊ ሲኖዶሶች የክርስትና ትምህርት በዐሠርቱ ትእዛዛት፣ በሐዋርያት የእምነት መግለጫ፣ በጌታ ጸሎት፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ [የሮማ ካቶሊካውያን ውዳሴ ለማርያም] በሚሉ ርእሶች ተከፋፍለው ስብከት እንዲካሄድ ጥሪ ያደርጉ ነበር። ከዐቢይ ጾም አንደኛ እሑድ ቀጥሎ ያለው ረቡዕ፣ ዓርብ ወይም ቅዳሜ፣ በቤተ ክርስቲያን ዘመን አቈጣጠር አራት ጊዜ የሚደረገው ጾም በዚህ ምክንያት ይካሄድ ነበር። ከተሐድሶ በፊትም ቢሆን እንኳ የዊተንበርግ ከተማ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይህን ልማድ የተከተለ ይመስላል። ሉተር ራሱ ከ1518 መባቻ ጀምሮ በተለያዩ የክርስትና ትምህርት ክፍሎች ላይ ይሰብክ ነበር።[1]

በ1520ዎቹ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዋና ቄስ ዮሐንስ ቡገንሀገን ያለ ጥርጥር ይህንን ልማድ ቀጥሎአል። ቡገንሀገን በ1528 የብራውንሽዌግን ከተማ ለማደስ ለጊዜው በሄደበት ወቅት ረዳት ሰባኪው ሉተር የክርስትና ትምህርት ማስተማሩን ጨምሮ የባልደረባውን ሥራ ተረክቦ ነበር። በዚህ ጊዜ በሦስት ተከታታይ የከሰዓት በኋላ ስብከቶች ላይ የተወሰዱ የአድማጮች ማስታወሻዎች (ከግንቦት 18 እስከ ኅዳር 30፣ ከመስከረም 14 እስከ መስከረም 25 እና ከኅዳር 30 እስከ ታኅሣሥ 18) እስከ ዛሬ ድረስ አሉ።[2] እነዚህ ስብከቶች በሉተር ስብከቶችና በክርስትና ትምህርት ይዘቶች መካከል የነበረውን አስደናቂ ተመሳሳይነት ከማሳየትም አልፈው የአሰባበክ ስልቱንም ለማብራራት ያግዛሉ።

የትልቁ ክርስትና ትምህርት ኅትመት ወይም አታሚዎች እንደሚሉት የጀርመኑ ክርስትና ትምህርት የታተመው የጠለቀ ዕውቀትና በቂ የሆነ ትምህርት ያላገኙ ቄሶችን በመሠረታዊ እምነት ማሠልጠን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነበር። በ1527 የበጋ ወራት የሳክሶኒው የንጉሡ ነገሥቱ መራጭ በግዛቱ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን የሚጎበኝ ቡድን ሾመ። የቡድኑ አባላት ከቤተ መንግሥት ሁለት፣ ከዩኒቨርስቲ ሁለት (አንድ ከሕግ፣ አንድ ከሥነ መለኮት) የተውጣጡ ሲሆን ተልእኮአቸውም ሰበካዎችና ካህናቱ የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብና አካላዊ ፍላጎታቸውን ማጥናትና በእነዚህ ግዛቶች  የሚሰጠው የክርስትና ትምህርት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማጥናት ነበር። ከሥነ መለኮት ፋኩልቲ የመጀመሪያው ተወካይ በመሆን ያገለገለው ፊሊፕ ሜላንክተን የካህናትንና የሰባኪዎችን የሥነ መለኮት የዕውቀት ደረጃ መገምገሚያ ቅጽ በላቲን ቋንቋ ያዘጋጀ ሲሆን እርሱም «የጉብኝቱ አንቀጽ» *Visitation Articles* (*ቪዚቴሽን አርቲክልስ*) ተብሎ ይጠቀስ ነበር። ሜላንክተን፣ ሉተርና ቡገንሀገን የሚገኙበት የሥነ መለኮት ልዑካን ቡድን በላቲን የተጻፈውን መመሪያ በጀርመንኛ በመተርጎምና በማስተካከል በሳክሶኒ ግዛት በሚገኙ ካህናት ጎብኚዎች የተዘጋጀ መመሪያ ሆኖ በ1528 መጀመሪያ ላይ ታትሞ ወጣ።[3]

ይህ ሰነድ ጠቃሚ የሆነ የተሐድሶ ትምህርትና ልምምድ ሰነድ ሆኖ ቢያገለግልም ጠ ቃሚነቱን የሚያሳንሱ ተቺዎች አልታጡለትም ነበር። ገና ከጅምሩ በ1527 ዮሐንስ አግሪኮላ የሚባለው የሉተር ተማሪ የነበረውና በአይስሌበን ከተማ የላቲን ትምህርት ቤት ዲሬክተር ሆኖ በማገልገል ላይ የነበረው ሰው በላቲን የተዘጋጀውን ሰነድ እና ደራሲውን

---

[1] *ለምሳሌ ላልተማሩ ሰዎች የተዘጋጀውን የጌታን ጸሎት ማብራሪያ* ተመልከት (1519) (WA 2:80-130; *LW* 42:15-81), እንዲሁም *በዐሠርቱ ትእዛዛት ላይ የተሰጠውን ስብከት፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫና የጌታን ጸሎት የያዘ* A Personal Prayer Book (1522) (WA 10/2: 375-406: *LW* 43.5-45).

[2] WA 30/1: 2-122 ለሦስተኛው ተከታታይ ትርጉም፣ LW 51:135-93 ተመልከት።

[3] WA 26:195-240; *LW* 40: 265-320; የ*LW* ትርጉም ርእስን ማረም።

ሜላንክተንን ተቃውሞ ነበር። የአግሪኮላ አቋም እውነተኛ ንስሓ ቅጣትን ከመፍራት ሳይሆን እግዚአብሔርን ከመውደድ ብቻ መውጣት አለበት የሚል ነበር። (ይህ ወንጌልን ከሕግ ያስቀደመ አቋም ነው)። ሉተር ግን ንስሐ እግዚአብሔርን ከመፍራትና ከመውደድ የሚወጣ እንደ ሆነ በማሳየት ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ላይ ያለን አጠቃላይ እምነት ደግሞ ንስሐን የሚቀድም ነው ቢባልም፣ እምነት ንስሐ መግባትን ተከትሎ የሚመጣ ክስተት ነው ብሎ ማሰቡ የተሻለ ነው በማለት ሁለቱንም የሚያካትት አስታራቂ ቋንቋ ሰጥቶአል።

አግሪኮላ ብዙዎቹን ዐሳቦቹን የሚያንጸባርቁለትን ሦስት የታወቁ የክርስትና ትምህርቶች አዘጋጅቶ ነበር። ሜላንክተን ደግሞ በሳክሶኒ ቤተ መንግሥት ያገለግል በነበረው በጆርጅ እስጠላቲን በመደፋፈር ለአግሪኮላ መጻሕፍት ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉና ዋና የሆኑትን የክርስትና ትምህርት ክፍሎችን ማብራራት ጀመረ። ሉተር ራሱ በ1528 መጨረሻ ላይ የራሱን የክርስትና ትምህርት መጻፍ ስለ ጀመረ ሜላንክተን ሦስተኛው ትእዛዝ ላይ ደርሶ ሥራውን አቋረጠ። ሉተርም ለዐሥርቱ ትእዛዛት ስለ እምነት፣ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድን አስመልክቶ የሰጠው ስፍራና ማብራሪያ የሚያመለክተው ቀደም ሲል በአግሪኮላና በሜላንክተን መካከል የነበረውን ክርክር በሚመለከት አቋሙን የሚያሳይ ነበር።

እንዲሁም ትልቁ የክርስትና ትምህርት ካህናት ትምህርት እንዲያገኙበት ታስቦ ተጨማሪ ትምህርቶች የቀረቡበት ነው። ሉተር ትልቁን የክርስትና ትምህርት መጻፍ የጀመረው በመስከረም 1528 ሁለተኛውን የክርስትና ትምህርት ካጠናቀቀ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ነበር። ተከታታይ ከሆኑት ስብከቶቹ ሦስተኛውን ስብከት በታኅሣሥ ከፈጸመ በኋላ የመጨረሻዎቹን እነዚህን ስብከቶች መሠረት በማድረግ ሁለተኛውና ሦስተኛውን ትእዛዛት በተመለከተ ከለሳቸው። አንደኛውን ትእዛዝና የትእዛዛቱን ማጠቃለያ አስመልክቶ የጻፋቸው ጽሑፎች ቀድሞውኑ ታትመው ስለ ነበር በእነዚህ ትእዛዛት ላይ ዐዲስ አስተያየት ጨምሮ በትእዛዛቱ ክፍል መጨረሻ ላይ አደረጋቸው።[4] በጥር ወር ላይ ትልቁ የክርስትና ትምህርት እስከ ጌታ ጸሎት ተጠናቆ ነበር። በዚያን ጊዜ ግን ሉተር ታሞ ስለ ነበረ እስከ መጋቢት ማለቂያ ድረስ ሥራውን አቋረጠ። እንደ ገና የትልቁን ክርስትና ትምህርት ሥራውን ሲጀምር በሕማማቱ ሳምንት ከመጋቢት 21 እስከ 27 1529 ከሰበከው ስብከት ጋር ተገጣጠመለት። በዚያ ሳምንት በእምነት መግለጫና በጌታ ጸሎት ላይ የሰበካቸው ስብከቶች በትልቁ የክርስትና ትምህርት ባሉት በእነዚህ ርእሶች ላይ ትልቅ ተጽእኖ አሳድረዋል።[5]

የሉተር የጀርመንኛው የክርስትና ትምህርት በሚያዝያ፣ 1529 አጋማሽ ላይ ወጣ። ወዲያውኑ ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው የሕማማቱ ሳምንት ስለ እምነት መግለጫ በተሰበከው ስብከት ላይ የተመሠረተውን ክፍል በመጨመርና የጌታ ጸሎት መግቢያን ሰፋ አድርጎ በማብራራት ሥራውን አሻሻለ።[6] አታሚው ጆርጅ ራው ከሉቃስ ክራንች የሥራ መደብር በእንጨት ላይ ተፈልፍለው የተሠሩ ምስሎችን ጨመረባቸው።[7] መጽሐፉ በ1530 ሲወጣ ምናልባትም በኦግስቡርግ ጉባኤ በኮቡርግ ግንብ በቆየበት ወቅት ያዘጋጀውን ረጅም መቅድም ለመጀመሪያ ጊዜ ይዞ ወጣ።[8] በሉተር የሕይወት ዘመን የታረመው የ1538ቱ ኅትመት የመጨረሻው ኅትመት ሲሆን እርሱም በራሱ በሉተር የተደረጉ መለስተኛ እርማቶችን ያካተተ ነበር። በቪንሰንት ኦብሶፖውስ የተዘጋጀው የላቲኑ ትርጉም ደግሞ በ1529 ወጣ። ተርጓሚው ከጥንታዊ ታሪክ ዘመን የማይሸራቸው ጥቅሶችንና ፍንጮችን በማከል በላቲናዊ ዘይቤ ለዕይታ የሚሆን ነገር አስገኘ። ይህ ታትሞ የወጣው መጽሐፍ

---

[4] ትልቁን የክርስትና ትምህርት «ዐሥርቱን ትእዛዛት» 1-48 (በተለይ 30-48) ከ311-33 ጋር አነጻጽር።

[5] WA 29:132- 381። ለእነዚህ ስብከቶች ትርጉም የዶክተር ማርቲን ሉተርን የ1529ኙን የሕማማት ሳምንትና የፋሲካን ስብከቶች ተመልከት። Trans. Irving S. Sandberg (St. Louis: Concordia 1999), 29- 79.

[6] LC “Lord’s Prayer” 10-11 ተመልከት።

[7] በእንጨት ላይ ተፈልፍለው ስለ ተሣሉት ሥዕሎች በትንሹ የክርስትና ትምህርት የተሰጠውን ማስታወሻ ተመልከት።

[8] ቀጥሎ ባለው ክፍል ገጽ 583-88 ተመልከት።

ካሳደራቸው ተጽእኖዎች አንዱ በጆን ካልቪን ኢንስቲቲዩትስ ኦፍ ዘ ክርስቲያን ሪሊጅን *(Institutes of the Christian Religion)* መጀመሪያ እትም ላይ ነው።

ከ1580 ጀምሮ መጽሐፈ ስምምነቱ የሉተርን የክርስትና ትምህርት በማከል በዘመኑ *corpora doctrinae* ኰርፖራ ዶክትሪኔ (የመሠረተ እምነት መስፈርት አካላት) ከሆኑት ብዙ ምሳሌዎችን በመከተል አንዱ ሆኖ ወጣ። እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊያውቀው የሚገባውን አስፈላጊ ትምህርት ስለሚሰጥ በአብዛኛው ዜጋ ዘንድ የክርስትና ትምህርት መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚወክሉ ተደርገው ይወሰዱ ነበር።[9] መጽሐፈ ስምምነት ደግሞ የሁለቱን መቅድሞች ቅደም ተከተላቸውን ያለዋወጠውና የግል የኃጢአት ኑዛዜን ያስቀረው የጄናውን የሉተር ሥራዎች በምንጭነት ተጠቅሞአል። በተቃራኒው የአሁኑ ትርጉም የተሻሻለውንና የተብራራውን ሁለተኛውን የ1529ኙን ኅትመት ይዘት ይከተላል።

## የዶክተር ማርቲን ሉተር ትልቁ [የጀርመኑ] ክርስትና ትምህርት

### የማርቲን ሉተር መቅድም[1]

1 *ለክርስትና ትምህርት[2] ትኩረት የምንሰጠውና ሌሎችም ትኩረት እንዲሰጡት አበክረን የምናበረታታውና የምንለምነው ያለ ምክንያት አይደለም። ብዙ ሰባኪዎችና ቄሶች[3] አገልግሎታቸውንና ይህንን ትምህርት ችላ የሚሉ ሆነው መታየታቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ይህንንም የሚያደርጉት አንዳንዶች ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ መሆናቸው ስለሚሰማቸው የክርስትና ትምህርትን መናቃቸው ሲሆን፣ አንዳንዶች ደግሞ ከስንፍናና ከሆዳምነታቸው የተነሣና በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አገዛዝ ዘመን ያደርጉት እንደ ነበረ ሁሉ አሁንም የምድሪቱን በረከት ለኑሮአቸው ማሟያ ብቻ አድርገው በመመልከታቸው ነው።*

2 *በአሮጌዎቹ መመሪያዎች የነበረውና «ራሳቸውን የሚሰብኩ ሰብከቶች» «ጥሩ እንቅልፍ ይኑርህ» «ተዘጋጅ» እና «ቴሳውሮስ»[4] በሚሉ ርእሶች የተሰጠው ትምህርት ቀላል በሆነው መንገድ ተዘጋጅቶ በብዛት በሚገኙ መጻሕፍት ቀርቦላቸዋል። አሮጌዎቹ መመሪያዎች ግን ትክክለኝነትና ታማኝነት የሌለባቸው ስለ ሆኑ የእነዚህን መጻሕፍት ያህል ዋጋ የላቸውም። ቢኖራቸውም እንኳ የክርስትና ትምህርትን ማጥናትና ማንበብን ያህል አይደለም። እነዚህ አሳፋሪና የሆዳቸው[5] አገልጋዮች የሆኑ ቄሶች መንፈሳዊ መሪዎች ከሚሆኑ የአሳማና የውሻ አርቢ በመሆን ኑሮአቸውን ቢመሩ ይሻላል።*

3 *እንግዲህ ቄሶችና ሰባኪያን ዋጋ ከሌለውና አስጨናቂ ከሆነ የሰባት ሰዓታት[6] መነባንብ ነጻ ስለ ሆኑ በየጠዋቱ፣ በየቀትሩና በየምሽቱ አንድ ወይም ሁለት ገጾችን ከክርስትና ትምህርት፣ ከጸሎት መጽሐፍ፣[7] ከዐዲስ ኪዳን ወይም ከአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለራሳቸውና ለሰበካዎቻቸው አባላት ቢያነቡና የጌታን ጸሎት ቢጸልዩ መልካም ነው። በዚህ መንገድ ከብዙ ሸክምና ችግር ነጻ የወጡበትን ወንጌል ሊያከብሩና በባለውለተኝነት መንፈስ እንደ አሳሞችና ውሾች ከዚህ ገዳይ፣ አስነዋሪና ምድራዊ ነጻነት*

---

[9] AP ደንብና ሥርዓት 5ን እና SD ደንብና ሥርዓት 8ን ተመልከት።

[1] ከ1530 ጀምሮ ለሰባኪዎችና ለቄሶች የተዘጋጀው ይህ ረጅም መቅድም በመጽሐፈ ስምምነት የተቀመጠው አጭሩን የ1529 ቅደም ተከተል የሚከተል ሲሆን እርሱም በ1556 በጄና የታታመው የጀርመንኛ የሉተር ሥራዎች አራተኛው መጽሐፍ ቅደም ተከተልን ተከትሎ በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት በ1580 የታተመውን ነው።

[2] ሉተር «የክርስትና ትምህርት» የሚለውን ቃል የሚጠቀመው እንደ መጽሐፍ አርእስት ሳይሆን በሃይማኖት ትምህርት ጊዜ የሚሰጠውን ትምህርት ለማመልከት ነው።

[3] ሰባኪዎች (Prediger) ለስብከት አገልግሎት የሚጠሩ ሲሆን ቄሶች (Pfarrherren) ደግሞ በተጨማሪ ሌሎችን አገልግሎቶች ለመፈጸም የሚሾሙትን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን ያመለክታል።

[4] በመካከለኛው ክፍል ዘመን በስፋት የተሰራጩ የስብከት መጻሕፍት አርእስቶች።

[5] ይህ ሂስ ወይም ነቀፋን የሚያመለክት ቃል በተሐድሶ ዘመን ከሮሜ 16፡18 የተወሰደ ቃል ነው።

[6] በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የተለመደው የየዕለቱ ጸሎት።

[7] ከሮማ ካቶሊክ የጸሎትና መንፈሳዊ ጽሑፎች መጽሐፍ በተጨማሪ እንዲያገለግል ሉተር በ1522 ያሳተመው *የግል ጸሎት መጽሐፍ* (WA 10/2: 375-501; LW 43;3-45

4 ይልቅ ወንጌልን ባለማስታወሳቸው ሊያፍሩ ይገባቸዋል፡፡ ተራው ሕዝብ ወንጌልን ሲያቃልል
ትልቁ ጥረታችን ዋጋ አጥቶአል፡፡ ታዲያ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ የአገዛዝ ዘመን እንደ ታየው
ሁሉ ዛሬም ሰነፎች የምንሆን ከሆነ እኛ ምን እንጠብቃለን?
5 ከዚህም ሌላ በአስፈሪና ተንኮል በተመላበት በራስ የመተማመን ወረርሽኝና
መሰላቸት ተወረናል፡፡ ብዙዎች የክርስትና ትምህርትን ቀላልና የማይረባ በአንድ ጊዜ ንባብ
ብቻ የሚረዱት አድርገው ይቈጥሩታል፡፡ አንድ ጊዜ ካነበቡ በኋላ ደግሞ ማንበቡ አሳፋሪ
6 የሆነባቸው ይመስላል፡፡ ወደ ጎንም ይወረውሩታል፡፡ በእርግጥ ከመኳንንቱ መካከል ሳይቀር
ከአሁን በኋላ ሁሉንም ነገር ከመጽሐፉ ስለምናገኝ ያለ ሰባኪ በራሳችን መማር እንችላለን
የሚሉ ሥርዓት አክባሪ መሳዮች ነገር ግን በየትኛውም መንገድ ቢሆን ገንዘብን ለራሳቸው
የሚያከማቹ ደግሞ አሉ፡፡ ደስ እያላቸውም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንዲፈራርሱ
ሲያደርጉ ቄሶችና ሰባኪያን እንዲራቡም ይተውአቸዋል፡፡[8] ይህም አእምሮ ከጐደላቸው
ጀርመኖች የሚጠበቅ ድርጊት ነው፡፡ እኛ ጀርመኖች እንደዚህ ዓይነት አሳፋሪና አብረናቸው
መኖር የማንችል ሰዎች በመካከላችን አሉን፡፡
7 ነገር ግን ሌሎቹ በጣም ተምረናል ከፍ ባለ ስፍራ የምንገኝ ኃያላን ነን እንደሚሉ
ሁሉ እኔም ዶክተርና ሰባኪ ነኝ እላለሁ፡፡ የሆነ ሆኖ የክርስትና ትምህርትን እንደሚማር
አንድ ልጅ በየጠዋቱና በተመቸኝ ጊዜ ሁሉ የጌታን ጸሎት፣ ዐሥርቱን ትእዛዛት፣ የእምነት
8 መግለጫን፣ መዝሙረ ዳዊትንና የመሳሰሉትን ቃል በቃል አጠናለሁ፡፡ እስከ አሁንም ድረስ
በየዕለቱ የክርስትና ትምህርትን ማንበብና ማጥናት እንደሚኖርብኝ ዐስባለሁ፡፡ ይሁንና
እንደምመኘው ሙሉ በሙሉ ላውቀው ስለ ማልችል እንደ አንድ ትንሽ ልጅ የክርስትና
ትምህርት ተማሪ ሆኜ መቅረብ ይኖርብኛል፡፡ ይህንንም የማደርገው በደስታ ነው፡፡[9] እነዚህ
ምንም የማይረቡ ቅምጥሎች ግን በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ ሊታወቁ የሚገባቸውን ሁሉ
ያወቁ የዶክተሮች ዶክተር ሊሆኑ ይወዳሉ፡፡ ይህም አገልግሎታቸውን፣ የሕዝባቸውን ነፍስ
በእርግጥም እግዚአብሔርንና ቃሉን የመናቅ ምልክት ነው፡፡ መውደቅን አይፈሩም
አስቀድሞውኑ ከፋኛ ወድቀዋልና፡፡ እነዚህ አስቀድመን ያደግን ነን ባዮች[10] ግን ልክ እንደ
ልጆች ሆነው ሀ፣ ለ፣ ሐን መማር ያስፈልጋቸዋል፡፡
9 ስለዚህ እነዚህን ሰነፍ ሆዳሞችንና ተጠራጣሪ ቅዱሳን መሳዮች የሚመስላቸውን ያህል
በእውነት ያወቁና ታላላቅ ዶክተሮችም እንዳልሆኑ እንዲያስቡ ስለ እግዚአብሔር
እለምናቸዋለሁ፡፡ ይህንንም የክርስትና ትምህርት ክፍል ደኅና አድርገው የሚያውቁ
ቢመስላቸውም በበቂ ሁኔታ እንዳልተማሩና እንዳላወቁ እንዲያስቡ እለምናቸዋለሁ፡፡
የክርስትና ትምህርት ዕውቀታቸው እንከን ባይወጣው እንኳ (ይህ በምድር ባይቻልም)
ይህንን መጽሐፍ በየዕለቱ ማንበብና የመንፈሳዊ ተመስጦአቸው እና የውይይቶች አርእስት
ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ንባብ፣ ውይይትና ተመስጦ መንፈስ ቅዱስ ስለሚኖር
ዐዲስና ታላቅ ብርሃንን እንዲሁም የማድነቅ መንፈስን ስለሚሰጠን በክርስትና ትምህርት
ጥናታችን በየዕለቱ ይበልጥ ጣዕም ያለውና ከሰውነት የተዋሃደ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም
ክርስቶስ በማቴ 18፡20፦ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው
እገኛለሁ» በማለት በሰጠን የተስፋ ቃል መሠረት ነው፡፡

---

[8] ሉተር *ሐንስውርትን በመቃወም* (1541) (WA 51; 486, 27-33: *LW* 41:198-99)፡፡በእርግጥ እንዲሁ የምንጾም ሳንሆን (ከቅዱስ ከጳውሎስ ጋራ [1ቆሮ 4፡11]) በረሃብ እንሰቃያለን፡፡ በመራባቸው የሚያፈጡባችሁ የብዙ አገልጋዮች፣ የሚስቶቻቸውና የልጆቻቸው ዐይኖች በየቀኑ ይታያሉ፡፡ ያላቸው ዳቦና ውኃ እጅግ ጥቂት ሲሆን የሚለብሱትን ከማጣታቸው የተነሳ እንደ ቁራ እርቃናቸውን ይሄዳሉ፡፡ የኔ ነው የሚሉት ምንም ነገር የላቸውም፤ ገበሬውና የከተማ ነዋሪዎች ምንም አይሰጡአቸውም፡፡ መኳንንቶቹ ያላቸው ጥቂቶች ብቻ እንዲሆኑ ሁሉን ለራሳቸው ሲወስዱ ሌሎችን መርዳት አንችልም ይላሉ፡፡

[9] ይህ ሰፊ የትልቁ ክርስትና ትምህርት መግቢያ ተባባሪዎቹ በኦግስቡርግ ስብሰባ በመሳተፍ ላይ ሳሉ በ1530 በኮቡርግ በሉተር የተጻፈ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም «ለምሳሌ ይህንን ለሁሉም ሰው እገልጻለሁ፡፡ ይኸውም አረጋዊ የሥነ መለኮት ዶክተርና ሰባኪ መሆኔን እገልጻለሁ፡፡... ቢሆንም እንደ አንድ ትንሽ ልጅ ሆኜ የጌታን ጸሎት፣ ዐሠርቱን ትእዛዛት፣ የእምነት መግለጫንና የተመረጡትን የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች ልክ ልጆችን በምናሰለጥንበት መንገድ በየቀኑ የማጠናቸው ሲሆን ዘመኔን ሁሉ የክርስትና ትምህርት ተማሪ ሆኜ እቀጥላለሁ» ብሎ በመዝሙረ ዳዊት 117 (WA 31/1: 227, 13-22: *LW* 14;8) ላይ የጻፈው የትርጉም መጽሐፍ ነው፡፡

[10] ቃሉ እንዳለ ቢወሰድ «ጫማቸውን የቀደዱ» የሚል ምሳሌአዊ አባባል ዓይነት ነው፡፡

10 *በእግዚአብሔር ቃል አእምሮን መሙላትን፣ ስለ ቃሉ መነጋገርንና ማሰላሰልን
የመሰለ ዲያብሎስን፣ ዓለምን፣ ሥጋንና ክፉ ዐሳብን የመቃወሚያ ውጤታማ መንገድ
የለም። መዝ 1[፡2] ቀንና ሌሊት የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያስቡትን «ምስጉኖች» ብሎ
ይጠራቸዋል። ዲያብሎስን ለማሸነፍ ሁለንተናህን በእግዚአብሔር ትእዛዛትና ቃላት
ማስወረስን፣ ስለ እርሱም መናገርንና ማሰላሰልን የሚያህል የምስጋና ዕጣን ወይም የበለጠ
ጣፋጭ ሽታ ያለው ነገር ማቅረብ አይቻልም። በእርግጥ ዲያብሎስን የሚነቅልና የሚያባርር
እውነተኛው ቅዱስ ውሃና ምልክት ይህ ነው።*[11]
11 *ከዚህ የምታገኘው ጥቅም የሰይጣንን ክፉ ዐሳብ ለመንቀል ስለ ሆነ የክርስትና
ትምህርትን በጉጉት ማንበብ ደጋግሞ ማንበብ፣ ማሰላሰልና መለማመድ ይኖርብሃል።
ምክንያቱም ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና መቋቋም አይችልም።
የእግዚአብሔር ቃል እንደ በርኑ*[12] *ዴትሪሽ ባዶ ታሪክ ሳይሆን ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 1፡16
«የእግዚአብሔር ኃይል» በእርግጥም የዲያብሎስን ቤት*[13] *የሚያቃጥልና ለእኛ ሊለካ
የማይችል ኃይል፣ መጽናናትንና እርዳታን የሚሰጠን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።*
12 *ቃላትን ለምን አባክናለሁ? ከእግዚአብሔር ቃል የሚፈልቀውን በረከት ሁሉ
ብቈጥር ጊዜንና ወረቀትን ከየት አገኛለሁ? ዲያብሎስ የሺዎች ጥበብ አለቃ ነው። ታዲያ
ይህንን የሺዎች ጥበብ አለቃ የሚነቅለውንና የሚያባርረውን የእግዚአብሔርን ቃል ምን
ብለን እንጥራው? በተለይ እኛ ቄሶችና ሰባኪዎች የሆንን ይህንን ጉልበታም በረከት የተሞላ
13 ኃያልና ፍሬአማ የሆነውን ቃል በቧልተኝነት እንናቀውን? እንዲህ የምናደርግ ከሆነ ምግብ
መከልከል ብቻ ሳይሆን በውሾች ከቤት ልንባረርና ፍግ ልንበላ ይገባናል። የእግዚአብሔር
ቃል እንደ እንጀራ በየዕለቱ የሚያስፈልገን ብቻ ሳይሆን በየዕለቱ የሚገጥመንን ዲያብሎሳዊ
ውጊያና ደፈጣ ከሺህ ጥበቦቹ ጋር ለመቋቋም ልንጠቀምበት ያስፈልገናል።*
14 *ይህን የክርስትና ትምህርት በየዕለቱ ለማንበብ ሊገሥጸን የማይበቃ ከሆነ ደግሞ
ሊያበረታታን የሚገባ ሌላ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አለ። ምክንያቱም በዘዳግም 6[፡7-8]
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስንቀመጥ፣ ስንራመድ፣ ስንቆም፣ ስንተኛ፣ ስንነሣ፣ በዐይናችን
በእጆቻችን እንደ ቋሚ ምልክት አድርገን እንድንይዘው ታዝናል። እግዚአብሔር ያለ በቂ
ምክንያት ይህንን እንድናደርግ አይፈልግብንም፤ አያዝንም። የሚገጥመንን ተከታታይና
አስፈሪ አደጋ፣ እንዲሁም የዲያብሎስን ሽንገላ ያውቃል። ስለዚህ ሊያስጠነቅቀን፣ ጥሩ
የጦር ዕቃ ሊያስታጥቀንና እንዲሁም ከሚንበለበለው ፍላጻ*[14] *ሊከላከልልን፣ መርዙና
ምርቀዛው እንዳያገኘን የመከላከያ ክትባት የሆነውን ቃሉን ሊሰጠን ይፈልጋል። አ! ምን
15 ያህል ዕብዶች፣ ግድ የለሾችና ሞኞች ነን? ኃይለኞች በሆኑት ጠላቶቻችን አጋንንት
መካከል የምንኖር፣ ነገር ግን የጦር ዕቃዎቻችንን የምንንቅና ለእርሱም ግምት የማንሰጥ
እጅግ ሰነፎች ነን።*
16 *እነዚህ የክርስትናን ትምህርት ሊያጠኑ የማይፈልጉ የተሰላቹና ኩሩ ቅዱሳን ነን
ባዮች ከእግዚአብሔር ከራሱ፣ ከቅዱሳን መላእክቱ፣ ከነቢያቱ፣ ከሐዋርያቱና ከሁሉም
ክርስቲያኖች በላይ ራሳቸው ዐዋቂ እንደ ሆኑ የሚያስቡ ምንድን ናቸው? ነገር ግን
እግዚአብሔር ራሱ ከማስተማር የተሻለ ወይም የተለየ እንደሌለ ስለሚያውቅ ይህንን
በክርስትና ትምህርት የተገለጠውን እውነት ምንም ልዩነት ሳያደርግ ማስተማሩን
ይቀጥላል። እንዲሁም ቅዱሳን ሁሉ (ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ አጠናቀው ማወቅ ወይም
መማር ባይችሉም) ከዚህ የተለየና የተሻለ የመማሪያ መንገድ እንደሌለ ያውቃሉ። እኛስ
አንድ ጊዜ በማንበብ ወይም በመስማት ሁሉን ያወቅንና ደግመን ማንበብና ማጥናት*

---

[11] የተቀደሰ ውሃ ክፉ መናፍስትን ያስወጣል ይባል ስለነበረ አጋንንትን ለማውጣት ያገለግል ነበር።

[12] የበርኑ ዴትሪችን አፈ ታሪኮች ሉተር የውሸት ምሳሌ አድርጎ ብዙ ጊዜ ይጠቅሳቸዋል። የበርኑ ዴትሪች በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የጀርመኖች አፈ ታሪክ ውስጥ ታላቁን የኦስትሮጎዝ ንጉሥ ለማወደስ የሚያገለግል ስም ነበር።

[13] ይህን አባባል ሉተር ሁልጊዜ የሚጠቀምበት ሲሆን የመጀመሪያው ትርጉም ግን «አንድ ሰው የሌላን ሰው ንብረት በእሳት ማውደምን» ያመለክታል።

[14] ኤፌ 6፡11 እና 16።

እንደሚያስፈልገን የሚሰማን ሰዎች አስገራሚዎች አይደለንምን? እግዚአብሔር ራሱ በአንድ
ሰዓት አስተምሮ የማይጨርሰውን እኛ በአንድ ሰዓት አንብበን ሁሉንም እንረዳለን ብለን
ማሰባችን አስገራሚ ነው:: እግዚአብሔር ከፍጥረተ ዓለም እስከ ፍጻሜ ድረስ በማስተማሩ
ሥራ የሚተጋ ሲሆን ነቢያት ሁሉና ቅዱሳን ደግሞ ለመማር ሲተጉ ዘመናቸውን በሙሉ
እንደ እግዚአብሔር ተማሪ ሆነው ኖረዋል፤ እንደዚህ ሆነው መቀጠልም ይገባቸዋል::

17 ዐሥርቱ ትእእዛዛትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ያውቃል፣
እነርሱንም የሚያውቅ ሰው መንፈሳዊና ምድራዊ ጕዳዮችንና ሁኔታዎችን አስመልክቶ
ሊመክር፣ ሊረዳ፣ ሊያጽናና፣ ሊዳኝ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፤ ይህን ያህል የተረጋገጠ ነው::
መሠረተ እምነትን፣ የሕይወት ልምምድን[15]፣ ሰዎችን፣ ሕጎችንና በዓለም ያሉ ሌሎችንም
18 ነገሮች ሊገመግምና ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል:: በተጨማሪም መዝሙረ ዳዊት ሙሉ በሙሉ
የመጀመሪያውን ትእዛዝ ማሰላሰልና መለማመድ አይደለምን? እኔ ያለ ምንም ጥርጥር
እነዚህ ሰነፎችና አጉል ደፋር ሰዎች ሙሉውን ቅዱሳት መጻሕፍት ቀርቶ ከመዝሙራት
አንዱን እንኳ ዐያውቁም እላለሁ:: ነገር ግን ዐዋቂዎች በመምሰል የቅዱሳት መጻሕፍትን
ትምህርት ዋና ነገርና አጠቃሎ የያዘውን የክርስትና ትምህርት ይንቃሉ::

19 ስለዚህ ክርስቲያኖችን ሁሉ በተለይ ቄሶችንና ሰባኪዎችን ገና ሳያድጉ ዶክተሮች
ወይም ዐዋቂዎች ነን ሁሉንም ነገር ዕናውቃለን እንዳይሉ እንደ ገና እለምናቸዋለሁ፤ (ከንቱ
ዐሳብ እንደ ዐዲስ ልብስ እየጠበበ ይሄዳል!)[16] ክርስቲያኖች ሁሉ በየቀኑ በክርስትና
ትምህርት ራሳቸውን እንዲያሠለጥኑና ሳያቋርጡ እንዲለማመዱት እንዲሁም በታላቅ
ጥንቃቄና ትጋት ከእንዲህ ዓይነቱ መርዛማ ዋስትናና እብሪተኝነት ራሳቸውን ይጠብቁ::
ማንበቡን፣ ማስተማሩን፣ መማሩንና ማሰላሰሉን ይቀጥሉ:: ዲያብሎስን እስከ ሞት ድረስ
እስኪያስተምሩትና እነርሱም ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ ይልቅ የተማሩ እንደ ሆኑ በልምድ
እስኪያረጋግጡና እርግጠኞች እስኪሆኑ ድረስ ይቀጥሉ::

20 እንዲህ ያለውን ትጋት ቢያሳዩ ልምምዳቸው ፍሬ እንደሚኖረው፣ ብዙ ጥቅምም
እንደሚያገኙበትና እግዚአብሔርም ታላላቅ ሰዎች አድርጎ እንደሚያስነሣቸው ተስፋ
እሰጣቸዋለሁ::: አብዝተው የክርስትና ትምህርትን ባጠኑ ቍጥር ከትምህርቱ ጥቂቱን ብቻ
እንደሚያውቁና ብዙ መማርም እንደሚገባቸው አምነው ይቀበላሉ፤ እንዲህ ባደረጉ ጊዜ
ሁሉም ነገር ስለ ተሟላላቸውና ከአቅም በላይ በመንጠራራታቸው አሁን ሊያሸቱት
የማይፈልጉትን ነገር የክርስትና ትምህርትን በደንብ ባወቁ ጊዜ በደስታ ለመቀበል ጥማትና
ጉጉት ይኖራቸዋል:: ወደዚህም እንድንደርስ እግዚአብሔር ጸጋውን ይስጠን:: አሜን::

## መቅድም[17]

1 ይህ ስብከት ልጆችንና ያልተማሩትን ለማስተማር የተዘጋጀ ነው:: ስለሆነም ከጥንት
ጀምሮ በግሪክ ቋንቋ «ካቲኪዝም» ማለት የልጆች መምሪያ (የክርስትና ትምህርት) ተብሎ
2 ሲጠራ ቆይቶአል::[18] እያንዳንዱ ክርስቲያን ማወቅ ያለበትን ይዞአል:: አንድ ሰው ለሙያው
የሚገባው ዕውቀት ሳይኖረው ሲቀር ሙያው እንደሚናቅ ሁሉ የክርስትና ዕውቀትንም

---

[15] ለሉተር፣ *Stande* (“estates”, “station” or “walks of life”) የማኅበረሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች ሲሆኑ እነርሱም ቤተሰባዊ፣ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ናቸው:: እያንዳንዱ የአኗኗር ዘይቤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠው ሥራና ኃላፊነት አለው::

[16] ምሳሌአዊ አባባል::

[17] ይህ በግንቦት 18 ቀን 1528 ስብከት ላይ የተመሠረተ የ1529 የመጀመሪያው አጭር መቅድም ነበር::

[18] በግሪክ ቋንቋ ካቴኪስሞስ የሚለው ስም ካቴኬይን ከሚለው ግሥ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም እንደገና መናገር ወይም ድምፅ ማሰማት ነው:: ስለሆነም ማስተማር ማለት ነው:: በመጀመሪያ ይህ ቃል በቃል የሚሰጠውን የክርስትና እምነት ትምህርት የሚያመለክት ሲሆን እርሱም በጥያቄና በመልስ የተዘጋጀና የክርስትና ትምህርት ተማሪዎች ከመጠመቃቸው በፊት እንዲያውቁት ይፈለግባቸው የነበረ በኋላ ላይ ግን ይህ ቃል እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት ለሚቀርብበት መጽሐፍ የተሰጠ ስያሜ ነው::

የማያውቅ ሰው ክርስቲያን እንዳልሆነና ወደ ቅዱስ ምሥጢሩ[19] መቅረብ እንደሌለበት
3 ሊቈጠር ይገባል፡፡ በዚህም ምክንያት ወጣቶች ልዩ ልዩ የክርስትና ትምህርት ክፍሎችን
ወይም የልጆችን መምሪያ ሊማሩና በትጋትም ሊለማመዱት ይገባል፡፡
4 ስለዚህ የቤተሰቡ ኃላፊ ልጆቹንና አገልጋዮቹን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ምን
ያህል የክርስትና ትምህርትን እንደሚያውቁ ማረጋገጥ ሲኖርበት ባያውቁ ግን ትምህርቱን
5 በትጋት እንዲቀጥሉ ማድረግ አለበት፡፡ ምንም የማያውቁ አረጋውያን (በእርግጥ ዛሬም
በየዕለቱ እናያቸዋለን) ወደ ቅዱስ ምሥጢር ሲመጡና በሁሉም የክርስቲያን መብቶች ተጠ
ቃሚ ሲሆኑ በደንብ አስታውሳለሁ፡፡ አሁን ወደ ቅዱስ ምሥጢር[20] የሚመጡ ግን ከልጆችና
ከጀማሪዎች የተሻለ ሊያውቁና ስለ ክርስትና አስተምህሮ የተሟላ መረዳት ሊኖራቸው
6 ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ያልቀሰሱ ምእመናን ከጥንት ጀምሮ የክርስትና ቅርስ የሆኑት ሦስቱ
ክፍሎች[21] (በእርግጥ በትክክል የሚማሩትና የሚይዙት በጥቂቱ ቢሆንም) በቂ ናቸው፤
ያውም በእውነት ክርስቲያን ለመሆን የሚፈልጉና በስም ብቻ ክርስቲያን የሆኑ ወጣቶችም
ሆኑ አረጋውያን ሁሉ በደንብ እንዲረዱትና እንዲያውቁት ነው፡፡ እነርሱም የሚከተሉት
ናቸው፡-[22]

*አንደኛ፡- ዐሥርቱ የእግዚአብሔር ትእዛዛት*[23]

1 አንደኛው፡- ሌሎች አማልክት በፊቴ አይኑሩህ
2 ሁለተኛው፡- የአምላክህን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ
3 ሦስተኛው፡- የእረፍት ቀንን ትቀድሰው ዘንድ ዐስብ[24]
4 አራተኛው፡- አባትህንና እናትህን አክብር
5 አምስተኛው፡- አትግደል
6 ስድስተኛው፡- አታመንዝር
7 ሰባተኛው፡- አትስረቅ
8 ስምንተኛው፡- በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር
9 ዘጠነኛው፡- የባልንጀራህን ቤት አትመኝ
10 ዐሥረኛው፡- የባልንጀራህን ሚስት አሽከሩንና ገረዱን ከብቶቹን ማናቸውንም አትመኝ[25]

11-12 *ሁለተኛ፡- የእምነታችን ዋና አንቀጾች*

እኔ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡
ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊ
ጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት
በተነሣ፣ ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ ከዚያም
13 በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡ ደግሞም

---

[19] ይህ የሉተር ሀሳብ ብቻ የነበረ ሳይሆን የመካከለኛው ክፍለ ዘመንም መመሪያ ነበር፡፡

[20] የመካከለኛውን ክፍለ ዘመን ልማድ በመከተል ሉተር «ቅዱስ ምሥጢር» ሲል የጌታን እራት ያመለክት ነበር፡፡

[21] ዐሥርቱ ትአዛዛት፣ የእምነት መግለጫና የጌታ ጸሎት ይይዛል፡፡ በዊተንበረግ እስከ 1525 ድረስ ይሰጥ በነበረው የክርስትና ትምህርት ጥምቀትንና የጌታ እራትን አያካትትም ነበር፡፡

[22] እዚህ የቀረበው የአምስቱ ክፍሎች አባባል በትልቁ የክርስትና ትምህርት ውስጥ ካለው ጋር  አይመሳሰሉም፡፡ እንዲሁም ከትንሹ የክርስትና ትምህርት ወይም የሉተር የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር አባባሉ አይመሳሰልም፡፡

[23] ዘጸአት 20፡2-17፤ ዘዳግም 5፡6-21 ተመልከት፡፡

[24] *Feiertag* የሚለው የጀርመንኛ ቃል በተራ አባባል «የክብረ በዓል ቀን» ማለት ነው፡፡

[25] ሉተር ለትእዛዛቱ ቁጥር ሲሰጥ አሰጣጡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰቀሉ ሥዕላሥዕሎችንና በጌታ  እራት ውስጥ እውነተኛ የጌታ ሥጋ መኖሩን የተቃወሙት ኡልሪች ዝዊንግሊና ሌሎች የተሐድሶ ሥነ መለኮት ምሁራን  የተከተሉትን የዕብራውያንን መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን የተለመደውን የቩልጌት የቁጥር አሠጣጥን ነበር፡፡

በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣[26] በቅዱሳን አንድነት፣[27] በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ በዘለዓለም ሕይወት አምናለሁ:: አሜን::

*ሦስተኛ:- ክርስቶስ ያስተማረው ጸሎት ወይም አባታችን ሆይ*

14 *አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ:: አሜን::*[28]

15 እነዚህ ቃል በቃል ልንደግማቸው የሚገቡን እጅግ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው::
16 ልጆች ጠዋት ሲነሡ፣ ወደ ማዕድ፣ ወደ መኝታቸው ሲሄዱ እንዲደግሙአቸው እነዚህን
ክፍሎች መማር አለባቸው:: እነዚህን ክፍሎች እስኪያጠኑአቸው ድረስ ምንም ምግብና
17 መጠጥ ሊሰጣቸው አይገባም:: እያንዳንዱ የቤተሰብ ኃላፊ ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮቹንም
18 እነዚህን ክፍሎች ለመማር ፈቃደኞች ባይሆኑ ከቤት ሊያባርራቸው ይገባል:: እነዚህን
ክፍሎች ለመማር የማይፈልገውን ጋጠወጥ ወይም በጥባጭ በምንም መልኩ መታገሥ
አይገባም:: ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ያለው ሁሉ ግልጽ፣ አጭርና ቀላል ሆኖ
19 በእነዚህ ሦስቱ ክፍሎች ተገልጦአል:: በእርግጥ የተወደዱ አባቶች ወይም ሐዋርያት
(ማናቸውም ቢሆኑ)[29] የክርስቲያንን ንግግር፣ ጠባይና ትኩረት የሚቀርጽ ትምህርት፣
ሕይወትና ጥበብ አጠቃለው ሰጥተውናል::
20 አንድ ሰው እነዚህን ሦስቱን ክፍሎች ከተረዳ በኋላ ማቴዎስና ማርቆስ በወንጌላቸው
መጨረሻ እንደ ገለጹት ክርስቶስ ስላቋቋማቸው ቅዱሳት ምሥጢራት ማለትም ስለ
ጥምቀት፣ ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ደም ምን ማለት እንዳለበት ማወቁ ትክክለኛ ነው::
ይህም ቃል ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን የተሰናበተበትና የላከበት ቃል ነው::

21 *ስለ ጥምቀት*

«*እንግዲህ ሂዱ አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው*» … (*ማቴ* 28፡19) «*ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል::*»[30]

22 ለማንኛውም ሰው ስለ ጥምቀት ይህን ያህል ከመጽሐፍ ቅዱስ ካወቀ ይበቃል::
ሌላውም ቅዱስ ምሥጢር ቅዱስ ጳውሎስ እንዳቀረበው ይህንኑ በሚመስል ቀላል መንገድ
ሊጠና ይችላል::

23 *ስለ ቅዱስ ምሥጢር*

«ጌታችን ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፣ ቈርሶም:- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው::

---

[26] በ15ኛው ክፍል ዘመን የጀርመን ቤተ ክህነት አጠቃቀም *ecclesia catholica* የሚለውን የላቲን ቃል *cherisliche kirche* ብሎ መተርጎሙ የተለመደ ነበር:: ሉተርም የተከተለው ይህንኑ ልማድ ነበር::
[27] በጀርመንኛ Gemeinchaft ለሚለው Gumeine የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበትን ገጽ 435ን ተመልከት::
[28] ማቴዎስ 6፡9-13፤ ሉቃስ 11፡2-4ን ተመልከት::
[29] ሐዋርያት እያንዳንዳቸው አንዳንድ የእምነት መግለጫ አንቀጽን ጽፈዋል የሚለውን ልማዳዊ አባባል ለመቃወም ሉተር ፍላጎቱ አልነበረም::
[30] ማቴዎስ 28፡19፤ ማር 16፡16 (የሉተርን ትርጒም ተመልከት)::

«እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፡- ይህ ጽዋ ለኃጢአት ስርየት
ስለ እናንተ የሚፈስስ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን
ለመታሰቢያዬ አድርጉት»[31] አለ።
24 እንግዲህ ወጣቶቻችን ሊያጠኑአቸውና ቃል በቃል ሊይዙአቸው የሚገባቸውና
ሁሉንም የክርስትና አስተምህሮ አጠቃለው የያዙትን አምስቱን ክፍሎች አቅርበናል።
25 ወጣቶቻችን ይህንን ትምህርት ከስብከት ብቻ ይማሩታል ብላችሁ አታስቡ። እነዚህን
ክፍሎች ካጠኑ በኋላ ዕውቀታቸውን ለማጠንከር ከመዝሙረ ዳዊት ወይም ሕዝቡ
ከሚዘምራቸው መዝሙሮች[32] እንዲያጠኑ ስጡአቸው። በዚህም ዓይነት መንገድ ወጣቶቻችን
በየዕለቱ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀታቸው እየጨመረና እያደገ ይሄዳል።
26 ይሁን እንጂ፣ እነዚህን ክፍሎች ቃል በቃል ማወቃቸው ብቻ በቂ ሊሆን
አይችልም። ወጣቶቹ በተለይ በክርስትና ትምህርት የተጠቀሱትን[33] ትምህርቶች በተብራራ
መልኩ ለማግኘትና ለመማር እንዲችሉ የስብከት ፕሮግራሞችን መሳተፍና መስማት
ይኖርባቸዋል። ይህንን ባደረጉ ጊዜ አስቀድመው የሰሙትን ለመድገምና ለሚጠየቁት
ጥያቄዎች ጥሩና ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ይቻላቸዋል። እንዲህም ባደረጉ ጊዜ ስብከትን
27 መስማት ከንቱ እንዳልሆነ ይገነዘቡታል። በየጊዜው የክርስትና ትምህርትን ከባድ ሳይሆን
ቀላልና አጭር በሆነ መንገድ ለመስበክ ጥንቃቄ የምናደርግበት ምክንያት ትምህርቱ
28 በወጣቶቹ አእምሮ ጠልቆ እንዲገባ፣ ጸንቶም እንዲቆይና እንዲያስታውሱት ነው። ስለዚህ
ከዚህ በመቀጠል እላይ የተጠቀሱትን ክፍሎች በተቻለ መጠን ቀላል በሆነ መንገድ አንድ
በአንድ እናተኩርባቸዋለን።

## [ክፍል አንድ፡- ዐሥርቱ ትእዛዛት][34]

*የመጀመሪያይቱ ትእዛዝ*

1 «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ»
ይህም ማለት እኔን ብቻ እንደ አምላክህ አድርገህ ልትቈጥረኝ ይገባሃል ማለት
ነው። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ መረዳት ይቻላል? ሌላ አምላክን ማምለክ
ማለት ምን ማለት ነው? ወይም እግዚአብሔርን ማምለክ ምን ማለት ነው?
2 መልስ፡- «አምላክ» መልካምን ሁሉ እንደሚሰጠን በተስፋ የምንጠባበቀውና
በሚያስፈልገን ሁሉ መጠጊያ ሊሆነን እንደሚችል የምናምነው ነው። ስለዚህ አምላክ አለን
ማለት በዚያ አምላክ ነው ባልነው ነገር በሙሉ ልብ መደገፍና መታመን እንጂ ከዚያ
ወጪ ምንም ሊሆን አይችልም። አዘውትሬ እንዳልኩት አንድን አካል እግዚአብሔር ወይም
ጣዖት እንዲሆን የሚያደርገው የልብ መደገፍና ማመን ብቻ ነው። እምነትህና መደገፊያህ
3 ትክክል ከሆኑ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክህ ነው። በሌላ አባባል እምነትህ የተሳሳተ
ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክህ አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁለቱ ማለትም
እምነትና እግዚአብሔር አይነጣጠሉም። ልብህ አጥብቆ የሚደገፍበትና የሚተማመንበት
ማንኛውም ነገር እርሱ በእርግጥም እግዚአብሔር አምላክህ ነው እላለሁ።
4 ስለዚህ የዚህ ትእዛዝ ዓላማ ወደ አንዱ እውነተኛ አምላክ በቀጥታ የሚሸሸውንና
እርሱን ብቻ አጥብቆ የሚይዘውን እውነተኛ እምነትና የልብ መተማመንን መፈለግ ነው።
ይህ ማለት «እኔ ብቻ አምላካችሁ እንደ ሆንሁ አስቡ፤ ሌላ አምላክ ፈጽሞ አትፈልጉ»
ማለት ነው። በሌላ አባባል «ምንም ዓይነት መልካም ነገር ቢጎድልባችሁ ስለዚያ ነገር ወደ

[31] 1ቆሮ 11፡23-25 (የሉተር ትርጉም)።
[32] ሉተር ራሱ በክርስትና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስድስት መዝሙሮችን ጽፎአል።
[33] በ1533 በቤተ ክርስቲያን ደንብ መሠረት በዊተንበርግ በዓመት አራት ጊዜ በክርስትና ትምህርት ላይ እንዲሰበክ ይደረግ ነበር።
[34] ይህ አርእስት በ1580 መጽሐፈ ስምምነት ውስጥ የለም።

እኔ ተመልከቱ፤ ከእኔም ፈልጉት፤ አሳዛኝ ሁኔታና ጭንቀት ሁሉ ሲገጥማችሁ ቀስ ብላችሁ
ወደ እኔ ተጠጉ፤ ከእኔም ጋር ተጣበቁ፤ እኔ፣ እኔ ራሴ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ
እሰጣችኋለሁ፤ የማጠግባችሁና ከማንኛውም አደጋ ታመልጡ ዘንድ የምረዳችሁ እኔ ነኝ፤
ብቻ ልባችሁ በሌላ በማንም ላይ አይጣበቅ ወይም አይረፍ» ማለት ነው።
5 እንግዲህ ይህ እንዲገባንና እንድናስታውሰው በየዕለቱ የሚገጥሙንን ተቃራኒዎች
እንደ ምሳሌ በመተቀስ ሰፋ አድርጌ ማብራራት ይኖርብኛል። ገንዘብና ንብረት ሲኖራቸው
እግዚአብሔርና የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እንዳላቸው የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ። ለሌላ
ለማንም ግድ እስከማይላቸው ድረስ በልበ ደንዳናነት በእነዚህ ነገሮች ይታመኑባቸዋል፤
6 ይመኩባቸዋልም፤ እንደዚህ ያሉ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ ልባቸውን የጣሉባቸውና
የሚያመልኩአቸው በስም የሚታወቁ ማለትም ገንዘብና ንብረት አምላካቸው[35] ይሆናሉ
7 ማለት ነው። ይህም በምድር ላይ እጅግ በጣም የተለመደው ጣዖት ነው። ገንዘብና ንብረት
ያላቸው በገነት መሐል ላይ የተቀመጡ ያህል ዋስትና ያላቸው፣ ደስተኞች እና የማይፈሩ
8 እንደ ሆኑ ይሰማቸዋል። በሌላ በኩል ምንም የሌላቸው አምላክ እንደሌላቸው የማያውቁ
9 ይመስል ይጠራጠራሉ፤ ተስፋም ይቈርጣሉ፤ ገንዘብ ባይኖራቸውም ደስተኛ የሆኑ፣
የማይጨነቁና የማያጕረመርሙ በጣም ጥቂቶችን እናያለን። ይህ የሀብት ፍላጎት እስከ ሞት
ድረስ ከተፈጥሮአችን ጋር የተጣበቀና የማይለቀን ነው።
10 እንዲሁም በላቀ ትምህርታቸው፣ በጥበባቸው፣ በኃይላቸው፣ በዝናቸው፣
በቤተሰባቸውና በክብራቸው የሚመኩና የሚደገፉባቸው እንደ እውነተኛ አምላክ እንደ
እግዚአብሔር አይሁን እንጂ የሚያመልኩት አምላክ አላቸው። እንደዚህ ዓይነት
አለኝታዎች ሲኖሯቸው ሰዎች ደፋሮች፣ ከአደጋ እንደሚጠበቁ ዋስትና የሚሰማቸው
ትዕቢተኞች እንደሚሆኑና አለን የሚሉአቸውን ነገሮች ሲያጧቸው ወይም ሲወሰዱባቸው
ደግሞ እንዴት ተስፋ እንደሚቈርጡ አሁንም አስተውሉ። ስለዚህ የሚመለክ አምላክ አለው
ማለት በትክክለኛ ትርጕሙ ሙሉ በሙሉ ልብ የሚታመንበት አንድ ነገር መኖር ማለት
እንደ ሆነ ደግሜ እላለሁ።
11 እንደ ገናም በጽጽስናው ሥርዓት ውስጥ ሳለን በጭፍንነታችን እናደርጋቸው
የነበሩትን ነገሮች ተመልከት፤ ማንም ጥርሱን ቢያመው ይጾምና ቅዱስ አፖሎንያን ይጠራ
ነበር። ቤታቸው በእሳት እንዳይቃጠል የሚጨነቁ ሰዎች ቅዱስ ላውረንስን እንደ ልዩ
ጠባቂአቸው አድርገው ይማጸኑት ነበር። መቅሠፍትን ከፈሩ ለቅዱስ ሰባስቲያን ወይም
ለሮች ስዕለት ይሳሉ ነበር።[36] እንደዚህ ዓይነት ሥፍር ቊጥር የሌላቸው ሌሎች አስጸያፊ
ነገሮች ይካሄዱ ነበር። እያንዳንዱም ሰው በተቸገረ ጊዜ የሚረዳውንና የሚያመልከውን
12 የራሱን ቅዱስ ሰው ይመርጥ ነበር። ምትሀተኞችና ጠንቋዮች እንደሚደርጉት ዲያብሎስ
በርካታ ገንዘብ እንዲሰጣቸው፣ በፍቅር ጕዳይ እንዲረዳቸው፣ ከብታቸውን እንዲጠ
ብቅላቸው፣ የጠፋ ዕቃቸው እንዲመለስላቸው፤ ወዘተ ጭምር ከእርሱ ጋር ተስማምተው
የሚኳዙትም በዚህ ክፍል ይመደባሉ። እነዚህ ሁሉ ከእውነተኛው አምላክ ይልቅ ልባቸውን
በሌላ ላይ አድርገዋል። በመሆኑም ከእውነተኛው አምላክ ምንም መልካም ነገር አይጠ
ብቁም፤ አይፈልጉምም።
13 ስለዚህ ይህ ትእዛዝ የሚጠይቀው ምን ያህል እንደ ሆነ በቀላሉ ይገባናል፤ ማለትም
የሰው ልብ እና መታመን በሌላ በማንም ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንዲያርፍ
ነው። በሚገባ ልትገምቱ እንደምትችሉት እግዚአብሔር ወይም አምላክ አለ ማለት እርሱን
በእጆቻችሁ መያዝ፣ በቦርሳ ውስጥ መክተት ወይም በሣጥን ውስጥ አድርጎ መቈለፍ ማለት

---

[35] ማቴዎስ 6፡24ን ተመልከት።

[36] አፖሎኒያ በየካቲት 9 ቀን 248 ወይም 249 ሰማዕት ሆነች። ምክንያቱም ገዳዮችዋ ወይም ሰቃዮችዋ ለጥርስ ሕመም ይረዳል ብለው ስለ ቈጠሩ ጥርሶችዋን ነቀሉ። የሮማው ዲያቆን ላውረንስ ነሐሴ 10 ቀን 258 ሥጋ ወይም ዓሣ ለመጥበስ በተዘጋጀ ብረት ላይ ተቃጥሎ ሰማዕት ሆነ ተብሎ ይነገርለታል። የሮማው ሰባስቲያን በአራተኛው ምእት ዓመት (? መጀመሪያ ላይ ጥር 20 ቀን በቀስት ተወግቶ ተገደለ ተብሎ ይነገርለታል)። የሞንቴፔለር ፍራንሲስካን መነኩሴ የነበረው ሮች በጣሊያን ተከሥቶ በነበረው ወረርሽኝ የተጠቁ የበሽታው ሰለባዎችን ይንከባከብ ነበር። በየመቱ ነሐሴ 16 ቀን ይዘከራል።

14 አይደለም፡፡ ይልቁንም ልባችን ሲጨብጠውና ከእርሱ ጋር ሲጣበቅ በዚያን ጊዜ እርሱን
15 እንይዛለን ማለት ነው፡፡ በሙሉ ልባችን ከእርሱ ጋር መጣበቅ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ
ለእርሱ ከመስጠት በስተቀር ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ አንዱና ዘለዓለማዊው መልካም እርሱ
ስለ ሆነ ከእርሱ በስተቀር ከሌላ ከማንኛውም ነገር ዘወር ሊያደርገን ይፈልጋል፡፡ «ቀድሞ
ከቅዱሳን ስትፈልጉት ለነበረው ወይም ከንዋይ እና ከሌላ ነገር ለመቀበል ተስፋ
ላደርጋችሁት ነገር ሁሉ ወደ እኔ ዘወር በሉ፡፡ እንደምረዳችሁና መልካም ነገሮችን ሁሉ
አትረፍርፌ እንደማፈስላችሁ እዩኝ» ያለ ይምስል ነው፡፡
16 ልብ ከእርሱ በቀር ምንም መጽናኛ ወይም መተማመኛ እንዳይፈልግ ወይም ከእርሱ
እንዳይለይ እግዚአብሔር በዘለዓለማዊ የቀኑጣ ቅጣት ማስጠንቀቂያ የሚያዝዝበት፣ ሰውም
ስለ እግዚአብሔር ብሎ ምድራዊውን ነገር ሁሉ ለማጣት ፈቃደኛ የሚሆንበትና
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እውነተኛ አክብሮትና አምልኮ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ
17 ታገኛላችሁ፡፡ በሌላ በኩል ዓለም እንዴት ከሐሰትና ከጣዖት አምልኮ በስተቀር ምንም ነገር
እንደማይለማመድ በቀላሉ ማየትና መፍረድ ትችላላችሁ፡፡ አንድ ዓይነት አምልኮ
ያልመሠረተና ያንን ጠብቆ ያልኖረ ክፉ ሕዝብ ከቶ የለም፡፡ ሁሉም ሰው ለብዙ በረከት፣
ለእርዳታና ለመጽናናት ተስፋውን የጣለበት የራሱ አምላክ አቋቁሞአል፡፡
18 ለምሳሌ እምነታቸውን በኃይልና በመግዛት ላይ ያደረጉ አረማውያን ጁፒተርን
እንደ ታላቁ አምላካቸው አክብረውታል፡፡ ለሀብት፣ ለደስታ፣ ለተድላና ለመልካም
ሕይወት የጣሩ ሌሎችም ሄርኩለስን፣ ሜርኩሪን፣ ቬኑስን ወይም ሌሎችን ሲያከብሩ እርጉዝ
ሴቶች ደግሞ ዲያናን ወይም ሉሲናን ወዘተ. አምልከዋል፡፡[37] ሁሉም ልባቸው በጣም
ከሚፈልገው ነገር አምላክ አበጅተዋል፡፡ ስለዚህ በሁሉም አረማውያን አእምሮ የአምላክ
19 መኖር ማለት በእርሱ መደገፍና እርሱን ማመን ማለት ነው፡፡ ችግሩ በሰማይና በምድር
ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ በመሆኑ፣ በዚህ እውነተኛ አምላክ ላይ
20 አልተመሠረተምና እምነታቸው ውሸት እና የተሳሳተ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሠረት
አረማውያን ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ዐስተሳሰብ በጣዖት ላይ አድርገው በከንቱ ወይም
21 በባዶነት ይደገፋሉ፡፡ እንግዲህ ይህ ሁሉ ጣዖት ነው፡፡ ጣዖትን ማምለክ ማለት አንድ
ምልክት ማቆምና ወደ እርሱ መጸለይ ብቻ ሳይሆን ከፍጥረት፣ ከቅዱሳን ወይም ከዲያብሎስ
እርዳታና መጽናናት በመፈለግ በእነርሱ ላይ በዋናነት ልብን የመጣል ሁኔታ ነው፡፡ ይህ
ዓይነቱ አምልኮ ስለ እግዚአብሔር ምንም ግድ የማይለው ሲሆን አንዳች መልካም ነገርም
ከእርሱ አይጠብቅም፤ ወይም እግዚአብሔር ሊረዳ እንደሚፈልግና መልካም ነገር ሁሉ
ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ሊያምን አይፈልግም፡፡
22 በተጨማሪም ሌላ ሐሰተኛ አምልኮ አለ፡፡ ይህንን ጣዖት ቀደም ብለን
የተለማመድነው ሲሆን አሁንም በዓለም በመላ በስፋት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ሃይማኖቶች
ሁሉ በዚህ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ እርሱም እርዳታን፣ መጽናኛንና ድነትን በራስ
መልካም ሥራ የሚፈለግና በዚህ መልካም ሥራው መንግሥተ ሰማይን ከእግዚአብሔር
ለማውረድ የሚፈልግ ሕሊና ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ምን ያህል ሀብት ለቤተ ክርስቲያን
እንዳወረሰ፣ ምን ያህል እንደ ጾመና ምን ያህል ጊዜ የቅዱስ ቊርባን ሥርዓትን እንዳካሄደ፣
ወዘተ ማሰብ ተግባሩ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አመለካከት እግዚአብሔር ከእኛ በታች ያለ
አገልጋይና ወይም ባለ ዕዳ እኛ ደግሞ የእርሱ ጌቶች የሆንን ይመስል በነዚህ ነገሮች ላይ
23 ስለሚደገፍና በራሱ የተትረፈረፈ[38] ጽድቅ ሁሉንም ለማግኘት ስለሚፈልግ የእግዚአብሔርን

[37] ሄሪኩለስና ሜርኩሪ እንደ ብልጽግና ሀብት አምጪ አማልክት ተደርገው በሮማውያን ይመለኩ ነበር፡፡ ቬኑስ ከአፍሮዳይት ጋር በፍቅር ስኬት የሚያስገኙ እንደ ሆኑ ይቈጠራሉ፡፡ ዲያና የሮማውያን የጨረቃ አምላክ ስትሆን አብዛኛውን ጊዜ ከአርጤሚስ ጋር ትመሳሰላለች፡፡ ሉሲያና ልጅን የምትሰጥ ሴት አምላክ ሆና ከጁኖ ጋር ተመሳሳይ ነች፡፡

[38] የተትረፈረፈ ጽድቅ የሚባለው በመካለኛው ክፍለ ዘመን ሥነ መለኮት ዐስተሳሰብ አንድ ሰው እግዚአብሔር ከሚፈልግበት በላይ መልካም ሥራዎችን ሠርቶ ሲገኝ ነው፡፡ እነዚህ ከበቂ በላይ የሆኑ መልካም ሥራዎች ለሌላ ሰው ተጨማሪ መልካም ሥራ ሆነው ሊቈጠሩ ይችላሉ፡፡

ስጦታ ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም::[39] ይህ እግዚአብሔርን ጣዖት፣ በርግጥም አምላክ
መሰል[40] ማድረግና ራሳችንን በእግዚአብሔር ቦታ ማስቀመጥ አይደለምን? ነገር ግን ይህ
ዐስተሳሰብ በቀላሉ የማይጨበጥ በመሆኑ ለወጣቶች ተስማሚ አይደለም::
24 አካልን፣ ሕይወትን፣ ምግብን፣ መጠጥን፣ ዕድገትን፣ ጤናን፣ ጥበቃን፣ ሰላምንና
አስፈላጊ የሆኑትን ጊዜአዊና ዘለዓለማዊ በረከቶችን ሁሉ የሚሰጠን እግዚአብሔር ብቻ ስለ
ሆነ እርሱን ብቻ መታመን፣ እርሱን ብቻ ተስፋ ማድረግና የሚያስፈልገንን መልካም ነገር
ሁሉ ከእርሱ መጠበቅን ማስተማር የዚህ ትእዛዝ ትምህርት መሆኑን ለሕዝቡ መንገር
ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ክፉ ነገር በሚያገኝን ጊዜ እግዚአብሔር ከመከራ ይጠብቀናል፤
ያድነናልም:: (ብዙ ጊዜ ደጋግሜ እንዳልሁት) መልካምን የምንቀበለውና ከክፉ ሁሉ
25 የምናመልጠው በእግዚአብሔር ብቻ ነው:: እኛ ጀርመኖች ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከሌሎች
ቋንቋዎች ይልቅ ውበትና ክብር ባለውና «መልካም»[41] ከሚለው ቃል በተገኘው ስም
እግዚአብሔርን የምንጠራው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል:: ምክንያቱም እርሱ መልካምነቱ
የተትረፈረፈና በእውነት መልካም ለሆነው ነገር ሁሉ ዘለዓለማዊ ምንጭ ስለ ሆነ ነው::
26 ምንም እንኳ ከሰዎች ወደ እኛ የሚመጣ ብዙ መልካም ነገር ቢኖርም እንደ
ትእዛዙና ሕጉ የምንቀበላቸው ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ናቸው:: ወላጆቻችንና
ባለሥልጣናት እንዲሁም ጎረቤት መልካምን ነገር እንዲያደርጉልን ከእግዚአብሔር ትእዛዝን
ተቀብለዋል:: ስለዚህ በረከቶቻችንን የምንቀበለው ከእነርሱ ሳይሆን በእነርሱ በኩል
ከእግዚአብሔር ነው:: ፍጥረታት እግዚአብሔር በረከቱን የሚያስተላልፍባቸው እጆች፣
መተላለፊያ መንገዶችና መሣሪያዎች ብቻ ናቸው:: ለምሳሌ እግዚአብሔር ለልጁ ሕይወት
ማቆያ እንዲሆን ጡትና ወተትን ለእናቲቱ ሲሰጥ ሕይወት ይቀጥል ዘንድ ደግሞ ከምድር
እህልንና ማንኛውንም ዓይነት ፍራፍሬዎችን ለሰው ይሰጣል:: ስለዚህ ማንም እግዚአብሔር
27 ካላዘለት በስተቀር እንዳችን ሊወስድ የሚችል አይምሰለው:: ስለዚህ ይህ ትእዛዝ በሚጠ
ይቀን መሠረት የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድናውቅና እንድናመሰግነው አሠራሩ ግድ
ይለናል:: ስለ ሆነም እንግዲህ በተፈጥሮ አማካይነት የምንቀበለውን የእግዚአብሔር ስጦታ
እንዳንንቅ ወይም እንዳንፈልግ መጠንቀቅ አለብን:: ይህ አንዳችን ነገር ከእግዚአብሔር
መቀበል ሳይሆን ከራሳችን መፈለግ ነው::
28 እያንዳንዱ ሰው ይህንን ትእዛዝ ከሁሉ አስበልጦ ያክብረው እንጂ እንዳያቀልለው
ይጠንቀቅ:: ልብህን በሚገባ መርምረውና ከእግዚአብሔር ጋር ይጣበቅ ወይ አይጣበቅ እንደ
ሆነ ፈትነው:: በተለይ ጭንቀት በገጠመህና አንዳች ነገር ባስፈለገህ ጊዜ ከእግዚአብሔር
ውጭ የሆነውን የሚያወግዝና ከእርሱ ብቻ መልካምን ነገር የሚጠብቅ ልብ ካለህ እውነተኛ
አምላክ አለህ:: በተቃራኒው ነገሮች በተበላሹበት ጊዜ ልብህ ከሌላ ነገር ጋር ቢጣበቅ፣
ከእግዚአብሔር ይልቅ መልካምን ነገርና እርዳታ ከዚያ ነገር ቢጠብቅና ወደ
እግዚአብሔር ባይሸሽ ያን ጊዜ ሌላ አምላክና ጣዖት አለህ ማለት ነው::
29 ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ በቀላሉ እንደማያየው ነገር ግን አጥብቆ
የሚጠብቀው መሆኑን በመጀመሪያ እጅግ ከባድ የሆነ ማስጠንቀቂያን፣ ቀጥሎ እጅግ ያማረ
አጽናኝ ተስፋን ከዚህ ትእዛዝ ጋር አያይዟል:: ወጣቶቹ ልብ እንዲሏቸውና
እንዲያስታውሷቸው እነዚህ ሁለቱ ነገሮች በጥልቀት ሊነገሩአቸውና ሊቀረጹባቸው ይገባል::

---

[39] በመካከለኛው ባላባታዊ ሥርዓት አንድ ወኪል የሆነ ሰው ጌታውን በታማኝነት የማገልገል ግዴታ ነበረበት::

[40] በጀርመንኛ *Apfelgott, ይህ ቃል ምናልባትም Aftergott* ከሚለው ቃል በስሕተት የተተረጎመና «እውነተኛ ያልሆነ አምላክ» ሊሆን ይችላል:: በሰኔ 15/1539 ሉተር ስለ ንጉሡ ፈርዲናንድ ሲጽፍ *Apfelkonig* ሲለው ይኸውም «ንጉሥ መሰል» ማለቱ ነው፣ በ1530ም ሲጽፍ *Apfekonige oder gemalete Herren* «ነገሥታት ወይም ጌቶች መሰል» እንደ ማለት ነው:: የኋለኛውም አገላለጽ ማላገጫ ሲሆን እርሱም «የተለሰኑ ቅዱሳን» እንደ ማለት ነው:: በዚያን ጊዜ የሰብአዊነት ፍልስፍናን ይከተል የነበረው ሰባስቲያን ፍራንክ *Apfelkaiiser* የሚለውን አነጋገር የሚጠቀም ሲሆን ትርጒሙም «ንጉሠ ነገሥት መሰል» እንደ ማለት ነው፤ ለምሳሌ በበርሊን *Apfelbischof* «ጳጳስ መሰል» የሚለው አነጋገር ደግሞ ከዓቢይ ጾም በፊት ያለው ማክሰኞ ነው::

[41] በጀርመንኛ *gut* ይህ አገላለጽ በቋንቋ ደንብ ትክክለኛ አይደለም:: «እግዚአብሔር» ለሚለው አባባል (Gott) ከጎቲክ ወይም ከመካከለኛው ጀርመንኛ ጋር አይዛመዱም::

## *የመጀመሪያው ትእዛዝ አባሪ የጽሑፍ ማብራሪያ*[42]

30 «በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት
በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ደረስ
ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ[43] አምላክ ነኝና።»[44]
31 (ወደ ኋላ ላይ እንደምንሰማው) እነዚህ ቃላት ሁሉንም ትእዛዛት የሚመለከቱ
ቢሆንም በቀጥታ የተያያዙት ከዝርዝሩ አናት ላይ ከዚህ ትእዛዝ ጋር ነው። ምክንያቱም
አንድ ሰው ትክክለኛ ዐስተሳሰብ እንዲኖረው ይህ አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው ትክክለኛ
ዐስተሳሰብ ካለው ሕይወቱ በሙሉ ትክክለኛ የሚሆን ሲሆን ይህ ባይሆን ደግሞ ሕይወቱ
32 ሁሉ የዚህ ተቃራኒ ይሆናል። እግዚአብሔር ከእርሱ በቀር በሌላ የሚታመኑትን ምን ያህል
እንደሚቈጣ ነገር ግን በሙሉ ልባቸው በእርሱ ብቻ ለሚታመኑት ደግሞ ምን ያህል ቸር
እንደ ሆነ ከእነዚህ ቃላት ተማሩ። በእርሱ በማይታመኑት ላይ ቍጣው እስከ አራተኛ
ትውልድ ድረስ እንደማይበርድ፣ በታቀራኒው ግን ቸርነቱና በጎነቱ ለብዙ ሺህ ትውልድ
33 ነው። ስለዚህ በምንም ዓይነት ኑሮ ውስጥ ቢሆኑ ምንም ግድ እንደሌላቸው አውሬዎች
34 ሰዎች በውሸተኛ ዋስትና መኖር ወይም በዕድል መታመን የለባቸውም። እርሱ ከእርሱ
የሚመለሱት ክፉዎች ሳይቀጡ እንዳይታለፉ ነገር ግን እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ
እስኪደመሰሱ ቍጣው የማይቆም አምላክ ነው። ስለዚህ እንዲፈራ እንጂ እንዳይናቅ
ይፈልጋል።
35 መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት እንደሚያሳየውና የየዕለቱ ተሞክሮ እንደሚያስተምረን
በታሪክ ይህንን አረጋግጦአል። ከዚህም የተነሣ ከመጀመሪያው የጣዖት አምልኮን ሁሉ ፈጽሞ
አጥፍቶአል፤ በጣዖታትም ምክንያት አረማውያንንና አይሁዶችን ገልብጦአቸዋል።
በዘመናችንም እንዲሁ ከሐሰተኛ አምልኮ ጋር የሚጣበቁት እስኪጠፉ ድረስ ሐሰተኛ
36 አምልኮን ይገለብጣል። ዛሬም እግዚአብሔር ቢቈጣም ቢደሰትም ግድ የማይላቸው ነገር ግን
በገንዘባቸው የሚኩሩና የሚታመኑ የእግዚአብሔርን ቍጣ መቋቋም እንችላለን ብለው
የሚያስቡ ኩራተኞች፣ ጉልበተኞችና ሆዳሞች አሉ። ይሁን እንጂ፣ አይሳካላቸውም። ዋስትና
እንዳላቸውና ጉልበተኞች እንደ ሆኑ የሚያስቡ ሌሎች እንደ ሆኑት ሁሉ ከታመኑበት ነገር
ጋር ሳያስቡ ይወድማሉ።
37 እነዚህ አእምሮአቸው ጠጣር የሆነባቸው ሰዎች እግዚአብሔር ሲታገሣቸውና
ዋስትናቸውን ዝም ብሎ ሲመለከት እርሱ ኩራታቸውን የማያውቅና ክፉ አካሄዳቸው
የማይመለከተው መስሎ ስለሚታያቸው እስከ ልጅ ልጃቸው ድረስ በከፋ ሁኔታ
ሊያደቃቸውና ሊቀጣቸው ይገባል። እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ሁሉም ሰው
ተመልክቶ እንዲገረምና እርሱ የሚቀልድ አምላክ አለመሆኑን እንዲገነዘብ ነው።
38 እግዚአብሔር «የሚጠሉኝን» ሲል በእርሱ አእምሮ ያሉት እነዚህ በጥመታቸውና
በኩራታቸው ወደ ፊት የሚገፉ ናቸው። የተሰበከላቸውን ወይም የተነገራቸውን እምቢ
የሚሉ ናቸው። እውነተኛው ቅጣታቸው ከመምጣቱ በፊት ወደ ልቦናቸው እንዲመለሱና
አካሄዳቸውን እንዲቀይሩ አንድ ሰው ቢገሥጻቸው እንደ አውሬና ዕብድ የሚያደርጋቸው
ናቸው። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በየዕለቱ ከጳጳሳቱና ከነገሥታቱ ይገጥመናል።
39 ነገር ግን ምሕረቱን ማለትም ወሰን የሌለው መልካምነቱንና በረከቱን አጥብቀው
ለሚሹት እግዚአብሔር የሚሰጠው አጽናኝ ተስፋና ዋስትና እነዚህ ቍጣዎቹ አስፈሪ
የሆኑትን ያህል እንዲያውም ከዚያም በላይ ከመሆናቸውም አልፈው ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን
40 ለልጆቻቸው እስከ ብዙ ሺህ ትውልድ ድረስ ነው። በእርግጥ ለጊዜውና ለዘለዓለም የሚሆን

---

[42] ይህ ንዑስ ርእስ የሚገኘው በላቲኑ የመጽሐፈ ስምምነት ትርጉም ብቻ ነው።
[43] ዘጸአት 34፡14 «ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ።»
[44] ዘጸአት 20፡5-6 (የሉተር ትርጉም) ይህ ክፍል ሉተር ከተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው። ቀጥሎ ያለው ትርጉም ፍጹም የተለየ ነው።

*መልካምን ነገር ብንሻ ፍጹም በሆነ መታመን ልባችንን በእርሱ ላይ እንድናሳርፍ ይህ*
*ተስፋው እንዲያንቀሳቅሰንና እንዲገፋፋን እግዚአብሔር በመለኮታዊ ግርማ ሞገሱ ወደ እኛ*
*ቀርቦ በቸርነቱ አጥብቆ ይጋብዘናል፤ የተትረፈረፈ ተስፋም ይሰጠናል።*
41 *ስለዚህ ይህ ቃል ዘለዓለማዊ በረከትን፣ ደስታንና መዳንን ወይንም ቀጣን፣*
*ጭንቀትንና ሕመምን ይዞ የሚመጣ መሆኑን እያንዳንዱ ሰው ይገንዘብ፤ ምክንያቱም ይህንን*
*ቃል የሚናገረው ተራ ሰው እንደ ሆነ አድርጎ እንዳያስብ ጥንቃቄ ያድርግ። ከነበረከቶቹ*
*ሁሉ አምላክህ ሊሆን፣ ሊጠብቅህ፣ በሚያስፈልግህ ሁሉ ሊረዳህ ከሚፈልገው ቸር ከሆነው*
42 *እግዚአብሔር ሌላ ምን ትፈልጋለህ? ወይስ ትመኛለህ? አለመታደል ሆኖ ዓለም ይህ*
*የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አያምንም ወይም አይቈጥረውም። በገንዘብ ሳይሆን*
*በእግዚአብሔር የሚታመኑት በእጦትና በኀዘን እንዲሠቃዩ ዲያብሎስ እንደሚዋጋቸው*
*ዓለም ያያል። እነርሱ ገንዘብ፣ እውቀና ወይም ክብር የላቸውም፤ የሚኖሩትም በመከራ*
*ነው። በሌላ በኩል ግን ገንዘብ ያላቸው ሥልጣን፣ ተቀባይነት፣ ክብር፣ ይዞታና ሁሉንም*
*ዓይነት ዋስትና እንዳላቸው ሆኖ በዓለም ዐይን ይታያል። ስለዚህ ይህ ዐይነቱ ተቃውሞ*
*ከፊት ለፊታችን ቢጋፈጥም እነዚህን ቃላት የማይዋሹ ወይም የማያታልሉን፣ ነገር ግን*
*እውነትን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን ተረድተን አጥብቀን ልንይዛቸው ይገባናል።*
43 *ሰዎች ትልቅ ሀብት ነው የሚባለውን ቢያግበሰብሱ በዕድሜአቸው መጨረሻ ጊዜ*
*ምን እንዳከናወኑ እስቲ ራስህ ዐስብና ወይም ከአካባቢህ ጠይቅና ንገረኝ። ድካማቸው ከንቱ*
*መሆኑና እንደባከኑ ትረዳለህ። ምንም እንኳ ታላቅ ሀብት ቢያከማቹም እነዚህ አፈር ሆነው*
*ጠፍተዋል። በብልጽግናቸው ደስታን ፈጽመው እንዳላገኙ ወይም ለሦስተኛ ትውልዳቸው*
44 *ሊደርስ እንዳልቻለ ትገነዘባለህ።*[45] *ለዚህ በቂ የሆነ ምሳሌ ከታሪኮችና በዕድሜ ከገፉ ሰዎች*
45 *ተሞክሮዎች ታገኛለህ። እነዚህን ሰዎች እስቲ በትኩረት አስተውላቸው። ሳኦል*
*በእግዚአብሔር የተመረጠ ታላቅ ንጉሥና ቅን ሰው ነበር። ነገር ግን ሥልጣን እንደ ጨበጠ*
*ልቡን ከእግዚአብሔር*[46] *መልሶ ተስፋውን በዘውዱና በነበረው ኃይሉ ላይ በጣለ ጊዜ*
46 *ከነበረው ሁሉ ጋር ጠፋ፤ ከልጆቹ አንድ ስንኳ አልተረፈም።*[47] *በሌላ በኩል ድሃ፣ የተናቀ፣*
*ነፍሱን ከሚሹት የተነሣ ሁሌ የሚሸሽግ በሕይወት ስለመኖር ምንም ተስፋ ያልነበረው ሰው*
*ዳዊት ከሳኦል እጅ ድኖ ንጉሥ ሆነ።*[48] *እግዚአብሔር እንደማይዋሸና ሰውን እንደማያታልል*
*እነዚህ ቃሎች ያረጋግጣሉ። በሚታይ ገጽታቸው ሊያታልሉ የሚያደርጉትን ሙከራ*
*ለዲያብሎስና ለዓለም*[49] *ተውላቸው፤ ይህ የሚታየው ገጽታቸው ለጊዜው ነው፤ በኋላ ላይ ግን*
*ባዶ ይሆናል።*
47 *ስለዚህ እግዚአብሔር በሌላ ነገር ላይ ሊኖረን የሚችለውን መታመን ሊታገሠው*
*እንደማይችል ከአንደኛው ትእዛዝ በሚገባ እንማር። እርሱ በሙሉ ልባችን በእርሱ*
*ከመታመን ያለፈ ነገር ከእኛ አይፈልግም። ልክ አንድ ጫማ ሠሪ መርፌን፣ መዶሻንና*
*ክርን ለሥራው እንደሚጠቀምና በኋላ ላይ እንደሚያስቀምጣቸው ወይም አንድ መንገደኛ*
*ሆቴልን፣ ምግብንና ማደሪያን ለጊዜያዊ ፍላጎቱ ብቻ እንደሚጠቀም እያንዳንዱ ሰው*
*በአኗኗር ዘይቤው*[50] *እንደ እግዚአብሔር ሥርዓት እነዚህ ምድራዊ የሆኑ ነገሮች ጌታና*
*ጣዖት እንዳይሆኑበት የእግዚአብሔርን ስጦታዎች በመጠቀም ረገድ በቀጥታ በትክክለኛ*
*መንገድ እንንዛለን።*

---

[45] *ሉተር ደጋግሞ የሚጠቅሰው ከጊዜ በኋላ የመጣ የላቲን ምሳሌአዊ አባባል* «*በማታለል የተገኘ ሀብት ለሦስተኛ ትውልድ አይደርስም*» *ይላል።*
[46] 1 *ሳሙኤል* 15፡11*ን ተመልከት።*
[47] *ዮናታን አሚናዳብና ሜልኪሳ ከፍልስጥኤሞች ጋር በተደረገው ጦርነት ሞቱ* (1*ሳሙ* 31፡2) *የሳኦል ታናሹ ልጅ ኢያቡስቴ አንገቱን ተቀላ* (2 *ሳሙ* 4፡7)።
[48] 1 *ሳሙ* 18-2 *ሳሙ* 2 *ተመልከት።*
[49] *ቪንሰንት ኦብሶፖየስ በመጀመሪያ* 1529 *የትልቁ ክርስትና ትምህርት ላቲን ትርጒም እና በ*1580 *የጀርመን እና በ*1884 *የላቲን የመጽሐፈ ስምምነቱ እትሞች* «*አይደለም*» *የሚለውን በዚህ ነጥብ ይጨምራል። ስለዚህ ምንባቡን አለመረዳት አስከትሎአል።*
[50] German: Stand.

48 አንደኛውን ትእዛዝ በተመለከተ ይህ ይብቃን። ይህ ትእዛዝ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ እርሱን ለማብራራት ሰፊ ጊዜ መውሰዱ ተገቢ ነበር።[51] አስቀድሜ እንዳልኩት ልባችን ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ቢሆንና ይህን ትእዛዝ ብንጠብቅ የተቀረው ሁሉ እርሱን ይከተላል።

*ሁለተኛው ትእዛዝ፦*

49 «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ»

50 ልክ የመጀመሪያው ትእዛዝ ውስጣዊ ልብን እንደሚመራና ስለ እምነት እንደሚያስተምር ሁለተኛው ትእዛዝ ወደ ውጪአዊ አካላችን ይመራንና ከንፈራችንና ምላሳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ የሆነ የግንኙነት መስመር እንዲከተሉ ትክክለኛ አቅጣጫ ያስይዘናል። ከልባችን በመጀመሪያ የሚፈልቁትና የሚወጡት ቃላት ናቸው። አምላክን የሚያመልክ ወይም አምላክ ያለው ሰው ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ ለሚጠይቅህ ሰው እንዴት መመለስ እንደሚቻል ለማወቅ እላይ እንዳስተማርኩት የዚህና የሌሎች ትእዛዛት ትርጉም ምን እንደ ሆነ በቀላሉ ለመረዳትና ለራስህ ለማድረግ ትእዛዛቱን ከራስህ ጋር ማዛመድን መማር ይገባሃል።

51 የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ወይም በስሙ አለአግባብ መጠቀም ማለት
ምን ማለት ነው? ተብላችሁ ብትጠየቁ በአጭሩ «ሐሰትን ወይም ማንኛውንም ዓይነት
ስሕተት ለመደገፍ እግዚአብሔር አምላክን በማንኛውም መንገድ መጥራት የእግዚአብሔርን
52 ስም አለአግባብ መጠቀም ነው» ብላችሁ መመለስ ይገባችኋል። ስለዚህ ይህ ትእዛዝ
የሚከለክለን የእግዚአብሔርን ስም በሐሰት ማንሣትን ወይም ልባችን እውነቱ ነገር የትኛው
እንደ ሆነ እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት የእውነቱ ተቃራኒ የሆነውን በመደገፍ ስሙን
መጥራትን፦ ለምሳሌ በፍርድ ቤት መሐላ ከፈጸመ በኋላ አንዱ ወገን በሌላው ላይ
የሚዋሸውን ውሸት ነው። ለውሸትና ለማታለል በእግዚአብሔር ስም ከመጠቀም የበለጠ
ዐይን ያወጣ ስሕተት የለም። ይህም የትእዛዙ ግልጽና ቀላል ማብራሪያ ይሁን።

53 የእግዚአብሔር ስም ያለ አግባብ የሚነሣባቸው ሁኔታዎችን ሁሉ መዘርዘር የማይቻል ቢሆንም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ስም መቼና እንዴት ባሉ መንገዶች ያለ አግባብ እንደሚነሣ ለራሳቸው አስበው ሊደርሱበት ይችላሉ። በአጭሩ ግን የመለኮትን ስም ያለ አግባብ መጠቀም ከሁሉ በፊት በንግድ ጒዳዮች ገንዘብን፣ ንብረትንና ክብርን በሚያካትቱ ጒዳዮች በሕዝብ ፊት በሸንጎ ወይም በገበያ ስፍራ ወይም ሰው በሐሰት ሲመሰክርና በእግዚአብሔር ስም ወይም በገዛ ነፍሱ በውሸት ሲምል ይከሰታል። በተለይ ይህ ክስተት በጋብቻ ጒዳይ ሁለት ሰዎች እርስ በርስ በምሥጢር ሲተጫጩና በኋላ ላይ በመሐላ ሲካካዱ ማየት የተለመደ ነው።[52] ከሁሉ የሚበልጠው ጥፋት ግን ሕሊናን በሚነኩ በመንፈሳዊ ጒዳዮች ላይ የሐሰት ሰባኪዎች ሲነሡና ሐሰተኛ ፍሬቢስ ትምህርታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገው ሲያቀርቡት ነው።

54 ተመልከቱ፦ ይህ ሁሉ በተራና ዓለማዊ ጒዳዮችም ሆነ በውስብስብና ከባድ
የእምነትና የአስተምህሮ ጒዳይ ላይ አንድ ሰው ስሕተቱን ለመሸፈን ራሱን በእግዚአብሔር
ስም ለማስጌጥ ወይም የራሱን መልካም ገጽታ ለማሳየት ሲል ድርጊቱን በእግዚአብሔር ስም
55 ለማጽደቅ መሞከር ነው። ሰው ሁሉ የሚያውቃቸውና የእግዚአብሔርን ስም በሚያስደነግጥ
ሁኔታ የሚያቃልሉ ባለጌዎች ብቻ ሳይሆኑ እውነትንና የእግዚአብሔርን ቃል በአደባባይ
የሚሳደቡና - እነዚህ የተፈረደባቸውን ወንጀለኞች በሚሰቅሉ ሰዎች ትምህርት ሊሰጣቸው

---

[51] ሉተር፣ የዐሠርቱ ትእዛዛት አቀነባበር ጠቃሚነታቸው እየቀነሰ በሚሄድ ቅደም ተከተል መሠረት እንደሆነ ያምናል።

[52] ከዚህ በኋላ ሉተር በምሥጢር የሚደረገውን መተጫጨት «በጋብቻ ጒዳዮች» መመሪያው ውስጥ አካትቶአል (15030) WA 30/3; 205-48; *LW* 46; 259-320)።

ይገባል - ለዲያብሎስ አሳልፈው የሚሰጡ ተሳዳቢዎችም ከሐሰተኞች መካከል የሚቈጠሩ ናቸው። ስለዚህ ነገር አሁን ከዚህ የበለጠ መናገር አያስፈልግም።

56 እንግዲህ ይህ ትእዛዝ እጅግ በጣም ትልቅ ትእዛዝ እንደ ሆነ በመረዳት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከማንሣት የከፋ ኃጢአት እንደሌለ ዐውቀን ስሙ አለአግባብ እንዳይነሣ በትጋት መከላከል ይገባናል። መዋሸትና ማታለል በራሳቸው ትልልቅ ኃጢአቶች ናቸው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ልናጸናቸው መሞከርና እፍረታችንን ለመደበቅ መሸፈኛ ማድረግ እጅግ አደገኛ ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ አንዱ ውሸት ሁለት ከዚያም አልፎ የውሸቶች ክምር ይሆናል።

57 ስለዚህ እግዚአብሔር ለዚህ ትእዛዝ ከባድ ማስጠንቀቂያ ጨምሮበታል።
«እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚያነሣውን ከበደል አያነጻውምና»[53] ይህም ማለት
እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚያነሣውን ሳይቀጣ አይተወውም ማለት ነው።
እግዚአብሔር ከእርሱ የሚርቀውን ሰው ያለ ቅጣት እንዲቀር እንደማይፈቅድ ሁሉ ስሙ
58 ውሸትን ለመደበቅ ጥቅም ላይ እንዲውል አይፈቅድም። ያለ መታደል ሆኖ በመላው ዓለም
እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው የሚደገፉበት ጥቂቶች የመሆናቸውን ያህል
የእግዚአብሔርን ስምም ለውሸትና ለሁሉም ዓይነት ክፋት የማይጠቀሙበት ጥቂቶች
መሆናቸው የተለመደ በሽታ ሆኖአል።

59 በተፈጥሮ ሁላችንም ባጠፋን ጊዜ ማንም እንዳያይብን ወይም እንዳያውቅብን
የመሸፈንና ነውራችንን ቸል ብለን የማለፍ ጥሩ ጠባይ አለን። ማንም ሰው በፈጸመው ክፋት
እስኪመካ ድረስ ድፍረት የለውም። ስለዚህ ሁላችንም ማንም ሰው ሳያውቅብን በስውር
ኃጢአት ማድረግን እንመርጣለን። አንድ ሰው በጥፋተኝነቱ በሚያዝበት ጊዜ ቆሻሻ ሥራው
60 ክቡር፣ ነውሩ ተደናቂ እንዲመስል የእግዚአብሔር ስም በግድ ተጎትቶ ይገባል። ይህ
ዓይነቱ አደራረግ በዓለም በመላ የተለመደ ሲሆን እንደ ታላቅ ጎርፍ ምድርን ሁሉ
አጥለቅልቆአል። ስለዚህ የሚገባንን በማግኘት ላይ ነን። ይኸውም መቅሠፍት፣ ጦርነት፣
ድርቅ፣ ሰደድ እሳት፣ ጎርፍ፣ ስድነት ወይም ከቊጥጥር ውጪ የሆኑ ባለትዳሮች፣ ልጆችና
የቤት ሠራተኞች እንዲሁም ሁሉም ዓይነት ችግሮች ደርሰውብናል።[54] ይህን የሚያህል
መከራ ከወዴት ሊመጣ ቻለ? ከዐመፃችን የተነሣ ምድር እስከ አሁን እኛን መደገፍና
መመገብ መቻሏ ታላቅ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው።

61 ስለዚህ ይህንን ለመረዳት እንዲችሉ ከሁሉ በላይ ወጣቶቻችን ይህንንና ሌሎቹንም ትእዛዛት በከፍተኛ አክብሮት እንዲይዙአቸው በጥብቅ ሊፈለግባቸውና ሊማሩ ይገባቸዋል። የወላጆችን ወይም የሞግዚቶቻቸውን ቅጣት በመፍራት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራት እንዲያደጉ ትእዛዙን በተላለፉ ጊዜ ወዲያውኑ ተከታትለን ልንቀጣቸው፣ በትእዛዙ ልንጋፈጣቸውና ባለማቋረጥ ልንቀርጻቸው ይገባናል።

62 እስከ አሁን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ተገንዝባችኋል። በአጭሩ ለመድገም ያህል፣ መዋሸት፣ እውነት ያልሆነን ነገር እውነት እንደሆነ አድርጎ በእግዚአብሔር ስም ለማሳመን መሞከር፣ መራገም፣ መማል፣ ምትሐትን መለማመድና የትኛውንም ዓይነት ክፉ ነገር ማድረግ ነው።

63 በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ስም እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባችሁ መማር ይገባችኋል። «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» ከሚሉት ቃላት ጋር ለእኛ ጥቅምና ትርፍ የተገለጠና የተሰጠን ስም በመሆኑ እግዚአብሔር ስሙን በአግባቡ

---

53 ዘጸአት 20፡7።

54 ይህ ዝርዝር የተነገረ አልነበረም። ከነሐሴ 1527 እስከ ጥር 1528 እና በ1528 መጸው ወራት ዊተንበርግ በከባድ መቅሰፍት ተመትታ ነበር። በነሐሴ 5 ቀን 1528 የሉተር ሴት ልጅ ኤልሳቤጥ ሞተች። ከ1527 ጀምሮ ንጉሠ ነገሥት ቻርለስ አምስተኛ እንግሊዝን፣ ፈረንሳይን፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳትን፣ ሚላንንና ቬኒስን (የ1526 የኮኛክ ሊግ) ሲወጋ ቆይቶአል። በተጨማሪም በ1528 ከቱርኮች አንጻር ጦርነት አስግቶ ነበር። የመካከለኛ ዘመን ከተሞችን የሚያሰጋ ተደጋጋሚና አደገኛ የእሳት ቃጠሎ ይከሰት ነበር። ዊተንበርግ ከፍተኛ የውሃ እጥረትን ባስከተለ ግለት ትሠቃይ ነበር። በተጨማሪም ዊተንበርግ የኤለቤ ወንዝ በሚያስከትለው ጎርፍ ትጠቃ ነበር።

64 መጠቀም እንዳለብን እንድንረዳ ይነግረናል። ስለዚህ ሐሰትንና ክፋትን ለመደገፍ ቅዱስ
ስሙን እንዳንጠቀም የተከለከልን ሲሆን በምትኩ እውነትና መልካም ለሆነው አገልግሎት
ሁሉ፦ ለምሳሌ አስፈላጊ በሆነበትና በሚጠቅም ቦታ በትክክለኛው መንገድ ስንምል ወይም
ትክክለኛውን ትምህርት ስናስተምር ወይም በችግራችን ጊዜ ሁሉ ስሙን ስንጠራ ወይም
በብልጽግና ጊዜ ስናመሰግነውና ስንወድሰው እንድንጠቀምበት ተፈቅዶልናል። ይህ ሁሉ
በመዝሙር 50፡15 ትእዛዝ ላይ «በመከራ ቀን ጥራኝ፤ አድንህማለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ»
ተብሎ ባጭሩ ተጠቃሎአል። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም እውነትን ለመደገፍና
በመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ መጥራት ማለት ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ በጌታ ጸሎት
እንደምንጸልየው የእግዚአብሔር ስም ይቀደሳል ማለት ነው።
65 እዚህ ላይ የመላው ትእዛዝ ፍሬ ነገር ተገልጾ ታገኛላችሁ። በዚህ መንገድ ስንረዳው
ብዙ መምህራንን[55] ያስቸገረውን በወንጌላትም ውስጥ መሐላ ለምን እንደተከለከለ ነገር ግን
ኢየሱስ፣ ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎችም ብዙ ጊዜ የመማላቸውን[56] ጥያቄ በቀላሉ
66 ትፈቱታላችሁ። በአጭሩ ማብራሪያው ይህ ነው፦ ክፉ ሥራን ማለትም ሐሰትን ደግፈን
ወይም አስፈላጊ በማይሆንበት ሁኔታ ሳይሆን በጎ ለሆነውና ባልንጀሮቻችንን ሊጠቅም
ለሚችል ነገር መማል ይገባናል። ይህ በእውነቱ እግዚአብሔር የሚወደስበት፣ እውነትና
ፍትህ የሚጸኑበት፣ ሐሰት የሚታረምበት፣ ሰዎች የሚታረቁበት፣ መታዘዝ የሚገለጽበትና
ጥል የሚወገድበት መልካም ሥራ ይሆናል። ምክንያቱም እዚህ ላይ እግዚአብሔር ራሱ
67 ጣልቃ ስለሚገባ ትክክለኛን ከስሕተት መልካምን ከክፉ ይለያል። አንዱ ወገን በሐሰት
ቢምል ፍርድ ይከተለዋልና ያ ሰው ከቅጣት አያመልጥም። ረጅም ጊዜ ቢወስድም እንዲህ
ዓይነት ድርጊት የሚያደርጉ ሰዎች አንዱም ሥራቸው አይሳካላቸውም። በሐሰት መሐላ
68 የተገኘ ነገር ሁሉ ከእጃቸው አፈትልኮ ያመልጣል፤ በጭራሽም አይደሰቱበትም። ይህንን
የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን በመሐላ ባፈረሱ ሰዎች ላይ ተመልክቼዋለሁ። ከዚያ በኋላ
አንዲትም አስደሳች ሰዓት ወይም ጤናማ ቀን አግኝተው አልተደሰቱም፤ በመሆኑም
በአካላቸው፣ በነፍሳቸው እና በንብረታቸው ወደሚያሳዝን ፍጻሜ ደርሰዋል።
69 ስለዚህ ቀደም ሲል እንዳደረግሁት አሁንም በማስጠንቀቂያና በማስፈራሪያ፣
በመቈጣጠርና በቅጣት ልጆች ከውሸት እንዲጠነቀቁና በተለይም ውሸትን ለመደገፍ
የእግዚአብሔርን ስም እንዳያነሡ ትምህርት እንዲሰጣቸው እመክራለሁ፤ አበረታታለሁም።
እውነት ያልሆነውን ነገር ለመደገፍ የእግዚአብሔርን ስም ቢያነሡና ቢምሉ መልካም ነገር
አይሆንላቸውም። ዓለም ከቀድሞ ይልቅ መክፋቱ ግልጽ ነው። አገዛዝ ጠፍቷል፤ መታዘዝ
የለም፤ ታማኝነት ኅድሎአል፤ እምነት ጠፍቷል፤ ትምህርትና ተግሣጽ ሊረዳቸው የማይችል
ጠማማና ልቅ ሰዎች ብዙ ናቸው። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ቍጣ ይህንን ትእዛዝ እያወቁ
በሚንቁ ሰዎች ላይ የመጣ ቅጣት ነው።
70 በሌላ በኩል ልጆች የእግዚአብሔርን ስም እንዲያከብሩና በሁኔታዎችና በገጠመኞች
ሁሉ ባለማቋረጥ እንዲጠሩት ደግሞ ደጋግሞ ማዳፋፈርና ማበረታታት ይገባል፤ ምክንያቱም
የእግዚአብሔርን ስም የማክበሪያው ተገቢ መንገድ ለመጽናናትና እርሱን ተስፋ ለማድረግ
ስሙን መጥራት ስለሆነ ነው። ስለዚህ እላይ እንደሰማነው በመጀመሪያ ልብ በእምነት፣
ከዚያም ከንፈር በምስክርነት እግዚአብሔርን ያከብራል።
71 ይህ የተባረከና ጠቃሚ ልምድ ዘወትር በዙሪያችን ላለውና ወደ ኃጢአትና እፍረት
አደጋና ችግር ሊከተን አድፍጦ ለሚጠብቀን ሰይጣን ጥሩ መከላከያ ነው። ሰይጣን
የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ ስለማይወድና ከልብ በሚጠራበትና በሚጸለይበት ጊዜ ረጅም
72 ጊዜ መቆየት አይችልም። ስሙን በመጥራታችን እግዚአብሔር ባይጠብቀን ኖሮ በርካታ

[55] የሂፖዎቹ አውግስጢኖስና ጀሮም ምሳሌ ናቸው። የሕፃናት ጥምቀትን የሚቃወሙ ክፍሎች ብዙዎቹ መሐላን ይቃወሙ ስለ ነበር ጉዳዩ አሳሳቢ ሆኖ ተገኝቶ ነበር።
[56] ማቴ 5፡33-37፤ 26፡63-64፤ ገላ 1፡20 እና 2ቆሮ 1፡23ን ተመልከት። በሌላ በኩል አጠቃላይ መሐላን በተመለከተ ሉተር የተራራውን ስብከት አስመልክቶ የሰባካቸውን ስብከቶች ተመልከት (1532) (WA 32: 381, 23-386, 34: *LW* 21: 99-104).

አሰቃቂና አስደንጋጭ አደጋዎች በደረሱብን ነበር፡፡ እኔ ራሴ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን
ስም በጠራሁበት ቅጽበት ድንገተኛና ታላቅ አደጋ መከልከሉንና መወገዱን በእርግጥ
ተለማምጃለሁ፡፡ ስለዚህ ዲያብሎስ እንደሚፈልገው ሊጎዳን እንዳይችል እርሱን ለመቃወም
ዘወትር የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም በከንፈራችን እናኑር እላለሁ፡፡
73 የእግዚአብሔር ጥበቃ ይሆንልን ዘንድ በየዕለቱ ሊመጣ ከሚችል አደጋ ሁሉ
እንዲጠብቀን ለእግዚአብሔር ራሳችንን፣ ነፍሳችንን፣ ሥጋችንን፣ ባለቤቶቻችንን፣
ልጆቻችንን፣ ሠራተኞቻችንንና ያለንን ሁሉ አሳልፎ ለእግዚአብሔር የመስጠት ልማድ
ቢኖረን ይጠቅመናል፡፡ ስለዚህ ነው በመካከላችን ቡራኬ፣ ምስጋና[57] እንዲሁም የማታና
74 የማለዳ በረከቶች ተጀምረው እስከ ዛሬ የቀጠሉት፡፡ አስፈሪ ወይም አስደንጋጭ ነገር ሲታይ
ማማተብ ወይም «እግዚአብሔር ሆይ አድነኝ» ወይም «ጌታ ክርስቶስ እርዳኝ»፣ እንዲሁም
ሌሎች በልጅነት ጊዜ የተማርናቸው ልማዶች ሁሉ ዓላማቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ልጆች
በቅዱስ ኒኮላስና በሌሎች ቅዱሳን[58] ክብረ በዓላት ጊዜ እንዲጾሙ ትምህርት
እንደሚሰጣቸው ሁሉ አንድ ሰው ያልጠበቀው ምንም ያህል አናሳ ይሁን መልካም ዕድል
ሲገጥመው «እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን!» «እግዚአብሔር ይህን አደረገልኝ!» ማለት
ይችላል፡፡ እነዚህም ልምምዶች ገዳም ውስጥ ከሚደረጉ የሕይወት ልምምዶች ወይም
ከካርቱሲያኑ ቅድስና ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙና በፊቱም ተቀባይነት ያላቸው
ናቸው፡፡[59]
75 እንዲህ ቀለል ባሉ ዘዴዎች የመጀመሪያውና ሁለተኛው ትእዛዛት የተለመዱ
እንዲሆኑና ወጣቶችም እንዲለማመዱአቸው እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር
ልናሳድጋቸው እንደሚገባን ተመልከቱ፡፡ እንዲህ ስናደርግ መልካም ነገር ሥር ይሰድና
በቅሎ ፍሬ ያፈራል፡፡ በዚህም ለመላው አገር ደስታና ፍስሐ የሚሆኑ ሰዎች ሙሉ ሰው ወደ
76 መሆን ያድጋሉ፡፡ ልጆች በርኅራኄና ደስ በሚያሰኙ ዘዴዎች መማር እንዲችሉ ማድረግ
ትክክለኛ የማሳደጊያ መንገድ ይሆናል፡፡ አንድ ሰው በመምታትና በመደብደብ ለማስተማር
የሚያደርገው ጥረት መልካም ውጤት አይኖረውም፡፡ ቢሆን ቢሆን በበለጠ ልጆቹ መልካም
ሆነው የሚቆዩት በትር ጀርባቸው ላይ እስካለ ድረስ ነው፡፡
77 ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ማስተማር ከዱላና ከበትር ይልቅ እግዚአብሔርን
መፍራትን በልባቸው ሥር እንዲሰድ ያደርጋል፡፡ ለልጆች ስንሰብክ ስብከቱ በልባቸው ጠ
ልቆ እንዲገባ የልጆችን የአነጋገር ዘይቤ ተጠቅመን ልንሰብካቸው ይገባናል፡፡ እስከ አሁን
የመለኮትን ስም በንግግራችን ብቻ ሳይሆን በድርጊታችንና በአኗኗራችን ተገቢ ባልሆነ
መንገድ መጠቀምን የከለከልን ሲሆን በስሙ በተገቢው መንገድ መጠቀም እግዚአብሔርን
ደስ እንደሚያሰኘውና በዚህ ዓይነት መንገድ ስሙን የሚጠሩትን እርሱ አብዝቶ
እንደሚባርካቸውና አለአግባብ በስሙ የሚጠቀሙትን በጣም እንደሚቀጣ ሰው ሁሉ
እንዲያውቅ የእግዚአብሔርን ስም የመጥራት ትክክለኛው መንገድ የትኛው እንደ ሆነ
አስተምረናል፡፡

---

[57] ከመዝ 145፡15-16 እና ከመዝሙር 106፡1፤ 136፡26፤ 147፡9-11 የተወሰዱት ቡራኬና ምስጋና በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከምግብ በፊትና በኋላ የሚጸለዩ ጸሎቶች ነበሩ፡፡ እነርሱንም ሉተር በክርስትና ትምህርት ውስጥ አካትቶአቸዋል፡፡
[58] የቅዱስ ኒኮላስ ክብረ በዓል ታኅሣሥ 6 ቀን የሚውል ሲሆን እርሱም ስጦታ የመስጫ ጊዜ ነው፡፡ ኒኮላስም ጥሩ ዝና የነበረው በሊሲያ የምትገኘው የሚራ መሪ ቄስ ሲሆን ለልጆች ስጦታን የሚሰጥ ለጋስና ቅዱስ ነበር፡፡
[59] የካርቱሲያን ማኅበር በቅዱስ ብሩኖ አማካይነት በፈረንሳይ በግረኖብል አጠገብ በምትገኘው በቻርተሩስ ግራንዴ ውስጥ የተቋቋመ ማኅበር ነው፡፡

*ሦስተኛው ትእዛዝ፦*

78 *«የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ»*
79 *«ቅዱስ ቀን» ወይም «የበዓል ቀን»*[60] *የሚለው ቃላችን የመጣው ሰንበት ከሚለው*
*የዕብራይስጡ ቃል ሲሆን እርሱም በተገቢው መንገድ ሲተረጎም ማረፍ ወይም ዕረፍት*
*ለማድረግ ሥራን ማቆም ማለት ነው። በመሆኑም «ሥራን ለማቆም» የምንጠቀምበት*
80 *የተለመደ አባባል ሲሆን ቃል በቃል «ዕረፍት መውሰድ»*[61] *ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን*
*እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ለይቶ ለዕረፍት እንዲሆን አደረገው፤ እንዲሁም ከሌሎች*
*ቀናት ሁሉ ይበልጥ የተቀደሰ እንዲሆን አዘዘ።*[62] *ውጫዊ አከባበርን በተመለከተ ትእዛዙ*
*የተሰጠው ለአይሁድ ብቻ ነበር። ይኸውም ሰዎችና እንስሳት በማያቋርጥ ሥራ*
*እንዳይደክሙ ከከባድ ሥራ እንዲቆጠቡ፣ እንዲያርፉና ኃይላቸው እንዲታደስ ለማድረግ*
81 *ነበር። ይሁን እንጂ፣ ከጊዜ በኋላ አይሁዳውያን ይህንን ትእዛዝ በጣም አጥብበው*
*በመተርጎም በሚያስከፋ ሁኔታ ያለ አግባብ ሥራ ላይ ስላዋሉት በወንጌል*[63] *እንደምናነበው*
*ከማንኛውም ዓይነት ሥራ በመታቀብ ትእዛዙ ሊፈጸም የሚችል ይመስል ክርስቶስን*
*ይሰድቡና እነርሱ ራሳቸው በዕለተ ሰንበት የሚያደርጓቸውን ነገሮች እንኳ እንዲያደርግ*
*አይፈቅዱለትም ነበር። የትእዛዙ ዐሳብ ግን ይህ አልነበረም። ይልቁንም እንደምንሰማው*
*ቅዱሱን ቀን ወይም የዕረፍትን ቀን መቀደስ ይገባናል ማለት ነው።*
82 *ስለዚህ በውጪአዊ ትርጒሙ መሠረት ይህ ትእዛዝ እኛን ክርስቲያኖችን*
*አይመለከተንም። ምክንያቱም ከተወሰኑ ልማዶች፣ ሰዎች፣ ወቅቶችና ቦታዎች*[64] *ጋር እንደ*
*ተያያዙት የብሉይ ኪዳን ደንቦች ሁሉ ይህም ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ውጪአዊ ነገር በመሆኑ*
83 *ነው። ከእነዚህ ውጫዊ ነገሮች ደግሞ በክርስቶስ ነጻ ወጥተናል።*[65] *ነገር ግን እግዚአብሔር*
*በዚህ ትእዛዝ የሚፈልግብን ምን እንደ ሆነ ለማያስተውሉ ሰዎች ክርስቲያናዊ ትርጓሜ*
*ለመስጠት የተቀደሱ ቀናትን ለአስተዋይና ዕውቀት ላላቸው ክርስቲያኖች ብለን*
*እንደማናከብር ማስገንዘብ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ለእነርሱ እነዚህ አያስፈልጓቸውም።*
*በመጀመሪያ ደረጃ የበዓል ቀናትን የምናከብራቸው ለሰውነታችን ስለሚያስፈልጉት ነው።*
*ሳምንቱን ሙሉ ሥራቸውን ወይም ንግዳቸውን ሲያንቀሳቅሱ የቆዩ አብዛኞቹ ወንዶችና*
*ሴቶች ሠራተኞች ለዕረፍትና ሰውነታቸውን ለማደስ በሳምንት አንድ ቀን ሥራ ማቋረጥ*
84 *እንደሚገባቸው ተፈጥሮ እንኳ ያስተምረናል፤ ይጠይቀናልም። ቀናቱን የምንጠብቅበት*
*ሁለተኛውና እጅግ በጣም አስፈላጊው ምክንያት ሰዎች በዚህ ካልሆነ ሌላ ጊዜ በማያገኟቸው*
*በእንደዚህ ዓይነት የዕረፍት ቀናት ጊዜና ዕድል አግኝተው በአምልኮ ፕሮግራሞች ላይ*

---

[60] *በጀርመንኛ ፌይርታግ የሚለው ቃል ትርጒም የሚከበር ቀን ማለት ሲሆን ቃሉ ሰፋ ተደርጎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከበሩ እንደ ቅዱሳን ቀናት ያሉትን በዓላት የሚያጠቃልል ሆነ።*

[61] *በጀርመንኛ ፌይራቤንድ ማቼን ፌየርን የቃል በቃል ትርጒሙ ማክበር ሲሆን ፌይርታግ ማለት የሚከበር ቀን ወይም የበዓል ቀን ማለት ነው። የበዓሉ ዋዜማ ፍዬራቤንድ ይባላል። በዋዜማው ሥራን ማቆም ፍዬራቤንድ ማቼን ሲሆን በዋዜማው በዓሉን ማክበር መጀመርን ያመለክታል። በኋላ ላይ በማንኛውም ቀን «የማቆም ጊዜ» ማለት ሆነ። ሉተር የሚጠቀመው ሌላው አባባል ሄይሊገን አቤንድ ጌቤን ሲሆን የቃል በቃል ትርጒሙም «የተባረከ ዋዜማን መስጠት» ሲሆን ፍቺውም ሠራተኞች ከበዓሉ በፊት ያለውን ምሽት ሥራን እንዲያቆሙ ፈቃድ መስጠት ማለት ሆነ።*

[62] *ዘፍ* 2፡3።

[63] **ማቴ** 12፡1-13፤ **ማር** 2፡23-28፤ 3፡2-4፤ **ሉቃ** 6፡1-10፤ 13፡10-17፤ 14፡1-6፤ **ዮሐ** 5፡9-18፤ 7፡22-23፤ 9፡14-16።

[64] *ሥዕሎችንና ቅዱሳት ምሥጢራትን አስመልክቶ ሉተር የሰማይ ነቢያት የሚባሉትን በመቃወም እንዲህ በማለት ጽፎ ነበር* (1525) (WA 18: 81, 7-17: *LW* 40: 97-98): *«ምስሎችንና ሰንበትን አስመልክቶ የሙሴ ሕግጋትና ሌሎችም ከተፈጥሮ ሕግጋት ውጪ የሆኑ ሕጎች የተፈጥሮ ሕግ ድጋፍ ስለሌለው ባዶና ለየት ባለ መልክ ለአይሁድ ሕዝብ የተሰጠ ሕግ ነው፤ ይህም ማለት ንጉሠ ነገሥት ወይም ንጉሥ በራሱ ግዛት ውስጥ እንዲያገለግል የሚያወጣው ሕግ ዓይነት ነው። ለምሳሌም እንደ ሳክሶኒው ሳችሴንስንጌል እና ተፈጥሮአዊ ሕግጋት እንደ ሆኑቱ ወላጆችህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ እንደሚሉትና በሁሉም ስፍራ እንደሚያገለግሉት ሕግጋት ማለት ነው። ይህም ማለት የሙሴ ሕግጋት ለአይሁዶች እንደ ሳችሴንስንጌል ስለሆነ እኛን አሕዛብን ግራ ሊያጋባን አይገባውም። ይኸውም እዚያም የተፈጥሮ ሕጉ ተመሳሳይ ቢሆንም ሳችሴንስንጌል በፈረንሳይ እንደማይሠራ ማለት ነው። ሳችሴንስንጌል በ13ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ የተጻፈና ከእንግሊዙ ሕግ ጋር እኩል ቢሆንም በመጀመሪያ በማግድቡርግና በሃልቤርስታድ ቀጥሎ በጀርመን በመላ የሚያገለግል ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕገጋትን የያዘ ነው»።*

[65] **ቈላ** 2፡16-17 *ይመልከቱ።*

*እንዲገኙና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ለመወያየት እንዲሰበሰቡና ምስጋና፣ መዝሙርና ጸሎት ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡባቸው ነው::*[66]

85 *ነገር ግን የትኛውም ቀን በራሱ ከሌላው የተሻለ ስላልሆነ በአይሁዳውያን መካከል ይደረግ እንደ ነበረው ይኸኛው ወይም ያኛው ቀን መሆን ይገባዋል በማለት ለአንድ ለተወሰነ ቀን ብቻ አምልኮን መወሰኑ ተገቢ አይደለም እላለሁ። በእውነቱ አምልኮ በየቀኑ ሊደረግ ይገባዋል። ይሁን እንጂ፣ ይህ አብዛኛው ሕዝብ ሊያደርገው ከሚችለው በላይ ስለ ሆነ በሳምንት ቢያንስ አንድ ቀን ሊለይለት ይገባል። እንግዲህ ከጥንት ጀምሮ እሑድ ለዚህ ዓላማ በመመደቡ ነገሮች ሥርዓት በጠበቀ ሁኔታ እንዲከናወኑና ማንም አስፈላጊ ባልሆነ ፈጠራ ትርምስ እንዳይፈጥር ቀኑ ሊለወጥ አይገባም::*

86 *እንግዲያስ የትእዛዙ ቀላል ትርጕም ይህ ነው፡- ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ የበዓል ቀናት ስናከብር የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር እነዚህን ቀናት መጠቀም አለብን። በዚህ ቀን ልናደርገው የሚገባን እውነተኛው ተግባር ለወጣቶችና ለአብዛኛው ሕዝብ ጥቅም ይሆን ዘንድ ቃሉን መስበክ ሊሆን ይገባል። ይሁን እንጂ፣ ሰንበትን ማክበር ድንገተኛና ልናስወግደው የማንችለውን ሥራ ከመሥራት እስኪያግደን ድረስ እጅግ ውሱን መሆን አይገባውም::*

87 *በዚህ መሠረት «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ ዐስብ» ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ስትጠየቁ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» ማለት «ቅዱስ አድርጎ መጠበቅ ነው» ብላችሁ መልሱ። ቀኑን ቅዱስ አድርጎ መጠበቅስ ምን ማለት ነው? ቀኑን ቅዱስ አድርጎ መጠበቅ ማለት ቅዱስ ቃላትን ለመናገር፣ ቅዱስ ሥራን ለመሥራትና ቅዱስ ሕይወትን ለመምራት ከማዋል ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ቅዱስ ተደርጎ የተፈጠረ በመሆኑ ቀኑ በራሱ መቀደስ አያስፈልገውም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለአንተ የተቀደሰ እንዲሆን ይፈልጋል። ስለዚህ ቅዱስ የሆነ ወይም ያልሆነ ነገር በማድረግ ቀኑን በማሳለፍህ*
88 *ቀኑ በአንተ ምክንያት የተቀደሰ ወይም የረከሰ ይሆናል ማለት ነው። እንዲህ ያለ መቀደስ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? የሰንበትን ቀን የምንቀድሰው ከምድጃው ጀርባ ስንቀመጥና ከከባድ ሥራ ስንቆጠብ ወይም አናታችን ላይ የአበባ ጕንጕን ስናደርግና የክት ልብሳችንን*[67] *ስንለብስ ሳይሆን፣ እንደ ተባለው የእግዚአብሔርን ቃል ስንጠቀምበትና ራሳችንን በቃሉ ስናለማምድ ነው::*

89 *በእውነቱ እኛ ክርስቲያኖች ሁሉንም ቀናት የተቀደሱ ቀናት ልናደርጋቸውና ራሳችንን ለተቀደሱ ነገሮች ብቻ ልናውል፡- ማለትም በየዕለቱ በእግዚአብሔር ቃል ቊጥጥር ሥር ልንሆንና በልባችንና በአንደበታችን ልንይዘው ይገባናል። ይሁን እንጂ፣ አስቀድመን እንዳልነው ሁላችንም ጊዜውና ነጻ የመዝናኛ ሰዓቶች የሌሉን ስለ ሆነ በእነዚህ ነገሮች ላይ ብቻ ማተኮር የምንችልበትና በተለይ ዐሠርቱን ትእዛዛት፣ የእምነት መግለጫንና የጌታ ጸሎትን በትኩረት የምንመለከትበት፣ በሳምንትም ለወጣቶች ለበርካታ ሰዓታት፣ ለመላው ማኅበረሰብ ደግሞ ቢያንስ አንድ ቀን መለየትና በዚህ ሁኔታ በሚጠና የእግዚአብሔር ቃል መሠረት መላው ሕይወታችንንና ሕልውናችንን ልንቈጣጠረው ይገባናል። ይህም ተግባራዊ*
90 *በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ቅዱሱ ቀን በእውነት ይከበራል። ነገር ግን ይህ በማይሆንበት ጊዜ የክርስቲያኖች ቅዱስ ቀን ተብሎ ሊጠራ አይገባውም፤ ምክንያቱም ክርስቲያን ያልሆኑት በዘመናችን የእግዚአብሔርን ቃል ስለማይሰብኩ ወይም ስለማይተገብሩ ነገር ግን በተቃራኒው ስለሚያስተምሩና ስለሚኖሩ አንዱንም ቀን ቅዱስ አድርገው ሳይጠብቁ ዕለት*

---

[66] *ሥዕሎችንና ቅዱሳት ምሥጢራትን አስመልክቶ ሉተር የሰማይ ነቢያት የሚባሉትን በመቃወም እንዲህ በማለት ጽፎ ነበር* (1525) (WA 18: 81, 26-82, 6: *LW* 40: 98) *«ሙሴ ስላዘዘው ሰንበትን ወይም እሑድን ማክበር አያስፈልግም፣ ሰውና እንስሳት እንዲያርፉና ኃይላቸውን እንዲያድሱ ተፈጥሮ ያስተምረናል። ሙሴም ይህንን የተፈጥሮ ሕግ ተገንዝቦ ክርስቶስ እንዳደረገው በሰው ሥር አስቀሞጦታል ማቴ* 12፡1 *እና ማር* 3፡2። *ለዕረፍት የሚከበር ከሆነ ሰንበትን ማክበር የማይፈልግ ሰው የሰንበትን ሕግ ተላልፎ ተፈጥሮ እንደሚፈቅድለት በሌላ ቀን ሊያርፍ ይችላል። ሰንበት ለስብከትና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የተሰጠ ቀን ነው»*።

[67] *ወጣቶች ለጭፈራና ለዘፈን ሲዘጋጁ የሚያደርጓቸው ነገሮች::*

ዕለት በቤተ ክርስቲያን እየዘመሩና ደወል እየደወሉ የሚቆሙ የቀሳውስት ስብስብም ቀኑን
በዕረፍትና በሥራ ፈትነት ሊያሳልፉ ይችላሉ፡፡
91 ከቅዱሳን መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ በላይ እውነተኛው ቅዱሱ[68] የእግዚአብሔር ቃል
ነው፡፡ በእርግጥም እኛ ክርስቲያኖች የምናውቀውና ያለን እርሱ ብቻ ነው፡፡ የቅዱሳን ሁሉ
አጽሞች ወይም ቅዱስና የተለዩ ልብሰ ተክህኖዎች በአንድ ላይ ቢከመሩ ቅንጣት ያህል
ሊረዱን አይችሉም፤ ምክንያቱም ማንንም ሊቀድሱ የማይችሉ በድን ነገሮች ስለ ሆኑ ነው፡፡
92 የእግዚአብሔር ቃል ግን ሁሉንም የሚቀድስ መዝገብ ነው፡፡ ቅዱሳን ራሳቸው ቅዱሳን
የሆኑት በእርሱ ነው፡፡ በየትኛውም ጊዜ ብናስተምረው፣ ብንሰብከው፣ ብንሰማው፣
ብናነበው፣ ወይም ብናሰላስለው በውጪአዊ ሥራ ምክንያት ሳይሆን ቅዱሳን በሚያደርገን
በቃሉ ምክንያት ቀኖቻችንና ሥራዎቻችን የተቀደሱ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም ሕይወታችንና
ሥራችን በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ወይም ቅዱስ ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር
ቃል ላይ መመሥራት ይገባቸዋል በማለት ባለማቋረጥ ደጋግሜ እናገራለሁ፡፡ ይህ
93 በሚሆንበት ጊዜ ትእዛዙ ተግባራዊና የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በተቃራኒው ምንም ያህል ውብና
የሚያበራ ቢመስልም ወይም የእግዚአብሔርን ቃል ሳያውቁ በገዛ ሥራቸው ቅድስናን
እንደሚፈልጉ እንደ መንፈሳዊ የሕይወት[69] ዘይቤ አራማጆች በቅዱሳን ቅሪቶች ሙሉ
ለሙሉ ቢሸፈንም ከእግዚአብሔር ቃል የተለየ ማንኛውም ተግባር ወይም ሥራ
በእግዚአብሔር ፊት ያልተቀደሰ ነው፡፡
94 እንግዲህ ይህ ቀን የራሱ አገልግሎት እንዲኖረው የዚህ ትእዛዝ ኃይልና ጉልበት
ያለው በማረፉ ላይ ሳይሆን በመቀደሱ ላይ እንደ ሆነ አስተውሉ፡፡ ሌላው ሥራና ንግድ
በእውነቱ ሠሪው በመጀመሪያ ቅዱስ ካልሆነ እነርሱ ቅዱስ እንቅስቃሴዎች አይባሉም፡፡
ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ ሰው ሁሉ ቅዱስ የሚሆንበትን ሥራ ማከናወን ይገባዋል፡፡ ይህም
ሥራ እንደ ሰማነው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ይከናወናል፡፡ ስለዚህ ቦታዎች፣
ጊዜያት፣ ሰዎችና ውጪአዊ የአምልኮ ሥርዓቶች በሙሉ የተመሠረቱትና የተወሰኑት
የእግዚአብሔር ቃል ኃይሉን በአደባባይ እንዲገልጥ ነው፡፡
95 በእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ የትኛውም ቀን ስለማይቀደስ እጅግ ብዙ ነገር
በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚመረኮዝ ስለ ሆነ እግዚአብሔር ይህ ትእዛዝ በጥብቅ እንዲጠ
በቅ እንደሚፈልግና ቃሉን የሚንቁትን በተለይ በተሰጣቸው ጊዜ ሊማሩ ፈቃደኛ
96 ያልሆኑትን እንደሚቀጣ ልንገነዘብ ይገባናል፡፡ ስለዚህ ይህ ትእዛዝ የሚጣሰው
በስግብግብነታቸው ወይም በቁም ነገር የለሽነት የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ቸል
በሚሉት ወይም በመጠጥ ቤቶች ፍጹም ሰክረው እንደ አሳማ በሚጋደሙት፣ ቅዱሱን ቀን
ያለ አግባብ በሚጠቀሙበትና በሚያረክሱት ብቻ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ
ማንኛውም ሌላ መዝናኛ በሚሰሙት፣ በዘልማድ ብቻ ስብከት ለመስማት በሚሄዱ፣
በዓመቱ መጨረሻ ላይ ልክ እንደ ዓመቱ መጀመሪያ ትንሽ ዕውቀት ብቻ ይዘው ወደ
97 ቤታቸው በሚመለሱትና በሌላውም ሕዝብ ይጣሳል፡፡ አንድ ሰው ወደ ቅዱስ ቊርባን ሥነ
ሥርዓት ከሄደ ወይም ወንጌል ሲነበብ[70] ከሰማ ሰንበትን በአግባቡ እንዳከበረ ተደርጎ ይታሰብ
ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ማንም ስለ እግዚአብሔር ቃል አይጠይቅም፤ ወይም ማንም
አያስተምረውም፡፡ አሁንም የእግዚአብሔር ቃል እያለን እንኳ ይህንን ተገቢ ያልሆነ ድርጊት
ማስተካከል ተስኖናል፤ ምክንያቱም እንዲሰበክልንና እንድንመከርበት ፈቃደኞች እንሁን
እንጂ በልብ ትኩረት ስለማንሰማ ነው፡፡

---

[68] በጀርመንኛ *Heiligtumb* የቅዱሳን መገልገያ ዕቃ ማለት ሲሆን ሉተር የሰጠውን ትርጉም ለመረዳት እርሱ፡- «የቅዱሳንን መገልገያ ዕቃዎችና ሌላም ነገር እንድናከብር ትምህርት ይሰጠን ነበር እውነተኛው ቅዱስ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ነው» በማለት የጻፈውን አንብቡ፡፡
[69] ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት እንዲሁም ቄሶችና ጳጳሳት፡፡ *Against the Spiritual Estate of the Pope and the Bishops, Falsely So Called* (1522) (WA 10/2: 105-58; *LW* 39:239-99) የሚለውን ርእስ የሉተርን ጽሑፍ ተመልከት፡፡
[70] በቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓት ጊዜ ሊቈርቡ የማይፈልጉ አባላት ወንጌሉ ከተነበበ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ይወጣሉ፡፡

98 *እንግዲህ ቃሉን ልትሰሙ ብቻ ሳይሆን ልትማሩትና ልትጠብቁት የሚገባችሁ
መሆኑን አስተውሉ። የራሳችን ውሳኔ ነው ወይም በጣም አስፈላጊ አይደለም ብላችሁ
አታስቡ። ቃሉን እንዴት እንደ ሰማችሁት፣ እንደ ተማራችሁትና እንዳከበራችሁት
በኃላፊነት የሚጠይቃችሁ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።*
99 *እንደዚሁም ሁሉንም የሚያውቁና ተጨማሪ ትምህርት እንደማያስፈልጋቸው
የሚሰማቸው ከዚህም የተነሣ አንድ ወይም ሁለት ስብከት ሰምተው የሚሰለቻቸውና
የሚደክማቸው ትዕቢተኛ መናፍስትም ቅጣት ይገባቸዋል። ይህም ሞት ከሚገባቸው
ኃጢአቶች መካከል የሚቈጠር ሲሆን እርሱም ኦሲዲያ*[71] *ነው። ኦሲዲያ ዲያብሎስ
ብዙዎችን የሚያታልልበትና በድንገትም የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው የሚነጥቅበት
የተራቀቀ ዘዴ ሲሆን እንደ ስንፍና፣ ስልቹነት፣ የማይድንና ቀስ በቀስ የሚጎዳ መንፈሳዊ
በሽታና የመሳሰሉትን ያካትታል።*
100 *ይህንን ልንገራችሁ። ምንም እንኳ ቃሉን ጠንቅቃችሁ የምታውቁ ብትሆኑ በየዕለቱ
በዲያብሎስ ግዛት ያላችሁና እርሱም ሳታውቁ ጥርጥርን በልባችሁ ውስጥ ጭሮ እነዚህን
ሦስቱንና ሌሎችንም ትእዛዛት እንድትተላለፉ ለማድረግ የማያርፍ መሆኑን ነው። ስለዚህ
ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችሁ፣ በአፋችሁና በጆሮአችሁ ማኖር አለባችሁ።
ምክንያቱም ልባችን ባዶ በሆነበትና ቃሉን በማንሰማበት ጊዜ ሁሉ ዲያብሎስ ሳናውቅ ወደ*
101 *ልባችን ገብቶ ጥፋት ያደርሳል። በሌላ በኩል ግን የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ
ስናስበው፣ ስንሰማውና ስንጠብቀው የቃሉ ኃይል ያለ ፍሬ አይቀርም። ይህ ቃል
የማይሠራና የሞተ ቃል ስላልሆነ ልባችንን በዐዲስ መረዳት፣ በደስታና በአምልኮ*
102 *በማንቃቃት ንጹሕ የሆነ ልብንና አእምሮን ይፈጥራል። ስለዚህ ሌላ ነገር ለቃሉ ባያነሣሣን
እንኳ በዚህ ቃል አማካይነት ዲያብሎስ እንደሚወጣና እንደሚሸሽ፣ ይህ ትእዛዝ
እንደሚፈጸምና እግዚአብሔር ከግብዝነት ይልቅ በዚህ እንደሚደሰት ዐውቀን ቃሉን
ለማጥናት መነሣሣት አለብን።*

## *አራተኛ ትእዛዝ*

103 *እስካሁን ትኵረታቸውን እግዚአብሔር ላይ ያደረጉትን የመጀመሪያዎቹን ሦስት
ትእዛዛት ተምረናል። አንደኛ፣ እግዚአብሔርን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በሙሉ ልባችን
ልናምነው፣ ልንወደውና ልንፈራው ይገባናል። ሁለተኛ፣ ቅዱስ ስሙን ውሸትን ወይም
ማንኛውንም ዓይነት ክፉ ዓላማ ለመደገፍ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ውዳሴና ለሥራችንም ሆነ
ለባልንጀሮቻችን ጥቅምና መዳን ልንጠቀምበት ይገባል። ሦስተኛ፣ በበዓላት ወይም በዕረፍት
ቀናት ባሕርያችን ወይም ሕይወታችን ሁሉ የተገራ እንዲሆን ራሳችንን የእግዚአብሔርን
ቃል በትጋት ለማጥናት መስጠት ይገባናል። ቀጥሎ ግን ከባልንጀራችን ጋር የተያያዙ
ሌሎች ሰባት ትእዛዛት ይቀርባሉ። ከእነዚህም የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው፦*
104 *«አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለው ነው።*
105 *እግዚአብሔር ይህንን የሕይወት ስምሪት ማለትም ለአባትነትና ለእናትነት
ከየትኛውም በሥሩ ካሉ የሕይወት ስምሪቶች የበለጠ ልዩ ክብርና ስፍራ ሰጥቶታል።
ወላጆቻችንን እንድንወዳቸው ብቻ ሳይሆን እንድናከብራቸውም ጭምር እግዚአብሔር
አዝዞናል። ወንድሞችን፣ እኅቶችን እና ባልንጀሮችን በተመለከተ እንድንወዳቸው እንጂ
ከዚህ ያለፈ ወይም የበለጠ እንድናደርግላቸው አልታዘዝንም። ነገር ግን እግዚአብሔር
አባትና እናትን በምድር ላይ ካሉ ሌሎች ሰዎች ሁሉ ለይቶና አብልጦ ከራሱ ቀጥሎ*
106 *አስቀምጧቸዋል፤ ምክንያቱም ማክበር ከመውደድ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነገር ነው። ማክበር
መውደድ ብቻ ሳይሆን በውስጣቸው ወደ ተሰወረው ግርማ ሞገስ አነጣጥሮ መግባትን፣*

---

[71] *ቃሉ ከአርስጣጣሊስ የሥነ ምግባር መመሪያ፣* bk. IV, *Acedia (or acidia)* *የተገኘ ሲሆን ሞት ከሚገባቸው ሰባቱ ኃጢአቶች መካከል አንዱ ነው።*

107 ትሕትናን እና ጨዋነትን ያካትታል፡፡ ማክበር እነርሱን በፍቅርና በከፍተኛ አክብሮት
ማናገርን ብቻ ሳይሆን ከሁሉ በላይ በድርጊቶቻችን፣ በልባችንና በአካላችን ከእግዚአብሔር
ቀጥሎ የመጨረሻውን ከፍተኛ ስፍራ ለእነርሱ መስጠታችንና እነርሱን ማክበራችንን
ማሳየትንም ይጠይቃል፡፡ በሙሉ ልባችን ልናከብረው የሚገባንን ማንኛውንም ሰው በእውነት
ከፍተኛና የከበረ አድርገን መቍጠር ይገባናል፡፡
108 ስለዚህ ወጣቶች ወላጆቻቸውን እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች አድርገው
እንዲያከብሯቸውና ምንም ያህል ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ፣ ወይም ድሃ፣ አቅመ
ደካማ ወይም የማይመች ባሕርይ ያላቸው ቢሆኑ በእግዚአብሔር የተሰጡ እናታቸውና
አባታቸው መሆናቸውን ማስታወስ እንደሚገባቸው ሊቀረጽባቸው ይገባል፡፡ ከኑሮአቸው
ደረጃ ወይም ከድካማቸው የተነሣ አክብሮት ሊነፈጋቸው አይገባም፡፡ ስለዚህ ወላጆች ምንም
ዓይነት ሰዎች ቢሆኑ ሥርዓቱ እንዲህ እንዲሆን የፈጠረውንና የደነገገውን የእግዚአብሔርን
ፈቃድ እንጂ የሰዎቹን ማንነት ማሰብ የለብንም፡፡ በእርግጥ በእግዚአብሔር ፊት ሁላችንም
እኩል ነን፡፡ ነገር ግን በመካከላችን እንደዚህ ዓይነት መበላለጥ እና ተገቢ የሆነ ልዩነት
እንዲኖር አድርጓል፡፡ ስለዚህም ነው እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ሥልጣን ካለኝ እንደ
አባታችሁ ልትታዘዙኝ ይገባል ብሎ የሚያዝዘን፡፡
109 እንግዲህ በመጀመሪያ፣ ወላጆችን ስለ ማክበር ይህ ትእዛዝ ምን እንደሚፈልግባችሁ
ተማሩ፡፡ ለወላጆች በምድር ከሁሉ በላይ እንደ ከበረ መዝገብ ዋጋ ልትሰጡዋቸው ይገባል፡፡
110 ሁለተኛ፣ በንግግራችሁ ሥርዓት በጎደለው ሁኔታ ሳይሆን በአክብሮት እንድትቀርቡአቸው
እንጂ እንዳትነቅፏቸው ይልቁንም እንድትገዙላቸውና ከመስመር ርቀው ቢወጡ እንኳ
111 ከሚፈጽሙት ስሕተት አንደበታችሁን ልትቈጥቡ ይገባል፡፡ ሦስተኛ፣ በተግባሮቻችሁም
ጭምር ማለትም በአካላችሁና በሀብታችሁ ልታገለግሏቸው፣ ልትረዷቸው፣ በእርጅናቸው፣
በሕመማቸው፣ በድካማቸው ወይም በድህነታቸው ጊዜ በመንከባከብ ልታከብሯቸው ይገባል፡፡
ይህን ሁሉ በደስታ ብቻ ሳይሆን በትሕትናና በአክብሮት ለእግዚአብሔር የምታደርጉትን
ያህል ልትፈጽሙት ይገባል፡፡ ወላጆቻቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው በልባቸው
የሚያውቁ ሰዎች ወላጆቻቸው በእጦትና በረሀብ እንዲሠቃዩ ማድረግ የሌለባቸው ሲሆን
ከራሳቸው አስበልጠው ወይም ከራሳቸው እኩል ያላቸውን ሁሉ የተቻላቸውን ያህል
ሊያካፍሏቸው ይገባል፡፡
112 ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በሁለተኛ ደረጃ ምን ዓይነት ትልቅ፣ መልካምና ቅዱስ
ሥራ ለልጆች እንደ ተሰጠ አስተውሉ፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን እንዲህ ዓይነቱ ነገር
ሙሉ በሙሉ ይናቃል፤ ይገፋልም፡፡ ማንም ይህንን አገልግሎት እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ
ወይም እንደ ቅዱስ፣ እንደ መለኮታዊ ቃልና አስተምህሮ አይቀበለውም፡፡ እንደ
እግዚአብሔር ትእዛዝ ቈጥረነው ቢሆን ኖሮ በእነዚህ ቃላት መሠረት የሚኖሩ ሁሉ ቅዱሳን
ሰዎች እንደ ሆኑ ለሁሉም ግልጽ በሆነ ነበር፡፡ የሁሉም መረዳት እንዲህ ቢሆን ኖሮ ማንም
ገዳም ማቋቋም ወይም ለየት ባለ መልኩ መንፈሳዊ ነው የሚባል የአኗኗር ዘይቤ
መመሥረት አያስፈልገውም ነበር፡፡[72] ይልቁንም እያንዳንዱ ልጅ ይህንን ትእዛዝ በመጠበቅና
ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት በቀና ሕሊና፡- «መልካም እና ቅዱስ ሥራ ማድረግ
እንደሚኖርብኝ እግዚአብሔር ራሱ ስላዘዘ ለወላጆቼ ክብርና መታዘዝን ከመስጠት የተሻለ
113 ነገር መኖሩን ዐላውቅም፤ እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ራሳችን ከምንፈለስፈው ከማንኛውም
ነገር የበለጠ ክቡር መሆን አለበት፤ ከእግዚአብሔርም የበለጠ ወይም የተሻለ መምህር
ስለማይገኝ እርሱ ከሚሰጠው ትምህርት የሚሻል በእርግጥ አይኖርም፤ በእውነት መልካም
ሥራዎችን ማድረግ ከፈለግን ምን ማድረግ እንዳለብን በበቂ ሁኔታ እርሱ የሚያስተምረን
ሲሆን እርሱም እነዚህን በማዘዝ ደስ የሚሰኝባቸው ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ይገልጣል፤

[72] «መንፈሳዊ የአኗኗር ዘይቤ» የሚለው ሐረግ በሃይማኖታዊ ማኅበሮች ውስጥ የሚኖሩ ቄሶችንና አባላትን ለማመልከት የተለመደ ቃል ነበር፡፡

እንግዲህ ይህን ያዘዘው እግዚአብሔር ከሆነና የተሻለ ምንም ነገር የማይፈለግብኝ ከሆነ
በጭራሽ ላሻሽለው አልችልም» ማለት ይችላል።
114 ስለዚህ ቀና ልጆች በተገቢው መንገድ በተማሩና በእውነተኛ ብፅዕና ባደጉ ነበር።
ይህ ሲሆን ወላጆቻቸውን እየታዘዙና እያገለገሉ በቤት ውስጥ በመኖር ለሰው ሁሉ
የመልካምነትንና የደስተኝነትን ግልጽ ትምህርት የሚያስተላልፉ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ፣
ማንም ሰው ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ትኩረት የመስጠት ግዴታ እንዳለበት አልተሰማውም።
በዚህ ፈንታ ልጆች ልብ ሊሉት እንዳይችሉ ቸል ተብሎና ተትቶ ነበር። የእግዚአብሔርን
ይሁንታ ሳንጠይቅ ልጆቻችን እኛው በፈለሰፍናቸው ነገሮች በመደነቅ አፋቸውን ከፍተዋል።
115 ስለዚህ በመጨረሻ ስለ እግዚአብሔር ብለን ከፊታቸው ሌሎች ነገሮችን በማንሣት
ልጆች ለዚህ ትእዛዝ ቀዳሚ ስፍራ መስጠት እንደሚገባቸው እንማር። ልጆች በእውነተኛ
መልካም ሥራዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል ከፈለጉ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ወይም
በወላጆቻቸው ምትክ ከበላያቸው ላሉ ሰዎች ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ ይገባቸዋል። ይህንን
የሚያውቅና የሚያደርግ ልጅ በመጀመሪያ ደረጃ በገዛ ራሳቸው በመረጡት ሥራ ከተጠ
መዱት ሰዎች በተቃራኒ፦ «ተመልከቱ ይህ ሥራ በሰማይ ያለውን አምላኬን የሚያስደስት
ነው። ይህንን በእርግጠኝነት ዐውቃለሁ» በማለት በደስታ ለመናገር የሚችልበት ትልቅ
116 መጽናናት ያገኛል። በገዛ ሥራቸው የተጠመዱት በሙሉ ከበርካታ፣ ታላላቅ፣ አድካሚና
አስቸጋሪ ሥራዎቻቸው ጋር ይቅረቡና ይናገሩ። እግዚአብሔር ለገዛ ግርማው ከመታዘዝ
ቀጥሎ ከደነገገውና ካዘዘው ለአባትና ለእናት ከመታዘዝ የበለጠና የከበረ አንዳች ሥራ
ማስገኘት ይችሉ እንደ ሆነ እንመልከት። እንደ ዋና አድርገው ለእግዚአብሔር ቃልና
ፈቃድ ከታዘዙ፣ የወላጆቻችን ፈቃድና ቃል ለእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ተገዢ እስከ
ሆኑና የቀደሙትን ትእዛዛት እስካልተቃረኑ ድረስ ምንም ነገር ከወላጆቻችን ፈቃድና ቃል
የበለጠ ተደርጎ መቈጠር የለበትም።
117 በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንደዚህ የከበሩና እርሱን የሚያስደስቱ ሥራዎችን
እንድትሠሩ ስለ መረጣችሁና ብቁ ስላደረጋችሁ ከልባችሁ ልትደሰቱና ልታመሰግኑት
ይገባል። ይህም ሥራ እጅግ በጣም ተራና የተናቀ ተደርጎ የሚታይ ቢሆን እንኳ በእኛ
ብቃት ሳይሆን የከበረ ዕንቊና ቅዱስ መቅደስ በሆነው በእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ
118 ውስጥ ቦታ ስላለውና ስለ ተቀመጠ እንደ ታላቅና ክቡር ነገር ልትቈጥሩት ይገባል። እጅግ
በጣም ጥንቁቅ የሚባሉት ባሕታውያን[73] ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት[74] በመንፈሳዊ
ልምምዶቻቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሆነ አንዳች ሥራን በማቅረብ ደስታን
በተሞላ ልብ «ይህ ሥራ በጣም እንደሚያስደስትህ ዐውቃለሁ» ማለት ቢችሉ ምን ያህል
ዋጋ በከፈሉ ነበር። እነዚህ ምስኪን እና ጎስቋላ ሰዎች በእግዚአብሔርና በመላው ዓለም ፊት
ቆመው በዚህ ትእዛዝ መሠረት በኖረው አንድ ትንሽ ብላቴና ፊት በሀፍረት በመሸማቀቅ
በመላ ሕይወታቸው ለልጁ የሚጠጣ ውሃ እንኳ ለመስጠት የማይበቁ መሆናቸውን ለመናዘዝ
119 ሲገደዱ ምን ይሆኑ ይሆን? ለዚህም ብድራታቸው ነቀፋና ችግር ብቻ ስለሚሆን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከእግራቸው በታች በመርገጥ ራሳቸው በፈለሰፏቸው[75] ሥራዎች
ራሳቸውን በከንቱ ማሠቃየታቸው ለዲያብሎሳዊ ጥመታቸው ይጠቅማቸዋል።
120 «እስቲ ተመልከቱ፣ እነርሱ እስከ ሞት ድረስ ቢጾሙና በጕልበታቸው ተንበርክከው
መጸለዩን ባያቋርጡ እንኳ ይህ ከባሕታውያን ሁሉ ቅድስና ይበልጣል» ብሎ ልባችን ወደ
ሥራ መሄድ ሲችልና የታዘዘውን ሲፈጽም በደስታ ሊዘልና ሊጥለቀለቅ አይገባውምን?

[73] ቪሰንት ኦፕሶጠውስ ወደ ላቲን ቋንቋ በተረጎመው የክርስትና ትምህርት በዚህና በሚቀጥለው አንቀጽ Carthusians የሚለውን ስያሜ Carmelites በሚለው ተክቶ ነበር። (በ1584 በተካሄደው የመጽሐፈ ስምምነት ኅትመት የታረመው ሁለተኛው ለውጥ ብቻ ነበር)። በ1154 የተቋቋመው የካርሜላይት ማኅበር ሲጀመር ውስብስብ ያልሆነ የአኗኗር ዘይቤን ይከተል የነበረ ሲሆን በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ማለቂያ ላይ ግን ወደ (Mendicant) ማኅበር ተለወጠ። በ16ኛው ክፍለ ዘመን በሁለቱ ባሕታውያን የአቪሎዋ ቅድስት ቴሬሣና የመስቀሉ ቅዱስ ዮሐንስ ተሐድሶ አካሄደ።
[74] የሴቶች ባሕታውያን ማኅበር በ1147 ተቋቋመ።
[75] ለምሳሌ ለባሕታውያኑ በጥብቅ ጸጥታ ውስጥ ሆኖ መቆየት ግዴታ ነበር።

*ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህንን ማዘዙን የተረጋገጠ መልእክትና መለኮታዊ ምስክርነት*
*ሲኖራችሁ እነዚህን ሌሎች ሥራዎች በተመለከተ ግን አንዲትም ቃል አላዘዘም። ነገር ግን*
*ይህንን አለማመኑ የዓለም አሳዛኝና አስቃቂ ዕውርነት ነው፤ ዲያብሎስ በሐሰተኛ ቅድስናና*
*በገዛ ሥራችን አብረቅራቂነት ፍጹም አዚም አድርጎብናል።*
121 *ስለዚህ በድጋሚ ልናገር። ከእግዚአብሔር ንጹሕ ቃል ወደሚዋሽ የዲያብሎስ ከንቱ*
*ነገሮች እንዳንወሰድ ሰዎች ጆሮዎቻቸውንና ዓይኖቻቸውን ከፍተው ልብ ቢሉ ደስ ይለኛል።*
*ይህ ከሆነ ሁሉ መልካም ይሆናል። ወላጆች በቤታቸው የበለጠ ደስታ፣ ፍቅር፣ በጎነትና*
122 *ስምምነት ያገኛሉ። ልጆች የወላጆቻቸውን ልብ ሙሉ በሙሉ ይማርካሉ። በሌላ በኩል ዱላ*
*በጀርባቸው ላይ ካላረፈ በስተቀር የማይታዘዙና የሚጠበቅባቸውን በጭራሽ የማያደርጉ*
*ልጆች እግዚአብሔርንም ወላጆቻቸውንም ያስቈጧቸዋል። በመሆኑም ራሳቸውን ከዚህ*
123 *በረከትና ከሕሊና ደስታ እያጎደሉ በሥራቸው መከራን ብቻ የሚያከማቹ ይሆናሉ። ሰው*
*ሁሉ በቅሬታ እንደሚናገረው በዓለማችን ላይ ነገሮች በአሁኑ ጊዜ እያደጉ ያሉት በዚህ*
*መንገድ ነው። ወጣቱም ሆነ ሽማግሌው መረንና ያልተገራ ሆነዋል፤ በማንኛውም ሰው ላይ*
*የልከኝነትና የጨዋነት ወይም የክብር ስሜት ዐይታይም። በድብደባ ካልተገደዱ በስተቀር*
*ምንም ነገር ወደው አይሠሩም። በቻሉት መንገድ ሁሉ ከበስተጀርባ ሆነው እርስ በርስ ስም*
*ይጠፋፋሉ፤ ሰውን ያዋርዳሉ። በመሆኑም እግዚአብሔር በሁሉ ዓይነት ችግርና መከራ*
124 *ውስጥ እንዲሰጥሙ በማድረግ ይቀጣቸዋል። ወላጆችም እንኳ ቢሆኑ እንደ ሕግ ስለ*
*ልጆቻቸው ብዙ ማድረግ አይችሉም፤ አንድ ሞኝ ሌላውን ያሳድጋል፤*[76] *እነርሱ የኖሩትን*
*ዓይነት ኑሮ ከእነርሱም በኋላ ልጆቻቸው ይኖራሉ።*
125 *ይህን ትእዛዝ የምንጠብቅበትም የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚልቀው ምክንያት ይህ*
*መሆን አለበት እላለሁ። አባት ወይም እናት ባይኖረን ከዚህ ትእዛዝ የተነሣ እግዚአብሔር*
*አባት ወይም እናት ብለን የምንጠራውን የእንጨት ወይም የድንጋይ ቍራጭ እንዲያቆምልን*
*እንመኝ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር ሕያው የሆኑ ወላጆች ስለ ሰጠን እነርሱን*
*በማክበርና በመታዘዝ ምን ያህል ደስተኛ ልንሆን በተገባን፤ እንደምናውቀው ይህ*
*እግዚአብሔርንና መላእክቱን ሁሉ እጅግ የሚያስደስት፣ አጋንንትን ሁሉ የሚያበሳጭ*
*ከመሆኑም ባሻገር በቀደሙት ትእዛዛት ከተጠቀሰውና ከከበረው እግዚአብሔር አምላክ*
*ቀጥሎ ወላጆቻችንን ማክበር ልናደርገው የምንችለው እጅግ ትልቁ ሥራ መሆኑን*
126 *ስለምናውቅ ነው። ምጽዋት መስጠትና ለባልንጀሮቻችን የምናደርጋቸው ሌሎች የበጎነት*
*ሥራዎች ሁሉ እንኳ ከዚህ ጋር አይስተካከሉም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህንን*
*የሕይወት ይዞታ ከሌሎች ሁሉ በላይ ከፍ አድርጎታል። በእርግጥም በምድር ላይ በእርሱ*
*ስፍራ አቁሞታል። ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድና ደስታ የምንችለውን ያህል በደስታ*
*እንድናደርግ ምክንያትና ተነሣሽነት ሊሆነን ይገባል።*
127 *ከዚህ በተጨማሪ ከወላጆቻችን ለተቀበልናቸው ቸርነትና በጎ ነገሮች ሁሉ በዓለም*
128 *ፊት ውለታ ያለብን መሆኑን ማሳየት ግዴታችን ነው። ነገር ግን እዚህም ላይ እንደ ገና*
*ዲያብሎስ ዓለምን ይገዛልና እኛ ሁላችን እግዚአብሔርን እንደምንረሳ ሁሉ ልጆችም*
*ወላጆቻቸውን ይረሳሉ። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመግበን፣ እንደሚጠብቅንና*
*እንደሚጋርደን፣ ምንስ ያህል በነፍስም በሥጋም እንደሚባርከን ማንም ዐያስብም። በተለይ*
*ክፉ ቀን ሲመጣ ትዕግሥት አጥተን እንቈጣለን፤ እናጕረመርማለን። በሕይወታችን ሁሉ*
*የተቀበልናቸውን በረከቶች ሁሉ እንረሳለን። ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር በወላጆቻችንም ላይ*
*እናደርጋለን። በመንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ካልተመራ በቀር ይህን የሚገነዘብና የሚያጤን ልጅ*
*የለም።*
129 *እግዚአብሔር ይህንን የዓለም ብልሹነት በደንብ ያውቃል። በመሆኑም ትእዛዛቱ*
*ሰዎች ሁሉ ለወላጆቻቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እንዲያስቡ ያስታውሱአቸዋል፣*

---

[76] *ምሳሌአዊ አነጋገር።*

*ያስገድዱአቸዋልም፡፡ ከዚያም አካላቸውንና ሕይወታቸውን ከወላጆቻቸው እንደ ተቀበሉና
በወላጆቻቸውም እንክብካቤና ጥበቃ ባይደረግላቸው ኖሮ በገዛ ቆሻሻቸው መቶ ጊዜ ይጠፉ
130 እንደ ነበር ይገነዘባሉ፡፡ ስለዚህ ነው የጥንቱ ጠቢባን ዲዮ፣ ጠሬንቲቡስ ኤት ማጅስትሪስ
ኖን ፖቴስት ሳቲስ ግራቲኤ ሪፖንዲ* Deo, parentibus et magistris non potest satis gratiae
*rependi*, «*እግዚአብሔር፣ ወላጆችና መምህራን በበቂ ሁኔታ ሊመሰገኑና ውለታቸው
ሊመለስ*[77] *በጭራሽ አይቻልም*» *ያሉት፡፡ ጉዳዩን በዚህ መንገድ የሚያዩትና የሚያስቡት
ያለምንም ግፊት ለወላጆቻው ክብር ይሰጣሉ፤ እግዚአብሔርም መልካምን ነገር ሁሉ
በእነርሱ በኩል እንደ ሰጣቸው ተገንዝበው ወላጆቻቸውን ከፍ አድርገው ያዩአቸዋል፡፡*
131 *ከዚህ ሁሉ በላይ ይህንን ትእዛዝ እንድንጠብቅ የሚያነሣሣን ሌላው ጠንካራ
ማበረታቻ እግዚአብሔር ከትእዛዙ ጋር የሰጠን «በምትኖርበት ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም»
የሚለው ተወዳጅ የተስፋ ቃል ነው፡፡ ይህ ትእዛዝ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን
132 እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያስብ ራሳችሁ ልታዩ ትችላላችሁ፡፡ ትእዛዙ እርሱን ደስ
የሚያሰኘውና የሚያረካው ብቻ ሳይሆን በሁሉም በረከት ወደ ተሞላ ሰላማዊና አስደሳች
133 ሕይወት ሊመራን እጅግ ለላቀ ጥቅማችን የታሰበ መሣሪያም እንደ ሆነ ይናገራል፡፡ ስለዚህ
ቅዱስ ጳውሎስም በኤፌሶን* 6፡2-3 *ላይ «መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ
እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርሷም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ
ናት» በማለት ይህንን ትእዛዝ እጅግ ያከብረዋል፤ ያወድሰዋልም፡፡ ምንም እንኳ ሌሎቹ
ትእዛዛት የራሳቸው የሆነ የተስፋ ቃል በተዘዋዋሪ መንገድ ቢኖራቸውም እንደዚህኛው ግን
በግልጽና በቀጥታ የተነገረ የለም፡፡*
134 *ይህንን ትእዛዝ የሚጠብቅ ሁሉ ፍሬውንና ብድራቱን ማለትም መልካም ቀናትን፣
ደስታንና ብልጽግናን እንደሚያገኝ ታያላችሁ፡፡ በሌላ በኩል ትእዛዙን የማይታዘዙት ሁሉ
ቅጣት፣ በአጭር መቀጨትና በሕይወት ደስተኛ አለመሆን ይገጥማቸዋል፤ ምክንያቱም
በቅዱሳት መጻሕፍት ረጅም ዕድሜ መኖር ማለት ማርጀት ብቻ ሳይሆን ለረጅም
የሕይወት ዘመን የሚሆነውን ነገር ሁሉ ማግኘት ማለት ስለ ሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ያለ
እነርሱ በዚህ ሕይወት መደሰት ወይም ለረጅም ጊዜ መዝለቅ የማይቻልባቸውን ለምሳሌ
ጤና፣ የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ ምግብ፣ ሰላምና መልካም አስተዳደር የመሳሰሉትን ማግኘት
135 ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ለአባትህና ለእናትህ መልስ መስጠት ወይም ከእነርሱ ምሪት
ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆንክ ለፍርድ አስፈጻሚው  መልስ ስጥ፤ ለእርሱም ደግሞ መልስ
ካልሰጠህ ለጨካኙ አጫጅ*[78] *ለሞት መልስ ስጥ! ይህ በአጭሩ የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡፡
136 ለእርሱ ታዘዝ፤ ፍቅርንና አገልግሎትንም ስጠው፤ እርሱም ሁሉን አትረፍርፎ ይመልስልሃል፡፡
በሌላ በኩል ብታስቈጣው ሞትንና የሞት ቅጣት አስፈጻሚውን ይልክብሃል፡፡*
137 *ባለመታዘዝ ምክንያት ካልሆነ በቀር በየዕለቱ የሚሰቀሉ፣ አንገታቸውን የሚቀሉ፣
ወይም በእሽክርክሪት ላይ ተወጥረው የሚሠቃዩ በርካታ ወሮበሎች ለምን ይኖራሉ? እነዚህ
በበጎነት ለማደግ ፈቃደኞች አይደሉምና በውጤቱም ከእግዚአብሔር ቅጣት የተነሣ
በሕይወታቸው የሚታየውን መጥፎ ዕድልና ሐዘን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት
ክፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ በተፈጥሮአዊውና በጊዜው በሚሆን አሟሟት  አይሞቱም፡፡*
*ይሁን እንጂ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውና የሚታዘዙ በሰላምና በመረጋጋት
ረጅም ዕድሜን በመኖር ይህንን በረከት ይቀበላሉ፡፡ እላይ እንደ ተጠቀሰው እስከ ሦስትና
138 አራት ትውልድ ድረስ የልጅ ልጆቻቸውን ያያሉ፡፡ በተጨማሪም ከተሞክሮ እንደምናውቀው
መልካም የሆኑና ብዙ ልጆች ያሏቸው ዕድሜ ጠገብ ቤተ ሰቦች ሲገኙ እነርሱ በተራቸው*

---

[77] *ሉተር ልጆችን በትምህርት ቤት ስለ ማቆየት* (1530) (WA 30/2: 579; *LW* 46:252-53) *በጻፈውና ከአሕዛብ ወገን የሆነው አርስጣጣሊስም እንደሚለው «በአጭሩ አንድ ጥንቁቅ እና ቅን የትምህርት ቤት ኃላፊ መምህር ወይም በታማኝነት ልጆችን የሚያሠለጥን ወይም የሚያስተምር ማንም ሰው በምንም መልኩ አገልግሎቱ በክፍያ ሊተመን አይችልም»፡፡ Aristotle, Nicomachean Ethics 8, 16 and 9, 1 ን ተመልከት፡፡*

[78] *በጀርመንኛ Streckebein ቃል በቃል በሆነ ትርጉም እግርን መዘርጋት ሲሆን ሞትን የሚያመለክት የጀርመን ሕግና ሉተር ብዙውን ጊዜ ይጠቀምበት የነበረው ቃል ነው፡፡*

በመልካም አስተዳደግ ያደጉና ወላጆቻቸውን ያከበሩ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው፡፡ በሌላ
በኩል ስለ ክፉዎች በመዝሙረ ዳዊት 109፡13 ላይ «ልጆቹ ይጥፉ፤ በአንድ ትውልድ ስሙ
139 ይደምሰስ»[79] ተብሎ ተጽፏል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለመታዘዝ እጅግ ከፍ ያለ ዋጋ
እንደሚሰጥ፣ እጅግም ደስ እንደሚሰኝበትና በብልጽግናው እንደሚባርከው ነገር ግን
ትእዛዙን የሚተላለፉትን ለመቅጣት እንደማያመነታ በማወቅ ለእርሱ መታዘዝ አስፈላጊ
መሆኑ ማስጠንቀቂያ ይሁናችሁ፡፡
140 ይህንን ሁሉ የምለው ትእዛዙ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ ማንም ስለማያምንና
በተለይም ከጳጳሳዊ ሥርዓት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ትኩረት ወይም ትምህርት ሳይሰጥበት
ስለ ቆየ አሁን ግን ይህ ትእዛዝ በወጣቶች ላይ በሚገባ እንዲቀረጽባቸው ነው፡፡ እነዚህ
ቃላት ግልጽና ቀላል በመሆናቸው ሰዎች ሁሉ በሚገባ እንደሚያውቋቸው ያስባሉ፡፡ ስለዚህ
ቀለል አድርገው ያልፏቸውና ትኩረታቸውን በሌሎች ጉዳዮች ላይ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን
ትእዛዝ ቸል ሲሉ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደሚያስቈጡት ትእዛዙን ሲያከብሩ ደግሞ
ምን ያህል የከበረውንና ተቀባይነት ያለውን ሥራ እንደሚያከናወኑ ማስተዋልና ማመን
ይሳናቸዋል፡፡
141 በተጨማሪ ከዚህ ትእዛዝ ጋር በተያያዘ ተግባራቸው ማዘዝና ማስተዳደር ለሆነ
የበላይ አለቆች ስለሚገባው መታዘዝ መጥቀስ ይገባናል፡፡ ሥልጣን ሁሉ ከወላጅነት ሥልጣን
የሚገኝና የሚወጣ ነው፡፡ አባት ልጁን በራሱ ማሳደግ ካልቻለ አንድ የትምህርት ቤት ኃላፊ
ልጁን እንዲያስተምረው ያደርጋል፡፡ እርሱም በጣም ደካማ ከሆነ የጓደኞቹንና የጎረቤቶቹን
እርዳታ ይጠይቃል፡፡ የሚሞት ከሆነ ደግሞ ለዚህ ዓላማ ለተሾሙ ሌሎች ሰዎች ኃላፊነቱንና
142 ሥልጣኑን ይሰጥና ይወክላል፡፡ በተጨማሪ ቤቱን ከእርሱ ሥር ሆነው የሚያስተዳድሩ ወንድ
ወይም ሴት ሠራተኞች ሊኖሩት ይገባል፡፡ ስለዚህም ቤተ ሰብን በተመለከተ ዋና ወይም
የበላይ ተብለው የሚጠሩት ሁሉ በወላጆች ስፍራ ስለሚቆሙ የማስተዳደር ኃይልና
ሥልጣናቸውን ከእነርሱ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ በሥልጣን ክልላቸው እንደ አባቶች ስለ
ተሾሙና ለሕዝባቸውም አባታዊ ልብ ሊኖራቸው ስለሚገባ በቅዱሳት መጻሕፍት አባቶች
ተብለው ተጠርተዋል፡፡ ስለሆነም ከጥንት ጀምሮ ሮማውያንና የሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች
የቤቱን ጌቶችና እመቤቶችን ቤተ ሰብ (ጠትሪስ ኤት ማትሪስ ፋሚሊያስ) ብለው ይጠ
ሯቸዋል፡፡ ማለትም የቤት አባቶችና የቤት እናቶች እንደ ማለት ነው፡፡ እንደገናም ልዑላንና
የበላይ ገዢዎቻቸው የመላው አገር አባቶች (ጠትሪስ ጠትሪኤ)[80] ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡
ሌሎቹ እንዲህ ባለ መንገድ ገዢዎቻቸውን የሚመለከቱ ከሆነ እኛ ስለ ገዢዎቻችን እንዲህ
የማናደርገውን ወይም መሪዎቻችንን በእንደዚህ ዓይነት አክብሮት የማንይዛቸውንና
የማናከብራቸውን እኛን ክርስቲያን ተብዬዎችን እጅግ የሚያሳፍረን ነው፡፡
143 ልጅ የአባቱና የእናቱ ውለታ ያለበትን ያህል ሌሎቹ የቤተ ሰቡ አባላትም
አለባቸው፡፡ ስለዚህ ወንዶችና ሴት አገልጋዮች ለጌቶቻቸውና ለእመቤቶቻቸው ለመታዘዝ
ብቻ ሳይሆን እንዲገዙላቸው፣ እንደ አባቶቻቸውና እንደ እናቶቻቸው አድርገው
እንዲያከብሩአቸውና የሚጠበቅባቸውን ማንኛውንም ነገር ባለማመንታት በደስታና በልግስና
ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ እላይ በተገለጸው ምክንያት ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነና
ከሌሎች ሥራዎች ሁሉ የበለጠ እርሱን የሚያስደስተው በመሆኑ ሊያደርጉት ይገባል፡፡
144 ለማገልገል ስላገኙት ዕድል[81] ገንዘብ እንኳ ለመክፈል ፈቃደኞች መሆን ያለባቸው ሲሆን
ወርቃማ የሆኑ ሥራዎች እንዴት እንደሚሠሩ ለመማር እንዲችሉ ጌቶችና እመቤቶች
በማግኘታቸው ሊደሰቱ ይገባቸዋል፡፡ በቀድሞ ጊዜ እነዚህ ሥራዎች ቸል ተብለውና ተንቀው

[79] የሉተር ትርጉም፡፡
[80] ሴስሮ የካትላይንን ሴራ ካጋለጠ በኋላ ይህንን ማዕረግ አግኝቶአል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የሮማ ነገሥታት የማዕረግ መጠሪያ ሆነ፡፡
[81] በአባሪ ጽሑፎች የሚደረጉ እንደዚህ ዓይነት ክፍያዎች በመካከለኛው ዘመን ጉልታዊ ሥርዓት የተለመዱ ነበሩ፡፡

ነበር፡፡ ለራሳቸው ጉዳትና በመጥፎ ሕሊና በዲያብሎስ ስም ወደ ገዳማት፣ ወደ ሃይማኖታዊ
ጉዞዎችና የስርየት ማግኛ ጽሑፎች[82] ፍለጋ ይሮጡ ነበር፡፡

145 የመታዘዙ ሥራ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ግልጽ ቢሆን የቤት ውስጥ ሠራተኛ
ሴት በደስታ እየዘለለች እግዚአብሔርን የምታወድስና የምታመሰግን ከመሆኗም በላይ
ቀለብና ደሞዝ የምታገኝበትን ሥራ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በመሥራት እንደ ታላላቅ
146 ቅዱሳን የሚቈጠሩት እንኳ የሌላቸውን በረከት ታገኝ ነበር፡፡ ይህንን ማወቅና «የዘወትር
የቤት ሥራህን ብትሠራ እርሱ ከመነኩሳት ሁሉ ቅድስናና የመሥዋዕትነት ሕይወት የተሻለ
ነው» ማለት ትልቅ ክብር አይደለምን? በተጨማሪም የምትሠራው ሁሉ እንደሚሳካና
እንደሚቀና የተስፋ ቃሉ አለህ፡፡ ሥራን በተመለከተ ከሁሉ በተሻለ መልኩ የተባረከ ወይም
147 ቅዱስ የሆነ ሕይወት መኖር የምትችለው እንዴት ነው? በእርግጥ በእግዚአብሔር ዕይታ
ሰውን ቅዱስ የሚያደርገው እምነት ነው፡፡ ሥራችን ሰዎችን የሚያገለግል ሲሆን እምነት
ደግሞ እግዚአብሔርን ያገለግላል፡፡ እዚህ ላይ ማንኛውንም በረከት፣ ጥበቃና ከለላ ከጌታ
148 ታገኛለህ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ደስተኛ ሕሊና እንዲኖርህ የሚያደርግና መቶ እጥፍ
ብድራትን የሚመልስልህ ቸር አምላክ ይኖርሃል፡፡ ቀናና ታዛዥ ሰው ብትሆን በእውነት
የተከበርህ ሰው[83] ነህ፡፡ እንዲህ ባትሆን ግን የእግዚአብሔርን ቍጣ እና ቅሬታ እንጂ ሌላ
ነገር አታገኝም፡፡ በልብህም ሰላም አይኖርም፡፡ በመጨረሻም ችግርና መከራ ሁሉ
ይደርስብሃል፡፡

149 ይህ ካላሳመነህና ቀና ሰው ካላደረገህ በሞት ወደሚቀጣውና ወደ ጨካኙ አጫጅ
አሳልፈን እንሰጥሃለን፡፡[84] ስለዚህ ምክርን ሊቀበሉ የሚወዱ ሁሉ እግዚአብሔር
እንደማይቀልድ ማወቅ ይገባቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ይናገርሃል፤ መታዘዝንም ከአንተ ይጠ
ብቃል፡፡ ብትታዘዘው ውድ ልጁ ትሆናለህ፡፡ ይህንን ትእዛዙን ብትንቅ ግን ሃፍረት፣
መከራና ሐዘን ብድራትህ ይሆናሉ፡፡

150 እላይ እንደገለጽነው ለሕዝብ ባለሥልጣናት መታዘዝም «አባትነት» በሚባለው
የሕይወት ይዞታ ውስጥ የሚካተትና ሁሉን የሚጠቀልል እንደ መሆኑ ተመሳሳዩን መናገር
ይቻላል፡፡ ምክንያቱም እዚህ ላይ አንድ ሰው ለአንድ ቤተ ሰብ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው
ነዋሪዎች፣ ለዜጎች እና ለበታች ሠራተኞችም አባት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
በወላጆቻችን በኩል እንደሚያደርገው እግዚአብሔር በባለሥልጣኖቻችን በኩል ምግብን፣
መጠለያንና ቤተ ሰብን ይሰጠናል፤ በእነርሱም በኩል ይጠብቀናል፡፡ ስለዚህ እንደ ዋና
መለያቸው ይህን ስምና ማዕረግ ከሙሉ ክብር ጋር ስለ ተሸከሙ፣ በምድር ላይ እንደ ክቡር
ሀብትና በዋጋ እንደማይገመት ጌጥ ልናከብራቸውና ልንቀበላቸው ይገባናል፡፡

151 ታዛዥና ጠቃሚ ለመሆን ፈቃደኛ የሆኑ ክብርም የሚጠይቀውን ሥራ ሁሉ
ለማድረግ የተዘጋጁ ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኙትና ሐሴትና ደስታ
ብድራታቸው እንደ ሆኑ ያውቃሉ፡፡ በሌላ በኩል በፍቅር ባያደርጉትና ባለሥልጣንን ቢንቁና
ቢያምፁ ወይም አለመረጋጋትን ቢፈጥሩ ምንም ዓይነት ሞገስ ወይም በረከት እንደማያገኙ
ይወቁ፡፡ አንዲት የወርቅ ሳንቲም[85] እንዳገኙ ሲተማመኑ ሌላ ቦታ ላይ ዐሥር እጥፍ ያጣሉ፤
ወይም ደግሞ በስቅላት በሚቀጡበት ሥራ ላይ ይወድቃሉ፤ ወይም በጦርነት፣ በቸነፈርና
በድርቅ ይጠፋሉ፤ ወይም ልጆቻቸው መጥፎ ባሕርይ ይዘው ያድጉባቸዋል፡፡ በመጨረሻም

[82] በመካከለኛው ዘመን መሠረተ እምነት የስርየት ማግኛ ጽሑፎች ለኃጢአት ጊዜያዊ ቅጣት መደምሰሻዎች ወይም ከሙታን ነፍስ ጊዜያዊ ማቆያ መውጫዎች ነበሩ፡፡ ታማኞች ከሚያደርጉት ከክርስቶስ፣ ከድንግል ማርያምና ከቅዱሳን ሥራዎች በላይ ለራሳቸው መዝገብ አከማችተዋል፡፡ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ይህንን መዝገብ በቤተ ክርስቲያን ስም ተቈጣጥሮአል፡፡ የስርየት ማግኛ ጽሑፎቹ ራሳቸው የማይሸጡ የነበሩ ቢሆንም፣ የስርየት ጽሑፍ ተቀባዮቹ መቀበላቸውን በሚያመለክቱ የምስክር ወረቀቶች ሽያጭ የተጧጧፈ ንግድ ነበር፡፡ የኃጢአት ጸጸትና ኑዛዜ የሚቀድሙ ቢሆንም በተግባር የኃጢአት ቅጣት እንዲደመሰስና ከሙታን ነፍስ ጊዜያዊ ማቆያ ለመውጣት ለገንዘብ ማግኛ ሲባል የስርየት ማግኛ ጽሑፍ የምስክር ወረቀቶችን ሰዎች እንዲገዙ ማድረጉ የሕዝብን ትኩረት ስቦአል፡፡

[83] በጀርመንኛ፣ Junker.

[84] በጀርመንኛ፣ Streckebein.

[85] Gulden የሚባለው በመጀመሪያ ትልቅ የወርቅ ሳንቲም በኋላም የብር ሳንቲም ነበር፡፡

የክፉ ሥራቸውን ብድራት እስኪያገኙ ድረስ ሠራተኞቻቸው፣ ጎረቤቶቻቸው፣ ባዕድ የሆኑ
ሰዎች እና አምባገነኖች ጉዳትን፣ ኢፍትሐዊነትንና ጥቃትን ያደርሱባቸዋል፡፡
152 እንግዲህ የመታዘዝ ሥራዎች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ እንደ ሆኑና እንደዚህ
ያለ የተትረፈረፈ ብድራትም እንዳላቸው ብንገነዘብ በፍጹም በረከት ተሞልተን ልባችን
የሚፈልገውን ሁሉ እናገኛለን፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ከማይታወቅ ጨኺ የጎዳና አዟሪ[86]
የወጡ ይመስል ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃልና ትእዛዛት እንደሚንቁ ዐይተህ አንተም
153 እንዲሁ ብታደርግ እግዚአብሔርን የምትጻፈር ሰው እንደሆንህ እናያለን፡፡ አንተው
እንዳደረግኸው መልሶ ሊከፍልህ ለእርሱ እንዴት ይከብደዋል? በዚህ ምክንያት
በእግዚአብሔር ዘንድ ከመዋረድ፣ ከመናቅና ከእርሱ ዘንድ ከሚመጣው መከራ ይልቅ
154 በእግዚአብሔር ሞገስ፣ ሰላም እና በረከት እጅግ የተሻለ ሕይወት ትኖራለህ፡፡ በአሁኑ ጊዜ
ዓለም ታማኝ ባለመሆን፣ በእፍረት፣ በመከራ እና በግድያ የተሞላችው ለምን ይመስልሃል?
ምክንያቱም ሁሉም የገዛ ራሳቸው ጌታና ከባለሥልጣናት[87] አመራር ነጻ መሆንን እንዲሁም
ለማንም ግድ ሳይላቸው ደስ ያላቸውን ሁሉ ለማድረግ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ስለዚህ
እግዚአብሔር አንዱን ወሮበላ በሌላው[88] አማካይነት ይቀጣዋል፡፡ አንተም ጌታህን
ስታጭበረብርና ስትንቅ ሌላው ሰው ይመጣና በአንተ ላይ እንዲሁ ያደርጋል፡፡ በእርግጥ
ከክፉ አደራረግህ የተነሣ በገዛ ቤትህ በሚስትህ፣ በልጆችህ ወይም በአገልጋዮችህ አማካይነት
ዐሥር እጥፍ ትቀበላለህ፡፡
155 በእርግጥም መከራ የሚሰማን ከመሆኑ የተነሣ ስለ ክህደት፣ ስለ ሁከትና ስለ ፍትሕ
መጓደል እናጕረመርማለን፤ እናንጎራጕራለን፡፡ ነገር ግን እኛ ራሳችን በትክክል ቅጣት
የሚገባን ወሮበሎች መሆናችንና ተቀጥተንም በጭራሽ የማንሻሻል መሆናችንን ለማየት
ፈቃደኞች አይደለምን፡፡ ጸጋንና በረከትን እምቢ ከማለታችን የተነሣ ያለ ምንም ምሕረት
156 መከራ እንጂ ሌላ ነገር አለመቀበላችን ትክክል ነው፡፡ በምድር ላይ በጥቂት ቦታዎች ጥቂት
እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ኖረው እንጂ እንደዚህ የበዙ በረከቶች ባልተሰጡን ነበር፡፡
እንደ እኛ ቢሆን ኖሮ በቤት ውስጥ ቤሳ ቤስቲን[89] ወይም በእርሻችን ላይ አንዲት ገለባ
157 ባልኖረችን ነበር፡፡ ከዘቀጥንበት መከራና ዕውርነት እንድንወጣና የእግዚአብሔርን ቃልና
ፈቃድ በትክክል ተረድተን ከልባችን እንድንቀበለው ምናልባት አንድ ሰው እንኳ ልብ
ይለው ይሆናል በሚል ተስፋ በርካታ ቃላትን ተጠቅሜ ለማስተማር ተገድጃለሁ፡፡
ከእግዚአብሔርም ቃል ለአሁኑም ሆነ ለዘላለም የተትረፈረፈ ሐሴትን፣ ደስታንና ድነትን
እንዴት እንደምናገኝ ልንማር እንችላለን፡፡
158 እንግዲህ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ ሦስት ዓይነት አባቶችን አስተዋውቀናል፡፡ እነርሱም፡-
በደም የሆኑ አባቶች፣ የቤተ ሰብ መሪ አባቶችና የአገር መሪ አባቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም
መንፈሳዊ አባቶች አሉ፡፡ እነዚህ «አባት» ተብለው ሊጠሩ የሚፈልጉ ነገር ግን አባታዊ
ተግባራቸውን ያልተወጡትና በጳጳሳዊ ሥርዓት ያሉት አይደሉም፡፡ ምክንያቱም መንፈሳዊ
አባት የሚለው ስም በእግዚአብሔር ቃል የሚገዙንንና የሚመሩንን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡
159 ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4፡15 ላይ «ብዙ አባቶች የሉአችሁም፤ እኔ በክርስቶስ
ኢየሱስ በወንጌል ወልጃችኋለሁና» በማለት አባትነት እንዲህ ዓይነት በመሆኑ ይመካል፡፡
160 እነዚህ እውነተኛ አባቶች ስለ ሆኑ ከሌሎች ሁሉ በላይ ሊከበሩ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ዓለም
እንደዚህ ዓይነት አባቶችን የሚያከብርበት መንገድ እነርሱን ከአገር ማሳደድና ቍራሽ ዳቦ

[86] በጀርመንኛ፣ Holhipler ቃል በቃል ትርጉም «ዳቦ አዟሪ፡፡»
[87] ጀርመንኛ፣ *Kaiserfrei* ቃል በቃል ትርጉም «ከንጉሠ ነገሥቱ ነጻ የሆነ፡፡»
[88] ምሳሌያዊ አገላለጽ፡፡
[89] ቃል በቃል ትርጉም *Heller* ትንሽ ሳንቲም በታወቁ አገላለጾች እዚህ ግባ የማይባል የገንዘብ መጠንን ይወክላል፡፡

*እንኳ መንፈግ ስለ ሆነ ይህን ክብር አይሰጣቸውም።*[90] *በአጭሩ ቅዱስ ጳውሎስ በ*1*ኛ*
*ቆሮንቶስ* 4፡13 *ላይ እንደሚናገረው «የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ» መሆን ተገብቷቸዋል።*
161 *ሆኖም ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ ለነፍሳቸው ለሚተጉላቸው «እጥፍ ክብር»*[91] *የማሳየት*
*ግዴታ ስላለባቸው በመልካም ሊይዟቸውና የሚያስፈልጋቸውንም ሊያቀርቡላቸው እንደሚገባ*
*ሊቀረጽባቸው ያስፈልጋል። ይህን ብታደርጉ እግዚአብሔርም የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ*
162 *በመስጠት በእጦት እንዳትሠቃዩ ያደርጋችኋል። ነገር ግን እዚህ ላይ ሰው ሁሉ*
*ይቃወማችኋል። ሁሉም ሆዳቸው እንዳይራብ ይፈራሉ። ስለዚህ ቀድሞ ዐሥር የወፈሩ ሰዎች*
163 *ሆድን*[92] *እንዳልሞሉ አሁን አንድ መልካም ሰባኪን መደገፍ ተስኖአቸዋል። በዚህም*
*ምክንያት እግዚአብሔር ቃሉንና በረከቱን ሊከለክለንና ከዚህም በተጨማሪ ላብና ደም*
*እስኪወጣን ድረስ የሚጨምቁን የሐሰት ሰባኪዎች*[93] *እንደገና እንዲነሱና ወደ ዲያብሎስ*
*እንዲመሩን ፈቅዶላቸዋል።*
164 *የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ትእዛዝ የሚጠብቁት ግን ለተፈጥሮአዊም ሆነ*
*ለመንፈሳዊ አባቶቻቸው ስላደረጉት አስተዋጽኦና ስለሚሰጧቸው ክብር የተትረፈረፈ*
*ብድራት እንደሚቀበሉ የተስፋ ቃል አላቸው። ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት ምግብ፣*
*ልብስና ገንዘብ ማግኘት ሳይሆን ረጅም ሕይወት፣ የእግዚአብሔር ድጋፍና ሰላም ኖሮአቸው*
165 *ለዘላለም ባለጠጎችና የተባረኩ ይሆናሉ። ስለዚህ እናንተ ማድረግ የሚገባችሁን ብቻ አድርጉ*
*እና እንዴት እንደሚደግፋችሁና የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እንደሚያዘጋጅላችሁ*
*ለእግዚአብሔር ተዉለት። የተስፋ ቃል እስከ ገባላችሁና እስከ አሁንም እንዳልዋሻችሁ ሁሉ*
*አሁንም አይዋሻችሁም።*
166 *አክብሮት ልንሰጣቸው የሚገባቸው ሰዎች በመኖራቸውና በዚህም ምክንያት*
*እንደዚህ ያለ የተስፋ ቃል የተሰጠን በመሆኑ ልባችን በደስታና በፍቅር እስኪቀልጥ ድረስ*
*እጆቻችንን ዘርግተን እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ይህ ሊያበረታታን ይገባል። እነዚህን*
*የተስፋ ቃላት ለማግኘትም እስከ ምድር ዳርቻ ለመሮጥም ፈቃደኛ መሆን ይገባናል።*
*ምክንያቱም የዓለም የተባበረ ጥረት በሕይወታችን ላይ አንዲት ሰዓት መጨመር ወይም*
*አንዲት የስንዴ ቅንጣት ብድግ ማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር ግን እንደ ልባችሁ*
*መሻት ማንኛውንም ነገር አትረፍርፎ ሊሰጥ ይችላል፤ ፈቃደኛም ነው። ይህንን የሚንቅም*
*ሆነ ለነፋስ አሽቀንጥሮ የሚወረውር አንዲትን የእግዚአብሔርን ቃል እንኳ መስማት*
*አይገባውም።*
167 *እዚህ ላይ ይህ ትእዛዝ የሚመለከታቸው ሁሉ ከበቂ በላይ ተነግሯቸዋል። በተጨማሪ*
*ኃላፊነታቸውን በተመለከተ እንዲመሩአቸው የተሾሙባቸውን ሰዎች እንዴት መያዝ*
*እንደሚገባቸው ለወላጆች መስበክ መልካም ነው። ኃላፊነታቸው በዐሠርቱ ትእዛዛት በግልጽ*
*ተዘርዝሮ ባይቀመጥም በሌሎች በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግን በዝርዝር*
*ተብራርቶአል። እንዲያውም እግዚአብሔር በዚህ ስለ አባት እና ስለ እናት በሚናገረው*
168 *ትእዛዝ እንዲካተት አድርጓል። ምክንያቱም ይህ ኃላፊነት ወይም ሥልጣን በወሮበሎችና*
*በአምባገነኖች እንዲያዝ አይፈልግም። እነዚህንም አክብሮት እንዲቀበሉ እዚህ ክብር*
*(ማለትም በማስተዳደር ኃይልና መብት) ላይ አያስቀምጣቸውም። በዚህ ፈንታ ወላጆች*
*የተባሉት ሁሉ ከሁሉ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ዕዳ እንዳለባቸው፤ ለልጆቻቸው፣*
*ለሠራተኞቻቸውና ለበታቾቻቸው ቊሳዊ ድጋፍ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር*
*ምስጋናና ክብር ሊያመጧቸው የተሰጧቸውን ኃላፊነትና ተግባራት ማሰብ ይገባቸዋል።*

---

[90] *በተሐድሶ የመጀመሪያዎቹ ዐሥርተ ዓመታት የሉተርን መልእክት የሰበኩት ብዙዎች ሰባኪዎች የተያዙበትን ሁኔታ የሚያንጸባርቅ አባባል ሲሆን ይህም የሆነው ከ*1525 *የገበሬዎች ዓመፅ በኋላ ነበር። ከ*1527-28 *የተካሄደው የሳክሶኒው ጉብኝት ይህንን ዐሳይቷል።*

[91] 1*ጢሞቴዎስ* 5፡17።

[92] *በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ገቢ ከመሬትና ከንብረቶች የሚገኝ ስጦታ ነበር። ነገር ግን ተሐድሶ በተካሄደበት ጊዜ የሚገኘው ሀብት በባለሥልጣናት ሥር በመዋሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ያለ ምንም ገቢ ቀርተዋል።*

[93] «*የሐሰት ሰባኪዎች*» (*ሚክያስ* 2፡11 *ተመልከት*) *በ*16*ኛው ክፍለ ዘመን የታወቀ አባባል ነበር።*

169 ስለዚህ የወላጅነት ኃላፊነት የእናንተ የመደሰትና የስሜት ተለዋዋጭነት ጉዳይ እንዳይደለ
ዐስቡ። ስለ ጉዳዩ በተጠያቂነት የሚያቆመን የእግዚአብሔር ጥብቅ ትእዛዝና ውሳኔ ነው።
170 ዳሩ ግን እንደ ገና አስቸጋሪው ሐቅ ማንም ይህንን የሚያስተውል አለመኖሩ ነው።
ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ልጆችን የሰጠን ለራሳችን ደስታና መዝናናት፣ ሠራተኞቻችንን
እንደ ላምና አህያ ልናሠራቸው፣ የሚገዙልንን ሰዎች ደግሞ ደስ እንዳለን እንድንይዛቸው
ነገር ግን ምን እንደሚማሩ ወይም እንዴት እንደሚኖሩ እኛን እንደማይመለከተን አድርጎ
171 ያስባል፤ ማንም ይህ መለኮታዊ ትእዛዝ እንደ ሆነና የምንጠየቅበትና ስለ ቸልተኛነታችንም
እርሱ የሚቀጣን መሆኑን ለመገንዘብ ፈቃደኛ አይደለም። ወይም ለወጣቱ ምን ያህል
172 አስፈላጊ መሆኑን በጥብቅ ትኩረት የሚሰጥ የለም። ለማኅበራዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው
ጉዳይ ችሎታና ብቃት ያላቸውን ሰዎች የምንፈልግ ከሆነ እግዚአብሔርን እና ዓለምን
እንዲያገለግሉ ለማስተማርና ለማሠልጠን የምንቈጥበው ጒልበት፣ ጊዜና ገንዘብ በእውነቱ
173 ሊኖር አይገባም። ለእነርሱ ብዙ ገንዘብና ንብረት ወጣ ብሎ ማሰብ አይገባንም። በእርግጥም
ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ከእኛ እርዳታ ውጪ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን
ሊሰጣቸውና ባለጠጎች ሊያደርጋቸው ይችላል። ነገር ግን እንደ ፈቃዱ እንድናሳድጋቸውና
174 እንድንመራቸው እግዚአብሔር ልጆችን በአደራ ሰጥቶናል። ይህ ኃላፊነት ባይኖር ኖሮ
አባቶችና እናቶች አያስፈልጉትም ነበር። ስለዚህ ባያደርጉት መለኮታዊውን ጸጋ
እንደሚያጡ ዐውቀው ሰዎች በመጀመሪያ ልጆቻቸውን እግዚአብሔርን በመፍራት ዕውቀት
እንዲያድጉ ቀጥሎም ተሰጥኦ ካላቸው በመደበኛው ትምህርት ላይ ተሰማርተው እንዲማሩና
በሚፈለጉበት ቦታ ሁሉ እንዲያገለግሉ የማድረግ ዐቢይ ኃላፊነት አለባቸው።
175 ይህ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ክብር የሚሆኑ ሰዎች
እንዲሠለጥኑ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርከንና ጸጋውንም ይሰጠን ነበር። በተጨማሪም
መልካምና ብቁ የሆኑ ዜጎች እንዲሁም ቤታቸውን በበጎነት የሚያስተዳድሩ (ቲቶ 2፡5)
በታማኝነት ቅን ልጆችንና አገልጋዮችን የሚያሳድጉና የሚመሩ መልካም ሴቶች ይኖሩን
176 ነበር። ልጆቻችሁን ጠቃሚና እግዚአብሔርን የሚፈሩ መንፈሳዊ ሰዎች አድርጋችሁ
ሳታሳድጉአቸው ስትቀሩና ቸልተኛ ስትሆኑ ምን ያህል የከፋ ጉዳት እንደምታደርሱ ዐስቡ።
እናንተ ምንም ያህል ቅዱሳንና ቀና ብትሆኑ በገዛ ልጆቻችሁ መልካም ያልሆነ አስተዳደግ
177 ምክንያት በራሳችሁ ላይ ኃጢአት፣ ቍጣና ሲኦልን ታወርዳላችሁ። ይህ ትእዛዝ ስለ ተናቀ
እግዚአብሔር ዓለምን ክፉኛ ይቀጣል። ስለዚህም ሥርዓት፣ መንግሥት ወይም ሰላም
ጠፍቷል። ሁላችንም ስለዚህ ሁኔታ እናጒረመርማለን። ነገር ግን የገዛ ራሳችን ስሕተት
እንደ ሆነ ማየት ይሳነናል። እኛ እነርሱን ካሠለጠንንበት የተሳሳተ መንገድ የተነሣ ስድና
178 የማይታዘዙ ሠራተኞች አሉን። ይህ ለማስጠንቀቂያ ያህል በቂ ነው፤ የበለጠ ማብራሪያ
በሌላ ጊዜ ይቀርባል።[94]

## *አምስተኛ ትእዛዝ*

179 «አትግደል»
180 እስከ አሁን መንፈሳዊና ሕዝባዊ ስለ ሆኑት አስተዳደሮች ተነጋግረናል።
የተነጋገርነውም መለኮታዊ ስለ ሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝና ምድራውያን የሆኑት
አባቶቻችን ስለሚያደርጉልን አመራርና ለእነርሱም ስለ መታዘዝ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ
ትእዛዝ ከቤታችን ወጣ በማለትና በባልንጀሮቻችንና በጎረቤቶቻችን መካከል እንዴት
181 እንደምንታይ እንማራለን። ስለዚህ በዚህ ትእዛዝ የእግዚአብሔርን ወይም የምድራዊውን
መንግሥት ሥልጣን አናነሣም። በዚህ ትእዛዝ ጥናታችን ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ
ምድራዊ መንግሥት የማናነሣው የአንድን ሰው ምድራዊ ሕይወት ለመንሣት ወይም

[94] ከዚህ በኋላ በአጭሩ ሉተር A Sermon on Keeping Children in School (1530) (WA 30/2: 517-88; *LW* 46:207-58) የሚለውን ጽፎአል።

*ለመግደል ያላቸው ሥልጣን አጠያያቂ ስለማይሆን ነው፡፡ በወላጆች ምትክ ሆነው ክፉ አድራጊዎችን እንዲቀጡ እግዚአብሔር ለአስተዳዳሪዎች ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል፡፡ በጥንት ዘመን ለምሳሌ ከሙሴ መጻሕፍት እንደምናነበው ወላጆች ልጆቻቸውን ለሞት ፍርድ እንዲያቀርቡ ታዘዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የተከለከለው በግለ ሰቦች ላይ ተግባራዊ እንዳይሆን እንጂ ለመንግሥታዊ ባለሥልጣናት አይደለም፡፡*

182 *ክርስቶስ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5ን ባብራራበትና ባጠቃለለበት የወንጌሉ ትምህርት[95] በየዓመቱ ስለምንሰማ ይህን ትእዛዝ መረዳት ቀላል ነው፡፡ ይኸውም በእጅ፣ በልብ፣ በቃል፣ በምልክት ወይም በአመለካከት ወይም ዝቅ በማድረግ እንዳንገድል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ምትክ ከሆኑት ከወላጆችና ከመሪዎች በስተቀር ቊጣ የተከለከለ ነው፡፡ ቊጣ፣ ተግሣጽና ቅጣት የእግዚአብሔርና የተወካዮቹ የተለየ መብት ስለ ሆኑ ይህንና ሌሎችንም ትእዛዛት በሚተላለፉት ላይ ሊተገበሩ ይገባል፡፡*

183 *እግዚአብሔር በሚገባ እንደሚያውቀው ይህ ትእዛዝ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆነው ዓለም ክፉና ይህም ሕይወት በመከራ የተሞላ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንና ሌሎችንም ትእዛዛት በበጎነትና በክፉት መካከል ልዩነት አድርጎ እግዚአብሔር አቁሞአቸዋል፡፡ በሌሎች ትእዛዛት ላይ የሚደረጉ ጥቃቶች የመኖራቸውን ያህል በዚህም ትእዛዝ ላይ የሚደረጉ በደሎች አሉ፡፡ ክፉ በሚያደርጉብን ብዙ ሰዎች መካከል መኖር ይገባናል፣ እንዲሁም*
*184 ጠላቶቻቸው ልንሆን ምክንያት አለን፡፡ ለምሳሌ አንተ ከእነርሱ የተሻለ ቤት፣ ርስትና ንብረት እንዲሁም የላቀ ሀብት ከእግዚአብሔር ስለ ተቀበልህ በቅንዓት ተነሣስተው ስለ አንተ ክፋት በቊጣ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ እንዲህ በመሰለ መንገድ በሰይጣን አነሣሽነት በምታገኘው ጥቂት መንፈሳዊም ይሁን አካላዊ ጥቅም ምክንያት የሚቀናቀኑህን ጠላቶች ልታፈራ ትችላለህ፡፡ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች በምናይበት ጊዜ ልባችን በቊጣ ተሞልቶ ደማቸውን ለማፍሰስና ልንበቀላቸው ልንነሣሣ እንችላለን፡፡ ከዚያም መራገምና መሳደብ*
*185 ቀጥሎም በእነርሱ ላይ መዓትና ግድያ ማውረድ ይከተላል፡፡ እዚህ ላይ እግዚአብሔር እንደ ቸር አባት ሆኖ በመካከላቸው በመግባት የተጣሉት ሰዎች ሰላማዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በአጭሩ እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ከክፋትና ከብጥብጥ እንዲጠበቁ፣ እንዲድኑና ከለላ እንዲያገኙ እንዲሁም ባልንጀራችንን ከጉዳት ለመጠበቅ ይህንን ትእዛዝ የመከላከያ ግድግዳ፣ ምሽግና መጠጊያ አድርጎ አቁሞአል፡፡*

186 *የዚህ ትእዛዝ ትርጒም የሚያስተምረው አንድ ሰው የቱንም ያህል የሚገባው ቢሆን ስለ የትኛውም ክፉ ሥራው ሌላውን ሰው መጉዳት የሌለበት መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ግድያ ብቻ ሳይሆን ወደ ግድያ የሚያመሩ ነገሮች ሁሉ የተከለከሉ ናቸው፡፡ ብዙ ሰዎች በተግባር ሌሎችን ባይገድሉም እንኳ ምኞታቸው ቢፈጸም ጠላቶቻቸውን ፈጽመው የሚያጠ*
*187 ፉበትን እርግማኖች ያወርዱባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰው በተፈጥሮው ይህን ያደርጋል ይሁን እንጂ ማንም ሰው ሌላው ጉዳት እንዲያደርስበት ፈቃደኛ እንደማይሆን በማንም የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለባልንጀራችን በልባችን ያለንን የመራራነት ምንጭ ለማድረቅ ይፈልጋል፡፡ ለፈቃዱ እንድንገዛ፣ በልብ መታመንና ጸሎት የሚያስቸግሩንን ጉድለቶች ለእርሱ እንድናስረክብ ይህንን ትእዛዝ እንደ መስተዋት ሁልጊዜ በፊታችን በማድረግ እንድንጠብቀው ይፈልጋል፡፡ ከዚያም ጠላቶቻችን እንዲያጓሩ፣ እንዲቆጡና የከፋውን እንዲያደርጉ ልንተዋቸው እንችላለን፡፡ ለቊጣችን ምክንያት የሆኑትን ጠላቶቻችንን አስመልክቶ ቊጣችንን ለማርገብና ትዕግሥተኛና የዋህ መሆንን ልንማር እንችላለን፡፡*

188 *በአጭሩ አብዛኛው ሕዝብ በትክክል እንዲያውቀው ለማድረግ አለመግደልን አስመልክቶ የትእዛዙ አጭር ማጠቃለያ የሚከተለው ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በእጆቻችን ወይም በምግባራችን ማንንም መጉዳት የለብንም፡፡ ቀጥሎም ማንንም ለመጉዳት፣ ለመሟገት ወይም ለመምከር በምላሳችን መጠቀም የለብንም፡፡ እንደ ገና ደግሞ የባልንጀራችንን ኑሮ*

---

[95] *ማቴዎስ 5፡20-26 ከቅድስት ሥላሴ በኋላ ላሉት ስድስት ሳምንታት እና ከጴንጤቆስጤ በኋላ ላሉት ሰባት እሁዶች የተመደ ጥቅስ ነበር፡፡ ሉተር በዚህ ጥቅስ ላይ ከሰበካቸው ስብከቶች አሥራ ስድስቱ እስከ አሁን አሉ፡፡*

የሚበድል ዘዴ መፍጠር ወይም መደገፍና ልባችንን በጥላቻና በቀኄጣ የሚሞላ የጠላትነት
መንፈስ ማስተናገድ የለብንም ማለት ነው። ስለዚህ ለሰዎች ሁሉ በተለይ ክፉን ለሚመኝልህ
ወይም ለሚያደርግብህ ሰው በሥጋም ሆነ በነፍስ ነቀፋ የሌለብህ ሆነህ ቅረበው።
ምክንያቱም መልካምን ለሚመኝልህና ለሚያደርግልህ ክፉን መመለስ ሰብአዊነት ሳይሆን
ዲያብሎሳዊ ስለ ሆነ ነው።
189 በሁለተኛ ደረጃ ይህ ትእዛዝ የሚጣሰው ሰው ክፉን በሚያደርግበት ጊዜ ብቻ
ሳይሆን ለባልንጀራው መልካም ነገርን ባለማድረጉ ወይም መልካም ሊያደርግለት ዕድሉ
እያለው ባልንጀራውን ከአካላዊ ሥቃይና ጉዳት ሳይከላከልለት፣ ሳይጠብቀውና ሳያድነው
190 ሲቀር ነው። አንድን ሰው ልታለብሰው ሲገባህ ራቁቱን ብታየውና ዝም ብትለው በቅዝቃዜ
እንዲሞት ተውኸው ማለት ነው። አንድን ሰው ተርቦ ብታይና ባታበላው ለርሃብ ዳርገኸዋል
ማለት ነው። እንዲሁም አንድን ሰው እንዲሞት ብትኮንነው ወይም ከአደጋ
የሚያመልጥበትን ዘዴ እያወቅህ ዝም ብትለው ገደልኸው ማለት ነው። በተመሳሳይ አደጋ
ውስጥ ወድቆ ብታየው[96] ሕይወቱን ለማዳን መንገድ እያለ ባታድነው ገደልኸው ማለት
ነው። አንድን ሰው ፍቅርህን ብትነፍገውና ሕይወቱን ለማዳን ልትሰጠው የሚገባህን
አገልግሎት ብትነሣው ያ ሰው ቢሞት እኔ ለመሞቱ ምንም አስተዋጽኦ አላደረግሁም ብትል
አያዋጣህም።
191 ስለዚህ በሥጋና በሕይወት፣ በችግርና በአደጋ ላይ ላሉ ለሌሎች የሚገባውን ምክርና
እርዳታ የማይሰጡትን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር በግልጽ ነፍሰ ገዳዮች ብሎ ይጠራቸዋል።
ክርስቶስ ራሱ እንዳስታወቀው በፍርድ ቀን እንዲህ ብሎ ይፈርድባቸዋል። «ተርቤ ነበር፤
አላበላችሁኝም፤ ተጠምቼ ነበር፤ አላጠጣችሁኝም። እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም። ታርዤ
አላለበሳችሁኝም። ታምሜና ታስሬ ነበር፤ ነገር ግን አልጠየቃችሁኝም»።[97] ይህ ማለት
«እኔና ቤተ ሰቦቼ እንድንራብ፣ እንድንጠማ እንዲበርደን የጫካ አውሬዎች እንዲቦጫጭቁን
በወኅኒ ቤት እንድንበሰብስ ወይም በእጦት ምክንያት እንድንጠፋ ተዋችሁን ማለት ነው።»
192 እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ድርጊት አድራጊ ሰዎችን ነፍሰ ገዳዮችና ደም አፍሳሾች
ብሎ ከመጥራት ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም እነዚህን ወንጀሎች ባትፈጽም እንኳ
ባልንጀራህ በክፉ አጋጣሚዎች እንዲማቅቅ እና እንዲጠፋ አደረግህ ማለት ነው። ይህ
ድርጊት ልክ አንድን ሰው በውኃ ውስጥ ገብቶ ወይም በሚነድ እሳት ውስጥ ወድቆ
ለመውጣት ሲታገል ዐይቼ እርሱን ለማዳን እጆቼን እንደ አለመዘርጋት ነው። እንግዲህ
እንዲህ አድርጌ እያለሁ ከነፍሰ ገዳይነትና ከወንበዴነት ሌላ በምን ዐይን ልታይ እችላለሁ?
193 ስለዚህ ማንም ሰው እንዲቸገር ማድረግ የለብንም። ነገር ግን ማንኛውንም ቸርነትና
194 ፍቅር እንድናሳይ የእግዚአብሔር እውነተኛ ዓላማ ነው። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ይህ ሁሉ
ቸርነት ለጠላቶቻችን ሊደርሳቸው ይገባል። ክርስቶስ በማቴ 5፡46-47 እንዳለው
ለወዳጆቻችን ብቻ መልካም ማድረግ የአሕዛብ በጎነት ብቻ ነው።
195 እንደገና እኛ እውነተኛና የከበሩ የሆኑትን ሥራዎች ማለትም የዋሕነትን፣
ትዕግሥትን፣ በአጭሩ ፍቅርንና ርኅራኄን ለጠላቶቻችን እንድናሳይ የሚያበረታታና
የሚያነሣሣ የእግዚአብሔር ቃል አለን። እርሱ አምላካችን መሆኑን ሊያስታውሰን፣
ሊያሳስበን፣ ሊያጽናናንና ሊከላከልልን እንደሚወድ በመረዳት የብቀላን ስሜት እንድንጫነው
አንደኛውን ትእዛዝ ሁልጊዜ እንድናስታውስ ይፈልጋል።
196 ይህ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ቢጻፍ እጆቻችን በመልካም ሥራ በተሞሉ ነበር። ይህ
197 ግን ለመነኮሳት ሊሰበክ አይገባም። ምክንያቱም የካርቱሲያን ገዳም መነኮሳት «መንፈሳዊ
ይዞታ»ን ስለሚሸረሽር ነው። ይህም እነርሱ መልካም ሥራ ነው የሚሉትን እንደ ማሰናከልና
ገዳማትን ባዶ እንዲሆኑ እንደ ማድረግ ስለሚቈጠር ነው። ምክንያቱም በዚህ ዐይነት

[96] በታረመውና በ1538 በዊተንበርግ የታተመው ትልቁ የክርስትና ትምህርትና በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) መካከል የቃላት ልዩነት አለ፤ ይኸውም «ያለ ጥፋቱ የተፈረደበት» የሚለው ነው።

[97] ማቴዎስ 25፡42-43።

ትምህርት የሚነገረው የተለመደው ክርስቲያናዊ አኗኗር በቂና ከበቂም በላይ ስለ ሆነ ነው፡፡ መነኮሳቱ ግን ይህን ትእዛዝና ሌሎችንም ትእዛዛት ተራ ምክር እንጂ ትእዛዝ እንዳልሆኑ አድርገው ስለሚጥሉአቸው በሐሰተኛና ግብዝነት በተሞላው አገልግሎታቸው በዓለም በመላ እንደሚሳለቁና እንደሚያስቱ ማንም ያያል፡፡[98] በተጨማሪም ግብዝነት በተሞላበት አገልግሎታቸው «እጅግ በጣም ፍጹም የሆነ ሕይወት» በሚሉት ሥራቸው ያለ እፍረት እየኮሩ ጥሩ የሆነ ከመስቀልና ከመከራ የራቀ ሕይወት በገዳማት ውስጥ ይቀጫሉ፡፡ ወደ ገዳማትም ሮጠው የገቡት ምንም መከራ እንዳያገኛቸው ወይም ለማንም መልካም ነገርን
198 እንዳያደርጉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መልካም ሥራዎችን መሥራት እግዚአብሔርና መላእክቱ የሚደሰቱበት በእግዚአብሔር ቃል የታዘዙ እውነተኛ፣ ቅዱስና መለኮታዊ ሥራዎች መሆናቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህ ተቃራኒ የሆነ የሰው ቅድስና ሁሉ የከረፋና የቈሸሸ ከእግዚአብሔር ቍጣና ኵነኔ በስተቀር ሌላ የሚያመጣው ነገር የሌለው ነው፡፡

## ስድስተኛ ትእዛዝ

199 «አታመንዝር»

200 ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ትእዛዛት ሁሉ በማናቸውም መንገድ ባልንጀራችንን እንዳንጎዳ እንደሚያስተምሩን ቀደም ካለው ትእዛዝ ዐሳብ ልንረዳ እንችላለን፡፡ እነርሱም በሚያስደንቅ ሁኔታ የተቀመጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ትእዛዛት በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ባልንጀሮቻችን ይናገራሉ፡፡ ከዚያም ከሚቀርቡን ሰዎች ቀጥሎ ላሉ ሰዎች ደግሞ ከራሳቸው ሕይወት ቀጥሎ በጣም ውድ፣ ከሥጋቸውና ከደማቸው ጋር አንድ ስለ ሆኑት የትዳር አጋሮቻቸው ይናገራሉ፡፡[99] ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እዚህ ላይ ካለው በረከት የበለጠ በሌሎች በረከቶች ላይ ሰው ጉዳት ሊያደርስ
201 አይችልም፡፡ ስለዚህ የሌላውን የጋብቻ አጋር መድፈር በዚህ ትእዛዝ በግልጽ ተከልክሎአል፡፡ ምንዝር በተለየ መንገድ የተጠቀሰው በአይሁድ ሕዝብ መካከል አንድ ሰው እንዲያገባ ሕግ በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡ ወጣቶች በተቻለ መጠን ቀደም ብለው እንዲያገቡ የሚበረታቱ ሲሆን ሳያገቡ መኖር የማይደገፍ፣ ዘማዊነትና አሳፋሪ አኗኗር ተቀባይነት የሌለው ስለ ነበረ እንደ ዛሬው ሕዝቡ በትዕግሥት የሚያልፈው ጕዳይ አልነበረም፡፡ በዚህ መሠረት ምንዝርና በእነርሱ መካከል እጅግ የተሠራጨ ንጽሕና የጎደለው ሕይወት ነበር፡፡

202 እንደዚህ ያለ እፍረተ ቢስነት፣ ጋጠ ወጥነትና ብልግና የተሞላ ዝቅጠት በመካከላችን ካለ ምንም ብለን ብንጠራው ይህ ትእዛዝ ንጽሕና የጎደለው አኗኗርን ይቃወማል፡፡ በዚህ ትእዛዝ የተከለከለው ውጫዊ ድርጊት ብቻ ሳይሆን የብልግና ምክንያቶች ሁሉ፣ ማለትም የብልግና ተግባርን ማደፋፈር፣ ልብህ ከንፈርህና መላ ሰውነትህ ንጽሕና ለጎደለው ሁኔታ እርዳታና ድጋፍ
203 እንዳይኖራቸው ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ባልንጀሮችህ አደጋ ላይ በወደቁ ወይም እርዳታ ባስፈለጋቸው ጊዜ ልትከላከልላቸው፣ ልትጠብቃቸውና ልትታደጋቸው፣ ከዚያም በላይ
204 ክብራቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ ልትረዳቸው ይገባል፡፡ ስሕተት እንዳይፈጸም (መከላከል እየቻልክ) ባታደርገው (ነገሩ አይመለከተኝም ብለህ) ጣትህን እንኳ ባታነሣ ወንጀልን እንደ ሠራ
205 ወንጀለኛ ነህ፡፡ በአጭሩ ሰዎች በንጽሕና ሊኖሩና ባልንጀሮቻቸው በንጽሕና እንዲኖሩ ሊረዱ ይገባል፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር በዚህ ትእዛዝ ባልን ወይም ሚስትን ከእነዚህ ሕግ ተላላፊዎች ሊጠብቅ ይፈልጋል፡፡

206 ይህ ትእዛዝ በተለይ ጋብቻን እንደ ትክክለኛ የአኗኗር መንገድ አድርጎ ስለሚያቀርብልን በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ይህንን የአኗኗር መንገድ እንደሚያከብረው፣ እንደሚያወድሰውና በዚህ ትእዛዝ እንደሚጠብቀው መገንዘብ ይኖርብሃል፡፡ እላይ በአራተኛው ትእዛዝ እንዳየነው «አባትህንና እናትህን አክብር» ብሎ አዟል፡፡ እዚህ ላይ ግን እኔ እላለሁ፣

[98] በሮማ ካቶሊክ ልማድ መሠረት በሁሉም ሰው ላይ አስገዳጅነት ባላቸው መለኮታዊ «ትእዛዞችና» (Praecepta)፣ በሰው ፈቃድ በተለይም ከሁሉ የሚበልጠውን ጸጋ በሚፈልጉ እንደ መነኩሳት ባሉ ሰዎች በሚከበሩት «የወንጌል ምክሮች» (Consilia evangelical)፣ መካከል ልዩነት ይደረጋል፡፡ እነዚህን የወንጌል ምክሮች አለማክበር የተፈቀደ ነው፡፡

[99] ዘፍጥረት 2፡24፡፡

የጋብቻን አኗኗር እግዚአብሔር በአስተማማኝ መሠረት ላይ አስቀምጦአል፤ ጠብቆአልም፡፡
207 በሚከተሉትም ምክንያቶች ጋብቻን እንድናከብረው፣ እንድንጠብቀውና አምላካዊ በረከት
እንዳለበት የኑሮ መንገድ አድርገን እንድንደሰትበት ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ወንድና
ሴት አድርጎ በተለያየ ጾታ የፈጠረው ለፌዝ ሳይሆን ለእርስ በርሳቸው እውነተኞች እንዲሆኑ፣
ፍሬ እንዲኖራቸው፣ ልጆችን እንዲወልዱና ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያሳድጉ ከሌሎች
208 ድርጅታዊ ተቋማት አስቀድሞ ጋብቻን አቋቁሞአል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን አኗኗር
ከሁሉ በበለጠ የባረከ ሲሆን ይህ የኑሮ ዘይቤ የሚያስፈልገውን ነገር በሙላት ለማግኘት
እንዲችል በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር ሰጥቶታል፡፡ የጋብቻ ሕይወት የፌዝ ወይም
የስንፍና ፍላጎት ሳይሆን የተከበረ ተቋምና የእግዚአብሔር ጥብቅ ዓላማ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡
ምክንያቱም ሰዎች በዓለም ላይ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ አምላካዊ ዕውቀትን፣ ፈሪሃ
እግዚአብሔር ያለበት አኗኗርንና ክብርን ሁሉ እንዲያሳድጉና ክፋትንና ዲያብሎስን እንዲዋጉ
ለእርሱ እጅግ በጣም አስፈላጊው ስለ ሆነ ነው፡፡
209 ስለዚህ ዕውሩ ዓለምና ሐሰተኞች ካህኖቻቸው እንደሚያደርጉት ይህን የጋብቻ ሕይወት
መናቅና መተው ተገቢ እንዳልሆነ ሁልጊዜ አስተምሬአለሁ፡፡ እግዚአብሔር ጋብቻን ባከበረበትና
በቀደሰበት በቃሉ አኳያ እንድናየው ከዚህም ቃል የተነሣ ደግሞ ይህን አኗኗር፣ ከሌሎች
ሁኔታዎች በላይ ስለ ሆነ ከእነርሱ ጋር ሳናስተካክለው ከነገሥታት፣ ከልዑላን፣ ከጳጳሳትና
ከሌሎችም በላይ በማድረግ ቅድሚያ ልንሰጠው ይገባል፡፡ በመንፈሳዊና በዓለማዊ ሕይወት
አስፈላጊነት ራሳቸው ትሑታን ሊሆኑና ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጋብቻ እንዲገቡ ጋብቻን እንደ አንድ
210 የአኗኗር ዘይቤ መፍቀድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ የሚከለከል አኗኗር ሳይሆን
የከበረ፣ በሁሉም ዘንድ የሚደረግ በክርስቲያን አገሮች ሁሉና በመላው ዓለም ሊስፋፋ የሚገባው
ሥርዓት ነው፡፡
211 በሁለተኛ ደረጃ ጋብቻ ሊከበር የሚገባው የሕይወት አካሄድ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም
ነው፡፡ ይህም ማለት በአጠቃላይ ለዚህ የተፈጠሩ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ በዚህ የሕይወት አካሄድ
ውስጥ መኖር እንደሚገባቸው እግዚአብሔር በጥብቅ አዟል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከጋብቻ
ሕይወት ነጻ ያደረጋቸውና ለጋብቻ ምቹ ያልሆኑ እግዚአብሔር ከጋብቻ ውጪ ንጽሕናን
እንዲጠብቁ ከፍተኛና ከተለመደው ሕይወት ውጪ የሆነ ስጦታ የሰጣቸው ሰዎች ከጋብቻ
212 ውጪ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደ ፈቀደለት ተፈጥሮ የሚሠራ ከሆነ ከጋብቻ
ውጪ ንጹሕ ሆኖ መኖር አይቻልም፡፡ ይኸውም ሁሉም እንደሚረዳው ሥጋና ደም፣ ተፈጥሮአዊ
ዝንባሌና ወሲባዊ ፍላጎት የማይቆሙና የማይገቱ ሆነው ራሳቸውን ይገልጣሉ፡፡ ስለዚህ በተቻለ
መጠን ሰዎች ከርኩሰት እንዲጠበቁ ለማድረግ ሁሉም ለራሱ የተሰጠው ድርሻ ኖሮት በእርሱም
እንዲረካ እግዚአብሔር ጋብቻን አቋቋመ፡፡ እንዲህም ሆኖ ልብን በንጽሕና ለመጠበቅ
የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልጋል፡፡
213 የጳጳሳዊ ሠራዊት የሆኑቱ ካህናት፣ ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት ግን ጋብቻን በመናቅና
በመከልከል አብዛኛውን ሕዝብ እያታለሉ ቃል ኪዳናቸውን የሚጠብቁ በማስመሰል ሲኩራሩ
214 ታያላችሁ፡፡ በታላቅ የቅድስና ዐሳብ የሚመሩ አስመስለው ጋብቻን የሚከለክሉ ነገር ግን
በአደባባይ ያለ እፍረት ዝሙት የሚፈጽሙ ወይም ብዙ ጊዜ እንደ ታየው ለማውሣት እንኳ
የሚያሳፍሩ ድርጊቶች የሚያደርጉትን ሰዎች ያህል ለንጽሕና አነስተኛ ግምት የሚሰጥ ሰው
215 የለም፡፡ በአጭሩ ከክፉ ድርጊት ቢጠበቁም እንኳ ልባቸው ርኩሰትንና ክፉ ምኞትን የተሞላ
216 ስለ ሆነ በጋብቻ ሊወገድ በሚችል ምኞት ሲቃጠሉ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ ከጋብቻ ውጪ ያለው
የቅድስና መሐላ በዚህ ትእዛዝ የተወገዘና ዋጋ የሌለው ነው፡፡ በእርግጥ በገዳም መሐላ የተታለሉ
ምስኪኖችና የተማረኩ ሕሊናዎች ቅድስና የጎደለውን ኑሮአቸውን በመተው ወደ ጋብቻ ሕይወት
ሊገቡ ይገባቸዋል፡፡ የገዳም ኑሮ በእግዚአብሔር የተፈቀደ ቢሆን እንኳ በራሳቸው ኃይል
ንጽሕናን መጠበቅ አይችሉም፡፡ በገዳም በቆዩ ቁጥር ያለ ጥርጥር ይህን ትእዛዝ ይተላለፋሉ፡፡
217 ይህን የምለው ወጣቶቻችን ጋብቻ የተባረከና እግዚአብሔርን የሚያስደስት አኗኗር
መሆኑን ዐውቀው የጋብቻን ሕይወት እንዲፈልጉ ነው፡፡ በመሆኑም ጋብቻን በመናቅ አሁን
በስፋት በሚታየውና በየአደባባዩ በሚካሄደው ዘማዊነትና በሌሎች አስነዋሪ ድርጊቶች ያደፈውን
218 ጋጠወጥ ጠባይ በጊዜ ሂደት እንደገና ተመልሶ ተገቢ ክብሩን ያገኛል፡፡ ስለዚህ ወላጆችና

219 የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ወጣቶች በንጽሕናና በክብር እንዲያድጉ፣ ባደጉ ጊዜም በክብር በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲያገቡ የመቈጣጠር ኃላፊነት አለባቸው። ከዚያ በኋላ በጋብቻ ሕይወታቸው ሐሤትና ደስታ እንዲኖራቸው እግዚአብሔር በረከቱንና ጸጋውን ይጨምራል።

በመጨረሻ ይህ ትእዛዝ ሰዎች ሁሉ በተለየ ሁኔታቸው (ማለት በተለይ በጋብቻ የኑሮ ይዞታ) በተግባር፣ በቃል፣ እንዲሁም በዐሳብ በንጽሕና እንዲኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የትዳር ጓደኛ እንዲወዱና እንዲንከባከቡ ይፈልግባቸዋል። የጋብቻ ንጽሕና ተጠብቆ በሚኖርበት ሁሉ ባልና ሚስት በሙሉ ልባቸውና በፍጹም ታማኝነት ለእርስ በርስ እንክብካቤ በማድረግ በአንድነት፣ በፍቅርና በስምምነት መኖራቸው ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው። እንግዲህ ንጽሕናን መስህብ ያለውና ተፈላጊ እንዲሆን ከሚያደርጉት ዋና መንገዶች አንዱ ይህ ነው። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ንጽሕና ሁልጊዜ ያለ ምንም ትእዛዝ እንዲያው ይከተላል። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ የትዳር ጓደኞች እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱና
221 እንዲከባበሩ በጥብቅ የሚመክረው።[100] እዚህ ላይ እንደ ገና ያለ እግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ በተመረጡ «መንፈሳዊ የአኗኗር ዘይቤዎች» ላይ በደስታ ልትኩራራባቸው የምትችል የከበሩ መልካም ሥራዎች ይኖሩሃል፦

*ሰባተኛ ትእዛዝ*

222 «አትስረቅ»

223 ከራስህና ከትዳር ጓደኛህ ቀጥሎ እግዚአብሔር እንዲጠበቅና እንዳይሰረቅ የሚፈልገው ምድራዊ ንብረት ሲሆን እርሱም የባልንጀራችንን ንብረት እንዳንዘርፍ ወይም እንዳንወስድበት
224 አሏል። ምክንያቱም መስረቅ ማለት የሌላውን ሰው ንብረት ያለ አግባብ የራስ ለማድረግ ከመፈለግ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? እነዚህ ጥቂት ቃላት በባልንጀሮቻችን ለመጠቀም በእነርሱ ላይ ጉዳት እንዲደርስ የምናደርገውን ተግባራችንን ያጠቃልላሉ። ስርቆት ሰዎች ትኩረት ቢነፍጉትም የተስፋፋና የተለመደ ከመሆንም አልፎ ከቁጥጥር በላይ ነው። ስለዚህ ሌቦች የሆኑ ሁሉ ቢቀጡ ዓለም ሰው የሌለባት ትሆን ነበር። ሰዎችን ሁሉ በተለይ ስሕተታቸውን የማይቀበሉትን በመስቀያ ላይ ብንሰቅል የመስቀያ እንጨትና የሰቃዮች እጥረትም ይከሰት ነበር። ምክንያቱም እንዳልኩት መስረቅ ማለት በገበያ፣ በሱቅ፣ በልኳንዳ፣ በወይንና በሌሎች መጠጦች መሸጫና በሥራ መደብሮች፣ በማንኛውም የግብይትና የገንዘብ መለወጫ ስፍራ የማይገባንን መውሰድ ጭምር ነው እንጂ ከሣጥን ወይም ከኪስ ገንዘብን መውሰድ ብቻ አይደለም።

225 ይህንን ነገር በሚገባ ለመረዳት ሌብነት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ የሚገልጽ አንድ ምሳሌ እንመልከት። በቤት የሚያገለግል ሠራተኛ ጉዳቱን ማስወገድ እየቻለ አገልግሎቱን በትጋት ሳያከናውን ቢቀርና የአሠሪውን ዕቃ ቢያጠፋ ወይም ሲጠፋ ዝም ብሎ ቢመለከት ወይም በሌላ መንገድ በስንፍና፣ በግድየለሽነት ወይም ከክፋቱ የተነሣ የአሠሪውን ጥቅም ሳያስብ በሥራው ቢሰንፍና የአሠሪውን ንብረት ለጉዳት አሳልፎ ቢተው ድርጊቱ የስርቆት ያህል ይሆናል ማለት ነው። በድንገት ወይም ሳይታሰብ ስለሚደርሱ ጉዳቶች ሳልናገር ነገር ግን እንዲህ ባለ መንገድ በአንድ ዓመት ሠላሳ ወይም አርባ ገልደን (የጀርመን ገንዘብ) በሚያህል የገንዘብ መጠን ቀጣሪህን ማታለል ትችላለህ ማለት ነው። ይህን ያህል ገንዘብ ከሳጥን የሰረቀ ሰው ሌባ ተብሎ በስቅላት[101] ይቀጣል። በሥራው ላይ ሆኖ ጥፋት ያደረሰው ግን የሰረቀ መሆኑን የማያምን ከመሆኑም በላይ ማን እርሱን ሌባ ብሎ ለመጥራት ይደፍራል?

226 ባለሙያዎችና ሠራተኞች ሥራቸውን ሲሠሩ ክፉ ሥራቸውን መልካም ነው ቢሉ፣ ርካሽ ዕቃቸውን በውድ ዋጋ ቢሸጡ ባልንጀራቸውን ስለሚያታልሉ ሌቦች ናቸው እላለሁ። እንዲሁም የቀን ሠራተኞች በሥራቸው የታመኑና ተግተው ሥራቸውን የማይሠሩ ከሆነ ሌቦች ናቸው። እንደዚህ ያሉ ሌቦች እንዳይሰርቁን በቁልፍ ልንከላከላቸው ከምንችለው በግልጽ ከሚሰርቁን

---

[100] ኤፌሶን 5፡22፣25፤ ቈላስይስ 3፡18-19።
[101] ሌብነት በስቅላት የሚያስቀጣ ወንጀል ነበር።

ሌቦች የባሱ ናቸው። በግልጽ የሚሰርቁን ሌቦች ገንዘባችንን እንዳይነኩቁ ቤታችንን በቁልፍ ልንዘጋ እንችላለን። ቄፍረው ሲሰርቁ ከተገኙና ከተያዙ ደግሞ ሁለተኛ እንዳይደግሙት ማድረግ እንችላለን። ነገር ግን ከእነዚህ ሊጠበቅ የሚችል ማንም የለም። በሥራ ከሚያታልሉን ግን ማንም የማያመልጥ ስለ ሆነ በእነርሱ ድርጊት ዐሥር እጥፍ ገንዘብ ከሕዝቡ ኪስ ይጠፋል። ሌቦች ብሎ የሚሰድባቸው ወይም በክፉ ዐይን ሊመለከታቸው የሚደፍር ማንም አይገኝም። እነዚህ የምናምናቸውና ይጎዱናል ብለን የማንጠብቃቸው ባልንጀሮቻችንና የቤት ሠራተኞቻችን በትናንሽ ነገር ጭምር የሚያጭበረብሩን ናቸው።

227 ከዚህም በተጨማሪ በገበያም ሆነ በየዕለቱ በሚከናወን ሥራ ተመሳሳይ የማጭበርበር ሥራ በስፋትና በኃይል ይታያል። አንዱ ሌላውን ደረጃ ባልጠበቁ ዕቃዎች፣ በሐሰተኛ ሚዛንና መለኪያ፣ እንዲሁም በሐሰተኛ ገንዘብ በማታለል ጥቅሙን ይወስድበታል። እንደገናም አንዱ
228 ሌላውን ሆነ ብሎ በንግድ ያታልለዋል፤ ይሸልተዋል፤ ይገፍፈዋል፤ ያሰቃየዋል። ይህንን የመሰለውን ክፉ ሥራ ሁሉ ማን ሊቈጣጠር ይችላል? ባጭሩ ሌብነት በዓለም ላይ በየንግድ ዘርፉ የተለመደ ሙያና የሰፋ ሆኖአል። ስለዚህ ዓለምን በመላ ብንቃኝ ብዙ ሌቦችና አጭበርባሪዎች የሞሉባት ነች። ከገንዘብ ሌቦችና ሳጥን ሰባሪዎች የራቁ፣ መደገፊያ ባለው ወንበራቸው ላይ የተቀመጡ፣ እንደ ጨዋ ሰዎችና እንደ ተከበሩ ንጹሐን ዜጎች የሚታዩ
229 በሕጋዊነት ጥላ ሥር ሆነው ግን ሕዝብን የሚዘርፉ አሉ። እነዚህ የባለ ድጋፍ ወንበር ሽፍቶችና[102] የአውራ ጎዳና ላይ ዘራፊዎች ተብለው የሚጠሩትም በዚህ ምክንያት ነው።

230 በግልጽ ስርቆት ተይዘው ቅጣታቸውን ከሚቀበሉት ሌቦች ይልቅ ጥሩ ሰዎች የሚመስሉ አንድም ትንሽ ዕቃ በግልጽ ሳይሰርቁ ነገር ግን ከጌቶችና ከመሳፍንቱ[103] ጋር በመመሳጠር አንድ ወይም ሁለት ከተማ ብቻ ሳይሆን አገርን ባጠቃላይ ስለሚያጠቁ አውራዎቹ ሌቦች ስናስብ ሁልጊዜ የሚታሰሩና የሚገረፉ ትናንሽ ሌቦችን አስመልክተን ዝም እንል ይሆናል። የዓለምን ሁሉ ጥሪት ዘርፎ እስከ አሁን በእጁ የያዘውና የቀማኞች ሁሉ አውራ ጠባቂ የሆነው ቅዱስ የሮም መንበረ ጵጵስና ከነዘረፋውና ካግበሰበሰው ይዞታዎቹ ጋር ያለውስ እንዴት ነው?

231 ባጭሩ ዓለማችን እንዲህ ነች። እነዚህ በግልጽ ሊሰርቁና ሊዘርፉ የሚችሉ ማንም ሳይቀጣቸውና ሳይነቅፋቸው መክበርን የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህ ንጹሐንና የተከበሩ ሆነው እንዲታዩ አንድን ወንጀል የፈጸሙ ትናንሽ ሌቦች ይዋረዳሉ፤ ይቀጣሉም። በእግዚአብሔር ፊት ግን ሁለቱም አንድ ናቸው። ሁሉም ከእግዚአብሔር እጅ የሚገባቸውን ይቀበላሉ።

232 እንግዲህ አሁን እንዳልነው ይህ ትእዛዝ ሰፊ ነው። ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ቊጣ በፊታቸው እንዲሆን፣ በውስጣቸውም እንዲቀረጽና ከክፋት እንዲርቁ ይህን ትእዛዝ አጉልተን እናብራራለን። ምንም እንኳ ዳኛው፣ የእስረኛ ጠባቂው ወይም ወንጀለኛ ሰቃዩ[104] ይህንን ትእዛዝ ቢሰብኩት የተሻለ ቢሆንም ስብከቱ ከክርስቲያኖች ይልቅ ለአታላዮችና ለወንበዴዎች ያስፈልጋቸዋል።

233 ስለዚህ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቊጣ እየፈራ ለባልንጀራው የሚጠቅመውን እንዲፈልግ እንጂ ገንዘቡን ሊቀማውና በንግድም ሊያታልለው እንደማይገባው ይወቅ። በተለይም የባልንጀራችንን ንብረት ልንከባከብለት፣ ልናሳድግለትና የሚያስፈልገውን ነገር ልናሟላለት የምንችልበትን ገንዘብ፣ ደመወዝና መግቦት ስናገኝ አብዝተን ይህንን ልናደርግለት ይገባል።

234 ይህንን ሁሉ በድፍረት የሚንቁ ከእስር ቤትና ከቅጣት ሊያመልጡ ይችሉ ይሆናል
እንጂ ከእግዚአብሔር ቊጣና ቅጣት ሊያመልጡ አይችሉም። በድፍረትም እስከ መጨረሻው
235 ቢጸኑ ምስኪን መሆናቸው አይቀርምና ተጨማሪ መከራና ጭንቀት ይመጣባቸዋል። እንግዲህ
የጌታህ ወይም የእመቤትህ ንብረት ጠባቂ በመሆንህ እንደ ልብህ ሆድህን ትሞላ ይሆናል። ነገር
ግን ዋጋህን እንደ ሌባ ወስደህ እንደ ጨዋ ልትከበር ትፈልጋለህ። ብዙዎቻችሁ ለጌቶቻችሁ

---

102 በጀርመን ሽቱልሆልበር በጊዜው በነበረው አነጋገር አራጣ አበዳሪ ማለት ሲሆን ሉተር ሽቱል ወንበር እና ሬውበር ዘራፊ የሚል አገላለጽ ሲሰጠው ታችኛው ጀርመንኛ ስቶል ትርጒሙም በወለድ የሚሰጥ ብድር እንደሆነ ያሳያል።

103 ጎላ ባሉት ፊደላት የተጻፉ ቃላት በ1529 በዊተንበርገና በኤርፉርት በታታሙት ሁለቱ የትልቁ የክርስትና ትምህርት እተሞች የተካተቱ ነበሩ። ነገር ግን የመጀመሪያው የዊተንበርግ እትም በሂደት ላይ እያለ ምናልባት በአታሚው አማካይነት አስቀድሞ ተወግደዋል ንባቡ ግን በ1580 በጀርመንኛ በታተመው መጽሐፈ ስምምነት ውስጥ እንዲመለስ ተደርጎአል።

104 በጀርመንኛ ሚስተር ሀንስ በቀጥተኛ ትርጉሙ ጌታ ጃክ ማለት ሲሆን ሉተር ይህንን አገላለጽ በተደጋጋሚ ለዳኞች ይጠቀም ነበር።

ወይም ለእመቤቶቻችሁ ንቀት ያላችሁ ከመሆናችሁ የተነሣ ንብረታቸው ከጥፋት እንዲድን
236 ለማድረግ ፈቃደኞነት የሌላችሁ ናችሁ፡፡ የምታተርፉትን ተመልከቱ፡፡ እግዚአብሔር
ለጥፋታችሁ እንድታገኙ የረዳችሁ የራሳችሁ ንብረት ባለቤት ሆናችሁ በምትኖሩበት ጊዜ ክፉ
ብድራትን የምትቀበሉበትና ያደረሳችሁትን ጥፋት የእያንዳንዷን ሳንቲም ሠላሳ እጥፍ
የምትመልሱበት ጊዜ ይመጣባችኋል፡፡
237 እንዲሁም በሙያተኞችና በቀን ሠራተኞች ተመሳሳይ ቅጣት ይደርስባቸዋል፡፡ እነርሱም
በሌሎች ሰዎች ንብረት ላይ ጌታ የሆኑና የጠየቁትን ሁሉ ሊወስዱ መብቱ የተሰጣቸው
238 ይመስላቸዋል፡፡ ሌሎችን ማታለሉን እስከ ቻሉ ድረስ ይቀጥሉበት፡፡ እግዚአብሔር ግን ትእዛዙን
አይረሳምና የሚገባቸውን ቅጣት ይሰጣቸዋል፡፡ እርሱም በለመለመ ዛፍ ላይ ሳይሆን በደረቀ
239 እንጨት ላይ ይሰቅላቸዋል፡፡[105] በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ አይበለጽጉም፡፡ የጥንት ሮማውያን
እንዲህ ያሉ ሌቦችን በአንገት ልብሳቸው አንቀው እንደሚገድሉ ሁሉ ዛሬም ትክክለኛ
መንግሥት ቢኖር እንደዚህ ያለውን አስጸያፊ ተግባር ያስቆም ነበር፡፡
240 የገበያን ዋጋ በመለዋወጥ ያለ አግባብ ለመበልጸግ ነጻ ገበያን ወደ ወንበዴዎች ዋሻ
በሚለውጡትም ላይ ተመሳሳይ ዕጣ ይወድቅባቸዋል፡፡ ድሆች ዛሬም የሚጭበረበሩ
ከመሆናቸውም በላይ ከባድ ሸክምና ከፍተኛ የዋጋ መናር ወድቆባቸዋል፡፡ ዋጋ የሚያንሩቱ ዋጋ
ለመጨመር ያለ ገደብ መብት የተሰጣቸው ይመስል በቂ ምክንያት ሳይኖራቸው
241 በእምቢተኝነትና በጭካኔ ዋጋ በማናር የገበያን መርህ ያለ አግባብ ይጠቀሙበታል፡፡ እንደነዚህ
ያሉቱ በስግብግብነታቸው ከዋጋ በላይ ያስከፍሉ፤ የሰውን ገንዘብ ይቀሙና ለራሳቸው ያከማቹ፤
242 ነገር ግን እኛ ሁሉን በእጁ የያዘውን እግዚአብሔርን ታምነን እንኖራለን፡፡ ብዙ ጊዜ ከሰረቁ
በኋላ እግዚአብሔር በዐይኑ ይመለከታቸዋልና የጐተራው እህላቸው፣ በመጥመቂያ ያለው
መጠጣቸው እና የበረታቸው እንስሳት ያልቁባቸዋል፡፡ አዎን፣ ማንንም በአንድ ብር ያህል
ባታለላችሁትና ባጭበረበራችሁት ገንዘብ እንዳትጠቀሙ ያከማቻችሁት ንብረት ይዝጋል፡፡[106]
243 በእርግጥ ሁልጊዜ እንደምናየው የተሰረቀ ገንዘብ ብዙ ጊዜ አይቆይም፡፡ ገንዘብ ለማግኘት
ሌት ተቀን ለፍተውና ደክመው ምንም የማይበለጽጉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ብዙ ቢሰበስቡም
በሰበሰቡት እንዳይጠቀሙ ወይም ለልጆቻቸው እንዳያወርሱት ብዙ መከራና ጭንቅ
ይመጣባቸዋል፡፡
244 ነገር ግን ሁሉም ይህንን ዐይቶ ይመለከተኛል ባይልም እንድናስተውል እግዚአብሔር
ሊያስተምረን ተከታታይ ቅጣቶችን በአንዲት ሰዓት የገንዘብ ንብረቶቻችንን ጠራርገው
የሚወስዱ፣ ቤቶቻችንን የሚያቃጥሉ፣ ልጆቻችንንና ሚስቶቻችንን የሚገድሉ ጦረኞችንና
ዘራፊዎችን ይልክብናል፡፡
245 በአጭሩ የቱንም ያህል ይሁን ብትሰርቅ የሰረቅኸውን ያህል እጥፍ እንዲሰረቅብህ ዕወቅ፡፡
ነገሮችን በኃይል የሚወስድና ታማኝ ያልሆነ ሰው ተመሳሳይ ዕድል የሚደርስበት መሆኑን
ማወቅ ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ከሌላ የሚሰርቅ በመሆኑ እግዚአብሔር አንዱን ሌባ
በሌላው ይቀጣል፡፡ አለበለዚያ በቂ ገመድና መሰቀያ እንጨት ከወዴት እናገኝ ነበር፡፡
246 ስለዚህ ለመማር የሚፈቅድ ሁሉ ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንጂ ቀልድ እንዳልሆነ
ይወቅ፡፡ እናንተን የምትንቁንን፣ የምታጭበረብሩንን፣ የምትሰርቁንና የምትዘርፉንን በትዕግሥት
እንቀበላችኋለን፡፡ የጌታ ጸሎት እንደሚያስተምረን ጭካኔአችሁን ታግሠን ምሕረትንና ይቅርታን
እንድታገኙ እንጸልይላችኋለን፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ጻድቅ ሰው የሚበቃውን የሚኖረው ሲሆን
እናንተ ከሌሎች ይልቅ ራሳችሁን ትጎዳላችሁ፡፡ ነገር ግን በድኾች ላይ እንዴት እንደምታደርጉ
247 ተጠንቀቁ፡- ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ሰዎች ሁሉ በቸርነታችሁ ብቻ
የሚኖሩ ቢመስላችሁ፣ እስከ ዐጥንታቸው ድረስ ብትገፍፉአቸውና ብትግጡአቸው፣ ፊታችሁን
ከእነርሱ ብትመልሱና ልትረዱአቸው ሲገባችሁ በጭካኔ ብታባርሩአቸው፣ ተጐሳቁለው
ችግራቸውን ሊሰማቸው የሚችል ሰው ስለሌለም ወደ ሰማይ ይጮኻሉ፡፡ ደግሜ እላለሁ
ከዲያብሎስ እንደ ሆነ ሁሉ ከዚህ ተጠንቀቁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማቃሰትና ጩኸት የሚያስቅ
ጉዳይ አይደለም፤ ነገር ግን እናንተና መላው ዓለም ልትሸከሙት የማትችሉት እጅግ ከፍ ያለ

[105] በደረቅ እንጨት ላይ መሰቀል በእርጥብ እንጨት ላይ ከመሰቀል ይልቅ የውርደት ቅጣት ተደርጎ ይታሰብ ነበር፡፡
[106] ማቴዎስ 6፡19-20፤ ሉቃስ 12፡33 ተመልከት፡፡

ውጤት ያስከትላል። ምክንያቱም ጩኸታቸው ድኾችንና የተጨነቀ ልብን ወደሚጠብቅ ወደ
እግዚአብሔር ይደርሳል፤ እርሱም ሳይቀጣ አይተወውም። ነገር ግን ይህንን ብትንቁ በራሳችሁ
ላይ ምን እንደምታመጡ ዕዩ። ይሁን እንጂ ቢሳካላችሁና ቢከናወንላችሁ በመላው ዓለም ፊት
እኔንና እግዚአብሔርን ውሸታሞች ልትሉን ትችላላችሁ።
248 እንግዲህ በቂ ማስጠንቀቂያና ምክር ሰጥተናል። ይህንን ልብ የማይሉ ወይም የማይሰሙ
ከልምዳቸው እስኪማሩ ድረስ በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ እንተዋቸዋለን። ነገር ግን ወጣቶች
እንዲጠነቀቁ፣ ባለፈው ክፉ መንገድ እንዳይሄዱና የእግዚአብሔር ቍጣና ቅጣት
እንዳይደርስባቸው፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ዓይኖቻቸውን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ
249 እንዲያደርጉ ይህ ትምህርት ሊቀረጽባቸው ይገባል። የእኛ ኃላፊነት በእግዚአብሔር ቃል
ማስተማርና መገሠጽ ብቻ ነው። ግልጽ ወንጀልን መቅጣት የሚገባቸው ግን መሳፍንትና
የመንግሥት ሹማምንት ናቸው። ድኾች እንዳይበደሉና እንዳይጨቈኑ ራሳቸው በሌሎች ሰዎች
ኃጢአት ተጠያቂዎች እንዳይሆኑ ሹማምንት የሆኑቱ በሁሉም የንግድና የሥራ አቅጣጫ
ሥርዓትን ለማስፈንና ለማጽናት የነቁና የበረቱ መሆን ይኖርባቸዋል።
250 ስርቆት ምን እንደ ሆነ በበቂ ሁኔታ ተብሎአል። ይህ በጠባቡ መገደብ የለበትም፤ ነገር
ግን ከባልንጀራችን ጋር የሚኖረንን ማንኛውንም ግንኙነት የሚመለከት መሆን አለበት። ቀደም
ባሉት ትእዛዛት እንዳደረግነው እናጠቃልለዋለን፦ በመጀመሪያ፣ በማንኛውም መንገድ
የባልንጀራችንን ንብረት እንዳንጎዳ፣ እንዳንይዝበትና ጣልቃም እንዳንገባበት፣ ለባልንጀራችን
ንብረት ጉዳት የሚሆን ሥራ ሲሠራ ብናይ በዚያ ሥራ በምክር ወይም በድርጊት ተባባሪ
እንዳንሆን ተከልክለናል። እንዲህ ባለው ነገር መስማማት ወይም መፍቀድ የለብንም፤ ይልቁን
251 ልናስቀረውና ልንከለክለው ይገባናል። በተጨማሪም፣ የባልንጀሮቻችን ጥቅም እንዲጠበቅላቸውና
እንዲያድግላቸው እንዲሁም ለወዳጆቻችንና ለጠላቶቻችን ለሁለቱም በሚያስፈልጋቸው
በማንኛውም ነገር የእርዳታ እጃችንን እንድንዘረጋላቸው ታዝናል።
252 መልካም ሥራዎችን የሚፈልግና የሚመኝ ማንኛውም ሰው እዚህ ላይ ከልብ ተቀባይነት
ያላቸውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ከበቂ በላይ ነገሮችን ያገኛል። ንጉሡ ሰሎሞን ደግሞ
በምሳሌ 19[:17] «ለድሃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ እግዚአብሔርም በሙላት
ይመልስለታል» ብሎ እንደሚያስተምረው ለባልንጀራችን ስለምናደርገው መልካም ሥራ ሁሉ
253 እግዚአብሔር አምላካችን በቸርነቱ ብድራቱን ይመልስልናል። በእርግጥ እዚህ ላይ
በሚያስፈልግህ ነገር በቂ የሆነና ምንም ነገር እንዳታጣ ወይም እንዳይጐድልብህ የሚያደርግ
ባለጠጋ ጌታ አለ። ስለ ሆነም ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድና በሸፍጥ ከምታገኘው ጥቅም ይልቅ
ደስተኛ በሆነ ሕሊና መቶ እጥፍ ደስታ ሊኖርህ ይችላል። ይህንን በረከት ማግኘት የማይፈልግ
ማንኛውም ሰው ለእርሱ የሚበቃው ቍጣና መከራ ያገኘዋል።

*ስምንተኛ ትእዛዝ*

254 «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።»
255 ከሰውነታችን፣ ከሚስታችንና ከንብረታችን ሌላ አንድ ዋና ነገር አለን። እርሱም
ክብራችንና መልካሙ ዝናችን ነው። ምክንያቱም ይህ የሆነው በሰው መካከል ተንቆና ተዋርዶ
256 መኖር ስለማይቻል ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የባልንጀራችን ማንኛውም ገንዘብና ሀብት
እንዲጎድልበት እንደማይፈልግ ሁሉ የባልንጀራችን ስምና ክብር እንዲሁም ጠባይ እንዲጐድል
አይፈልግም፤ እያንዳንዱ ሰው በትዳር ጓደኛው፣ በልጁ፣ በአገልጋዩ፣ እንዲሁም በጎረቤቱ ፊት
257 የራሱ ክብር እንዲጠበቅለት ይፈልጋል። በመጀመሪያውና እጅግ በጣም ቀላል በሆነው ትርጒሙ
(«በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር») የሚሉት ቃላት እንደሚያጸኑት አንድን ምስኪንና
ንጹሕ ሰው በመወንጀልና በሐሰት ምስክርነት በአካሉ፣ በንብረቱ ወይም በክብሩ ላይ ድቀትን
ለማምጣት በባልንጀራችን ላይ በዳኛ ፊት የሐሰት ምስክር እንዳንመሰክርበት ነው።
258 እንግዲህ ይህ እኛን በጥቂቱ የሚመለከተን ይመስላል፤ በአይሁዶች መካከል ግን ልዩ
በሆነ መንገድ የተለመደ ጉዳይ ነበር። ያቺ አገር የላቀ፣ ሥርዓት ያለው መንግሥት ነበራት፤
አሁንም እንኳ እንዲህ ዓይነት መንግሥት ባለበት ይህ ኃጢአት ገና አልተቀነሰም። ምክንያቱ

*ይህ ነው፡- ዳኞች፣ ከንቲባዎች፣ መሳፍንት፣ ወይም ሥልጣን ያላቸው ሌሎች በፍርድ
በሚቀመጡበት ጊዜ በዓለም እንደ ተለመደው ሰዎች ማንኛውንም ሰው ማስቀየምን መጸየፋቸው
ከቶ የማይቀር ተገቢ ነገር ነበር፡፡ በዚህ ፈንታ፣ መወደድን፣ ገንዘብን፣ ስኬትን፣ ወይም
ወዳጅነትን ለማትረፍ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ድኻው ይጨቈናል፤ ፍርዱ ይጣመምበታል፤
ቅጣትንም ይቀበላል፡፡*

*እንዲሁም በዓለም ከሚዳኙቱ ዳኞች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ እግዚአብሔርን የሚፈሩ
259 መሆናቸው የተለመደ አለመታደል ነው፡፡*[107] *አንድ ዳኛ ከሁሉ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣
ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ጥበብና መልካም አእምሮ ያለው፣ ደፋርና ማመንታት
የሌለበት ሰው መሆን አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ምስክር የማይፈራ፣ ከዚያም በላይ ልበ
ቅን መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ያለ አድልዎ የሚዳኙ ዳኞች አብዛኛውን ጊዜ ወዳጆቻቸውንና
ዘመዶቻቸውን እንዲሁም ሊጠቅሙአቸውና ሊጎዱአቸው የሚችሉ ትላልቅ ሰዎችን ሊያሳዝኑ
ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ፍጹም ዐይኑን የታወረ ሰው ያህል ዐይኖቻቸውን ጨፍነው እና ጆሮዎቻቸውን
ደፍነው በእጃቸው በቀረበው መረጃ መሠረት መዳኘት ይኖርባቸዋል፡፡*

260 *እንግዲያው የዚህ ትእዛዝ የመጀመሪያው አጠቃቀም ሰዎች ሁሉ ባልንጀሮቻቸው ቅን
ፍርድ እንዲያገኙ መርዳት ነው፡፡ ዳኞችም ሆኑ ምስክሮች በማንኛውም ነገር ቅን የሆነው ነገር
እንዲፈጸምና እንዲያሸንፍ እገዛ ማድረግ እንጂ እውነቱ እንዲጣመም መፍቀድ የለባቸውም፡፡
261 ምክንያቱም እዚህ ላይ ሕግ ዐዋቂዎቻችን በተለይ ነገርን ሁሉ በቅን ልቦና ያለ አድልዎ
እንዲመለከቱ፣ እውነት የሆነው ሁሉ እውነት እንዲባል እንጂ ከሐሰት ጋር እንዳይደባለቅ
እንዲሁም ከአንድ ሰው ገንዘብ፣ ንብረት፣ ክብር ወይም ሥልጣን የተነሣ ማንኛውንም ነገር
ማጣመም ወይም ማሳሳት ወይም መጫን የማይገባ ነው፡፡ ይህ የዚህ ትእዛዝ አንዱ ገጽታ ሲሆን
ግልጽ ትርጒሙም በፍርድ ቤት በሚካሄዱ ሥራዎች ሁሉ የሚተገበር ነው፡፡*

262 *ቀጥሎ ትእዛዙ በመንፈሳዊ ሥልጣን ወይም አስተዳደር ክልል ተግባራዊ በሚደረግበት
ጊዜ እላይ ከተነገረውም ሰፋ ያለ ነው፡፡ እዚህም ላይ ሰዎች ሁሉ በባልንጀሮቻቸው ላይ በሐሰት
ይመሰክራሉ፡፡ ትክክለኞች ሰባኪያንና ክርስቲያኖች ቢኖሩ ዓለም እነርሱን መናፍቃን፣
ከሐዲዎች፣ እንዲያውም አድመኞችና ተስፋ የቈረጡ ወሮበሎች አድርጎ ስለሚቈጥራቸው
ይህንን የሚደርስባቸውን ውግዘት መታገሥ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል
እጅግ በጣም አሳፋሪ በሆነ መንገድና በስደት፣ በስድብ፣ በተቃርኖ፣ በጥመት፣ አግባብ ባልሆነ
አጠቃቀምና በስሕተት ትርጒም ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ ነገር ግን ይህ ድርጊት እውነትንና
የእግዚአብሔርን ልጆች መቃወምና ማሳደድ እንደ ኃጢአት የማይቈጠርበት የዚህ ጨለማ
ዓለም ባሕርይ እንደ ሆነ ይታወቅ፡፡*

263 *የዚህ ትእዛዝ ሦስተኛው ገጽታ ሁላችንን የሚመለከት ሲሆን እርሱም ባልንጀራችንን
የምናቈስልበትን ወይም የምናስቀይምበትን የአንደበት ኃጢአት ሁሉ ይከለክላል፡፡ «በሐሰት
መመስከር» የሌላ ሳይሆን የአንደበት ሥራ ነው፡፡ ስለዚህ በባልንጀራችን ላይ በአንደበታችን
የሚሠራውን ሁሉ በመቈጣጠር እንድናቆመው እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ይህም ሐሰተኛ
ሰባኪዎች የሚያስተምሩትን የሐሰት ትምህርት፣ ዳኞችና ምስክሮች የሚሰጡትን የሐሰት
264 ፍርድና ከፍርድ ቤቶች ውጪ የሚነገሩትን የሐሰት ንግግሮች ሁሉ ይመለከታል፡፡ በተለይም
ምንም እፍረት የማይታይበትን ዲያብሎስ እኛን የሚጋልብበትን ሐሜትን ወይም ስም
ማጥፋትን ይመለከታል፡፡*[108] *ስለዚህ ብዙ ሊባል ይችላል፡፡ እንደሚታወቀው ሐሜት በሁላችንም
መካከል የተለመደና እያንዳንዱ ሰው ስለ ባልንጀራው ከመልካም ነገር ይልቅ ክፉ ለመስማት
የሚፈልግበት ጠንቀኛ ወረርሽኝ ነው፡፡ እኛ ራሳችን ክፉዎች ብንሆንም ማንም ስለ እኛ ክፉ
ቢናገር ልንቀበለው አንችልም፤ በዚህ ፈንታ ዓለም ሁሉ ስለ እኛ ወርቃማ ነገሮችን ሲናገር
ልንሰማ እንፈልጋለን፡፡ ማንም ስለ እኛ መልካምን እንዲያወራ ስለምንፈልግ ክፉ በተወራብን
ጊዜ መታገስ ያቅተናል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ስለ ሌሎች መልካም ነገር ሲናገር ልንታገስ
አንችልም፡፡*

---

[107] የቅን፣ ጠንቃቃና ጥበበኛ ዳኛ ምሳሌ አድርጎ የኤሌክቶራል ሳክሶኒውን ቻንስለር ግሬጎሪ ብሩከን ሉተር አንድ ጊዜ ጠቅሶአል (WATER 2, no.1421:LW 54:150)

[108] ምሳሌአዊ አባባል ነው፡፡

265 ስለዚህ ይህንን ክፉ ነገር እንድናስወግድ፣ ይኸውም በጻኝነት ካልተሾምን በስተቀር
ባልንጀራችን ኃጢአት ሲሠራ ብናይ እንኳ በአደባባይ ልንፈርድበትና ልናወግዘው
266 ያልተፈቀደልን መሆኑን ልብ ልንል ይገባናል። በኃጢአት ላይ መፍረድና ስለ ኃጢአት ማወቅ
በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ስለ ኃጢአት በእርግጥ ታውቁ ይሆናል፤ ነገር ግን በኃጢአት
ላይ መፍረድ የለባችሁም። በእርግጥ ባልንጀራዬ ኃጢአት ሲሠራ ዐይቼ ወይም ሰምቼ ይሆናል፤
ነገር ግን ኃጢአቱን ለሌሎች እንድናገር አልታዘዝኩም። ጣልቃ ገብቼ በባልንጀራዬ ላይ
ብፈርድ ከእርሱ በሚብስ ኃጢአት እወድቃለሁ። ስለ አንድ ኃጢአት ባወቃችሁ ጊዜ ግን
ምንም አታድርጉ፤ ነገር ግን ጆሮአችሁን ወደ መቃብር አዙራችሁ ዳኛ ሆናችሁ እስከምትሾሙና
በዚህ ጉዳይ ላይ ለመፍረድ ሥልጣን እስክታገኙ ድረስ ቅበሩት።
267 ለዚህ የሚያበቃቸው ነገር ሳይኖራቸው በሌላው ለመፍረድ ቀድመው የሚጣደፉ
ሐሜተኞች ተብለው ይጠራሉ። አሳሞች በፍግ ላይ እንደሚንከባለሉና በአፍንጫቸው
እንደሚያሸቱ፣ ሐሜተኞችም የአንድን ሰው ጉድለት በየጥጋ ጥጉ በማሥራጨት የማባባስ ዕድል
268 በማግኘታቸው ይደሰታሉ። እንዲህ ማድረግ ግን ራስን በእግዚአብሔር ምትክ ፈራጅ ከማድረግ
ሌላ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም አንድ ዳኛ ሌባን ሌባ፣ ነፍሰ ገዳይን ነፍሰ ገዳይ፣ ከሐዲን
ከሐዲ ነህ፣ ወዘተ ብሎ ከባድ ፍርድ ሊያስተላልፍ ይችላል። ስለዚህ በዚህ ዓይነት ጥፋት
ባልንጀራቸውን የሚከስሱ የንጉሥ ነገሥትንና የገዥዎችን ሥልጣን እንደ ራሳቸው አድርገው
ይቈጥራሉ። ምንም እንኳ ሰይፍ በእጃቸው ባይዙም መርዘኛ ምላሳቸውን በመጠቀም
ባልንጀራቸውን ያዋርዳሉ፤ ይጎዳሉም።
269 ስለዚህ አንድ ሰው ጥፋተኛ ለመሆኑ የተወሰነ ዕውቀት ቢኖራችሁ እንኳ ስለ ሌላ ሰው
ክፉ እንዳትናገሩ እግዚአብሔር ይከለክላል። ያወራኸው ጥቂት ቢሆን እንኳ እርግጠኛ ሳትሆን
270 ብትቀር አሉባልታ ብቻ ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ትላለህ፡- «እውነት ከሆነ ለምን
አልናገረውም?» መልስ፡- «ለምን ወደ ትክክለኛው ዳኛ ፊት አታቀርበውም?» ነገር ግን
«እውነቱን ማረጋገጥ አልችልም ወይም ሐሰተኛ ተብዬ እጠራ፣ እንዲሁም ወደ ውርደት እጣል
ይሆናል።» ትላለህ ኧኸ! ወዳጄ ሆይ፣ ጥብስ ሸተተህ?[109] እንግዲያውስ እውነቱን በሚመለከተው
ባለሥልጣን ፊት ለማሳወቅ በራስህ የማትተማመንና ክስ ለማቅረብ የማትደፍር ከሆነ
አንደበትህን ያዝ። አንድ ነገር የምታውቅ ከሆነ ለራስህ ያዝ እንጂ ለሌሎች አትንገር።
ምክንያቱም አንድን ማረጋገጥ የማትችለውን ነገር ደጋግመህ ብታወራው ነገሩ እውነት ቢሆንም
ውሸታም ሆነህ ትገኛለህ። በተጨማሪ ማንም ሰው በሕግ ካልሆነ ክብሩና መልካም ስሙ
ሊወሰዱበት ስለማይገባ ታማኝ ያልሆነ ሰው ሥራ ትሠራለህ።
271 በበቂ ማስረጃ ማረጋገጥ የማይቻል ማንኛውም የሚዘገብ ነገር ሁሉ የሐሰት ምስክር
272 ነው። ስለዚህ ማንኛውም በግልጽ ያልተረጋገጠ ነገር እንደ እውነት ተደርጎ መነገር የለበትም።
በአጭሩ ምሥጢር የሆነ ነገር ሁሉ ምሥጢር ሆኖ መቅረት አለበት ወይም እንደ ሰማነው
273 በማናቸውም ሁኔታ በምሥጢር ሊገለጽ ይገባል። ስለዚህ አንድ ሰው የማይገባውን እየተናገረ
ሌላውን ሰው ሲያማ ወይም ስም ሲያጠፋ ብታገኙት እንደዚህ ያሉትን ሰዎች በግልጽ ገስጹና
አሳፍሩአቸው። አለበለዚያ እነዚህ ሰዎች አንድን ምስኪን ሰው በውርደት ከሚጥሉበት ተግባር
ራሳቸውን ነጻ ማድረግ ሲችሉ አንደበታቸውን ይይዛሉ። የሰው ክብርና መልካም ስም በቀላሉ
ሊጉድፍ ይችላል፤ ነገር ግን በቀላሉ ሊታደስ አይችልም።
274 እንግዲህ በዚህ ዓይነት መንገድ በባልንጀራችን ላይ ክፉ እንዳንናገር በፍጹም
የተከለከልን መሆናችንን ታያለህ። ይሁን እንጂ ገዢዎችን፣ ሰባኪዎችን፣ አባቶችንና እናቶችን
በተመለከተ ክፉ ሥራ ያለ ቅጣት እንዳይታለፍ በዚህ ዓይነት መንገድ ይህንን ትእዛዝ
እንድንተረጉም በተለየ ሁኔታ ተገልጾአል። አምስተኛው ትእዛዝ የሰውን አካል እንዳንጎዳ
እንደሚከለክለን ዐይተናል፤ ሆኖም ግን ፍርድን የሚያስፈጽመውን ሥቃዩን በሚመለከት ለየት
ይላል።[110] ከመንግሥት በተሰጠው ኃላፊነት ለባልንጀራው በጎ ማድረግ ሳይሆን ጉዳትና ክፋት
ብቻ ይፈጽማል፤ እግዚአብሔር በደለኞችን የሚቀጣበት ሥልጣን ለመንግሥት ስለ ሰጠ ክፉ

[109] ምሳሌአዊ አባባል ነው።
[110] በጀርመንኛ፡- Meister Hans.

ሥራ የሠሩት ቢቀጡ ትእዛዙ አይፈርስም። በተመሳሳይ ሁኔታ ማንም ሰው በግል በማንም ላይ
ሊፈርድና ማንንም ሊኰንን ሥልጣን ባይኖረውም እንኳ ይህንን እንዲያደርጉ ትእዛዝ
ከተሰጣቸውና ማድረግ ካልቻሉ ከማንኛውም የኃላፊነት ቦታ ሕግን ለይተው በእጃቸው እንደ
ወሰዱት ያህል ኃጢአት እያደረጉ ነው። በዚህ ዓይነት አንድ ሰው ክፉውን እንዲገልጥ፣ ክስ
እንዲያቀርብ፣ ማስረጃ እንዲሰጥ፣ ምስክሮችን እንዲመረምርና እንዲመሰክር አስፈላጊነቱ ይጠ
275 ይቃል። አንድ ሐኪም አንድን በሽተኛ ለማከም አንዳንድ ጊዜ የተጐዳውን እና በባለቤቱ ብቻ
የሚነካውን የሰውነት ክፍል ለመመርመርና ለመንካት ከሚገደድበት ድርጊት የተለየ አይደለም።
ልክ እንደዚሁ ባለ ሥልጣናት፣ አባቶችና እናቶች፣ ወንድሞችና እኅቶች፣ እንዲሁም ጥሩ
ጓደኞች በሚያስፈልግበትና በሚጠቀምበት ጊዜ ሁሉ ክፉውን ለመገሠጽ የጋራ ግዴታ
አለባቸው።

276 ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ለማከናወን ትክክለኛው መንገድ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል
18[111] «ወንድምህ ቢበድልህ ሂድ አንተም ከእርሱ ጋራ ሆነህ ብቻውን ምክረው» የሚለውን
መመሪያ መከተል ነው።[112] እዚህ ላይ ይህንን አስጸያፊና ያልተገባ ተግባር ለማስወገድ በጥንቃቄ
ለመመልከት የሚያስችለውን አንደበትህን ለመቈጣጠር ግሩምና የከበረ ምክር ታገኛለህ። ይህም
መመሪያ ይሁንህ። ከዚያም ስለ ባልንጀራህ አንዳችን ነገር ብትሰማ ባልንጀራህን እንዲሻሻል
ምከረው እንጂ እርሱን ለማማት አትጣደፍ። በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው ይህንን ወይም
ያንን አደረገ ተብሎ ከሌሎች በሚነገርህ ጊዜ ይህንኑ አድርግ። ሌሎች ክፉ የሚሠራውን ቢያዩ
ሄደው ያንን ሰው በግል እንዲወቅሱት አለበለዚያ አንደበታቸውን እንዲቈጥቡ አስተምራቸው።

277 ይህንን ትምህርት በየዕለቱ በቤተ ሰብ ከሚካሄዱት ሥራዎች ልትገነዘብ ትችላለህ። ይህ
የአንድ ቤተ ሰብ ኃላፊ የሚያደርገው ነው፦ የቤቱ ባለቤት አንድ ሠራተኛ የሚጠበቅበትን
አለመሥራቱን በሚያይበት ጊዜ በግሉ ይነግረዋል። የሥራው ባለቤት ሞኝ ቢሆን ኖሮ
ሠራተኛውን ቤቱ ያስቀምጥና ወደ ውጪ ወጥቶ ክፋቱን ለጓደኞቹ ቢያወራ ያለ ጥርጥር «አንተ
ሞኝ ይህ የእኛ ጉዳይ አይደለም። አንተው ራስህ ለምን አትነግረውም?» ተብሎ በተነገረው
278 ነበር። ይህ አሠራር ተገቢ፣ ስሕተቱ እንዲታረም የሚያደርግና የባልንጀራህን ክብር የሚጠ
ብቅለት አሠራር መሆኑን ተመልከት። በተመሳሳይ ክፍል ክርስቶስ ደግሞ እንደሚለው «ቢሰማህ
ወንድምህን አዳንኸው።»[113] ይህንን አደረግህ ማለት ትልቅ ሥራ ሠራህ ማለት ነው። ወይም
ገንዘብህ ማድረግ ቀላል ነገር እንደ ሆነ ታስባለህ? መነኮሳትና ቅዱሳት ትእዛዛት ሁሉ በአንድ
ላይ ከሥራዎቻቸው ጋር ቢከማቹ፣ አንድን ወንድም ገንዘባችን አድርገናል ብለው ሊናገሩ ይችሉ
እንደ ሆነ ይመልከቱ!

279 ክርስቶስ በተጨማሪ፦ «ባይሰማህም ደግመህ ከአንተ ጋር አንድ ወይም ሁለት ሰዎችን
ውሰድ በሁለትና በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ ይጸናልና» ሲል ያስተምራል።[114] ስለሆነም
ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች በቀጥታ ማነጋገር ያስፈልጋል እንጂ በሌሉበት እነርሱን ማማት
280 ትክክል አይደለም። ይህ ባይሰምርልህ ግን ጉዳዩን ወደ ማኅበረሰቡ በማምጣት በዳኛ ወይም
በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፊት አቅርበው። እዚህ ላይ ይህንን ስታደርግ ከአንተ ጋር የወሰድካቸው
ምስክሮች አብረውህ ስለሚሆኑ የአጥፊውን ጥፋት ስለሚያረጋግጡና በእነዚያ ምስክሮች
መሠረት ላይ ዳኛው ቆሞ ውሳኔና ፍርድ ስለሚሰጥ ብቻህን አይደለህም። አጥፊውን ከበደሉ
281 ለመመለስና ለማሻሻል ትክክለኛና ተገቢው መንገድ ይህ ነው። ነገር ግን ስለ አንድ ሰው በየጥጋ
ጥጉ እየሄድህ ሐሜት ብትነዛና ቈሻሻ ብትበትንበት ማንም አይሻሻልም። በተጨማሪ፣ ሰዎች
282 በተደጋጋሚ ለምስክርነት ሲጠሩ አንዳች ነገር እንደ ተናገሩ ይክዳሉ። የእንደዚህ ዓይነት
283 ለፍላፊዎች ቀልድ መበላሸቱ ለሌሎች ማስጠንቀቂያ እንዲሆን በትክክል ያገለግላል። ባልንጀራህ
እንዲሻሻል ወይም ለእውነት ፍቅር ኖሮህ ብታደርገው ኖሮ የቀን ብርሃንን በመሸሽ በስውር
ባላደባህም ነበር።

---

[111] በስሕተት ከማቴዎስ 19 የተጠቀሰው ይህ ጥቅስ በኋለኛው የትልቁ ክርስትና ትምህርት ውስጥ ታርሟል።
[112] ማቴዎስ 18፡15 (RSV).
[113] ማቴዎስ 18፡15 (RSV).
[114] ማቴዎስ 18፡16 (NRSV).

284 ይህ ሁሉ የሚያሳየው ስውር ኃጢአትን ነው። ነገር ግን ኃጢአታቸው ግልጽ ቢሆን፣ ዳኛውና ሁሉም ሰው ቢያውቁት በራሳቸው ላይ ውርደትን ካመጡት ያለ ኃጢአት ልትሸሽና ልታስወግዳቸው ትችላለህ፤ እንዲሁም በይፋ ምስክር ልትሆንባቸው ትችላለህ። ምክንያቱም አንድ ነገር በቀን ብርሃን በሚገለጥበት ጊዜ ብንናገር ስም የማጥፋት ወይም ኢፍትሐዊነት ወይም የሐሰት ምስክር ጥያቄ ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ በግልጽ በመጻሕፍት የተዘጋጀና በዓለም ሁሉ የተሠራጨውን የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ትምህርት ልንመረምር እንችላለን። ኃጢአት በግልጽ ከታወቀ ሰው ሁሉ ዐውቆት ከእርሱ እንዲጠበቅ ለማድረግ ግልጽና ተገቢ ቅጣት ሊከተል ይገባል።

285 እንግዲህ የዚህ ትእዛዝ ማጠቃለያና ፍሬ ነገር አለን፦ ማንም ሰው ባልንጀራውን፣ ወዳጁን ወይም ጠላቱን ለመጉዳት አንደበቱን መጠቀም የለበትም። ማንም ሰው ዳኛ ካልሆነ በስተቀር ወይም ያንን ሰው ለማረም ካልሆነ በደሉ እውነትም ይሁን ውሸት ስለ ባልንጀራው ክፉ መናገር የለበትም። ይልቁኑ አንደበታችንን ለሰው ሁሉ የተሻለ ነገር ለመናገር ብቻ መጠ ቀም ይገባናል፤ የባልንጀሮቻችንን ኃጢአትና ጉድለት ለመሰወር፣ ድርጊታቸውንም ለማጽደቅ፣
286 እንዲሁም በክብራችን ለመሸፈንና ለመጋረድ መጠቀም አለብን። ይህንንም የምናደርግበት ዋና ምክንያት ክርስቶስ ባልንጀራችንን አስመልክቶ ትእዛዛትን ባጠቃለለበት ወንጌል «ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው» ስላለ ነው።[115]

287 ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12[:22-23]፦ «ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁኑ የሚያስፈልጉ ናቸው፤ ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፤ በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል» እንደሚለው፣ ተፈጥሮ ደግሞ በገዛ አካሎቻችን ተመሳሳይ ነገር ያስተምረናል። ማንም ሰው ፊቱን፣ ዐይኑን፣ አፍንጫውንና አፉን አይሸፍንም፤ ምክንያቱም እነዚህ አካሎች እጅግ በጣም የተከበሩ ናቸው። ነገር ግን ደካሞች የሆኑና የምናፍርባቸውን የአካላችንን ክፍሎች በጥንቃቄ እንሸፍናለን። እጆቻችን፣ ዐይኖቻችንና መላው አካላችን እንኳ እነርሱን ለመሸፈንና ለመጋረድ መርዳት
288 አለባቸው። በመሆኑም በእርስ በርስ ግንኙነታችን ማንኛውንም ያልተከበረውንና ደካማ የሆነውን ለባልንጀሮቻችን ልንጋርድላቸው ይገባል። እንዲሁም ልናገለግላቸው፣ ልንረዳቸውና መልካም ስማቸውን ልናስተዋውቅ ይገባል። በሌላ በኩል ለውርደታቸው አስተዋጽኦ ከሚያደርግ
289 ከማንኛውም ነገር ልንከላከልላቸው ይገባል። ስለ ባልንጀሮቻችን በምንሰማው ሁሉ ላይ (በግልጽ የታወቀ ክፉ ነገር ካልሆነ) የተሻሉ ገንቢ የሆኑ ነገሮችን ለማኖር እንዲሁም በተሳሳተ መንገድ ነገሮችን በመተርጐም በመጠምዘዝ ባልንጀራቸውን ለመተቸት በትጋት ምሥጢር ለማውጣትና አንድን ነገር አጥምደው ለመያዝ ሙከራ የሚያደርጉትን መርዛማ ምላሶች መቃወም በተለየ ሁኔታ መልካምና የተከበረ ተግባር ነው። በአሁኑ ጊዜ ይህ በተለይ የተወደደውን የእግዚአብሔር ቃልና የእርሱን ሰባኪዎች ይመለከታል።

290 ዕውሩ ዓለምና ሐሰተኞች ቅዱሳን ቢገነዘቡት ይህ ትእዛዝ እግዚአብሔርን በጣም ደስ
291 የሚያሰኙና እጅግ የበዙ መልካም ነገሮችን ይዟል። አንደበታችን በብልቶቻችን መካከል ትንሽ ቢሆንም እንደ እርሱ መልካም ሊያደርግ ወይም ጉዳትን ሊያደርስ የሚችል ነገር በእኛ ወይም በአካባቢያችን የለም።[116]

*ዘጠነኛና ዐሥረኛ ትእዛዛት*

292 «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ።»

«የባልንጀራህን ሚስት፣ አሽከሩን፣ ገረዱን፣ በሬውን፣ አህያውን ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።»

293 እነዚህ ሁለቱ ትእዛዛት ቃል በቃል ሲወሰዱ ተለይተው ለአይሁዶች የተሰጡ ናቸው፤ ሆኖም በከፊል እኛንም የሚመለከቱ ናቸው። አይሁዶች እነዚህን ትእዛዛት ምንዝርን ወይም

[115] ማቴዎስ 7፡12።
[116] ያዕቆብ 3፡5ን ተመልከት።

ስርቆትን እንደሚያመለክቱ አድርገው አይተረጒሙአቸውም፤ ምክንያቱም እነዚህ በቀደሙት
ትእዛዛት በበቂ ሁኔታ የተከለከሉ ናቸው። ደግሞም አይሁዶች በትእዛዛቱ የታዘዙትን በጠበቁና
የተከለከሉትን ባልተላለፉ ጊዜ ትእዛዛትን ሁሉ የጠበቁ ይመስላቸዋል። ስለዚህ የባልንጀራን
ሚስት ወይም ንብረቱን መመኘትና መፈለግም ኃጢአት መሆኑን ለማሳወቅ ስለ ፈለገ
294 እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ትእዛዛት ጨምሮ ሰጠ። እነዚህ ትእዛዛት በተለይ ያስፈለጉት
በዚያን ጊዜ በነበረው የአይሁድ አስተዳደር አሽከር ወይም ገረድ እንደ አሁኑ ዘመን ነጻ ሆነው
ደመወዛቸውን እንደ ፈለጉ ማግኘት የማይችሉ ስለ ነበረ ነው። ይልቁን ልክ እንደ ማንኛውም
295 ከብትና ሌላ ንብረት አካላቸውና ያላቸው ሁሉ የባለቤቱ ንብረት ነበሩ። በተጨማሪም ማንም
ሰው ሚስቱን በግልጽ የፍቺ ወረቀት[117] በመስጠት ሊፈታትና ሌላ ሚስት ሊያገባ ይችል ነበር።
ስለዚህ ማንም ሰው የሌላ ሰውን ሚስት ሊወስድ የፈለገ እንደ ሆነ አንድ ሰበብ ፈልጎ ሚስቱን
በመፍታት የፈለጋትን ሴት ከባሏ በመለየት በሕጋዊ መንገድ ሊያገባት ይችል ነበር። በእኛ
መካከል ባለቤቱ አሽከሩን ወይም ገረዱን በሚያባርርበት ወይም የሌላን ሰው አሽከር
በሚያባብልበት ጊዜ ከሆነው የበለጠ በእነርሱ መካከል ኃጢአት ወይም ነውር አልነበረም።
296 ስለዚህ (ምንም እንኳ ሰፊና ከፍ ያለ አተገባበር ቢኖራቸውም) ሰው የባልንጀራው
የሆነውን ሁሉ ማለትም ሚስቱን፣ አገልጋዮቹን፣ ቤቱንና እርሻውን፣ መስኩን፣ የግጦሽ መሬቱን
ወይም ከብቱን በመውሰድ በግልጽ በመልካም ማስመሰልና በምክንያት በብልሃትና በተንኮል
በሰው ፊት ቅን በሚመስል መንገድ ለራሱ እንዳያደርገው ለመከልከል አይሁዶች እነዚህን
ትእዛዛት በትክክል ተርጒመዋል እላለሁ። እላይ ሰባተኛው ትእዛዝ የይዞታ መብት ሳይኖረን
የአንድን ሰው ንብረት እንዳንይዝበት ይከለክለናል። ነገር ግን እዚህ ላይ ደግሞ በሌሎች ሰዎች
ዐይን በማጭበርበር የማንወቀስበት ቢሆን እንኳ በማታለል ከባልንጀራችን ንብረት አንዳችም
እንዳንወስድ ተከልክሎአል።
297 አንድ ሰው የእርሱን ወይም የእርሷን ያህል ሌላው ሰው እንዳይኖረው መፈለግ ይህ
የሰው ልጆች ባሕርይ ነው። ሁሉም የተቻለውን ያህል ለራሱ ብቻ ሊያከማችና ሌሎች ለራሳቸው
298 እንዲፈልጉ ይሞክራል። ሆኖም ሁላችንም ራሳችን ቅን ሰዎች እንደ ሆንን እንቈጥራለን፤
እንዲሁም ተንኮላችንን ለመሸፈን መልካም ፊት እናሳያለን። በየዕለቱ የተሻልን ሆነን በመገኘት
ግልጽ ማታለያ ዘዴና ጥመት ያለበትን ብልሃት በመፍጠር በፍትሐዊነት ጥላ ሥር በመደበቅ
ሌላ ትርፍ ለማግኘት እናስባለን። ይህም ድርጊታችን ትክክለኛ ነው ብለን የምንኵራበት ሲሆን
299 አደራረጉ ጥመት እንዳልሆነ ለሌሎች ልናሳይ እንጣጣራለን። በዚህም ስለ እውነት ለፍትሕና
ለባልንጀራችን ችግር ሳይገዳቸው ቃላትን እያለዋወጡ እውነትን ከሚያጣምሙ ዳኞችና ጠበቆች
የተለየን አይደለንም። በአጭሩ «ሕግ ለጠንቃቃው ያደላል»[118] እንደሚባለው ንቁና ብልጡ
በእንዲህ ዓይነት ጉዳዮች የበለጠ ከሕጉ ይጠቀማሉ።
300 ስለዚህ ይህ የመጨረሻው ትእዛዝ ቀደም ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ዓለም ክፉ
ወስላቶች አድርጎ ለሚቈጥራቸው ሳይሆን ማንንም ስላልበደሉ ሐቀኞች በመምሰል የሰውን ሁሉ
ምስጋና ለሚፈልጉት የተነገረ ነው። በተለይ እንደ ዛሬው ባላባቶች፣ ጌቶችና መሳፍንት ከዚህም
በላይ እንደሚያደርጉ አይሁዶችም ራሳቸውን በዚህ መንገድ አይተዋል። ይሁን እንጂ ተራው
ሕዝብ ሀብት ለማግኘት ሲፈልግ ስለ ክብሩና ስለ መብቱ ብዙ ስለማይጨነቅ በባልንጀራው ላይ
ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት በሰባተኛው ትእዛዝ ተመልክቶአል።
301 አብዛኛውን ጊዜ ይህ የሚሆነው ሰው አንዳችን ነገር ከባልንጀራው ለመንጠቅና ለማግኘት
ወስኖ በሚሠማራበት የክስ ሂደት ነው። ለምሳሌ ሰዎች በትልቅ ውርስ፣ መሬት ወዘተ ላይ
በሚጨቃጨቁበትና በሚታገሉበት ጊዜ ማንኛውንም ሕጋዊ የሚመስሉ ነገሮችን ምርጫቸው
ያደርጋሉ፤ ሕጉ እንዲደግፋቸው ለማድረግም በመቀባትና በማጌጥ ተቃውሞ ሊያነሣ ወይም
ሕጋዊ ድርጊት ሊመሠርት በማይችል መልኩ የንብረት ባለቤትነት መብት ያገኛሉ።
302 በተመሳሳይ መልኩ፣ ሰዎች ሕንፃ፣ ከተማ፣ አገር ወይም አንድ ሌላ ትልቅ ነገር ለማግኘት
ቢመኙ፣ ንብረቱ ከሌላ ሰው እስኪወሰድና በሕጋዊ መንገድ እስኪሰጣቸው ድረስ በድርጊትና

[117] ዘዳግም 24:1ን ተመልከት።

[118] "Vigilantibus *jura subveniunt*" ተብሎ በላቲን በተሰጠው ጥቅስ ውስጥ ያለ ምሳሌአዊ አባባል ነው።

በሕጋዊ ማኅተም ከመስፍኑ በሕጋዊ መንገድ እንዳገኙ በማሳየት በጉቦ ወይም በዝምድና በሚገኝ
መንገድ ሁሉ ይሞክራሉ::
303 በየዕለቱ በሚከናወነው ሥራም ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል፤ ሰዎች ከአንድ ሰው እጅ
በማታለል ሁሉንም ነገር በሚወስዱበት ጊዜ ተጎጂው ለመከላከል አቅም አይኖረውም:: ትርፍ
ለማግኘት አጋጣሚ ፈልጎ፣ ከባላንጣው ወይም ከዕዳው የተነሣ ንብረቱን ሊይዝ ወይም ያለ
ኪሣራ ሊሸጥ አይችልም:- ሰውየውን በግማሽ ወይም ባነሰ ዋጋ እስከሚያገኙ ድረስ
ያጣድፉታል:- ሆኖም ይህን ነገር በሕገ ወጥ መንገድ እንደ ተገኘ አይቈጥሩትም፤ ይልቁን
በሕጋዊ መንገድ እንደ ተገዛ ይቈጥሩታል:: ስለዚህ «ቅድሚያ የመጣ ቅድሚያ ይገለገላል»:-
እንዲሁም «ለራስህ ጥንቃቄ አድርግ»[119] እና ሌሎች መውሰድ የሚችሉትን ያህል ይውሰዱ
304 የሚሉት አባባል ዓይነት ነው:: ሰዎች በዚህ ተወዳጅ ሰበብ ይህን ያህል ለራሳቸው
የሚወስዱበትና ዓለምም እንደ ስህተት የማይቈጥረውን ይህንን ዐስተሳሰብ እንደ ክፉ ሥራ
ሊቈጥር የሚደፍር ማነው? ዓለም አንድ ሰው ለባልንጀራው ጥቅም የሚሆን ነገር ማድረጉን
ወይም ለሚያጣው ነገር መስዋእት መክፈል የማይችለውን ማየት አትፈልግም:: ይህ በግሉ
እንዲያጋጥመው የሚፈልግ ማነው? ከዚህ የተነሣ እነዚህ ሰበቦችና አስመሳይነት ሐሰት ናቸው::
305 ይህ ሚስቶችን አስመልክቶ በጥንት ዘመን ነገሩ እንደዚሁ ነበር፤ እንዲህ ያሉ
ማጭበርበሮችን ያውቃሉ፤ አንድ ሰው የሌላውን ሚስት የራሱ ለማድረግ ሲመኝ በራሱ ወይም
በሌሎች ሰዎች አማካይነት የቀድሞ ባሏን የሚያበሳጭባቸውን የተለያዩ መንገዶችን ይፈልጋል::
ወይም ደግሞ እርሷ ለባሏ የማትታዘዝና አብራው እንዳትኖር አስቸጋሪ ሴት እንድትሆን
በማድረግ ባሏ እንዲተዋትና እንዲፈታት እና ለሌላው ሰው እንድትሆን ያደርግ ነበር:: እንዲህ
ያለ አደራረግ ያለ ጥርጥር በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕግ[120] የተለመደ ነበር፤ ምክንያቱም
በወንጌልም እንኳ ቅዱስ ማርቆስ ሲመሰክር[121] እንደምናነበው ንጉሥ ሄሮድስ ወንድሙ በሕይወት
እያለ የወንድሙን ሚስት የራሱ አድርጎ የወሰደ ሲሆን ትክክለኛና የተከበረ ሥራ እንደ ሠራ
306 ሰው በሥልጣን ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር:: ነገር ግን ዐዲስ ኪዳን የተጋቡ ሰዎች እንዳይፋቱ[122]
ስለሚያዝ እንዲህ ያለ ምሳሌነት በዚህ ዘመን በእኛ መካከል እንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ::
አሁንም ቢሆን በእኛ ዘመን አንድ ሰው ባለጸጋ እጮኛውን በዘዴ በማታለል ነጥሎ ሊወስድ
ይችላል:: እንዲሁም በመካከላችን የአንድን ሰው ወንድ ወይም ሴት ሠራተኛ ለመውሰድ
ማባበልና ማታለል ወይም በጥሩ ቃላት ማማለል የተለመደ ሆኖአል::
307 ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የባልንጀሮችህ የሆነውን ማናቸውንም ነገር መውሰድ እና
በእነርሱ ጉዳት የአንተን ስግብግብነት ማርካት፣ ከዚህም የተነሣ ኪሣራ እንዲያጋጥማቸው
እንደማይፈልግ መማር አለብን፤ ምንም እንኳ በዓለም ፊት በክብር ንብረት መያዝ የምትችል
ቢሆንም እነዚህ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህን ማድረግ ስውር ተንኮልና ክፋት ሲሆን እንደ
ተናገርነው ከመያዝ ለማምለጥ «ከጠረጴዛ በታች»[123] የሚፈጸም ነው:: ምንም እንኳ በማንም ላይ
ስህተት እንዳልሠራህ ብትሆንም፣ በባልንጀራህ መብት ላይ በደል ፈጽመሃል:: ሌብነት ወይም
ማታለል ተብሎ ላይጠራ ይችላል ነገር ግን መመኘት ነው:- ይኸውም በባልንጀሮችህ ንብረት
ላይ እቅድ ነድፈሃል፤ ይህንንም ያደረግኸው ከፈቃዳቸው ውጪ በማጥመድና እግዚአብሔር
308 የሰጣቸውን በመመኘት ነው:: ዳኛ ወይም ሌላ ሰው ንብረቱን እንድትይዝ ፈቅዶ ሊሆን
ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አይፈቅድም፤ ምክንያቱም እርሱ ክፉ ልብህንና ዓለማዊ
አታላይነትን ያያል:: ለዓለም አንድ ስንዝር[124] ብትሰጣት ብዙ ርቀት[125] በመውሰድ
ኢፍትሓዊነትንና አመጽን ታስከትላለች::

[119] ሁለት ምሳሌአዊ አባባሎች ሆነው ቃል በቃል ሲተረጉሙ አንደኛው «የቀደመው ከሁሉ የላቀ ነው» እንደ ማለት ሲሆን ሁለተኛው «እያንዳንዱ ለራሱ የሚሆነውን ይፈልግ» ነው::
[120] በላቲን «በአይሁዶች መካከል» ማለት ነው::
[121] ማቴዎስ 14:3-4፤ ማርቆስ 6:17-20::
[122] ማቴዎስ 5:31-32፤ 19:3-9፤ ማርቆስ 10:2-12፤ ሉቃስ 16:18፤ 1ቆሮንቶስ 7:10-11::
[123] «በቆብ ሥር» የሚለው አባባል ቃል በቃል ሲተረጎም ምሳሌአዊ አባባል ሆኖ ጥንቆላ ከሚለው ሀሳብ የመነጨ ነው::
[124] በጀርመንኛ Finger ቃል በቃል ሲተረጎም “finger” እንደ መለኪያ ያገለግላል::
[125] በጀርመንኛ *Elle* ሲሆን 15 ወይም 20 ኢንች ያህል የሚለካበት መለኪያ ነው::

309 ይህ የተለመደ የዚህ ትእዛዝ ትርጕም ነው። በመጀመሪያ ባልንጀሮቻችንን ለመጉዳት
እንዳንፈልግ ወይም ጉዳት እንዲደርስባቸው እንዳንተባበር ታዝናል ወይም ለዚህም ዕድል
እንዳንሰጥ ታዝናል። በዚህ ፈንታ ለራሳችን እንዲደረግልን እንደምንፈልገው ሁሉ ባልንጀሮቻችን
የራሳቸው የሆነውን እንዲኖራቸው በደስታ ለማስተዋወቅ ማንኛውም የሚጠቅማቸውንና
310 የሚያገለግላቸውን እንዲያድግላቸው በደስታ ከሌላ እንድንከላከልላቸው ነው። እንግዲህ እነዚህ
ትእዛዛት በቀጥታ ያነጣጠሩት በምቀኝነትና በአሳዛኝ ምኞት ላይ ነው፤ ስለዚህ በባልንጀሮቻችን
ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ጉዳት ሥርና መሠረት እግዚአብሔር ያስወግዳል። ስለዚህ
በግልጽ ቃላት፡- «አትመኝ» ወዘተ በማለት አስቀምጦአል። ከዚህ ሁሉ ልብ ንፁሕ እንዲሆን
ይፈልጋል፤ ይህም ቢሆን በእዚህ ምድር እስካለን ድረስ ይህን ልንፈጽም አንችልም። እንግዲህ
ይህ ትእዛዝ እንደ ቀሩት ሁሉ በተከታታይ እየከሰሰን፣ በእርግጥ በእግዚአብሔር ፊት ደግሞ
ምን ያህል በእውነት ቅኖች እንደ ሆንን ያሳያል።

*[የዐሠርቱ ትእዛዛት ማጠቃለያ]*[126]

311 እዚህ ላይ ሕይወታችን በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን ለማድረግ
የመለኮታዊ ትምህርት ማጠቃለያ የሆኑት ዐሠርቱ ትእዛዛት አለን። እነርሱም መልካም
ሥራዎች ሁሉ የሚመነጩባቸው እውነተኛ ምንጭና መልካም ሥራዎች ሁሉ የሚፈስሱባቸው
እውነተኛ መሥመሮች ናቸው። ከነዚህም ዐሥርቱ ትእዛዛት ውጪ የትኛውም ድርጊት ወይም
መልካም ሕይወት በዓለም ፊት ምንም ያህል ታላቅ ወይም ውድ ቢሆን እግዚአብሔርን
ማስደሰት አይችልም።
312 ታላላቅ ቅዱሳናችን እነዚህን ትእዛዛት ምንም እንደማይጠቅሙ ወይም ከረጅም ዘመናት
በፊት እንደ ተፈጸሙ በመቍጠር ችላ በማለት ለመንፈሳዊ ሥርዓታቸውና በራሳቸው ለፈጠ
ሩአቸው እንዲሁም ለክብራቸው ሲሉ ለፈለሰፉአቸው አስቸጋሪ ሥራዎች ክብደት በመስጠት
እንዴት እንደሚኩራሩ እንመልከት።
313 ለእኔ እንደሚመስለኝ እነዚህን ትእዛዛት ለመጠበቅ ጭምትነትን፣ ትዕግሥትን፣ ጠ
ላቶቻችንን መውደድን፣ ንጽሕናን፣ ቸርነትን ወዘተ. የመሳሰሉትን ሁሉ በመለማመድ ሙሉ
በሙሉ ልንጠመድ ይገባል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ሥራዎች በዓለም ፊት አስፈላጊ ወይም
ትኵረት የሚያሰጡ አይደሉም። ለተወሰኑ ልዩ ጊዜያቶች፣ ቦታዎች፣ ወጎችና ሥነ ሥርዓቶች
ያልተለመዱና ለታይታ የሚቀርቡ አይደሉም፤ ነገር ግን ያለ ምንም መደነቅ በየዕለቱ አንዱ
314 ጎረቤት ለሌላው የሚያደርጋቸው የተለመዱ ተግባሮች ናቸው። ሌሎቹ ድርጊቶች የሰውን
ዓይንና ጆሮ የሚማርኩ ናቸው። በታላቅ ድምቀት፣ በውድ ገንዘብ፣ በአስደናቂ ሕንፃዎች
በመደገፍ በአንፀባራቂና በደመቀ ሁኔታ የከበሩ ናቸው። ዕጣን ማጨስ፣ መዘመርና ደወል
መደወል፣ ሻማ እና ጧፍ ማብራት ከመታየትና ከመሰማት በስተቀር ምንም አይደለም። ቄሱ
ወርቃማ የአገልግሎት ልብስ[127] ለብሶ ቢቆም ወይም አንድ ያልቀሰሰ ሰው ቀኑን ሙሉ ቤተ
ክርስቲያን በጉልበቱ ተንበርክኮ ቢውል በበቂ ሁኔታ ሊነገር የማይቻል ውድ ሥራ እንደ ሆነ
ይቈጠራል። ነገር ግን አንዲት ምስኪን የቤት ሠራተኛ በታማኝነት ሕፃኑን ልጅ እንደ ተነገራት
ስትንከባከብ ምንም ሥራ እንደ ሠራች አይቈጠርም። አለበለዚያ ወንዶችና ሴቶች መነኩሳት
በገዳማቸው ውስጥ ምን ይፈልጋሉ?
315 እስቲ አስቡ እነዚህ ራሳቸውን ያጸደቁቱ ተስፋ ቢስ ቅዱሳን ዐሠርቱ ትእዛዛት ከሚያዙን
የበለጠ የአኗኗርን መንገድ ሊያስተምሩ መድፈራቸው ሰይጣናዊ አሠራር አይደለምን? እንደ
ተናገርነው ይህ ለተራው ሰው የተለመደ ኑሮ እንደ ሆነና የእነርሱን ግን ለቅዱሳንና ለፍጹማን
316 የተሰጠ አገልግሎት አስመስለው ያቀርባሉ። እነዚህ ጎስቋላና ዕውር ሞኞች ከዐሠርቱ ትእዛዛት
አንዲቷን እንኳን እንዲጠብቅ የታዘዘውን ሙሉ በሙሉ መፈጸም የሚችል አንድም ሰው

[126] ይህ ርእስ በመጀመሪያው እትም ውስጥ አይገኝም። በሁለተኛው (1529) እና በጀርመኑ (1530) እና (1538) እትም እንዲሁም በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት 1580 እጥጉ ላይ ተደርጎአል።
[127] ወርቅማው ካባ ለቅዱስ ቍርባን ጊዜ በሚለበስ ልብስ ላይ የሚደረብ የደወል ቅርጽ ያለው ካባ ሆኖ በወርቅ፣ በብርና በከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ ካባ ነው።

እንደማይገኝ ማየት ይሳናቸዋል። በኋላ ላይ እንደምንሰማው ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የእምነት
መግለጫና የጌታ ጸሎት እዚህ ላይ ሊደግፉን ይገባል። በእነርሱም አማካይነት እርዳታ
ልንፈልግና ልንቀበል ያለ ማቋረጥ ልንጸልይ ይገባናል። ስለዚህ ጉራዎቻቸው ሁሉ «በርግጥ
አንድ ግሮቸን ለመክፈል የሌለኝ ነገር ግን ዐሥር ገልዴን እከፍላለሁ» በማለት እንደሚኩራሩ
ዓይነት ነው።[128]

317 ደጋግሜ ይህንን የምልበት ምክንያት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ የተተከለውንና
የተጣበቀውን መርዝ እንድናስወጣና በምድር የሚኖሩ የሁሉም መደብ ሰዎች ወደ እነዚህ
እንዲያዘነብሉና እንዲታዘዙ ነው። ዐሠርቱ ትእዛዛትን መፈጸም ከሰው አቅም በላይ ስለ ሆነ
ከእነርሱ ጋር የሚስተካከል አስተምህሮን ወይም የማኅበራዊ አስተዳደር መመሪያን ሰዎች
ከማውጣታቸው በፊት ረጅም ዘመን ያልፋል። እነርሱን ሊፈጽማቸው የሚችል ሰው ቢገኝ እርሱ
ሰማያዊና መልአካዊ ሰው ሲሆን ሥራውም በምድር ላይ ሊገኝ ከሚችለው ቅድስና በጣም
318 የሚበልጥ ነው። አንተም ትኩረት ሰጥተህ ልታደርጋቸውና ልትፈጽማቸው የምትችለውን እስከ
መጨረሻ ብታደርግና ብትጣጣር ሌላ ቅድስናንና ሥራን እስከ መተው ትደርሳለህ።

319 የመጀመሪያውን ክፍል[129] አስመልክቶ ለትምህርትና ለምክር ይህ ይብቃ። ይሁን እንጂ
ለማጠቃለያ ከመጀመሪያው ትእዛዝ ጋር ተያይዞ አስቀድሞ እላይ የተባለውን መድገም
ይገባናል፤ ይህንንም የምናደርገው ዐሠርቱን ትእዛዛት እንዴት እንደምናስተምርና ተግባራዊ
እንደምናደርግ ስንማር እግዚአብሔር መሰጠትን ከእኛ እንደሚፈልግ ለማሳየት ነው።

320 «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ
እስከ ሦስትና አራትም ትውልድም ድረስ የማመጣ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ
ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ ነኝና።»

321 ይህ አባሪ ጽሑፍ ምንም እንኳ በተለይ ከመጀመሪያው ትእዛዝ ጋር የተያያዘ ቢሆንም
እላይ እንደ ሰማነው ለሁሉም ትእዛዛት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ሁሉም ትእዛዛት ወደ እርሱ
ማመልከት አለባቸው። እነዚህን ዐሠርቱን ትእዛዛት ለመጠበቅ ለምን ቆም ብለን እንዳሰብንና
እንደተገደድን እንዲያስታውሱና እንዲጠብቁ በወጣቶች ፊት ማኖርና ማስተጋባት አለብን
ብዬአለሁ። ይህ አባሪ ጽሑፍ ዘልቆ ከእያንዳንዱ ትእዛዝ ጋር የተያያዘና የተዋሐደ ሆኖ ሊቈጠር
ይገባል።

322 እንግዲህ አስቀድመን እንደ ተናገርን ሁሉ እነዚህ ቃላት እኛን ለማሸበርና ለማስጠንቀቅ
ብቻ ሳይሆን እኛን ለመማረክና ስሜታችንን ለመሳብ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንቀበልና
እንደሚሠራም በአጽንኦት እንድንቈጥረው ቀኍጣ የሞላበት ዛቻና ተወዳጅነት ያለበትን ተስፋ
ይዘዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ትእዛዛቱ እንዴት አስፈላጊና ጥብቅ እንደሆኑ
እንደሚቈጣጠር፤ ማለትም ትእዛዛቱን የሚንቁአቸውንና የሚተላለፉትን በአስፈሪና በከባድ
ሁኔታ እንደሚቀጣቸው፣ እንደገናም ትእዛዛቱን በደስታ የሚያከብሩትን፣ የሚጠብቁትንና
በዚያው መሠረት የሚኖሩትን በብልጽግና እንደሚሸልም፣ እንደሚባርክና በመልካም ነገሮች
323 ሁሉ እንደሚሞላባቸው እግዚአብሔር ያውጃልና ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር ራሱን እንደ
ርኅሩኅ አባት ስለ ገለጸና ሁሉንም ጸጋና በረከት የሚሰጠን ስለ ሆነ እርሱ እንዳይቆጣ ሥራችን
ሁሉ እርሱን ከሚፈራ ልብ የመነጨ፣ ወደ እርሱ ብቻ የሚመለከትና እርሱን ከመፍራትም
የተነሣ ከፈቃዱ ተቃራኒ የሆነውን ነገር የማያደርግ እንዲሆን ከእኛ ይፈልጋል። በግልባጩ
አነጋገር ድርጊቶቻችን ሁሉ እርሱን ከሚታመን ልብ የሚመነጩና ስለ እርሱም የሚጠይቀንን
ሁሉ የሚያደርግ እንዲሆን ይፈልጋል።

324 ይህ የሌሎቹ ትእዛዛት ሁሉ ምንጭ የሆነው የመጀመሪያውና ዋናው ትእዛዝ ፍችና
ትክክለኛ ትርጕም ነው። «ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለው ቃል፣ በቀላሉ «እንደ አንዱ
እውነተኛ አምላክህ አድርገህ ፍራኝ፤ ውደደኝ፤ እንዲሁም እመንብኝ» ማለት ነው። ምክንያቱም
ልብህ ለእግዚአብሔር እንዲህ ዐይነት አመለካከት ካለው ይህንን ትእዛዝና ሌሎችንም ትእዛዛት
ፈጽመሃልና። በሌላ በኩል በሰማይ ወይም በምድር ያለውን ማንኛውንም ነገር የሚፈራና
325 የሚወድ ሰው ይህንንም ሆነ ሌላ ማንኛውንም ትእዛዝ አይጠብቅም። ስለሆነም መላው ቅዱሳት

[128] አንድ ጉልዴን ሃያ አንድ ግሮቸን ያህል ነው።

[129] ይህ የክርስትና ትምህርት የመጀመሪያው ክፍል ሲሆን እርሱም ዐሠርቱ ትእዛዛት ማለት ነው።

መጻሕፍት እነዚህን ሁለት ነገሮች፣ እግዚአብሔርን መፍራትንና በእርሱ ማመንን በማገናኘት
በሁሉም ስፍራ ይህንን ትእዛዝ አውጀዋል፤ አቅርበዋልም። ነቢዩ ዳዊት [መዝ 147፡11]፡-
«እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱም በሚታመኑ ይደሰታል» ብሎ በሚናገርበት ጊዜ በተለይ
በመዝሙራቱ ሁሉ ትእዛዙን ያውጀዋል። «እግዚአብሔር ሌሎች አማልክት በሌሉአቸው
በእነዚያ ይደሰታል» እንደሚል ሁሉ ሙሉውን ትእዛዝ በአንድ ቀለበት የሚያብራራ ይመስላል።
326 ስለሆነም የመጀመሪያው ትእዛዝ ውበቱን ለሌሎች ትእዛዛት ሁሉ ግልጽ የሚያደርግና
የሚያካፍል ነው። ይህ ያለ ማቋረጥ እንዲደጋገምና እንዳይረሳ የመጨረሻውን ከመጀመሪያ ጋር
እንደሚያስርና ሁሉንም ነገር በአንድ ላይ እንደሚይዝ እንደ አበባ ጉንጉን ማሰሪያና መያዣ
እነዚህ በሁሉም ትእዛዛት ውስጥ ያሉ አያያዥ ቃላት የመደምደሚያ ቃላት እንዲኖሩ አድርግ።
ለምሳሌ በሁለተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔርን እንድንፈራና በመሳደብ፣ በመዋሸት፣ በማታለል፣
እንዲሁም በሌላ ዓይነት የሥነ ምግባር ውድቀትና በክፋት ስሙን በከንቱ እንዳናነሣ ነገር ግን
የመጀመሪያው ትእዛዝ በሚጠይቀው መሠረት ከፍቅርና ከእምነት በሚመነጬት በጸሎት፣
በውዳሴ እንዲሁም በምስጋና እርሱን በመጥራት ስሙን በተገቢው መንገድ እንድንጠቀምበት
ተነግሮናል። በተመሳሳይ መንገድ ቃሉን እንዳንንቅ፣ ነገር ግን እንድንማረው፣ በደስታ
እንድንሰማው፣ ቅዱስ አድርገን እንድንጠብቀው፣ እንዲሁም እንድናከብረው ይህ ፍርሃት፣ ፍቅር
እንዲሁም እምነት ሊያስገድደን ይገባል።
327 እንደገና፣ ባልንጀራችንን በሚመለከቱት በሚከተሉት ትእዛዛት ሁሉ ማንኛውም ነገር
ከመጀመሪያው ትእዛዝ ኃይል ይወጣል፡- ለአባቶች፣ ለእናቶች፣ ለአለቆች፣ እንዲሁም ለባለ
ሥልጣናት ሁሉ ስለ ራሳቸው ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ብለን መገዛት፣ ማክበር፣ እንዲሁም
መታዘዝ አለብን። አንድን ነገር የምታደርገው አባትህንና እናትህን ደስ ለማሰኘት ብቻ
አይደለም። ይልቁኑ፣ እግዚአብሔር ከአንተ ለሚፈልገውና በጣም በእርግጥ ከአንተ ለሚጠይቀው
ነገር ትኩረት ስጥ። ይህንን ብታስቀር፣ ቁጡ ዳኛ አለህ፤ አለበለዚያ መሐሪ አባት አለህ።
328 እንደገና፣ (እነዚህ ነገሮች በታዘዙበት ቅደም ተከተል መሠረት)፣ እንደዚያ ለማድረግ
ዕድሉና አጋጣሚው የነበረህና የሚገስጽህ ያልነበረ ቢሆንም በባልንጀሮችህ ላይ ጥፋት፣ ጉዳት፣
ወይም ጥቃት መፈጸም፣ ወይም በማንኛውም መንገድ ሰውነታቸውን፣ የትዳር ጓደኛቸውን፣
ንብረታቸውን፣ ክብራቸውን ወይም መብታቸውን በሚመለከት ጉዳት ልታደርስባቸው
አይገባም። በተቃራኒው፣ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር አብዝቶ ብድራትህን እንደሚመልስልህ
መተማመን በምትችለው በማንኛውም ሁኔታና ስፍራ ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ባለህ ፍቅርና
እርሱን ለማስደሰት ለሰዎች ሁሉ መልካም ማድረግ፣ መርዳትና ጥቅማቸውን ከፍ ማድረግ
329 አለብህ። ስለሆነም የመጀመሪያው ትእዛዝ ለሌሎች ትእዛዛት ሁሉ ዋናና መፍለቂያ መሆኑን
ትመለከታለህ፤ እንደገናም፣ መጨረሻና መጀመሪያ የተያያዙና በአንድ ላይ የተሳሰሩ ይሆኑ
ዘንድ ሁላቸውም ወደ እርሱ ይመለሳሉ፤ በእርሱም ይደገፋሉ።
330 እንደ ከብቶች በድብደባና በግዳጅ ሳይሆን፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍርሃትና
አክብሮት ያድጉ ዘንድ ወጣቶችን ስለዚህ ሁሉ ማስተማር፣ መገሠጽ፣ እንዲሁም ማሳሰብ
ሁልጊዜ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው እላለሁ። እነዚህ ትእዛዛት ከፍ ባለ ቅንነት የሚመለከታቸው፣
የሚቈጣውና የሚንቁአቸውን የሚቀጣው፣ እንዲሁም፣ በተቃራኒው የሚጠብቁአቸውን
አትረፍርፎ የሚሸልመው እጅግ በጣም ታላቅና ባለግርማ የሆነው የእግዚአብሔር ትእዛዛት
እንጂ የማይረቡ የሰው ቀልዶች አይደሉም። ሰዎች ይህንን ከግምት ውስጥ በሚያስገቡበትና
በሚያስተውሉበት ስፍራ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በደስታ ለማድረግ ሳይታሰብ የሚነሣሣ
331 ስሜትና ፍላጎት ይኖራቸዋል። ስለዚህ የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ በእያንዳንዱ ቅጥርና ጥግ፣
እንዲሁም በልብሶች ላይ እንኳ ዐሥርቱን ትእዛዛት እንዲጻፉ ያደርግ የነበረው ያለ ምክንያት
አይደለም።[130] አይሁድ እንዳደረጉት፣[131] ለዕይታ ብቻ እዚያ እንዲኖሩ ለማድረግ ሳይሆን ነገር
ግን በቀጣይነት በፊታችን ያለ ማቋረጥ በአእምሮአችን ልንጠብቃቸው እንዲሁም
332 በሥራዎቻችንና በመንገዶቻችን ሁሉ ተግባራዊ ልናደርጋቸው ይገባናል። እያንዳንዳችን በሁሉም

[130] ዘዳግም 6፡8-9፤ 11፡20።
[131] ማቴዎስ 23፡5።

ሁኔታዎች፣ በሁሉም እንቅስቃሴዎችና አድራጎቶች፣ በምንመለከትበት ቦታ ሁሉ እንደ ተጻፉ
ያህል፣ በምንሄድበት ቦታ ወይም በምንቆምበት ስፍራ ሁሉ የዕለት ተዕለት ልምምድ ጉዳይ
ልናደርጋቸው ይገባናል። ስለሆነም በቤት፣ በራሳችንና በውጪ በባልንጀሮቻችን መካከል
ዐሥርቱን ትእዛዛት ተግባራዊ ለማድረግ በቂ የሆነ አመቺ ጊዜ እናገኛለን፤ እንዲሁም ማንም
ሰው እነርሱን ከርቀት መፈለግ አይኖርበትም።
333 እነዚህ ዐሥርቱ ትእዛዛት ከሌሎች ትእዛዛት ተለይተው ትምህርት የሚሰጥባቸውና
ተግባራዊ ከሚሆኑ ሥርዓቶች፣ ትእዛዛት፣ እንዲሁም ሥራዎች ሁሉ በላይ በከፍተኛ ሁኔታ
እንዴት እንደሚወደሱና ከሚገባ በላይ እንደሚሞገሱ ደግመን እናያለን። እዚህ ላይ ምላሽ
የሚያሻው ጥያቄ መሰንዘር እንችላለን፡- ጠቢባንና ቅዱሳን ሁሉ ወደ ፊት ይውጡና፣ ቢችሉ፣
እግዚአብሔር በእነዚህ ትእዛዛት እጅግ በጣም ታላቅ ከሆነው ከቀኊጣውና ከቅጣቱ ማስፈራራት
በታች እጅግ በጽናት የሚፈልገውንና የሚያዝዘውን፣ በዚሁ ጊዜም በመልካም ነገሮች ሁሉና
በበረከቶች እኛን የሚያረሰርስባቸው የከበሩ ተስፋዎችን ለእኛ የሚጨምርበት እንደዚያ ያለ
ማንኛውንም ሥራ ይሥሩ። ስለዚህ ከሌሎች አስተምህሮዎች ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ለእኛ
እንደ ሰጠን ከሁሉ እንደሚበልጠው መዝገብ ግምትና ዋጋ ልንሰጣቸው ይገባል።

## ሁለተኛ ክፍል፡- የእምነት መግለጫ

1 እስከ አሁን ድረስ ከክርስትና አስተምህሮ የመጀመሪያውን ክፍል ሰምተናል፣ በእርሱም
እግዚአብሔር እንድናደርገውና እንዳናደርገው የሚፈልገውን ዐይተናል። እኛ ከእግዚአብሔር
መጠበቅና መቀበል ስላሉብን ነገሮች ሁሉ የሚገልጸው የእምነት መግለጫው ቀጥሎ ይቀርባል።
2 በአጭሩ፣ እግዚአብሔርን በፍጹም እንድናውቀው ያስተምረናል። እርሱም ዐሠርቱ ትእዛዛት
የሚጠይቁንን ለመፈጸም እንድንችል ያግዘን ዘንድ የተሰጠ ነው። ከላይ እንደተናገርነው ዐሠርቱ
ትእዛዛት ከፍ ብለው የተቀመጡ በመሆናቸው የሰው ችሎታ ሊጠብቃቸው በጣም ትንሽና
ደካማ ነው። ስለዚህ ይህንን ለማድረግ የትና እንዴት ኃይል እንደምናገኝ ለማወቅ እንደ ሌላው
ሁሉ ይህንን ክፍል መማር አስፈላጊ ነው። ዐሥርቱ ትእዛዛት ሊጠበቁ እንደሚገባቸው
3 ለመፈጸም በራሳችን ኃይል ብንችል ኖሮ የእምነት መግለጫውም ሆነ የጌታ ጸሎት፣ ባላስፈለጉን
4 ነበር። ነገር ግን የእምነት መግለጫውን ጥቅምና አስፈላጊነት ከማብራራታችን በፊት፣ እንደ
መጀመሪያው እርምጃ፣ ማንኛውም ሰው ራሱን የእምነት መግለጫውን ቢማር፣ ቢያውቅና ቢረዳ
በቂ ነው።
5 በመጀመሪያ ደረጃ የእምነት መግለጫው በዐሥራ ሁለት አንቀጾች የተከፋፈለ ነበር።[132]
በእርግጥ፣ በእግዚአብሔር ቃል ያሉትና የእምነት መግለጫው ክፍል የሆኑት መሠረታዊ ነገሮች
ሁሉ አንድ ላይ ቢሰበሰቡ ኖሮ፣ ብዙ ተጨማሪ አንቀጾች ይኖሩ ነበር፤ ወይም ሁላቸውም በጣም
6 ጥቂት በሆኑ ቃላት በግልጽ አይነገሩም ነበር። ነገር ግን ልጆችን ለማስተማር እጅግ በጣም
ግልጽና ቀላል ለማድረግ እኛ የምናምነው ማንኛውም ነገር በተዛመደባቸው በሥላሴ ሦስቱ
አካላት መሠረት መላውን የእምነት መግለጫ በአጭሩ በሦስት ዋና ዋና አንቀጾች[133] አጠቃለን
እናቀርባለን። ስለሆነም እግዚአብሔር አብን የሚመለከተው የመጀመሪያው አንቀጽ ፍጥረትን፣
ወልድን የሚመለከተው ሁለተኛው ድኅነትን፤ መንፈስ ቅዱስን የሚመለከተው ሦስተኛው
7 መቀደስን ይገልጻሉ። ከዚያ በኋላ የእምነት መግለጫው፡- «በፈጠረኝ በእግዚአብሔር አብ
አምናለሁ፤ በአዳነኝ በእግዚአብሔር ወልድ አምናለሁ፤ በሚቀድሰኝ በእግዚአብሔር መንፈስ
ቅዱስ አምናለሁ» በሚል አጭር ቃል ማጠቃለል እንችላለን። አንድ አምላክ አንድ እምነት፤
ነገር ግን ሦስት አካላት፣ ስለዚህም ደግሞ ሦስት አንቀጾች ወይም የእምነት መግለጫዎች
8 ናቸው። በእነዚህ ቃሎች ላይ በአጭሩ አስተያየት እንስጥ።

---

[132] 400 ዓ.ም. ገደማ በማስረጃ የመጀመሪያ የሆነው ወግ፣ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እያንዳንዳቸው ለሐዋርያት የእምነት መግለጫ አንዳንድ ሐረግ አቅርበዋል።

[133] በ1520 ሉተር አስቀድሞ የእምነት መግለጫውን «ሦስቱ ቅዱስ፣ የሥላሴ መለኮታዊ አካላት በሚዛመዱበት መሠረት፣ መጀመሪያ ከአብ፣ ሁለተኛ ከወልድ፣ እንዲሁም ሦስተኛ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተጣጥሞ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች» ከፍሎአቸዋል (WA 7:214; LW 43:24).

9 «እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን ... በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።»
10 ይህ የእግዚአብሔር አብን ባሕርይ፣ ፈቃድ፣ ተግባራት፣ እንዲሁም ሥራ
የምንገልጽበትና በምሳሌ የምናስረዳበት እጅግ በጣም አጭሩ መንገድ ነው። ዐሥርቱ ትእዛዛት
ከአንድ አምላክ በላይ እንዳይኖረን ያብራሩ ስለ ሆነ፣ እንዲህ ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል፡-
«እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሕልውና አለው? ምንስ ይሠራል? እናውቀው ዘንድ እንዴት
ልናመሰግነው ወይም ልንስለው ወይም ልንገልጸው እንችላለን?» ይህ በዚህ ቦታና በሚከተሉት
አንቀጾች ትምህርት ተሰጥቶበታል። የእምነት መግለጫው በመጀመሪያው ትእዛዝ ላይ
11 ከተመሠረተ የክርስቲያኖች ምላሽና መግለጫ በቀር ሌላ ነገር አይደለም። አንድን ወጣት ልጅ፡-
«ወዳጄ ሆይ፣ ምን ዓይነት አምላክ አለህ? ስለ እርሱስ ምን ታውቃለህ?» ብለህ ብትጠይቀው
እርሱ ወይም እርስዋ፡- «መጀመሪያ፣ አምላኬ ሰማይንና ምድርን የሠራው እግዚአብሔር አብ
ነው፤ ከእርሱ ብቻ በቀር ምንንም እንደ እግዚአብሔር አልቈጥርም፤ ምክንያቱም ሰማይንና
ምድርን ሊፈጥር የሚችል ማንም የለም» ብሎ ይመልሳል።
12 በጣም ለተማሩና በመጠኑ የበለጠ በቂ መረዳት ላላቸው ሰዎች ሦስቱ አንቀጾች በሙሉ
በይበልጥ በተሟላ ሁኔታ ሊተነተኑና በብዙ ክፍሎች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። ነገር ግን ለወጣት
ተማሪዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን ማመልከት በቂ ነው፤ ይኸውም፣ እንዳልነው፣
13 ይህ አንቀጽ ፍጥረትን ይመለከታል። «የሰማይና የምድር ፈጣሪ» የሚሉትን ቃላት ማጉላት
ይገባናል። በእነዚህ ቃላት «ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር
አምናለሁ፣» ወዘተ. ስትል ምን ማለትህ ነው? መልስ፡- እኔ የእግዚአብሔር ፍጡር መሆኔን
ሥጋ፣ ነፍስ፣ እንዲሁም ሕይወት፣ ትንንሽና ትልልቅ ብልቶችን፣ ስሜቶችን ሁሉ፣ አመክንዮና
መረዳት፣ የመሳሰሉትንም፤ ምግብና መጠጥ፣ ልብስ፣ ቀለብ፣ የትዳር ጓደኛና ሠራተኞች፣
ቤትና እርሻ፣ ወዘተ. እንደ ሰጠኝና ያለ ማቋረጥ እንደሚደግፈኝ አምናለሁ፤ አጸናለሁም።
14 ከዚህም ሌላ ፍጥረት ሁሉ ማለትም ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እንዲሁም የሰማይ ከዋክብት፣ ቀንና
ሌሊት፣ አየር፣ እሳት፣ ውሃ፣ ምድርና እርሷ የምትሰጠው እንዲሁም የምታፈራው ሁሉ፣
አዕዋፍ፣ ዓሣ፣ እንስሳት፣ እህል፣ እንዲሁም ሁሉም ዓይነት ፍሬ ለሕይወት የሚጠቅመውንና
15 የሚያስፈልገውን እንደሚሰጠኝ አምናለሁ። በተጨማሪም፣ አካላዊና ምድራዊ በረከቶችን
16 ማለትም መልካም አስተዳደርን፣ ሰላምንና ጸጥታን ይሰጣል። ስለ ሆነም ማናችንም በራሳችን
ሕይወት እንደሌለን እዚህ የተጠቀሰ ወይም ሊጠቀስ የሚችል የቱንም ያህል ትንሽና የማይጠ
ቅም ቢመስል ከእኛ እንዳልሆነ ወይም በራሳችን ኃይል ልንጠብቃቸው እንደማንችል ከዚህ
አንቀጽ እንማራለን። ይህ ሁሉ «ፈጣሪ» በሚለው ቃል የተጠቃለለ ነው።
17 በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ያለንንና በዐይናችን የምናየውን ነገር የሰጠን ብቻ
ሳይሆን ሁሉንም ዓይነት አደጋና ጥፋት በመከላከል፣ በየዕለቱ ከሁሉም ዓይነት ክፋት፣ መከራና
መጥፎ አጋጣሚ ይከላከልልናል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ምንም ክፉ እንዳያጋጥመን የሚጠ
18 ነቀቅልን ቸር አባት በመሆኑ ያለ እኛ በጎ ምግባር በፍቅሩና በመልካምነቱ ብቻ ነው። ነገር ግን
የዚህ ርእሰ ጉዳይ ተጨማሪ ውይይት «ሁሉን የሚችል አብ» በሚለው ሥር በዚህ አንቀጽ
ሌሎች ሁለት ክፍሎች ይቀርባል።
19 ስለዚህ ያለን ነገር ሁሉ፣ እንዲሁም ከዚህ ሌላ በሰማይና በምድር ያለውን ነገር ሁሉ
በየዕለቱ የሚሰጥ፣ የማያቋርጥ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር የሚጠበቅ በመሆኑ፣ በዐሥርቱ
ትእዛዛት እንደጠየቀውና እንዳዘዘው፣ እርሱን እንድንወደው፣ እንድንወድሰው፣ እንዲሁም ያለ
ማቋረጥ እንድናመሰግነው፣ በአጭሩ፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለእርሱ አገልግሎት እንድናውል
በኃላፊነት የታጠርን ነን።
20 እዚህ ላይ አንዳንድ ሰዎች ይህንን አንቀጽ እንዴት እንደሚያምኑ የምንገልጽ ቢሆን ኖሮ
ብዙ ሊባል ይቻል ነበር። ሁላችንም እናልፈዋለን፤ እንሰማዋለን፤ እንደግመዋለንም፤ ነገር ግን
21 ቃላቱ እንድናደርግ ስለሚያዝዙን ነገር ዐናይም ወይም ዐናስብም። ከሙሉ ልባችን ያመንነው
ቢሆን ኖሮ ሕይወት፣ ሀብት፣ ኃይል፣ ክብር፣ የራሳችን የሆኑ ይመስል፣ እኛ ራሳችን
መፈራትና መገልገል የነበረብን ያህል አንጀነንም፤ አንኩራራም፤ ጕራም አንነዛም ነበር። ይህ

ድርጊት የእግዚአብሔርን በረከቶችና ስጦታዎች ሁሉ ለራሱ ትዕቢት፣ ስስት፣ ደስታ፣ እንዲሁም እርካታ ብቻ ያለ አግባብ የሚጠቀመው፣ እንደ ጌታ ወይም ፈጣሪ ሊያመሰግነው ወይም ሊቀበለው ከቶ አንዴም ወደ እግዚአብሔር የማይመለሰው፣ በዕውርነቱ የሰጠመውና የጎሰቋላው፣ የጠማማው ዓለም አደራረግ ነው፡፡

22 ብናምነው ይህ አንቀጽ ሁላችንንም ትሑታን ሊያደርገንና ሊያስፈራን ይገባል፡፡ እኛ በየዕለቱ በዐይኖቻችን፣ በእጆቻችን፣ በሥጋችንና በነፍሳችን፣ በገንዘባችንና በንብረታችን፣ እንዲሁም ባለን ነገር ሁሉ፣ በተለይም የእግዚአብሔርን ቃል ከሚቃወሙት ጋር ኃጢአት እንሠራለን፡፡ ሆኖም ግን ክርስቲያኖች ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ማገልገልና መታዘዝ የሚገባቸው መሆኑን በመቀበላቸው ብልጫ አላቸው፡፡

23 ስለዚህ ምክንያት ይህንን አንቀጽ በየዕለቱ ተግባራዊ ልናደርገው፣ በአእምሮአችን ልንቀርጸው፣ እንዲሁም በምናየው በማንኛውም ነገርና ወደ እኛ በሚመጣ በእያንዳንዱ በረከት ልናስታውሰው ይገባናል፡፡ ከስጋት ወይም ከአደጋ በምናመልጥበት ጊዜ ሁሉ፣ አባታዊ ልቡና ለእኛ ያለው ወሰን የለሽ ፍቅሩ ይሰማንና እናይ ዘንድ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ እንዴት እንደሚሰጥና እንደሚያደርግ ማወቅ ይገባናል፡፡ ስለ ሆነም ልባችን ለእግዚአብሔር ባለን ምስጋናና እነዚህን በረከቶች ሁሉ ለእርሱ ክብርና ምስጋና ለመጠቀም ባለን ፍላጎት ይሞቃል፣ ይቀጣጠላልም፡፡

24 የዚህ አንቀጽ ትርጒም በአጭሩ እንደዚህ ያለ ነው፡፡ እርሱም እኛ ስላለንና ከእግዚአብሔር ስለምንቀበለው እንዲሁም በምላሹ ለእርሱ ስላለብን ነገር በመጀመሪያ አብዛኛው ሰዎች መማር የሚያስፈልጋቸው ነው፡፡ ይህ ከፍ ያለ ቁም ነገር ዕውቀት፣ ከዚህም እንኳ ከፍ ያለ መዝገብ ነው፡፡ እዚህ ላይ እንደምንሰማው፣ አብ በልጁና በመንፈስ ቅዱስ በኩል በማይገለጹ ዘላለማዊ በረከቶች እኛን ካረሰረሰበት እውነት ሌላ፣ ከፍጥረት ሁሉ ጋር ራሱን እንዴት እንደ ሰጠን፣ በዚህ ሕይወትም የሚያስፈልገንን አትረፍርፎ እንዳቀረበልን እንመለከታለን፡፡

*ሁለተኛው አንቀጽ*

25 እኔ በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሲኦል በወረደ፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን በተነሣ፣ ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡»

26 ከዚህ ቀጥሎ ስለ ሁለተኛው የሥላሴ አካል በማጥናት ከእርሱ ስለ ተቀበልናቸው ስጦታዎች ማለትም እላይ ከተጠቀሱት ምድራዊ ነገሮች ሁሉ በላይ ራሱንም ጭምር ሳይቈጥብ እንደ ሰጠን እናጠናለን፡፡ ይህ አሁን የምናጠናው የእምነት መግለጫ አንቀጽ አድማሱ የሰፋና የበለጸገ ቢሆንም እንዴት እንደ ዳንን ልጆች ይማሩት ዘንድ በአንዱ ሐረግ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ትኵረት በማድረግ ምን እንደሚያስተምር እናጠናለን፡፡ ሁሉም ሰው የዚህን አንቀጽ ዋና ነገር ይማር ዘንድ «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» በሚሉት ቃላት ላይ እናተኵራለን፡፡

27 እንግዲህ ማንም ሰው «በሁለተኛው የእምነት መግለጫ አንቀጽ መሠረት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምታምነው ምንድን ነው?» ብሎ ቢጠይቅህ መልሱ በአጭሩ «እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ጌታዬ እንደ ሆነ አምናለሁ» ይሆናል፡፡ «ጌታ መሆን ማለትስ ምንድን ነው?» ተብሎ ለሚጠየቀውም ጥያቄ ምላሹ እርሱ «ከኃጢአትና ከሰይጣን፣ ከሞት፣ ከክፉ ነገርም ሁሉ አዳነኝ ማለት ነው፡፡ እርሱ እስከሚያድነኝ ድረስ በዲያብሎስ፣ በኃጢአትና በዕውርነት የተማረክሁና ሞት የተፈረደብኝ ከመሆኔም በላይ የሚያድነኝ ጌታ አልነበረኝም» የሚል መሆን አለበት፡፡

28 በእግዚአብሔር አብ ከተፈጠርንና መልካምን ነገር ሁሉ ከእርሱ ከተቀበልን በኋላ ዲያብሎስ ወደ አለመታዘዝ፣ ወደ ኃጢአት፣ ወደ ሞት፣ ወደ መከራም ሁሉ መራን፡፡ በውጤቱም ከእግዚአብሔር ቍጣ በታች የወደቅን፣ ፊቱም የከበደብንና የዘላለም ኵነኔ
29 የተፈረደብን ስንሆን ከምግባራችን አንጻር የሚገባን ይኸው ነበር፡፡ አንድያና ዘለዓለማዊው

የእግዚአብሔር ልጅ ወሰን ከሌለው ርኅራኄው የተነሣ በመከራችን ሊረዳን፣ ከጕስቍልናችን
ሊያድነንና ከጨካኞች እጅ ሊታደገን ከሰማይ እስኪወርድ ድረስም ያለ ምክር፣ ያለ ረዳት፣ ያለ
30 አጽናኝ ቀርተን ነበር። አሁን ግን እነዚህ ጨካኞችና አሳሪዎች ተነቅለው ስፍራውን ስለ ለቀቁ
የእነርሱ ሥልጣን የሕይወት ጌታ፣ ጻድቅና የመልካም ነገር ሁሉ ባለቤት በሆነው በኢየሱስ
ክርስቶስ ተነጥቆአል። እርሱም እኛን የጠፉን ምስኪኖችን ከገሃነም መንጋጋ ነጥቆ ነጻ አወጣን፤
ወደ አብም ሞገስና ጸጋ መለሰን። በጽድቁ፣ በጥበቡ፣ በኃይሉና በበረከቱ ሊመራን ገንዘቡ
አድርጎ ይከልለናል፤ በጥበቃውም ሥር ያኖረናል።
31 ስለዚህ የዚህ እምነት መግለጫ አንቀጽ አጠቃላይ ትምህርት «ጌታ» ማለትም አዳኝ
ሲሆን እርሱም ከዲያብሎስ ወደ እግዚአብሔር፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ
የመለሰን አሁንም የሚጠብቀን አዳኝ ነው የሚል ነው። የተቀረው የዚህ የእምነት መግለጫ
አንቀጽ መዳናችን እንዴትና በማን እንደ ተፈጸመ፣ ክርስቶስን ምን ያህል ውድ ዋጋ
እንዳስከፈለው፣ እኛንም ወደ መንግሥቱ ለማስገባት እንዴት ያለ መከራ እንደ ተቀበለ
ያስረዳል። ይኸውም ክርስቶስ ኃጢአትን እንዲያሸንፍ የሰውን ሥጋ ለብሶ በመንፈስ ቅዱስ
በመፀነስና ከድንግል ማርያም በመወለድ፣ እኔ ስላጠፋሁት ጥፋት የሚገባኝን የኃጢአት ዕዳ
በመክፈል፣ ለእኔም የሚገባኝን መከራ ለመቀበል በመሞትና በመቀበር አዳነኝ እንጂ በብርና
በወርቅ አልገዛኝም ማለት ነው። ይህንንም ሁሉ ያደረገው ጌታዬ እንዲሆን ነው። እነዚህንም
ሲያደርግ ለራሱ ሲል ወይም ስላስፈለጉት አልነበረም። እነዚህ ሁሉ ካደረገ በኋላ ሞትን ድል
አድርጎና ሽሮ[134] ከሞት በመነሣት በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ ሁሉን ይገዛል።
በመጨረሻም በዳግም ምጽአቱ ከክፉ ዓለም፣ ከዲያብሎስ፣ ከሞትና ከኃጢአት ፈጽሞ
እስኪያሳርፈን ድረስ ዲያብሎስና ተከታዮቹ ኃይላት ከእግሩ በታች ሊገዙ ይገባቸዋል።
32 ነገር ግን ይህን ሁሉ መግለጽ ለልጆች በሚቀርበው አጭር ስብከት[135] ሳይሆን ረዘም ላሉ
በተለይ በዓመት ውስጥ በተወሰኑ[136] ወቅቶች ማለትም በልደት፣ በሕማማቱ፣ በትንሣኤና
33 በዕርገት ወቅቶች ማቅረብ ተገቢ ይሆናል። የምንሰብከው ወንጌል በመላ ይህንን የእምነት
መግለጫ አንቀጽ በትክክለኛ መንገድ በመረዳት ላይ ይመረኮዛል። ምክንያቱም ድነታችንና
በረከታችን የተመሠረተው በዚህ ላይ ስለሆነና ስለ እርሱም ተምረን እስከማንጨርሰው ድረስ
የበለፀገና ሰፊ ስለ ሆነ ነው።

*ሦስተኛው አንቀጽ*

34 እኔ በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን አንድነት፣[137]
በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣ በዘለዓለም ሕይወት አምናለሁ።
35 ለዚህ አንቀጽ ቀደም ሲል እንዳልኩት «መቀደስ» ከሚለው የተሻለ ርእስ ልሰጠው
አልችልም። በዚህም ርእስ መንፈስ ቅዱስና እኛን ቅዱሳን የማድረግ ሥራዎቹ ተብራርተው
ተገልጸዋል። ስለዚህ ሌላ መተኪያ እስከማይገኝለት ድረስ ትክክለኛ መገለጫ ወይም መጠሪያ
36 ቃል ስለ ሆነ *መንፈስ ቅዱስ* በሚለው ሐረግ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን። በእግዚአብሔር
ቃል ሌሎች ዓይነት መናፍስት ተጠቅሰዋል። እነርሱም የሰው መንፈስ[138] ሰማያዊ መናፍስትና[139]
ክፉው መንፈስ[140] ናቸው። ነገር ግን የቀደሰንና አሁንም የሚቀድሰን የእግዚአብሔር መንፈስ
ብቻ ስለ ሆነ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል። አብ ፈጣሪ፣ ወልድ አዳኝ ተብለው
እንደሚጠሩ ሁሉ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ መንፈስ ቅዱስ ቀዳሽ ወይም የሚቀድሰን ተብሎ
37 ይጠራል። ይህ መቀደስ እንዴት ይከናወናል? መልስ፦ ወልድ በልደቱ፣ በሞቱና በትንሣኤው

---

[134] ኢሳ 25፡7 ተመልከት።
[135] ይህ በሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ ለልጆችና ለአገልጋዮች የሚቀርብ ስብከት ነው።
[136] ልደት፣ ዐቢይ ጾም፣ ፋሲካ፣ ዕርገትና ልዩ ልዩ በዓላት ስለ ክርስቶስ ሕይወት የሚናገሩ የወንጌል ክፍሎች የሚነበቡባቸው ጊዜያት ናቸው።
[137] በጀርመንኛ ቃሉ "Gemeine" ሲሆን እላይ በገጽ 384 "Gemeinschaft" የሚለውን ቃል ተመልከት።
[138] ለምሳሌ 1ቆሮ 2፡11።
[139] ሉተር እነዚህን እንደ መልካም መላእክት ተርጕሞአቸዋል። ለምሳሌ 2 መቃቢያን 11፡ 6፤ 15፡ 23።
[140] ለምሳሌ 1ሳሙ 16፡14 እና 23፤ ጦቢት 3፡8፤ ሐዋ 19፡12 እና 15።

ሁላችንን እንደ ገዛን መንፈስ ቅዱስም መቀደሳችንን በቅዱሳን አንድነት፣[141] በኃጢአት ስርየት፣
በሥጋ ትንሣኤ፣ በዘለዓለም ሕይወት እውን ያደርገዋል፡፡ ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ
መጀመሪያ ለእኛ ወንጌልን ወደሚሰብክበትና ወደ ክርስቶስ ወደሚያመጣበት የራሱ ወደ ሆነው
ኅብረት ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን እቅፍ ያመጣናል ማለት ነው፡፡
38 በመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ካልተሰበከልንና የክርስቶስም ሥራ ለልባችን[142] ካልተገለጠልን
እኔም ሆንኩ አንተ ክርስቶስን ለማወቅና በእርሱም ለማመን እንዲሁም ለእርሱ ለመገዛት ከቶ
አይቻለንም፡፡ ሥራው ተጠናቅቆአል፤ ተፈጽሞአልም፡፡ ክርስቶስ በሥቃዩ፣ በሞቱና በትንሣኤው
የመዳናችንን ሥራ ፈጽሞአል፡፡ ነገር ግን ይህ የእርሱ ሥራ ማንም እንደማያውቀው ሆኖ ቢሰወር
ኖሮ ሁሉም ከንቱ ሆኖ በቀረ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ትልቅ ስጦታ ተቀብሮ እንዳይቀር
እግዚአብሔር ቃሉ እንዲታተምና እንዲታወጅ በማድረግ እንዲሁም በቃሉ ይህንን የድነት
39 ስጦታ የሚያቀርብልንና የሚያስገነዝበንን መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፡፡ ስለዚህ መቀደስ ማለት
ይህንን በረከት ለመቀበል በራሳችን ወደዚህ መቀደስ መምጣት የማንችለውን እኛን ወደ ጌታ
ክርስቶስ ከማምጣት በስተቀር ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡
40 እንግዲህ ይህንን የእምነት መግለጫ ክፍል የምትችለውን ያህል በግልጽ አጥናው፡፡ አንድ
ሰውም «'በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ' ስትል ምን ማለትህ ነው?» ብሎ ቢጠይቅህ «መንፈስ ቅዱስ
41 ስሙ እንደሚገልጸው እንደሚቀድሰኝ አምናለሁ» ብለህ መመለስ ትችላለህ፡፡ «መንፈስ ቅዱስ
ይህንን እንዴት አድርጎ ይፈጽመዋል? መሣሪያውስ ምንድን ነው»? ተብለህ ብትጠየቅ መልስህ፡-
«በቤተ ክርስቲያን በኩል፣ በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤና በዘለዓለም ሕይወት ይህን
42 ይፈጽምልኛል» የሚል መሆን አለበት፡፡ በመጀመሪያ የሰዎች ልብ እንዲበራና እንዲቀጣጠል፣
ቃሉንም እንዲረዱትና አጥብቀው እንዲይዙት፣ እንዲጠብቁትም ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ
ቃሉን የሚገልጽባትና የሚያውጅባት በዓለም ላይ ልዩ ማኅበረሰብና[143] የምእመናን እናት
ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጋር የጠበቀ አንድነት አለው፡፡
43 ከዚህ በፊት እምነት ፈጽሞ በጠፋበት በጳጳሳዊው ሥርዓት እንደ ተደረገው የክርስቶስ
ጌትነትና የመንፈስ ቅዱስ ቀዳሽነት እንዲሰበክና የሰው ልብ ለመረዳት እንዲነቃቃ መንፈስ
ቅዱስ በማያደርግበት ቦታ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት ክርስቶስ ያለ እኛ በጎ ሥራና
ምግባር ብፅዕናን ያስገኘልንና እግዚአብሔር አብ እንዲቀበለን ያደረገ ጌታ መሆኑን ማንም
44 አያምንም ማለት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ምን ይጎድላል? እውነትን የሚገልጽ፣ የሚሰብክና
የሚያውጅ መንፈስ ቅዱስ ይጎድላል ማለት ነው፡፡ ይልቁንም በሥራችን ጸጋን እንደምናገኝና
እንደምንድን ያስተማሩን ሰዎችና ክፉ መናፍስት አሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን
ልትኖር አትችልም፡፡ ይህ የሚሆነው ክርስቶስ በማይሰበክበት ቦታ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠራ፣
45 የሚመሠርት፣ የሚመራና የሚሰበስብ መንፈስ ቅዱስ ስለሌለ ነው፡፡ ስለዚህ የእምነት መግለጫ
46 ይዘት እስከ አሁን የተባለው ይብቃ፡፡ ነገር ግን በክፍሉ የተዘረዘሩት አንዳንድ ዐሳቦች ለሁሉም
ሰው ግልጽ ሊሆኑ ስለማይችሉ በአጭሩ ማብራራት ያስፈልገናል፡፡
47 የእምነት መግለጫው ቤተ ክርስቲያንን (communio sanctorum)*[144]* *የቅዱሳን አንድነት*[145]
ብሎ ይጠራታል፡፡ የሁለቱም አባባሎች ትርጉም ተመሳሳይ ነው፡፡ የእምነት መግለጫው ወደ
ጀርመንኛ ቋንቋ በተተረጎመበት ጊዜ አባባሉ ከተለመደው ውጭና ለመረዳት የሚያስቸግር ሆኖ
በመገኘቱ ሥራው ሲጀመር ይህ ሐረግ አልተካተተበትም[146] ነበር፡፡ ይህንን አባባል በሚገባ
እንተርጒመው ካልን በጀርመንኛ ለዚህ ሐረግ ለየት ያለ ቃል መጠቀም ይኖርብናል፡፡
«ኤክሌሺያ» (*ecclesia*) የሚለው ቃል በጀርመንኛ ትክክለኛ ትርጒሙ ጉባኤ[147] ማለት ነው፡፡

---

[141] በጀርመንኛ፡- *Gemeine.*
[142] ቃል በቃል «ልብ» ማለት ነው፡፡
[143] በጀርመንኛ፡- *Gemeine.*
[144] በላቲን ቋንቋ የተጻፈ ነው፡፡
[145] በጀርመንኛ፡- *Gemeinschaft.*
[146] *የቅዱሳን ኅብረት* የሚለው ሐረግ በእምነት መግለጫው ላይ የተጨመረው በኋላ ላይ መሆኑን ሉተር ገና በ1519 አመልክቶአል፡፡ የቃሉም ትርጒም «የሁሉም የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን» እንደ ማለት ነው፡፡ ይህንን ሐረግ የያዘው የእምነት መግለጫ የመጀመሪያው ጽሑፍ የሬሜሲያናው ጳጳስ የኒሴታስ እንደ ሆነ ይታመናል፡፡
[147] በጀርመንኛ፡- *Versammlunge* ነው፡፡ በቆየውና በከፍተኛ መደብ በሚነገረው ጀርመንኛ የላቲኑ ቃል ኤክሌሺያ *kirihha* እና *samanunga* ተብሎ ይተረጎም ነበር፡፡ ነገር ግን በመካከለኛው ከፍተኛ መደብ ጀርመንኛ *kirche* ብቻ ተብሎ ይነገራል፡፡

48 ነገር ግን በጀርመንኛ በተለምዶ የሚጠቀሙበት ቃል «ኪርኬ» (*Kirche*) ሲሆን ይህንንም ቃል
ማንኛውም ሰው የሚረዳው ለአንድ ለተለየ ዓላማ የተለየ ቤት ወይም ሕንጻ አድርጎ እንጂ
ለሰዎች ስብስብ አይደለም። ይህ ቤት ግን ሰዎች በዓላማ እየመጡ የሚሰበሰቡበት ባይሆን ቤተ
ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ አይችልም። ምክንያቱም ቤቱ ይህንን ስያሜ ሊያገኝ የሚችለው በዚያ
ስፍራ ከተሰበሰቡትና የተለየ ዓላማ ካላቸው ሰዎች የተነሣ ነው። ስለዚህ «ቤተ ክርስቲያን»[148]
የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ ከጀርመን ቋንቋ በተገኘው ቃል ሳይሆን የሰዎች የጋራ
ስብስብ *ኤክሌዥያ* (*ecclesia*) እንደሚለው የግሪኩ ቃል ነው። በዚያ ቋንቋ ቃሉ *ኪሪያ* (*kyria*)
ሲሆን በላቲን *ኩሪያ* (*curia*) ነው።[149] ስለዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋችን በሆነው ትክክለኛው
ጀርመንኛ «የክርስቲያኖች ማኅበረሰብ ወይም ስብስብ»[150] ሲሆን ከሁሉ የተሻለና ግልጽ የሆነው
ሐረግ ደግሞ «ቅዱስ ክርስቲያን ሕዝብ» የሚል ይሆናል።[151]
49 በተመሳሳይ ሁኔታ *ኮሚኒዮ* (*communio*) የሚለውና አብሮ የተያያዘው ቃል «ቊርባን»
ተብሎ ሳይሆን «ማኅበረ ሰብ»[152] በሚል ሊተረጎም ይገባዋል። ይህም ቤተ ክርስቲያን የሚለውን
ዐሳብ ለመተርጎምና ለማብራራት የሚጠቅም ነው። ነገር ግን ማንም ጀርመናዊ በዚህ መልኩ
ባይናገረውና ባይረዳውም ላቲንና ጀርመንኛን የማይረዱ አማኞች «የቅዱሳን ኅብረት»[153] ብለው
ይተረጕሙታል። ትክክለኛውን ጀርመንኛ እንጠቀም ካልን ማለት ያለብን «የቅዱሳን ማኅበረ
ሰብ»[154] ነው። ይህም ማለት በቅዱሳን ብቻ የተዋቀረ ማኅበረሰብ ወይም በይበልጥ ግልጽ በሆነ
50 አባባል «ቅዱስ ማኅበረ ሰብ»[155] ማለት ነው። ይህን የምለው ሰዎች ቃሉን በሚገባ እንዲረዱት፣
በአጠቃቀም ጊዜ የጸና መሠረት ከመያዙ የተነሣ የማይነቀል እንዲሆንና ቃሉን መለወጥ
ከመናፍቃን የማይተናነስ ስሕተት መፈጸም እንደ ሆነ ለማስገንዘብ ነው።
51 እንግዲህ የዚህ ሐረግ ትርጕምና ዋና ዐሳብ ይህ ነው። እርሱም፦ «እኔ ክርስቶስ ራስ
የሆነላት ትንሽ ቅዱስ መንጋ እና የቅዱሳን ኅብረት በምድር ላይ እንዳለች አምናለሁ» የሚል
ነው። ይህም ኅብረት የተጠራው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ አንድ እምነት፣ ዐሳብና
መረዳት ነው። እርሱም በውስጡ የተለያዩ ስጦታዎችን የያዘ ሲሆን ባለመለያየትና ባለመከፋፈል
52 እንዲሁም በመዋደድ የሚሆን ኅብረት ነው። እኔም የዚህ ማኅበረሰብ አካልና አባል ስሆን
በውስጡ ያሉት በረከቶች ሁሉ አካልና ተካፋይ[156] ነኝ። ወደዚህ ኅብረት የመጣሁትና
የተዋሃድሁት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሲሆን ይህም የሆነው የመግቢያው መነሻ ነጥብ
የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቴና አሁንም ቢሆን በመስማት ላይ በመሆኔ ነው።
ወደዚህ ኅብረት ከመምጣታችን በፊት ግን ሁለንተናችን የሰይጣን የሆነና ስለ ክርስቶስም ስለ
53 እግዚአብሔርም አንዳችም የማናውቅ ነበርን። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ እስከ ዳግም ምጽአት
ድረስ ከቅዱሳን ኅብረት[157] ወይም ከክርስቲያኖች ጋር አብሮ ይቆያል። በዚህም ኅብረት
አማካይነት ይሰበስበናል፤ ቃሉን ለማስተማርና ለመስበክ በኅብረቱ ይጠቀማል። በዚህም ኅብረት
ቅድስናን የሚፈጥርና የሚጨምር ሲሆን ይህም በየዕለቱ እንዲያድግ፣ በእምነት እንዲጠነክርና
የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንዲያፈራ ያደርጋል ማለት ነው።

---

[148] ጀርመንኛ፦ *kirche .*

[149] ሉተር *curia* የሚለውን የላቲን ቃል *kuria* ከሚለው የግሪክ ቃል ጋር በስሕተት ቢያዛምደውም የዘመናዊው ቋንቋ ጥናት እንደሚያሳየው *kirche የሚለው የጀርመን ቃል Kuriakos* ከሚለው የግሪኩ ቃል የመጣ ሲሆን («የጌታ መሆን») ማለት ነው። ይኸው ቃል ጥንታውያን ከሆኑና ወደ ሌላ ቋንቋ ከተወሰዱት ቃላት አንዱ ሆኖ በአርዮሳዊ ሚስዮናውያን አማካይነት ከጎቶች ግዛት በዳንዩብ ወንዝ በኩል ወደ ጀርመን የመጣ ቃል ነው።

[150] በጀርመንኛ፦ *Gemeine* ሲሆን ሉተር ራሱ በተረጎመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም ያለ ምንም መዛባት *ecclesia* ለሚለው የግሪኩ ቃል *Gemeine*ን ተጠቅሞበታል።

[151] በጀርመንኛ፦ *Ein heilige christenheit* ሲሆን በOn *the Councils and the Church* (1539) ሉተር የጀርመንኛ ቃል ያልሆነውና ትርጉም የሌለው *kirche christenheit* «ክርስትና» ወይም *christiches volk* «ክርስቲያን ሕዝብ» በሚለው ቃል እንዲተካ ምክር ሰጥቶ ነበር (WA 50: 624, 14-20; *LW* 41:
143-44)።

[152] *Gemeinschaft* ሳይሆን *Gemeine* ነው።.

[153] በጀርመንኛ፦ *Gemeinschaft der Heiligen*

[154] በጀርመንኛ፦ *ein Gemeine der Heiligen.*

[155] በጀርመንኛ፦ *ein heilige Gemeine.*

[156] 1ቆሮ 1፡9 ይመልከቱ። ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጕም «እናንተ የክርስቶስ በረከቶች ሁሉ ወራሾችና ተካፋዮች ናችሁ።» የሚል የግርጌ ማስታወሻ በጽሑፉ ላይ አኑሯል።

[157] በጀርመንኛ፣ *Gemeine.*

54 በተጨማሪም በቅዱሳን ኅብረት በቅዱሳት ምሥጢራት፣ በንስሐ በሚሆን የኃጢአት ስርየትና በሚያጽናኑ የወንጌል ቃላት አማካይነት የኃጢአት ይቅርታ እንዳለን እናምናለን፡፡ ይህ ስለ ኃጢአት ይቅርታ የሚሰጠው ትምህርት ወይም ስብከት ቅዱሳት ምሥጢራትን፣ ወንጌልንና የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ኃላፊነት የሚያጠቃልል ነው፡፡ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ በኩል የተገኘና ቅድስና በቅዱሳን ኅብረት ወይም በቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራ ቢሆንም እኛ ፍጹም ከኃጢአት የጸዳን ስላልሆንን የኃጢአት ይቅርታ ያለ ማቋረጥ ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም አሮጌውን ሥጋችንን ተሸክመን ስለምንዞር ነው፡፡

55 ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን የሚደረጉ አገልግሎቶች ሁሉ በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ በቃሉና በተአምራቱ[158] አማካይነት በየዕለቱ ፍጹም የኃጢአት ይቅርታ እንድንቀበል የታዘዙ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ኃጢአት ቢኖርብን የኃጢአት ስርየት ባለበት በክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ውስጥ ስላለን መንፈስ ቅዱስ ኃጢአት እንዳይገዛን ይረዳናል፡፡ እዚህ ላይ ሙሉ የኃጢአት ይቅርታ አለ፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፡፡ እንዲሁም እኛም ይቅር እየተባባልን እርስ በርሳችን እንቻቻላለን፤ እንረዳዳለንም፡፡

56 ከክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ውጭ የኃጢአት ስርየት ስለሌለ ቅድስናም የለም፡፡ ስለዚህ ወንጌልና የኃጢአት ስርየት ሳይኖራቸው በሥራቸው ቅዱሳን ሊሆኑ የሚፈልጉ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን የለዩ ናቸው፡፡

57 ይህ በእንዲህ እንዳለ ቅድስና ስለ ተጀመረና ስለሚያድግም ሥጋችን ከነርኩሰቱ
የሚሞትበትንና የሚቀበርበትን እንዲሁም ለፍጹም ቅድስና በክብር የሚነሣበትን ዐዲስና
58 ዘለዓለማዊ ሕይወት እንጠባበቃለን፡፡ ይሁን እንጂ ግማሽ ንጹሐንና ቅዱሳን ሆነን ብቻ ነው
የምንቆየው፡፡ ስለዚህ የኃጢአት ይቅርታ ወደማያስፈልገን ሕይወት እስክንደርስ ድረስ መንፈስ
ቅዱስ ይቅርታን እየሰጠን በቃሉ በውስጣችን መሥራት አለበት፡፡ በዚያኛው ሕይወት ንጹሕና
ፍጹም፣ ጽድቅና ስምምነት የሞላበት፣ ከኃጢአት፣ ከሞትና ከማንኛውም መከራ ነጻ የሆነ፣
ዐዲስ፣ የማይሞትና የከበረ አካል ይኖራል፡፡

59 በዚህ ምድር ላይ በእነዚህ ሁለቱ መሣሪያዎች ማለትም በቤተ ክርስቲያንና በኃጢአት ስርየት ቅድስናችንን መጀመርና መጨመር የመንፈስ ቅዱስ ሥራና አገልግሎት ነው፡፡ ከዚህም ምድራዊ ሕይወት ስናልፍ በቅጽበተ ዓይን ቅድስናችን ይፈጸምና በሁለቱ የዚህ አንቀጽ መጨረሻ ክፍሎች አማካይነት ይጠብቀናል፡፡

60 «የሥጋ ትንሣኤ»[159] የሚለው ሐረግ በጥሩ ጀርመንኛ ትክክለኛ መልእክት የሚያስተላልፍ አይደለም፡፡ ፍሌሽ *(Fleish)*[160] የሚለውን ቃል ስንሰማ ቶሎ የሚመጣልን ከልኳንዳ ቤት ሥጋ ሌላ አይታሰብም፡፡ በትክክለኛው ጀርመንኛ ማለት ያለብን «የትንሣኤ አካል» ነው፡፡[161] ይሁን እንጂ፣ ቃሎቹ በሚገባ እስከ ገቡን ድረስ ይህ እጅግም አስፈላጊ አይደለም፡፡

61 ይህ የእምነት መግለጫ ሁልጊዜ በጉባኤያችን ሕያው ወይም ተግባራዊ ሆኖ መቀጠል አለበት፡፡ አሁን የፍጥረተ ዓለም ሥራ ያለፈ ሲሆን የድነት ሥራም ተፈጽሞአል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግን እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ያለ ማቋረጥ ሥራውን ይሠራል፡፡ ለዚህም ዓላማ የሚናገርባትና ሥራውን የሚፈጽምባትን ማኅበሩን[162] በምድር ላይ አቋቁሞአል፡፡ ይህም ገና ቤተ

---

[158] ቅዱሳት ምስጢራቱ ናቸው፡፡

[159] በጀርመንኛ *Auferstehung des Fleisches* ነው፡፡

[160] *Fleisch* የሚለው የጀርመንኛ ቃል ሥጋ ማለት ነው፡፡

[161] በጀርመንኛ *Auferstehung des Leibs oder Leichnams* ቃል በቃል ሲተረጎም የሥጋ ትንሣኤ ወይም የሬሳ መነሣት ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በሥጋ ትንሣኤ ቢያምኑም ቍሳዊ ነገር ሁሉ ክፉ ነው በማለት የነፍስና የሥጋን መዳን የሚክዱ አንዳንድ ቡድኖች በቤተ ክርስቲያን ተነሥተው ነበር፡፡ «የሥጋ ትንሣኤ» የሚለውም ቃል በእምነት መግለጫ የተካተተው ይህንን አመለካካት ለመቃወም ነበር፡፡ ሰውን ሥጋ ነው ብሎ የሚጠራው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ሥጋ ማለት ሁለንተናዊ ሰብአዊነት፣ አካልና ነፍስ ነው በማለት ሉተር በዮሐ 1፡14 ማብራሪያ ላይ የጻፈውን (WA 10/1, 1: 235, 18-21; *LW* 52: 80-81) ተመልከት፡፡ በእምነት መግለጫው «በሥጋ ወይም በሁሉም ሰው ትንሣኤ አምናለሁ» በምንልበት ቦታ እስከ 1543 ድረስ የቀድሞው የእንግሊዝኛው የሐዋርያት የእምነት መግለጫ «የሥጋ ትንሣኤ» ይል ነበር፡፡ ነገር ግን ሄነሪ 8ኛ «ማንኛውም ክርስቲያን በማጥናት ማግኘት ያለበት አስፈላጊ አስተምህሮ» በማለት «የአካል ትንሣኤ» የሚል ሐረግ ለሕዝብ እንዲታወቅ ትእዛዝ አወጣ፡፡

[162] በጀርመንኛ *Gemeine* ነው፡፡

*ክርስቲያንን አጠናቆ ያልሰበሰበና የኃጢአት ይቅርታ መስጠቱንም ያላጠናቀቀ በመሆኑ ነው።*
62 *ስለዚህ በየዕለቱ ወደ ማኅበረ ሰቡ በቃሉ እያስጠጋን በዚሁ ቃልና በኃጢአት ስርየት እምነትን*
*በሚሰጠን፣ በሚጨምርልንና በሚያጠነክርልን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። ሥራው በተፈጸመና*
*እኛም ለዚህ ዓለምና ለማይገቡ ነገሮች ሞተን በእርሱ በኖርን ጊዜ ለዘለዓለም ፍጹማንና ቅዱሳን*
*ያደርገናል። ይህም በቃሉ አማካይነት እንዲፈጽም በእምነት እንጠባበቃለን።*
63 *በዚህ የእምነት መግለጫ የእግዚአብሔር ማንነት፣ ፈቃድና ሥራ እንዳለ አጠር ብለው*
*ነገር ግን በእውነት በበለጸጉ ቃላት ተጽፈዋል። በእነርሱም ከሰው ጥበብ፣ መረዳትና የማመዛዘን*
*ችሎታ በላይ የሆኑ ጥበቦች ተካተውባቸዋል። ምንም እንኳ ዓለም በመላ እግዚአብሔር ማን*
*እንደ ሆነ፣ ምን እንደሚያስብና እንደሚሠራ ለማወቅ ቢጥርም ይህ ከቶ አልተሳካለትም። በዚህ*
64 *ክፍል ግን ይህንን ዕውቀት ተትረፍርፎ ታገኘዋለህ። በእነዚህ በሦስቱ የእምነት መግለጫ*
*አንቀጾች እግዚአብሔር ራሱ አባታዊ የሆነውን ልቡን፣ እጅግ ጥልቅና በሰው ቋንቋ ሊነገር*
*የማይቻለውን ፍቅሩን ገልጾልናል። እርሱ ሊያድነንና ሊቀድሰን ፈጥሮናል። በተጨማሪም*
*በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ለእኛ ከመስጠቱም በላይ እኛን ወደ ራሱ የሚያስጠጋቸውን*
65 *ልጁንና ቅዱስ መንፈሱን ሰጥቶናል። ከፍ ሲል እንዳብራራነው የአብን ርኅራኄና ጸጋ የልቡ*
*ነጸብራቅ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በስተቀር በራሳችን ልናውቀው*
*አይቻለንም። ከእርሱ ውጭ ቊጡና ፈራጅ ዳኛ እንጂ ሌላ ልናይ አንችልም። እንደዚሁም*
*መንፈስ ቅዱስ ካልገለጠልን ስለ ክርስቶስ አንዳችም ነገር ልናውቅ አንችልም።*
66 *ስለዚህ እነዚህ ሦስቱ የእምነት አንቀጾች እኛን ክርስቲያኖችን በዓለም ላይ ካሉ ሕዝቦች*
*ሁሉ የተለየን ያደርጉናል። ከሕዝበ ክርስቲያኑ ውጭ ያሉ ሁሉ አረማውያን ሆኑ ቱርኮች፣*
*አይሁዶች ወይም ሐሰተኞች ክርስቲያኖችና ግብዞች ምንም እንኳ አንዱንና እውነተኛውን*
*እግዚአብሔርን ቢያምኑና ቢያመልኩም እርሱ ስለ እነርሱ ያለውን ዐሳብ አያውቁም። በፍቅሩና*
*በባርኮቱ ላይ እምነት በማጣታቸውም በዘለዓለም ቊጣና እርግማን ሥር ናቸው። ጌታ ኢየሱስ*
*ክርስቶስ ስለሌላቸው በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ያልበራላቸውና በስጦታው ያልተባረኩ ናቸው።*
67 *እንግዲህ የእምነት መግለጫው ይዘት ከዐሥርቱ ትእዛዛት በእጅጉ የተለየ መሆኑን*
*ትመለከታለህ። ዐሥርቱ ትእዛዛት ምን ማድረግ እንዳለብን የሚያስተምሩን ሲሆን የእምነት*
*መግለጫው ግን እግዚአብሔር ምን እንደ ሠራልንና እንደ ሰጠን ይነግረናል። በተጨማሪም*
*ዐሥርቱ ትእዛዛት በሁሉም ሰዎች ልብ*[163] *ተጽፈዋል። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት*
*ብቻ ካልሆነ ማንኛውም የሰው ጥበብ የእምነታችንን መግለጫ በራሱ ሊገነዘበው አይችልም።*
68 *ስለዚህ እግዚአብሔር በትእዛዛቱ መሠረት የሚጠይቀንን ነገር ማሟላት ባለመቻላችን*
*የእግዚአብሔር ቊጣና መርገም በእኛ ላይ ስለሆኑ ዐሥርቱ ትእዛዛት እኛን ክርስቲያኖች*
*ማድረግ አይቻላቸውም። ነገር ግን የእምነት መግለጫው ንጹሑን የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ እኛ*
*በማምጣት እኛ እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኝ፣ በእርሱም ዘንድ ተቀባይነት ያገኘን ጻድቃን*
69 *ያደርገናል። በዚህም ዕውቀት አማካይነት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መውደድና በእነርሱም*
*ሐሤት ማድረግ ይሆንልናል። በእምነት መግለጫው እንደ ተብራራው እግዚአብሔር ራሱን*
*ከስጦታዎቹና ከኃይሉ ጋር በሙላት ለእኛ መስጠቱ ዐሥርቱን ትእዛዛት እንድንፈጽም*
*ይረዳናል። አብ ፍጥረተ ዓለምን ሁሉ፣ ወልድ መዳንን፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ስጦታዎቹን ሁሉ*
*ሰጥቶናል።*
70 *ብዙ ጫና ሳይደረግባቸው ሰዎች ትክክለኛ የእምነት መሠረት እንዲኖራቸው*
*ለማስተማር እንዲቻል ስለ እምነት መግለጫው እስከ አሁን የተባለው በቂ ነው። ሰዎች*
*የእምነት መግለጫን ዋና ዐሳብ ከተረዱ በኋላ በራሳቸው ተነሣሽነት የበለጠውን ክፍል ይማራሉ።*
*በቅዱሳት መጻሕፍት የተማሩትን ሁሉ ከእነዚህ አስተምህሮዎች ጋር በማነጻጸርና በመረዳትም*
*ቀጣይ እድገት ይኖራቸዋል። ምክንያቱም በሕይወት እስካለን ድረስ ስለ እምነት የምንሰብከውና*
*የምንማረው በቂ የሆነ ነገር በእምነት መግለጫው እናገኛለን።*

---

[163] *ሮሜ 2፡15ን ተመልከት። ይህ ሉተር ስለ ተፈጥሮ ሕግና ስለ ማኅበረ ሰብ ጽድቅ የነበረውን ዕንስ ዐሳብ ያንጸባርቃል።*

## ክፍል ሦስት፡- የጌታ ጸሎት

1 እስከ አሁን ምን ማድረግና ማመን እንዳለብን ሰምተናል። ከሁሉ የሚበልጠውና
የተባረከው ሕይወትም እስከ አሁን የሰማናቸውን እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።
2 ከዚህ ቀጥሎ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን የሚያሳየን ሦስተኛው ክፍል ይከተላል። ማንም ሰው
በጌታ ማመን ቢጀምርም ዐሥርቱን ትእዛዛት ሙሉ በሙሉ መጠበቅ በማይችልበት ሁኔታ
ውስጥ ነን። በተጨማሪም ዲያብሎስ ከሥጋችንና ከዓለም ጋር ሆኖ ዐሥርቱ ትእዛዛት
እንዳይተገበሩ ባለው ኃይሉ ሁሉ ይቋቋማቸዋል። ከዚህ የተነሣ ወደ እግዚአብሔር ያለ ማቋረጥ
እንድንጸልይና እርሱ የሚያስፈልገንን ኃይል እንዲሰጠን፣ እንዲጠብቀንና በእምነታችን
እንዲያሳድገን፣ ዐሥርቱንም ትእዛዛት ለመታዘዝ እንድንችል እንዲረዳን፣ በመንገዳችን ላይ ያለ
ማንኛውም መሰናክልና ጎታች ነገር እንዲወገድ ጸሎታችን ወደ እግዚአብሔር ጆሮ እንዲደርስ
3 መጮኽን የመሰለ አስፈላጊ ነገር የለም። ይሁን እንጂ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንዴት
መጸለይ እንዳለብን እንድናውቅ ቀጥሎ እንደምናየው ቃላቱንና መንገዱን አስተምሮናል።
4 ነገር ግን የጌታችንን ጸሎት ክፍል በክፍል ከመግለጻችን በፊት ዋናውና አስፈላጊው
ነገር ክርስቶስና ሐዋርያቱ እንዳደረጉት ሰዎች እንዲጸልዩ ማበረታታትና ማደፋፈር ነው።[164]
5 መጀመሪያ ማወቅ ያለብን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ የተነሣ መጸለይ ግዴታችን ነው፤ ምክንያቱም
በሁለተኛው ትእዛዝ «የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ» የሚለውን ሰምተናል። በዚያም
ስለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ቅዱስ ስሙን መጥራትና ማመስገን ነው። የእግዚአብሔርን ስም
6 መጥራት ከመጸለይ የተለየ ነገር አይደለም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ አታድርግ
የሚለው ትእዛዝ እንደ ሌሎቹ ትእዛዛት ማለትም ከእኔ በቀር ሌላ አምላክን አታምልክ፣
አትግደል፣ አትስረቅ፣ እንደሚሉት ትእዛዛት ሁሉ በጥብቅ የተደነገገ ስለሆነ ማንም ሰው የእርሱ
መጸለይ ወይም አለመጸለይ ምንም ልዩነት አያመጣም ብሎ እንዳያስብ መጠንቀቅ አለበት።
ቁም ነገር የሌላቸው ሰዎች በተሳሳተ አመለካከታቸው «ለምን እጸልያለሁ? እግዚአብሔር
ጸሎቴን እንደሚሰማ ወይም መስማት እንደሚፈልግ በምን ዐውቃለሁ? እኔ ባልጸልይ ሌላው
ይጸልያል» በማለት ጸሎት የለሽ በሆነ ሕይወት ውስጥ ይዘፈቃሉ። ለአለመጸለያቸው ምክንያት
ሲሰጡ በግብዝነትና እውነተኛ ባልሆነ መንገድ የሚደረጉ ጸሎቶች ተቀባይነት የላቸውም፤
ወይም ጸሎት መጸለይ ግዴታና አስፈላጊ አይደለም ብለን እንደምናስተምር ይናገራሉ።
7 በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ነው ተብሎ ይወሰድ የነበረው ጫጫታና ጩኸት ዓይነት
ትክክለኛ ጸሎት አለመሆኑ ግልጽ እውነት ነው። ይህን ውጫኢዊ ድግግሞሽ በአግባቡ ከተጠ
ቀምንበት ለልጆች፣ ለተማሪዎችና ለአዳዲስ ሰዎች እንደ መማሪያ ልምምድ ሊያገለግል
8 ይችላል። ለመዘመርና ለማንበብ ጠቃሚ ቢሆንም ትክክለኛ ጸሎት ግን አይደለም። ሁለተኛው
ትእዛዝ እንደሚያስተምረው መጸለይ የእግዚአብሔርን ስም በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ መጥራት
ነው። መጸለይን እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቅ ሲሆን የእኛ ምርጫ ጉዳይ አይደለም። ልክ
ለአባቶቻችን፣ ለእናቶቻችንና ለባለ ሥልጣናት መታዘዝ እንዳለብን ሁሉ ክርስቲያን መሆን
ከፈለግን መጸለይ ተግባራችንና ግዴታችን ነው። በጸሎትና በምልጃ የእግዚአብሔር ስም
ይከበራል፤ ለመልካም ዓላማ ይውላል። ይህን ከሁሉ በላይ ማስተዋል ያስፈልጋል። ስለዚህ
ከጸሎት የሚያግዱንና የሚያስተጓጉሉንን ማናቸውንም ዐሳቦች ማራቅና ጸጥ ማሰኘት አለብን።
9 እንግዲህ አንድ ልጅ ለአባቱ «የመታዘዝ ጥቅሙ ምንድን ነው? የፈለግሁትን ባደርግ ምን
እሆናለሁ?» ቢል ሕጉ «መታዘዝ አለብህ»፤ ይገባሃል ይለዋል። በተመሳሳይ መንገድ መጸለይ
ለእኔ ምርጫ የተተወ ሳይሆን *የእግዚአብሔርን ቍጣና ሐዘን በመፍራት ማድረግ የሚገባኝ
ተግባርና ግዴታ ነው።*[165]

[164] ለምሳሌ ማቴዎስ 7፡7፤ ሉቃስ 18፡1፤ 21፡36፤ ሮሜ 12፡12፤ ቈላስይሰ 4፡2፤ 1ተሰሎንቄ 5፡17፤ 1ጢሞቴዎስ 2፡1፤ ያዕቆብ 1፡6፤ 5፡13፤ 1ጴጥሮስ 4፡8፤ ይሁዳ 20 ይመልከቱ።

[165] ዘመም ያለው ጽሑፍ በመጀመሪያው የትልቁ ክርስትና ትምህርት ኅትመት፣ በጄናው ኅትመት የሉተር ሥራዎች ወይም በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) የለም። የሚገኘው በታረመው የክርስትና ትምህርት (1529) እና በኋላ በላቲኑ ትርጒም (1544) እና ዐዲስ በተተረጎመውና እዚህ በተካተተው የላቲኑ መጽሐፈ ስምምነት (1584) ነው።

10 *ስለዚህ ብንጸልይ ወይም ባንጸልይ ልዩነት አያመጣም፤ ጸሎቶች የሚደረጉት ከእኔ*
*ይልቅ ጻድቃን በሆኑት ሰዎች ወይም ከእኔ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ባላቸው*
*ሰዎች ነው በማለት እንዳንጸልይ እንቅፋት የሚሆኑብንን ወይም እኛን ከጸሎት የሚመልሱንን*
*ዐሳቦች ጸጥ ማሰኘት እንደሚኖርብን መገንዘብ ያስፈልገናል። በእርግጥም በተፈጥሮ የሰው ልብ*
*እጅግ ክፉ ከመሆኑ የተነሣ መለኮታዊ ቊጣ እንጂ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአተኝነታችን ጸሎቱን*
*ሊሰማለትና ጥንቃቄም ሊያደርግለት እንደሚፈልግ ስለማይገነዘብ ዘወትር ከእግዚአብሔር*
11 *ይሸሻል። ባለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቊጣ እንዳንቀሰቅስ እንደዚህ ያሉትን ዐሳቦች*
*በመቋቋምና ይህንን ትእዛዝ በማክበር ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብን እላለሁ። በዚህ*
*ትእዛዝ ምንም ያህል ኃጢአተኞች ብንሆን እርሱ ወደ ውጭ እንደማይጥለን ወይም*
*እንደማያባርረን ግልጽ አድርጎአል። ይልቁንም እግዚአብሔር ራሳችንን በፊቱ በማዋረድ*
*ችግራችንና ሐዘናችንን ለእርሱ እንድናስታውቅ፣ ጸጋና እርዳታን ከእርሱ እንድንለምን እኛን*
*ወደ ራሱ ማስጠጋት ይፈልጋል። ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናነበው እርሱ የሚቈጣው*
*በኃጢአታቸው የተቀጡት ሰዎች ወደ እርሱ ስላልተመለሱና ቊጣውን አብርደው በጸሎቶቻቸው*
*ጸጋውን ስላልፈለጉ ነው።*

12 ጸሎትን በጥብቅ ከሚደነግገው እውነት አኳያ ጸሎታችንን ምን ጊዜም ቢሆን ማናናቅ
13 ሳይሆን ይልቁንም ትልቅ ቦታ ልንሰጠው እንደሚገባን መደምደም ይገባችኋል። ከሌሎቹ
ትእዛዛት ምሳሌ እንውሰድ፡- አንድ ልጅ የወላጁን ትእዛዝ ከቶ መናቅ ሳይሆን፡- «ይህ ድርጊት
የመታዘዝ ድርጊት ነው፤ ስለ ሆነም የማደርገው ነገር በታዛዥነት ልፈጽመው የሚገባኝና
የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከመሆን ሌላ ዓላማ የለውም። በዚህ ልታመንና ልደገፍ እችላለሁ፤ ከእኔ
ተገቢነት የተነሣ ሳይሆን ከትእዛዙ የተነሣ እጅግ ላከብረው ይገባኛል» በሚል መንፈስ ሁልጊዜ
ማሰብ ይገባዋል። ጸሎትንም አስመልክቶ እውነቱ ተመሳሳይ ነው። የጸሎቶቻችን ቃላትና ዓላማ
በእግዚአብሔር እንደሚፈለጉና እርሱን በመታዘዝ እንደሚፈጸሙ አድርገን መቊጠር
ይኖርብናል። «በእኔ በኩል ይህ ጸሎት ምንም አይጨምርም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስላዘዘው
አስፈላጊ ነው» ብለን ማሰብ ይገባናል። ስለ ሆነም ማንም ሰው ስለ ምንም ነገር ይጸልይ፤ ነገር
ግን ለዚህ ትእዛዝ በመታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይገባዋል።

14 በመሆኑም ሰው ሁሉ እነዚህን ቃላት በልቡ እንዲያኖርና መቼም ቢሆን ጸሎትን
እንዳይንቅ እንማጸናለን፤ እናበረታታለንም። ጸሎት ማንም ትኩረት ሊሰጠው የማይገባ፣
እግዚአብሔር ሰማው አልሰማው ሥርዓቱ ከተከናወነ በቂ ነው ብለው ሰዎች እንዲገምቱ
የሚያደርግ ትምህርት በዲያብሎስ ስም ይሰጥ ነበር። ይህ ግን ጸሎትን በዕድል ላይ መቸከልና
ዝም ብሎ ያለ ዓላማ ማጉተምተም ይሆናል። እንደዚህ ያለው ጸሎት ዋጋ ቢስ ነው።

15 እኛ ብዙውን ጊዜ «እኔ ቅዱስ ወይም ብቁ አይደለሁም። እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ወይም
ቅዱስ ጳውሎስ ጻድቅና ቅዱስ ብሆን ኖሮ እጸልይ ነበር» በማለት ለመደናቀፍና መንገዳችንን
ለመቀየር ራሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን። እንደዚህ ያሉ ዐሳቦች ከእኛ ይራቁ! ለቅዱስ ጳውሎስ
የሠራው ትእዛዝ ለእኔም ይሠራል። ሁለተኛው ትእዛዝ የተሰጠው ለጳውሎስ የሆነውን ያህል
ለእኔም ነው። እርሱ ከዚህ በተሻለ ወይም ይበልጥ ቅዱስ በሆነ ትእዛዝ ከእኔ አስበልጦ ሊመካ
አይችልም።

16 ስለዚህ፡- «የማቀርበው ጸሎት እንደ ቅዱስ ጳውሎስና እንደ ሌሎች ቅዱሳን ጸሎት ሁሉ
የከበረ፣ ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነው፤ ምክንያቱ ይህ ነው፤ ጳውሎስ በሰብእናው
ከእኔ ይበልጥ ቅዱስ መሆኑን በፈቃደኝነት እቀበላለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ የሚበልጠኝ በዚህ ትእዛዝ
ምክንያት አይደለም። እግዚአብሔር ጸሎትን የሚያየው በሰውየው ምክንያት ሳይሆን በቃሉና
ለቃሉ በምናሳየው መታዘዝ ምክንያት ነው። ቅዱሳን ሁሉ ጸሎታቸውን በመሠረቱበት በዚህ
ትእዛዝ ላይ እኔም ጸሎቴን እመሠርታለሁ። በተጨማሪም ሁሉም ሊያገኙ የሚጸልዩትን ወይም
ከዚህ በፊት በጸሎት የጠየቁትን ወይም ፈጽሞ ያልጠየቁትን ነገር ለማግኘት እጸልያለሁ»[166]
ማለት አለብህ።

[166] የ1538 የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) ይህን ይጨምራሉ። «እንዲሁም የእነዚያ ቅዱሳን ያህል እና ከእነርሱ በበለጠ መልኩ እነዚህ ጸሎቶች ያስፈልጉኛል።»

17 ይህም ማለት ጸሎቶቻችን ሁሉ ከማንነታችን ውጪ ኃጢአተኞች ወይም ጻድቃን፣
የተገባን ወይም ያልተገባን በመሆናችን ላይ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመታዘዝ ላይ የተመሠረቱ
18 መሆናቸው የመጀመሪያውና እጅግ አስፈላጊው ነጥብ ነው። እግዚአብሔር እንደማይቀልድ፣
[እንደ ትእዛዙ] ካልጸለይን እንደሚቈጣና እንደ ሌሎች ዓይነት አለመታዘዞች ሁሉ እንደሚቀጣን
መረዳት አለብን። እንዲሁም ጸሎቶቻችን ከንቱ ሆነው እንዲቀሩ ወይም የማይመለሱ ሆነው
እንዲጠፉ አይፈቅድም፤ ሊመልሳቸው ባያስብ ኖሮ እንድትጸልይ ባላዘዘህና እንደዚህ ባለ ጥብቅ
ትእዛዝም የጸሎትን አስፈላጊነት ባላጠናከረ ነበር።
19 በሁለተኛ ደረጃ ለጸሎት እንድንደፋፈርና እንድንነሣሣ የሚያደርገን ነገር ጸሎታችንን
እንደሚመልስ እግዚአብሔር የገባልንና ያረጋገጠልን የተስፋ ቃሉ ነው። ጸሎታችን ጥርጥር
የሌለበትና የተረጋገጠ ነገር ነው። በመዝሙረ ዳዊት 50፡15 «በመከራ ቀን ጥራኝ አድንህማለሁ»
የሚል ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል 7፡7-8 «ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ የሚለምን ሁሉ
20 ይቀበላልና» ብሏል። እንደዚህ ዓይነት የተስፋ ቃሎች በልባችን የጸሎትን ናፍቆትና ፍቅር
ሊቀሰቅሱና ሊያቀጣጥሉ ይገባል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዳንንቀው፣
ለነፋስም እንዳንበትነው ወይም በጥርጥር እንዳንጸልይ የሚፈልግ ሲሆን በሌላ በኩል ጸሎታችን
እጅግ እንደሚያስደስተው፣ በእርግጠኝነትም እንደሚሰማና እንደሚፈጽምልን በቃሉ
ያረጋግጣል።
21 ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት የተስፋ ቃላትን ይዘህ፡- «ውድ አባት ሆይ፣ እነሆ መጣሁ»
በገዛ ራሴ ፈቃድ ወይም ከብቃቴ የተነሣ ሳይሆን ሊጥለኝ ወይም ሊያታልለኝ ከማይችለው
ከትእዛዝህና ከተስፋ ቃልህ የተነሣ እጸልያለሁ» ማለት ትችላለህ። እንደዚህ ዓይነቱን የተስፋ
ቃል የማያምኑ እግዚአብሔርን እያስቈጡትና በግልጽ ክብሩን እየተጋፉ እንዲሁም እርሱን
ሐሰተኛ አድርገው እየከሰሱት መሆናቸውን ደግመው መገንዘብ ይገባቸዋል።
22 ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ትእዛዝና የተስፋ ቃል ጋር እግዚአብሔር በራሱ ተነሣሽነት
ለጸሎት የምንጠቀምባቸውን ቃላትና አቀራረብን በአንደበታችን ማስቀመጡ ለጸሎት
ሊያበረታታንና ወደ ጸሎት ሊስበን ይገባል። በዚህ መንገድ ስለሚያስፈልጉን ነገሮች እንዴት
በጥልቀት እንደሚያስብልን ዐይተን እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት እንደሚያስደስተውና እንደሚሰማው
በጭራሽ መጠራጠር የለብንም። ስለሆነም ይህ ጸሎት ራሳችን ከምንፈጥራቸው ሌሎች ጸሎቶች
23 ሁሉ እጅግ የላቀ ነው። እኛ የፈጠርነው ጸሎት ሆኖ ቢሆን ኖሮ፡- «እጸልያለሁ፤ ነገር ግን
እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘው ወይም ትክክለኛውን ቅርጽና ዘይቤ እንደ ያዝኩኝ ማን
ያውቃል?» በማለት ሕሊናችን ሁልጊዜ ይጠራጠር ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊሰማው
የሚወድና ጠንካራ ምስክርነት ያለው ከዚህ (ከጌታ ጸሎት) የበለጠና የከበረ ጸሎት በዚህ
ምድር[167] አይገኝም። ይህንን ስጦታ በዓለም በሚገኝ ሀብት ሁሉ መለወጥ አይገባንም።
24 ያለ ማቋረጥ እንድንጸልይ የሚያነሣሣን ጕድለታችን ሲሆን በዚህ በሚጎድለን ነገር ላይ
እንድናተኵር ጸሎት ተሰጥቶናል። ለእርዳታ ጥሪ የሚያደርግ ሰው የሚፈልገውን ነገር
በመጥቀስና በመግለጽ ልመና ማቅረብ አለበት። አለበለዚያ ጸሎት ተብሎ ሊጠራ አይችልም።
25 ስለዚህ በቀንና በማታ በሚያስፈራ ሁኔታ የሚያላዝኑት እና የሚያልጎመጉሙት ነገር
ግን ትንሽ የምትባለውን ነገር[168] እንኳ ለመጠየቅ የማያስቡትን የመነኩሴዎችንና የቀሳውስትን
ጸሎቶች በትክክል ውድቅ አድርገናል። አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ከቀሳውስታቸው ጋር አንድ
ላይ ብንሰበስብ አንዲት የወይን ጠብታን ያህል እንኳ በሙሉ ልባቸው ጸልየው እንደማያውቁ
ማመን ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም አንዳቸውም እግዚአብሔርን በመታዘዝና የተስፋ ቃሉን
በማመን ወይም የሚያስፈልጋቸውን ነገር ግምት ውስጥ በማስገባት መቼውንም ቢሆን ጸልየው
ዐያውቁምና ነው። ከሁሉ የተሻለ ነው ብለው የሚያስቡት ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ስጦታ
መቀበል ሳይሆን ለእግዚአብሔር ሊሰጡት እንደ ክፍያ የሚያገለግል መልካም ሥራ
መሥራታቸውን ብቻ ነው።

[167] የ1538 የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) «ከየዕለቱ የጌታ ጸሎት የበለጠ» የሚለውን ሐረግ ይጨምራሉ።
[168] ቃል በቃል ሲተረጎም «ለጸጉር ስፋት» እንደ ማለት ነው።

26 ነገር ግን እውነተኛ ጸሎት መሆን ያለበት ከፍጹም ልብ ነው:: ወደ እግዚአብሔር
ለመጮኽ የሚገፋፋንና የሚያነሣሣን መከራ ወይም ጕድለት ሊሰማን ይገባል:: እንዲህ ሲሆን
ጸሎት በትክክለኛ መልኩ ያለ ትግል በቅጽበት ይመጣል:: ማንም ለጸሎት እንዴት
27 እንደሚዘጋጅ ወይም ተገቢው መሰጠት እንዴት እንደሚፈጥር መማር አያስፈልገውም:: ይሁን
እንጂ፣ ማጤን ያለብን ለእኛም ሆነ ለሌላው ሰው የሚያስፈልገው ይህ ነገር በጌታ ጸሎት
ውስጥ በሰፊው ተካቶ የምታየው ነገር መሆኑ ነው:: ስለዚህ እርሱ ሁላችንም ብዙ ነገሮች
ስለሚጎድሉን መጸለይን ችላ እንዳንል እንዲያስታውሰንና በልባችን እንዲቀረጽ ያደርጋል::
ምክንያቱም ችግሩ የሚጎድሉን ነገሮች ቢኖሩም እነዚህ ጕድለቶቻችን ስሜታችንን ያልነኩ
ወይም ያላየናቸው መሆናቸው ነው:: እግዚአብሔር እነዚህን ጕድለቶቻችንን ሳያውቃቸው ቀርቶ
ሳይሆን እኛ ሐዘናችንን፣ ፍላጎቶቻችንና የሚያሳስቡንን ነገሮች ለእርሱ እንድናሳውቅ ይፈልጋል::
ይህም ልባችንን ወደ ከበሩና ከፍ ወዳሉ ምኞቶች እንድናነሣሣና በርካታ ነገሮችን ለመቀበል
ሸርጣችንን ሰፋ አድርገን እንድንዘረጋ ነው::
28 ስለዚህ ከእኛ እያንዳንዱ ሰው ከወጣትነት ጊዜ ጀምሮ እኛን ወይም በዙሪያችን ያሉ
ሌሎች ሰዎችን፣ ሰባኪዎችን፣ ባለ ሥልጣናትን፣ ጎረቤቶችንና አገልጋዮችን የሚነካ ማንኛውም
ነገር መኖሩን ስናውቅ ለሚያስፈልጉን ነገሮች በየዕለቱ የመጸለይ ልማድ ማዳበር ይኖርብናል::
አስቀድሜ እንዳልኩት እግዚአብሔር ትእዛዙና የተስፋ ቃሉ እንዲናቁ እንደማይፈልግ ዐውቀን
29 ሁልጊዜ እርሱን ስለ ትእዛዛቱና ስለ ተስፋው በጸሎት ማስታወስ ይገባናል:: ይህን የምልበት
ምክንያት ሰዎች በሥርዓት መጸለይን እንደ ገና እንዲማሩና በየዕለቱ ለጸሎት ጕልበት
የሌላቸው ሆነው እጅግ ማስተዋል በጎደለውና ስሜት አልባ በሆነ ሁኔታ እንዳይንቀሳቀሱ
ለማድረግ ነው:: ዲያብሎስ ለጸሎት ስሜት የሌለው መሆንን ስለሚፈልግ ባለ በሌለ ኃይሉ
ጸሎታችንን ለማደናቀፍ ተግቶ ይሠራል:: ምክንያቱም ጸሎት በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ
ሲውል ምን ያህል ጥፋትና ጉዳት እንደሚደርስበት በሚገባ ያውቃል::
30 ስለዚህ በእግሮቻቸው ሥር እኛን ለመጨፍለቅ የሚሞክሩትንና በእኛ ላይ የተሰለፉትን
ዲያብሎስና የእርሱን ኃይላት ለመቋቋም የራሳችን የሆነ አቅም ስለሌለን ደኅንነታችንና
ዋስትናችን በጸሎት ብቻ እንደሚገኝ ማወቅ አለብን:: ይህንኑ ተገንዝበን ዲያብሎስን ለመቋቋም
ክርስቲያኖች ራሳቸውን ማስታጠቅ የሚኖርባቸውን መሣሪያዎች መጨበጥ ይገባናል:: ስለዚህ
በእኛ በኩል እንደ ብረት ግድግዳ ሆኖ ጣልቃ በመግባት የጠላቶቻችንን ምክርና ሤራ
ለመመከትና ዲያብሎስ እኛንና ወንጌሉን ጭምር ሊያጠፋ የሚጠቀምባቸውን የግድያና የዓመፅ
ዕቅዶችን ያስቆመው በቀድሞም ጊዜ እንደዚያ ያሉ ትልልቅ ውጤቶችን ያስገኘው ከጥቂት
ፈሪሃ እግዚአብሔር ካላቸው ሰዎች ጸሎት በስተቀር ሌላ ምንድን ይመስላችኋል? የዲያብሎስ
ዕቅድ በጸሎት ባይፈርስ ኖሮ ከእኛ የቀደሙ ሰዎች በጣም የተለየ ትዕይንት ባዩ ነበር::
ዲያብሎስ መላዋን ጀርመን በራሷ ደም ያጠፋት ነበር:: አሁን ግን በራስ መተማመን ሊስቁና
የትችት አስተያየታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ:: ነገር ግን እነርሱንና ዲያብሎስን ልንቋቋም
32 የምንችለው በጸሎት ብቻ ነው:: አንድ ጥሩ ክርስቲያን «ውድ አባት ሆይ፣ ፈቃድህ ይፈጸም»
ብሎ በሚጸልይበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከሰማይ «አዎ፣ ውድ ልጄ ዲያብሎስና መላው
ዓለም ምንም ያድርጉ ግን ፈቃዴ በእርግጥ ይፈጸማል» ብሎ ስለሚመልስ እኛ ብንጸናና
ባንታክት በጸሎት ብቻ ዲያብሎስን ድል እናደርጋለን::
33 ይህን ሁሉ የምንለው ሰዎች ከሁሉ በላይ ጸሎትን ታላቅና የከበረ ነገር አድርገው ዋጋ
እንዲሰጡት፣ አንድን ነገር በጸሎት በመጠየቅ እና በፍሬ ቢስ ልፍለፋ መካከል ያለውን ልዩነት
በሚገባ እንዲረዱና አንድን ግልጽ የሆነ ነገር ከእግዚአብሔር እንዲለምኑ ለማነሣሣት ነው::
ጸሎትን በምንም መንገድ አንቃወምም:: ነገር ግን ክርስቶስ የቃላት ብዛትን እንዳልተቀበለውና
እንደ ከለከለው ሁሉ እኛም ፈጽሞ ጥቅም የሌጭላቸውን ማላዘንና ማጉተምተምን
34 እናወግዛለን::[169] እንግዲህ የጌታን ጸሎት ባጭሩና በግልጽ ሁኔታ እናጠናለን:: ይህም ጸሎት
በሰባት ተከታታይ አንቀጾች የተከፋፈለ ሲሆን በእነዚህም አንቀጾች ባለማቋረጥ የሚያስጨንቁን፣

[169] ማቴዎስ 6:7፤ 23:14::

ከመግዘፋቸውም የተነሣ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ለጸሎት ሊያነሣሡን የሚገቡ አስፈላጊ ነገሮች በሙሉ ተካተውበታል።

*የመጀመሪያው ጸሎት*

35 «ስምህ ይቀደስ።»
36 ይህ ግልጽ ያልሆነና በጀርመንኛ ፊሊጣዊው አነጋገር የማይገኝ ነው። አፍ በፈታንበት
37 ቋንቋ «ሰማያዊ አባት ሆይ፣ ስምህ ብቻ እንዲቀደስ ፍቀድ» እንላለን። «ስሙ ቅዱስ እንዲሆን
መጸለይስ ምንድን ነው? አስቀድሞስ የተቀደሰ አይደለምን?» መልስ፦ አዎ፣ በይዘቱ ዘወትር
በራሱ የተቀደሰ ነው፤ ነገር ግን እኛ ስሙን የምንጠቀምበት መንገድ ቅዱስ አይደለም።
ክርስቲያኖች በሆንንበትና በተጠመቅንበት ጊዜ የእግዚአብሔር ስም ተሰጥቶናል። በተጨማሪም
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ተጠርተን ከእርሱ ጋር ተካፋዮች በመሆን የእግዚአብሔር
የሆኑት ሁሉ ለእኛ ጥቅም ሊሆኑ የሚችሉባቸው የጸጋ መሣሪያዎችንም አግኝተናል።
38 ስለሆነም የእግዚአብሔር ስም ተገቢውን ክብር በእኛ ዘንድ እንዲያገኝና እርሱም እጅግ
በጣም ታላቅና የተቀደሰ ነገር በመሆኑ የተለየና የተቀደሰ ተደርጎ እንዲጠበቅ፣ እኛም እንደ
መልካም ልጆች ስሙ በሰማይ የተቀደሰ እንደ ሆነ በእኛም መካከል፣ በመላው ዓለምና በምድር
ላይ የተቀደሰ ሆኖ እንዲቆይ መጸለያችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው።
39 ስሙ በእኛ መካከል እንዴት ሊቀደስ ይችላል? ለዚህ ሊሰጥ የሚችል ግልጽ መልስ
የምናስተምረውና የምንኖረው ኑሮ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበትና ክርስቲያናዊ ሲሆን ነው።
ስለዚህ በዚህ ጸሎት እግዚአብሔርን አባታችን ብለን ስለምንጠራ እግዚአብሔር ከእኛ ክብርና
ምስጋናን እንጂ የሚያሳፍር ነገር እንደማይቀበል ዐውቀን በማንኛውም መንገድ እንደ መልካም
ልጆች መልካም ባሕርይ ያለን ሆነን መገኘት ይገባናል።
40 በምድር ላይ የምንሠራው ማንኛውም ሥራ በቃል ወይም በድርጊት ሊመደብ
41 ስለሚችል የእግዚአብሔርን ስም በቃላት ወይም በሥራ ልናረክሰው እንችላለን። በመጀመሪያ
ደረጃ ሰዎች ውሸቶቻቸውን ሸፋፍነው ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ ስሙን በመጠቀም
ሐሰተኛና አታላይ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ሲሰብኩ፣ ሲያስተምሩና በእግዚአብሔር ስም
ሲናገሩ ስሙ ይረክሳል። ይህ እጅግ በጣም አስከፊ የሆነ መለኮታዊ ስሙን የማቃለልና
42 የማዋረድ መንገድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ሰዎች በመለኮታዊ ስሙ እፍረታቸውን ለመሸፈን
ሲሉ በመማል፣ በመራገምና በምትሐታዊ መንገድ ወዘተ. ያለ አግባብና ክብር በጎደለው መልኩ
43 ሲጠቀሙበት ስሙ ይረክሳል። ቀጥሎም ክርስቲያኖችና የእግዚአብሔር ሰዎች ተብለው የሚጠ
ሩት ዘማዊዎች፣ ሰካራሞች፣ ስግብግቦች፣ ምቀኞችና ሐሜተኞች ሲሆኑ በግልጽ በሚታይ
የክፋት ሕይወትና የተንኮል ሥራዎች ሁሉ ስሙ ይረክሳል። ከእነዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር
ስም እየረከሰና እየተሰደበ ነው።
44 በቃልና በድርጊት በሚቃወመው መጥፎና ስድ ልጁ ምክንያት ንቀትና ነቀፌታ
የሚደርስበት አንድ ምድራዊ አባት እፍረትና ውርደት እንደሚሆንበት ሁሉ እግዚአብሔርም
በስሙ የተጠራንና የተትረፈረፈውን በረከቱን የምንጠቀምበት እኛ እንደ ቅዱሳንና ሰማያዊ
ልጆች ማስተማር፣ መናገርና መመላለስ ሲሳነን በድርጊታችን የእግዚአብሔር ልጆች ሳይሆን
የዲያብሎስ ልጆች ተብለን ስንጠራ መስማት ያሳዝነዋል።
45 ስለዚህ በዚህ ጸሎት እግዚአብሔር በሁለተኛው ትእዛዝ ለሚፈልግብን ነገር
እንደምንጸልይ ታያለህ። ያም ስሙን ለከንቱ መሐላ፣ ለእርግማንና ለማታለል ወዘተ. ማንሳት
ሳይሆን በትክክል ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና እንድንጠቀምበት የሚገባ መሆኑ ነው።
በቀደመው ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ግድያ ወይም ሌላ ወንጀል ሲፈጸም፣ ቤተ ክርስቲያን
እንድትረክስ ተደረገ እንደሚባለው የተባረከው ኅብስት የሚቀመጥበት ዕቃ ወይም ቅሪተ
የቅዱሳን አስከሬን[170] ሲረክሱ በራሳቸው ቅዱሳት የሆኑ ነገሮችን አግባብ የሌለው አጠቃቀም
የረከሱ እንደሚያደርጋቸው ሁሉ ማንም ሰው ለየትኞቹም የስሕተት ድርጊቶች የእግዚአብሔርን

[170] የቅዱሳን አስከሬን የተባረከው ኅብስት እንዲታይ ተደርጎ ለአምልኮ የሚቀመጥበት ዕቃ ነው።

46 ስም ቢጠቀም ይህ ቅዱስ ስሙን ያረክሰዋል፡፡ ስለዚህ «መቀደስ» የሚለው ቃል፣ በቃልና በሥራ
እርሱን «ማወደስ፣ ከፍ ከፍ ማድረግ እና ማክበር» የሚል ትርጉም ያለው መሆኑን ብንረዳ ይህ
ጸሎት ቀላልና ግልጽ ይሆንልናል፡፡
47 እንግዲያውስ እንዲህ ዓይነት ጸሎት ምን ያህል እንደሚያስፈልገን ተመልከት! ዓለም
በመላ ለዲያብሎሳዊ መሠረተ እምነታቸው ቅዱስ ስሙን እንደ መሸፈኛና ማረጋጋጫ ለመጠ
ቀም በሚፈልጉ መናፍቃንና ሐሰተኛ አስተማሪዎች የተሞላች ነች፡፡ ስለዚህ ጳጳሳቱን፣
አምባገነኖቹን፣ አክራሪዎቹንና ሌሎች በሐሰት የሚሰብኩትንና የሚያምኑትን ሁሉ በመቋቋም
ወንጌላችንንና ንጹሑን አስተምህሮ የሚያጠቁትን፣ የሚያሳድዱትንና የሚያፍኑትን በመቃወም
ያለ ማቋረጥ መጮኽና መጣራት ይገባናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ጸሎት የእግዚአብሔር ቃል
እያለን ነገር ግን ምስጋና ቢስ ለሆንን እና እንደሚገባን በቃሉ ለማንኖረው ለእኛም ነው፡፡
48 እንዲህ ያሉ ነገሮችን ከልብህ ብትለምን እግዚአብሔር ደስ እንደሚለው እርግጠኛ መሆን
ትችላለህ፡፡ ክብሩና ውዳሴው ከሌላ ከማንኛውም ነገር ይልቅ ከፍ ከፍ ሲል፣ ቃሉን በንጽሕና
ሲያስተምሩት፣ ከሐሰተኞች ሲከላከሉትና ዋጋ ሲሰጡት ከመስማት የበለጠ እግዚአብሔር
የሚፈልገው ምንም ነገር የለም፡፡

*ሁለተኛው ጸሎት*

«*መንግሥትህ ትምጣ*»

49 በመጀመሪያው ጸሎት እግዚአብሔር በእኛ እንዲወደስና ከፍ ከፍ እንዲል፣
በትምህርትና በኑሮ ስሙ እንዲከብርና እንዲቀደስ፣ ዓለም ውሸቷንና ክፋቷን ለመሸፈን
ክብሩንና ስሙን እንዳትጠቀምበት እንዲከላከል ጸልየናል፡፡ በዚህ ጸሎት ደግሞ መንግሥቱ
50 እንድትመጣ እንጸልያለን፡፡ የእግዚአብሔር ስም በራሱ ቅዱስ እንደ ሆነ ነገር ግን ስሙ
በመካከላችን ቅዱስ እንዲሆን እንደምንጸልይ መንግሥቱም ያለ ጸሎታችን በራሷ ትመጣለች፤
ሆኖም ግን ወደ እኛ እንድትመጣ እንጸልያለን፤ ማለትም ስሙ ከሚቀደስባቸውና መንግሥቱ
ከምታድግባቸው፣ ከምትሰፋባቸው ከእነርሱ መካከል እንድንሆን በመካከላችንና ከእኛ ጋር
እንድትገኝ እንጸልያለን፡፡
51 የእግዚአብሔር መንግሥት ምንድን ነች? መልስ፡- በቀላሉ እላይ በእምነት መግለጫችን
እንደ ሰማነው ከኃጢአት፣ ከሞትና ከክፉ ሕሊና ሊዋጀን፣ ከዲያብሎስ ኃይል ነጻ ሊያወጣን፣
ወደ ራሱ ሊያቀርበንና የጽድቅ፣ የሕይወትና የድነት ንጉሥ ሆኖ ሊገዛን እግዚአብሔር ልጁን
ጌታችን ክርስቶስን ወደ ዓለም መላኩ ነው፡፡ ወደዚህም ግብ ሊያደርሰን ደግሞ በቅዱስ ቃሉ
አማካይነት ይህንን እንዲያስተምረን፣ ልቦናችንን እንዲያበራልንና በኃይሉ በእምነት እንዲያጠ
ነክረን መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፡፡
52 እዚህ ላይ ይህ ሁሉ በእኛ እውን እንዲሆን፣ በቅዱስ ቃሉ እና በክርስቲያናዊ አኗኗር
የእግዚአብሔር ስም በእኛ ዘንድ እንዲወደስ ከጅማሬው እንጸልያለን፡፡ እኛ ይህንን የተቀበልነው
ታማኞች ሆነን እንድንገኝና በየዕለቱ በእርሱ እንድናድግ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሌሎች
ሰዎች መካከልም ተቀባይነት ኖሮአት ተከታዮች እንድታገኝና በመላው ዓለም በሕዝቦች መካከል
በኃይል እንድትሰፋ እንጸልያለን፡፡ በዚህ መንገድ አሁን በተጀመረው በዚህ መንግሥት
ለዘለዓለም ሁላችንም በአንድነት እንድንኖር፣ ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ወደ ጸጋው
መንግሥት እንዲመጡና የድነት ተካፋዮች እንዲሆኑ እንጸልያለን፡፡
53 የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እኛ መምጣት በሁለት መንገዶች ይከናወናል፤ ይኸውም
በመጀመሪያ፣ በዚህ ምድር ላይ በቃሉና በእምነት አማካይነት ትመጣለች፡፡ ሁለተኛ፣
በዘለዓለማዊነት በፍጻሜው መገለጥ[171] ትመጣለች፡፡ እንግዲህ ለእነዚህ ለሁለቱም ክስተቶች
እንጸልያለን፤ ማለትም [የእግዚአብሔር መንግሥት] እስካሁን በውስጥዋ ለሌሉባት እንድትመጣና
በዚህ ዘመን በዕለታዊ ዕድገትና ከዚህ በኋላ ላለንባት ለእኛ ከዚህም በኋላ በዘለዓለማዊ ሕይወት
54 እንድትመጣልን እንጸልያለን፡፡ ይህ ሁሉ በቀላሉ፡- «የተወደድህ አባት ሆይ፣ ወንጌሉ በመላው

[171] ማለትም የክርስቶስ ሁለተኛው ምጽአት፡፡

ዓለም በእውነት እንዲሰበክና በእምነት ተቀባይነት እንዲያገኝ በእኛም እንዲሠራና እንዲኖር
ቃልህን እንድትሰጠን እንለምንሃለን፤ ስለሆነም በቃልህና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መንግሥትህ
በመካከላችን እንድታሸንፍ የዲያብሎስ መንግሥት እንዲጠፋ፣ በእኛ ላይ ምንም መብት ወይም
ኃይል እንዳይኖረው በመጨረሻ የዲያብሎስ መንግሥት ሙሉ በሙሉ እስኪደመሰስ፣ እንዲሁም
ኃጢአት፣ ሞትና ሲኦል እስኪወገዱ እኛ በፍጹም ጽድቅና ብፅዕና ለዘለዓለም እንድንኖር
እንጸልያለን» ማለት ነው።

55 እዚህ እየጸለይን ያለነው ለቁራሽ ዳቦ[172] ወይም ለጊዜያዊ ጠፊ በረከት ሳይሆን
ዘለዓለማዊ ለሆነ በዋጋ ሊተመን ለማይችልና እግዚአብሔር ራሱ ላለው ነገር ሁሉ እንደሆነ
ታያለህ። ይህን ጉዳይ እንድንለምን እግዚአብሔር ራሱ ባያዘን ኖሮ የትኛውም ሰብአዊ ልብ
56 መመኘት ከሚችለው በላይ ይሆንበት ነበር። ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔር ከመሆኑ የተነሣ
ማንም ሰው ሊገነዘብ ከሚችለው በላይ በፈለቀና በፈሰሰ መጠን ይበልጥ መስጠት እንደሚቀጥል
ተሟጦ እንደማያልቅ ዘላለማዊ ምንጭ አትረፍርፎና በልግስና መስጠት የመቻሉ ክብር
እንዲታወቅለት ይፈልጋል። እግዚአብሔር በርካታና ታላላቅ ነገሮችን ከእርሱ እንድንለምን
ከመጠበቅ ይበልጥ አበክሮ ከእኛ የሚፈልገው ምንም ነገር የለም፤ ይልቁንም በሙሉ ልብ
በመተማመን ካልለመንንና ካልፈለግን ይቈጣል።

57 አንድን ድሀ ጠርቶ የፈለገውን ማናቸውንም ነገር እንዲጠይቅ የሚያዝዝ፣ ታላላቅ
የሆኑና በንጉሥ የሚሰጡ ስጦታዎችን ለመስጠት የተዘጋጀ እጅግ ባለ ጠጋና ኃያል ንጉሥ
ነገሥትንና አንድ የዕለት ምግብ ብቻ የሚጠይቅ ለማኝን ዐስብ። እንዲህ ዓይነቱ ለማኝ
በእውነትም የንጉሡ ነገሥቱን ግርማዊ ትእዛዝ ስለሚያቃልል በንጉሡ ነገሥቱ ፊት ሊቀርብ
የማይገባው ወስላታ ወሮበላ እንደ ሆነ በትክክል ሊቈጠር ይችላል። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር
በቃላት ሊገለጹ የማይችሉ እጅግ ብዙ በረከቶችን የሚያቀርብልንንና ሊሰጠን ቃል የሚገባልንን
ስጦታዎች ብናቃልላቸው ወይም እንደምንቀበላቸው ባናምንና ቍራሽ እንጀራ ብቻ ለመጠየቅ
በግድ ብንደፍር ይህ ድርጊታችን ለእግዚአብሔር ትልቅ ነቀፌታና ውርደት ማሳየት ይሆናል።

58 እዚህ ላይ ጥፋቱ ሙሉ በሙሉ ያለው ከእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ በረከቶችን ያለ
ጥርጥር መጠበቅ ቀርቶ ሆድን ለመሙላት እንኳ እግዚአብሔርን ተስፋ በማያደርገው አሳፋሪ
አለማመን ላይ ነው። ስለዚህ በአለማመን ላይ ራሳችንን ማጠንከር ይገባናል። የምንለምነውም
በመጀመሪያው ነገር የእግዚአብሔር መንግሥት ይሁን «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ፈልጉ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የእናንተ ይሆናሉ»[173] ብሎ ክርስቶስ እንደሚያስተምረው
ያኔ በእርግጥም ሌሎች ነገሮች ሁሉ ተትረፍርፈው ይሰጡናል። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊና
ሊጠፉ የማይችለውን ሊሰጠን ቃል ገብቶልን እያለ በጊዜያዊ ነገሮች እጦት እንድንሠቃይ
እንዴት ሊፈቅድ ይችላል?

*ሦስተኛ ጸሎት*

59 *«ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን።»*

60 እስካሁን ድረስ የእግዚአብሔር ስም በእኛ እንዲቀደስና መንግሥቱ በመካከላችን
እንድታሸንፍ ጸልየናል። እነዚህ ሁለት ነጥቦች ለእግዚአብሔር ክብርና ለድነታችን
የእግዚአብሔርን ሀብት ሁሉ ከእርሱ ጋር የራሳችን የምናደርግበትን ነገር ሁሉ ያቅፋሉ። ነገር
ግን እነዚህን ሁለት ነገሮች አጥብቀን መያዛችንና ከእነርሱ መነጠልን አለመፍቀዳችን የዚያኑ
61 ያህል እጅግ አስፈላጊ ነው። በአንድ መልካም አስተዳደር መልካም ገነቢዎችና ገዢዎች ብቻ
ሳይሆኑ አስከባሪዎች፣ ተከላካዮችና ንቁ ጠባቂዎችም ያስፈልጋሉ። እዚህም ላይ ልክ እንደዚሁ
ነው። እጅግ በጣም አስፈላጊ ስለሆነው፦ ስለ ወንጌል፣ ስለ እምነትና ከዲያብሎስ ኃይል
የተዋጀነውን እኛን እንዲከላከልልን ለመንፈስ ቅዱስ የጸለይን ብንሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ
እንዲፈጸምም መጸለይ ይገባናል። እነዚህን የከበሩ ሀብቶች አጥብቀን ለመያዝ ከሞከርን

[172] በጀርመንኛ ፓርቱከን - ቃል በቃል «ትንሽ ምጽዋት»።
[173] ማቴዎስ 6፡33፤ ሉቃስ 12፡31።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጸሎቶች እንዳይፈጸሙ ትግላችንን ለማደናቀፍና ለማጨናገፍ ከሚደፍሩ
ሁሉ የሚደረጉ አስገራሚ ድብደባዎችንና ጥቃቶችን መታገሥ ይገባናል::
62 ዲያብሎስ የልመናዎችን መፈጸም የሚቃወምበትና የሚያስተጓጉልበት ስልት በማንም
ሊታመን የማይችል ነው:: ማንኛውም ሰው በትክክል ሲያስተምር ወይም ሲያምን ማየቱን
ሊታገሠው አይችልም:: እጅግ በጣም በማይረቡ ሰበቦች ምክንያት ተሸፍነው በእግዚአብሔር
ስም የተከበሩት ሐሰቶቹና አስጸያፊ ርኵሰቶቹ ከነሙሉ አሳፋሪነታቸው ሲወጡበትና
ሲጋለጡበት፣ እርሱ ራሱ ከሰዎች ልብ ተገፍቶ ሲወጣና መንግሥቱ ሲፈርስበት ከልክ በላይ
ያመዋል:: ስለዚህ ዲያብሎስ እንደ ተቈጣ ጠላት ዓለምንና የገዛ ሥጋችንን እንኳ ሳይቀር እንደ
ተባባሪዎቹ አስከትቶ ተገዢዎቹን ሁሉ እየመራ ባለው ኃይልና ብርታት ሁሉ ያጓራል፤
63 ይደነፋል:: የእግዚአብሔርን ቃል አምነንና ተቀብለን እንኳ ሥጋችን በራሱ ርኵስና ወደ ክፋት
ያዘነበለ ነው:: ዓለምም ራሱ ጠማማና ተንኰለኛ ነው:: እዚህ ላይ እኛን ለማደናቀፍ፣ ለማሸሽ፣
አቅም ለማሳጣት፣ አንድ ጊዜ እንደ ገና ከኃይሉ ሥር ሊያደርገን እያራገበና እያቀጣጠለ
64 እነዚህን ይቀሰቅሳቸዋል:: ብቸኛ ዓላማው፣ ፍላጎቱና ዐሳቡ ይህ ነው:: ለዚህ ዓላማውም ሊያስብ
የሚችላቸውን ጥበቦች፣ ማታለያዎች፣ መንገዶችና ዘዴዎችን ሁሉ በመጠቀም ቀንና ሌት ያለ
ዕረፍት ይሠራል::

65 ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች መሆን የምንፈልግ ዲያብሎስን ከመላእክቱ ሁሉ ጋር[174] እና
ዓለምን እንደ ጠላቶቻችን መቀኈጠር እና ማናቸውንም የተቻላቸውን መከራና ሐዘን
እንደሚያመጡብን በእርግጥ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባናል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር
ቃል በሚሰበክበት፣ ተቀባይነት ከሚያገኝበት ወይም ከሚታመንበትና ፍሬ ከሚያፈራበት ቦታ፣
ቅዱሱና የከበረው መስቀልም ሩቅ አይሆንም:: ማንም ሰው ሰላም እንደሚኖረው ዐያስብ፤
ይልቁን በምድር ላይ ያሉትን ሁሉ፦ ንብረቶች፣ ክብር፣ ቤትና እርሻ፣ የትዳር ጓደኛና ልጆች፣
66 አካልና ሕይወትን መሥዋዕት ማድረግ ይገባናል:: እንግዲህ ይህ ማለት ምንም ነገር ቢደርስብን
በትዕግሥት በመቀበልና የሚወሰዱብንንም ነገሮች ሁሉ በመተው ጸንተን መቆም ይገባናል
ማለት ስለ ሆነ ይህ ሥጋችንንና አሮጌውን ፍጥረት ያሳዝናቸዋል::

67 ስለሆነም እንደ ሌላ ማናቸውም አጋጣሚ በዚህም ምክንያት ያለማቋረጥ እንዲህ ብሎ
መጸለይ ያስፈልጋል፤ «ውድ አባት ሆይ፣ የዲያብሎስ ወይም የጠላቶቻችን ፈቃድ አይደለም፤
ቅዱስ ቃልህን የሚያሳድዱና የሚያፍኑ ወይም መንግሥትህን ከመምጣት የሚከለክሉ ፈቃድ
አይደለም፤ ያንተ ፈቃድ ትሁን:: በዚህ ምክንያት ደግሞ የትኛውንም ዓይነት መከራ መቀበል
ቢኖርብን ደካማው ሥጋችን እንዳይሸነፍ ወይም በድካም ወይም በስንፍና እንዳይሰናከል
በትዕግሥት እንድንሸከመውና ድል እንድንነሣው ስጠን::»

68 በእነዚህ ሦስት ልመናዎች ራሱን እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በጣም ቀላል
በሆኑ መንገዶች እንደተገለጹባቸው ተመልከት፤ ይህ ሁሉ የሆነው ለእኛው ጥቅም ነው:: ያለ
እኛ ሊደረግ የሚገባው ነገር በእኛም እንዲደረግ በምንጠይቅበት ጊዜ እላይ እንደጠቀስነው
የምንጸልይበት ጉዳይ እኛን ብቻ የሚመለከት ይሆናል:: ያለ እኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ስም
በራሱ ቅዱስ እንደ ሆነና መንግሥቱም እንደምትመጣ ሁሉ ወንጌሉን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት
በሚያደርጉት ሙከራ ዲያብሎስና ሠራዊቱ ሁሉ በተቃዋሚነት ማዕበል ቢያስነሡና በቊጣ
ቢነሣሡም ፈቃዱ ትፈጸማለች፤ ታሸንፍማለች፤ ነገር ግን ለገዛ ራሳችን ስንል ዲያብሎስና
ሠራዊቱ ቢቈጡም እንኳ ምንም እንዳያከናውኑ በሁከትና በስደት ሁሉ ፊት ለእግዚአብሔር
ፈቃድ ተገዝተን ጸንተን እንድንቆይ የእርሱ ፈቃድ በመካከላችን እንድትፈጸም መጸለይ
ይገባናል::

69 ዲያብሎስ[175] ጳጳሳት፣ አምባገነኖችና መናፍቃን ወንጌላችንን ለመቃወም ሊያደርጉ
የሚችሉትን ሁሉ ለመመለስና ለማሸነፍ እንደዚህ ዓይነት ጸሎት መከላከያችንና ምሽጋችን
ሊሆን ይገባል:: ሁሉም በንዴት ይጡፉና እጅግ በጣም የከፋውን ነገር ያድርጉ፤ ፈቃዳቸውና
አድማቸው እንዲያሸንፍ እንዴት እንደሚያፍኑንና እንደሚያጠፉን ያሴሩና ያቅዱ:: በዚህች

[174] ስለ ዲያብሎስ መላእክት ማቴዎስ 25:41 ተመልከት::
[175] የ1538 የዊተንበርግ እትም ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) «ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት» የሚል ይጨምራሉ::

አጭር ልመና የታጠቁ አንድ ወይም ሁለት ክርስቲያኖች ዲያብሎስና ሠራዊቱ ቢወድቁባቸው
70 የሚደቁባቸው መከላከያ ይሆኑናል። ምንም ያህል ኩሩ፣ ጽኑና ኃይለኛ እንደ ሆኑ ቢያስቡም የዲያብሎስና የጠላቶቻችን ፈቃድና ዓላማ እንደሚከሽፍና ከንቱ እንደሚሆን፣ ሊሆንም እንደሚገባው ማወቅ መጽናናታችንና ትምክህታችን ነው፤ ምክንያቱም ፈቃዳቸው ካልተቀጨና ካልተጨናገፈ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ልትጸና ወይም ስሙ ሊቀደስ አይችልም።

*አራተኛው ጸሎት*

71 «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።»

72 እዚህ ላይ ትንሿን የዳቦ ቅርጫት ማለትም ለአካላችንና ለምድራዊ ሕይወታችን የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንመለከታለን። ይህ ጸሎት አጭርና ቀላል፣ ነገር ግን ሁሉንም ነገር የሚያጠቃልል ቃል ነው። «ለዕለት እንጀራ» ስትጸልዩ የዕለት እንጀራ እንዲኖራችሁና እንድትደሰቱበት ለሚያስፈልጋችሁ ለማንኛውም ነገርና በተቃራኒው እንዳትደሰቱበት ጣልቃ የሚገባና የሚያደናቅፍ ማናቸውንም ነገር በመቃወም ትጸልያላችሁ። ስለሆነም ምድጃውንና የዱቄት ዕቃውን ብቻ ሳይሆን የዕለት እንጀራችንንና በሕይወት የሚያቆዩ አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ የሚያስገኙትንና የሚያቀርቡልንን ሰፋፊ እርሻዎችንና መላውን ምድር ጭምር እንዲያካትቱ ዐሳቦቻችንን ሰፋ ማድረግና ማሳደግ ይገባችኋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እህሉ እንዲበቅል ባያደርግ፣ መስክ ላይ ባይባርከውና ባይጠብቀው ኖሮ ገበታ ላይ የምናስቀምጠው ወይም ከመጋገሪያ የምንወስደው ቀሩራሽ ዳቦ በጭራሽ ሊኖረን አይችልም ነበር።

73 በአጭሩ ለማስቀመጥ ይህ ልመና በዚህ ዓለም ላይ ለመላው ዘመናችን የሚጠቅመንን ማናቸውንም ነገር ያካትታል፤ ምክንያቱም ለእርሱ ሲባል ብቻ ነው የዕለት እንጀራ የሚያስፈልገን። እዚህ ላይ ሕይወታችን ምግብ፣ ልብስና[176] ለአካላችን የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮች ብቻ ሳይሆን በዕለታዊ ሥራችንና በመካከላቸው ከምንኖረውና ከምንመላለሰው ሰዎች ጋር በማናቸውም ዓይነት ጉድለቶች ሰላምና ስምምነትም ያስፈልጉታል። በአጭሩ የቤት ውስጥ፣ ማኅበራዊ ወይም ፖለቲካዊ[177] ጉዳዮችን ሥርዓት መያዝን የሚመለከት ማንኛውንም ነገር ማለት ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁለቱ ግንኙነቶች ጣልቃ ሲገባባቸውና እንደሚገባቸው በተገቢ መልኩ ከመሥራት በሚከለከሉበት ቦታ ለሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችም ጣልቃ ይገባባቸዋል፤
74 ሕይወት ራሷም ለምንም ያህል ጊዜ ተጠብቃ መቆየት አትችልም፤ በእርግጥም ከሁሉ ይበልጥ ለኑሮአችን የሚያስፈልገው ለባለ ሥልጣናትና ለመንግሥት መጸለይ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የዕለት እንጀራችንንና የዚህን ዓለም ሕይወት ምቾቶች ሁሉ በዋናነት የሚያዘጋጅልን በእነርሱ አማካይነት ነው። እግዚአብሔር የተረጋጋና ሰላማዊ መንግሥት ካልሰጠ ን ከእርሱ የተትረፈረፉ መልካም ነገሮችን ሁሉ የተቀበልን ቢሆንም እንኳ የትኞቹንም ጠብቀን ማቆየት ወይም ያለ ሥጋት በደስታ ልንጠቀምባቸው አንችልም፤ ምክንያቱም ክፍፍል፣ ብጥብጥና ጦርነት ባየለበት በእዚያ ስፍራ ላይ የዕለት እንጀራችን ይወሰድብናል ወይም ቢያንስ ይቀነስብናል።

75 በመሆኑም በልዑላን ኃላፊነት አማካይነት የጥበቃና የሰላም ተጠቃሚዎች መሆናችንንና ያለ እነርሱ የዕለት እንጀራና ያልተቋረጠ በረከት ሊኖረን እንደማይችል ልዑላንና አገልጋዮቻቸውን ለማስታወስ የየትኛውም ቀና ልዑል ምስል በቀሩራሽ ዳቦ[178] መለያ አርማው

[176] 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡8 ተመልከት፤ «ምግብና ልብስ ካለን ይበቃናል፤» እስከ 1541 ሉተር ያንን ምንባብ እዚህ ላይ እንደሚያደርገው *Futter und Decke ፉተር ኡንድ ደከ* «መመገብ እና መሸፈን» ብሎት ነበር፤ ከ1541 በኋላ ግን *Nahrung und Kleider ናህሩንግ ኡንድ ክሌይደር* «ምግብ እና ልብስ» በማለት ተርጉሞታል።

[177] ሉተር በመካከለኛው ዘመን ማኅበራዊ ቃል መሠረት ኅብረተ ሰብ በሦስቱ ማለትም በቤተ ሰብ፣ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች እንደተዋቀረ ዘወትር ያስብ ነበር።

[178] በ*ታኅሣሥ* 15/1528 (WA 30/1: 103,22-104,2; LW 51:177) በትልቁ ክርስትና ትምህርት ስብከቱ ሉተር የንጉሥ ነገሥቱ ወይም የልዑሉ ምስል በዳቦው ቁራሽ ላይ መቀረጽ አለበት በማለት ተቃራኒውን ደግፎአል።

ከአንበሳ[179] ወይም ከጤና አዳም ጉንጉን[180] ይልቅ ቢጌጥ ወይም ደግሞ ቀኍሽ ጳቦ በሳንቲሞች
ላይ ቢቀረጽ[181] ተስማሚ ይሆን ነበር። መሪዎች ክብር ሁሉ ይገባቸዋል፤ በእነርሱ አማካይነት
ያለንን ንብረት በሰላምና በጸጥታ እንደምንደሰትበት አድርገን እኛ ለእነርሱ ያለብንን ግዴታዎች
ልንፈጽምና ልናገለግላቸው እንዲሁም የምንችለውን ሁሉ ልናደርግላቸው ይገባናል። ምክንያቱም
ከእነርሱ ውጪ አንዲት ሳንቲም እንኳ ማስቀመጥ አንችልም። በተጨማሪም በእነርሱ
አማካይነት እግዚአብሔር አሁንም የበለጠ በረከቶችንና መልካም ነገሮችን እንዲሰጠን ተገንዝበን
ልንጸልይላቸው ይገባናል።
76 ይህ ጸሎት በምድር ላይ ያሉ ግንኙነቶችን ሁሉ በማጠቃለል እንዴት እንደሚሸፍን
በጣም ባጭሩ እንዘርዝር፤ አንድ ሰው ከዚህ ጸሎት የሚያካትታቸውን ነገሮች ሁሉ በበርካታ
77 ቃላት እየዘረዘረ ከዚህ ውስጥ ረዥም ጸሎት ማዘጋጀት ይችላል። ለምሳሌ እግዚአብሔር
ምግብና መጠጥ፣ ልብስና መጠለያ፣ እርሻ፣ ቤተ ሰብና ጤናማ አካል እንዲሰጠን፣ በተጨማሪም
የእርሻው እህልና ፍራፍሬ እንዲያፈራና ብዙ ምርት እንዲሰጥ እንዲያደርግ፣ ቤታችንን
በመልካም እንድናስተዳድር እንዲረዳንና መልካም የትዳር ጓደኛ፣ ልጆችና አገልጋዮች እንዲሰጠ
ንና እንዲጠብቅልን፣ ምንም ይሁን ምን ሥራችንን፣ ሙያችንን ወይም መደበኛ ተግባራችንን
እንዲያበለጽግልንና እንዲያቃናልን፣ ታማኝ ጎረቤቶችና መልካም ጓደኞች እንዲሰጠን ወዘተ.
መለመን እንችላለን። እንደገናም በመልካም እንዲያስተዳድሩ ለንጉሡ ነገሥቱ፣ ለነገሥታትና
ለባለ ሥልጣናት በተለይ ደግሞ ለልዑላን፣ ለአማካሪዎች ሁሉ፣ ለሕግ ባለ ሥልጣኖችና
ለአስተዳዳሪዎች ጥበብ፣ ብርታትና ብልጽግናን እንዲሰጣቸው፣ በቱርኮችና[182] በጠላቶቻችን ሁሉ
ላይ ድል አድራጊ እንዲሆኑ፣ አገልጋዮቻቸውና በአጠቃላይ ሕዝባቸው በታዛዥነት፣ ሰላምና
78 ስምምነት በአንድነት እንዲኖሩ እንዲያደርጋቸው ልንለምን እንችላለን። በተጨማሪም
አካላችንንና ኑሮአችንን ከሚጎዳ ማዕበልና በረዶ፣ እሳትና ጎርፍ፣ ከመርዝ፣ ከቸነፈርና ከከብት
መቅሰፍት፣ ከጦርነትና ከደም መፋሰስ፣ ከረሀብ፣ ከጨካኝ አውሬዎችና ክፉ ሰዎች ወዘተ.
79 እንዲከልለን ልንለምን እንችላለን። እነዚህ መልካም ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሚመጡና
እነርሱንም ለማግኘት መጸለይ እንደሚገባን ለሰው ሁሉ አጥብቆ ማሳሰብ መልካም ነው።
80 በተለይ ግን ይህ ጸሎት በተቃራኒነት ያነጣጠረው በአጠቃላይ ዓላማውና ፍላጎቱ
ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸውን ሁሉ መውሰድ ወይም ማስተጓጎል በሆነው በዋናው ጠላታችን
በዲያብሎስ ላይ ነው። እርሱ ሰዎችን በውሸቶቹ ለማታለልና ከኃይሉ ሥር ለማምጣት መንፈሳዊ
ሥርዓትን በማሰናከልና በመገልበጥ አይረካም፤ ነገር ግን በምድር ላይ የየትኛውንም ዓይነት
መንግሥት ወይም የተከበሩና ሰላማዊ ግንኙነቶች መመሥረትንም ይከላከላል፤ ያስተጓጉላል።
ለዚህ ነው እጅግ በጣም ብዙ ጠብ፣ ግድያ፣ ተቃዋሚነትንና ጦርነትን የሚያመጣው፤
81 ሰብሎችንና ከብቶችን ለማጥፋት ማዕበልና በረዶ የሚልከው፤ አየሩን የሚመርዘው፤ ወዘተ.
በአጭሩ የትኛውም ሰው ከእግዚአብሔር ቀኍሽ ጳቦ እንኳ መቀበሉና እርሷንም በሰላም
መብላቱ ያመዋል። ቢችልና ወደ እግዚአብሔር የሚደረገው ጸሎታችን ባይከለክለው ኖሮ
በተለይ የእግዚአብሔር ቃል ያለንና ክርስቲያኖች መሆን የምንፈልገውን በእርግጥ በእርሻ ውስጥ
አንዲት ገለባ፣ በቤት ውስጥ አንዲት ሳንቲም ወይም ሕይወታችን እንኳ ለአንዲት ተጨማሪ
ሰዓት አትኖርም ነበር።
82 ስለሆነም እግዚአብሔር በሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ እንዴት እንደሚንከባከበንና
ለዕለታዊ ሕይወታችን በታማኝነት የሚያስፈልጉንን እንደሚያዘጋጅልን ሊያሳየን እንደሚፈልግ
83 ትመለከታለህ። ለእኛ፣ ለክፉ ሰዎችና ወስላቶች እንኳ እነዚህን በረከቶች አትረፍርፎ ቢሰጠንና
ቢያዘጋጅልንም ከእርሱ እጅ እንደ ተቀበልናቸው እንድንገነዘብና ለእነርሱና ለእኛ ያለውን

---

[179] በማይሴን የድንበር ግዛት መለያ አርማ ላይ በወርቅ ላይ ጥቁር አንበሳ፣ በቱሪንጂያ ክፍለ ግዛት አርማ ላይ በሰማያዊ ላይ ቀይና ነጭ መስመር ያለበት አንበሳ፣ በሳክሰን መራጭ ግዛት አርማ ላይ የጤና አዳም ጉንጉን ይታይ ነበር። የሳክሰን እና የብሩንስዊክ [ደቡብ ክፍል] አርማዎች ላይ አንበሳ ይታያል።

[180] ለምሳሌ፣ በሳክሶኒ ግዛት መራጭ የክት ልብስ እጅጌ ላይ እንዳለው ዓይነት። የጤና አዳም በአውሮጠ በቀኍጥቋጦ መልክ ያለ ተክል ወይም እንጨት ሲሆን በመካከለኛውና ከዛም በኋላ ባሉት ዘመናት በአብዛኛው በመድኃኒትነት አገልግሏል።

[181] *Lowenpfenning*, «አንበሳ - ሳንቲም»፣ በሳክሶኒ እና ብሩንስዊክ Brunswick በኮታቸው እጅጌ ላይ የሚታይ የአንበሳ ቅርጽ ነው።

[182] ሉተር የክርስትና ትምህርቶችን እየጻፈ ባለበት ወቅት የቱርክ ወታደሮች ቅድስቲቱን የሮም ግዛት ለመቈጣጠር እያቀኑ ነበር፣ ከጥቂት ወራት በኋላ በመስከረም 1529 ቬናን ተቈጣጠሩዋት።

አባታዊ መልካምነቱን ለይተን እንድናውቅ ስለ እነርሱም እንድንጸልይ ይፈልጋል፡፡ በእርግጥም በየዕለቱ እንደምናየውና እንደምንለማመደው እርሱ እጁን ሲሰበስብ[183] ምንም ነገር አይበለጽግም
84 ወይም ምንም ያህል ጊዜ አይቆይም፡፡ አሁን እንኳ በዓለም በውሸተኛ ገንዘብ ምክንያት ማለትም በሕዝባዊ ግብይት፣ በንግድና በጉልበት ሥራ በየዕለቱ ብዝበዛና የአራጣ ብድር ድሆችን በግድየለሽነት በሚጨቁኑና የዕለት እንጀራቸውን በሚነሷቸው ሰዎች በኩል ምን ያህል ችግር አለ! እርግጥ ነው ይህንን መታገሥ ይገባናል፤ ነገር ግን በዝባዦችና ጨቋኞች የሆኑት የተለመደውን የቤተ ክርስቲያን የምልጃ ጸሎት[184] እንዳያጡ ይጠንቀቁ፤ ይህ የጌታ ጸሎት ልመና በተቃራኒነት እንዳይገለጥባቸው ይጠንቀቁ፡፡

*አምስተኛው ጸሎት*

85 «እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን»
86 ይህ ጸሎት የሚገናኘው ከአሳዛኝ መከረኛ ሕይወታችን ጋር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ያለንና የምናምን ብንሆንም ለፈቃዱ የምንታዘዝና የምንገዛ፣ በእግዚአብሔር ስጦታና በረከት በሕይወት የሚያኖሩን ብንሆንም ያለ ኃጢአት አይደለንም፡፡ አሁንም በየዕለቱ እንሰናከላለን፤ ክፉኛ በሚያበሳጩንና ትዕግሥት ለማጣት፣ ለቁጣና ለበቀል ወዘተ. ምክንያት በሚሆኑብን
87 ሰዎች መካከልና በዓለም ስለምንኖር እንተላለፋለን፡፡ በተጨማሪም በእንደዚህ ዓይነት ማቆሚያ የለሽ ግጭት ሁልጊዜ ጸንቶ መቆም እንዳይቻል በየአቅጣጫው የሚከበንና እንደሰማነው ጥቃቱን በቀደሙት ጸሎቶች ሁሉ ላይ በተቃራኒነት ያነጣጠረው ሰይጣን ከጀርባችን ይከታተለናል፡፡
88 እዚህ ላይ እንደ ገና እግዚአብሔርን መጥራትና «ውድ አባት ሆይ፣ ኃጢአታችንን ይቅር በለን» ብሎ መጸለይ እጅግ ያስፈልጋል፡፡ ያለ እኛ ጸሎትና ከጸሎታችን በፊት ኃጢአትን ይቅር ሳይል ቀርቶ አይደለም፤ ከመጸለያችን ወይም እንዲያውም ስለዚያ ከማሰባችን በፊት ከኃጢአት ይቅርታ በስተቀር ሌላ ነገር የሌለበትን ወንጌሉን ሰጥቶናል፤ እዚህ ላይ ዐሳቡ ለእኛ
89 ይህንን ይቅርታ ለይቶ ማወቅና መቀበል ነው፡፡ ምክንያቱም ዕለት ዕለት የምንኖርበት ሥጋችን በባሕርዩ በእግዚአብሔር የማይታመንና የማያምን፣ በየዕለቱ በቃልና በድርጊት በማድረግና ባለማድረግ ተግባራት ኃጢአት እንድንሠራ በክፉ ምኞቶችና ዘዴዎች ባለማቋረጥ ይቀሰቀሳል፡፡ በመሆኑም ሕሊናችን ዕረፍት የለሽ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔርን ቁጣና ቅርታ ይፈራና በወንጌሉ መጽናናትና መተማመኑን ያጣል፡፡ ስለዚህ ሕሊናችንን የሚያድሰውን መጽናናት ለማግኘት ወደዚህ ልመና ባለማቋረጥ መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡
90 ይህ አሠራር ትዕቢታችንን ለመግራትና ትሑታን ሆነን እንድንቆይ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሊያገለግል ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ይህንን መብት ለራሱ ብቻ ለይቶ ስላስቀመጠው ማንም ሰው በመልካምነቱ ቢመካና ሌሎችን ቢንቅ በዚህ ጸሎት ራሱን መመርመር፣ ይህንን ልመናም በሕሊናው እጅግ ከፍ ያለውን ስፍራ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ያኔ እርሱ ከሌሎች ምንም የበለጠ ጻድቅ አለመሆኑንና በእግዚአብሔር ፊት ሰዎች ሁሉ በጉልበታቸው ተንበርክከው
91 ይቅርታ ማግኘት በመቻላቸው ሊደሰቱ የሚገባቸው መሆኑን ይገነዘባል፡፡ ማንም ሰው በዚህ ሕይወት ይህ ይቅርታ በማያስፈልገው ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል አድርጎ ዐያስብ፡፡ በአጭሩ እግዚአብሔር ባለማቋረጥ ይቅር ካላለን የጠፋን ነን፡፡
92 በመሆኑም ይህ ልመና እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እንዳይቈጥርብንና በየዕለቱ እንደሚገባን እንዳይቀጣን ነገር ግን በቸርነቱ ሁሉንም ነገር እንዲያደርግልን፣ ቃል እንደ ገባልን ይቅር እንዲለንና በፊቱ በጸሎት ለመቆም ደስተኛና የተጽናና ሕሊና እንዲሰጠን በእርግጥም እግዚአብሔርን መማጸን ነው፡፡ ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የሠመረ ካልሆነና እንደዚህ ዓይነት መተማመን ላይ መድረስ ካልቻለ ለመጸለይ በጭራሽ አይደፍርም፡፡ ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት መተማመንና ደስተኛ ልብ ሊመጣ የሚችለው ኃጢአታችን ይቅር መባሉን በማወቅ ነው፡፡

---

[183] ምሳሌያዊ አገላለጽ፡፡

[184] በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ጊዜ የሚደረግ አጠቃላይ ጸሎት፡፡ ምሳሌያዊ አገላለጽ ሆኖ «ማኅበራዊ አክብሮትን ማጣት» የሚል ትርጉም አለው፡፡

93 ይሁን እንጂ አስፈላጊና አጽናኝ ሐረግ ተጨምሯል፤ «እኛ የበደሉንን ይቅር
እንደምንል»፤ ሁሉም ነገር ይቅር እንደ ተባለና እንደ ተተወ እግዚአብሔር ማስተማመኛ ቃል
ገብቶልናል፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው እኛም ባልንጀራችንን ይቅር ያልን እንደ ሆነ ብቻ ነው።
94 ምክንያቱም በየዕለቱ በእግዚአብሔር ላይ በጣም ብዙ ኃጢአት የምንሠራ ሲሆን እርሱ ግን
ሁሉንም በጸጋው ይቅር እንደሚለን እኛም የሚጎዳንን፣ የሚረብሸንንና፣ ኢፍትሐዊ ድርጊት
የሚፈጽምብንንና የሚጠላንን፣ የሚመቀኝንን ወዘተ. ጎረቤታችንን ሁልጊዜ ይቅር ማለት
95 ይገባናል። ይቅር ካላላችሁ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላችሁ ዐታስቡ። ሰዎችን ይቅር ካላችሁ
96 ግን በሰማይ ይቅር የመባላችሁ መጽናናትና ማረጋገጫ ይኖራችኋል። (እግዚአብሔር ይህን
ዋስትና የሚሰጠው ሙሉ በሙሉ በነጻ ነው እንጂ ይቅር በማለታችሁ ምክንያት አይደለም፤
ካልተደባለቀ ጸጋ የተነሣ ወንጌሉ እንደሚያስተምረው ያ የተስፋ ቃል ስለ ተገባለት ነው።) ነገር
ግን በሉቃስ 6፡37 ከዚህ ልመና ጋር ከሚስማማው የተስፋ ቃል ጎን ለጎን ለብርታታችንና
ለዋስትናችን ይሆን ዘንድ እንደ ምልክት ይህንን ቅድመ ሁኔታ አቁሟል፤ «ይቅር በሉ፤ ይቅርም
ትባላላችሁ።» ስለዚህ ክርስቶስ በማቴዎስ 6፡14 ከጌታ ጸሎት በኋላ ወዲያውኑ «ለሰዎች
ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና» በማለት
ይደግመዋል።
97 ስለዚህም በምንጸልይበት ጊዜ የተስፋ ቃሉን እንድናስታውስና፡- «ውድ አባት ሆይ፣
ለጥፋት ማካካሻ ማስተሰሪያ ማዘጋጀት በመቻሌ ወይም በመልካም ሥራዎቼ ምንም ነገር
የተገባኝ ሳይሆን የተስፋ ቃልህን በመስጠትህና በአንተ በራስህ እንደ ተነገረ የኃጢአት ይቅርታ
እወጃ ያህል የተረጋገጠ በማድረግ ማገተምህን በእርሱ ላይ ከማድረግህ የተነሣ ይቅር እንድትለኝ
በመጸለይ ወዳንተ እመጣለሁ» ብለን እንድናስብ ይህ ምልክት ከልመናው ጋራ ተያይዟል።
98 ውጪአዊ ምልክቶች በሆኑት በጥምቀትና በጌታ እራት ሊከናወን የሚችለውን ያህል ይህም
ምልክት ሕሊናችንን ለማበርታትና ደስ ለማሰኘት ተመሳሳይ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል።
በተጨማሪም ከሌሎቹ ምልክቶች በላይና ባሻገር ሁልጊዜ ከእኛ ጋር በማቆየት በየሰዓቱ
እንድንጠቀምበትና እንድንለማመደው በትክክል የተመሠረተልን ነው።

*ስድስተኛው ጸሎት*

99 «ወደ ፈተና አታግባን»
100 የምንለምናቸውን ስጦታዎች ሁሉ ጠብቆ ለማቆየትና በእነርሱም ለመጽናት ስለ ችግሩና
ስለሚጠይቀው ጥረት አሁን በቂ ነገር ሰምተናል። ይሁን እንጂ ይህ ያለ ውድቀትና ያለ
መሰናከል አይከናወንም፤ በተጨማሪም የኃጢአት ይቅርታና መልካም ሕሊና ያገኘን፣
የኃጢአታችንም ይቅርታ ሙሉ በሙሉ የታወጀልን ብንሆንም ሕይወት እንዲህ በመሆኗ አንድ
ሰው ዛሬ ይቆማል፤ እንዲሁም ነገ ይወድቃል። ስለዚህ ምንም እንኳ በዚህ ጊዜ ቅንና
በእግዚአብሔር ፊት በመልካም ሕሊና የምንቆም ብንሆንም እንድንወድቅ እንዳይተወን
ለመከራዎችና ለክፉ ፈተናዎች እንዳንሸነፍ እንደ ገና መጸለይ ይገባናል።
101 (በቀደሙት ጊዜያት ደቡብ ሳክሶናውያን «ቤኮሩንግ» *(Bekorunge)* ብለው የሚጠሩት)[185]
102 ክፉ ፈተና ሦስት ዓይነት ነው፤ የሥጋ፣ የዓለምና የዲያብሎስ። ምክንያቱም በሥጋ ስለምንኖርና
አሮጌው ፍጥረት በአንገታችን ላይ ተንጠልጥሎ ስለሚገኝ ነው፤ ለሥራ ይሰማራና በየዕለቱ ወደ
ርኩሰት፣ ስንፍና፣ ሆዳምነትና ሰካራምነት፣ ስስትና ማታለል፣ ባልንጀራችንን ወደ ማጭበርበርና
የአታላይነት ድርጊቶች በአጭሩ በተፈጥሮ ወደሚጣበቁብንና ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ
በመሆንና በምሳሌነታቸው፣ በምንሰማቸውና በምናያቸው ነገሮች ወደምንቀሰቀስባቸው ክፉ
ምኞቶች ሁሉ ይስበናል። ይህ ሁሉ ብዙ ጊዜ የዋህ ልብን እንኳ ያቈስላል፤ እንደ እሳት
ያቀጣጥላል።

---

[185] በጥንታዊው በደቡብና ማዕከላዊ ጀርመን በሚነገረው ጀርመንኛ የጌታ ጸሎት ትርጒሞች የተለመደው ይህ *ኮሩንጋ (korunga)* ወይም *ቢኮሩንጋ (bikorunga* )የሚለው ቃል እስከ ዛሬም በሰሜን ጀርመን ቀበሌኛም ጥቅም ላይ ይውላል። ሉተር ቃሉን «በጣም ውብ የሆነ ጥንታዊ ጀርመንኛ» ይለዋል፤ ሉተር ሳክሰን ሲል ደቡብ ሳክሰን ማለቱ ነው። በ16ኛው ምእት ዓመት በዊተንበርግ የሰሜን ጀርመን ቀበሌኛ ይነገር ነበር።

103 *ቀጥሎም በቃልና በድርጊት የሚያጠቃን፣ ወደ ቍጣና ትዕግሥት የለሽነት የሚነዳን ዓለም ይመጣል። በአጭሩ በውስጡ ምቾትን፣ ክብርን፣ ዝናንና ኃይልን ከመውደድ ጋር ከጥላቻና ከቅንዓት ጋር ተያይዞ ጠላትነት፣ ጥቃትና ፍትሕ የለሽነት፣ ቃልን ማጠፍ፣ በቀል፣ መራገም፣ መሳደብ፣ ሐሜት፣ እብሪትና ትዕቢት በቀር ሌላ ነገር የለበትም። ምክንያቱም ማንም ሰው የሁሉ ታናሽ ለመሆን ፈቃደኛ አይደለም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ላይኛው ወንበር ላይ መቀመጥና በሁሉም የሚታይ መሆንን ይፈልጋል።*

104 *ከዚህ በኋላ በሁሉም አቅጣጫ ወጥመድ የሚያዘጋጅልንና የሚያስቸግረን በተለይ ግን ሕሊናና መንፈሳዊ ጒዳዮችን በሚመለከት ቦታ ላይ የተቻለውን ሁሉ የሚያደርገው ዲያብሎስ ይመጣል። የእርሱ ዓላማ የእግዚአብሔርን ቃልና ሥራዎቹን ሁሉቱንም እንድናቃልልና እንድንንቅ ማድረግ፣ ከእምነት፣ ተስፋና ፍቅር መነጠል፣ ወደ አለማመን፣ ሐሰተኛ ዋስትናና ድንዳኔ መጎተት ወይም ደግሞ በተቃራኒው ወደ ተስፋ መቍረጥ፣ ክህደት፣ በእግዚአብሔር ላይ በድፍረት ወደ መናገርና ወደ ማይቈጠሩ ሌሎች አስጸያፊ ኃጢአቶች እኛን መንዳት ነው። እነዚህ ወጥመዶችና መረቦች ናቸው፤ በእርግጥም በሥጋና በደም ሳይሆን በዲያብሎስ ወደ ልባችን የሚወረወሩ እውነተኛዎቹ መርዛማ «የሚንበለበሉ ፍላጻዎች»*[186] *ናቸው (ኤፌሶን* 6፡16)።

105 *አንድ በአንድ ቢመጡም እንኳ እነዚህ ማንኛውም ክርስቲያን ሊቋቋማቸው የሚገባ ታላላቅ አሳዛኝ አደጋዎችና ክፉ ፈተናዎች ናቸው። በሁሉም አቅጣጫ በምንጠቃበት፣ በምንታደንበትና በምንጨነቅበት በዚህ የረከሰ ሕይወት እስከ ቆየን ድረስ እንዳንደክምና እንዳንዝል፣ ወደ ኃጢአት፣ እፍረትና አለማመን ተመልሰን እንድንወድቅ እግዚአብሔር እንዳይተወን በየሰዓቱ የመጮኽና የመጸለይ ግዴታ አለብን። አለበለዚያ እጅግ በጣም ትንሿን ጥቃት እንኳ ለማሸነፍ የማይቻል ይሆናል።*

106 *እንግዲህ «ወደ ፈተና አለመግባት» ማለት መከራው ባይወገድም ወይም ባይጠናቀቅም እንኳ እግዚአብሔር ፈተናውን ለመቋቋም ኃይልንና ብርታትን እንዲሰጠን መለመን ነው። ምክንያቱም በሥጋ እስከኖርንና ዲያብሎስ በዙሪያችን እስከ ዞረ ድረስ ክፉ ፈተናዎችንና አታላይ መስህቦችን ማንም ማምለጥ አይችልም። ጥቃቶችን መታገሥና በእነርሱም የምንቸገር ቢሆንም ልንቀበላቸው እንጂ ልናመልጣቸው አንችልም፤ ነገር ግን እንዳንወድቅባቸውና በእነርሱም እንዳንዋጥ እንጸልያለን።*

107 *ስለዚህ መፈተን ለፈተናው ከመስማማት*[187] *ወይም «እሺ» በማለት ከመሸነፍ ፍጹም
የተለየ ነገር ነው። በሁላችንም ላይ የሚደርሰው ፈተና በተመሳሳይ ደረጃ ባይሆንም ሁላችንም
ፈተና በሕይወታችን ልናይ ይገባል። አንዳንዶች ከሌሎች ይበልጥ ተደጋጋሚ፣ ኃይለኛና ክፉ
ፈተናዎች ይገጥሟቸዋል። ለምሳሌ ወጣቶች በዋናነት በሥጋ ይፈተናሉ። ጎልማሶችና በዕድሜ
የገፉ ሰዎች በዓለም ይፈተናሉ። ስለ መንፈሳዊ ጒዳዮች ግድ የሚላቸው ሌሎች ማለትም*
108 *ጠንካራ ክርስቲያኖች በዲያብሎስ ይፈተናሉ። ነገር ግን ከፈቃዳችን ጋር ተቃራኒ እስከ ሆነና
እንዲወገድልን የምንፈልግ እስከሆንን ድረስ በፈተናው ገጠመኝነት ብቻ ልንጎዳ አንችልም።
በሕይወታችን ባይገጥመን ኖሮማ ፈተናም ተብሎ ሊጠራ አይችልም ነበር። ለፈተናው እጅ
መስጠት ግን ነጻ ልጓም መስጠትና ፈተናውን አለመቋቋም ወይም ለሚቃወመው እርዳታ
አለመጸለይ ነው።*

109 *በተመሳሳይ ሁኔታ እኛ ክርስቲያኖች ላልተቋረጡ ጥቃቶች የታጠቅንና የተዘጋጀን መሆን ይገባናል። ከዚያም ዲያብሎስ ከእኛ ሩቅ የሆነ ይመስል አደጋ እንደሌለብን ሆነን ያለ ጥንቃቄ መሽከርከር አይገባንም፤ ነገር ግን የእርሱን ጥቃት ሁልጊዜ መጠበቅና መመከት ይገባናል። በአሁኑ ጊዜ በንጽሕና የምኖር፣ ታጋሽ፣ ቸርና በእምነት ጽኑ ብሆንም ዲያብሎስ በዚህ ሰዓት ልቋቋመው የማልችለውን ፍላጻ ወደ ልቤ ምናልባት ይልካል። ምክንያቱም እርሱ*

---

[186] **ኤፌሶን** 6፡16።

[187] **ሉተር** "An *Exposition of the Lord's Prayer for Simple Laymen" (1519)* (WA 2:124,26-29; LW 42:73) **በሚለው መጽሐፍ «የመናንያን መጽሐፍ ውስጥ [ማለትም በጀሮም በተጻፈው** *Lives of the Hermits* ] **አንድ ወጣት ወንድም እንዴት ከክፉ ዐሳቦቹ መገላገል እንደናፈቀ እናነባለን፤ በዕድሜ የገፋው አባት፡- 'ውድ ወንድም ወፎች ከራስህ በላይ እንዳይበሩ መከልከል አትችልም፤ ነገር ግን በፊትህ ላይ ጎጇቸውን እንዳይሠሩ ልታደርጋቸው በእርግጥ ትችላለህ፤'» ሲል ጽፏል፤ ሉተር ይህንን ምሳሌ አዘውትሮ በጽሑፎቹ ውስጥ ተጠቅሞበታል።**

በጭራሽ የማያቆም ወይም የማይደክም ጠላት ስለ ሆነ ነው፤ ይኸውም አንዱ ጥቃት ሲያቆም
ዐዳዲሶች ሁልጊዜ ስለሚነሡ ነው።

110 በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ብቸኛ ረድኤታችንና መጽናኛችን በጌታ ጸሎት መሸሸግና
ከልባችን እግዚአብሔርን «ውድ አባት ሆይ፣ እንድጸልይ አዘኸኛል፤ ከፈተና የተነሣ አልውደቅ»
111 ብለን መማጸን ነው። ከዚያ በኋላ ክፉው ፈተና ሲያቆምና በመጨረሻም ሽንፈቱን ሲቀበል
ታያላችሁ። አለበለዚያ በገዛ ራሳችሁ ዐሳቦችና ብቃቶች ራሳችሁን ለመርዳት ከሞከራችሁ
ሁኔታውን ታባብሱትና ለዲያብሎስ የሰፋ ቀዳዳ ትሰጡታላችሁ፤ ምክንያቱም እርሱ ያለው
የእባብ ጭንቅላት ነው፤ ሾልኮ ሊገባ የሚችልበት አንድ ቀዳዳ ካገኘ መላ አካሉ በማይቋቋሙት
ሁኔታ ወደ ውስጥ ዘልቆ ይገባል። ነገር ግን ጸሎት ሊቋቋመውና መልሶ ሊያባርረው ይችላል።

*የመጨረሻው ጸሎት*

112 «ከክፉ አድነን እንጂ አሜን።»
113 በግሪኩ[188] ይህ ጸሎት፡- «ከክፉው ወይም ከተንኮለኛው አድነን ወይም ጠብቀን» ሲል
ይነበባል። የጸሎታችን ፍሬ ነገር በአጠቃላይ በቀንደኛ ጠላታችን ላይ እንዲያነጣጥር ልመናው
ዲያብሎስ የክፋት ሁሉ ጥርቅም መሆኑን የሚናገር ይመስላል። ምክንያቱም የምንለምነውን
ሁሉ፡- የእግዚአብሔር ስም ወይም ክብር፣ የእግዚአብሔር መንግሥትና ፈቃድ፣ የዕለት
እንጀራችን፣ መልካምና ደስተኛ ሕሊና፣ ወዘተ. የሚያደናቅፍ እርሱ ስለ ሆነ ነው።
114 ስለዚህ በመጨረሻ ሁሉንም ነገር፡- «ውድ አባት፣ ሆይ ይህን ክፉ ዕድል ሁሉ
115 እንድናስወግድ እርዳን» በማለት እንጠቀልለዋለን። የሆነ ሆኖ ይህ ጸሎት በዲያብሎስ
መንግሥት ሥር ሊወድቅብን የሚችለውን ክፉ ሁሉ ድህነት፣ እፍረት፣ ሞትና ባጭሩ በምድር
ላይ ሊቈጠሩ እስከማይችሉ ድረስ የበዙትን አሳዛኝ መከራዎችንና የልብ ሐዘኖችን ሁሉ
ያካትታል። ምክንያቱም ዲያብሎስ ሐሰተኛ ብቻ ሳይሆን ነፍሰ ገዳይም ጭምር[189] በመሆኑ
(ዮሐንስ 8፡44) ባለማቋረጥ ሕይወታችንን ይፈልጋል፤ ቍጣውንም አደጋዎችንና ጉዳቶችን
በአካላችን ላይ በማምጣት ያፈሰዋል። አንዳንዶችን አድቅቋቸዋል፤ ሌሎችን ወደ እብድነት
ነድቷል፤ ጥቂቶችን አስጥሟቸዋል፤ በርካቶችን ራስን ወደ መግደል ወይም ሌሎች አስፈሪ
116 አደጋዎች አድርሶአቸዋል፤ ስለዚህ ይህንን ቀንደኛ ጠላታችንን በመቃወም ባለማቋረጥ ከመጸለይ
በቀር በምድር ላይ የምንሠራው ምንም ነገር የለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ካልደገፈን
ለአንዲት ሰዓት እንኳ ከእርሱ ተጠብቀን ደኅና አንሆንም።
117 ስለዚህ አካላዊ ደኅንነታችንን እንኳ ለሚያጠቃ ለማንኛውም ነገር ወደ እርሱ
እንድንጸልይ፣ እግዚአብሔር ከሌላ ከማንም ሳይሆን ከእርሱ ብቻ እርዳታ እንድንፈልግና
118 እንድንጠብቅ እንደሚፈልግ ታያላችሁ። ነገር ግን ይህንን ጸሎት በመጨረሻ ያስቀመጠበትም
ምክንያት ከክፉ ሁሉ እንድንጠበቅና እንድንድን ካስፈለገ መጀመሪያ ስሙ በእኛ መቀደስ፣
መንግሥቱ በመካከላችን መምጣትና ፈቃዱ መፈጸም ስለሚገባቸው ነው። በመጨረሻ
ከኃጢአትና ከእፍረት ከሚጎዳን ወይም ከሚያቈስለን ከማንኛውም ነገር ይጠብቀናል።
119 ስለዚህ ስለ አለመጸለይ ሰበብ በጭራሽ እንዳይኖረን እግዚአብሔር ሁልጊዜ
የሚያውኩንን መከራዎችን ሁሉ ባጭሩ በፊታችን አስቀምጧል። የጸሎት ውጤታማነት ግን
ለጸሎት «አሜን» ማለትን በመማራችን የሚገኝ ነው፤ ማለትም ጸሎታችን በእርግጥ እንደ
120 ተሰማና እንደ ተመለሰ አለመጠራጠር ነው። ይህ ቃል[190] እንደ ዕድል በአጋጣሚ በማይጸልየው
ነገር ግን ልመናዎቹን ለመመለስ ቃል በመግባቱ እግዚአብሔር እንደማይዋሽ በሚያውቀው ሰው

---

[188] የትልቁ የክርስትና ትምህርት የመጀመሪያ እትም «በዕብራይስጡ» የተሳሳተ በማለት ይነበባል፤ ይህ ስሕተት በቀጣይ እትሞች ላይ ተስተካክሏል።

[189] ዮሐንስ 8፡44።

[190] ሉተር "An *Exposition of the Lord's Prayer for Simple Laymen" (1519)* (WA 2:126,29-31; LW 42:76) በሚለው መጽሐፍ «'አሜን' የምትለዋ ትንሽ ቃል የተገኘችው ከዕብራይስጥ ወይም ከአይሁዳውያን ነው፤ በጀርመንኛ አንድ ነገር እጅግ በጣም የተረጋገጠ እውነት ነው ማለት ነው። ይህ ቃል በማንኛውም የልመና ጸሎት ሊኖረን የሚገባውን እምነት እንደሚገልጽ ማስታወሱ መልካም ነው፤» ሲል ጽፏል።

ዘንድ ጥያቄ የሌለበት የእምነት ቃል እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። እንደዚህ ዓይነት እምነት
ሲጎድል ምንም እውነተኛ ጸሎት ሊኖር አይችልም።
121 ስለዚህ ሰዎች በሙሉ ልባቸው «አዎን» ማለትን ለመጨመርና እግዚአብሔር
ጸሎታቸውን እንደ ሰማ በእርግጠኛነት ለመደምደም ባይችሉ አደገኛ መታለል ነው። ከዚያ
ይልቅ «እግዚአብሔር ጸሎቴን እንደ ሰማ እስከመካ ድረስ ለምን ደፋር መሆን ይገባኛል? እኔ
122 እንደ ሆንኩ ምስኪን ኃጢአተኛ ነኝ» በማለት በጥርጣሬ ውስጥ ይቆያሉ። ያ ማለት
እግዚአብሔርን እስኪንቁና እንደ ዋሽ አድርገው እስኪከሱት ድረስ ዓይናቸው ያለው
በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ሳይሆን በገዛ ሥራዎቻቸውና በብቃታቸው ላይ ነው ማለት
123 ነው። ስለዚህ ቅዱስ ያዕቆብ፡- «ማንም ቢጸልይ በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠ
ራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና ... ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ
አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው» እንደሚለው ተጠራጣሪዎች ምንም አይቀበሉም (ያዕቆብ
124 1፡6-7)። እነሆ፣ በከንቱ እንዳንጸልይ ወይም በምንም መንገድ ጸሎቶቻችንን መናቅ
እንደማይገባን እግዚአብሔር እርግጠኛ መሆናችንን የሚፈልገው ይህን ያህል ነው።

## አራተኛ ክፍል፡- ስለ ጥምቀት

1 አሁን የተለመዱ የክርስቲያን አስተምህሮ ሦስቱን ዐበይት ክፍሎች[191] ጨርሰናል።
አሁንም በክርስቶስ ስለ ተመሠረቱ ስለ ሁለቱ የጸጋ መሣሪያዎቻችን አንድ ነገር ማለት
ይገባናል። ምክንያቱም ቀደም ሲል ስለ እነርሱ የተሰጠ ምንም ትምህርት ያልነበረ መሆኑ
አሳዛኝ ቢሆንም ማንኛውም ክርስቲያን ስለ እነርሱ ቢያንስ የተወሰነና አጠር ያለ መሠረታዊ
ትምህርት ሊኖረው ይገባል፤ ምክንያቱም ያለ እነርሱ ማንም ክርስቲያን ሊሆን አይችልም።
2 በመጀመሪያ ወደ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በምንቀላቀልበት ጥምቀት ላይ በማተኮር
እንጀምራለን። ሰዎች በቀላሉ ሊረዱት እንዲችሉ ሥርዓት በተከተለ መንገድ ልንመለከተውና
ልናውቀው በሚያስፈልገን ነገር ላይ ራሳችንን እንገድባለን። ከሐሰተኞችና ከመናፍቃን እንዴት
ሊጠበቅና ሊከላከሉት እንደሚገባ ለሊቃውንቱ እንተወዋለን።
3 በመጀመሪያ ደረጃ ጥምቀት በተመሠረተበትና በጉዳዩ ላይ የሚባሉት ማናቸውም ነገር
ከሚዛመድባቸው ማለትም ጌታ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ [28፡19]፡-
4 ከሚላቸው ቃላት ጋራ ከሁሉ ይልቅ የምንተዋወቅ መሆን ይገባናል፤ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤
አሕዛብን አስተምሩ፤ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው»።[192]
5 በተመሳሳይ መልኩ በማርቆስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ [16፡16]፡- «ያመነ የተጠ
መቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» ብሎአል።
6 በመጀመሪያ ጥምቀት በሰዎች የተሠራ ወይም የተፈለሰፈ ነገር ሳይሆን ከመለኮታዊ
ምንጭ መሆኑን ማንም እንዳይጠራጠር እነዚህ ቃላት የእግዚአብሔር ትእዛዝና ድንጋጌ
መሆናቸውን ተመልከት። ዐሥርቱ ትእዛዛት፣ የእምነት መግለጫና የጌታ ጸሎት ከማንም ሰው
ምናብ የወጡ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር በራሱ የተገለጡና የተሰጡ ናቸው። እንደዚሁም ጥምቀት
ሰዋዊ ጨዋታ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር የተመሠረተ በመሆኑ ልመካበት እችላለሁ።
በተጨማሪም መጠመቅ እንደሚገባን አለበለዚያ እንደማንድን በከባድ ሁኔታና በጥብቅ ታዟል፤
በመሆኑም በግድየለሽነት የምናደርገው ወይም በክብረ በዓላት ቀናት እንደምንለብሰው ዐዲስ
7 ቀይ ኮት አድርገን ልናየውና ልንቈጥረው አይገባንም።[193] ጥምቀትን የላቀ፣ የከበረና ከፍ ያለ
አድርገን መቍጠራችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በአሁኑ ጊዜ ዓለም ጥምቀት ውጫአዊ
ነገር እንደሆነና ውጫአዊ ነገሮች ደግሞ ምንም እንደማይጠቅሙ በጩኸት በሚናገሩ የእምነት

[191] በጀርመንኛ *Häuptstück ሃኡፕትስተክ*፤ ሉተር *Häuptstück ሃኡፕትስተክ* የሚለውን ቃል በሁለት ትርጒም ማለትም "ዐበይት ክፍሎች" በሚለው ትርጒሙ እና በተጨማሪም "ዐበይት አንቀጾች" ወይም "እጅግ በጣም አስፈላጊ" በማለት ተጠቅሞበታል። የክርስትና ትምህርቱ መጽሐፍ የአሁኑ "ዐበይት ክፍሎች" ትርጒም በኑረምበርጉ ምዕራብ ጀርመንኛው *Kinderbüchlein ኪንደርቡክሌይን* የተገኘ ነው (1531)።

[192] የሉተር ትርጒም።

[193] ቀይ ኮት ለክብረ በዓል ጊዜ ተገቢ ልብስ ነበር።

8 ቡድኖች በመሞላትዋ ለውዝግቦቻችንና ለጦርነቶቻችን ዐቢይ ምክንያት ሆኖአል።[194] ነገር ግን
ምንም ያህል ውጪአዊ ምልክት ቢሆንም ልዩነት አያመጣም፤ ጥምቀትን ያቋቋሙ፣
የመሠረቱና ያረጋገጡ የእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ጸንተው ይኖራሉ። እግዚአብሔር
የመሠረተውና ያዘዘው ነገር ጥቅመ ቢስ ሊሆን አይችልም። ይልቁን ከውጪ ሊታይ ከሚችለው
9 አንጻር ሲታይ ምንም የማይረባ ቢመስልም እንኳ እጅግ በጣም የከበረ ነገር ነው። ርእሰ ሊቃነ
ጳጳሳቱ በደብዳቤዎቹና በትእዛዛቱ[195] የኃጢአት ስርየት ወረቀቶችን ሲያድልና መሠዊያዎችንና
አብያተ ክርስቲያናትን ከደብዳቤዎቹና ከማኅተሞቹ[196] የተነሣ ብቻ ሲያጸና ሰዎች እንደ ትልቅ
ነገር ይቈጥሩት የነበረ ከሆነ ጥምቀትን ደግሞ እግዚአብሔር ስላዘዘው እጅግ በጣም የበለጠና
ከሁሉ የከበረ አድርገን ልንቈጥረው ይገባናል። ከዚያ ይበልጥ ጥምቀት የሚከናወነው በእርሱ
ስም ነው። ስለዚህም ቃላቱ «ሂዱ አጥምቁ» «በራሳችሁ ስም» ሳይሆን «በእግዚአብሔር
ስም»ሲሉ ይነበባሉ።
10 በእግዚአብሔር ስም መጠመቅ በሰዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር በራሱ መጠመቅ ነው።
በሰዎች እጆች የሚከናወን ቢሆንም በእውነቱ የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ከዚህ ተጨባጭ
እውነት የተነሣ ከየትኛውም ሰው ወይም ቅዱሳን ሥራ እጅግ በጣም የላቀ ዋጋ ያለው መሆኑን
ሰው ሁሉ በቀላሉ ሊደመድም ይችላል። ሰው ከእግዚአብሔር ሥራ የሚበልጥ ምን ሥራ
መሥራት ይችላል?
11 እዚህ ላይ ግን ዲያብሎስ በሚታዩ ሐሰተኛ ነገሮች ሊያሳውረንና ከእግዚአብሔር ሥራ
አርቆ ወደ ገዛ ሥራችን ሊመራን ለሥራ ይሰማራል። አንድ የሒሳብ ዐዋቂ በርካታ ታላላቅና
አስቸጋሪ ሥራዎችን ሲሠራ እጅግ በጣም አስገራሚ ዕይታ ይፈጥራል፤ እኛ ሁላችን ደግሞ ለገዛ
12 ራሳችን ክንውኖችና ውዳሴ የሚገባቸው ምግባሮች የበለጠ ዋጋ እንሰጣቸዋለን። ቅዱሳት
መጻሕፍት እንደሚያስተምሩን ግን የሁሉንም መነኮሳት ሥራዎች ሁሉ በአንድ ቁልል ብንከምር
ምንም ያህል የከበሩና አብረቅራቂ መስለው ቢታዩ ልዩነት አያመጡም፤ እግዚአብሔር እንዲት
ገለባ እንዳነሣ ያህል እንኳ የከበሩና መልካም አይሆኑም። ለምን? ድርጊቱን የሚያከናውነው
እርሱ የበለጠ የከበረና የተሻለ ነውና። እዚህ ላይ አንድ ሰው ሌላውን ሰው የሚገመግመው እንደ
ሥራዎቹ ሳይሆን ሥራዎቹ ዋጋ እንዲኖራቸው በሚያደርገው ሰው መሠረት መሆን ይገባዋል።
13 ነገር ግን ጤነኛ ያልሆነ አእምሮ ወደ ፊት ይጣደፍና[197] ጥምቀት እኛ እንደምናደርጋቸው
ሥራዎች አብረቅራቂ ስላልሆነ ዋጋ እንደሌለው ይቈጥረዋል።
14 አሁን «ጥምቀት ምንድን ነው?» ለሚለው ጥያቄ ተገቢውን መልስ እንዴት
እንደምታዘጋጅ ልትረዳ ትችላለህ፤ ማለትም በቀላሉ ተራ ውሃ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃልና
ትእዛዝ ዐውድ የተቀመጠና በእነርሱም የተቀደሰ ውሃ ነው ማለት ነው። ውሃው በራሱ ከሌሎች
ውሃዎች የበለጠ የከበረ ሆኖ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዛት ስለ ተጨመሩበት
መለኮታዊ ውሃ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም።
15 ስለዚህ የእኛዎቹ ዐዳዲስ መናፍስት[198] ጥምቀትን ለመሳደብ የእግዚአብሔርን ቃልና
ሥርዓት ወደ ጎን አድርገው ከጉድጓድ የተቀዳውን ውሃ ብቻ እያሰቡ፣ «እፍኝ ውሃ ነፍስን
እንዴት ሊረዳ ይችላል?» እያሉ መለፍለፋቸው ፍጹም ተንኮልና ዲያብሎሳዊ የድፍረት ስድብ
16 ነው። አዎን ወዳጄ፣ ለብቻው ተነጥሎ ከታሰበ ውሃ ውሃ መሆኑን የማያውቅ ማን ነው? ነገር
ግን እግዚአብሔር ሥርዓቱን ካያያዘበትና ከቈለፈበት እንደገናም ለብቻው እንዲነጠል
የማይፈልገውን እጅግ በጣም የከበረ ጌጥ እንዲህ መዘንጠል እንዴት ትደፍራለህ? የውሃው
እውነተኛ ጥቅም ያለው በእግዚአብሔር ቃል ወይም ትእዛዝና በእግዚአብሔር ስም ነውና ይህ
ሀብት ከሰማይና ከምድር እጅግ የበለጠና የከበረ ነው።

---

194 ይህ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ ጽንፈኛ ሰባኪዎች የሚጠቀሙበት መከራከሪያ ነበር።

195 ትእዛዝ እጅግ በጣም ሥርዓት የጠበቀ የጳጳሱ አዋጅ ነው። ስሙን ያገኘው ከተጻፈው ወፍራም የቆዳ ጥቅል ጋራ ከተያያዘው የጳጳሱ ማኅተም መጠቅለያ (በላቲን ቡላ) ነው። ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታቸው አነስተኛ የሆኑ ጳጳሳዊ አዋጆች «መልእክቶች» ወይም «አጭር ደብዳቤዎች» ተብለው የሚጠሩና በስስ የቆዳ ጥቅልል ላይ የሚጻፉ ናቸው።

196 በሉተር ዘመን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳሳቱ የተወሰኑ መሠዊያዎችና አብያተ ክርስቲያናት የኃጢአት ስርየት ማግኛ ጽሑፎች ሊገኙባቸው የሚችሉ ቦታዎች መሆናቸውን «አጽንተው» ነበር።

197 የ1538ቱ የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እትም እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) በእነዚህ ቃላት ምትክ «ነገር ግን የእብደት አመክንዮ ይህንን አያመለክትም» የሚል አለው።

198 በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሕፃናትን ጥምቀት የማይቀበሉ ሰዎች በተለይ ዳግም አጥማቂዎች።

17 በመሆኑም ልዩነቱን አስተውል፤ ከተፈጥሮአዊው ነገር የተነሣ ሳይሆን እጅግ የከበረ ነገር
እዚህ ላይ ከመጨመሩ የተነሣ ጥምቀት ከሌላ ውሃ ሁሉ በጣም የተለየ ነገር ነው፤ እግዚአብሔር
ራሱ ክብሩን፣ ኃይሉንና ብርታቱን አያይዞበታልና። ስለዚህ በቀላሉ ተፈጥሮአዊ ውሃ ሳይሆን
መለኮታዊ፣ ሰማያዊ፣ ቅዱስና የተባረከ ውሃ ነው፤ ያም በሌሎች በምትችለው በማናቸውም
ቃላት አወድሰው የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ስለ ያዘና ስለሚያስተላልፍ ማንም በበቂ ሁኔታ
18 ሊያደንቀው ከማይችለው ሰማያዊና ቅዱስ ቃሉ የተነሣ ነው። ቅዱስ አውግስጢኖስ፡- «አክሴዳት
ቬርቡም አድ ኤሌመንቱም ኤት ፊት ሳክራመንቱም»[199] (Accedat verbum ad elementum et fit
sacramentum) ማለትም «ንጥረ ነገሩ ወይም ተፈጥሮአዊው ነገር ላይ ቃሉ ሲጨመርበት ቅዱስ
ምሥጢር» ማለትም ቅዱስ፣ መለኮታዊ ነገርና ምልክት ይሆናል» ብሎ አስተምሮአል።
19 ስለዚህ ቅዱሳት ምሥጢራትንና በእግዚአብሔር የተወሰኑና የተመሠረቱ ውጫዊ
ነገሮችን ሁሉ (የአንድን ፍሬ ሽፋን እንደምናይ) በአጠቃላይ ውጪአዊ ሽፋናቸው መሠረት
ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ውስጣቸው እንደ ተጨመረባቸው ሆነው ሊታዩ እንደሚገባ
20 ባለማቋረጥ እናስተምራለን። በተመሳሳይ መንገድ ስለ አባትነትና እናትነት እንዲሁም
መንግሥታዊ ሥልጣን እንናገራለን። እነዚህን ሰዎች ከአፍንጫቸው፣ ዓይናቸው፣ ቆዳቸውና
ጸጉራቸው ሥጋና አጥንት አንጻር ካየናቸው ከቱርኮችና ከአረማውያን ምንም የተለዩ
አይመስሉምና አንድ ሰው፡- «ይህንን ሰው ከሌሎች አስበልጬ ማሰብ ይገባኛል?» ብሎ ይጠይቅ
ይሆናል። ምክንያቱ ግን «እናትህንና አባትህን አክብር» የሚለው ትእዛዝ ስለ ተጨመረ ነው።
እኔ በእግዚአብሔር ግርማና ክብር ያጌጠና የተሸፈነ ሌላ ሰው ይታየኛል። ትእዛዙ ይህንን
ሥጋና ደም እንዴትና ለምን ማክበር እንደሚገባኝ የሚያሳየኝ አንገቱ ላይ ያለ ወርቃማ
ሰንሰለት[200] አዎን ጭንቅላቱ ላይ ያለ ዘውድ ነው እላለሁ።
21 በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲያውም በይበልጥ ከቃሉ የተነሣ ጥምቀትን ልታከብርና ከፍ ከፍ
ልታደርግ ይገባሃል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ በቃላትና በድርጊቶች አክብሮት ከሰማይ
በተአምራት አጽንቶታል። ክርስቶስ ሲጠመቅ ሰማያት መከፈታቸው፣ መንፈስ ቅዱስ እየታየ
መውረዱና[201] መለኮታዊው ክብርና ግርማ በየቦታው መገለጣቸው ቀልድ እንደ ነበረ ታስባለህ?
22 ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ቃሉና ውሃው በምንም መንገድ እርስ በርሳቸው መለያየት
እንደማይገባቸው እንደ ገና አስጠነቅቃችኋለሁ። ቃሉ ከውሃው በተለየበት ቦታ ውሃው የቤት
ሠራተኛ ለማብሰያነት ከምትጠቀምበት ውሃ የተለየ አይደለምና በእርግጥም «የመታጠቢያው
ቦታ ባለቤት ጥምቀት» ተብሎ ሊጠራ ይችላል።[202] ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ሥርዓት ቃሉ
አብሮት ሲሆን ጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር ነው፤ የክርስቶስም ጥምቀት ተብሎ ይጠራል። ይህ
አበክሮ ሊነገር የሚገባው የመጀመሪያው ነጥብ የቅዱሳት ምሥጢራት ባሕርይና ክብር ነው!
23 በሁለተኛ ደረጃ እንግዲህ ጥምቀት ምን እንደሆነና እንዴት ሊታይ እንደሚገባው
ስለምናውቅ ለምንና ለምን ዓላማ እንደ ተመሠረተ ማለትም ምን ጥቅሞች፣ ስጦታዎችና
ውጤቶችን እንደሚያመጣ መማር ይገባናል። ይህንንም እላይ ከተጠቀሱት የክርስቶስ ቃላት
የበለጠ ሊያስረዳን የሚችል የለም፤ «ያመነ የተጠመቀም ይድናል።»[203] እጅግ በጣም ቀላል በሆነ
24 መንገድ ሲቀመጥ ይህ ነው፡- የጥምቀት ኃይሉ፣ ውጤቱ፣ ጥቅሙ፣ ፍሬውና ዓላማው ማዳን
ነው። ማንም ሰው ልዑል ለመሆን ሳይሆን ቃላቱ እንደሚሉት የሚጠመቀው «ለመዳን» ነው።
25 ማንም ሰው በሚገባ እንደሚያውቀው መዳን ከኃጢአት፣ ከሞትና ከዲያብሎስ መዳን፣ ወደ
ክርስቶስ መንግሥት መግባትና ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር መኖር እንጂ ሌላ ነገር አይደለም።
26 እዚህ ላይ እንደ ገና በጥምቀት በቃላት ሊገለጽ የማይችል ሀብት ስለምናገኝ እንዴት
የከበረና አስፈላጊ ተደርጎ ሊታይ እንደሚገባው ታያላችሁ። ይህም [ጥምቀት] ቀላልና ተራ ውሃ
ሊሆን እንደማይችል ያሳያል፤ ምክንያቱም ተራ ውሃ እንዲህ ዓይነት ውጤት ሊኖረው

---

[199] *Tractate 80* *accedit* ተብሎ በሚነበበው በዮሐንስ 15፡3 ላይ፤ ( MPL 35:1840; NPNF, ser. 1,7:344) ሉተር ይህንን ምንባብ አዘውትሮ ጠቅሶታል።
[200] የተለየ የሥልጣን ምልክት።
[201] ማቴዎስ 3፡16።
[202] የሉተርን *Sermon on Baptism* (1534) (WA 37: 642, 17-18) ይመልከቱ፤ «ውሃማ ብቻ ወይም ምድራዊ ውሃ ወይም (ተገንጥለው የወጡት እንደሚጠሩት) የመታጠቢያ ውሃ ወይም የውሻ እጥበት...»።
[203] ማርቆስ 16፡16።

27 አይችልምና፤ ነገር ግን ቃሉ ያደርገዋል። ይህ ደግሞ እላይ እንዳልነው የእግዚአብሔር ስም
እንዳለበት ያሳየናል። የእግዚአብሔር ስም ባለበትም በዚያ ሕይወትና ደኅንነት ሊኖሩ ይገባል።
በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ በቲቶ 3:5 ላይ እንደ ጠቀሰው «ለዐዲስ ልደት የሚሆን መታጠብ»
እንዲሆን ጥምቀት ኃይሉን የሚያገኘው በቃሉ አማካይነት ስለ ሆነ መለኮታዊ፣ የተባረከ፣
ፍሬያማና ጸጋን የተሞላ ውሃ እንደ ሆነ በሚገባ ተገልጿል።

28 ነገር ግን የኛ ሁሉን ዐዋቂዎች ዐዳዲስ መናፍስት[204] እምነት ብቻ እንደሚያድንና
ሥራዎችና ውጪአዊ ነገሮች ምንም እንደማይጨምሩለት ይናገራሉ። እኛም እንዲህ ብለን
እንመልሳለን፤ እውነት ነው፤ በኋላ ላይ እንደምንሰማው ከእምነት በስተቀር ከእኛ የሆነ ነገር
29 ያንን አያደርገውም። እነዚህ ዕውር መሪዎች ግን እምነት የሚያምነው የሚንጠላጠልበትና
የሚቆምበት አንድ ነገር ሊኖረው እንደሚገባ ለማየት ፈቃደኞች አይደሉም። ስለሆነም እምነት
ውሃውን አጥብቆ ይይዝና ጥምቀት ፍጹም ድነትና ሕይወት ያለበት ነገር መሆኑን ያምናል።
እላይ በበቂ ሁኔታ እንደ ገለጽነው ጥምቀት በውሃው አማካይነት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃልና
ሥርዓት ጋራ በመዋሐዱና ከስሙ ጋር የተያዘ በመሆኑ ነው። ይህንን ሳምን ቃሉን በጥምቀት
የሰጠውን፣ የተከለውንና ይህንን ሀብት አጥብቀን መጨበጥ እንድንችል ውጫዊ ነገር የሰጠንን
እግዚአብሔርን ማመን እንጂ ሌላ ምንድን ነው?

30 እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ነገሩ ውጫዊ ጥምቀት በመሆኑ ብቻ እምነትን ከተያያዘበትና
ከተጣበቀበት ማረፊያ ዓላማ ለመለየት እስኪሞክሩ ድረስ ሞኞች ናቸው። አዎን፣ በስሜት
ሕዋሳት መታየትና መጨበጥ እንዲችል እንዲሁም መላው ወንጌል ውጪአዊ የቃል እወጃ
የሆነውን ያህል በዚህ መንገድ ወደ ልብ እንዲደርስ የእምነት ማረፊያ ውጫዊ መሆን
ይገባዋል። በአጭሩ እግዚአብሔር የሚያደርገውንና በእኛ ውስጥ በሥራ ላይ የሚያውለውን
ማንኛውንም ነገር በእንደዚህ ዓይነት ውጪአዊ ሥርዓት አማካይነት ሊያከናውነው ይፈልጋል።
የትም ቦታ ላይ ይናገር በእርግጥም ለምንም ዓላማ ወይም በምንም መንገድ አማካይነት ይናገር
31 እዚያ ጋ እምነት መመልከትና ያንንም አጥብቆ መያዝ ይገባዋል። እዚህ ላይ «ያመነ
የተጠመቀም ይድናል» የሚሉት ቃላት አሉን። እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር
ሥርዓት ወደ ተቀመጠው ውሃ ወደ ጥምቀት ካልሆነ ወደ ምንድን ነው? በመሆኑም ጥምቀትን
አልቀበልም የሚል ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል፣ እምነትንና ወደ ጥምቀት የሚመራንን
እንዲሁም ከጥምቀት ጋራ የሚያስተሳስረንን ክርስቶስን አለመቀበሉ ይከተላል።

32 በሦስተኛ ደረጃ የጥምቀትን ታላቅ ጥቅምና ኃይል ከተገነዘብን እነዚህን የጥምቀት
33 ስጦታዎችና ጥቅሞች የሚቀበለው ሰው ማን እንደ ሆነ በተጨማሪ እናስተውል። ይህ እንደ ገና
በእነዚሁ ተመሳሳይ ቃላት እጅግ በጣም ውብና ግልጽ በሆነ መንገድ ተገልጾአል፤ «ያመነ የተጠ
መቀም ይድናል»፤ ማለትም እምነት ብቻ አንድን ሰው የሚያድነውን መለኮታዊ ውሃ በሚጠ
ቅም መልኩ ለመቀበል የሚበቃ ያደርገዋል። ምክንያቱም ውሃውን በሚያጅቡት ቃላት
የተሰጡትና ቃል የተገባላቸውን እነዚህ በረከቶች ከልባችን ካላመንናቸው ልንቀበላቸው
34 አንችልም። ጥምቀት ምንም እንኳ በራሱ ወሰን የለሽ መለኮታዊ መዝገብ ቢሆንም ያለ እምነት
ምንም አይጠቅምም። በመሆኑም «ያመነ» የሚለው ነጠላ አገላለጽ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ
የተነሣ ድነትን ለማግኘትና መብቃትን በማሰብ ልናደርጋቸው የምንችላቸውን ሥራዎች ሁሉ
አውጥቶ ይጥላል። ምክንያቱም በእምነት ያልሆነ ነገር ሁሉ ለድነት ምንም የሚያበረክተው
አስተዋጽኦ አለመኖሩና ምንም የማይቀበል መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

35 ነገር ግን አንዳንዶች «ጥምቀት ራሱ ሥራ ከሆነና ሥራዎች ደግሞ ለድነት ምንም
እንደማይጠቅሙ ከተናገርህ እምነት ምን ቦታ አለው?» ብለው መጠየቅ ለምደዋል። መልስ፦
አዎ፣ የእኛ ሥራዎች ለድነት ምንም የማይጠቅሙ መሆናቸው እውነት ነው፤ ይሁን እንጂ
ጥምቀት የእኛ ሥራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራ ነው (እንደ ተባለው የክርስቶስን ጥምቀት
ከተራ መታጠቢያ ቦታ እጥበት በግልጽ መለየት ይገባችኋል) የእግዚአብሔር ሥራዎች ጠቃሚና
ለድነት አስፈላጊ ናቸው፤ ያለ እምነት ሰው አጥብቆ ሊጨብጣቸው ስለማይችል እምነትን

[204] የዝዊንግሊ ተከታዮች ወይም ዳግም አጥማቂዎች።

36 የሚያካትቱ ሳይሆኑ ይልቁንም እምነትን የሚጠይቁ[205] ናቸው። ውሃው እላይህ ላይ እንዲፈስ
በመፍቀድህ ብቻ ጥምቀትን በሚጠቅምህ ሁኔታ መቀበል ወይም ጠብቀህ ማቆየት አትችልም።
ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም ተጠምቀህ በውሃው ውስጥ ቃል የተገባለትን ድነት ለመቀበል
እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝና ሥርዓት ከተቀበልከው ጠቃሚህ ይሆናል። ይህንን የሰው እጅ
ወይም አካል ሊያደርገው አይችልም፤ ነገር ግን ልብ ሊያምነው ይገባል።
37 ስለዚህ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታ ክርስቶስ ደግሞ ሥራ ሳይሆን በቃሉ ዐውድ
ውስጥ የተቀመጠ፣ በቃሉ ለእኛ የተሰጠንና በእምነት የምንቀበለው መዝገብ የሆነውን ያህል
ጥምቀትም እኛ የምናደርገው ሥራ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚሰጠንና እምነት አጥብቆ
የሚይዘው መዝገብ እንደ ሆነ በግልጽ ታያላችሁ። ስለዚህ እምነትን እየተቃወምን እንደምንሰብክ
አድርገው የሚጮኹብን ሰዎች ጥቃት ያደርሱብናል። በእውነቱ እምነት ብቻ እጅግ በጣም
አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ያለ እርሱ ምንም ነገር ልንቀበል ወይም ልናገኝ እንደማንችል
አበክረን እንናገራለን።
38 በመሆኑም ስለዚህ ቅዱስ ምሥጢር ሊታወቁ የሚገባቸውን ሦስት ነገሮች በተለይ
የእግዚአብሔር ሥርዓት መሆኑንና በሙሉ ክብር ሊያዝ እንደሚገባው ዐይተናል። ጥምቀት
ሙሉ በሙሉ ውጪአዊ ነገር የነበረ ቢሆን እንኳ የእግዚአብሔር ሥርዓት መሆኑ ብቻ ይበቃ
ነበር። በተመሳሳይ መልኩ «አባትና እናትን አክብር» የሚለው ትእዛዝ ሰብዓዊ ሥጋንና ደምን
39 ብቻ ይመለከታል፤ ነገር ግን እኛ ሥጋና ደምን ሳይሆን ይህ የተቀመጠበትንና በእርሱም
ምክንያት ይህ ሥጋ እናትና አባት ተብሎ የተጠራበትን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ
እንመለከታለን። በተመሳሳይ መንገድ «ሂዱና አጥምቁ» ከሚሉት ቃላት የበለጠ ምንም ነገር
ባይኖረን እንኳ እንደ እግዚአብሔር ሥርዓት ልንቀበለውና ልንፈጽመው ይገባን ነበር። እዚህ
ላይ ግን የእግዚአብሔር ትእዛዝና ብያኔ ብቻ ሳይሆን የተስፋ ቃሉም በተጨማሪ አለን። ስለዚህ
እግዚአብሔር ካዘዘውና ከደነገገው ሌላ ነገር ይበልጥ እጅግ የከበረ ነገር ነው። በአጭሩ
መጽናናትንና ጸጋን እጅግ የተሞላ ከመሆኑ የተነሣ ሰማይና ምድር ሙሉ በሙሉ ሊረዱት
40 አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ እዚህ ላይ አንድ የተለየ ነገር አለ፤ ይኸውም እያንዳንዱ ሰው ማመን
አለበት። ምክንያቱም የጎደለው መዝገብ አይደለም፤ ይልቁንስ የቀረው ነገር መዝገቡ፣ መያዝና
በኃይል መጨበጥ የሚገባው መሆኑ ነው።
41 ስለዚህ በጥምቀት ማንኛውም ክርስቲያን ዘመኑን ወይም ዘመኗን በሙሉ የሚያጠናውና
የሚለማመደው በቂ ነገር አለ። ክርስቲያኖች ዘወትር ጥምቀት ቃል የሚገባላቸውንና
የሚያመጣላቸውን በረከቶች በሞትና በዲያብሎስ ላይ ድል ማግኘትን፣ የኃጢአት ይቅርታን፣
የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ሙሉውን ክርስቶስንና መንፈስ ቅዱስን ከስጦታዎቹ ጋር አጥብቀው
42 ለማመን በቂ ድርጊት አላቸው። በአጭሩ የጥምቀት በረከቶች ወሰን የለሽ ከመሆናቸው የተነሣ
ድንጉጥ ባሕርያችን ቢያጤናቸው ሁሉም እውነት ሊሆኑ ይችሉ እንደሆን ይጠራጠር ይሆናል።
43 ለምሳሌ አንድ ሐኪም ያለው ክህሎት በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ሰዎች አይሞቱበትም
ወይም ቢሞቱም እንኳ[206] ከዚያ በኋላ ለዘላለም ይኖራሉ እንበል። በእንደዚህ ዓይነት ሰው ላይ
ዓለም ገንዘብ እንዴት እንደሚያወርድበትና እንደሚያዘንብበት ብቻ ዐስብ። እንደዚህ ያለ ሰው
ከሚያጣብቡት የባለጠጎች አጀብ የተነሣ ሌላ ማንም ሰው ሊቀርበው አይችልም ነበር። እዚህ
ላይ ግን በጥምቀት ሞትን የሚውጥና[207] ሰዎችን ሁሉ በሕይወት የሚጠብቅ እንደዚህ ዓይነት
መዝገብና መድኃኒት ወደ እያንዳንዱ ሰው ደጅ በነጻ ቀርቧል።
44 በመሆኑም ኃጢአቶቻችን ወይም ሕሊናችን ሲያስጨንቁን ብርታትና መጽናናት
እንደምናገኝበት አድርገን ጥምቀትን ማክበርና ጥቅም ላይ ማዋል ይገባናል። «እኔ ግን ተጠ
ምቄአለሁ! ከተጠመቅሁ ደግሞ በነፍስም በሥጋም እንደምንድንና የዘላለም ሕይወት
45 እንደሚኖረኝ የተስፋው ቃል አለኝ» ማለት ይገባናል። በጥምቀት እነዚህ ሁለት ነገሮች

[205] *fodern* ፎደርን የሚለው የሉተር ቃል «መጠየቅ» (*forden)* (ፎርደን) ፝ «ማራመድ» (ፌርደርን) (*Fördern*) ማለት ይሆናል። የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ የአብሶፖኤሁስ የላቲን ትርጉም ቃሉን *requirunt* ሬኩሩንት ወደሚለው ቃል በመመለስ እንደ «መጠየቅ» ተረድቶታል።

[206] የ1538ቱ የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እትም እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) «ወደ ሕይወት ይመለሳሉ» የሚል ይጨምራል።

[207] ኢሳይያስ 25፡7።

የሚደረጉበት ምክንያት ይህ ነው፤ አካል ሊቀበል የሚችለው ውሃውን ስለ ሆነ አካል ውሃ
46 ይፈስበታል፤ በተጨማሪም ነፍስ እንድትቀበለው ቃሉ ይነገራል። ምክንያቱም ውሃውና ቃሉ
አንድ ላይ አንድ ጥምቀት ከመሆናቸው የተነሣ አካልም ነፍስም ሁለቱም ይድናሉ፤ ለዘለዓለም
ይኖራሉ፤ ይህም የሚሆነው ነፍስ በምታምነው በቃሉ አማካይነት፣ አካል ከነፍስ ጋር
ከመዋሐዱና ጥምቀትን ሊገነዘብ ከሚችልበት ብቸኛ መንገድ የተነሣ ነው። ስለዚህ በጥምቀት
አማካይነት ሙሉ በሙሉ ቅዱስና የተባረክን ስለምንሆን ከጥምቀት የበለጠ አካልንና ነፍስን
ሊያስውብ የሚችል ዕንቁ በምድር ላይ ሊያስገኘው እስከማይችል ሌላ ዓይነት ሕይወት ወይም
ሥራ የለም።

ለአሁኑ ዓላማችን የጥምቀትን ባሕርይ፣ ትሩፋቶችና ጥቅሞችን በተመለከተ ይህ
ይብቃን።

*[የሕፃናት ጥምቀት]*[208]

47 እዚህ ነጥብ ላይ ዲያብሎስ በልዩ ልዩ የእምነት ክፍሎች ዓለምን ግራ ለማጋባት
ወደሚጠቀምበት ጥያቄ ማለትም ወደ ሕፃናት ጥምቀት[209] እንመጣለን። ልጆች ያምናሉ?
48 እነርሱንም ማጥመቅ ትክክል ነው? ይህንን በአጭሩ እንመልሳለን። ይህንን ጥያቄ የዋሆች
ውድቅ ያድርጉትና ለተማሩት ይተዉት። እናንተ ግን መመለስ ከፈለጋችሁ በዚህ መንገድ
መልሱ፤
49 የሕፃናት ጥምቀት ክርስቶስን ደስ የሚያሰኝ መሆኑ በራሱ በክርስቶስ ሥራ በበቂ ሁኔታ
ተረጋግጧል። እግዚአብሔር እንደዚህ [በሕፃንነታቸው] የተጠመቁትን ብዙዎችን ቀድሷቸዋል፤
መንፈስ ቅዱስንም ሰጥቷቸዋል። ዛሬ እንኳ አስተምህሮአቸውና ሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስ
እንዳላቸው የሚመሰክሩላቸው በርካቶች አሉ። በተመሳሳይ መንገድ እኛም ቅዱሳት መጻሕፍትን
ለመተርጎም ኃይልና፣ ያለ መንፈስ ቅዱስ የማይቻለውን ክርስቶስን ማወቅ በእግዚአብሔር ጸጋ
50 ተሰጥቶናል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሕፃናትን ጥምቀት ባይቀበለው ኖሮ ለየትኞቹም መንፈስ
ቅዱስን ወይም ምኑንም አይሰጣቸውም ነበር። በአጭሩ በዘመናት መካከል እስከ ዛሬዋ ቀን
ድረስ በምድር ላይ ክርስቲያን ሊሆን የሚችል አንድም ሰው አይኖርም ነበር። ምክንያቱም
እንደ ቅዱስ በርናርድ፣[210] ጌርሶን፣[211] ዮሐንስ ሑስ[212] እና ሌሎች[213] ጥቂት አባቶች ሁሉ
እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመስጠት ጥምቀትን ከማጽናቱ የተነሣ እና ቅድስት ቤተ
ክርስቲያን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ስለማትጠፋ እነርሱ[214] ጥምቀት እግዚአብሔርን ደስ
የሚያሰኝ መሆኑን ማመን አለባቸው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱን ሊቃረን፣ ሐሰትንና
ክፋትን ሊደግፍ፣ ጸጋውን ወይም መንፈሱን ለእንደዚህ ዓይነት ዓላማዎች ሊሰጥ አይችልም።
51 ይህ ለማያስተውሉና ላልተማሩት ከሁሉ የሚሻለውና እጅግ በጣም ጠንካራው ማረጋገጫ ነው
ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ማንም ሰው «በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን
አንድነት … አምናለሁ» የሚለውን የእምነት አንቀጽ ሊወስድብን ወይም ሊሽረው ስለማይችል
ነው።
52 በተጨማሪም ዐቢዩን ትኩረት በተጠመቀው ግለሰብ ማመን አለማመን ላይ አናደርግም፤
ምክንያቱም በኋለኛውም ሁኔታ ጥምቀት ዋጋ የለሽ አይሆንም እንላለን። ሁሉም ነገር
53 በእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ላይ ጥገኛና ተደጋፊ ስለ ሆነ ነው። ምናልባት ይህ ለመገንዘብ

---

[208] ይህ ርእስ በመጀመሪያው እትመት ላይ አልነበረም፤ በሁለተኛው እትመት (1529) እና በ1530 እና 1538 የጀርመንኛ እትሞች ሕዳግ ላይ ተቀምጦ ነበር፤ በጽሑፉ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባው በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) ነው።

[209] ከመስመር ስለወጡ አስተምህሮዎች የተጠቀሰው ሕፃናትን የማጥመቅን ተገቢነት የሚክዱ ቡድኖችን ነው። ስለ ሕፃናት ጥምቀት *Concerning Rebaptism: A Letter of Martin Luther to Two Pastors* (1528) (WA 26:144-74; LW 40:225-62) የሚለውን የሉተርን መጽሐፍ ተመልከት።

[210] ሉተር አዘውትሮ Bernard of Clairvaux የክላይርቫክሱን በርናርድ እንደ መንፈሳዊ ሰው ምሳሌ ይጠቅሳል።

[211] ሉተር እና ሌሎች አዳሾች ዮሐንስ ጌርሶንን የቤተ ክርስቲያንን ጉባኤዎችን በመደገፉና በተግባራዊ ሥነ መለኮቱ በእጅጉ ያከብሩት ነበር።

[212] John Huss ዮሐንስ ሁስ በቆንስጣንሱ ጉባዔ ተወግዞ በስቅላት የተገደለ።

[213] የ1538ቱ የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እትም እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) «በልጅነታቸው የተጠመቁ» የሚል ይጨምራሉ።

[214] የሕፃናትን ጥምቀት የሚቃወሙት።

ቀላል ያልሆነ ነጥብ ነው፤ ነገር ግን ይህ ቀደም ሲል «ጥምቀት በቀላሉ ውሃና የእግዚአብሔር ቃል በውስጥና ከእርስ በእርሳቸው ጋራ ናቸው፤ እምነት ቢጎድል እንኳ ቃሉ ውሃውን ካጀበው ጥምቀት ትክክለኛ ነው» ባልኩት ላይ የተመሠረተ ነው። ምክንያቱም እምነቴ ጥምቀትን አይፈጥረውም ይልቁንም እምነቴ ጥምቀትን ይቀበላል። በተገቢ ሁኔታ ባይቀበሉት ወይም ባይጠቀሙበት እንኳ ጥምቀት ተቀባይነት የሌለው አይሆንም፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንዳልኩት ጥምቀት የተያያዘው ከእምነታችን ጋር ሳይሆን ከቃሉ ጋር ነው።

54 ምንም እንኳ አንድ አይሁዳዊ በማታለልና በክፉ ዓላማ ዛሬ ቢመጣና እኛ በመልካም እምነት ብናጠምቀው እንኳ ጥምቀቱ ትክክለኛ ነው ማለት ይገባናል፤ ምክንያቱም እንደሚገባ ሊቀበለው ባይችልም ውሃው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስለ ነበረ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ቅዱስ ምሥጢርን[215] ሳይገባቸው የሚካፈሉ ባያምኑም እንኳ እውነተኛውን ቅዱስ ምሥጢር ይቀበላሉ።

55 በመሆኑም ከመስመር ወጥተው ልዩ ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ተቃውሞ የማይመስል ነገር መሆኑን ታያላችሁ። ቀደም ሲል እንዳልነው ሕፃናት ባያምኑ እንኳ (ቀደም ብለን እንዳሳየነው አለማመናቸው እውነት ባይሆንም) ጥምቀቱ ትክክለኛ ስለ ሆነ ማንም ዳግመኛ ሊያጠምቃቸው አይገባም። በተመሳሳይ መልኩ ቅዱስ ምሥጢርም አንድ ሰው በክፉ ዓላማ ስለ ቀረበው ከንቱ አይሆንም። በተጨማሪም ያው ሰው ያን በአግባብ ካለመጠቀሙ የተነሣ በመጀመሪያው ጊዜ ቅዱስ ምሥጢሩን በእውነት ያልተቀበለ ይመስል ወዲያውኑ እንደ ገና እንዲወስድ አይፈቀድለትም። ያ ቅዱስ ምሥጢርን እጅግ በከፋ መንገድ መሳደብና ማንቋሸሽ ይሆናል። እኛ በተሳሳተ መንገድ ስለ ተጠቀምንበት የእግዚአብሔር ቃልና ሥርዓት ስሕተትና እርባና ቢስ እንደ ሆነ ለማሰብ እንዴት እንደፍራለን?

56 ስለዚህ ካሁን በፊት ያላመንክ ከሆነ አሁን እመንና «ጥምቀቴ በእርግጥም ትክክለኛ ነበር፤ የሚያሳዝነው ግን እኔ በትክክል አልተቀበልኩትም ነበር» ብለህ ተናዘዝ እላለሁ። ራሴን ጨምሮ የተጠመቁ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት «በእምነቴና በሌሎች እምነት ወደዚህ እመጣለሁ፤ ነገር ግን በእምነቴና በርካታ ሰዎች ለእኔ በሚያደርጉት ጸሎት ላይ ልመሠረት አልችልም። በዚያ ምትክ የጥምቀት ዐሳብ ቃልህና ትእዛዝህ በመሆኑ ላይ እመሠረታለሁ» ማለት ይገባናል። በተመሳሳይ መንገድ ወደ [መሠዊያው] ቅዱስ ምሥጢር የምሄደው በገዛ ራሴ እምነት ጥንካሬ ሳይሆን በክርስቶስ ቃል ጥንካሬ ነው። እኔ ጠንካራ ወይም ደካማ እሆን ይሆናል፤ ያንን መወሰኑን ለእግዚአብሔር እተወዋለሁ። ነገር ግን ይህንን ዐውቃለሁ እንድቀርብ፣ እንድበላና እንድጠጣ እንዳዘዘኝና ሥጋውንና ደሙን እንደሚሰጠኝ ዐውቃለሁ፤ እርሱ አይዋሽም ወይም አያታልለኝም።

57 በመሆኑም በሕፃናት ጥምቀትም ተመሳሳዩን እናደርጋለን። ልጁን እንዲያምን በሚል ዓላማና ተስፋ እናመጣውና እግዚአብሔር እምነት እንዲሰጠው እንጸልያለን። ነገር ግን ልጁን የምናጠምቀው በዚህ መሠረትነት ሳይሆን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ብቻ ተመሥርተን ነው። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደማይዋሽ ዕናውቃለን። ባልንጀራዬና እኔ በአጭሩ ሰዎች ሁሉ ያታልሉና ያሳስቱ ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ሊያታልል አይችልም።

58 ስለዚህ አስመሳይና የማያስተውሉ መናፍስት ብቻ እውነተኛ እምነት በሌለበት እውነተኛ
ጥምቀትም ሊኖር አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። በተመሳሳይ መንገድ «እኔ
እምነት ከሌለኝ ክርስቶስ ፈጽሞ አያስፈልግም» ብዬ ልከራከር እችላለሁ። ወይም እንደ ገና
«እኔ ታዛዥ ካልሆንኩ አባት፣ እናትና ባለ ሥልጣናት ፈጽሞ ባዶ ናቸው» ብልስ? ሰዎች
ማድረግ የሚገባቸውን በማያደርጉበት ወቅት ያለአግባብ የተጠቀሙበት ነገር ምንም ሕልውና
59 ወይም ዋጋ የለውም ብሎ መደምደም ትክክል ነው? ወዳጄ ይልቁንስ ክርክሩን ገልብጠውና
እንዲህ ብለህ ደምድም፤ እንዲያውም በትክክል ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ስለተቀበሉት ጥምቀት
ሕልውናና ዋጋ አለው፤ በገዛ ራሱ ትክክል ባይሆን ኖሮ ማንም ሰው ያለአግባቡ ሊጠቀምበት
ወይም ሊበድልበት አይችልም ነበር። አባባሉ እንዲህ ሲል ይቀጥላል «አቡሰስ ኖት ቶሊት፣

[215] እዚህ ላይና በአንቀጽ 55 እና 56 የጌታ እራት።

ሴድ ኮንፊርማት ሰብስታንቲያም፣»[216] (Abusus not tollit, sed confirmat substantiam) ማለትም፣
«ያለአግባብ መጠቀም ነገሩን ጨርሶ አያጠፋውም፤ ነገር ግን ሕልውናውን ያጸናል፡፡» ወርቅ
አንዲት አመንዝራ ሴት በኃጢአትና በእፍረት ስላጌጠችበት ወርቅነቱ አይቀንስም፡፡
60 ስለዚህ መደምደሚያው የተጠመቀው ሰው አንድ ሰው ብቻ ቢሆንና እርሱ ወይም እርሷ
እውነተኛ እምነት ያልነበራቸው ቢሆኑ እንኳ ጥምቀት ሁልጊዜ ትክክለኛ፣ [በእውነት ላይ
የተመሠረተና] ሙሉ ሥረ ነገሩን ጠብቆ ይቆያል የሚል ይሁን፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር
61 ሥርዓትና ቃል በሰዎች ሊለወጡ ወይም ሊቀየሩ አይችሉም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጭፍራዎች
በጣም ከመታወራቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃልና ትእዛዝ ዐያዩም፤ ጥምቀትን በጅረት
ወይም በማሰሮ ውስጥ እንዳለ ውሃና ባለ ሥልጣኑን እንደ ተራ ሰው ብቻ ይቈጥሩታል፡፡
እምነትን ወይም መታዘዝን ካለማየታቸው የተነሣ እነዚህ ነገሮች ዋጋ እንደሌላቸው ያምናሉ፡፡
62 እዚህ ላይ ከገዢዎች ዘውዳቸውን ለመንጠቅ፣ ከእግሩ ሥር ሊረጋግጠው፣ በተጨማሪም
የእግዚአብሔርን ሥራና ሥርዓቶች ሁሉ ማጣመምና ከንቱ ማድረግ የሚወድ ሾላካ፣ ተንኮለኛ
63 ዲያብሎስ ያደባል፡፡ ስለዚህ ንቁ መሆንና በሚገባ በመታጠቅ ጭፍኖቹ እንደሚያልሙት
ጥምቀትን እንደ ባዶ ምልክት በመቊጠር ከቃሉ ዘወር ለማለት ራሳችንን እንዳንሰጥ መጠንቀቅ
ይገባናል፡፡
64 በመጨረሻም[217] ጥምቀት ምን እንደሚያመለክትና ወደ ክርስቲያን ማኅበረሰብ
በመጀመሪያ የምንገባበትን ይህን የቅዱስ ምሥጢር ምልክትና ውጪአዊ ሥርዓት እግዚአብሔር
65 ለምን እንደ ደነገገ ማወቅ ይገባናል፡፡ ይህ ድርጊት ወይም መንፈሳዊ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ[218]
በሚሸፍነን ውሃ ውስጥ መጥለቅንና እንደ ገና መውጣትን ያካትታል፡፡ እነዚህም ሁለቱ ክፍሎች
ማለትም ከውሃው ሥር መነከርና ከውስጡም ብቅ ማለት በመላው የሕይወት ዘመናችን
በውስጣችን መቀጠል ያለባቸው የአሮጌው አዳም መገደልና የዐዲሱ ፍጥረት ትንሣኤ ወደ
ሆነው የጥምቀት ኃይልና ውጤት ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም የአንድ ክርስቲያን ሕይወት አንዴ
ጀምሮ ከዚያ ሁሌም የሚቀጥል የየዕለቱ ጥምቀት ነው፡፡ ምክንያቱም የዐዲስ ፍጥረት የሆነው
ነገር ሁሉ እንዲበቅል አሮጌውን አዳም የሚመለከተው ነገር ሁሉ ባለማቋረጥ እንዲወገድ
66 ማድረግ ይገባናል፡፡ አሮጌው ፍጥረት ምንድን ነው? ከአዳም የተወለድንበት፣ በቀላሉ የሚቈጣ፣
አናዳጅ፣ ቀናተኛ፣ ርኩስ፣ ስስታም፣ ሰነፍ፣ ኩሩ፣ አዎን የማያምን ነው፡፡ በተንኮሎች ሁሉ
67 የተሞላ በተፈጥሮ ምንም መልካም ነገር የሌለው ነው፡፡ እዚህ ላይ ወደ ክርስቶስ መንግሥት
ስንገባ በኖርን መጠን ይበልጥ ጨዋ፣ ይበልጥ ታጋሽና የዋህ እንድንሆንና ከስስት፣ ከጥላቻ፣
ከቅንዓት እና ትዕቢት በይበልጥ እንድንለይ ይህ የተበላሸ ባሕርይ በየዕለቱ መሞት ይገባዋል፡፡
68 ይህ በውሃ መጠመቅ በክርስቲያኖች መካከል የሚሆን ትክክለኛ የጥምቀት አጠቃቀም
ነው፡፡ ይህ በማይሆንበት ስፍራ ይልቁንም አሮጌው ፍጥረት ነጻነት ሲሰጠውና ባለማቋረጥ እየጠ
69 ነከረ በሚያድግበት ስፍራ ጥምቀትን እየተጠቀምንበት ሳይሆን እየተቃወምነው ነው፡፡ ከክርስቶስ
ውጪ የሆኑት ማድረግ የሚችሉት ከዕለት ወደ ዕለት እየከፉ መሄድ ነው፡፡ «ክፉት ይበልጥ
በቆየ መጠን ይበልጥ የከፋ ይሆናል»[219] እንደሚለው ምሳሌ ነው፤ እርሱም እውነት ነው፡፡
70 ከአንድ ዓመት በፊት አንድ ሰው ኩሩና ስስታም ከነበረ በዚህ ዓመት ይህ ዓይነቱ ሰው ይበልጥ
ኩሩና ስስታም ይሆናል፡፡ ክፉት እንደዚህ ሆኖ ከወጣትነት ጀምሮ በሰዎች ውስጥ ያድጋል፤
ይጨምራልም፡፡ ጨቅላ ሕፃን የተለዩ ተንኮሎች የሉትም፤ ነገር ግን ይበልጥ ባደገ መጠን
ተንኮለኛና የረከሰ ይሆናል፡፡ ለአካለ መጠን ሲደርስ እውነተኛዎቹ ተንኮሎች ቀን በቀን ይበልጥ
ኃይለኛ ይሆናሉ፡፡

---

[216] የሕግ አባባል *Concerning Rebaptism* (1528) በሚለው መጽሐፍ ውስጥም የተጠቀሰ፤ (WA 26:161፣ 25-26; LW 40:248) ሉተር «አንድ ሌባ ስለሰረቀው ወይም ያለአግባብ ስለተጠቀመበት ወርቅ ገለባ አይሆንም፤ አራጣ አበዳሪ በማጭበርበር ቢያገኘውም ብር ወደ ወረቀትነት አይቀየርም፤» የሚለውን ይጨምራል፡፡

[217] ስለ ሕፃናት ጥምቀት በተቀጥላነት ካስረዳ በኋላ እዚህ ላይ ሉተር በአራተኛ ነጥብ ጥምቀትን በአጠቃላይ ማስረዳቱን ይቀጥላል፤ አንቀጽ 3፣23 እና 32ን ተመልከት፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ሉተር «አሮጌው አዳም» (ሮሜ 5፡12-6፡6) እና «አሮጌው ፍጥረት» (*አልተር ሜንስች*) (*alter Mensch*) (በሚሉት ቃላት መካከል ልዩነትን ያደርጋል፡፡

[218] እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ሕፃኑን በማጥመቂያው ገንዳ ውስጥ ሦስት ጊዜ መንከር የተለመደ ነበር፤ (Cf. LW 35:29; WA 2:727,4-19) ሌላው በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረው ተግባር ማርጠብ የጥምቀቱን ውሃ ሕፃኑ ላይ ሦስት ጊዜ ማፍሰስ ነበር፡፡

[219] ሉተር ይህንን ምሳሌ «ይበልጥ ሲሸመግል ይበልጥ ስስታም፤ ይበልጥ በቆየ መጠን የባሰ የከፋ ይሆናል፤» በሚለው መልክም አዘውትሮ ይጠቅሰዋል፤ WA 32:451,33-34; LW 21:184 ተመልከት፡፡

71
ስለዚህ አሮጌውን ፍጥረት በጥምቀት ኃይል ካልተቈጣጠሩትና ካልተጫኑት የባሕርዩን
ዝንባሌዎች ባለመከልከል ይከተላል። በሌላ በኩል ክርስቲያኖች ስንሆን በመጨረሻ እስኪጠፋ
ድረስ አሮጌው ፍጥረት በየዕለቱ እየቀነሰ ይሄዳል። በጥምቀት ውስጥ በእውነት መጥለቅና
72 በየዕለቱ እንደ ገና መውጣት ማለት ይህ ነው። በመሆኑም ውጫአዊው ምልክት የተወሰነው
በእኛ ላይ ኃይለኛ ውጤት አምጪ ሥራ እንዲሠራ ብቻ ሳይሆን ወደ አንድ ነገር የሚጠቁም
73 እንዲሆን ነው። እምነት ከፍሬዎቹ ጋር ባለበት ስፍራ ጥምቀት ባዶ ምልክት አይደለም፤ ነገር
ግን ውጤቱ ያጅበዋል። እምነት በጎደለበት ስፍራ ግን ፍሬ የለሽ ምልክት ብቻ ሆኖ ይቀራል።
74 እዚህ ላይ ጥምቀት በኃይሉና በሚያመለክተው ነገር በሁለቱም ቀደም ሲል ምሥጢረ
ንስሐ[220] ተብሎ ይጠራ የነበረውንና እንደ እውነቱ ከሆነ ጥምቀት እንጂ ሌላ ነገር ያልሆነውን
75 ሦስተኛውንም ቅዱስ ምሥጢር እንደሚጠቀልል ታያላችሁ። ንስሐ አሮጌውን ፍጥረት በቁርጠ
ኝነት ከማጥቃትና ወደ ዐዲስ ሕይወት ውስጥ ከመግባት ሌላ ምንድን ነው? ስለዚህ በንስሐ
የምትኖር ከሆነ ይህን ዐዲስ ሕይወት ማወጅ ብቻ ሳይሆን እርሱን በሚያስገኘው፣ በሚጀምረውና
76 በሚለማመደው በጥምቀት ውስጥ እየተመላለስክ ነው። በጥምቀት ዐዲሱ ሕይወት እንዲወጣና
እየጠነከረ እንዲሄድ፣ አሮጌውን ፍጥረት ለመጫን ጸጋ፣ መንፈስ ቅዱስ እና ብርታት
ተሰጥቶናል።
77 ስለዚህ ጥምቀት ለዘላለም ይኖራል። አንድ ሰው ከጸጋው ርቆ ቢወድቅና ኃጢአት ቢሠራ
78 አሮጌውን ፍጥረት እንደ ገና ድል እንድንነሣ የምንገባበት መብቱ ሁልጊዜ አለን። ነገር ግን
እንደ ገና ውሃው እላያችን ላይ ሊፈስብን አያስፈልግም። መቶ ጊዜ ውሃ ውስጥ ብንነከርም
ከአንድ ጥምቀት የበለጠ አይሆንም። ውጤቱና ጠቀሜታውም የሚቀጥልና የሚኖር ይሆናል።
79 ስለዚህ ንስሐ ወደ ጥምቀት መመለስና መቅረብ፣ ቀደም ሲል ወደ ተጀመረ ነገር ግን ወደ
ተተወው ነገር እንደገና መመለስ እና መለማመድ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም።
80 ይህንን የምለው፣ ጥምቀት ኃጢአት ውስጥ ተመልሰን ከወደቅን በኋላ ልንጠቀምበት
እንደማንችል ያለፈ ነገር አድርጎ የሚያሳየውን በመካከላችን ለረጅም ጊዜ የቆየውን አመለካከት
ለማስተካከል ነው። ይህ ዐሳብ የመጣው አንድ ጊዜ የተከናወነውን ድርጊት ብቻ ከመመልከት
81 ነው። በእርግጥ ለዚህ ዕይታ ተጠያቂው ወደ ክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰብ ስንገባ የተሳፈርንባት
መርከብ በውሃ ተጥለቅልቃ ከሰጠመች በኋላ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ልንዋኝበት የሚገባን ሁለተኛው
82 መርህ[221] ምሥጢረ ንስሐ ነው ብሎ የጻፈው ቅዱስ ጀሮም ነው።[222] ይህ ለእኛ ምንም ቀጣይ
ጥቅም እንዳይኖረው አድርጎ የጥምቀትን ዋጋ ያርቃል። ስለዚህ ይህን ማለት ስሕተት ነው።[223]
መርከቡ የእግዚአብሔር ሥርዓት እንጂ የእኛ ነገር ስላልሆነ አይሰበርም። ነገር ግን የእኛ
መንሸራተትና ከመርከብ ውጪ መውደቅ ይኖራል። ይሁን እንጂ የወደቁት ሰዎች እንደ
ቀድሞው ወደ መርከቧ እንደ ገና ገብተው ለመሳፈር መውጣት እስኪችሉ ድረስ ወዲያውኑ
አስተውለው ወደ መርከቧ መዋኘት ይገባቸዋል።
83 ስለሆነም ከዲያብሎስ መንጋጋ[224] የሚነጥቀንና የእግዚአብሔር ገንዘብ የሚያደርገን፣
ኃጢአትን ድል የሚነሣ፣ የሚያርቅና ዕለት ዕለት ዐዲሱን ሰው የሚያበረታና ከዚህ መከራ
ወጥተን ወደ ዘላለም ክብር እስክንሻገር ድረስ የሚጸናውና የሚኖረው ጥምቀት ምን ዓይነት
ታላቅና አስደናቂ ነገር እንደ ሆነ እንመለከታለን።
84 ስለዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ ጥምቀታቸውን ሁልጊዜ ሊለብሱት እንደሚገባቸው ዕለታዊ
ልብሳቸው ይቊጠሩት። በየዕለቱ አሮጌውን ፍጥረት እየጨቈኑና በዐዲሱ ሕይወት እያደጉ

---

[220] በላቲን (እና ጀርመንኛ) ፖኤኒቴንሺያ *poenitentia* (በጀርመን፡ ቡሴ *Buße*) ማለት የጸጋ መሣሪያ የሆነውን መናዘዝን (ጸጸት) ወይም በቄሱ የሚታዘዘውን የኃጢአት ዕዳ ክፍያ ድርጊት (ንስሐ) ወይም ውስጣዊ የንስሐ ዝንባሌ ማለት ይሆናል፤ ሉተር አልፎ አልፎ ንስሐን እንደ የጸጋ መሣሪያ ይጠቅሳል፤ ነገር ግን እንዲህ በማድረግ ሥርዓቱን በሚፈጽመው ሰው በሚነገረው የኃጢአት ይቅርታ አዋጅ፣ ወይም ፍትሐት ላይ በማተኮር የጥምቀት አንድ ክፍል አድርጎት ነው የሚቈጥረው።

[221] ጥምቀት የመጀመሪያው መርህ ተደርጎ ይቈጠር ነበር።

[222] መልእክት 130.9 ወደ ድሜጥሮስ (Demetrias) (MPL22:1115; NPNF, ser.2, 6:266) መልእክት 122.4 ወደ ሩስቲከስ (Rusticus) (MPL22:1046; NPNF, ser.2, 6:229)፤ መልእክት 147.3 ወደ የወደቀው ሳቢኒያኑስ (Sabinianus) (MPL22:1197; NPNF, ser.2, 6:291)ን፣ የኢሳይያስ ማብራሪያን ምዕራፍ 3፣8-9 (MPL 24:65) ተመልከት። ይህንን የጀሮምን አረፍተ ነገር ሉተር አዘውትሮ ይጠቅሰው ነበር።

[223] የ1538ቱ የዊተንበርግ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እትም እና የጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) «ወይም ደግሞ በጭራሽ በትክክል አልተረዳነውም ነበር ማለት ነው፤» የሚል ይጨምራሉ።

[224] ቃል በቃል «ጉሮሮ» ወይም «ማንቁርት»።

85 ከፍሬዎቹ ጋራ በእምነት ውስጥ መገኘት ይገባቸዋል፡፡ ክርስቲያኖች መሆን ከፈለግን
ክርስቲያኖች የሚያደርገንን ሥራ መለማመድ ይገባናል፤ ርቀው የወደቁት ደግሞ ወደዚያ
86 ይመለሱበት፡፡ የስርየት መክደኛው[225] ክርስቶስ ኃጢአት ብንሠራ እንኳ ከእኛ እንደማይርቅ
ወይም ወደ እርሱ ለመመለስ እንደማይከለክለን መዝገቦቹና ስጦታዎቹ ዘላቂ ናቸው፡፡ በጥምቀት
የኃጢአት ይቅርታ አንዴ እንዳገኘን አሮጌውን ፍጥረት በአንገታችን ተሸክመነው እስከ ዞርን
ድረስ ይቅርታው በዘመናችን ሁሉ በየዕለቱ ይዘልቃል፡፡

## [አምስተኛ ክፍል፡-] የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር

1 ስለ ቅዱስ ጥምቀት እንደሰማነው ሁሉ ሁለተኛውም ቅዱስ ምሥጢር ምን እንደ ሆነ፣
ጥቅሞቹ (ትሩፋቶቹ) ምን ምን እንደሆኑና ማን ሊቀበለው እንደሚገባ በመግለጥ በሦስት
2 አርእስት ሥር ልናየው ይገባናል፡፡ ይህ ሁሉ ክርስቶስ ቅዱስ ቊርባንን ለማቋቋም በተናገራቸው
ቃላት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለ ሆነም ክርስቲያን መሆንና ወደ ቅዱስ ቊርባን መምጣት
የሚመኝ ማንኛውም ሰው ሊያውቃቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ምን እንደሚፈልጉ ወይም ለምን
እንደሚመጡ የማያውቁትን ወደ ቅዱስ ቊርባን ልናቀርባቸው እና ልናድላቸው ስለማናስብ
ነው፡፡ ቃላቱም እነዚህ ናቸው፤[226]
3 «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራውን ወስዶ
አመሰገነ፤ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንዲህ አለ፤ 'እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ
የተሰጠ ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት'፤

እንደዚሁም ደግሞ ከእራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ አመሰገነ፤ ለእነርሱም ሰጣቸውና
'እንካችሁ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፡፡ ይህ ጽዋ ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ የሚፈሰው በደሜ
የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፡፡ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡'»
4 እዚህ ላይም ይህንን ቅዱስ ምሥጢር ከሚንቁትና ከሚያቃልሉት ጋራ መጣላትና
መነታረክ አንፈልግም፡፡ ይልቁንም ጥምቀትን በተመለከተ እንዳደረግነው በመጀመሪያ ከሁሉ
ይልቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው ምን እንደሆነ ማለትም ዋናው ነገር የእግዚአብሔር ቃልና
ሥርዓት ወይም ትእዛዝ መሆኑን እንማራለን፡፡ እርሱም በማንም የታለመና የተፈለሰፈ ወይም
5 የተፈጠረ ሳይሆን ያለማንም ምክርና ውይይት በክርስቶስ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለዚህ ዐሠርቱን
ትእዛዛት፣ የጌታ ጸሎትንና የእምነት መግለጫውን እናንተ ባትጠብቋቸውም፣ ባትጸልዩባቸውም
ወይም ባታምኑባቸውም ባሕሪያቸውንና ዋጋቸውን ጠብቀው እንደሚቆዩ ሁሉ ይህ የተባረከ
ቅዱስ ምሥጢርም እኛ በማይገባ መልኩ ብንጠቀምበትና ብንይዘውም እንኳ ሳይዛባና ሳይጣስ
6 ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር ስለ እምነታችንና አኗኗራችን በጣም ግድ ከመሰኘቱ የተነሣ የእርሱን
ሥርዓት እንዲነኩ ይፈቅዳል ብለህ ታስባለህ? አይደለም! እኛ እንዴትም አድርገን እንያዛቸው
የዚህ ዓለም ጊዜያዊ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር እንደፈጠራቸውና ሥርዓት እንዳበጀላቸው
7 ይኖራሉ፡፡ ይህም ዘወትር አበክሮ ሊነገር ይገባል፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ቃል በተቃራኒው
በመቆም ቅዱሳት ምሥጢራትን እኛ እንደምናደርጋቸው አድርጎ የሚቈጥራቸውን የተቃውሞ
መናፍስት ልፍለፋ ሁሉ ሙሉ በሙሉ መርታት የምንችል ስለሆነ ነው፡፡
8 እንግዲህ የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ምንድን ነው? መልስ፡- እኛ ክርስቲያኖች
እንድንበላና እንድንጠጣ በክርስቶስ ቃል የታዘዝነው በኅብስቱና በወይኑ ውስጥና ሥር ያለ የጌታ
ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ነው፡፡ ስለ ጥምቀት ውሃ ብቻ እንዳልሆነ ያልነውን እዚህም
9 እንላለን፤ ቅዱስ ቊርባን ኅብስትና ወይን ነው፤ ነገር ግን በማዕድ የሚቀርበው ዓይነት ኅብስትና
ወይን ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተቀመጠና ከቃሉ ጋር የተያያዘ
ኅብስትና ወይን ነው፡፡

---

[225] ሮሜ 3፡25ን ተመልከት፤ (ማስታወሻ፡ «የማስተስረያ ቦታ»)፤ ዕብራውያን 4፡16፡፡

[226] ሉተር የጌታ እራት ማቋቋምን በ1ቆሮንቶስ 11፡23-25፤ ማቴዎስ 26፡26-28፤ ማርቆስ 14፡22-24 እና ሉቃስ 22፡19-20 ማጣቀሻዎች ላይ ያጣምራል፡፡

10 ይህንን ቅዱስ ምሥጢር የሚያደርገውና ከተለምዶአዊው ኅብስትና ወይን የሚለየው
የክርስቶስ ሥጋና ደም ተብሎ እንዲጠራና በእውነትም እንዲሆን የሚያደርገው ቃሉ ነው
እላለሁ። ምክንያቱም «አክሴዳት ቨርቡም አድ ኤለመንቱም ኤት ፊት ሳክራመንቱም»
(Accedat verbum ad elementum et fit sacramentum) ማለትም «ቃሉ ከውጪአዊው ኅብስትና
ወይን ጋር ሲጣመር ቅዱስ ምሥጢር ይሆናል»[227] እንደ ተባለው ነው። ይህ የቅዱስ
አውግስጢኖስ አባባል እጅግ ተገቢና በጥሩ ሁኔታ የተቀመጠ ከመሆኑ የተነሣ ከዚህ የተሻለ
ምንም ነገር ማለት አይችልም ነበር። ቃሉ ኅብስትና ወይኑን ቅዱስ ምሥጢር ሊያደርገው
11 ይገባል፤ አለበለዚያ ተራ ኅብስትና ወይን ሆኖ ይቀራል። እዚህ ላይ ይህ የአንድ ልዑል ወይም
ንጉሠ ነገሥት ቃልና ሥርዓት አይደለም፤ ነገር ግን ፍጥረት ሁሉ በእግሩ ሥር ሊንበረከክለትና
እርሱ እንደሚለው መሆኑን ሊመሰክርለት የሚገባውና ሰዎች በሙሉ አክብሮት፣ ፍርሃትና
ትሕትና ሊቀበሉት የሚገባ የመለኮታዊ ግርማው ቃልና ሥርዓት ነው።
12 «መቶ ሺህ አጋንንት ከአክራሪዎች ሁሉ ጋራ ወደ ፊት ይቅረቡና ኅብስትና ወይን
እንዴት የክርስቶስ ሥጋና ደም ሊሆኑ ይችላሉ? ይበሉ» ማለት ትችላለህ። እንደዚያም ሆኖ
መናፍስቱና ሊቃውንቱ ሁሉ በአንድ ላይ ሆነው ግርማዊው መለኮት ከሁሉ በምታንሰው ጣቱ
13 ላይ ካለው ጥበብ ያነሰ ኃይል እንዳላቸው ዐውቃለሁ። የክርስቶስ ቃል እነሆ፦ 'ውሰዱ ብሉ ይህ
ሥጋዬ ነው' 'ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ይህ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው' ይላል። እዚህ ላይ
አቋማችንን ይዘን ክርስቶስን ሊያስተምርና እርሱ የተናገረውን ሊቀይር የሚደፍር ማን መሆኑን
14 እናያለን። በእርግጥ ቃሉን ከኅብስቱና ከወይኑ ብታርቁ ወይም ከቃሉ ነጥላችሁ
ብትመለከቷቸው ከተራ ኅብስትና ወይን በስተቀር ሌላ ምንም ነገር እንደማይኖራችሁ እሙን
ነው። ነገር ግን ትክክልና አስፈላጊ እንደ ሆነው ቃላቱ እስካሉ ድረስ ከእነርሱ የተነሣ ኅብስቱና
ወይኑ በእውነትም የክርስቶስ ሥጋና ደም ናቸው። ነገር ሁሉ የክርስቶስ ከናፍርት
እንደሚናገሩትና እንደሚሉት እንደዚያው ነው። እርሱ ሊዋሽ ወይም ሊያታልል አይችልም»
በሚለው ቃል ሕሊናህን አበርትተህ ማወጅ ትችላለህ።
15 በመሆኑም ሰዎች የሚያስቸግሯቸውን የጥያቄ ዓይነቶች ሁሉ ለምሳሌ ክፉ ካህን ቅዱስ
ቊርባንን ማደል ይችል እንደሆነና እንዳልሆነ፣ እንዲሁም ተመሳሳይ ጥያቄዎችን መመለስ
16 ቀላል ነው። ድምዳሜአችን፦ አንድ ወንበዴ ቅዱስ ምሥጢሩን ቢቀበል ወይም ቢያድል እንኳ
አንድ ሰው እጅግ በጣም በሚገባ ሁኔታ የሚጠቀምበት ያህል ቅዱስ ምሥጢሩ እውነተኛ ነው
(ማለትም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው)። ምክንያቱም ቅዱስ ምሥጢሩ የተመሠረተው በሰው
ቅድስና ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስለ ሆነ ነው። በምድር ላይ የትኛውም ቅዱስ
አዎን፣ በሰማይ የትኛውም መልአክ ኅብስትንና ወይንን ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም መለወጥ
እንደማይችል ሁሉ፤ ያለ አግባብ በመጠቀምም እንኳ ቢሆን ማንም ሰው ቅዱስ ቊርባንን
17 መለወጥ ወይም መቀየር አይችልም፤ ምክንያቱም አንድ ቅዱስ ምሥጢር የተመሠረተበት ቃል
ከአንድ ግለ ሰብ አለመብቃት ወይም አለማመን የተነሣ ሐሰተኛ አይደረግም። ክርስቶስ
«ካመናችሁ ወይም ከተገባችሁ ሥጋዬና ደሜን ታገኛላችሁ» አላለም። ነገር ግን ያለው «ውሰዱ፤
18 ብሉና ጠጡ፤ ይህ ሥጋዬና ደሜ ነው» ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ «ይህንን አድርጉት (ማለትም
አሁን የማደርገውን፣ እኔ የምመሠርተውን የምሰጣችሁንና እንድትወስዱ የምነግራችሁን») ሲል
«የሚገባችሁ ሆናችሁም የማይገባችሁ ልዩነት አያመጣም፤ ከኅብስቱና ከወይኑ ጋር በተያያዙት
በእነዚህ ቃላት ኃይል ሥጋዬንና ደሜን ታገኛላችሁ» የማለት ያህል ነው። ይህንን ለይታችሁ
19 ዕወቁና በሚገባ አስተውሉት። መላው ክርክራችን፣ እስካሁን ከተነሡት ወይም ምናልባት
ከሚነሡት ስሕተቶችና ማታለሎች ሁሉ መመከታችን እና መከላከያችን በእነዚህ ቃላት ላይ
ያረፈ ነው።
20 በመሆኑም የመጀመሪያውን ክፍል ማለትም የዚህን ቅዱስ ምሥጢር ምንነት በአጭሩ
አጢነናል። አሁን ወደ ኃይሉና ጠቀሜታው እንዲሁም ይህ ቅዱስ ምሥጢር በእርግጥ ለምን
ዓላማ እንደ ተመሠረተ ወደ ማጥናት እንመጣለን። ምክንያቱም ምን ልንፈልግ እንደሚገባንና
21 እዚያም ምን እንደምናገኝ ማወቃችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም አሁን ከተጠቀሱት

[227] እላይ ቊጥር 199ን ተመልከት።

ቃላት ግልጽና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ነው፤ «ይህ ሥጋዬ ነው [ለእናንተ የተሰጠ] ይህ
22 ደሜ ነው ለኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የፈሰሰ»። ያ ማለት በአጭሩ በቅዱስ ምሥጢሩ
አማካይነትና ውስጥ የኃጢአት ይቅርታ የምናገኝበትን ታላቅ መዝገብ ስለምንቀበል ወደ እርሱ
እንሄዳለን ማለት ነው። ለምን? ምክንያቱም ቃላቱ በዚያ ስላሉና ያንን ብልጽግና ስለሚሰጡን
ነው። ይህ ብልጽግና የእኔ እንዲሆንና በእርግጥ ከኃጢአቴ፣ ከሞትና ከክፉቶች ሁሉ እንድድን
ለእኔ እንደ ተሰጠኝ እንደ እርግጠኛ ቃል ኪዳንና ምልክት ይጠቅመኝ ዘንድ እንድበላና
እንድጠጣ ስለሚያዘኝ ነው።
23 ስለዚህ ቅዱስ ምሥጢር ዐዲሱን ፍጥረት ስለሚመግብና ስለሚያጠነክር «የነፍስ ምግብ»
ተብሎ መጠራቱ ተገቢ ነው። በመጀመሪያው ደረጃ በጥምቀት አማካይነት እንደ ዐዲስ
ተወለድን። ይሁን እንጂ፣ ቀደም ሲል እንዳልኩት ሰብአዊ ሥጋችንና ደማችን አሮጌ ቆዳቸውን
አልጣሉም። ብዙ ጊዜ እስክንደክምና እስክንታክት አንዳንድ ጊዜም እስክንሰናከል ድረስ እጅግ
24 በርካታ የዲያብሎስና የዓለም እንቅፋቶች፣ እንዲሁም ጥቃቶች ያጋጥሙናል። ስለዚህ
እምነታችን እንዲታደስና እንዲጠነክር በትግሉ እንዳይደናቀፍ ነገር ግን በይበልጥ እየበረታ
25 እንዲሄድ የጌታ እራት እንደ ዕለታዊ ምግብና ሕይወት ማቆያ ይሰጣል። ምክንያቱም ዐዲሱ
26 ሕይወት ባለ ማቋረጥ የሚያድግና የሚጠነክር መሆን ይገባዋል። ነገር ግን ላቅ ያለ ተቃውሞን
ደግሞ መታገሥ ይገባዋል። ዲያብሎስ ብስጩ ጠላት ነው። እንደምንቋቋመውና አሮጌውን
ፍጥረት እንደምናጠቃ ሲያይ፣ በኃይል ሊመደስሰን ሳይችል ሲቀር፣ የማታለያ ዓይነቶችን ሁሉ
በመጠቀም በየአቅጣጫው እየተሹለከለከና ሳይታወቅበት እየዞረ እምነታችንን እንድንክድ ወይም
ተስፋ እንድንቈርጥ[228] ግድ የለሾችና ትዕግሥት የለሾች እስክንሆንና በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ
27 እስከሚያደክመን ድረስ አያቆምም። ለእንደዚህ ዓይነት ጊዜያትና በልባችን ላይ ጫናው እጅግ
በሚሰማው ጊዜ ይህ የጌታ እራት መጽናናትን፣ ዐዲስ ብርታትን እና መታደስን እንዲያስገኝልን
ተሰጥቷል።
28 እዚህ ላይ እንደ ገና የእኛ አታላይ መናፍስት በከፍተኛ ትምህርታቸውና ጥበባቸው
ራሳቸውን ያወለጋግዳሉ። «ኅብስትና ወይን እንዴት የኃጢአት ይቅርታ ሊያስገኙ ወይም
እምነትን ሊያጠነክሩ ይችላሉ?» እያሉ ይጮኻሉ፤ ይለፈልፋሉ። አታላዮቹ መናፍስት ኅብስት
በራሱ ኅብስት ስለ ሆነ ይህንን ያደርጋል እንደማንል ነገር ግን የክርስቶስ ሥጋና ደም ስለ
29 ሆኑት እና በቃሉ ስለ ታጀቡት ኅብስትና ወይን እንደምንናገር ሰምተዋል፤ ያውቃሉም። ይህ
ዓይነቱ የኃጢአት ይቅርታ የሚገኝባቸው መንገዶች ሌሎች ነገሮች ሳይሆኑ እነዚህ መዝገቦች
ናቸው እንላለን። ይህ መዝገብ የሚተላለፍልንና ወደ እኛ እንዲደርስ የሚደረገው በሌላ በምንም
መንገድ ሳይሆን «ለእናንተ የተሰጠ ለእናንተ የፈሰሰ» በሚሉት ቃላት አማካይነት ነው። እዚህ
ላይ ሁለቱንም ታገኛላችሁ፤ ያም የክርስቶስ ሥጋና ደም፣ እነርሱም እንደ መዝገብና ስጦታ
የእናንተ ናቸው። የክርስቶስ ሥጋ ምንም የማያደርግና ማንንም የማይረዳ ዋጋ የሌለውና
30 የማይጠቅም ነገር ሊሆን አይችልም። ይሁን እንጂ፣ ስጦታው የቱንም ያህል በራሱ ታላቅ
ቢሆንም በቃሉ ዐውድ ውስጥ ሊቀመጥና በቃሉ አማካይነት ሊሰጠን ይገባዋል። አለበለዚያ ስለ
እርሱ በጭራሽ ልናውቅ ወይም ልንፈልገው አንችልም።
31 ስለዚህ አታላዮቹ መናፍስት የክርስቶስ ሥጋና ደም በጌታ እራት እንዳልተሰጠንና
እንዳልፈሰሰልን ተደርጎ በቅዱስ ምሥጢሩ የኃጢአት ይቅርታ ልናገኝ እንደማንችል
መናገራቸው የማይመስል ነገር ነው። ምንም እንኳ ሥራው በመስቀል ላይ የተከናወነና የኃጢአት
ይቅርታ የተገኘ ቢሆንም ስጦታው በቃሉ አማካይነት እንጂ በሌላ በማናቸውም መንገድ ወደኛ
ሊመጣ አይችልም። በአፍ በሚነገረው ቃል በስብከት ባይታወጅልን ኖሮ ያ መከናወኑን ወይም
ለእኛ መሰጠቱን እንዴት ልናውቅ እንችል ነበር? ቅዱሳት መጻሕፍትንና ወንጌሉን በጽናት
ከማመን ውጭ ከምን ምንጭ ስለ ይቅርታ ሊያውቁ፣ ሊጨብጡትና የራሳቸው ሊያደርጉት
32 ይችላሉ? እንግዲህ «በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን … በኃጢአት ስርየት አምናለሁ»
የሚለው መላው ወንጌልና የእምነታችን መግለጫ አንቀጽ በዚህ ቅዱስ ምሥጢር ውስጥ
የተካተቱና በቃሉ አማካይነት የተሰጡን ናቸው። ታዲያ እንዲህ ዓይነት መዝገብ ከቅዱስ

228 ምሳሌያዊ አገላለጽ።

ቍርባን ተቈርጦ እንዲወጣ መፍቀድ ለምን ይገባናል? በወንጌሉ ውስጥ በየቦታው የምንሰማቸው
ቃላት እነዚሁ እንደ ሆኑ እነርሱ[229] አሁንም መናገር ይገባቸዋል። ከቅዱስ ምሥጢሩ ተለይተው
መላው ወንጌሉ ወይም የእግዚአብሔር ቃል ምንም ዋጋ የላቸውም ለማለት መድፈር
እንደማይችሉ ሁሉ በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት እነዚህ ቃላት ምንም ዋጋ የላቸውም ማለት
አይችሉም።

33 እስከዚህ ድረስ መላውን ቅዱስ ምሥጢር በራሱ ምን እንደሆነና ከሚያስገኘውና
ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ተመልክተነዋል። እንግዲህ ይህንን ዓይነት ኃይልና ጥቅም የሚቀበለው
ሰው ማን እንደ ሆነ ደግሞ ማጤን ይገባናል። ባጭሩ እላይ ስለ ጥምቀትና በሌሎች በርካታ
ቦታዎች እንዳልነው መልሱ፡- ቃላቱ የተነገሩት ወይም የተሰበኩት ለድንጋይና ለእንጨት
ሳይሆን ለሚሰሟቸው፣ «እንካችሁ ብሉ፣» ወዘተ. ለተባሉት ሰዎች ስለ ሆነ ቃላቱ የሚሉትን
34 እና የሚሰጡትን ለሚያምን ሰው ነው የሚል ነው። እንዲሁም ኢየሱስ የኃጢአት ይቅርታን
ዝግጁ ሲያደርግና ሲሰጥ ይህንን ስጦታውን መቀበል የሚቻለው በእምነት እንጂ በሌላ መንገድ
አይደለም። «የምሰጣችሁ፣ እንዲሁም እንድትበሉና እንድትጠጡ የምነግራችሁ የራሳችሁ
እንድታደርጉት፣ እንድትደሰቱበትና እንድትወስዱት ነው» ያለ ያክል «ለእናንተ የተሰጠ» እና
«ለእናንተ የፈሰሰ» ሲል በቃሉ ይህንን እምነት እርሱ ራሱ ከእኛ ይጠይቃል። እነዚህ ቃላት
እንዲነገሯቸው የሚፈቅዱትና እውነት መሆናቸውን የሚያምኑ ሁሉ በቃላቱ የተነገሩትን
35 ያገኛሉ። ነገር ግን የማያምኑት ይህ ጸጋን የተሞላ በረከት በከንቱ እንዲቀርብላቸው
በመፍቀዳቸውና ሊደሰቱበት ባለመፈለጋቸው ምንም አያገኙም። መዝገቡ ተከፍቶ በየሰው በር፣
አዎ፣ በጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል፤ ነገር ግን ያንን መውሰድና ልክ ቃላቱ እንደሚነግሩህ
የሚሆን መሆኑን በሙሉ ልብ ማመን ደግሞ ያንተ ኃላፊነት ነው።

36 እንግዲህ ይህንን ቅዱስ ምሥጢር እንደሚገባ ለመቀበል የአንድ ክርስቲያን አጠቃላይ
ዝግጅት ይህ ነው። ይህ ስጦታ በቃላቱ ሙሉ በሙሉ ስለ ተሰጠ በልብ ብቻ መጨበጥና የራስ
37 ማድረግ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት ስጦታና ዘለዓለማዊ መዝገብ በእጅ ሊያዝ አይችልም።
አንድ ሰው የክርስቶስን ሥጋና ደም በተገቢው መልኩና አክብሮት እንዲይዝ ለማድረግ ጾም፣
ጸሎትና የመሳሰሉት እንደ ሜዳዊ ዝግጅትና እንደ ልጆች እንቅስቃሴ የራሳቸው ድርሻ
ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ሥጋ በቅዱስ ቍርባንና ከእርሱ ጋር የሚሰጠውን ስጦታ
መጨበጥና የራሱ ማድረግ አይችልም። ይህ የሚደረገው እንዲህ ዓይነት መዝገብን ለይቶ
በሚያይና በሚያምን የልብ እምነት ነው።

38 ይህን ቅዱስ ምሥጢር አስመልክቶ ለአጠቃላይ የማስተማር ዓላማ አስፈላጊነት ይህ
ይበቃል። ስለ እርሱ መባል ያለበት የቀረ ነገር ለሌላ ጊዜ ተትቶአል።[230]

39 በመደምደምም ቅዱስ ምሥጢርን በተመለከተ አሁን ትክክለኛውን ትርጓሜና
አስተምህሮ ስላገኘን ይህ በክርስቲያኖች ዘንድ በየዕለቱ የሚከናወነውና የሚታደለው ታላቅ
መዝገብ በከንቱ እንዲያልፍ እንዳናፈቅድ ምክርና ማበረታቻ እጅግ ያስፈልገናል። እኔ የምለው
ክርስቲያኖች መሆን የሚፈልጉ ይህንን የተባረከ ቅዱስ ምሥጢር አዘውትረው ለመቀበል
40 ራሳቸውን ማዘጋጀት ይገባቸዋል ነው። ምክንያቱም ሰዎች ቅዱስ ምሥጢርን ለመውሰድ
ግድየለሾችና ሰነፎች በመሆን ላይ እንደ ሆኑ ዐይተናል። አሁን የጳጳሱ ፍሬ ቢስ ነገር ስለ ቀረና
ከአስገዳጅነቱና ከትእዛዛቱ ነጻ ስለ ሆኑ ቅዱስ ምሥጢር የማያስፈልጋቸው ጠንካራ ክርስቲያኖች
የሆኑ ይመስል ወንጌልን የሚሰሙ በርካታ ሰዎች ሳይቀበሉት አንድ ወይም ሁለት ወይም ሦስት
41 ወይም ከዚያ ለበለጠ ዓመታት እንዲያልፉ ይፈቅዳሉ። ሌሎች ወደዚያ የሚገፋፋቸው ረሀብና
ጥማት እስካልተሰማቸው ድረስ ማንም ሊቀበል እንደማያስፈልገው ከማሰባችን የተነሣ ከእርሱ
እንዲከለከሉና እንዲታገዱ ፈቅደዋል። አሁንም ሌሎች አስፈላጊ ሳይሆን የምርጫ ጉዳይ እንደ
ሆነና በቀላሉ ካመኑ በቂ እንደ ሆነ ያስመስላሉ። በመሆኑም እጅግ አብላጫው ሕዝብ ርቀው
ሄደው ፍጹም አረመኔ ይሆኑና በመጨረሻም ቅዱስ ቍርባንን እና የእግዚአብሔርን ቃል
ይንቃሉ።

---

[229] Sacramentarian በሳክራሜንታሪያውያን ውዝግብ የሉተር ተቃዋሚዎች፣ Zwinglians ዝዊንግሊያውያንና ዳግም አጥማቂዎች።

[230] ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሉተር *Admonition concerning the Sacrament of the Body and Blood of Our Lord* (1530) (WA 30/2: 595-626; LW 38:91-137)ን ጻፈ።

42 እንግዲህ እውነት ነው፣ ቀደም ሲል እንዳልነው ዐዲስ የነፍሳት መግደያ ድርጅት
እንዳናቋቁም ማንም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ተገዶ ወይም ያለ ፍላጎቱ ቅዱስ ምሥጢርን
ሊቀበል አይገባም። ሆኖም ለረጅም ጊዜ ከቅዱስ ቊርባን የሚታቀቡና ራሳቸውን የሚያገልሉ
ዓይነት ሰዎች እንደ ክርስቲያኖች ሊቈጠሩ እንደማይገባ ሊታወቅ ይገባል። ምክንያቱም
ክርስቶስ ቅዱስ ቊርባንን እንደ ታይታ ነገር እንድንይዘው አልመሠረተልንም፤ ነገር ግን
ክርስቲያኖቹ እንዲበሉትና እንዲጠጡት በዚያውም እንዲያስታውሱት አዟል።
43 በእርግጥ ቅዱስ ቊርባንን የሚወዱና የሚያከብሩ እውነተኛ ክርስቲያኖች በገዛ ራሳቸው
ፈቃድ ለመሄድ ራሳቸውን ማነሣሣትና ማስገደድ ይገባቸዋል። ነገር ግን ክርስቲያኖች መሆን
የሚፈልጉትን የዋሃንና ደካሞችን ቅዱስ ምሥጢርን የመቀበሉን ምክንያትና አስፈላጊነት
44 ለማሳመን ስለዚህ ነገር ትንሽ መናገር አለብን። ይሁን እንጂ፣ ከእምነት፣ ከፍቅርና ከትዕግሥት
ጋር እንደ ተያያዙት ሌሎች ጒዳዮች ማስተማርና ማሳወቅ ብቻ አይበቃም፤ ነገር ግን ሰዎች
ግድየለሾችና የተሰላቹ እንዳይሆኑ በዚህ ጒዳይ ላይ ቀጣይነት ባለው ስብከት የየዕለቱ ማበረታቻ
ደግሞ ሊኖር ይገባል። ምክንያቱም ዲያብሎስ በተቻለው መጠን ይህንን በመቃወም
ከማንኛውም ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ሰዎችን በማባረርና በማሳደድ ዘወትር እንዴት
እንደሚዋጋ እናውቃለን።
45 በመጀመሪያ ደረጃ፣ በራሱ በክርስቶስ ቃላት «ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚል
ግልጽ ጽሑፍ አለን። እነዚህ ቃላት ክርስቲያኖች መሆን የሚፈልጉትን ሁሉ ቅዱስ ምሥጢርን
እንዲካፈሉ እያበረታቱ የሚያስተምሩንና የሚያዙን ናቸው። ስለዚህ እዚህ ላይ የክርስቶስ ደቀ
መዝሙር መሆን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ክርስቶስ የሚናገራቸው እነርሱን ነውና በሰዎች
ተገፋፍተን ከግዴታ የተነሣ ሳይሆን ጌታ ክርስቶስን ለመታዘዝና ለማስደሰት ይህንን ቅዱስ
46 ምሥጢር በታማኝነት ልንይዘው ይገባናል። ይሁን እንጂ፣ እዚህ ላይ አንተ፦ «ግን 'ይህንን
ባደረጋችሁት ጊዜ ሁሉ' የሚሉት ቃላት ተጨምረዋል፤ ስለዚህ እርሱ ማንንም አያስገድድም
47 ነገር ግን ለእኛ ነጻ ምርጫ ይተወዋል» ትል ይሆናል። መልስ፦ ያ እውነት ነው፤ ነገር ግን
በጭራሽ መካፈል አይገባችሁም አይልም። በእርግጥ፦ «ይህንን ባደረጋችሁት ጊዜ ሁሉ»
የሚሉት ቃላት በትክክል አዘውትረን ልናደርገው እንደሚገባን የሚጠቁም ዐሳብ አላቸው።
አይሁዶች በመጀመሪያዋ ሙሉ ጨረቃ፣[231] ዐሥራ አራተኛ ምሽት ያለ አንዳች የቀን መዛነፍ
በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲበሉ እንደሚገደዱበት እንደ ፋሲካ ምግብ በተለየ ጊዜ የተወሰነ
ሳይሆን ቅዱስ ቊርባኑ ነጻ እንዲሆን ከመፈለጉ የተነሣ ነው እነዚህ ቃላት የተጨመሩት።
48 (ምንም እንኳ በኋላ ላይ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አጣሞት ወደ አይሁዳውያን በዓል ቢመልሰውም)
«ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ዕድሉና እንደሚያስፈልገው ለየትኛውም የተለየ ቦታ ወይም ጊዜ
ሳይገደብ ከዓመቱ በዚህች አንድ ምሽት ሳይሆን ነገር ግን አዘውትራችሁ በፈቀዳችሁት
በየትኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የምትደሰቱበትን ፋሲካ ወይም እራት እየመሠረትኩላችሁ
ነው» ማለቱ ነው።[232]
49 ስለዚህ ቅዱስ ቊርባንን ለመናቅ ነጻነት እንዳልተሰጠን ትመለከታለህ። ሰዎች
የሚያደናቅፋቸው ምንም ነገር ሳይኖር ቅዱስ ቊርባንን ሳይፈልጉ ረጅም ጊዜ እንዲያልፍ
ሲፈቅዱ መናቅ ብዬ እጠራዋለሁ። እንደዚህ ዓይነት ነጻነት ስትፈልግ ክርስቲያን ያለመሆንንም
ቀጣይ ነጻነት ጭምር መውሰድ ትችላለህ፤ ያኔ አንደኛው ትእዛዝ የሌላኛውን ያህል የክርስቶስ
ትእዛዝ ስለ ሆነ ማመን ወይም መጸለይ አያስፈልግህም። ምክንያቱም፣ አንደኛው ልክ የሌላውን
ያህል የክርስቶስ ትእዛዝ ነው። ነገር ግን ክርስቲያን መሆን ከፈለግህ ይህ ትእዛዝ
50 እንደሚፈልግብህ ማድረግና መታዘዝ ይገባሃል። እንደዚህ ዓይነት ትእዛዝ ሁልጊዜ ራስህን
እንድትመረምርና፦ «እነሆ ምን ዓይነት ክርስቲያን ነኝ? ክርስቲያን ብሆን ኖሮ ጌታዬ
እንዳደረገው ያዘዘኝን ለማድረግ ቢያንስ ትንሽ ፍላጎት ይኖረኝ ነበር» ብለህ እንድታስብ
ሊያደርግህ ይገባል።

---

[231] ዘሌዋውያን 23፡5።

[232] ክርስቲያኖች «ቢያንስ በፋሲካ ጊዜ የሥጋ ወደሙን ቅዱስ ምሥጢር መቀበል» አለባቸው ተብሎ በአራተኛው የሉተራን ጉባኤ (1215) ታውጆአል።

51 በእርግጥ ለቅዱስ ቊርባን እንዲህ ዓይነት ጥላቻ ከማሳየታችን የተነሣ በጳጳሳዊው
ሥርዓት ሥር እያለን በግዴታና ከሰው ትእዛዛት ፍርሃት የተነሣ ብቻ ያለ ደስታና ፍቅር፣
ለክርስቶስ ትእዛዝ ግድ ሳይኖረን ወደ ቅዱስ ቊርባን ስንሄድ ምን ዓይነት ክርስቲያኖች እንደ
52 ነበርን ሰዎች በቀላሉ ማወቅ ይችላሉ። ነገር ግን እኛ ማንንም አንገፋፋም ወይም አናስገድድም፣
ማንም ደግሞ እኛን ለማገልገል ወይም ለማስደሰት እንደዚያ ማድረግ አያስፈልገውም።
ሊያነሣሣህ እና ሊያሳምንህ የሚገባው ኢየሱስ የሚፈልገውና እርሱን የሚያስደስተው መሆኑ
ነው። ወደ እምነት እንድትመጣ ወይም የትኛውንም በጎ ሥራ እንድትሠራ በሰዎች
እንድትገደድ መፍቀድ አይገባህም። እኛ እያደረግን ያለነው ስለ እኛ ብለህ ሳይሆን ለገዛ ራስህ
ብለህ ልታደርገው የሚገባህን ነገር እንድታደርግ አጥብቀን እየመከርንህ ነው። ኢየሱስ
ይጋብዝሃል፣ ያበረታታሃል፣ አንተ ግን ለቅዱስ ምሥጢሩ ንቀት ማሳየት ከፈለግህ አንተው
ራስህ መልስ መስጠት ይገባሃል።

53 በተለይ በራዶቹና ግድየለሾቹ ወደ ማስተዋላቸው እንዲመጡና እንዲነቁ ይህ
የመጀመሪያው ነጥብ ነው። አንድ ሰው ከቅዱስ ምሥጢር ሲርቅ ዕለት በዕለት ይበልጥ ልበ
ደንዳና እና በራድ እየሆነ በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ እንደሚያጣጥለው ሰዎች ሁሉ ከራሳቸው
54 ሁኔታ እንደሚገነዘቡት ከገዛ የሕይወት ተሞክሮዬ መረዳቴ በእርግጥ እውነት ነው። ይህንን
ለማስወገድ ልባችንን እና ሕሊናችንን መመርመርና ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ግንኙነት
እንዲኖረው በእርግጥ እንደሚፈልግ ሰው ማድረግ አለብን። ይበልጥ ይህንን ባደረግን መጠን
ልባችን ይበልጥ የሞቀና የተለኮሰ ይሆንና ሙሉ በሙሉ በራድ መሆኑ ይቀራል።

55 ነገር ግን፦ «የምገባ እንዳልሆንኩ ቢሰማኝስ?» አልክ እንበል። መልስ፦ ይህ
እግዚአብሔር እጅግ በጣም አነስተኛዋን እንከን እንዳያገኝብን ፍጹም ንጹሐን ለመሆን ራሳችንን
እንድናሠቃይ በጳጳሳዊ ሥርዓት ሥር ከነበረው ከቀደመው ሥርዓት በተለይ የወረስነው ሲሆን
56 የእኔም ትግል ነው። ከዚህ የተነሣ ሰው ሁሉ፦ «ወዮ የምትገባ አይደለህም!» በሚል ጭንቀት
ውስጥ እስኪገባ ድረስ እጅግ ድንጉጥ ሆንን። ከዚያም ተፈጥሮና አመክንዮ የእኛን ተገቢ
አለመሆን ከዚህ ታላቅ እና የከበረ በረከት ጋር ማቃረን ሲጀምሩ ደማቋ ፀሐይ ከጨለማ ፋኖስ
ጋር የምትቃረነውን ወይም ፍግ ከዕንቊዎች ጋር የሚቃረነውን ያህል ይሆናል። እንደዚህ
ዓይነት ሰዎች ይህን ከማየታቸው የተነሣ ወደ ቅዱስ ምሥጢር አይቀርቡም፤ እስኪዘጋጁ አንድ
ሳምንት ወደ ሌላኛው እና አንዱ ግማሽ ዓመት አሁንም ወደ ሌላ ዓመት እስኪያልፍ ይጠ
57 ብቃሉ። ዓይኖችህን መልካም እና ንጹሕ መሆንህ ላይ ለማሳረፍና ምንም ነገር እስከማያሠቃይህ
ድረስ ለመቆየት ከፈለግህ በጭራሽ ወደ ቅዱስ ምሥጢር አትሄድም።

58 ከዚህ የተነሣ በሰዎች መካከል ልዩነት ማድረግ ይገባናል። ጋጠወጥ እና ልቅ የሆኑት
ከቅዱስ ምሥጢሩ እንዲርቁ ሊነገራቸው ይገባል። ምክንያቱም የኃጢአትን ይቅርታ ለመቀበል
ዝግጁዎች ስላልሆኑ የኃጢአትን ይቅርታ ለመቀበል አይመኙም ጻድቃን ለመሆንም
59 አይፈልጉም። ይሁን እንጂ፣ እጅግ ደንዳኖች እና የረከሱ ያልሆኑ ነገር ግን መልካም ለመሆን
የሚፈልጉ ሌሎች ደካሞችና ተሰባሪዎች ቢሆኑም በራሳቸው መቅረት አይገባቸውም። ቅድስት
ሂላሪ ደግሞ እንዳለችው «ሰዎች ከማኅበረ ምእመናን እንዲወጡ የሚያደርጓቸውና የክርስቲያንን
ስም መብት የሚያሳጡ ዓይነት ኃጢአቶች ካላደረጉ በስተቀር» ራሳቸውን ከሕይወት
60 እንዳይከለክሉ «ከቅዱስ ምሥጢር ራሳቸውን ማግለል አይገባቸውም።»[233] ሰዎች በሥጋና
በደማቸው ውስጥ በርካታ የተለመዱ ድካሞች በማይገኙበት ነጥብ ላይ በጭራሽ አይደርሱም።

61 እንደዚህ ዓይነት ጥርጣሬ ያላቸው ሰዎች ይህ ቅዱስ ምሥጢር በእኛ ተገቢ መሆን ላይ
አለመመሥረቱን መገንዘብ እጅግ ከፍተኛው ጥበብ እንደ ሆነ መማር ይገባቸዋል። ምክንያቱም
የተጠመቅነው የሚገባንና ቅዱሳን ስለ ነበርን አልነበረም፤ ወደ ኃጢአት ኑዛዜም የመጣነው
ንጹሐንና ያለ ኃጢአት ሆነን አይደለም፤ በተቃራኒው ምስኪን ኃጢአተኞችና ችጋረኞች
እንዲያውም የማይገባን ስለ ሆንን እንመጣለን። እዚህ የማይካተተው ጿጋና ከኃጢአት መፈታት
የማይፈልግ፣ እንዲሁም ምንም የመሻሻል ዐሳብ የሌለው ሰው ነው።

[233] Gratian, *Decretum* III, dist. 2, chap. 15, ሂላሪን በመጥቀስ፦ «የአንድ ሰው ኃጢአት ውግዘትን የሚጠይቅ በጣም ትልቅ ካልሆነ፣ ከጌታ ሥጋ መድኃኒት ራሱን ማግለል የለበትም፡» ይሁን እንጂ ምንባቡ በአውግስጢኖስ፣ Epistle 54, c. 3 (*MPL* 33:201; *NPNF*, ser. 1, 1:301) ይገኛል።

62 ነገር ግን ጸጋንና መጽናናትን አጥብቀው የሚፈልጉ ሰዎች፡- «በእውነት የተገባሁ መሆን
እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን የምመጣው በየትኛውም የራሴ ተገቢነት ሳይሆን አንተ ስላዘዝህ ነው፤
የሚገባኝ ወይም የማይገባኝ መሆኔን ሳልመለከት ደቀ መዝሙርህ መሆን እፈልጋለሁ» በማለት
ለመሄድ ራሳቸውን ማስገደድና ማንም እንዲከለክላቸው ባለመፍቀድ መቅረብ ይገባቸዋል፡፡
63 ይሁን እንጂ፣ ዘወትር የሚታገለን ይህ እንቅፋትና መሰናክል ስላለብንና ከክርስቶስ አፍ ከወጡት
ቃላት ይልቅ በራሳችን ላይ ይበልጥ ስለምናተኵር ይህ አስቸጋሪ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ
በራሱ ላይ በጽናት እንዲያርፍና እንዲደገፍ በሚያደርገው መንገድ ነው አንድን ነገር ማድረግ
የሚወደው፤ አለበለዚያ አንዲት እርምጃ እንኳ ለመራመድ እምቢ ባይ ነው፡፡ ለመጀመሪያው
ነጥብ ይህ ይብቃ፡፡
64 በሁለተኛ ደረጃ፣ እላይ እንደ ሰማነው እጅግ በጣም በኃይል ሊስበንና ሊያስገድደን
የሚገባን ከትእዛዙ ጋር የተያያዘ አንድ የተስፋ ቃል አለ፡፡ እዚህ ላይ «ይህ ስለ እናንተ የተሰጠ
ሥጋዬ ነው፣» «ይህ ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ የፈሰሰ ደሜ ነው» የሚሉት ጸጋን
65 የተሞሉና አስደሳች ቃላት አሉ፡፡ ቀደም ሲል እንዳልኩት እነዚህ ቃላት ለአንተ እና ለእኔ
እንጂ ለእንጨት ወይም ለድንጋይ አልተሰበኩም፤ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ዝም ማለትና ቅዱስ
ምሥጢርን አለማቋቋም መልካም ይሆን ነበር፡፡ እንግዲያውስ ለአንተም በከንቱ እንዳይናገር
ራስህን በግል «እናንተ» በሚለው ቃል ውስጥ ጨምርና አሰላስል፡፡
66 ምክንያቱም በማቴዎስ 11፡28 «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤
እኔም ዐሳርፋችኋለሁ» እንደሚልና በሌሎችም ቦታዎች በደስታ እጅግ በጣም እንደሚጋብዘን
67 በዚህ ቅዱስ ምሥጢርም ከሰማይ ያመጣልንን በረከቶች ሁሉ ይሰጠናል፡፡ እርሱ ለእኛ እጅግ
ከፍተኛና እጅግ የላቀ ጥቅም ሊሰጠን በታላቅ ርኅራኄና በታማኝነት ሲጠራንና ሲያበረታታን
ፍጹም እስክንቀዘቅዝና እስክንደነድን፣ ለእርሱ ፍላጎትና ፍቅር እስክናጣ ድረስ ለረጅም ጊዜ
በእንደዚህ ዓይነት ጥላቻና ቸልታ ስንመለከተው በእርግጥም ይህ ኃጢአትና እፍረት ነው፡፡
68 ቅዱስ ምሥጢርን እንደ ጎጂ ነገር አድርገን ከእርሱ ልንሸሽ እንደሚገባ መቍጠር የለብንም፤
ነገር ግን እንደ ንጹሕ፣ ለጤና ጠቃሚ፣ የሚረዳ፣ መድኃኒትና በነፍስም በሥጋም ሕይወት
የሚሰጥ አድርገን ልንቈጥረው ይገባናል፡፡ ምክንያቱም ነፍስ ስትፈወስ አካልንም ይጠቅማል፡፡
ታዲያ ከቅዱስ ምሥጢር ስንበላ የሚገድለን መርዝ ለምን እናደርጋለን?
69 በእርግጥ ቅዱስ ምሥጢሩን የሚንቁና ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሕይወት የሚመሩ ሰዎች
ለጉዳታቸውና ለኵነኔአቸው የሚቀበሉት መሆኑ እውነት ነው፡፡ የታመመ ሰው በሐኪም
የተከለከለውን በፈቃዱ እንደሚበላና እንደሚጠጣ ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ቅዱስ ምሥጢሩ
70 መልካም ወይም ጤና ሰጪ አይሆንላቸውም፡፡ ድካማቸው የሚሰማቸውና እንዲወገድላቸው
የሚጓጉትና እርዳታ የሚፈልጉ ግን በሰውነታቸው ላለው መርዝ እንደ ውድ ማርከሻ ቈጥረው
ቅዱስ ምሥጢርን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቅዱስ ምሥጢር ጋራ
የእግዚአብሔርን ጸጋና ከስጦታዎቹ ሁሉ ጋር ከለላን፣ መከታንና በሞት፣ በዲያብሎስና
በማንኛውም መከራ ላይ ኃይል ያለውንና የሚያመጣውን የእግዚአብሔርን ጸጋና መንፈስ
ቅዱስን የኃጢአት ይቅርታ ከክርስቶስ አፍ ትቀበላላችሁ፡፡
71 በመሆኑም በእግዚአብሔር በኩል የጌታ ክርስቶስ ትእዛዝና የተስፋ ቃል አላችሁ፡፡ ይህ
በእንዲህ እንዳለ በእናንተ በኩል በአንገታችሁ ዙሪያ ላይ በተንጠለጠለውና ለዚህ ትእዛዝ
ግብዣና የተስፋ ቃል ምክንያት በሆነው አስፈላጊ ነገራችሁ ልትታገሡ ይገባል፡፡ እርሱ ራሱ
[በማቴዎስ 9፡12] «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም» ያለው
በኃጢአት፣ በሞት ፍርሃትና በሥጋና በዲያብሎስ ጥቃቶች ለደከሙና ለተቸገሩ ነው፡፡
72 የከበዳችሁና ድካም የሚሰማችሁ ከሆናችሁ እንድትታደሱ፣ እንድትጽናኑና እንድትበረቱ ወደ
73 ቅዱስ ምሥጢር በደስታ ሂዱ፡፡ ምክንያቱም በንጽሕናና በብቃት በሚገባ ሁኔታ ወደ ቅዱስ
ምሥጢሩ ለመምጣት ከሸክማችሁ እስክትላቀቁ ድረስ የምትጠብቁ ከሆነ ለዘለዓለም ርቃችሁ
74 መቆየት ይሆንባችኋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ «ንጹሕና ቅን ከሆንክ እኔ
አላስፈልግህም አንተም አታስፈልገኝም» የሚል ብያኔ እርሱ ያሰማሃል፡፡ ስለዚህ ወደ ቅዱስ
ምሥጢሩ መምጣት የማይገባቸው ሸክማቸው የማይሰማቸው ወይም ኃጢአተኛ መሆናቸውን
የማይቀበሉ ብቻ ናቸው፡፡

75 «ይህ አስፈላጊነቱ ሊሰማኝ የማይችል ወይም ለቅዱስ ምሥጢሩ መራብና መጠማት
የሌለኝ ከሆነ ምን ላድርግ?» ትላለህ እንበል፡፡ መልስ፡- በማይሰማቸው የዐስተሳሰብ ሁኔታ ውስጥ
ላሉት ዓይነት ሰዎች ከሥጋና ከደም ተፈጥረው እንደ ሆነ ለማወቅ እጃቸውን ሆዳቸው ላይ
እንዲያስቀምጡ ከመንገር የተሻለ ምክር ዐላውቅም፡፡ ሥጋና ደም ሆናችሁ ራሳችሁን ካገኛችሁት
ለገዛ ራሳችሁ ጥቅም ስትሉ ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ወደጻፈው መልእክት ዘወር በሉና
የሥጋችሁ ፍሬዎች ምን እንደሆኑ ስሙ፤ «የሥጋ ሥራም የተለገጠ ነው [ይላል] እርሱም
ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቍጣ፣
አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም
የሚመስል ነው»፡፡[234]

76 በዚህ ምክንያት አስፈላጊነቱ ሊሰማችሁ ባይችል ቢያንስ ቅዱሳት መጻሕፍትን እመኑ፡፡
ራሳችሁን ከምታውቁት የተሻለ ሥጋችሁን ስለሚያውቁ አይዋሹአቸውም፡፡ አዎን ቅዱስ
ጳውሎስም በሮሜ 7፡18 «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር ዐውቃለሁ» ሲል
ይደመድማል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ገዛ ራሱ ሥጋ በዚህ መንገድ ከተናገረ እኛ የተሻልን ወይም
77 የበለጠ ቅዱስ ለመሆን አንመኝ፡፡ ነገር ግን የማይሰማን የመሆኑ እውነት ከሁሉ የከፋ ነው፣
ሥጋችን በበሽታ እየተሠቃየ ራሱን እያጎሳቆለና እያስጨነቀ ቢሆንም ምንም ነገር የማይሰማው
78 ለምጻም ወይም የሥጋ ደዌ በሽተኛ ሥጋ የመሆኑ ምልክት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳልነው
በኃጢአት ፍጹም የሞትክ ብትሆን እንኳ ቢያንስ ይህንን ፍርድ በአንተ ላይ የሚናገሩትን
ቅዱሳት መጻሕፍትን እመን፡፡ በአጭሩ ኃጢአትህና ድካምህ ባልተሰሙህ መጠን ወደ ቅዱስ
ምሥጢር ለመሄድና እርዳታውንና መድኃኒቱን ለመፈለግ ይበልጥ ምክንያት ይኖርሃል፡፡

79 እንደገናም ዙሪያህን ተመልከትና በዓለም ውስጥ እንደሆንክና እንዳልሆንክ እይ፡፡
ካላወቅህ ስለዚህ ጉዳይ ባልንጀሮቻህን ጠይቅ፡፡ በዓለም ውስጥ ከሆንክ የኃጢአቶችና የችግሮች
እጥረት ይኖራል ብለህ ዐታስብ፡፡ ቅን ለመሆንና ወንጌሉን የሙጥኝ ለማለት እንደምትፈልግ
ሆነህ መንቀሳቀስ ጀምርና የሚጎዱህ፣ ክፉ የሚያደርጉብህ፣ የሚበድሉህ እና ኃጢአትና ክፉ
እንድታደርግ ምክንያት የሚሆኑብህ  ጠላቶች ያጋጥሙህ ወይ አያጋጥሙህ እንደሆነ እይ፡፡ ይህ
በሕይወትህ ካልገጠመህ እንግዲያውስ ስለ ዓለም ይህን ምስክርነት በየቦታው በሚሰጡት
ከቅዱሳት መጻሕፍት ስማ፡፡

80 በተጨማሪም ዲያብሎስ በዙሪያህ በርግጥ ይኖራል፡፡ ጌታችን ክርስቶስም ሙሉ በሙሉ
81 ስላላስወገደውና ስላልቻለ አንተም ከእግሮችህ በታች ሙሉ በሙሉ አትጨፈልቀውም፡፡ እንግዲህ
ዲያብሎስ ምንድን ነው? ቅዱሳት መጻሕፍት ሐሰተኛና ነፍሰ ገዳይ ብለው እርሱን ከሚጠሩበት
የተለየ አይደለምን፡፡[235] ችግርህ ሊሰማህ እንዳይችል ወይም ወደ ክርስቶስ መምጣት እንዳትችል
በማድረግ ልብን ከእግዚአብሔር ቃል እንዲርቅ የሚያባብልና የሚሰውር ሐሰተኛ ነው፡፡
82 በሕይወትህ በየሰዓቱ የሚመቀኝህ ነፍሰ ገዳይ ነው፡፡ በየቅጽበቱ ምን ያህል ሾተሎች፣ ጦሮችና
ቀስቶች እንደሚነጣጠሩብህ ማየት ብትችል ኖሮ ወደ ቅዱስ  ምሥጢር የቻልከውን ያህል
አዘውትረህ ለማምጣት ደስተኛ ትሆን ነበር፡፡ ፍጹም ያለ ፍርሃትና ያለ ጥንቃቄ የምንኖዝበት
ብቸኛ ምክንያት በሥጋ ውስጥ፣ በክፉ ዓለም ውስጥ ወይም ከዲያብሎስ መንግሥት ሥር
መሆናችንን ስለማንገምት ወይም ስለማናምን ነው፡፡

83 ስለዚህ የሚከተለውን ሞክር በሚገባ ተለማመደው፡፡ ራስህን መርምር፤ ዙሪያህን ትንሽ
ተመልከትና ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ አጥብቀህ ያዝ፡፡ አሁንም ምንም ስሜት የማይሰማህ
ቢሆን ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ወንድምህ ወይም እኅትህ ለመጮህ የበለጠ ምክንያት
ይኖርሃል፡፡ የሌሎችን ምክር ተቀበልና እንዲጸልዩልህ ጠይቃቸው፣ ድንጋዩ ከልብህ እስኪወገድ
84 ድረስ በጭራሽ ተስፋ አትቁረጥ፡፡ ያኔ ችግርህ ግልጽ ይሆንና እንደ ማንኛውም ሌላ ምስኪን
ኃጢአተኛ እጥፍ ወርደህ መስጠምህን እና መከራህን ለመፋለም ቅዱስ ምሥጢር እጅግ በጣም
እንደሚያስፈልግህ ታያለህ፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ለዚህ መከራህ ይበልጥ ንቁ እንድትሆንና ቅዱስ
ቍርባንን ይበልጥ እንድትፈልግ እግዚአብሔር ጸጋውን  ካልሰጠህ መከራው ዐይታይህም፡፡

---

[234] ገላትያ 5፡19-20፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሙ እንዳደረገው ሉተር «መግደል»ን በጽሑፉ ውስጥ የሚጨምረውን ንባብ ተከትሎ *ፖርኔያ porneia* የሚለውን ቃል «ዝሙት፣ ርኵሰት» ብሎ ይተረጒመዋል፡፡

[235] ዮሐንስ 8፡44፡፡

በተለይ ዲያብሎስ ለአንዲት ሰዓት እንኳ ከእርሱ በደኅንነት ተጠብቀህ መቆየት እንዳትችል ከቦ ስለሚመሸግብህ፣ ነፍስህንና ሥጋህን ለማጥመድና ለማጥፋት ባለማቋረጥ ስለሚያደባብህ ይህ ይደርስብሃል። ባልጠበቅህበት ጊዜ ድንገት መከራና ችግር ውስጥ ምንኛ ሊያስገባህ ይችላል!

85 እንግዲያውስ አረጋውያን ለሆንነውና በዕድሜ[236] ለገፋነው ብቻ ሳይሆን በክርስቲያናዊ
አስተምህሮና በትክክለኛው ግንዛቤ ሊያድጉ ለሚገባቸው ወጣቶችም ይህ እንደ ማበረታቻ
ያገለግል። በእንደዚህ ዓይነት ሥልጠና አሥርቱ ትእዛዛትን፣ የእምነት መግለጫን እና የጌታን
ጸሎት ወጣቶች በደስታ በሙሉ ልብ እንዲቀበሏቸው ከወጣትነታቸው ጀምረው
እንዲለማመዷቸውና የተላመዷቸው እንዲሆኑና ይበልጥ በቀላሉ እንዲሠርጹ ማድረግ እንችላለን።
86 ምክንያቱም በዕድሜ የገፉ ሰዎችን ለመለወጥ መሞከር ሙሉ በሙሉ ከንቱ ነው። ከእኛ በኋላ
የሚመጡትንና ኃላፊነታችንንና ሥራችንን የሚረከቡንን ሰዎች ካላሠለጠንን እነርሱም በተራቸው
ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉ ካላደረግን እነዚህና ሌሎች አስተምህሮዎች እንዲቀጥሉ ማድረግ
አንችልም። በዚህ መንገድ የእግዚአብሔር ቃልና ክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰብ፣ ተጠብቆ ይቆያል።
87 ስለዚህ የቤተ ሰብ ኃላፊዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንጋጌና ትእዛዝ ለልጆቻቸው ማስተማር
ወይም ሊያውቋቸው የሚገቡ ነገሮችን እንዲማሩ ማድረግ ግዴታቸው መሆኑን ያስታውሱ።
ምክንያቱም በመጠመቃቸውና ወደ ክርስቶስ ቤተ ሰቦች በመቀላቀላቸው በዚህ ምሥጢር
ኅብረት ሊደሰቱ ሊያገለግሉንና ጠቃሚ ሊሆኑልን ይገባቸዋል። ሁሉም እንድናምን፣
እንድንወድ፣ እንድንጸልይና ዲያብሎስን እንድንዋጋ ሊረዱን ስለሚገባቸው ነው።

*ለኃጢአት ኑዛዜ የሚሆን ማበረታቻ ቀጥሎ ይቀርባል።*[237]

## አጭር የኃጢአት ኑዛዜ ማበረታቻ

1 *የኃጢአት ኑዛዜን በተመለከተ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተና ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ*
*አምባገነናዊ አገዛዝ የጠራ ሊሆን እንደሚገባው ዘወትር እናስተምራለን። እርሱ በክርስቲያን*
*ማኅበረ ሰብ ላይ ካሰፈረው አስገዳጅና ሊሸከሙት ከማይችሉት ሸክም ነጻ ወጥተናል። እስከ*
*አሁን ድረስ ሁላችንም ከሕይወት ልምድ እንደምናውቀው እጅግ በጣም ለከፋ ኃጢአት ሰው*
*ሁሉ አስጨናቂ የኃጢአት ኑዛዜ እንዲያደርግ የሚያስገድደውን እጅግ ጨቋኝ ሕግ የመሰለ*
2 *አልነበረም። በተጨማሪም ማንም በበቂ ሁኔታ ሊናዘዛቸው የማይችላቸው የሁሉም ኃጢአት*
3 *ዓይነቶች ዝርዝር ሕሊናዎችን እጅግ የሚጫንና የሚያሠቃይ ነው። ከሁሉ የከፋው ደግሞ*
*የኃጢአት ኑዛዜ ምን እንደሆነና ምንስ ያህል ጠቃሚና አጽናኝ እንደሆነ ማንም አልተማረም*
*ወይም አልተረዳውም። ይልቁንም ከዚያ የበለጠ የሚጠሉት ሌላ ምንም ነገር ባይኖርም ሰዎች*
*የኃጢአት ኑዛዜ ማድረግ ስለነበረባቸው ሙሉ በሙሉ በጭንቀትና በሲኦላዊ ኃይለኛ ሥቃይ*
4 *ይደረግ ነበር። እነዚህ ሦስት ነገሮች አሁን ተወግደው በፈቃደኝነት የሚደረጉ ሆነዋል፤*
*እነርሱም ያለ ግዳጅ ወይም ፍርሃት ኃጢአት መናዘዝ መቻላችን፤ ኃጢአቶችን ሁሉ አንድ*
*ባንድ ከመዘርዘር ኃይለኛ ሥቃይ መፈታት፣ በመጨረሻም የኃጢአት ኑዛዜን ለሕሊናችን*
*መጽናናትና መበረታቻ እንዴት እንደምንጠቀምበት የማወቅ የተሻለ ዕድል ማግኘት ናቸው።*
5 *እንግዲህ ይህንን ሰው ሁሉ ያውቃል። ያለመታደል ሆኖ፣ ሰዎች እንደሚገባ*
*አልተማሩትም፤ ደስ ያላቸውን ማናቸውንም ነገር ካደረጉ በኋላ ወደ ኃጢአት ኑዛዜ መሄድ*
*የማይገባቸው ወይም የማያስፈልጋቸው አድርገው በመቍጠር ነጻነታቸውን ያለ አግባብ ይጠ*
*ቀሙበታል፤ አንድ ሰው ጥቅም የሚሰጠውን ማንኛውንም ነገር በፍጥነት ይረዳና በወንጌሉ*
*ውስጥ ልዝብና ትሑት የሆነውን ነገር ሁሉ ባልተለመደ መረጋጋት ይገነዘባል። ነገር ግን*
*እንዳልኩት እነዚህ አሳማዎች ወንጌሉ ወይም የትኛውም ክፍል ሊኖራቸው አይገባም። ይልቁንስ*

---

[236] ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ ሲታተም ሉተር አርባ አምስት ዓመቱ ነበር፤ በቀደመው ዓመት ውስጥ በተከታታይ ከባድ ሕመሞች ተሠቃይቶ ነበር።

[237] ይህ የኃጢያት ኑዛዜ ክፍል በመጀመሪያ የተጨመረው በ1529ኙ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ የታረመ እትም ውስጥ ነበር። በጄናው (Jena) (ምሥራቅ ጀርመን) የሉተር ሥራዎች እና በጀርመኑ መጽሐፈ ስምምነት (1580) እትም ውስጥና በበርካታ ቀጣይ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እትመቶች ውስጥም ተትቶ ነበር።

*በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሥር መቆየትና ከበፊቱ ይልቅ ለመናዘዝ፣ ለመጸም፣ ወዘተ. መነዳትና
መሠቃየት ይገባቸዋል፡፡ ወንጌሉን ለማመን እንደ እርሱም ለመኖርና አንድ ክርስቲያን
ሊያደርገው የሚገባውን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ከትሩፋቶቹ በየትኛውም
6 ሊደሰት አይገባውም፡፡ በወንጌሉ ትሩፋቶች መደሰት ብትመኝ ነገር ግን ስለ እርሱ ምንም
ካላደረክ እና ምንም ትኩረት ካልሰጠኸው ምን ይሆናል? ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ምንም
ስብከት አናቀርብላቸውም፤ ከነጻነታችን የትኛውንም ክፍል እንዲካፈሉና እንዲደሰቱበት
አንፈቅድላቸውም፤ ነገር ግን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና ቢጤዎቹ እንደ እውነተኛ አምባገነን ወደ
ጭቆና መልሰው እንዲያመጧቸውና እንዲያስገድዷቸው እንተዋቸዋለን፡፡ ወንጌሉን የማይታዘዙ
7 ሥርዓት አልበኞች እስረኛ ጠባቂና ሰቃይ እንጂ ሌላ ነገር አይገባቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በደስታ
ለሚሰሙት ለሌሎቹ ወንጌሉ የሚሰጠውን እንዲህ ያለ የከበረና አጽናኝ መዝገብ ችላ እንዳይሉ
እያበረታታናቸው፣ እያደፋፈርናቸውና እያሳመንናቸው ዘወትር መስበክ ይገባናል፡፡ ስለዚህ
የዋሃንን ለማስተማርና ለማበረታታት ስለ ኃጢአት ኑዛዜ ጥቂት ነገር ማለት እንፈልጋለን፡፡
8 ለመጀመር ያህል እዚህ እየተወያየንበት ካለው የኃጢአት ኑዛዜ በተጨማሪ
የክርስቲያኖች የጋራ የኃጢአት ኑዛዜ ተብለው ከመጠራት የበለጠ መብት ያላቸው ሌሎች
ሁለት ዓይነት የኃጢአት ኑዛዜዎች እንዳሉ ተናግሬአለሁ፡፡ ይቅርታ ለመጠየቅ ለእግዚአብሔር
ብቻ ወይም ለባልንጀራችን ብቻ ኃጢአትን ስለ መናዘዝ ልምምድ እገልጻለሁ፡፡ እነዚህ ሁለት
ዓይነት ኑዛዜዎች «እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» በምንልበት
9 በጌታችን ጸሎት ውስጥ ተካተዋል፡፡ በእርግጥ መላው የጌታችን ጸሎት እንዲህ ዓይነት ኑዛዜ
እንጂ ሌላ ምንም ነገር አይደለም፡፡ ጸሎታችን ሊኖረን የሚገባንን እንደሌለን ወይም ልናደርገው
የሚገባንን እንዳላደረግን ከመናዘዝና ጸጋና ደስተኛ ሕሊና እንዲኖረን የሚደረግ ልመና እንጂ
ሌላ ምንድነው? ይህ ዓይነት ኑዛዜ በሕይወት እስካለን ድረስ ባለማቋረጥ ሊከናወን የሚገባው
አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ይህም የእውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረታዊ ፍሬ ነገር ሲሆን
እርሱም ኃጢአተኞች መሆናችንን አምነን መቀበልና ጸጋን እንድናገኝ መጸለይ ነው፡፡
10 በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቲያኖች ሁሉ ለባንጀራቸው የሚያደርጉት ሁለተኛው ኑዛዜ
በጌታችን ጸሎት ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር ፊት ከመምጣታችን እና ይቅርታን
ከመጠየቃችን በፊት በደላችንን ለእርስ በርሳችን መናዘዝና ይቅር መባባል ይገባናል፡፡ ሁላችንም
አንዳችን የሌላችን በደለኞች ነን፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ሌላን ሰው ሳይፈራ በገሐድ ልንናዘዝ
11 ይገባናል፤ እንችላለንም፡፡ «አንድ ሰው ቅን ከሆነ ሁሉም እንደዚያው ናቸው» የሚለው ምሳሌ
እውነት ስለ ሆነ ማንም ሰው እንደሚገባው ወይም እንደሚገባት በእግዚአብሔር ወይም
በባልንጀራው ዘንድ አያደርግም፡፡ ነገር ግን ከኃጢአታችን አጠቃላይ ድምር በተጨማሪ አንድ
ሰው ሌላውን ሰው ለቁጣ ሊያነሣሣው ስለሚችል ይቅርታ እንዲጠይቅ የሚያደርጉ የተናጠል
12 ኃጢአቶችም አሉ፡፡ በመሆኑም በጌታ ጸሎት ውስጥ ሁለት እጥፍ የኃጢአት ይቅርታ ማስታወቅ
አለን፤ ባልንጀሮቻችንን ይቅር ስንልና ስንታረቃቸው በእግዚአብሔርና በባልንጀራችን ላይ
የሠራናቸው ኃጢአቶች ይቅር ይባሉልናል፡፡
13 ከዚህ በየዕለቱ አስፈላጊ ከሆነው ግልጽ ኑዛዜ በተጨማሪ በአንድ ወንድም ወይም እኅት
ፊት በግል የሚከናወን ምሥጢራዊ ኑዛዜ አለ፡፡ ይህም የሚሆነው ምንም ሰላም ሊኖረን
እስከማንችል ወይም ራሳችንን በበቂ ሁኔታ በእምነት ጠንክረን ማግኘት እስከማንችል ድረስ
14 አንድ የተወሰነ ጉዳይ እያመነመነ በሚከብደን ወይም በሚያጠቃን ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ
በሚሆንብን ጊዜ ምክር፣ መጽናናት እና ብርታት በመፈለግ በማናቸውም ጊዜ እና በምንመኘው
መጠን አዘውትረን ችግሮቻችንን በአንድ ወንድም ወይም በአንዲት እኅት ፊት ልናስቀምጥ
እንችላለን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ኑዛዜ እንደ ሌሎቹ ሁለቱ በትእዛዙ ውስጥ የተካተተ ሳይሆን
በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሁሉ እንዲጠቀሙበት ለሁሉም ሰዎች የተተወ ነው፡፡ በመሆኑም
በመለኮታዊ ትእዛዝ ክርስቶስ ራሱ በክርስቲያን ማኅበረሰብ አፍ ውስጥ የኃጢአት ይቅርታ
እወጀን አስቀምጦ አንዳችን ሌላችንን ከኃጢአት እንድንፈታ አዞናል፡፡[238] ስለዚህ ኃጢአቱ
የሚሰማውና መጽናናትን የሚፈልግ ልብ ቢኖር በሰው አማካይነት እግዚአብሔር ከኃጢአት*

[238] ማቴዎስ 18፡15-19፡፡

ስለሚፈታና ነጻ ስለሚያደርግ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያገኝበትና የሚሰማበት አስተማማኝ
መሸሸጊያ እዚህ አለው።
15 እንግዲያውስ አዘውትሬ እንዳልኩት ኑዛዜ ሁለት ክፍሎች እንዳሉት አስተውሉ።
የመጀመሪያው በኃጢአቴ አልቅሼ ለነፍሴ መጽናናትና መመለስን በምፈልግበት ጊዜ ይህም
የእኛ ሥራና ድርጊት ነው። ሁለተኛው በሌላ ሰው ከናፍርት ላይ በተቀመጠ ቃል አማካይነት
እርሱ ከኃጢአቴ ነጻ ሲያደርገኝ ነው። ይህም እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ነው። ይህ
የኃጢአት ኑዛዜን በጣም አስደናቂና አጽናኝ የሚያደርግ አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ ድንቅና
16 የከበረ ነገር ነው። በቀደሙት ጊዜያት አጽንኦቱን ሁሉ በእኛ ሥራ ላይ ብቻ በማድረጋችን
የሚያስጨንቀን ነገር በበቂ ሁኔታ መናዘዝ ወይም አለመናዘዛችን ነበር። እጅግ አስፈላጊ
የሆነውን ሁለተኛ ክፍል አላስተዋልንም፤ ወይም አልሰበክንም፤ ኑዛዜያችን ለእግዚአብሔር ጉቦ
ልንሰጥ የምንችልበት መልካም ሥራ ይመስል ነበር። ኑዛዜው በፍጹምነትና በሙሉ ዝርዝር
ሳይደረግ ሲቀር የኃጢአት ይቅርታው እወጃ ትክክለኛ እንዳልነበረና ኃጢአቱም ይቅር
17 እንዳልተባለ ይነገረን ነበር። በውጤቱም ሰው ሁሉ በንጽሕና ለመናዘዝ ተስፋ እስኪቆርጥ
(በእርግጥም የማይቻል ነበር) እና ሕሊና ምንም ሰላም ሊሰማውና በኃጢአት ይቅርታው አዋጅ
መተማመን እስከማይችል ድረስ ሰዎች ተነድተው ነበር። እነዚህም ነገሮች የከበረውን ኑዛዜ
ለእኛ የማይጠቅመን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለነፍሳት የተገለጠ ጉዳትና ጥፋት እንዲሁም
አድካሚና መራራ አድረገውብን ነበር።
18 ስለዚህ ሁለቱን ክፍሎች በግልጽ ለያይተን በማስቀመጥ መጠንቀቅ ይኖርብናል።
በራሳችን ሥራ ላይ አነስተኛ ዋጋ ማኖር ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ከፍ ከፍ ማድረግና
ማጉላት ይገባናል። ወደ ኃጢአት ኑዛዜ መሄድ የሚገባን ለእግዚአብሔር ሊቀርብ የሚችል
አስደናቂ ሥራ ለመሥራት እንደምንፈልግ ዓይነት ሆነን ሳይሆን ከእርሱ አንዳች ነገር
ለመቀበልና ለመረከብ መሆን አለበት። ወደ እግዚአብሔር መጥተህ እንዴት ያለህ ቅን ወይም
19 እንዴት ያለህ ክፉ መሆንህን ለመናገር አትደፍርም። ክርስቲያን ከሆንክ በዚህም ሆነ በዚያ
ይህንን በሚገባ አውቀዋለሁ፤ ካልሆንክ እንዲያውም የተሻለ አውቀዋለሁ። ነገር ግን በችግርህ
ምክንያት እያለቀስህና ደስተኛ ልብና ሕሊና ለማግኘት እንድትችል ለመረዳት ፈቃደኛ በመሆን
ልታደርገው ይገባል።
20 ማንም በትእዛዝ ወደ ኃጢአት ኑዛኤ ሊነዳህ አያስፈልገውም። ይልቁንም ይህንን
እንላለን። ክርስቲያን የሆነ ወይም መሆን የሚፈልግ ሁሉ ወደ ኃጢአት ኑዛዜ እንዲሄድና
ይህንን የከበረ መዝገብ እንዲፈልግ ይህንን የተወደደ ምክር ያገኛል። ክርስቲያን ካልሆንህና
21 እንዲህ ዓይነት መጽናናት ካልፈለግህ ግን ለሌላው ኃይል እንተውሃለን። ምንም ስለማያስፈልጉን
በዚህ ሁኔታ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን አምባገነንነት፣ ትእዛዛትና ግዳጅ ሙሉ በሙሉ እንሽራለን።
ቀደም ብዬ እንዳልኩት ይህንን እናስተምራለን፤ በፈቃደኝነት ለኃጢአት ስርየት ሲሉ ወደ ኑዛዜ
የማይሄዱ ሰዎች ይህንን ይርሱት። አዎን በኑዛዜያቸው ንጽሕና በመደገፍ እዚያ የሚሄዱ ሰዎች
22 ደግሞ ከዚያ ይራቁ። ነገር ግን አንድን ሥራ ለመሥራት ሳይሆን እግዚአብሔር ሊሳችሁ
የሚፈልገውን ለመስማት እንድትናዘዙና የሚያስፈልጋችሁን እንድትገልጡ እናደፋፍራችኋለን።
በውዳሴ ሁሉና በምስጋና ሊቀበሉት እንደሚገባ ታላቅና አስደናቂ ሀብት እያጎላችሁትና
እየተንከባከባችሁት ልታተኩሩበት የሚገባችሁ በቃሉ ወይም በኃጢአት ይቅርታ አዋጁ ላይ
ነው እላለሁ።
23 ይህ ሁሉ በግልጽ ተቀምጦልንና ከእርሱም ጋራ ወደ ኑዛዜ ሊያስጠጉንና ሊያሳምኑን
የሚገባቸው ጉድለቶች በግልጽ ተመልክተው ቢሆን ኖሮ ለኑዛዜ የሚያስገድድ ኃይል
አያስፈልግም ነበር። ክርስቲያኖችን የገዛ ሕሊናቸው አነሣሥቶአቸው በአንድ ቦታ ላይ ብዙ
የገንዘብ ወይም የልብሶች ስጦታ እየታደለ እንደሆነ እንደሰሙ ምስኪን ለማኞች ሥጦታውን
ለመውሰድ እንዲራመዱ ያደርጓቸው ነበር። የሚነዳቸውና የሚደበድባቸው ሹም ሳያስፈልጋቸው
24 ሥጦታው እንዳያመልጣቸው የቻሉትን ያህል ወደዚያ በፍጥነት ይሮጡ ነበር። አሁን ምንም
ምክንያት ሳይሰጥና እዚያ ምን ሊፈልጉ ወይም ሊቀበሉ እንደሚገባቸው ሳይጠቀስ ግብዣው
ወደ ትእዛዝ ተለወጠ እንበል። ሰው ሁሉ እንዴት ያለ ምስኪን ድሃ መሆኑን እንዲያይ እንጂ

አንዳች ነገር ለመቀበል ተስፋ ሳያደርጉ ቢሄዱ በምሬት ካልሆነ እንዴት በሌላ ሁኔታ ይሄዳሉ?
ለዚህ ትእዛዝ የበለጠ ጥላቻ ብቻ እንጂ ምንም ደስታ ወይም መጽናናት አይኖራቸውም።
25 በተመሳሳይ መንገድ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሰባኪዎች በቀደሙት ጊዜያት ስለ እነዚህ
አስደናቂ ብዙ ምዕዋዎች እና ሊገለጹ ስለማይቻል ስለዚህ ሀብት ዝም ብለው ነበር። የረከሱና
የጎደፉ ሰዎች እንደነበሩ ሊያሳዩአቸው ብቻ ሕዝቡን በአንድ ላይ በጅምላ ሰብስበውታል።
26 በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታዎች በፈቃደኝነት ወደ ኑዛዜ መሄድ የሚችል ማን ነበር? እኛ
በተቃራኒው ሰዎች ምንኛ በኃጢአት ጉድፍ የተሞሉ እንደሆኑ መመልከት ወይም ስላሉበት
ሁኔታ ማሰላሰል ይገባቸዋል አንልም። ይልቁንም ይህንን ምክር እንሰጣለን፤ ምስኪንና መከረኛ
27 ከሆንክ ሂድና ፈዋሹን መድኃኒት ተጠቀም። መከራቸውና ጉድለታቸው የሚሰማቸው ያለ
ጥርጥር ለኑዛዜ ፍላጎት አድሮባቸው በደስታ ወደዚያ ይሮጣሉ። ነገር ግን ቸል የሚሉና በገዛ
ፈቃዳቸው የማይመጡት በገዛ መንገዳቸው እንዲሄዱ እንተዋቸዋለን፤ ነገር ግን እንደ
ክርስቲያኖች እንደማንቆጥራቸው ማወቅ ይገባቸዋል።
28 በመሆኑም የኃጢአት ኑዛዜ ምን ዓይነት አስደናቂ፣ የከበረና አጽናኝ ነገር እንደሆነ
እናስተምራለን፤ በተለይ ደግሞ ትልቁን ጉድለታችንን ስናጤን እንደዚህ ዓይነት የከበረ በረከት
ሊናቅ እንደማይገባ እናስጠነቅቃለን። ክርስቲያን ከሆንህ የትም ቦታ ላይ የኔ አስገዳጅነት ወይም
የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ትእዛዝ አያስፈልግህም፤ ይልቁኑ ወደ ኑዛዜ ለመሄድ ራስህን ታስገድድና
29 ከእርሱም እንድትካፈል ትለምነኛለህ። ነገር ግን ከናቅኸውና ከኑዛዜ በኩራት ከራቅህ ክርስቲያን
ስላልሆንህ ቅዱስ ምሥጢርንም ልትቀበል አይገባህም ወደሚል ድምዳሜ መምጣት ይገባናል።
ምክንያቱም የትኛውም ክርስቲያን ሊንቀው የማይገባውን ንቀሃልና በዚህም የኃጢአት ይቅርታ
ሊኖርህ እንደማይችል አሳይተሃል። ይህ ደግሞ ወንጌሉንም እንደምትንቅ ማረጋገጫ ምልክት
ነው።
30 በአጭሩ፣ ከግዴታ ጋራ የተያያዘ ምንም ነገር አንፈልግም። ነገር ግን ማንም ሰው
ስብከታችንን እና ማስጠንቀቂያችንን ካልሰማና ትኩረት ካልሰጠው ከወንጌሉ የትኛውም ክፍል
ሊኖረው ከማይገባው ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖረንም።
ክርስቲያን ከሆንክ በግዴታ ሳይሆን በፍላጎትህ የኃጢአት ኑዛዜ ለማድረግ ከመቶ ማይሎች በላይ
31 ሮጠህ ለመምጣትና አገልግሎቱን እንድንሰጥህ ግድ ልትለን ደስተኛ መሆን ይገባሃል። እዚህ
ላይ ግዴታው አቅጣጫ መቀየር ይገባዋል። በትእዛዝ ሥር መምጣት የሚገባን እኛ ነን፤ እናንተ
በነጻነት መቅረብ ይገባችኋል፤ ማንንም አናስገድድም፤ ነገር ግን ለመስበክና ቅዱስ ምሥጢርን
ለማደል ግዴታ እንዳለብን ሁሉ የኃጢአት ኑዛዜ አገልግሎት ለመስጠትም ለመገደድ
እንፈቅዳለን።
32 ስለዚህ ወደ ኃጢአት ኑዛዜ እንድትሄድ ስመክርህ ክርስቲያን እንድትሆን
እያበረታታሁህ እንጂ ምንም እያደረግሁ አይደለም። ወደዚህ ነጥብ ካመጣሁህ ወደ ኃጢአት
ኑዛዜም አምጥቼሃለሁ። ቀና ክርስቲያኖችና ከኃጢአታቸው ነጻ መሆን በእውነት የሚፈልጉ፣
33 ደስተኛ ሕሊና እንዲኖራቸው የሚመኙ ቀደም ብለው በእውነት ይራባሉ፤ ይጠማሉ። በመዝሙር
42፡1፡- «ዋላ ወደ ውሃ ምንጭ እንደሚናፍቅ አምላኬ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች»
እንደሚለው በሙቀትና በጥማት እንደምትቃጠል እንደ ታደነች ዋላ ሕብስቱን ይነጥቃሉ።
ማለትም ዋላ ዐዲስ ምንጭ በመፈለግ በጉጉት እንደምትንቀጠቀጥ እኔም የእግዚአብሔርን ቃል
ወይም የኃጢአት ይቅርታ እወጃን እና ቅዱስ ምሥጢርን ወዘተ. እናፍቃለሁ፤ እንቀጠ
34 ቀጥማለሁ። በዚህ መንገድ እኛ ከምንፈልገው የበለጠ ሰዎች ሊያገኙት ከኋላችን እየሮጡ
እንዲመጡ እና ለእርሱም እንደዚህ ዓይነት መሻትና ፍቅር እንዲቀሰቀስባቸው ለማድረግ ስለ
ኃጢአት ኑዛዜ በተገቢው መልኩ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ታያላችሁ። ጳጳሳውያኑ
ራሳቸውንና እንዲህ ዓይነት መዝገብን ቸላ የሚሉትን እንዲያሰቃዩ እና እንዲያጎሳቁሉ
35 እንተዋቸዋለን። ነገር ግን እኛ ይህን እውቀትና ጸጋ ስላገኘን በውዳሴና በምስጋና እጆቻችንን
ወደ እግዚአብሔር እናንሳ።

# [የስምምነት መሠረታዊ መመሪያ]

## ለስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ በአርታዒያኑ የተዘጋጀ መግቢያ

ሁሉም እንቅስቃሴ መሥራቹ ወይም መሥራቾቹ ለሕዝባዊ ኑሮ የሚሆን የእንቅስቃሴውን ዐዲስ አቅጣጫና ዐሳብ የመሠረቱበትን መሠረታዊ መርሖች ተከታዮቹ ለማየትና ለማቀናጀት የሚሞክሩበት ጊዜ አለው። ይህ በሉተራውያን ተሐድሶ የታየ ነበር። በ1520ዎቹ ዓመታት መገባደጃ ላይ ከሉተር ቀደምት ተማሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ዮሐንስ አግሪኮላ በመጀመሪያ የሉተር የቅርብ ጓደኛና የሥራ ባልደረባ በነበረው በፊሊፕ ሜላንክተን የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ሕግ ጽንሰ ዐሳብ፣ እንዲሁም፣ ከዐሥር ዓመት በኋላ የራሱን የሉተርን የሕግ አስተምህሮ ተቃወመ። ይህም የሉተር አስተምህሮ ተቀባይነት በአተረጓጐም ረገድ የነበረው ክርክር እንዲጀመር አደረገ። በ1530ዎቹና በ1540ዎቹ ዓመታት ሜላንክተንና ቀድሞ በዊተንበርግ የቅርብ ጓደኛው የነበረው ኒኮላስ ቮን አምስዶርፍ መልካም ሥራ በድነት ላይ ያለውን ሚና፣ የሰው ፈቃድ እስራት ወይም ነጻነት ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የሉተራውያኑ ተሐድሶ ከካቶሊክ የጵጵስና አመራር ጋር ያለውን ግንኙነት፣ እርሱም ከመንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነትና እንዲሁም በጌታ እራት የክርስቶስ ሥጋና ደም እውነተኛ መገኘትን በሚመለከት አልተስማሙም ነበር። በሁለቱ መካከል የነበረው ፉክክር፣ በግዛቱ ውስጥ የነበረው የፖለቲካ እድገት መድረክ ያመቻቸላቸውና ከሉተር ሞት በኋላ የሉተርንና የሜላንክተንን ተከታዮች ያለያዩ ተከታታይ ክርክሮችን፣ አስቀድሞ አመላከተ።

በየካቲት 18 ቀን 1546 ከሉተር ሞት በኋላ በነበሩት ወራት ንጉሠ ነገሥት ቻርለስ 5ኛ በመጨረሻው በእምቢተኞቹ ሉተራውያን ዜጎቹ ላይ ፈቃዱን የመጫን ሙከራ ለማድረግ፣ ኃይሎችን ለማሰባሰብ፣ እንዲሁም ሉተርንና ተከታዮቹን ሕገ ወጥ ያደረገውን በ1521 የወጣውን የወርምስ ድንጋጌ በሥራ ላይ ለማዋል ችሎ ነበር። የ1545-47ቱ የስማልካልድ ጦርነት ወታደራዊ ስኬት በኦግስበርግ በተካሄደው ንጉሠ ነገሥታዊ ጉባኤ፣ በግዛቱ ላሉት ለፕሮቴስታንት መሳፍንታዊ ግዛቶችና ከተሞች፣ ዐዲስ ሃይማኖታዊ መመሪያ እንዲያወጣ ንጉሠ ነገሥቱን አስቻለው። «የኦግስበርግ ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ» የሉተራውያንን ልዩ ትምህርት የሚጨቁን ሲሆን ወደ ሮሙ ሊቀ ጳጳስ እንዲመለሱ ደግሞም ግብረገባዊና ተቋማዊ መልክ ከነበረው ከኢራስመስ የተሐድሶ አመለካከት ጋር የሚጣጣመውን የመካከለኛውን ዘመን አስተምህሮና ልማድ መልሰው እንዲቀበሉ ፕሮቴስታንቶችን የሚጠይቅ ነበር። በዚያው ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ የሳክሶኒን የምርጫ ግዛት፣ የዊተንበርግን ዩኒቨርስቲና የጆን ፍሬዴሪክን አብዛኛውን ግዛት ለ(ምሥራቃዊ) ሳክሶኒ ሉተራዊ መስፍን ለሞሪዝ በሽልማት ስም ሰጥቶት ነበር፤ ምክንያቱም፣ ከሞሪዝ አማት ከሄሲው ፊሊፕና ከእርሱ ዘመድ ከዮሐንስ ፍሬዴሪክ ጋር በነበረው ጦርነት ሞሪዝ ስለ ተባበረው ነበር። ቻርለስ፣ የቀድሞ ቃሉን በማፍረስ የሉተራዊ እምነቱን መተው እንደሌለበት ለሞሪዝ የቃል ተስፋ በመስጠቱና ሳክሶኒም ደግሞ ለኦግስበርጉ ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ መገዛት እንዳለበት አጽንቶ በማሳሰቡ፣ ሞሪዝ የዊተንበርግና የላይፕዚግ የሥነ መለኮት ሊቃውንቱን (በተለይም ፊሊፕ ሜላንክተንን) በአንድ በኩል ከግዛቱ የሃይማኖት መመሪያ ጋር የሚስማማ መልክ ያለው እየመሰለ፣ በሌላ በኩል የሉተርን ትምህርት የሚያስጠ ብቅ የድርድር ስምምነት በማዘጋጀት ዓለማዊ የሆኑትን አማካሪዎቹን እንዲረዱ ሾማቸው። የሳክሶኒን ሃይማኖታዊ ሕይወት በተመለከተ የወጣው ይህ ዐዲስ ዕቅድ በገሃድ ተቀባይነትን ያገኘ ሳይሆን በከፊልና በተለይ ብቻ የተገለጸ ነበር። ይሁን እንጂ፣ «የላይፕዚግ ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ» በሚል ስያሜ፣ ይህ ዐዲስ ዕቅድ፣ እነርሱና እምነታቸው በመምህራቸውና በጓደኞቹ የተካደ በመሰላቸው፣ በብዙዎቹ የሉተርና የሜላንክተን ተማሪዎች ዘንድ የተቃውሞ ማዕበል አስነሣ። ሜላንክተንና በዊተንበርግ ያሉ ጓደኞቹ በቅዱሳት መጻሕፍት ያልታዘዙ ወይም ያልተከለከሉ ነገሮች (አዲያፎራ) በተሰኘው መርሖ መሠረት የላይፕዚጉን ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ ድርድር ደግፈው ነበር። ስለሆነም፣ ለመንግሥት ሥልጣን ቤተ ክርስቲያን መገዛት አለባት፣ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ጒዳይ ለመወሰን ነጻነት አላት፣ እንዲሁም ድርድርና

ስምምነት በቤተ ክርስቲያን ላይ በኃይል በሚጫንባት ጊዜ እምነቷን በድፍረትና በግልጽ ማስታወቅ አስፈላጊ ስለ መሆኑ የተነሣው ይህ ውዝግብ፣ «በቅዱሳት መጻሕፍት ያልታዘዙ ወይም ያልተከለከሉ ነገሮች ውዝግብ» የሚል ስያሜ ተሰጠው:: ይህ ውዝግብ በ1548 የሳክሶኑ መመሪያ ከተቀረጸ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፊንድቶ ከዐሥር ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ቀጠለ (በስምምነት መሠረታዊ መመሪያ 10 ተገልጾአል)::

የላይፐዚግ ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ ከተሰኘው ክርክር ጋር ተያይዞ በሉተራውያን ተሐድሶ በአንዳንድ የድነት አስተምህሮ ገጽታዎች ትርጉም ላይ ተከታታይ ከሆኑት አለመግባባቶች መካከል የመጀመሪያው ተከሰተ:: የዊተንበርጉ ፕሮፌሰር ጆርጅ ሜጀር «መልካም ሥራ ለድነት አስፈላጊ ነው» ተብሎ በሰነዱ የቀረበውን ዐሳብ ስለ ደገፈ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ የነቀፌታ ማዕበልን ቀሰቀሰ፣ [እነዚህ ተቃዋሚዎች በኋላ በምሁራን “Gnesio-Lutherans” «ግኔሲዮ ሉተራንስ» (እውነተኞቹ ሉተራውያን) የተባሉት ናቸው፤ ለመምህራቸው ቀረብ ብለው የተገኙት ሜጀርና ሌሎች የሚላንክተን ተማሪዎች «ፊልጶሳውያን» የሚል ስያሜ ተሰጣቸው]:: እነዚህ ተቃዋሚዎች ይህ ዐሳብ በመካከለኛው ዘመን ወደ ነበረው ለድነት በሥራ ወደ መመካት መመለስ መሆኑን አመኑ፣ (የስምምነት መሠረታዊ መመሪያ 4):: መልካም ሥራ በድነትና በክርስትና ሕይወት ያለውን ሚና በተመለከተ ከተነሣው ክርክር በእነዚህ ሁለት ወገኖችና እንዲያውም በእውነተኞቹ ሉተራውያን መካከል እንኳን በሕጉ ጥቅምና በትክክለኛው የ«ወንጌል» ቃል ትርጉም ላይ ውዝግብ ተነሣ (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ 5፣6):: በዚያኑ ጊዜ ቀደም ባሉት በ1550ዎቹ እነዚህ ሁለቱም ወገኖች የሉተርን የመጽደቅ አስተምህሮ አተረጓጐም በተመለከተ በኑረምበርግ ከተማ የሉተር የረጅም ዘመን ደጋፊ በነበረውና በኦግስቡርግ ጊዜአዊ ማስማሚያ ሰነድ ምክንያት ከተማውን እንዲለቅ ተገድዶ በኩኒግስበርግ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር በሆነው በአንድሪው ኦሲያንደር የተሰነዘረውን አለፍ ያለ ዐስተሳሰብ ተቃወሙ:: ኦሲያንደር በፕላቶ ፍልስፍና ተጽእኖ ሥር በነበረው የብሉይ ኪዳን አተረጓጐም ትምህርት ቤት የሠለጠነ በመሆኑ፣ በእምነት አማካይነት በጸጋ መጽደቅ የሚገኘው የክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይ በአማኞች ውስጥ ለማደር በመምጣቱ ነው ብሎ አመነ:: ሌሎች የሉተር ተከታዮች በሙሉ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ያጸደቀው የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ትሩፋት ለእነርሱ በሚያስተላልፈውና በክርስቶስ መታመንን በሚያስከትለው በይቅርታው ቃል አማካይነት መሆኑን ያምኑ ነበር (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ 3)::

የሰውና የመለኮት ግንኙነት በተመለከተ ተያያዥነት ያለው ውዝግብ ከድነት ጋር በተገናኘ መልኩ በእግዚአብሔር ርዳታ በመልካምና በክፉ መካከል ምርጫ በማድረግ ለድነቱ ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር መተባበር ይችላል የሚለውን አስተምህሮ በተመለከተ፣ the synergistic controversy ዘ ሲነርጂስቲክ ኮንትሮቨርሲ (ተያያዥነት ያለው ውዝግብ) በመለወጥ ውስጥ የሰው ፈቃድ በሚኖረው ሚና ላይ ያተኮረ ነበር (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ 2):: ከዚህ ክርክር የውርስ ኃጢአትን ትርጉም የተመለከተ ሌላ ውዝግብ ተነሣ:: የእውነተኞቹ ሉተራውያን መሪ፣ በሥነ አተረጓጐም (ለቅዱስ መጽሐፍ መክፈቻ) እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ (የሜግዴቡርግ ሴንቸሪ ድርጅቶችን) አስተዋጽኦ ያበረከተውና እነዚያን ሥርዓቶች ለአያሌ ትውልዶች መልክ ያስያዘው ማትያስ ፍላሲየስ ኢሊሪከስ የውርስ ኃጢአት እምነት የጐደለውንና የወደቀውን ሰብዓዊ ፍጡር መደበኛ ባሕርይ፣ የሰይጣንን መልክ የሚያሳይ ነው፤ የእግዚአብሔርን መልክ ፈጽሞ አያሳይም ብሎ አስተማረ (የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ 1)::

በ1550ዎቹና በ1560ዎቹ ዓመታት የተከሰቱት ሁለተኛ ተከታታይ ክርክሮች ሉተራውያኑን ከዮሐንስ ካልቪንና ከተከታዮቹ ጋር አፋጠጡአቸው:: በሚላንክተን የቅዱሳት ምሥጢራት ሥነ መለኮትና የትምህርተ ክርስቶስ ዐሳብ ላይ ያተኮሩ ሁለት የትርጉም ዐስተሳሰብ ቡድኖች በጌታ እራት በክርስቶስ ሥጋና ደም የመገኘት ሁኔታ፣ እንዲሁም በእርሱ አካል በሚኖሩት በሁለቱ የክርስቶስ ባሕርያት መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ባሉት ተዛማጅ ጥያቄዎች ላይ ይከራከሩ ነበር (1564-74 የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ 7 እና 8)::

በ1550ዎቹ ቀደምት ዓመታት እነዚሁ ውዝግቦች እንደ ተነሡ ወዲያውኑ በሉተራውያኑ ምድር ያሉት የሥነ መለኮት ሊቃውንትና መንግሥታት ልዩነቶችን ለማስታረቅና አከራካሪ

በሆኑት ጉዳዮች ላይ ወደ ሥነ መለኮታዊ ስምምነት ለመድረስ ፈለጉ። በ1554 (በኑረምበርግ) እንደገናም በ1558 (በፍራንክፈርት የመዝናኛ ስፍራ በአብዛኛው በሜላንክተን በተረቀቀው) በሮማውያን ግዛት ያሉት ወንጌላውያን መሳፍንት ቀላል በሆኑ የመሠረተ እምነት መግለጫዎች አማካይነት ከስምምነት ላይ ለመድረስ ፈለጉ። የእውነተኞቹ ሉተራውያን ተቃውሞ እነዚህን ቀለል ባሉ መግለጫዎች ክርክሮችን የመፍታት ሙከራዎች አከሸፋቸው፤ በዚህ ፈንታ የእውነተኞች ሉተራውያንን አቋም የሚደግፉ መንግሥታት የራሳቸውን ዝርዝር የእምነት መግለጫዎች ወይም የስሕተት ማስተባበያዎች አወጡ።

የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ጽሑፍ ራሱ በ1561 በኑረምበርግ በነበሩት የዊተንበርግ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ተከታዮች መካከል መከፋፈልን የሚፈጥር ጉዳይ ሆነ። ሉተራውያኑ መሳፍንት በወንጌላውያኑ ግዛቶች ወደ ካልቪን የጌታ እራት አተረጓጐም አቅጣጫ በማዘንበል እውነተኞቹ ሉተራውያን ሊቀበሉት ከሚችሉት በላይ ሰፋ ያለ የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ትርጉም ለማራመድ በፈለገው፣ ከእነርሱ አንዱ በሆነው በግዛቱ የዙፋን እንደራሴ በነበረው በፍሬዴሪክ ሳልሳዊ ተግዳሮት ገጠማቸው። ደግሞም በ1557 የዚህ ቡድን የሥነ መለኮት ሊቃውንት ከሜላንክተንና ከደጋፊዎቹ ጋር ለመታረቅ ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀረ። ይህ ጥረት በ1568 እና በ1569 የፊልፕ ሜላንክተን ተከታዮች ፊልጶሳውያን እና እውነተኞቹ ሉተራውያን የሥነ መለኮት ሊቃውንት ልዩነታቸውን ለማስታረቅ በአልተንቡርግ ለውይይት በተሰበሰቡ ጊዜ እንደገና ተጀመረ፤ ውይይቱ ሁለቱን ወገኖች ይበልጥ እንዲለያዩ በማድረግ ተደመደመ።

በ1569 ሌላ የስምምነት ዘመቻ ተጀመረ። በሉተራውያኑ መካከል ስምምነትን ለመመሥረት እንደዚህ ያሉትን ዐንቀጾች ይደግፍ የነበረው የውርተምበርጉ ልዑል ክሪስቶፈር ለመስፍኑ ዘመድ በነበረው በብራውንሽዊግ ወልፌንቡቴል ልዑል በጁሊየስ ግዛቶች ተሐድሶን በማካሄድ ማርቲን ቼሚኒዝንና ኒኰላስ ሴልኔከርን እንዲረዳ ከፍተኛ የሥነ መለኮት አማካሪውን ጃኰብ አንድሪያን (ከፊልፕ ሜላንክተን ተከታዮች የሳክሶኒ የምርጫ ግዛት በመዋስ) ላከው። ክርስቶፈር በጁሊየስ ቤተ መንግሥት በእንግድነት በነበረበት ጊዜ በሉተራውያን ከተሞችና ክፍላተ አገር የሥነ መለኮት ሊቃውንትና አስተዳዳሪዎች መካከል ስምምነትን ለማስገኘት ከሰሜን ጀርመን የወንጌላውያን መንግሥታት ጋር ድርድር እንዲያካሂድ አንድሪያን ሾመው። አንድሪያ «አምስት አንቀጾች» በተሰኘው የራሱ አጭርና ቀላል ሰነድ አማካይነት ይህንን ሥራ ለመፈጸም ያደረገው ሙከራ አልተሳካም። ይሁን እንጂ፣ እርሱ ይህንን ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ በከፊል በቼሚኒዝ ሥነ መለኮታዊ ተጽእኖ አማካይነት ከፊልጶሳውያን ቡድን ተለይቶ ወደ እውነተኞቹ ሉተራውያን ተሳበ። እርሱም በ1573 «የኦግስቡርግን የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ሊቃውንት በለያዩአቸው ክርክሮች ላይ የቀረቡ ስድስት ስብከቶች» የተሰኘ ጽሑፍ አውጥቶ በአብዛኛው የእውነተኞቹ ሉተራውያንን አቋም በሚደግፉት በእነዚህ ስብከቶች በቀረቡት ዐሳቦች መሠረት ሉተራውያኑ እንዲታረቁ ጥሪ አቀረበ። ቼሚኒዝ፣ የሜክለንቡርጉ ዴቪድ ኪትሪዮስና ሌሎችም የሥነ መለኮት ሊቃውንት ምላሽ እንዲሰጡ ተጠየቁ። እነርሱም አንድሪያ አባል ከሆነበት ከቱቢንገን የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የበለጠ መደበኛነት ያለው ሥነ መለኮታዊ መግለጫ ጠየቁ። በዚህ ጥያቄ መሠረት አንድሪያ ራሱ በ1574 «የሸዋቢያን ስምምነት» የሚል ጽሑፍ አዘጋጅቶ የስምምነቱን መሠረታዊ መመሪያ የሰሜን ጀርመን የሥነ መለኮት ሊቃውንት በጠየቁት መልክ ቀረጸው። ቼሚንዝና ቺትሪዮስ የእርሱን ዐሳብ በ1575 ወደ ወጣው «የሳክሶን ሸዋቢያን ስምምነት» አሻሻሉት። በዚያኑ ጊዜ የውርቴምበርግ ግዛት (በክርስቶፈር ልጅ በሉድዊግ የሚመራው) እና የባዴንና የሄኔበርግ ግዛቶች በጥር 1576 በማውልብሮን የገዳም ደብር የተሰበሰበ የሥነ መለኮት ኮሚስዮን አቋቁመው «የማውልብሮን መመሪያ» የተሰኘ ሌላ የስምምነት ጽሑፍ አወጡ።

በዚህ ጊዜ የሳክሶኑ መራጭ በአገሩ ያሉ ቀደምት ፊልጶሳውያን የሥነ መለኮት ሊቃውንት ምንም እንኳ ጉዳዩን በምስጢር ለመያዝ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም እነርሱ ወደ መንፈሳዊነት አቅጣጫ ያዘነበለውን የሜላንክተንን ቅዱስ ምስጢራዊ ሥነ መለኮት ያስፋፉ መሆናቸውን ደረሰበት። የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ራሱ ይህንን ቡድን ሲጠቅስ «ሳክራሜንታሪያንስ» (በቅዱስ ቁርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት

የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች) በሚል ቃል ይጠቀማል። እነርሱም በዘመኑ በነበረው ክርክር መሠረት በትውፊታዊ አነጋገር «ክሪፕቶ ካልቪኒስትስ» (ስውር ካልቪናውያን) ተብለው ተጠርተዋል፤ በአሁኑ ጊዜ ምሁራን ደግሞ አልፎ አልፎ «ክሪፕቶ ፊሊፒስትስ» (ስውር ፊልጶሳውያን) ተብለው ይጠራሉ፤ ምክንያቱም ወደ መንፈሳዊነት ያደላውን የጌታን እራት አተረጓጐም «በስውር» እየያዙ ሳለ የሜላንክተንን ሥነ መለኮት በታማኝነት ለማጐልበት ይሞክሩ ስለ ነበረ ነው። በ1574 እነዚህ የሥነ መለኮት ሊቃውንትና ተራ ደጋፊዎቻቸው በነሐሴ ወር ከአመራር ቦታቸው ተወገዱ፤ በግዛቱ የሉተራውያንን የጌታ እራት መሠረተ እምነት መልሶ በማምጣት ጉዳይ አንድሪያ ከታማኙ ከሴልኔከርና በገዛ ራሱ ግዛት ውስጥ ካሉት ከሌሎች ጋር እንዲተባበር ጋበዘው። እርሱም በዚህ ሂደት በሉተራውያን አገረ ስብከቶችና አውራጃዎች አጠቃላይ ስምምነት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በማስተባበር ረገድ ከልዑል ጁሊየስና ከሌሎች ሉተራውያን መሳፍንት ጋር ለመተባበር ወሰነ።

አራት የሥነ መለኮት ሊቃውንትን ያቀፈ ኮሚቴ ተቋቋመ፤ እነርሱም አንድሪያ፣ ቼሚኒዝ፣ ቻትሪዮስና ሴልኔከር ነበሩ፤ በተጨማሪም ከብራንደንቡርግ የምርጫ ግዛት አንድሪው ሙስኩሉስና ክርስቶፈር ኰርነር የተባሉ ሁለት ተወካዮች ነበሩ። ይህ ኮሚቴ በሳክሶን የምርጫ ግዛት አገረ ስብከት አባሎች በመታገዝ የሽዋቢያን ሳክሶን ስምምነትንና የማውልብሮን መመሪያን በመውሰድ፣ ከእነርሱ የ1576ቱን «ቶርጋው ቡክ» (የቶርጋው መጽሐፍ) የተሰኘውን ቀረጸ። ይህ ሰነድ አስተያየት እንዲሰጥበት በመላው ጀርመን የወንጌላውያን አገረ ስብከቶች ከተሰራጨ በኋላ ሰነዱ በእነዚሁ የሥነ መለኮት ሰዎች የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ሙሉ መግለጫ የሆነው የ1577ቱ «በርገን ቡክ» (የበርገን መጽሐፍ) በድጋሚ ተሠራ። ስለ ክርክሮቹ የሰፈረው ጽሑፍ ለአንዳንዶቹ መሳፍንት በጣም ረጅም ስለ ሆነባቸው፣ አንድሪያ አጠር አድርጎ እንዲጽፈው ኃላፊነት ተሰጠውና የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ «ማጠቃለያ» ሆነ። ማጠቃለያውና ሙሉው መግለጫ በጀርመን ወንጌላውያን ግዛቶች አገረ ስብከቶች ዘንድ ቀረቡ። አንድሪያና ሌሎችም ከአብያተ ክርስቲያናታቸው ድጋፍን ለማግኘት ከአንዳንድ አገረ ስብከቶች ጋር ውይይቶችን በማካሄድ በ1578 እና በ1579 ያለ ድካም ከሠሩ በኋላ የተወሰነ ስኬትን አገኙ። መመሪያው በሁለት ሦስተኛ የጀርመን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ከጸደቀ በኋላ የመጽሐፈ ስምምነት ማጠቃለያ ሰነድ ሆኖ ተካተተ። መጽሐፈ ስምምነት ለይፋዊ ትምህርትና ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንደ እምነት መግለጫ መመሪያ አድርገው በተቀበሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አገልግሎትን ሰጥቶአል፣ እንዲሁም በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ተልእኮ አማካይነት ወደ ሌሎቹ አኅጉራት ተሠራጭቶአል።

ይህ ትርጒም የጀርመኑ ጽሑፍ የተጠቀመባቸው በርከት ያሉ የላቲን ሐረጎችን አካትቶአል (ረጃጅም የላቲን ጥቅሶች በግርጌ ማስታወሻዎቹ ይገኛሉ)። በዚያን ጊዜ ክህሎታዊ የሆኑ የሥነ መለኮት ቃላት በጀርመን ቋንቋ የተስፋፉ ስላልነበረ የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ጸሐፊዎች እንደዚህ ያሉ ክህሎታዊ ቃላትን የሚመለከቱ ነጥቦች በላቲኑ ቋንቋ አጋዥነት መቀመጥ እንዳለባቸው አመኑ። አንባቢዎች ሙሉ መግለጫው እንዴት እያደገ እንደ መጣ የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ ይህ ትርጒም በተጨማሪ በጆርጅ ፍሪሽል የሰነዶች ምንጭ ንባብ ላይ የተመሠረተ የሙሉ መግለጫውን ትንታኔ ያቀርባል፤ ይህም ምንባብ የተወሰደው *ፎርሙላ ኦቭ ኮንክርድ፣ ኢትስ ኦሪጅን ኤንድ ኰንቴንትስ* (ፊላደልፊያ ሉተራን ፐብሊኬሽን ሶሳይቲ 1916) *The Formula of Concord, Its Origin and Contents* (Philadelphia: Lutheran Publication Society, 1916) ከተሰኘው ጽሑፍ ነው። በሙሉ መግለጫው አንቀጾች መጀመሪያ ላይ ያሉት የሚከተሉት ስያሜዎች እነዚህን ምንጮች የሚያመለክቱ ናቸው።

ሀ. «የሽዋቢያ ስምምነት» በጃኰብ አንድሪያ፣ 1573
ለ. የ1573፣ የዴቪድ ቺትሪዮስ አስተዋጽኦ፣ ለሳክሶን - የሽዋቢያን ስምምነት
ሐ. የ1573፣ የማርቲን ቼምኒዝ አስተዋጽኦ፣ ለሳክሶን - የሽዋቢያን ስምምነት፣
መ. የማውልብሮን ሰነድ
ሠ. «የቶርጋው መጽሐፍ»፣ 1576
ረ. «የበርገን መጽሐፍ»፣ 1577
ሰ. በቶርጋው ወይም በበርገን የተዘጋጁት የቀድሞው ጽሑፍ ማሻሻያዎች

*የኦግስቡርግን የእምነት መግለጫ በሚደግፉት አንዳንድ የሥነ መለኮት ሊቃውንት መካከል ውዝግብ የተነሣባቸው አንዳንድ አንቀጾች ችግር በእግዚአብሔር ቃልና በእኛ የክርስትና ትምህርት የማጠቃለያ ይዘት መሪነት መሠረት የተፈታበትና የተቋጨበት ጥልቀት ያለው ግልጽ፣ ትክክለኛ እና በቃል የሚደገም የመጨረሻው ጽሑፍና መግለጫ፡፡*

## [አጠር ያለው ማጠቃለያ]

በኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ሊቃውንት መካከል ውዝግብ የተነሣባቸው አንቀጾች በእግዚአብሔር ቃል መሪነትና በክርስትና ባሕርይ ከዚህ በሚከተለው በቃል የሚደገም ጽሑፍ የተገለጸበትና የታረቁበት አጭር ማጠቃለያ፡፡

*ማንኛውም ትምህርት የሚመዘንበትና የተከሰቱትም ስሕተቶች በክርስትና ባሕርይ የሚገለጹበትና የሚወሰኑበት የስምምነት ማጠቃለያ፤ ሕግና መመሪያ ደንብን በተመለከተ፤*[1]

1 1. «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው» (መዝ 119፡105) ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ፣ «... ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላ 1፡8) እንዳለው፣ እኛ ትምህርቶች ሁሉ እንዲሁም አስተማሪዎች የሚገመገሙበትና የሚመዘኑበት ብቸኛ ሕግና መመሪያ ደንብ የብሉይና የዐዲስ ኪዳን፣ የነቢያትና የሐዋርያት ጽሑፎች ብቻ ናቸው ብለን እናምናለን፣ እናስተምራለን፣ እናስታውቃለንም፡፡

2 ሌሎች የጥንትም ሆኑ ወይም የዘመኑ መምህራን ጽሑፎች ምንም ዓይነት ስም ቢኖራቸው ከቅዱስ መጽሐፍ እኩል ተደርገው አይቈጠሩም፤ ዳሩ ግን ሁሉም በአንድነት ለእርሱ ይገዛሉ፤ እንዲሁም ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የነቢያትና የሐዋርያት ትምህርት በምን ሁኔታና የት እንደ ተጠበቀ ምስክር ከመሆን በስተቀር በማንኛውም ሌላ መንገድ ተቀባይነት ሊኖራቸው ወይም ከዚህ የበለጠ ሥልጣን ሊሰጣቸው አይችልም፡፡

3 2. ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ወዲያውኑ፣ እንዲያውም እነርሱ ገና በሕይወት እያሉ፣ የሐሰት መምህራንና መናፍቃን ቤተ ክርስቲያንን ወረሩአት፡፡ የጥንት ቤተ ክርስቲያን እነርሱን በመቃወም የሐዋርያት፣ የኒቅያ እና የአትናቴዮስ የእምነት መግለጫ የተሰኙ አንድ ዓይነትና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ የእምነት መግለጫዎችን፣ ቀጥተኛና እውነተኛ በሆነችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አዘጋጀች፡፡ እኛም ለእነዚህ ታማኝ በመሆን ከእነርሱ ተቃራኒ ሆነው በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገቡትን ማንኛቸውንም ኑፋቄዎችና ትምህርቶች እንቃወማለን፡፡

4 3. በዘመናችን በእምነት ጉዳዮች የተከሰተውን መለያየት በሚመለከት፣ በተለይም ከጵጵስናውና ከእርሱ የውሸት አምልኮ፣ የጣዖት አምልኮና አጕል እምነት ጋር፣ እንዲሁም ከሌሎች የእምነት ክፍሎች ጋር ባለን ልዩነት በ1530 በታላቁ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ጉባኤ ወቅት ለንጉሠ ነገሥት ቻርለስ 5ኛ የቀረበውን የመጀመሪያውን ያልተለወጠውን የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ከመከላከያው ጋር፣ እንዲሁም በ1537 በስማልካልድ ቀርበው በወቅቱ በነበሩት ታዋቂ የሥነ መለኮት ሊቃውንት የተፈረመባቸውን አንቀጾች ከክርስትና እምነታችን እና መግለጫችን ጋር አንድ ዓይነት ዐሳብና ማብራሪያ እንዳለው አድርገን እንቀበላቸዋለን፡፡

5 ደግሞም እነዚህ ጉዳዮች ያልቀሰሱትን ምእመናን እና የእነርሱንም የነፍስ ድነት የሚመለከቱ ስለሆኑ የዶ/ር ሉተርን ትንሹንና ትልቁን የክርስትና ትምህርቶች፣ ሁለቱም የክርስትና ትምህርቶች በሉተር የታተሙ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙ እንደ መሆናቸው መጠን፣ እንዲሁም በቅዱሳት መጻሕፍት በዝርዝር የተገለጹት ነገሮች በመሉ የተጠቃለሉባቸው በመሆኑና

[1] አጭር ማጠቃለያውን የሕጉንና የመመሪያውን ደንብ የስምምነት ጸሐፊዎች አሠራር የኋላ ታሪክ በተመለከተ ከታች SD 26 ቍጥር 7 ተመልከት፡፡ ..

እነርሱንም ማወቅ ለአንድ ክርስቲያን አስፈላጊ ስለ ሆነ ላልቀሰሱት ምእመናን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናሉ ብለን ለእነርሱ ያለንን ታማኝነት እንገልጻለን።

6 ሁሉም ትምህርቶች እላይ እንደ ተገለጸው ከእነዚህ መመሪያዎች ጋር መስማማት አለባቸው። አንድ ዓይነት ከሆኑ ከእኛ የእምነት ማብራሪያዎች ጋር ተቃራኒ የሆነ ማንኛውም ነገር መወገድና መወገዝ ይኖርበታል።

7 በዚህ መንገድ የብሉይና የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የማንኛቸውም ሌሎች ጽሑፎች ልዩነት ይጠበቃል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ብቻ፣ ሁሉም ነገር ያረፈበት ዋናው ምሰሶ እንደ መሆኑ መጠን፣ ማንኛውም ትምህርት መልካምም ሆነ ክፉ፣ ትክክልም ሆነ ስሕተት፣ የሚታወቅበትና የሚመዘንበት ብቸኛው ዳኛ ሕግና መመሪያ ደንብ ሆኖ ይኖራል።

8 ይሁን እንጂ፣ ሌሎቹ ምልክቶች፣ እንዲሁም እላይ የተዘረዘሩት ሌሎች ጽሑፎች እንደ እግዚአብሔር ቃል ዳኞች አይደሉም፤ ዳሩ ግን፣ በቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜያት አከራካሪ የሆኑትን የእምነት አንቀጾችና እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ተቃራኒ የሆኑ ትምህርቶች የሚወገዱበትንና የሚወገዙበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ምስክሮችና የእምነት ማብራሪያዎች ናቸው።

## I. (1)
## ስለ ውርስ ኃጢአት

### *የውዝግቡ ሁኔታ*[2]
### በዚህ ክርክር ውስጥ ያለው ዋናው ጥያቄ[3]

1 የውርስ ኃጢአት በእውነት ያለ አንዳች ልዩነት የሰብዓዊው ፍጥረት የተበላሸ ባሕርይ፣ መሠረታዊ ነገር፣ እንዲሁም መሠረታዊ የሰው ተፈጥሮ ነው ወይስ የመሠረታዊ ባሕርዩ ከፍተኛውና ከሁሉ የተሻለው ክፍል ማለትም አመክንዮታዊ ነፍስ ራሱ በከፍተኛ የእድገት ደረጃውና ኃይሉ ነው? ወይስ ደግሞ ከውድቀት በኋላ እንኳ በሰብዓዊ መሠረታዊ ተፈጥሮ፣ በመሠረታዊ ባሕርይ፣ በሥጋና ነፍስ እና በውርስ ኃጢአት መካከል ልዩነት አለ? በዚህስ አያያዝ ሰብዓዊው ተፈጥሮ አንድ ነገር ሆኖ በተበላሸው ተፈጥሮ ውስጥ የተተከለውና ይህንን ተፈጥሮ እንዲበላሽ የሚያደርገው የውርስ ኃጢአት ሌላ ነገር ነው?

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

እላይ በቀረበው መሪ መሠረተ ዐሳብና አጠቃላይ መግለጫ ላይ የተመሠረተው ንጹሕ ትምህርት፣ እምነትና መግለጫ

2 1. በሰብዓዊው ባሕርይና በውርስ ኃጢአት መካከል ያለው ልዩነት እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ንጹሕ፣ ቅዱስና ያለ ኃጢአት አድርጎ በፈጠረበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የሚገለጸው ከውድቀት በኋላም ባለን ባሕርያችን መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም። ከውድቀት በኋላም እንኳ ይህ ባሕርይ የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው፤ ሆኖም ይኖራል። ይህ ልዩነት በእግዚአብሔር ሥራና በዲያብሎስ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ከፍ ያለ ነው።

3 2. ደግሞም በተበላሸው ሰብዓዊ ባሕርያችንና በውርስ ኃጢአት መካከል ልዩነት እንደሌለ አድርጎ የሚያቀርበውን አስተምህሮ ሥነ ፍጥረትን፣ መቤዠትን፣ መቀደስንና የሥጋችንን ትንሣኤ በሚመለከት ከክርስትና እምነታችን አንቀጾች ጋር ተቃራኒ የሆነና አብሮ

---

[2] «የውዝግቡ ሁኔታ» ለሚለው አነጋገር የላቲኑ አጠራር።
[3] በዚህ ክርክር ስለ ተሳተፉት ወገኖች ከታች SD I. 531-35 ቁጥር 21-22 ተመልከት።

ሊኖር የማይችል ስለ ሆነ፣ ይህንን ልዩነት በጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለብን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።

4 ምክንያቱም እግዚአብሔር ከውድቀት በፊት የአዳምንና የሔዋንን ሥጋና ነፍስ የፈጠረ ብቻ ሳይሆን፣ ምንም እንኳ የተበላሹ ቢሆኑ ከውድቀት በኋላም የእኛንም ሥጋና ነፍስ ፈጥሯል፤ ደግሞም «እጅህ ለወሰችኝ ሠራችኝም»[4] (ኢዮብ 10፡8) ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር አሁንም እንደ ራሱ ሥራ አድርጎ ይቈጥራቸዋል።

5 ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጅ ምንም እንኳ ያለ ኃጢአት ቢሆን በአካላዊ አንድነቱ ይህንን ሰብዓዊ ባሕርይ ለበሰ፣ እርሱም የለበሰው ሌላ ዓይነት ሥጋ ሳይሆን የእኛን ሥጋ ነው። በዚህ መንገድ እርሱ የእኛ እውነተኛ ወንድም ሆነ፣ «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ … በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» ዕብራውያን 2[፡14]፣ እንዲሁም፣ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም፤ ስለዚህ … በነገር ሁሉ ከኃጢአት በቀር ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው» [2፡16፣17] ይላል።

6 ስለዚህ፣ ክርስቶስ ደግሞ ሰብዓዊ ባሕርይን እንደ ራሱ ፍጥረት አድርጎ ተቤዥቶታል፤ እንደ ራሱ ፍጥረት አድርጎ ይቀድሰዋል፤ ከሙታን ያስነሣዋል፤ በከበረ መልክም ያስጌጠዋል። ዳሩ ግን እርሱ የውርስ ኃጢአትን አልፈጠረውም፤ አልለበሰውም፤ አልተቤዠውም፤ ወይም አልቀደሰውም። ደግሞም በምርጦቹ ውስጥ የውርስ ኃጢአትን ወደ ሕይወት አያመጣውም፤ በክብርም አያስጌጠውም ወይም አያድነውም። በዚህ ፈንታ የውርስ ኃጢአት በትንሣኤ ፈጽሞ ይደመሰሳል።[5]

7 ከዚህ ሁሉ፣ በተበላሸው ባሕርይና ይህን ባሕርይ በሚያበላሸው በዚህ ባሕርይ ውስጥ በተተከለው ብልሽት መካከል ልዩነት መኖሩን ማወቅ ቀላል ነው።

8 3. በሌላ በኩል፣ የውርስ ኃጢአት የሰብአዊ ባሕርይ አነስተኛ ብልሽት እንዳልሆነ
እናምናለን፣ እናስተምራለን፣ እናስታውቃለንም፤ ይልቁን ብልሽቱ እጅግ ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ
በሰው ሥጋ ወይም ነፍስ ውስጥ በውስጣዊውም ሆነ በውጪአዊው ኃይላቱ አንዳችም መልካም
ነገር ወይም ሳይበላሽ የቀረ ነገር የለም። ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን «በአዳም ውድቀት ምክንያት
የሰው ባሕርይ ጠፍቶአል፣ የእኛም መሠረታዊ ባሕርይ ፍጹም ተበላሽቷል»[6] ብላ
9 እንደምትዘምረው ነው። የደረሰው ብልሽት ሊገለጽ የማይችል ከመሆኑ የተነሣ በእግዚአብሔር
10 ቃል ብቻ እንጂ በእኛ አመክንዮ ሊታወቅ አይችልም። ብልሽቱ እስከዚህ ድረስ ስለ ሆነ የሰውን
ባሕርይና የዚህን ባሕርይ ብልሽት አንዱን ከሌላው ሊለይ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
«ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ ዐውቃለሁ፣
እኔ ራሴ ዐየዋለሁ፣ ዓይኖቼም ይመለከቱታል» ተብሎ በ(ኢዮብ 19፡26-27)[7] እንደ ተጻፈ ይህ
ልዩነት ፍጹም ሊሆን የሚችለው በሞት አማካይነት በትንሣኤ ጊዜ፣ አሁን ያለን ባሕርይ ያለ
ውርስ ኃጢአት ሆኖ ከእርሱም ተለይቶና ተነጥሎ በሚነሣበትና ለዘላለም በሚኖርበት ጊዜ ነው።

---

[4] የስምምነቱ ጸሐፊዎች የዕብራይስጡን ጽሑፍ ተከትለዋል። የNRSV ማስታወሻ ሉተር እንደ ተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ «ለመርዳት አልመጡም» በማለት ይተረጕመዋል። ሉተር በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡ «አንተ ያልሠራኸው ወይም የአንተ ያልሆነ በእኔ ምንም የለም» በማለት ያስቀምጠዋል።

[5] ከአንቀጽ 3-6 ያሉት መከራከሪያዎች የማትያስ ፍላሽየስን ተከታዮች ለመቃወም ከቀረቡት ዋና ዋና መከራከሪያዎች መካከል አንዱን መስመር ያጠቃልላሉ።

[6] የኑረምበርግ ከተማ ጸሐፊ ላዛረስ ስፔንግለር ከጻፈው (1523) Lutheran Worship 363, The Lutheran Hymnal 369 ከተሰኘው የመዝሙር ጽሑፍ የተጠቀሰ።

[7] ሉተር በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት።

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*ሐሰተኛውን ተቃራኒ ትምህርት ስለ መቃወም*

11 1. ስለዚህ፣ የውርስ ኃጢአት ምንም ዓይነት የእኛ የራሳችን ባሕርይ ብልሽት ሳይሆን ከሌላ ሰው ስሕተት የሚመጣ፣ *reatus ሪአቱስ* ማለት፣ የበደል ስሜት ብቻ ነው የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም።[8]

12 2. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ክፉ ፍላጎቶች ኃጢአት ሳይሆኑ ባሕርያችን በተፈጠረበት ሁኔታ ውስጥ ያሉ መሠረተ ባሕርያት ናቸው፤ ከዚህም የተነሣ እላይ የተዘረዘሩት ጉድለቶች ወይም ብልሽቶች ከክርስቶስ ውጭ ያለው ሰብዓዊ ፍጥረት እንደ ቊጣ ልጅ የሚቈጠርባቸው እውነተኛ ኃጢአቶች አይደሉም የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።

13 3. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከውድቀት በኋላ እንኳ ሰብዓዊ ባሕርይ አልተበላሸም፤ በተለይም በመንፈሳዊ ጉዳዮች (በ)*ናቹራሊያ naturalia* ማለት፣ በተፈጥሮአዊ ኃይሎቹ ፍጹም መልካምና ንጹሕ ነው የሚለውን የጴላግዮሳውያንን ስሕተት[9] ደግሞ እንቃወማለን።

14 4. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የውርስ ኃጢአት በሰው ባሕርይ ውጪአዊ ገጽ ላይ የተቀባ አነስተኛና ኢምንት የሆነ እድፍ ብቻ ነው፣ እርሱም ጥልቀት የሌለው ቈሻሻ ስለ ሆነ ከበታቹ ያለው ሰብአዊ ባሕርይ በመንፈሳዊ ጉዳዮች እንኳ በጎ ኃይሎቹን እንደ ያዘ ይኖራል የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።

15 5. እንዲሁም፣ የውርስ ኃጢአት ለእነዚህ በጎ መንፈሳዊ ኃይሎች አንድን መግነጢስ (ማግኔት) በነጭ ሽንኩርት ጭማቂ[10] እንደ መቀባት የሚቈጠር ውጪአዊ እንቅፋት ብቻ እንጂ የእነርሱ መታጣት ወይም ጉድለት ጉዳይ አይደለም፤ ጭማቂው የመግነጢሱን (የማግኔቱን) የተፈጥሮ ኃይሎች የሚያስወግድ ሳይሆን በእነርሱ መካከል ጣልቃ የሚገባ ብቻ ነው። ወይም ይህ ጒድፍ ከፊት ላይ ወይም ቈሻሻ ቀለም ከግድግዳ ላይ በቀላሉ ታጥቦ እንደሚጠፋ ሊወገድ ይችላል የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።

16 6. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በሰው ውስጥ ያሉት፣ ሰብዓዊ ተፈጥሮ እና መሠረታዊ ባሕርይ ሙሉ በሙሉ የተበላሹ ሳይሆን ሰዎች በመንፈሳዊ ጉዳዮች እንኳ አንድ መልካም ነገር አላቸው፤ እንደ አቅም፣ ተሰጥኦ፣ የመሳሰሉት መልካም ነገሮች ስለ አሉአቸው በመንፈሳዊ ጉዳዮች አንድን ነገር ለመጀመር ወይም ለማስገኘት ወይም ከእነዚህ ዓይነት ድርጊቶች ጋር ለመተባበር ብቃት ወይም ችሎታ አላቸው የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።

17 7. በሌላ በኩል፣ የውርስ ኃጢአት ሰይጣን በሰብዓዊ ባሕርይ ውስጥ ያሰረጸው እና መርዝ ወይን እንደሚደባለቁ ከእርሱ ጋር የደባለቀው ዋናና ራሱን የቻለ አንድ ነገር ነው የሚለውን የማኒኬያውያንን[11] የሐሰት ትምህርት ደግሞ እንቃወማለን።

18 8. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ኃጢአትን የሚሠራው ፍጥረታዊው ሰው ሳይሆን በሰውዬው ውስጥ ያለ አንድ የተለየና ባዕድ የሆነ ነገር ነው፣ ስለሆነም ሊከሰስ የሚገባው ሰብአዊ ባሕርይ ሳይሆን በዚህ ባሕርይ ውስጥ ያለው የውርስ ኃጢአት ብቻ ነው የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።

[8] ይህንንና የሚቀጥለውን ሀሳብ በተመለከተ SD 1, ቁጥር 31 እና 32 ተመልከት።

[9] ስለ ጸጋና ሥራ በዘመኑ በነበረው ውዝግብ የአውግስጢኖስ ተቃዋሚ የነበረው እንግሊዛዊው መነኩሴ ጴላጊዮስ፣ ድነት በሰብዓዊ ፍጡራን ያለ መለኮት ጸጋ፣ ወይም በጣም ትንሽ በሆነ የመለኮት ጸጋ እርዳታ ሊፈጸም ይችላል ለሚለው አመለካከት ስሙን አወረሰ።

[10] በዘመኑ በብዛት ታዋቂ የነበረው እምነት።

[11] ክርስቲያን ያልነበረው ፈላስፋ ማኒ በመልካሙ ወገንና በክፉው ወገን ከሞላ ጐደል እኩልነት ያላቸውን መለኮታዊ ኃይሎች ወይም አካሎች ላስቀመጠው አክራሪ ለሆነው የሁለትዮሽ ዐስተሳሰብ ስሙን አወረሰ፤ የፍላሽየስና የእርሱ ተከታዮች ተቃዋሚዎች የውርስ ኃጢአት «በመደበኛ» መጠኑ፣ ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት የወደቀው ሰብዓዊ ባሕርይ አኳኋን ነው የሚለውን የእርሱን አመለካከት ለማሳየት «ማኒኬያዊ» በሚለው ቃል ይጠቀሙ ነበር፤ «በመደበኛ» የሚለው ቃል አንድ ነገር መጀመሪያ እንደታቀደለት መሆኑን የሚያመለክተውን የአሪስቶትልን ስሜት የሚያንጸባርቅ ነው፤ ተቃዋሚዎቹ የእርሱን አመለካከት ከጥንት ማኒኬያውያን ጋር ያስተካከሉት የፍላሽየስን ተጨባጭ ትምህርት በመፍራት ሳይሆን የእርሱ አመለካከት የሚያመራበትን አቅጣጫ በመፍራት ነበር።

19 9. ደግሞም እኛ[12] የውርስ ኃጢአት በእውነቱ ያለ አንዳች ልዩነት፣ የተበላሸው ሰው መሠረታዊ ተፈጥሮ፣ ማንነት እና መሠረታዊ ባሕርይ ነው፤ ስለ ሆነም ከውድቀት በኋላ በራሱና ከራሱ የተነሣ በሰብዓዊ ባሕርይና በውርስ ኃጢአት መካከል ምንም ዓይነት የልዩነት ዐሳብ ሊኖር አይገባም፤ በእኛም ዐስተሳሰብ አንዱ ከሌላው ሊለያዩ አይገባም የሚለውን ትምህርት እንደ ማኒኬያውያን ስሕተት አድርገን እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም።

20 10. ሉተር ይህንን የውርስ ኃጢአት 'የተፈጥሮ ኃጢአት'፣ 'የማንነት ኃጢአት'፣ 'የመሠረታዊ ባሕርይ ኃጢአት' ብሎ ይጠራዋል፤ ዳሩ ግን ይህን ሲል በሁለቱ መካከል አንዳች ልዩነት ሳይኖር፣ ይህ የሰውዬው ተፈጥሮ ማንነት ወይም መሠረታዊ ባሕርይ በራሱና ከራሱ የተነሣ፣ የውርስ ኃጢአት ነው በሚል ስሜት አይደለም፤ ይልቁንም እርሱ በእነዚህ መግለጫዎች አማካይነት በሰብዓዊው ባሕርይ ውስጥ በተተከለው የውርስ ኃጢአትና የግብር ኃጢአቶች በሚባሉት በሌሎች ኃጢአቶች መካከል ልዩነት መኖሩን ግልጽ ማድረጉ ነው።

21 11. ምክንያቱም የውርስ ኃጢአት አንድ ሰው በድርጊት የሚፈጽመው ኃጢአት አይደለም፣ ይልቁን በሰውዬው ማንነት፣ መሠረታዊ ተፈጥሮና መሠረታዊ ባሕርይ ውስጥ የተተከለ ነው። ያ ማለት ምንም እንኳ በተበላሸው ሰው ልብ ውስጥ ክፉ ዐሳብ ባይነሣም፣ ክፉ ቃል ባይወጣም፣ ክፉ ሥራ ባይሠራም ዳሩ ግን «ከልብ ክፉ ዐሳብ ... ይወጣልና» (ማቴ 15፡19) እንዲሁም «የሰው ልብ ዐሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና» (ዘፍ 8፡21) ተብሎ እንደ ተጻፈ የእኛ ባሕርይ ገና ስንወለድ በኃጢአተኛው ዘር አማካይነት በእኛ ውስጥ በተተከለውና እንደ ክፉ ዐሳብ፣ ክፉ ቃላትና ክፉ ሥራዎች ለመሳሰሉት የግብር ኃጢአቶች ምንጭ በሆነው በውርስ ኃጢአት የተበላሸ ነው።

22 12. ስለዚህ ማኒኬያውያን ስሕተታቸውን የሚሰውሩበትንና ብዙ የማያስተውሉ ሰዎችን ወደ ጥፋት ስሕተት የሚመሩበትን «ተፈጥሮ» የተሰኘውን ቃል የተለያዩ ትርጕሞች ልብ ማድረግ መልካም ነው።[13] ምክንያቱም «እግዚአብሔር የሰውን ተፈጥሮ ፈጠረ» ስንል አንዳንድ ጊዜ የሰውን ማንነት መሠረታዊ ባሕርይ የሚያመለክት ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ «መናደፍ የእባብ ተፈጥሮ ነው» እንዲሁም «ኃጢአትን መሥራት የሰው ተፈጥሮ ወይም ችሎታ ነው፤ በመሆኑም የሰው ተፈጥሮ ኃጢአት ነው፤» ስንል አንዳንድ ጊዜ በአንድ ነገር ተፈጥሮ ወይም መሠረታዊ ባሕርይ ውስጥ የተተከለውን መልካም ወይም ክፉ ችሎታ ጭምር የሚያመለክት ይሆናል፤ እዚህ ላይ «ተፈጥሮ» የሚለው ቃል የሰው ማንነት መሠረታዊ ተፈጥሮ ማለት ሳይሆን በዚያ ተፈጥሮ ወይም መሠረታዊ ተፈጥሮ ውስጥ የተተከለውን አንድ ነገር የሚያመለክት ነው።

23 13. *substantia* and *accidens* ሰብስታንቲያ እና አክሲዴንስ[14] የሚሉትን የላቲን ቃላት በተመለከተ እነርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ስላልሆኑና አብዛኛው ሕዝብ የማያውቃቸው ስለ ሆኑ እነርሱን ለማይገነዘበው ለአብዛኛው ሕዝብ ስብከት በሚሰጥበት ጊዜ በእነርሱ መጠቀም አይገባም፤፣ ተራው ሕዝብ ከእነዚህ ቃላት ነጻ መሆን አለበት።

24 ዳሩ ግን በትምህርት ቤትና በተማሩት ሰዎች ዘንድ እነዚህ ቃላት የታወቁ ስለ ሆኑ የአንድ ነገር መሠረታዊ ባሕርይ ከዚያ ነገር ጋር በ«ድንገተኛ» ሁኔታ ከሚጣበቅበት ነገር ለመለየት ያለ አንዳች ችግር በእነርሱ መጠቀም ይቻላል፤ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ስለ ውርስ ኃጢአት በሚካሄድ ምሁራዊ ውይይት ውስጥ በትክክል የተጠበቁ ናቸው።

25 በእግዚአብሔር ሥራና በዲያብሎስ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት በእነዚህ ቃላት አማካይነት እጅግ በጣም ግልጽ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ዲያብሎስ መሠረታዊ ተፈጥሮን ለመፍጠር ስለማይችል ዳሩ ግን እግዚአብሔር የፈጠረውን መሠረታዊ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ፈቃድ በ«ድንገተኛ» መንገድ ለማበላሸት ብቻ የሚችል ስለ ሆነ ነው።

[12] የሚከተሉት አምስት አንቀጾች በጀርመኑ የመጀመሪያ ቅጂ አንድ ወጥ ሆነው ከአንድ እስከ አምስት ተራ ቍጥር የተሰጣቸው ነበሩ።

[13] እዚህ ላይ «ማኒኬያውያን» የሚለው ቃል የተጠቀሰው የፍላሽየሳውያንን ወገን ለማመልከት ነው።

[14] ስለ እነዚህ ቃላት ከታች SD 1, 540 ቍጥር 45 ተመልከት።

# II.(2)
# ስለ ነጻ ፈቃድ

## *የውዝግቡ ሁኔታ*
## በዚህ ክርክር ውስጥ ያለው ዋናው ጥያቄ[15]

1 የሰው ፈቃድ ለክርክር የሚቀርበው ተመሳሳይ ባልሆኑ በአራት ሁኔታዎች (1. ከውድቀት በፊት፣ 2. ከውድቀት በኋላ፣ 3. ከዐዲስ ልደት በኋላ፣ 4. ከሥጋ ትንሣኤ በኋላ)[16] ስለ ሆነ ዋናው ጥያቄ የሚነሣው በሁለተኛው ሁኔታ ውስጥ ብቻ ያለው የሰው ፈቃድና ችሎታ ነው። ሰዎች ከመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ውድቀት በኋላ እና ከዳግም ልደታቸው በፊት፣ በመንፈሳዊ ጉዳዮች በራሳቸው ምን ዓይነት ኃይላት አላቸው? በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ዐዲስ ልደትን ከመቀበላቸው በፊት በራሳቸው ኃይላት በቃሉና በቅዱሳት ምሥጢራት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የቀረበላቸውን ጸጋ ለመቀበል ራሳቸውን እንደሚገባ ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ለማዘንበልና ራሳቸውን ለማዘጋጀት ይችላሉ ወይስ አይችሉም?

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተው የዚህ አንቀጽ ንጹሕ ትምህርት

2 1. በዚህ አንቀጽ ላይ የእኛ ትምህርት፣ እምነትና መግለጫ «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም» (1ቆሮ 2፡14) ተብሎ እንደ ተጻፈ ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች ቢጠየቁ የሰው አመክንዮና መረዳት በመንፈሳዊ ጉዳዮች ዕውሮች እና በራሳቸው ኃይላት ምንም የማይገነዘቡ ናቸው የሚል ነው።

3 2. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ዳግም ያልተወለደ ሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ዘወር ያለ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጠላትም መሆኑ፣ «የሰው ልብ ዐሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና» ተብሎ እንደ ተጻፈው (ዘፍጥረት 8፡21) ክፉና ከእግዚአብሔር ተቃራኒ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ምኞትና ፈቃድ ብቻ ያለው እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናሳውቃለንም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ «ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፤ መገዛትም ተስኖታል» (ሮሜ 8፡7)። «በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን» ተብሎ እንደ ተጻፈው (ኤፌ 2፡5) አንድ አስከሬን ለሥጋዊና ለምድራዊ ሕይወት ራሱን ሕያው ለማድረግ እንደማይችል ሁሉ በኃጢአት አማካይነት በመንፈስ የሞቱ ሰዎች ለመንፈሳዊ ሕይወት ራሳቸውን ማስነሣት አይችሉም። ስለዚህ እኛ «ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም» (2ቆሮንቶስ 3፡5)።

4 3. ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መለወጥን ያለ መሣሪያ ተግባራዊ
አያደርግም፤ ወንጌል ለማዳን «የእግዚአብሔር ኃይል» ነውና ተብሎ እንደ ተጻፈው (ሮሜ 1፡16)
5 ይህን ለመፈጸም የእግዚአብሔርን ቃል መስበክንና መስማትን ይጠቀማል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣
እምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነው (ሮሜ 10፡17)።[17] የእግዚአብሔር
ፈቃድ ሰዎች ቃሉን እንዲሰሙ እና ጆሮዎቻቸውን እንዳይደፍኑ ነው። በሐዋርያት ሥራ 16፡14
እንደ ልድያ በጸጋው አማካይነት ሰውን የሚለውጠው እርሱ ብቻ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ
ኃይል ሰምተውት ይለወጡ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ቃል ውስጥ በመገኘት የሰውን ልብ

---

[15] በዚህ ክርክር ስለ ተሳተፉት ወገኖች ከታች 11, 543-44 nn. 57-60 ተመልከት።
[16] ከአውግስጢኖስ ስለ መነጨው ስለዚህ ልዩነት ከታች SD 11: 543 ቊጥር 55 ተመልከት።
[17] በቡልጌቱ መሠረት የተጠቀሰ እንጂ፣ ሉተር የተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ወይም NRSV አይደለም።

6 ይከፍታል። ምክንያቱም ያለ እርሱ ጸጋ የእኛ «ፈቃድና ጥረት»፣ የእኛ መትከል፣ መዝራት፣ እና ማጠጣት «እርሱ ካላሳደገ በስተቀር» (ሮሜ 9:16፤ 1ቆሮ 3:7) ምንም ዋጋ የላቸውም። ይህም ክርስቶስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» እንደሚለው ነው (ዮሐንስ 15:5)። በእነዚህ ጥቂት ቃላት አማካይነት ነጻ ፈቃድ ምንም የራሱ ኃይል የሌለው መሆኑን በመግለጽ በእግዚአብሔር ፊት ማንም እንዳይመካ (1ቆሮ 9:16) ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ጸጋ ያስረክባል።

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*ተቃራኒ የሐሰት ትምህርት*

7 ስለዚህ ከዚህ የሚከተሉትን ስሕተቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል መርህን የሚቃረኑ በመሆናቸው እንቃወማቸዋለን፤ እናወግዛቸዋለንም፤

8 1. የሚሆነው ማንኛውም ነገር አሁን በሚሆንበት መንገድ መሆን አለበት እንጂ በሌላ መንገድ ሊሆን አይችልም፤ እንዲሁም በውጫዊ ነገር እንኳ ሰዎች የሚያደርጉትን ማንኛውንም ነገር የሚያደርጉት በመገደድ ስለ ሆነ እንደ ሥጋ ፍትወት፣ ዝርፊያ፣ ግድያ፣ ስርቆትና የመሳሰሉትን ማንኛቸውንም ክፉ ሥራዎች እንዲፈጽሙ ይገደዳሉ የሚሉትን ስቶይኮች[18] የተባሉትን ፈላስፋዎችና የማኒኬያውያን የእብደት ፈጠራ እንቃወማለን።

9 2. ደግሞም ሰዎች ራሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ፣ ወንጌሉን ለማመን፣ በሙሉ ልባቸው ለእግዚአብሔር ሕግ ታዛዦች ለመሆን ይችላሉ፤ በመሆኑም ያለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ በራሳቸው ኃይላት የኃጢአት ይቅርታንና የዘላለም ሕይወትን ሊያገኙ ይችላሉ ብለው የሚያስተምሩትን የጭፍን ጴላጊዮሳውያንን ስሕተት እንቃወማለን።

10 3. እንዲሁም ሰዎች በራሳቸው ኃይላት የራሳቸውን የሕይወት ለውጥ ሊያነሣሡ ይችላሉ፤ ዳሩ ግን ያለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ወደ ፍጻሜ ሊያደርሱት አይችሉም ብለው የሚያስተምሩትን የከፊል ጴላጊዮሳውያን ስሕተት እንቃወማለን።[19]

11 4. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሰዎች ምንም እንኳ ከዳግም ልደት በፊት በራሳቸው ነጻ ፈቃድ የራሳቸውን የሕይወት ለውጥ ለማነሣሣት የሚያስችል ብርታት ስለሌላቸው በራሳቸው የተፈጥሮ ኃይላት መሠረትነት ራሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና በሙሉ ልባቸው ለእግዚአብሔር ሕግ ታዛዦች ለመሆን ባይችሉም፣ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ስብከት አማካይነት አንድ ጊዜ ሥራውን ከጀመረና በእርሱም ጸጋውን ከሰጠ በኋላ የሰው ፈቃድ ትንሽና ደካማ ቢሆንም፣ በራሱ የተፈጥሮ ኃይላት በተወሰነ ደረጃ አንድን ነገር ለመሥራት፣ ለመርዳትና ለመተባበር፣ ራሱን ለጸጋ ለማስተካከልና ለማዘጋጀት፣ ይህንንም ጸጋ ለመጨበጥ፣ ለመቀበል እንዲሁም ወንጌሉን ለማመን ይችላል የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።[20]

12 5. እንዲሁም፣ ሰው ከዳግም ልደት በኋላ የእግዚአብሔርን ሕግ በትክክል ለመጠበቅና እርሱንም ሙሉ በሙሉ ለመፈጸም ይችላል፤ ይህም ሕግን የመፈጸም ተግባር በእግዚአብሔር ፊት የዘላለም ሕይወት የሚያስገኝልን ጽድቃችን ይሆናል የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን።[21]

13 6. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር ሰዎችን፣ ያለ ጸጋ መቀበያ መሣሪያ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሰሙ፣ በቅዱሳት ምሥጢራት እንኳ ሳይጠቀም፣ ወደ ራሱ

[18] ይህ ጥንታዊ የፍልስፍና ዘዴ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች በተለይም በሜላንክተን አካባቢ ያሉት ይጠቀሙበት የነበረው ፍጹም አስፈላጊነት ያላቸውን አመለካከቶች ሁሉ ለማሳየት ነበር።

[19] የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ጸሐፊዎች ሉተርን ጨምሮ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በነበረችው ጀርመን ላይ ሰፊ ተጽእኖ ያሳደሩትን አብዛኛዎቹን የኋለኛው መካከለኛ ዘመን እንደ ገብርኤል ባይኤል ያሉ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን ዐሳብ ተረድተው ነበር።

[20] የፊልጶሳውያንን የትብብር ዘዴ ለማመልከት የተጠቀሰ፤ ለምሳሌ በዮሐንስ ፕፌንገርና በቪክቶሪን ስትሪጌል ትምህርት ውስጥ ይገኛል።

[21] የአንዳንድ ዳግም አጥማቂዎችን ቡድኖች ፍጹማዊነትና የአንዳንድ የሮማ ካቶሊክ ወገኖች፣ በተለይም በገዳም ሥርዓቶች የሚታየውን ሰፊ ተቀባይነት የነበረውን ሃይማኖታዊ አካሄድ ለመቃወም።

ያመጣቸዋል፤ ያበራላቸዋል፤ ጻድቃን ያደርጋቸዋል፤ ያድናቸዋልም የሚለውን ዐሳብ የፈጠሩትን Enthusiasts የኢንቱሲያሲስትስን (የስሜታውያንን) ስሕተት እንቃወማለን[22] እናወግዛለንም።

14 7. እንዲሁም፣ በመለወጥና በዐዲስ ልደት እግዚአብሔር የአሮጌውን ፍጥረት መሠረታዊ ተፈጥሮ እና መሠረታዊ ባሕርይ፣ በተለይም አመክንዮታዊውን ነፍስ ፈጽሞ በማጥፋት የነፍስን ዐዲስ መሠረታዊ ባሕርይ ከባዶ ይፈጥራል የሚለውንም ዐሳብ እንቃወማለን።

15 8. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከዚህ የሚቀጥለው አነጋገር ያለ ተጨማሪ መግለጫ በሚነገርበት ጊዜ፦ የሰው ፈቃድ ከለውጥ በፊት፣ በለውጥ ውስጥና ከለውጥ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ይቃወማል፤ መንፈስ ቅዱስም እርሱን ሆነ ብለውና በጽናት ለሚቃወሙት ሰዎችም ይሰጣል፤ የሚለውን እንቃወማለን። ምክንያቱም አውግስጢኖስ እንደሚለው በመለወጥ ውስጥ እግዚአብሔር ፈቃደኞች ያልሆኑትን ሰዎች ፈቃደኞች በማድረግ በፈቃደኞቹ ይኖራልና።[23]

16 አንዳንድ የጥንትና የዛሬው ዘመን የቤተ ክርስቲያን መምህራን «እግዚአብሔር ሰዎችን ይስባል፣ ዳሩ ግን እርሱ የሚስበው ፈቃደኞች የሆኑትን ነው»፣ እንደገናም «የሰው ፈቃድ በለውጥ ጊዜ ዝም ብሎ አይቀመጥም፤ ዳሩ ግን አንድ ነገር ያደርጋል» ዓይነት መግለጫዎችን ይጠቀማሉ፤ እንደዚህ ያሉት መግለጫዎች ጥቅም ላይ የዋሉት በለውጥ ጊዜ ከእግዚአብሔር የጸጋ ትምህርት ተቃራኒ በሆነ መንገድ የተፈጥሮአዊውን ነጻ ፈቃድ ሕልውና ለማረጋገጥ ስለ ሆነ፣ እነዚህ መግለጫዎች ከጤናማ ትምህርት መልክ ጋር የማይስማሙ በመሆናቸው ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ በምንናገርበት ጊዜ እነርሱን መተው ተገቢ ይሆናል።

17 በሌላ በኩል በለውጥ ጊዜ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የመሳብ ኃይል አማካይነት ግትርና እምቢተኞች ሰዎችን ፈቃደኞች ያደርጋል፤ እንዲሁም ከዚህ ለውጥ በኋላ ዳግም የተወለደው ሰው ፈቃድ በየዕለቱ በሚደረገው ንስሐ ዝም ብሎ አይቀመጥም፣ ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ በእኛ በኩል በሚሠራው ሥራ ሁሉ ይተባበራል ማለት ትክክል ነው።

18 9. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ዶ/ር ሉተር በመለወጥ ሂደት ውስጥ የሰው ፈቃድ «ተደራጊ ብቻ ነው» (ማለትም ጭራሽ ምንም ነገር አያደርግም) ብሎ በሚጽፍበት ጊዜ *ሪስፔክቱ ዲቪኔ ግራቴ ኢን አክሲዴንዲስ ኖቪስ ሞቲቡስ*[24] (*respectu divinae gratiae in accendendis novis motibus)* የሚል ግንዛቤ ማግኘት አለበት፤ ይህም ማለት በሚደመጠው ቃል ወይም በቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎት አማካይነት የእግዚአብሔር መንፈስ የሰውን ፈቃድ በሚይዝበትና ዐዲስ ልደትንና መለወጥን በሚያስገኝበት ጊዜ ማለት ነው። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ዐዲስ ልደትንና መለወጥን በሚያስገኝበትና በሚያከናውንበት፣ እንዲሁም በመለኮታዊ ኃይሉና ተግባሩ ብቻ የሰውን ፈቃድ በሚለውጥበትና በሚያድስበት ጊዜ የታደሰው የሰው ፈቃድ ጸጋን መቀበል ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በሚመነጬት ሥራዎች ውስጥም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለሚተባበር የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሣሪያና መጠቀሚያ ይሆናል።

19 ስለዚህ ሰው መለወጥን ከማግኘቱ በፊት ብቃት ያላቸው ሁለት መንስኤዎች ብቻ አሉ፤ እነርሱም መንፈስ ቅዱስና እርሱ ለውጥን የሚያከናውንበት የእርሱ መሣሪያ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ናቸው፤ ሰብአዊው ፍጥረት ይህንን ቃል መስማት አለበት፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጸጋና አሠራር አማካይነት ብቻ እንጂ በገዛ ራሱ ኃይላት መሠረትነት ሊያምነውና ሊቀበለው አይችልም።[25]

---

[22] አንድ የጎዳግ ማስታወሻ ይህንን አመለካከት «ያለ እግዚአብሔር ቃል ስብከት ከሰማይ የመንፈስን መገለጥ የሚጠብቁት [እነርሱ] የስሜታውያን አመለካከት እንደሆነ» አድርጎ ይገልጸዋል፣ ደግሞም *CA* V. ተመልከት።

[23] አውግስጢኖስ *Against Two Letters of the Pelagians* I, 19, 37 (*MPL* 44:568; *NPNF*, ser. 1, 5:389).

[24] «ፍጹም ተቀባይነት» እና «ዐዳዲስ እንቅስቃሴዎችን በመፍጠር ውስጥ የመለኮትን ጸጋ በተመለከተ»።

[25] ሦስት የአርስጣጣሊያውያንን መንስኤዎች የጠቀሰበትን የሜላንክተንን የ1535 እና የ1543 Loci Communes ለማመልከት የተጠቀሰ ነው፤ እነዚህም ሦስት መንስኤዎች መንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ቃልና የሰው ፈቃድ ሲሆኑ ሜላንክተን ለመግለጽ የፈለገውም መለወጥንና ንስሐን ለማስገኘት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በፈቃድ ላይ  የሚጠቀምበትን አሠራር ለማመልከት ነው።

## III. (3)
## በእግዚአብሔር ፊት በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ፤

### *የውዝግቡ ሁኔታ፤*
### በዚህ ክርክር ውስጥ ያለው ዋናው ጥያቄ፤[26]

1 የእኛ አብያተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር ቃልና በኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ መሠረት እኛ ምስኪን ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን የምንሆነውና የምንድነው በክርስቶስ በማመን ብቻ ስለሆነ ክርስቶስ ብቻ ጽድቃችን እንደ ሆነ በአንድ ድምፅ ያስታውቃሉ። እርሱም እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው ነው፤ ምክንያቱም በእርሱ መለኮታዊውና ሰብአዊው ባሕርያት እርስ በርሳቸው አንድ ሆነው ስለሚገኙ ነው (ኤር 23፡6፤ 1ቆሮ 1፡30፤ 2ቆሮ 5፡21)። ከዚህ መግለጫ የተነሣ ክርስቶስ ጽድቃችን የሆነው በየትኛው ባሕርዩ ነው? የሚል ጥያቄ ተነሣ፤ በዚህም ምክንያት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርሳቸው ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ስሕተቶች ተፈጠሩ።

2 አንዱ ወገን ክርስቶስ ጽድቃችን የሚሆነው በመለኮታዊው ባሕርዩ ብቻ ነው፤ ይኸውም እርሱ በእምነት በእኛ ሲኖር ነው። መላው የሰው ፍጥረት ኃጢአቶች በእምነት በእኛ ከሚኖረው ከዚህ መለኮታዊነት ጋር ሲወዳደሩ በአንድ ትልቅ ባሕር ውስጥ እንዳለ እንደ አንድ ጠብታ የሚቈጠሩ ናቸው የሚለውን አቋም ያዘ። አንዳንዶች ግን ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን የሚሆነው በሰብአዊ ባሕርዩ ብቻ ነው የሚለውን አቋም ይዘዋል።

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

ከእነዚህ ሁለት ስሕተቶች ተቃራኒ የሆነው ንጹሑ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፤

3 1. እኛ ከእነዚህ ከሁለቱም ስሕተቶች በተቃራኒው ክርስቶስ ጽድቃችን የሚሆነው በመለኮታዊው ባሕርዩ ብቻ ወይም በሰብአዊ ባሕርዩ ብቻ አለመሆኑን በአንድ ድምፅ (ተስማምተን) እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም። በተቃራኒው ሙሉው ክርስቶስ በአምላክነቱና በሰብአዊነቱ እስከ ሞት ድረስ ለአባቱ በመታዘዙ ብቻ በሁለቱም ባሕርያቱ ጽድቃችን ነው፤ በዚህም መታዘዝ አማካይነት «በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ 5፡19) እርሱ ለእኛ የኃጢአት ይቅርታንና የዘላለም ሕይወትን አስገኘልን።

4 2. በዚህም መሠረት እኛ በእግዚአብሔር ፊት ያለን ጽድቅ ባለፈውም ሆነ አሁን ወይም ወደ ፊት በእኛ በኩል አንዳች ሥራ፣ ትሩፋት ወይም በገዛ ራሳችን የተገባን ሳንሆን በጸጋው ብቻ ኃጢአታችንን ይቅር የሚለን፣ የክርስቶስን የመታዘዝ ጽድቅ ለእኛ የሚሰጠንና የሚቈጥርልን፣ እንዲሁም በእርሱ ጽድቅ ምክንያት እግዚአብሔር በጸጋው ብቻ የሚቀበለንና እንደ ጻድቃን የሚቈጥረን መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።

5 3. ክርስቶስን የምንይዝበት ብቸኛ መንገድና መሣሪያ እምነት እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፤ ስለሆነም ደግሞ «በእግዚአብሔር ፊት የሚጠቅመውን ይህን ጽድቅ»[27] በክርስቶስ እንይዛለን። በክርስቶስ ምክንያት እንዲህ ያለ «እምነት ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርልናል» (ሮሜ 4፡5)።

6 4. ይህ እምነት የክርስቶስን ታሪክ ማወቅ ብቻ እንዳልሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም። ይልቁኑ፣ ከእርሱ መታዘዝ የተነሣ ብቻ፣ በጸጋው፣ የኃጢአትን ስርየት እናገኝ ዘንድ፣ በእግዚአብሔር አብ ቅዱሳንና ጻድቃን ሆነን እንቈጠር እና የዘላለም ሕይወት

---

[26] በዚህ ክርክር የተሳተፉትን ወገኖች በተመለከተ ከታች SD III, 562 ቍጥር 101-103 ተመልከት።
[27] ሉተር በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ከሮሜ 1፡17 የተጠቀሰ።

ይኖረን ዘንድ እምነት በወንጌሉ ቃል አማካይነት ክርስቶስ በእውነት ቤዛችን እንደ ሆነ ለይተን
የምናውቅበት እንዲሁም በእርሱ የምንታመንበት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
7 5. በዚህ አንቀጽ «ማጽደቅ» ማለት በቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አጠቃቀም መሠረት
«መፍታት» ማለትም «ከኃጢአት ነጻ መሆንን ማወጅ» ነው፤ «ኃጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ
ላይ የሚፈርድ ሁለቱም በአንድነት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው» (ምሳሌ 17:15)፤
«እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው» (ሮሜ 8:33)።
8 በዚህ ስፍራ በመከላከያው እንደሚታየው «ሬጀነሬቲዮ» እና «ቪቪፊካቲዮ»፣ (*regeneratio* and
*vivificatio*) ማለትም «ዐዲስ ልደት» እና «ሕያው ማድረግ» የሚሉት ቃላት የመጽደቅ
ተመሳሳይ ሆነው በሚገለጡበት ጊዜ በዚሁ ዓይነት ግንዛቤ ማግኘት አለባቸው፤ አለበለዚያ የሰው
ልጅ መታደስ ጉዳይ እንደ ሆኑ ተደርገው ሲቈጠሩ፣ «በእምነት ከመጽደቅ ሁኔታም» የተለዩ
ሊሆኑ ይገባል።
9 6. በክርስቶስ የሚያምኑትና በእውነት ዳግም የተወለዱት ሰዎች ምንም እንኳ እስከ
ዕለተ ሞታቸው ድረስ ታላቅ ድክመትና ዝለት የማይለያቸው ከመሆኑ እውነታ ባሻገር በእምነት
ለእነርሱ የተቈጠረላቸውን ጽድቅ፣ ወይም የነፍሳቸውን ድነት መጠራጠር የለባቸውም፤ ዳሩ
ግን፣ በተስፋውና በቅዱሱ የወንጌል ቃል መሠረት ከክርስቶስ የተነሣ ቸርነትን የተሞላ አምላክ
እንዳላቸው እርግጠኛ አድርገው ሊቈጥሩት እንደሚገባቸው እናምናለን፤ እናስተምራለን፤
እናስታውቃለንም።
10 7. በእግዚአብሔር ፊት የሚቈጠረውን የእምነትን ጽድቅ በተመለከተ ያለውን ንጹሕ
ትምህርት ይዞ ለማቆየት የሚከተሉትን የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አገላለጾችን በተለይ
*«ጠርቲኩሌ ኤክስክሉሲቬን»*[28] (*particulae exclusivae*) (በተለየ ሁኔታ ልዩ ሆኖ የተገለጠውን)
ማለትም የክርስቶስን ትሩፋት ከእኛ ሥራ ሙሉ በሙሉ የሚለዩትንና ክብርን ለክርስቶስ ብቻ
የሚሰጡትን በስፍራቸው አጥብቆ መያዝ አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤
እናስታውቃለንም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «በጸጋ»፣ «ያለ በጎ
ሥራ»፣ «ያለ ሕግ»፣ «ያለ ሥራ»፣ «ከሥራ አይደለም»፤ ወዘተ.። እነዚህ አገላለጾች በሙሉ እኛ
ጻድቃን የምንሆነውና ድነትን የምንቀበለው በክርስቶስ «በእምነት ብቻ» ነው ከማለት ሌላ
ምንም ማለት አይደሉም።
11 8. ምንም እንኳ ከመጽደቅ በፊት የሚቀድመው ጸጸትና ከእርሱ በኋላ የሚከተሉት
መልካም ሥራዎች በእግዚአብሔር ፊት ስለ መጽደቅ በሚናገረው አንቀጽ ውስጥ የማይገኙ
ቢሆንም፣ አንድ ሰው ኃጢአት ለመሥራትና ከሕሊናው ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ለመፈጸም
ካለው ክፉ ዐሳብ ጋርና ጐን መኖር የሚችል አንዳች እምነት ቀላቅሎ መፍጠር የለበትም ብለን
እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም። በዚህ ፈንታ አንድ ሰው በእምነት ከጸደቀ በኋላ
እውነተኛና ሕያው የሆነ «በፍቅር የሚሠራ እምነት» (ገላ 5:[6]) ይኖረዋል። ይህም ማለት
የሚያጸድቅ እምነት፣ እውነተኛና ሕያው እምነት በሚሆንበት ጊዜ መልካም ሥራዎች ሁልጊዜ
ይከተሉታል፤ ከእርሱም ጋር በእርግጥ አብረው ይገኛሉ ማለት ነው። ምክንያቱም እምነት
ሁልጊዜ በፍቅርና በተስፋ ይታጀባል እንጂ ፈጽሞ ብቻውን አይሆንምና።

*ተቃራኒ ወይም አሉታዊ ዐሳቦች*

ተቃራኒ ትምህርትን ስለ መቃወም፤

12 ስለዚህ ከዚህ የሚከተሉትን ስሕተቶች ሁሉ ማለትም፡-
13 1. ክርስቶስ ጽድቃችን የሚሆነው በመለኮታዊ ባሕርዩ መሠረት ብቻ ነው ወዘተ[29]
የሚለውን፣

[28] «ልዩነትን የሚያመለክቱ ቃላት።»
[29] የአንድሪው ኦሲያንደር አቋም።

14 2. ክርስቶስ ጽድቃችን የሚሆነው በሰብአዊ ባሕርዩ መሠረት ብቻ ነው፣ ወዘተ[30] የሚለውን፣

15 3. በነቢያቱና በሐዋርያቱ ጽሑፎች፣ በእምነት ስለ መጽደቅ በሚነገርበት ጊዜ «ማጽደቅ» እና «መጽደቅ» የሚሉት ቃላት «ከኃጢአት ነጻ ማድረግን ማወጅ» ወይም «ከኃጢአት ነጻ መሆንን ማወጅ» እና «የኃጢአት ይቅርታን መቀበል» ማለት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጥ በሚሰርፁ እና ይህንን ስርፀት ተከትለው በሚመጡ ሥራዎች ውጤት ከፍቅርና መልካም ሥራ የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን ማለት ነው[31] የሚለውን፤

16 4. እምነት ወደ ክርስቶስ መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ወደ መለኮታዊ ባሕርዩም መመልከት ይገባዋል፤ እርሱም በእኛ ውስጥ ሲያድርና ውጤቶችን ሲያስገኝ፣ በዚህ በውስጣችን በማደሩ አማካይነት ኃጢአታችን ይሸፈናል[32] የሚለውን፤

17 5. እምነት በእውነት ንስሐ በማይገባ፣ ከዚህም እምነት የሚመነጭ ፍቅርን በማያሳይና ሕሊናውን በመቃረን በኃጢአት በሚጸና ሰው የሚኖርና የሚቀመጥ እንዲሁም ዝም ብሎ በክርስቶስ መታዘዝ ላይ የሚታመን ዓይነት ነገር ነው የሚለውን፤

18 6. በአማኞች ውስጥ የሚያድረው እግዚአብሔር ራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታዎች ብቻ ናቸው የሚለውን፤

19 7. እምነት የሚያድነው ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራ ፍቅር ያለበት መታደስ በዚህ እምነት አማካይነት በእኛ ስለ ተጀመረ ነው የሚለውን ዐሳብ፤

20 8. በመጽደቅ ረገድ እምነት ግንባር ቀደም ሚና ያለው ሲሆን፣ መታደስና ፍቅርም በእግዚአብሔር ፊት የሚኖረን ጽድቅ ክፍል ናቸው:: ምንም እንኳ እነርሱ ለጽድቃችን እጅግ በጣም አስፈላጊው ምክንያት ባይሆኑም እንደዚህ ያለ ፍቅርና መታደስ ከሌለ በስተቀር ጽድቃችን በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ ወይም ፍጹም ሊሆን አይችልም የሚለውን፤

21 9. አማኞች በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቁትና ድነት የሚቀበሉት ለእነርሱ በተቈጠረላቸው በክርስቶስ ጽድቅና በውስጣቸው በተጀመረው በዐዲሱ መታዘዝ አማካይነት፤ ወይም በከፊል ለእነርሱ በተቈጠረላቸው በክርስቶስ ጽድቅ ሆኖ በከፊል ደግሞ በውስጣቸው በተጀመረው በዐዲሱ መታዘዝ አማካይነት ነው የሚለውን፤

22 10. የጸጋው ተስፋ የራሳችን የሚሆነው በልባችን በሚኖረው እምነትና በአፋችን በምንሰጠው ምስክርነት እንዲሁም በሌሎች መልካም ሥራዎች አማካይነት ነው የሚለውን፤

23 11. እምነት ያለ መልካም ሥራ አያጸድቅም ማለትም መልካም ሥራዎች ለጽድቅ የግድ አስፈላጊዎች ናቸው፣ ያለ እነርሱም መገኘት አንድ ሰው ለመጽደቅ አይችልም[33] የሚለውን፤ እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም::

## IV. (4)
## ስለ መልካም ሥራዎች

### *የውዝግቡ ሁኔታ፤*
### *መልካም ሥራን በተመለከተ የውዝግቡ ዋና ጥያቄ፤*[34]

1 የመልካም ሥራዎችን ትምህርት በሚመለከት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሁለት ውዝግቦች ተነሡ:-

2 በመጀመሪያ አንዳንድ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች በሚከተሉት መግለጫዎች ላይ ተከፋፈሉ:: የመጀመሪያው ወገን እንዲህ ብሎ ጻፈ:- መልካም ሥራዎች ለድነት አስፈላጊዎች

---

[30] የፍራንቼስኮ ስታንቻሮ አቋም::
[31] የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ ጸሐፊዎች በሮም ካቶሊክ ወገን ትምህርት ላይ የሰጡት ማጠቃለያ፣ ለምሳሌ በኦግስቡርግ ሽግግርና በትሬንት ጉባኤ ነው፤ SD III, 563, n. 107; 567-69, nn. 114-118; 570-71, nn. 122-128; 573, nn. 131-133.
[32] የአንድሪው ኦሲያንደር አቋም::
[33] ከ7-11 ያሉት ነጥቦች ሉተራውያን በዘመኑ በነበሩት የሮማ ካቶሊክ ሥነ መለኮታዊ ጽሑፎች ላይ ያቀረቡትን የነቀፌታ አመለካከት የሚያሳዩ ናቸው::
[34] በዚህ ክርክር የተሳተፉትን ወገኖች በሚመለከት ከታች SD IV, 574-75, ቍጥር 137-140 ተመልከት::

ናቸው፤ ያለ መልካም ሥራዎች ለመዳን አይቻልም፤ ያለ መልካም ሥራ ማንም የዳነ የለም፡፡ ሌላው ወገን ይህንን አቋም በመቃወም እንዲህ ሲል ጻፈ፡- መልካም ሥራዎች ለድነት ጎጂዎች ናቸው፡፡

3 በኋላ ላይ በአንዳንድ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል «አስፈላጊ» እና «ነጻ» በሚሉት ሁለት ቃላት ላይ ክፍፍል ተፈጠረ፡፡ አንዱ ወገን አስፈላጊነትና አስገዳጅነት የሌለበትን ዳሩ ግን ግብታዊ ከሆነ መንፈስ የሚመነጨውን ዐዲሱን መታዘዝ በተመለከተ «አስፈላጊ» የሚለውን ቃል መጠቀም አይገባም ሲል ተከራከረ፡፡ ሌላው ወገን እንደዚህ ያለው መታዘዝ ለእኛ ጥንቃቄ የሚገዛ ሳይሆን ዳግም የተወለዱ ሰዎች ይህን መታዘዝ መፈጸም ግዴታቸው ነው በማለት «አስፈላጊ» የሚለውን ቃል ያዘ፡፡

4 አንዱ ወገን በክርስቲያኖች መካከል ጭራሹን ሕግ መሰበክ የለበትም፤ ዳሩ ግን፣ በቅዱሱ ወንጌል መሠረት ብቻ ሰዎች መልካም ሥራ እንዲሠሩ ምክር ሊሰጣቸው ይገባል ሲል በተከራከረ ጊዜ ከእነዚህ የቃላት ትርጒም ክርክር የተነሣ በጒዳዩ ፍሬ ነገር ላይ ቀጣይ የሆነ ውዝግብ ተከሰተ፣ ሌላው ወገን ይህንን አቋም ተቃወመ፡፡

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

*ይህንን ውዝግብ በተመለከተ ንጹሕ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፤*

5 ጥልቀት ያለው መግለጫና የዚህ ክርክር ባሕርይ አድርገን የምናቀርበው የእኛ ትምህርት፣ እምነትና መግለጫ የሚከተለው ነው፡-

6 1. (ሙት እምነት ሳይሆን ዳሩ ግን ሕያው እምነት ከሆነ) ከመልካም ዛፍ መልካም ፍሬ መገኘቱ የተረጋገጠ እና ጥርጣሬ የሌለው ነገር እንደ ሆነ ሁሉ መልካም ሥራም እውነተኛ እምነትን የሚከተል ነው፡፡

7 2. ደግሞም ሐዋርያው በግልጽ እንደሚመሰክረው «እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቈጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል፤ እንዲህ ሲል፡- 'ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፣ ጌታ ኃጢአቱን የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው'» (ሮሜ 4፡6-8)[35] ደግሞም «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ኤፌ 2፡8-9) እንዳለ መልካም ሥራዎች የድነትን ጒዳይ ከሚመለከት ከማንኛውም ጥያቄና በእግዚአብሔር ፊት መጽደቃችንን ከሚመለከቱት አንቀጾቻችን ፈጽሞ መወገድ እንዳለባቸው እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለን፡፡

8 3. ደግሞም ሁሉም ሰው፣ በተለይም ዳግም የተወለዱትና በመንፈስ ቅዱስ የታደሱት ሰዎች፣ መልካም ሥራ የመሥራት ግዴታ እንዳለባቸው እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለን፡፡

9 4. በዚህ ሁኔታ «አስፈላጊ»፣ «ተገቢ»፣ «ግድ» የሚሉት ቃላት ዳግመኛ በተወለዱት
ሰዎች ረገድም ጭምር በትክክለኛ ሁኔታና በክርስትና መልክ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው፡፡
10 በምንም ዓይነት መንገድ እንደዚህ ዓይነት አጠቃቀም ከትክክለኛ ቃላትና ንግግር ሁኔታ
ሊቃረን አይችልም፡፡

5. በእርግጥ «አስፈላጊነት» እና «አስፈላጊ» የሚሉት ቃላት ዳግመኛ ለተወለዱት ሰዎች በሚነገሩበት ጊዜ በገዛ ራሳቸው እንደሚፈጽሙት ከእነርሱ እንደሚጠበቅ መታዘዝ ብቻ እንጂ እንደ ግዴታ መቈጠር የለባቸውም፤ በሕጉ አስገዳጅነት ወይም ተጽእኖ የሚፈጽሙት ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም እነርሱ «ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች» አይደሉም (ሮሜ 6፡14)፡፡

11 6. በዚህም መሠረት «ዳግመኛ የተወለዱት መልካም ሥራን የሚያደርጉት በነጻነት መንፈስ ነው» በሚባልበት ጊዜ ዳግመኛ የተወለዱት እንደ ፍላጎታቸው መልካም ሥራ ለመሥራትም ሆነ ላለመሥራት የራሳቸው ምርጫ ነው ተብሎ መቈጠር እንደሌለበት፤ ደግሞም

[35] ሉተር ከተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚጣጣም መንገድ በጥያቄ መልክ ከመዝ 32፡1 የተጠቀሰ፡፡

ሆነ ብለው በኃጢአት ጸንተው በሚኳዙበት ጊዜም እምነታቸውን እንደ ያዙ ይቀራሉ ማለትም እንዳይደለ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፡፡

12 7. ይህን ጉዳይ ጌታ ክርስቶስና የእርሱ ሐዋርያት በገለጹት መሠረት እንጂ በሌላ በማንኛውም መንገድ መረዳት የሌለብን ጉዳይ ነው፤ ማለትም ነጻ የወጣው መንፈስ እንደ ባሪያ ቅጣትን በመፍራት ሳይሆን እንደ ልጅ ጽድቅን በመውደድ የሚፈጽመው ነው (ሮሜ 8፡15)፡፡

13 8. ይሁን እንጂ፣ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 7[፡14-25] እና በገላትያ 5[፡17] ስለ ራሱ እንደሚማረረው፣ ይህ ፈቃደኝነት በተመረጡት የእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ ፍጹምነት ያለው ሳይሆን ታላቅ ድካምም የተጫነው ነው፡፡

14 9. በእርግጥ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ 8፡1) ከክርስቶስ የተነሣ ጌታ ይህንን ድካም በምርጦቹ ላይ አይቈጥርባቸውም፡፡

15 10. ደግሞም እምነትንና ድነትን በውስጣችን ሊጠብቀው የሚችለው የእኛ ሥራ ሳይሆን በእምነት የሚሠራ የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፤ መልካም ሥራዎች እርሱ በውስጣችን ለመገኘቱና ለማደሩ ምስክሮች ናቸው፡፡

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*ሐሰተኛና ተቃራኒ ትምህርት*

16 1. በዚህም መሠረት መልካም ሥራ ለድነት አስፈላጊ ነው ወይም ያለ መልካም ሥራ ከአሁን በፊት ማንም የዳነ የለም ወይም ያለ መልካም ሥራ ለመዳን አይቻልም ተብሎ የሚሰጠውን ትምህርትና የአነጋገር ዘይቤ እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም፡፡[36]

17 2. ደግሞም «መልካም ሥራ ለድነት ጐጂ ነው» የሚለውን የድፍረት አነጋገር ለክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዓት መሰናክልና እንቅፋት እንደ ሆነ አድርገን እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም፡፡[37]

18 ምክንያቱም በነዚህ በመጨረሻ ጊዜያት ሰዎችን ለክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዓትና ለመልካም ሥራ መምከር፣ እንዲሁም እንደ እምነታቸው ማረጋገጫና ለእግዚአብሔር ውለታ ምስጋና ለማቅረብ መልካም ሥራዎችን መለማመዳቸው ምንኛ አስፈላጊ እንደ ሆነ ማሳሰብ፣ መልካም ሥራ ስለ መጽደቅ ከሚናገረው አንቀጽ ጋር ሊደባለቅ እንደማይገባው እነርሱን ከማስጠንቀቅ ያነሰ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ጳጳሳዊና ፈሪሳዊ በሆነ የገዛ ራሳቸው መልካም ሥራ ሲታመኑ እንደሚኰነኑ ያህል በእምነት በመዘላበድ የኢፒኩሪያውያን ትምህርትም ሊኰነኑ ይችላሉ፡፡

19 3. ደግሞም እምነትና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት በድፍረት ኃጢአት ሊጠፉ አይችሉም፤ ዳሩ ግን ቅዱሳን የሆኑትና የተመረጡት ሰዎች ምንም እንኳ በዝሙትና በሌሎች ኃጢአቶች ቢወድቁና በእነርሱም ቢጸኑ መንፈስ ቅዱስን እንደ ያዙ ይቀራሉ የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም፡፡

[36] ጆርጅ ሜጀር የሚሟገትለት አነጋገር፡፡
[37] በሜጀርስቲክ ውዝግብ ኒኮላስ ቮን አምስዶርፍ የተጠቀመው የሉተር አገላለጽ፡፡

# V. (5)
# ስለ ሕግና ወንጌል

## *የውዝግቡ ሁኔታ*
## *በዚህ ክርክር ያለው ዋናው ጥያቄ*[38]

1 *የቅዱስ ወንጌሉ ስብከት በእውነት የኃጢአትን ይቅርታ የሚያውጅ የጸጋ ስብከት ብቻ ሳይሆን፣ ዳሩ ግን አለማመንን የሚያወግዝ (ይህም በሕጉ ሳይወገዝ በወንጌል ብቻ የተወገዘ ማለት ነው) የንስሐና የተግሣጽ ስብከት ጭምር እንደ ሆነ የሚገልጽ ክርክር ነበር።*

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

*ንጹሕ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት*

2 1. *በሕግና በወንጌል መካከል ያለው ልዩነት የእግዚአብሔር ቃል በጳውሎስ ምክር መሠረት በትክክል ተከፋፍሎ ይቀመጥ ዘንድ እንደ ልዩ ክቡር ብርሃን ተቈጥሮ በቤተ ክርስቲያን በታላቅ ትጋት መጠበቅ እንዳለበት እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።*[39]

3 2. *በትክክለኛ አነጋገር፣ ሕጉ ትክክለኛ ስለ ሆነውና እግዚአብሔርን ስለሚያስደስተው ነገር መመሪያ የሚሰጥና ኃጢአት የሆነውንና የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ የሆነውን ማንኛውንም ነገር የሚያወግዝ መለኮታዊ ትምህርት እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፤*

4 3. *ስለዚህ ኃጢአት የሆነውን የሚያወግዝ ማንኛውም ነገር የሕግ አዋጅ ነው፣ የእርሱም አካል ነው።*

5 4. *ይሁን እንጂ፣ ወንጌሉ፣ በትክክለኛ አነጋገር፣ ሕጉን ያልጠበቀውና በእርሱም የተኰነነው ሰው ማመን ያለበትን የትምህርት ዓይነት የሚገልጽ ነው፤ ይኸውም ክርስቶስ ኃጢአትን በሙሉ እንዳስተሰረየና ዋጋውንም እንደ ከፈለ እንዲሁም ያለ አንዳች ሰብአዊ ሥራ «በእግዚአብሔር ፊት የሚጠቀመውን ጽድቅ»*[40] *እና የዘላለም ሕይወት የሆነውን የኃጢአት ይቅርታን ለሰዎች እንዳስገኘ የሚገልጽ አስተምህሮ ነው።*

6 5. *የውዝግቡ መንስኤ የነበረ ቢሆንም፣ «ወንጌል» የሚለው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በአንድ ዓይነት ስሜት ብቻ የተነገረ አይደለም። ስለዚህ፣ «ወንጌል» የሚለው ቃል ክርስቶስ በማስተማር አገልግሎቱ እንዳወጀው እንዲሁም ሐዋርያቱ በተመሳሳይ መልኩ እንዳደረጉት* (*በማርቆስ* 1[፡15]፤ *የሐዋርያት ሥራ* 20[፡24] *ቃሉ መላውን የክርስቶስ ትምህርት ለማመልከት ጥቅም ላይ ሲውል ያኔ ወንጌሉ የንስሐና የኃጢአት ይቅርታ አዋጅ ነው ብሎ መናገር ወይም መጻፍ ትክክል እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።*

7 6. *ይሁን እንጂ፡- ሙሴ የሕግ መምህር፣ ክርስቶስ ደግሞ የወንጌል መምህር እንደ ሆነ ተደርጎ እንደሚነገረው፣ ሕግና ወንጌል አንዱ ከሌላው ጋር በተቃርኖ በሚቀመጡበት ጊዜ፣ እኛ ወንጌሉ የንስሐ ወይም የፍርድ አዋጅ እንዳልሆነ፣ ይልቁኑ፣ በትክክል ለመናገር፣ የመጽናናትና የደስታ መልእክት እንጂ የሚገሥጽ ወይም የሚያስፈራራ ሳይሆን፣ ከሕጉ ፍርሃት ሕሊናን የሚያጽናና፣ ወደ ክርስቶስ ትሩፋት ብቻ የሚያመለክትና በክርስቶስ መልካም ሥራ በተገኘው የእግዚአብሔር ጸጋና ሞገስ አስደሳች አዋጅ አማካይነት በሕግ ፍርሃት የተያዙትን ሕሊናዎች እንደገና የሚያነሣቸው እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።*

8 7. *የኃጢአትን መገለጥ በተመለከተ፡- ሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ምንም ሳይሰሙ የሕጉን ስብከት ብቻ እስከ ሰሙ ድረስ የሙሴ መጋረጃ* (2*ቆሮ* 3፡13-16) *በሕዝቡ ሁሉ ፊት ይሰቀል*

---

[38] በዚህ ክርክር የተሳፉትን ወገኖች በተመለከተ ከታች SD V, 581-82 ቍጥር 154-155 ተመልከት።

[39] ሉተር በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስና በጎዳጉ ማስታወሻ «በትክክል የሚገልጸው» የተሰኘው አነጋገር ሕግንና ወንጌልን «በትክክል የሚለየው» በሚል የተተረጐመበትን 2ጢሞቴዎስ 2፡15ን ተመልከት።

[40] ሉተር በተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ሮሜ 1፡17።

ነበር፤ ስለሆነም የኃጢአታቸውን እውነተኛ ባሕርይ ከሕጉ መገንዘብን ጨርሶ አይማሩም፡፡ በዚህ ፈንታ እንደ ፈሪሳውያን ራሳቸውን የሚያታልሉ ግብዞች፣ ወይም እንደ ይሁዳ ተስፋ የሚቈርጡ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ሕጉን ራሱ ወሰደና በመንፈሳዊ ሁኔታ ተረጐመው (ማቴ 5[፡21-48]፤ ሮሜ 7[፡14])፤ ስለሆነም በኃጢአተኞች ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ [ሮሜ 1፡18] ከሰማይ ይገለጣል፤ ሰዎችም ሕጉ ምን ያህል አስፈሪ መሆኑን ይማራሉ፡፡ በዚህ መገለጥ አማካይነት ወደ ሕጉ እንዲመለከቱ ይደረጋሉ፤ በዚያን ጊዜ ብቻ በሕጉ አማካይነት የኃጢአታቸውን ገጽታ ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል ሊገነዘቡ ይችላሉ፡፡ ሙሴ ይህን ግንዛቤ ከእነርሱ ጠምዝዞ ሊያወጣ ፈጽሞ ባልቻለ ነበር፡፡

9 ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ የክርስቶስ ሥቃይና ሞት አዋጅ የሚያስተክዝና የሚያስፈራ አዋጅ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቊጣ ምስክር መሆኑ እውነት ነው፤ በዚህም አማካይነት የሙሴ መጋረጃ ከእነርሱ ፊት ከተነሣ በኋላ ሰዎች (እኛ ልንፈጽመው የማንችለውን) በሕጉ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠይቀው ምን ያህል ከባድ ነገር እንደሆነ በማወቅ እኛ ጽድቃችንን ሁሉ መፈለግ ያለብን በክርስቶስ እንደ ሆነ በእውነት ይገነዘቡ ዘንድ አሁን በእውነት ወደ ሕጉ ይወሰዳሉ፡፡

10 8. የሆነ ሆኖ፣ ይህ ሁሉ (ማለትም የክርስቶስ ሥቃይና ሞት) የእግዚአብሔርን ቊጣ የሚያውጅና ሰዎችን የሚያሸብር እስከ ሆነ ድረስ፣ በትክክለኛው አነጋገር፣ የወንጌል ስብከት ሳይሆን፣ የሙሴና የሕግ ስብከት ነው፤ ስለሆነም የክርስቶስ ተገቢ ወይም ትክክለኛ ሥራ ከሚገለጽበት ከጸጋ፣ ከማጽናናትና ሕያው ከማድረግ ስብከት ውጪ የሆነ ባዕዳዊ ሥራ ነው፡፡ ይህም በትክክለኛው አነጋገር የወንጌል ስብከት ነው፡፡

*አሉታዊ ዐሳብ*

*መወገዝ የሚገባው ተቃራኒ ትምህርት*

11 1. በዚህም መሠረት ወንጌሉ፣ በትክክለኛው አነጋገር የንስሐ ወይም የቅጣት አዋጅ ነው እንጂ ሙሉ በሙሉ የጸጋ አዋጅ አይደለም የሚለው ትምህርት የተሳሳተና ጐጂ እንደ ሆነ እንቈጥራለን፤ እንቃወመዋለንም፡፡ ምክንያቱም በዚህ መንገድ ወንጌሉ እንደገና ተመልሶ የሕግ ትምህርት ይደረጋል፤ የክርስቶስ ትሩፋትና ቅዱሳት መጻሕፍት ይደበዝዛሉ፤ ክርስቲያኖችም እውነተኛውን መጽናናት ያጣሉ፤ እንዲሁም ለጵጵስናው ስህተት እንደገና በሩ ይከፈትለታል፡፡[41]

## VI. (6)
## ስለ ሕጉ ሦስተኛ ጥቅም

### *የውዝግቡ ሁኔታ*
### *ይህን ውዝግብ በሚመለከት ዋናው ጥያቄ*[42]

1 ሕጉ ለሰዎች የተሰጠው ለሦስት ምክንያቶች ነው፤ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ልቅ የሆኑና የማይታዘዙትን ሰዎች በመቃወም በእርሱ አማካይነት ውጪአዊ ሥነ ሥርዓት እንዲጠበቅ ለማድረግ ነው፤ ሁለተኛ፣ በእርሱ አማካይነት ሰዎች ኃጢአታቸውን ወደ መገንዘብ እንዲመጡ ነው፤ ሦስተኛ፣ ዳግም ከተወለዱ በኋላ (ሥጋ ከእነርሱ ጋር ገና ተጣብቆ ስላለ) በእርሱ መሠረት መላ ሕይወታቸውን ያስተካክሉበትና ይመሩበት ዘንድ ከሥጋቸው የተነሣ ትክክለኛ መመሪያ እንዲኖራቸው ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሦስተኛውን የሕግ ጥቅም በሚመለከት በጥቂት የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል ክርክር ተነሣ፡፡

---
[41] ከታች SD V, 586 ተመልከት፡፡
[42] በዚህ ክርክር የተሳተፉትን ወገኖች በተመለከተ ከታች SD VI, 587 nn. 165-166 ተመልከት፡፡

እርሱም ሕጉ ዳግም በተወለዱት ክርስቲያኖች ላይ መጫን አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ክርክር የሚመለከት ነበር። አንደኛው ወገን አዎን ሲል ሌላኛው ወገን አይደለም አለ።

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

*ይህንን ውዝግብ በሚመለከት ትክክለኛው የክርስትና ትምህርት*

2 1. በእውነት በክርስቶስ ያመኑትና በትክክል ወደ እግዚአብሔር የተመለሱት ሰዎች ምንም እንኳ ከሕጉ እርግማንና አስገዳጅነት በክርስቶስ አርነት ያገኙና ነጻ የወጡ ቢሆኑም እነርሱ በዚህ ምክንያት ያለ ሕግ እንዳይደሉ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፤ ይልቁንም እነርሱ በእግዚአብሔር ልጅ የተዋጁት ሕጉን ቀንና ሌሊት እንዲፈጽሙ ነው (መዝ 119፡1)። የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በእግዚአብሔር አምሳል[43] በተፈጠሩ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕግ በልባቸው ተጽፎ ስለ ነበር እነርሱ ከውድቀት በፊት እንኳ ቢሆን ያለ ሕግ አልኖሩም።

3 2. እኛ የሕጉ አዋጅ በትጋት መነገር ያለበት በማያምኑትና ንስሐ በማይገቡት ሰዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ በሚያምኑትና በእውነት በተለወጡት፣ ዳግም በተወለዱትና በእምነት በጸደቁት ዘንድም ጭምር እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።

4 3. ምክንያቱም እነርሱ ምንም እንኳ ዳግመኛ የተወለዱና «በአእምሮአቸው በመንፈስ የታደሱ» [ኤፌ 4፡23] ቢሆኑም፣ ይህ ዳግመኛ መወለድና መታደስ በዚህ ዓለም ፍጹም አይደለም። ይልቁንም እርሱ ጅማሬ ብቻ ነው። አማኞችም በአእምሮአቸው መንፈስ ከሥጋቸው ጋር፣ ማለትም እስከ ዕለተ ሞት ድረስ ከእነርሱ ጋር ከተጣበቀውና ከተበላሸው ባሕርይና ጠባይ፣ እንዲሁም በአሮጌው ተፈጥሮ ምክንያት ገና በሰው ዐስተሳሰብ፣ ፈቃድና በማንኛቸውም ሰብዓዊ ኃይላት ተጠልሎ ከሚገኘው ነገር ጋር በማያቋርጥ ጦርነት ተጠምደው ይኖራሉ። ሰዎች በራሳቸው የተሩነት ዐስተሳሰብ ላይ ተመሥርተው እነርሱ እንደ ፈለጉ በዘፈቀደ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለማበርከት ቁርጠኛ እንዳይሆኑ የእግዚአብሔር ሕግ ባለማቋረጥ መንገዳቸውን እንዲያበራላቸው ያስፈልጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አሮጌው ተፈጥሮ በገዛ ራሱ ፈቃድ መሠረት እንዳይንቀሳቀስ ዳሩ ግን በሕጉ ወቀሳና ማስፈራራት ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም በቅጣትና በመቅሠፍት ጭምር ፈቃዱን በመቃረን ለመሥራት እንዲገደድ፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን በመከተል ራሱን ለምርኮ እንዲሰጥ ሕጉ አስፈላጊ ነው (1ቆሮ 9[፡27]፤ ሮሜ 6[፡12]፤ ገላ 6[፡14]፤ መዝ 119[፡1]፤ ዕብ 13[፡21])።[44]

5 4. የሕጉን ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬዎችን ልዩነት በሚመለከት ሰዎችም ሕግን የሚፈጽሙት በቅጣትና በእግዚአብሔር ቀጥታ ማስፈራሪያነት ተጽእኖ በመገደድ እስከ ሆነ ድረስ በሕጉ መሠረት የሚፈጸሙ ተግባሮች የሕግ ሥራዎች ሆነው እንደሚቀሩና በዚህ ስም መጠራት እንዳለባቸው እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም።

6 5. ይሁን እንጂ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በአማኞች ውስጥ በሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ በተወለዱት የሚያስገኛቸው ሥራዎች ናቸው፤ እነርሱም አማኞች (ዳግመኛ በመወለዳቸው) ምንም ዓይነት ትእዛዝ፣ ማስፈራሪያ ወይም ሽልማት የማያውቁ ያህል የሚፈጽሙአቸው ናቸው። በዚህም ሁኔታ የእግዚአብሔር ልጆች ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቶቹ የክርስቶስ ሕግና የአእምሮ ሕግ ብሎ በሚጠራው በሕጉ የሚኖሩና በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት የሚመላለሱ ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ እነርሱ «ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደሉም» (ሮሜ 7[፡23] እና 8[፡1፣14])።

7 6. ስለዚህ ንስሐ ለሚገባውና ንስሐ ለማይገባው፣ ዳግመኛ ለተወለደውና ላልተወለደው ሕጉ አንድ ብቸኛ ሕግ፣ ሊለወጥ የማይችል የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ይኖራል። ለእርሱ መታዘዝን በተመለከተ ዳግመኛ ያልተወለዱት ሰዎች ሕጉ የሚጠይቀውን የሚፈጽሙት ያለ

---

[43] ዘፍጥረት 1፡26።

[44] በዚህ የስምምነቱ ጸሐፊዎች ተግባራዊ በሆነ የሕግና የወንጌል አጠቃቀም ላይ በሰበካ ደረጃ ምን ያህል ተጋድሎ እንዳደረጉ ግልጽ ነው።

*ፈቃዳቸው በመገደድ ስለ ሆነ ልዩነት አለ (ዳግም የተወለዱትም ቢሆኑ በሥጋቸው አንጻር ሕጉን የሚፈጽሙት በዚሁ ዓይነት ነው)፡፡ ይሁን እንጂ፣ አማኞች አዲስ የተወለዱ ከሆነ ምንም ዓይነት የሕግ ማስፈራሪያ ሊያስገድዳቸው እስከማይችል ድረስ ያለ አንዳች ተጽእኖ በፈቃደኝነት መንፈስ ይፈጽሙታል፡፡*

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*ሐሰተኛና ተቃራኒ ትምህርት*

8 1. *ስለዚህ ሕጉ እላይ በተገለጸው መሠረትና ደረጃ ሊሰበክ የሚገባው በማያምኑት፣ ክርስቲያኖች ባልሆኑትና ንስሐ በማይገቡት ሰዎች መካከል እንጂ በክርስቲያኖችና በእውነት በክርስቶስ ባመኑት መካከል አይደለም የሚለው ትምህርት የክርስትና ሥነ ሥርዓትንና እውነተኛ በጎነትን የሚጐዳ ተቃራኒ ትምህርትና ስሕተት አድርገን እንቃወመዋለን፡፡*

## VII. (7)
## *ስለ ክርስቶስ ቅዱስ እራት*

1 *የዝዊንግሊያውያንን አስተምህሮ የሚያስተምሩት ሰዎች የኦግስቡርግ የሃይማኖት መግለጫ በቀረበበት ጊዜ ወዲያውኑ ከዚህ መግለጫ ራሳቸውን ያገለሉ በመሆናቸው ከመግለጫው ሊቃውንት መካከል ሊቈጠሩ አይችሉም፡፡ ቢሆንም እነርሱ ራሳቸውን በስውር በማስገባት በዚህ የክርስትና እምነት መግለጫ ስም ስሕተታቸውን ስለሚያስፋፉ ይህንን ውዝግብ አስመልክቶ መግለጫ ለማቅረብ እንፈልጋለን፡፡*[45]

### *የውዝግቡ ሁኔታ*

### *በዚህ አንቀጽ በእኛ አስተምህሮና በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት በሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች (ሳክራሜንታሪያንስ) አስተምህሮ መካከል ያለው ዋና ጉዳይ፡፡*

2 *የሚገባቸው ሆኑ ወይም የማይገባቸው፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅኖች የሆኑ ወይም ያልሆኑ፣ አማኞች የሆኑ ወይም ያልሆኑ፣ ለአማኞች መጽናናትንና ሕይወትን ለማምጣት፣ እንዲሁም በማያምኑ ሰዎች ላይ ፍርድን ለማምጣት፣ በቅዱስ እራት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም በእውነትና በመሠረታዊ ባሕርያቸው ይገኛሉ፤ በኅብስቱና በወይኑ ይታደላሉ፤ ደግሞም ራሳቸውን ለቅዱስ ምሥጢሩ ባቀረቡ ሰዎች ሁሉ አፍ ይወሰዳሉ፡*

3 *በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ይህንን አይደለም ይላሉ፤ እኛ ደግሞ አዎን፣ እንላለን፡፡*

*ይህን ውዝግብ ለማብራራት ከሁሉ አስቀድሞ በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ ሁለት ዓይነት የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች እንዳሉ መገንዘብ ይገባል፡፡ የመጀመሪያዎቹ በልባቸው የሚያምኑትን በግልጽ ቋንቋ የሚናገሩ ብልጣብልጥ ያልሆኑ በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ናቸው፡- ይኸውም በቅዱስ እራቱ ከኅብስትና ከወይን በስተቀር ምንም ነገር እንደሌለ፣ ከዚህ የበለጠ ምንም ነገር እንደማይታደልና በአፍ*

---

[45] *ይህ አንቀጽ ምንም እንኳ በ«ሉተራውያን» መካከል ነገሥታትን በመምረጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባለ ቡድን በ*"Crypto - Philippist" *ላይ ያተኰረ ቢሆንም፣ የስምምነቱ ጽሑፍ አርቃቂዎች የ*"Crypto - Philippist" *ጽሑፎችን፣ የኡልሪክ ዝውንግሊንና የዙሪኩን ሄንሪክ ቡሊንገርን፣ የዮሐንስ ካልቪንን፣ የጄኔቫውን ቴዎዶር ቤዛንና በሄድልበርግ ፓላቲኔት በነበረው በተመራጩ ፍሬዴሪክ* III*ኛ ቤተ መንግሥት የነበሩትን «ካልቪኒስቶች» ወይም የተሐድሶ ምሁራንን በማውገዝ የተቀነባበረ መቃወሚያ አቀረቡ፡፡ በዚህ ክርክር የተሳተፉትን ቡድኖች ለማወቅ፣* SD VII, 592 n. 172 *ከታች ተመልከት፡፡*

4 እንደማይወሰድ የሚገልጹ ናቸው::[46] ሌሎች ደግሞ በከፊል የእኛን ቋንቋ የሚጠቀሙና እውነተኛው፣ ሕያው የሆነው የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ በመሠረታዊ ባሕርዩ በቅዱስ እራት በእውነት መገኘቱን እንደሚያምኑ የሚያስመስሉ፣ ነገር ግን ይህ እውን የሚሆነው በመንፈሳዊ ሁኔታ በእምነት አማካይነት ነው የሚሉ እጅግ አደገኛ የሆኑ ብልጣብልጥ በቅዱስ ቁርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች[47] ናቸው:: በዚህ ዓይነት አሳማኝ በሆኑ ቃላት ሽፋን በማታለል ከኅብስቱና ከወይኑ ሌላ የሚቀርብና በአፍ የሚወሰድ ነገር የለም የሚሉትን የመጀመሪያዎቹን ብልጣብልጥ ያልሆኑትን በቅዱስ ቁርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ዐሳብ ይዘው ይገኛሉ::

5 ለእነርሱ «በመንፈሳዊ ሁኔታ» ማለት የሚገኘው «የክርስቶስ መንፈስ» ወይም «በዚያ የማይገኘው የክርስቶስ ሥጋ ኃይልና የእርሱ ትርፋቱ» ነው ከማለት ሌላ ምንም አይደለም:: በዚህ ዐስተሳሰብ መሠረት ግን የክርስቶስ ሥጋ በየትኛውም መንገድ ወይም ዓይነት አይገኝም፣ ነገር ግን እርሱ የሚገኘው ከፍ ባለው ሰማየ ሰማያት ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ፣ እኛም በእምነታችን ዐሳብ አማካይነት ወደዚህ አካል ወደ ሰማይ ራሳችንን እናነሣለን:: ሥጋውንና ደሙን በዚያ መፈለግ ይገባናል እንጂ፣ በእራቱ ኅብስትና ወይን አማካይነት ከቶ አይደለም::

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

ቅዱስ እራትን በተመለከተ በቅዱስ ቁርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን የሚቃወም የንጹሕ አስተምህሮ መግለጫ[48]

6 1. በቅዱስ እራት የክርስቶስ ሥጋና ደም በእውነትና በመሠረታዊ ባሕርያቸው እንደሚገኙ፣ በኅብስቱና በወይኑ አብረው በእውነት እንደሚታደሉና እንደሚወሰዱ፣ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም::

7 2. የክርስቶስን የኪዳን ቃሎች በቀጥታ ቃል በቃል ከሚናገሩት ውጪ በሌላ መንገድ መረዳት አይገባም፤ ማለትም ኅብስቱ በዚያ ያልተገኘውን የክርስቶስን ሥጋ ወይኑ በዚያ ያልተገኘውን የክርስቶስን ደም የሚያመለክቱ ሳይሆን በምሥጢረ ውሕደት ምክንያት በእውነት እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ መሆናቸውን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም::

8 3. ቅዱስ እራት የሚባረክበት ቅዳሴን በተመለከተ የክርስቶስን ሥጋና ደም መገኘት የሚያመጣው የሰው ጥረት ወይም የአገልጋዩ ቃሉን መናገር ሳይሆን፣ ነገር ግን ብቸኛ በሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ ሥልጣን እንደ ሆነ እናምናለን፣ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም::

9 4. በተጨማሪም፣ በቅዱስ እራት አገልግሎት የክርስቶስ የምሥረታው ቃል በምንም ሁኔታ ሊተው እንደማይችል፣ ነገር ግን «የምንባርከው የበረከት ጽዋ ...» ተብሎ እንደ ተጻፈ (1ቆሮ 10:16) በግልጽ ሊነገር ይገባል፣ በማለት እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ በአንድ ልብ አጽንተን እንይዛለንም:: ይህ ጽዋውን መባረክ እውን የሚሆነው የክርስቶስን ቃሎች በመናገር ነው::

10 5. በዚህ ጉዳይ ላይ በቅዱስ ቁርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ተቃራኒ አቋም የመያዛችን ምክንያት ዶ/ር ሉተር

---

[46] የጄኔቫ፣ ዙሪክ፣ ሄይደልበርግ እና የሌሎችም የታደሰ ትምህርት ማዕከሎች የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ማጣቀሻ::

[47] The "Crypto - Philippist"

[48] በእነዚህ አዎንታዊ አሳቦች የስምምነቱ አዘጋጆች የጌታን እራት በሚመለከት የሉተርን አስተምህሮ ማጠቃለያቸውን አብራርተዋል:: SD VII, 598 ቁጥሮች 191-193፣ 600፣ 197፣ 609-11፣ ቁጥሮች 216-220 ተመልከት:: እነዚህ አሳቦች ከምሥጢሩ ክፍሎች ጋር እውነተኛ ምሥጢራዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም መገኘትን፣ በአፍ መቀበልን (*ማንዱካቲዮ ኦራሊስ*) (*manducatio oralis*)፣ እንዲሁም በተመሳሳይ የማያምኑና የሚያምኑ የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበልን (*ማንዱካቲዮ አምፒዮረም ወይም ኢንዲግምረም*) (*manducatio impiorum* or *indignorum*) ያጐላሉ:: በሉተራን የመጨረሻው ነጥብ የሚያርፈው፣ በክርስቶስ ክብር የሚታዘዝና የሚሰጠው ተስፋ፣ በአማኙ እምነት ሳይሆን በቅዱስ ቁርባን ሥነ ሥርዓት በሚነገረው ቃሉ የክርስቶስ ሥጋና ደም ይቀርባሉ::

በጻፈው *ታላቁ የእምነት መግለጫ* እንዳስቀመጠው፡- «የመጀመሪያው (ይህን አቋም የመያዙ
11 ምክንያት) ይህ የእምነታችን አንቀጽ፡- ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ በማይከፋፈልና በማይለያይ
12 በአንድ አካል እውነተኛ፣ በባሕርዩ፣ በተፈጥሮው፣ ሙሉ አምላክና ሰው መሆኑ ነው፤ ሁለተኛው
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡» ክርስቶስ በትክክልና በእውነት
በሰብዓዊነቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ፣ በሰማይና በምድር ሁሉን ነገር በእጁና
ከእግሮቹ በታች አድርጎ ይገዛል፡፡ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠና በዚህ መሠረት እነዚህን
ነገሮች ማድረግ የሚችል ሌላ ሰብዓዊ ፍጡር ወይም መልአክ ሳይሆን የማርያም ልጅ ብቻ
13-14 ነው፡፡ «ሦስተኛው የእግዚአብሔር ቃል ሐሰት ወይም የሚያሳስት አለመሆኑ ነው፡፡ አራተኛው
እግዚአብሔር ራሱ በአንድ ስፍራ የሚገኝባቸው የተለያዩ መንገዶች ያሉትና እነርሱንም
የሚያውቅ እንጂ ፈላስፋዎች «በአካባቢ» ወይም «በስፍራ» ብለው እንደሚጠሩት አንድ (ስፍራ
ወይም መንገድ) ብቻ አይደለም...፡፡[49]

15 6. የክርስቶስ *ሥጋና ደም* የሚወሰደው በእምነት በኩል በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በኅብስቱና ከወይኑ ጋር በአፍ፣ በኅብስቱና በወይኑ ቅዱስ ምሥጢራዊ ውሕደት ምክንያት አካላዊ አመጋገብ ባይሆንም በልዕለ ተፈጥሮአዊና በሰማያዊ መንገድ እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፡፡[50] ክርስቶስ «ውሰዱና ብሉ፣ ጠጡ» በሚልበት ጊዜ የክርስቶስ ቃላት በግልጽ ይህን ያሳያሉ፣ እንዲሁም ሐዋርያት ይህን አድርገዋል፡፡ ምክንያቱም «ሁሉም ከእርሱ ጠጡ» ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው (ማር 14[፡23])፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣ «የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ *ሥጋ* ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?» [1ቆሮ 10፡16]፡፡ ይኸውም ይህን እንጀራ የሚበላ የክርስቶስን *ሥጋ* ይበላል ማለት ነው፡፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና መምህራን ክሪሶስቶም፣ ሲፕሪያን፣ ሌዎ ቀዳማዊ፣ ጎርጎርዮስ፣ አምብሮዝ፣ አውግስጢኖስና ሌሎችም በአንድነት ስለዚህ ሁኔታ ይመሰክራሉ፡፡[51]

16 7. የሚያምኑና የሚገባቸው ብቻ ሳይሆኑ የማይገባቸውና የማያምኑ ጭምር እውነተኛውን የክርስቶስን *ሥጋና* ደም እንደሚቀበሉ፣ ዳሩ ግን የማይገባቸውና የማያምኑት ካልተመለሱና ንስሐ ካልገቡ በስተቀር እነርሱ የሚቀበሉት ሕይወትንና መጽናናትን ለማግኘት ሳይሆን ለፍርድና ለኵነኔ መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፡፡

17 ምክንያቱም እነርሱ ክርስቶስን እንደ አዳኝ ባይቀበሉትም፣ ከልባቸው በእውነት ለሚያምኑትና ለሚገባቸው ታዳሚዎች ሕይወትንና መጽናናትን እንደሚያጎናጽፋቸው ሁሉ ንስሐ በማይገቡት ታዳሚዎች ላይ ፍርድን ለመፈጸም እንደሚገኝም እንደ ጨካኝ ፈራጅ ሳይወዱ ሊቀበሉት ይገደዳሉ፡፡

18 8. የማይገባቸው ታዳሚዎች አንድ ዓይነት ብቻ ሲሆኑ እነርሱም የማያምኑት እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፡፡[52] ስለ እነርሱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፣ «በማያምን ግን ... አሁን ተፈርዶበታል» [ዮሐ 3፡18]፡፡ ሳይገባ ቅዱስ ምሥጢሩን መቀበል ይህንን ኵነኔ ይጨምራል፤ ያጐላል፤ ያባብሳልም (1ቆሮ [11፡27፣29])፡፡

19 9. ምን ያህልም ደካሞች ቢሆኑ እውነተኛ አማኞች ሕያው እምነትን እስከያዙ ድረስ ቅዱስ እራቱን ለኵነኔ እንደማይቀበሉ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ እራቱን የመሠረተው፣ በተለይ በእምነት ደካማ የሆኑትን ዳሩ ግን ንስሐ የሚገቡትን ክርስቲያኖች ለማጽናናትና ደካማ የሆነውን እምነታቸውን ለማበርታት ነው፡፡

---

[49] *Confession Concerning Christ's Supper* (1528) (WA 26:326, 29-327, 20; LW 37:214). ሉተር ከማንኛውም ነገር ጋር ለማይገናኝ ለተወሰነና ለተረጋገጠ ነገር አንድ ሁኔታ የሚፈጸምበትን ስፍራ የሚያመለክተውን ሎኬል (*locale*) የተባለውን የላቲን ቃል ይጠቀማል፡፡

[50] በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች የቅፍርናሆም ሰዎች የክርስቶስን ቃሎች በውን እንደሚቀበሉ (ዮሐ 6፡58) አድርገው እንደ ተረጎሙት በመጥቀስ ይከስሱአቸዋል፣ ስለዚህ የሉተራን መሠረተ እምነት ቈራቢዎች «የክርስቶስን ሥጋ በጥርሳቸው እየነጩ እንደ ማንኛውም ሌላ ምግብ በሆዳቸው እንዲዋሐድ ያደርጉታል» ማለት ነው፡፡ አንዳንዶች እንዲያውም የሉተራን አስተምህሮ የሰውን ሥጋ እንደ መብላት ነው በማለት አውግዘውታል፡፡

[51] ማጣቀሻዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል SD VII, 603-4 ቊጥር 200 እና 605 ቊጥር 203፡፡

[52] ማርቲን ቡሰር «የማይገቡ» አማኞችን (ኢንዲግኒ) «ቅን ካልሆኑ» (ኢምፒ) ለይቶአቸዋል፡፡ እዚህ ላይ የስምምነቱ አዘጋጆች ያንን ልዩነት ይቃወማሉ፡፡

20 10. በሰማያዊው ማዕድ ዙሪያ ያሉት ታዳሚዎች አጠቃላይ ተገቢነት የሚያገኙት በክርስቶስ ከፍተኛ ቅዱስ መታዘዝና ፍጹም በሆነ ትሩፋቱ እንደ ሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እናስታውቃለንም። የእርሱንም ቅዱስ መታዘዝና ፍጹም ትሩፋት በእውነተኛ እምነት የራሳችን የምናደርገው ሲሆን ዋስትናው የሚረጋገጥልን ደግሞ በቅዱስ ምስጢሩ ነው። ተገቢነት የሚገኘው በምንም ዓይነት በራሳችን በጎ ምግባር፣ ወይም በውስጣዊ ወይም በውጫአዊ ዝግጅት አይደለም።

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ተቃራኒ፣ የተወገዘ አስተምህሮ*

21 በሌላ በኩል፣ እላይ የቀረበውን አስተምህሮና የክርስቶስን እራት አስመልክቶ ያለንን እምነትና መግለጫ የሚቃወሙና የሚቃረኑትን፣ የሚከተሉትን የተሳሳቱ አንቀጾችን ሁሉ በአንድ ድምፅ እንቃወማለን፤ እንኮንናለንም።

22 1. ጳጳሳዊ የኅብስትና የወይን ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም መለወጥ transubstantiation (ትራንሰብስታንሺዬሽን) አስመልክቶ በጳጳሱ ሥርዓት ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ በቅዱስ እራት ኅብስትና ወይን መሠረታዊ ነገራቸው ወይም የተፈጥሮ ይዘታቸው ጠፍቶ ወደ ክርስቶስ ሥጋነት ተለውጠው ውጫአዊው ቅርጻቸው ብቻ እስከሚቀር ድረስ ሕልውናቸውን ያጣሉ የሚለውን።[53]

23 2. ለሕያዋንና ለሙታን ኃጢአት የሚደረግ የቅዱስ ቊርባን ጳጳሳዊ መሥዋዕትን።[54]

24 3. ግልጽ ከሆነው ከክርስቶስ ቃል ኪዳን በተቃራኒው ያልቀሰሱ ምእመናን ከቅዱስ ምሥጢሩ አንዱን ነገር ብቻ የሚሰጡበትና ጽዋው ከእነርሱ ተከልክሎና የክርስቶስን ደም የሚያጡበትን።[55]

25 4. የክርስቶስ የኪዳኑን ቃላት በቀላሉ እንደሚናገሩት መረዳት ወይም መታመን እንደማይኖርባቸው ነገር ግን ግልጽ ያልሆኑ አገላለጽ ስለ ሆኑ ትርጒማቸው ከሌሎች ምንባቦች መፈለግ አለበት የሚለውን ትምህርት።[56]

26 5. የክርስቶስ ሥጋ በቅዱስ ምሥጢር ከኅብስት ጋር በአፍ አይወሰድም፤ ነገር ግን ኅብስቱና ወይኑ ብቻ በአፍ ይወሰዳሉ፤ ይሁን እንጂ፣ የክርስቶስ ሥጋ የሚወሰደው በመንፈሳዊ ሁኔታ፣ በእምነት ብቻ ነው የሚለውን።

27 6. ኅብስቱና ወይኑ በቅዱስ እራት፣ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው የሚተዋወቁበት የመለያ ምልክት ከመሆን ያለፈ ነገር አይደለም የሚለውን፣

28 7. ኅብስቱና ወይኑ እጅግ የራቀውን የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚወክሉ፣ ምሳሌዎችና ምልክቶች ብቻ ናቸው የሚለውን፣

29 8. ኅብስቱና ወይኑ ከመታሰቢያነት፣ ከማኅተምነት ወይም ዋስትና ከመሆን ያለፉ ነገሮች አይደሉም፣ በጌታ እራት በእውነት ኅብስቱን ስንበላና ወይኑን ስንጠጣ እምነታችን ወደ ሰማይ በማድረግ በክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሚካፈል ለእኛ ለማረጋገጥ የሚሰጡ ናቸው የሚለውን።

30 9. በቅዱስ እራት የእምነታችን ማረጋገጫና ማጽኛ የሚሆነው በኅብስቱና በወይኑ ውጫአዊ ምልክቶች ብቻ እንጂ፣ የክርስቶስ ሥጋና ደም እዚያ በመገኘታቸው አይደለም የሚለውን።

---

[53] የትሬንት ጉባኤ፣ ክፍል 13፣ ምዕራፍ 4፣ 5፣ ቀኖናዎች 2፣ 4፣ 6።

[54] የትሬንት ጉባኤ፣ ክፍል 22፣ ምዕራፍ 2፣ ቀኖና 3።

[55] የትሬንት ጉባኤ፣ ክፍል 21፣ ምዕራፍ 1፣ ቀኖና 1-3።

[56] አንቀጽ 25-37 የዝውንግላዊ፣ የካልቪናዊ ወይም «የስውር ፊሊጶሳዊ» የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን አመለካከት ይወክላሉ። ከዚህ በታች ማጣቀሻዎችን በSD VII, 612-15, ቊጥሮች 227-240 ተመልከት።

31 10. በቅዱስ እራት የሚታደለው በዚያ የማይገኘው የክርስቶስ የሥጋና ደም ኃይል ውጤት ወይም ትሩፋት ብቻ ነው የሚለውን።

32 11. የክርስቶስ ሥጋ በሰማይ የተገደበ ስለ ሆነ በምድር ቅዱስ እራቱ በሚዘጋጅበት ጊዜ በአንድ ጊዜ በብዙ ወይም በሁሉም ስፍራ ሊገኝ የሚችልበት ምንም መንገድ የለም የሚለውን።

33 12. የለበሰው ሰብአዊ ተፈጥሮና ባሕርይ ይህን ስለማይፈቅድ በመሠረቱ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ በቅዱስ እራት የመገኘታቸውን ጉዳይ ተስፋ ሊሰጥ አይችልም፤ ወይም ያ እንዲሆን ሊያደርግ አይችልም የሚለውን።

34 13. እግዚአብሔር በአጠቃላይ ሁሉን ቻይነቱ መሠረት እንኳ ቢሆን ሥጋው በመሠረተ ባሕርዩ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆነ ስፍራ እንዲገኝ ሊያደርግ አይችልም የሚለውን።

35 14. በቅዱስ እራቱ የክርስቶስን ሥጋና ደም መኖር የሚያስገኘውና የሚፈጥረው ሁሉን ቻይ የሆነው የክርስቶስ ኪዳን ቃል ሳይሆን እምነት ነው የሚለውን።

36 15. አማኞች በቅዱስ እራት በኅብስቱና በወይኑ የክርስቶስን ሥጋና ደም መፈለግ የለባቸውም፤ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ዓይናቸውን ከኅብስቱ ወደ ሰማይ አንሥተው የክርስቶስን ሥጋ እዚያ መመልከት አለባቸው የሚለውን።

37 16. የማያምኑና ንስሐ የማይገቡ ክርስቲያኖች በቅዱስ እራት ኅብስቱንና ወይኑን ብቻ እንጂ እውነተኛውን የክርስቶስን ሥጋና ደም አይቀበሉም የሚለውን።

38 17. በዚህ ሰማያዊ ማዕድ ታዳሚዎቹ የተገባቸው መሆን በክርስቶስ ላይ ባለ እውነተኛ እምነት ብቻ ሳይሆን፣ በእርግጥ የሰዎችንም ውጫአዊ ዝግጅት የሚያካትት ነው የሚለውን።[57]

39 18. በእውነት የሚያምኑ፣ በክርስቶስ እውነተኛ፣ ሕያው፣ ንጹሕ እምነት ያላቸውና የያዙት ሰዎች በውጫአዊ አኗኗራቸው ገና ፍጹማን ስላልሆኑ ብቻ ይህንን ቅዱስ ምሥጢር ለፍርዳቸው ሊቀበሉ ይችላሉ የሚለውን።

40 19. በቅዱስ ምሥጢሩ ውጫአዊና የሚታዩ ነገሮች ኅብስቱና ወይኑ መከበር ይገባቸዋል የሚለውን።

41 20. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ለመልካም ሥነ ሥርዓት ስንል የማንናገረውን በቅዱስ ቍርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ባልበሰለ መልኩ፣ በሥጋዊነት፣ በፈንጠዝያነት፣ በጥላቻ ሁኔታ፣ እግዚአብሔርን በመሳደብ እንዲሁም እጅግ በሚያስቀይም ሁኔታ የዚህን ምሥጢር ልዕለ ተፈጥሮአዊና ሰማያዊ ምሥጢሮችን በተመለከተ የሚናገሩትን፣ አሳፋሪ የሆነውን፣ የሚያላግጥ፣ ስድብ የተሞላባቸውን ጥያቄዎችንና አገላለጾችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተገቢ ፍርድ እንተዋለን።

42 21. በዚህም የክርስቶስ ሥጋ በፈንጠዝያነት Capernaitic (ካፔርኒያቲካዊነት) መብላትንም ሙሉ በሙሉ እንቃወማለን። ሥጋው በጥርስ ታኝኮ እንደ ማንኛውም ምግብ በሆድ ውስጥ ይፈጫል የሚል ዐሳብ ይሰጣል። በቅዱስ ቍርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች የገዛ ሕሊናቸውን ምስክርነት በሚቃረን ሁኔታ በርካታ ተቃውሞዎቻችንን ቸል በማለት ይህንን አመለካከት በተንኰል የእኛ ያደርጉታል። በዚህም መንገድ የእኛን ትምህርት በሰሚዎቻቸው መካከል የተጠላ እንዲሆን ያደርጋሉ። በተቃራኒ ሁኔታ እኛ በክርስቶስ ያለተወሳሰበ የኪዳኑ ቃል መሠረት እውነተኛ፣ ዳሩ ግን፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነውን የክርስቶስን ሥጋ መብላትንና ደሙን መጠጣትን እንይዛለን፤ እናስተምራለንም። የሰው አመክንዮና መረዳት ይህንን ሊጨብጠው አይችልም፤ ነገር ግን፣ እንደ ሌሎቹ የእምነት አንቀጾች ሁሉ የእኛ መረዳት እዚህ ላይ ለክርስቶስ በመታዘዝ ምርኮኛ መሆን አለበት። እንዲህ ያለው ምሥጢር በእምነትና በቃሉ መገለጥ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሊጨበጥ አይችልም።

[57] አንቀጽ 38-40 የተወሰኑ የሮማ ካቶሊክ ልምምዶችን በድጋሚ ይቃወማሉ።

## VIII. (8)
## ስለ ክርስቶስ ማንነት

1 ቅዱስ እራቱን በተመለከተ ከነበረው ውዝግብ ንጹሕ ትምህርትን በሚያስተምሩት የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችና በካልቪን ተከታዮች (ሌሎች የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችንም ወደ ስሕተት በመሩት) መካከል የክርስቶስን ማንነት፣ የክርስቶስን ሁለት ባሕርያትና የእነርሱን ጠባያት በተመለከተ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር።

### *የውዝግቡ ሁኔታ*
### በዚህ ክርክር አለመግባባት የተፈጠረባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች [58]

2 ዋናው ጥያቄ በክርስቶስ ማንነት ውስጥ የሁለቱ ማለትም የመለኮታዊነቱና የሰብዓዊነቱ አንድነት እስከነ ባሕርያቸው (ማለትም፣ በተጨባጭና በእውነት) እርስ በርሳቸው በእርግጠኝነት ተቀራርበው የተያያዙ ናቸው? ተቀራርበው መያያዛቸውስ እስከ ምን ድረስ ነው? የሚል ነበር።

3 በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ፣ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መለኮታዊውና ሰብአዊው ባሕርያት በአንዱ አካል አንድ የሚሆኑት፣ በእርግጠኝነት (ማለትም በተጨባጭና በእውነት) አንዱ ያለውን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ከሌላው ጋር ሳይካፈል ነው በማለት ተናግረዋል።[59] በዚህ ፈንታ፣ ያላቸው የጋራ ስም ብቻ ነው። ምክንያቱም፣ አንድነቱ «ስሙ በአንድነት እንዲጠራ አድርጎታል» ይላሉ፤ ይህም ማለት፣ የማንነት አንድነቱ ስምን በጋራ ከመያዝ ባለፈ የሚያስገኘው ምንም ነገር የለም። ይህም አምላክ ሰው ተብሎ ተጠራ እንዲሁም ሰው አምላክ ተባለ ለማለት ነው። በሌላ አባባል፣ በእርግጠኝነት (ማለትም በተጨባጭና በእውነት) እግዚአብሔር ከሰብዓዊነት ጋር ምንም ቁርኝት (ተካፋይነት) የለውም፣ እንዲሁም ሰው ከመለኮታዊነት ወይም ከግርማውና ከጠባዩ ጋር ምንም ቁርኝት (ተካፋይነት) የለውም በማለት ይናገራሉ። ዶ/ር ሉተርና የእርሱ ደጋፊዎች በቅዱስ ቊርባን፣ በሥጋ ወደሙ የክርስቶስን እውነተኛ መገኘት የሚቃወሙ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎችን አቋም በመቃወም ይከላከላሉ።

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

በክርስቶስ ማንነት ላይ የቤተ ክርስቲያን ንጹሕ አስተምህሮ

4 ይህንን ክርክር በክርስትና እምነታችን መመሪያ መሠረት ለማብራራትና ለመፍታት የሚከተሉትን እናስተምራለን፤ እናምናለን፤ እንመሰክራለንም።

5 1. መለኮትና ሰብዓዊ ባሕርያት በክርስቶስ ማንነት አንድ ሆነዋል፣ ስለዚህም ደግሞ አንድ ብቸኛ የእግዚአብሔር ልጅ እና የሰው ልጅ እንጂ (ሉቃ 1 [፡31-35]፤ ሮሜ 9[፡5]) ሁለት ክርስቶሶች (በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ልጅ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ) የሉም።

6 2. መለኮትና ሰብዓዊ ባሕርያቱ ወደ አንድ ማንነት ያልተጨፈለቁ መሆናቸውንም እናምናለን፣ እናስተምራለን፣ እንመሰክራለንም። አንዱ ወደ ሌላው የተለወጠ አይደለም።

---

[58] በዚህ ክርክር ስለ ተሳተፉ ቡድኖች ከዚህ በታች SD VII, 592 ቊጥር 172 ተመልከት። ከሉተር ሞት በኋላ በጌታ እራትና በትምህርተ ክርስቶስ ላይ የተነሡ ውዝግቦች ሊለዩ እስከማይችሉ ድረስ በጣም የተጣመሩ ናቸው።

[59] እነዚህ አመለካከቶች በቀደሙት 1570ዎቹ በሳክሶን የንጉሠ ነገሥት መራጮች የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች በታተሙ ሥራዎች በተለያዩ መልኮች የተገለጹ ነበሩ። በክርስቶስ ማንነትና ሥጋ መልበስ ... የጸና መሠረት (2d ed, 1571), የጥቅምት 10፡1571 the Dresdener Abschied (Dresden Recess) እንዲሁም የ1574 exegesis Spicua & ferme integra controuersiae de sacra . ምንም እንኳ በቀጥታ የተጠቀሰው አልፎ አልፎ ቢሆን የማርቲን ቼምኒዝ De duabus naturies in Christo (On the two natures in Christ) (1570, 2d ed, 1578) በስምምነቱ አዘጋጆች አቋም የተገለጹትን አሳቦች አጉልብቶ ነበር። ይህ አቋም የስምምነቱ አዘጋጆች የሉተርን ትምህርተ ክርስቶስ ትርጒም ይወክላል፤ SD VIII, 617-24 እና ቊጥሮች 250-278 ተመልከት። የስምምነቱ አዘጋጆች በአበው ምንጮች መሠረት ከአንዳንድ የመጽሐፈ ስምምነት እትሞች ጋር በ1580 በታተመው Catalog of Testinmonies ስለ ትምህርተ ክርስቶስ አስተምህሮአቸው መከላከያቸውን አቅርበዋል።

ይልቁንም እያንዳንዱ የሌላው ጠባይ ሊሆኑ ከቶ የማይችሉ የገዛ ራሱ የሆኑ መሠረታዊ ጠባይዓትን ይይዛል።

7 3. የመለኮት ባሕርያት፡- ሁሉን ቻይነት፣ ዘላለማዊነት፣ ወሰን የለሽነት በሁሉ ስፍራ መገኘት፣ (እንደሚገለጥበት ተፈጥሮ ባሕርይና በራሱ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ አንጻር፣ በራሱና ከራሱ) ሁሉን ዐዋቂነት ወዘተ. ... ናቸው። እነዚህ ከቶውኑ የሰዋዊው ባሕርይ ሊሆኑ አይችሉም።

8 4. የሰብዓዊነት ባሕርያት፣ አካላዊ ፍጡር መሆኑ፣ ሥጋና ደም መሆኑ፣ ውሱንና የሚገደብ መሆኑ፣ የሚሠቃይ፣ የሚሞት፣ የሚወጣ፣ የሚወርድ፣ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀስ፣ በረሀብ፣ በጥማት፣ በብርድ፣ በሙቀት እና በመሳሰሉት የሚሠቃይ መሆኑ ናቸው። እነዚህ ከቶውኑ የመለኮታዊ ባሕርይ ሊሆኑ አይችሉም።

9 5. ሁለቱም ባሕርያት በአንድ ማንነት አንድ ስለ ሆኑ (ማለትም በአንድ አካል አንድ ስለ ሆኑ)፣ ይህ አንድነት ሁለቱ ባሕርያት እንደ ተጠበቁ፣ አንዱ ለሌላኛው ምንም ሳይሰጥ ወይም ከሌላኛው ምንም ሳይቀበል፣ ከሌላ አካል በተፈጥሮ ምንም ሳይካፈል (ማለትም፣ በማንነት አንድነት ምክንያት) ልክ ሁለት ጣውላዎች በማጣበቂያ የተጣበቁ ይመስል ከሌላ ተመሳሳይ ነገር ጋር ግንኙነት ወይም ኅብረት የሌለው ዓይነት እንዳልሆነ እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም። በዚህ ፈንታ፣ እግዚአብሔር በእውነት ከዚህ ሰብዓዊነት ጋር ያለው ፍጹም የተሟላ ኅብረት ይህ ነው፤ ከዚህ አካላዊ አንድነትና ከእርሱ ከሚመነጨው ከዚህ ፍጹም እጅግ ሊገለጽ ከማይችል ኅብረት ለእግዚአብሔር ሊሰጥ የሚችልና ስለ እግዚአብሔር ሊታመን የሚችል ሰብዓዊ ነገር ሁሉ እንዲሁም ሰው ለሆነው ለክርስቶስ ሊሰጥ የሚችልና ሰው ስለ ሆነው ክርስቶስ ሊታመን የሚችል መለኮታዊ ነገር ሁሉ ይመነጫል። የጥንት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ይህን የባሕርይ አንድነትና ኅብረት፣ የብረት ግለትንና የሥጋንና የነፍስን በሰው ውስጥ መገኘት ምሳሌ በማድረግ አስረድተዋል።

10 6. ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነና፣ ሰውም እግዚአብሔር እንደ ሆነ
እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም።[60] በእርግጠኝነትና በእውነት መለኮታዊውና
11 ሰብዓዊው ባሕርያት ፍጹም ግንኙነት ባይኖራቸው ኖሮ ያ ሊሆን የማይችል ነበር። የሰው ልጅ፣ የማርያም ልጅ፣ ሰብዓዊነቱ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር በአካልነት አንድ ባይሆን ኖሮ በእርግጠኝነትና በእውነት «እግዚአብሔር» የሚለውን ስም በመካፈሉ ብቻ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ሊሆን ወይም ተብሎ ሊጠራ እንዴት ይችል ነበር?

12 7. ስለዚህ፣ ማርያም ጭማሪ የለሽ፣ ያልተቀየጠ፣ ሰው ብቻ የሆነ ሕፃን ፀንሳ እንደ ወለደች ሳይሆን፣ ነገር ግን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ወለደች እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም። ስለዚህ በትክክል የአምላክ እናት ተብላ ትጠራለች፤ በእውነትም ነች።

13 8. ስለዚህ፣ የተሠቃየው፣ የሞተው፣ የተቀበረው፣ ወደ ሲኦል የወረደው፣ ከሞት የተነሣው፣ ወደ ሰማይ የወጣው፣ ስለ እኛ ወደ ታላቁና ሁሉን ወደሚችል የእግዚአብሔር ኃይል ከፍ ከፍ ያለው፣ ሰው የሆነው ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ሰብዓዊ ባሕርዩ ከእግዚአብሔር ልጅነቱ ባሕርይ ጋር እንዲህ ባለው ጥልቅና ሊነገር በማይችል ሁኔታ አንድ የሆነና ልዩ ኅብረት ያለው፣ ማለትም ይህ ሰብዓዊ ባሕርይ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር አንድ አካል የሆነ ሰው መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም።

14 9. ስለሆነም፣ «የክብርን ጌታ ሰቀሉት» እንዲሁም «በገዛ ደሙ የዋጃትን»[61] (1ቆሮ 2[፡8]፤ የሐዋ 20[፡28]) ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሰብዓዊ ተፈጥሮው ለመሆኑ እርግጠኛ ለመሆን እኛን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቀን ሊቀ ካህናችን እንዲሆን መከራን

---

[60] ቃል በቃል "dqb Gott Mensch und Mensch Gott Sei," Deus Sit homo, et homosit Deus የሚለው ተለምዶአዊውን የላቲን ትርጉምን በግልጽ ያንጸባርቃል። ይህ ሐረግ በትርጉም ለሚከሰት ልዩነት ክፍት ነው። ይህ ትርጉም እስከ መሠረታዊው መመሪያ ወቅት ድረስ በሉተራውያን መካከል የነበሩትን ውይይቶችና አለመግባባቶች ከግምት ውስጥ ያስገባል። (የሚከተሉት ምንባቦች ግልጽ እንደሚያደርጉት) በማርቲን ኬምኒዝ የነበረው ቡድን ግላዊ አንድነትን የሚገልጹ ረቂቅ አሳቦች ይወገዱ በማለት ጐትጉተዋል።

[61] ተጨባጭ በሆነ የጽሑፍ ረቂቅ ልማድ ላይ የተመሠረተው የሉተር የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በጣም አስቸጋሪ የሆነውን ንባብ እንደ መጀመሪያው ጽሑፍ አድርጎ ቈጠረው።

ለመቀበል ይችል ዘንድ ወደ መለኮታዊ አካሉ ባስገባውና የገዛ ራሱ ባደረገው በሰብዓዊ ተፈጥሮው ባሕርያት መሠረት የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እኛ በእውነት መከራን ተቀብሏል።

15 10. ስለዚህ በእርግጠኝነትና በእውነት እርሱ በእናቱ ማኅፀን በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ ጊዜ የሰብአዊ ተፈጥሮን ቢይዝም የሁሉን ቻይ አምላክ ልጅ በመሆኑና ከእግዚአብሔር ጋር ስለተገናኘ የሰው ልጅ ተብሎና ባሕሪውን በመያዝ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በመቀመጡ የከበረ መሆኑን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም።

16 11. ከአብ ጋር ባለው አካላዊ ኅብረት መሠረት ሁልጊዜ ይህን ታላቅ ግርማ ዘወትር በእጁ ይዟል፤ ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ ባደረገበት ሁኔታ ውስጥ ሊጠቀምበት አልፈለገም። በዚህ ምክንያት በቁመት፣ በጥበብና በጸጋ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ [ሉቃ 2፡52]። ስለዚህ ከትንሣኤው በኋላ የባርያን መልክ [ፊልጵ 2፡7] (ይህም ሰብዓዊ ባሕርዩ ሳይሆን) ሙሉ በሙሉ እስከተወበት ጊዜ ድረስ እርሱን ደስ ባሰኘው ጊዜ ብቻ እንጂ ሁልጊዜ ግርማውን አልገለጠም። ከዚያ በኋላ መለኮታዊ ግርማውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም፣ በመግለጥም፣ በማሳየት እንደገና ተጎናጸፈው፣ እንዲሁም በዚህ ሁኔታ ሁሉን ወደሚያውቅበት፣ ሁሉን ማድረግ ወደሚችልበት፣ ለፍጡራኑ ሁሉ ወደሚገኝበት፣ ደግሞም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉትን ሁሉ ከእግሮቹ በታችና በእጁ ወደሚይዝበት እርሱ ራሱም «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» [ማቴ 28፡18]፣ ብሎ እንደሚመሰክረውና ቅዱስ ጳውሎስ፣ «ይህ የወረደው፣ ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው» [ኤፌ 4፡10] ሲል እንደሚጽፈው እንደ አምላክ ብቻ ሳይሆን እንደ ሰውም ወደ ክብሩ ገብቶአል። በሁሉ ዘንድ እንደሚገኝ ይህን ኃይሉን መጠቀም ይችላል፤ ሁሉን ማድረግ ይችላል፤ እንዲሁም ሁሉን ያውቃል።

17 12. ስለዚህ፣ እንደ ምድራዊና ሰብዓዊ ባሕርይ መሠረት ሳይሆን ዶ/ር ሉተር የክርስትና እምነታችንን መሠረት አድርጎ እንደሚለውና እኛም ልጆቻችንን እንደምናስተምረው በእግዚአብሔር ቀኝ በመቀመጥ ሥልጣኑና ባሕርዩ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋውንና ደሙን ለማካፈል በቅዱስ እራት እንደሚገኝ ይገልጸዋል፣ ደግሞም ይህ ለእርሱ ቀላል ነው። ይህ መገኘት ምድራዊ ፈንጠዝያዊ መገኘት ሳይሆን የኪዳኑ ቃል «ይህ ሥጋዬ ነው» ወዘተ. እንደሚለው መገኘቱ እውነተኛና መሠረታዊ መገኘት ነው።[62]

18 ንስጥሮስ እንዳለው ሳይሆን በዚህ ትምህርታችን፣ እምነታችንና የእምነት መግለጫችን መሠረት የክርስቶስ አካል የተከፋፈለ አይደለም። እርሱም (ኮሙኒካቲዮ ኢድዮማቱም[63] (*communicatio idiomatum*) ማለትም፣ በክርስቶስ ያሉት የሁለቱን ባሕርያት እውነተኛ ኅብረት ይክዳል። ሉተር «ኦን ዘ ካውንስልስ ኤንድ ዘ ቸርች»[64] (*On the Councils and the Church*)፣ በሚለው መጽሐፉ እንዳብራራው የክርስቶስን አካል ይከፋፍላል) ወይም አውጤቂስ በሐሰት እንዳስተማረው ባሕርያቱ ከነጠባያቸው እርስ በእርስ ወደ አንድ ማንነት አልተቀላቀሉም። አለበለዚያም ደግሞ በክርስቶስ አካል ሰብዓዊው ባሕርይ አልተካደም ወይም አልጠፋም፤ አንዱ ባሕርይም ወደ ሌላኛው ባሕርይ አልተቀየረም። ይልቁንም፣ ክርስቶስ አሁንና ለዘላለምም አምላክና ሰው ሆኖ በአንድ ሊለያይ በማይችል አካል ይኖራል፣ ይህም ሐዋርያው እንደሚመሰክረው [1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16] ከቅድስት ሥላሴ ምሥጢር ቀጥሎ ያለው እጅግ ከፍተኛው ምሥጢር ነው፤ በዚህ ምሥጢር ላይ ነው ብቸኛ መጽናናታችን፣ ሕይወትና ድነታችን ያረፈው።

[62] ለምሳሌ የሉተር That These Words of Christ, "This is My Body" etc., እስካሁን የጸና ነው (1527) (WA 23-131-37; LW 37-55-59; የክርስቶስን እራት የሚመለከት መግለጫ (1528) (WA 26: 326-30; LW 37: 214-16).

[63] የባሕርያት የመለኪያ ጠባይዓት ግንኙነት።

[64] On the Council and the Churches (1539) (WA 50-584-95; LW 41:95-106).

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*በክርስቶስ ባሕርይ ላይ ተቃራኒው የሐሰት ትምህርት*

19 *በመሠረቱ፣ የሚከተሉት የተሳሳቱ አንቀጾች ከእግዚአብሔር ቃልና ግልጽ ከሆነው ከክርስትና እምነታችን መግለጫ*[65] *በተቃራኒ ሁኔታ እንደሚከተለው ሲያስተምሩ*[66] *እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም።*

20 1. *ንስጥሮስ በስንፍና እንደሚገልጸው አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ አካል አልሆኑም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ አንድ አካል አለ፤ ደግሞም የሰው ልጅ የሆነ ሌላ አካል አለ ሲል፣*

21 2. *አውጤቂስ በሀሳቡ እንደ ፈጠረው የመለኮታዊውና የሰብዓዊ ባሕርያት ወደ አንድ ይዘት እርስ በርሳቸው በአንድ ላይ ተቀላቅለዋል፤ እንዲሁም ሰብዓዊ ባሕርዩ ወደ መለኮታዊ ባሕርዩ ተቀይሮአል ሲል፣*

22 3. *አርዮስ እንደሚያምነው ክርስቶስ እውነተኛ፣ ተፈጥሮአዊ እና ዘላለማዊ አምላክ አይደለም ሲል፣*

23 4. *ማርሲዮን እንደ ዘየደው ክርስቶስ ሥጋና ነፍስ ያለው እውነተኛ ሰብዓዊ ባሕርይ አልነበረውም ሲል፣*

24 5. *አካላዊው አንድነቱ የጋራ መጠሪያዎች ወይም ስሞች ብቻ ይፈጥራል ሲሉ፣*[67]

25 6. *እግዚአብሔር ሰው ነው፣ ሰውም እግዚአብሔር ነው ምክንያቱም መለኮት ከሰብአዊነት ጋር ምንም የጋራ የሆነ ነገር የለውም፣ እንዲሁም ሰብአዊነት ከመለኮት ጋር በእውነት ማለትም በተጨባጭ ምንም የጋራ የሆነ ነገር የለውም፣ በሚባልበት ጊዜ፤ ይህ አገላለጽ ወይም ሞደስ ሎኪዌንዲ* (*modus loquendi*)*፣ ማለት የቃላት ጉዳይ ወይም የአነጋገር መንገድ ብቻ ነው፣ ሲሉ፤*

26 7. *የእግዚአብሔር ልጅ ለዓለም ኃጢአት ሞቶአል ወይም የሰው ልጅ ሁሉን ቻይ አምላክ ሆኖአል ሲባል፣ ይህ ኮሚኒካቲዮ ቨርባቲዮ* (*communicatio verbalis*)*ብቻ ስለሆነ፣ ከአነጋገር ዘይቤ ያለፈ አይደለም ሲሉ፤*

27 8. *በክርስቶስ ያለው ሰብአዊ ባሕርይ እንደ መለኮታዊ ባሕርይ አኳኋን የማይወሰን ባሕርይ መሆኑና መለኮታዊው ባሕርይ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ ይህም ከእግዚአብሔር በተለየና ወደ ሰብዓዊው ባሕርይ ውስጥ የፈሰሰ/የተቀዳ በአንድ ዓይነት መሠረታዊ የኃይልና የባሕርይ ተካፋይነት መሠረት ነው ሲሉ፣*[68]

28 9. *ሰብዓዊ ባሕርይ በመሠረታዊ ነገሩና በይዘቱ ወይም የራሱ በሆነው ባሕርዩ ከመለኮታዊ ባሕርይ ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንዲሆን በመደረጉ ከእርሱ ጋር እኩል ሆኗል ሲሉ፤*

29 10. *የክርስቶስ ሰብዓዊ ባሕርዩ በሰማይና በምድር በሁሉ ስፍራ ተዘረጋግቷል* (*ከመለኮታዊም ባሕርይ ጋር አብሮ ሊወሰድ የማይገባ ዐሳብ*) *ነው ሲሉ፤*

30 11. *በአካል በሁሉ ቦታ ለመገኘት ቀርቶ ከሰብአዊው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ የተነሣ በአንድ ጊዜ ከአንድ ቦታ በላይ በአካል መገኘት ለክርስቶስ የማይቻል ነው፣ ሲሉ፤*

31 12. *የእግዚአብሔር ልጅ፣ በተጨባጭ ከሰብዓዊነቱ ጋራ በሥቃዩ ምንም ኅብረት* (*ተሳታፊነት*) *እንደሌለው፣ መከራው ፈጽሞ እንዳልነካው ያህል ሰብዓዊነቱ ብቻ ነው ለእኛ የተሠቃየውና ያዳነን ሲሉ፤*

---

[65] *በሐዋርያት እምነት መግለጫና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ስምምነትን በተመለከተበት ጥናታዊ በነበረው አቀራረቡ አንድሬአ ተከራክሮ ነበር።* cf.. his Six Christian Sermons

[66] *እነዚህ አቋሞች ለሚገኙባቸው ለካልቪናውያንና «ለክሪስፕቶ - ፊሊፕሲት» የተወሰኑ ማጣቀሻዎች* SD VIII, 628-29 *ቊጥሮች* 288-291፣ 633-35፣ *ቊጥሮች* 301-304 *ተመልከት።*

[67] *በመጀመሪያ በላቲን ተጠቅሶ ከዚያም ተተርጒሞአል።*

[68] *አንቀጽ* 27-29 *እንደ ቲልማን ሄስሁስ ያሉ ሉተራውያን የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ላቀረቡአቸው ተቃውሞዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ።*

32 13. ክርስቶስ በምድር ከእኛ ጋር ያለው በቃሉ፣ በቅዱሳት ምሥጢራት እንዲሁም በችግራችን ጊዜያት ሁሉ በመለኮታዊነቱ መሠረት እንደሆነና፣ እንዲህ ያለው መገኘትም በፍጹም ከሰብዓዊ ባሕርዩ ጋር ግንኙነት እንደሌለው እኛን በሥቃዩና በሞቱ አማካይነት ካዳነን በኋላ በምድር ከእኛ ጋር በሰብዓዊ ባሕርዩ መሠረት ምንም የሚያደርገው ነገር የለም ሲሉ፤

33 14. ሰብዓዊ ባሕርይን የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ፣ የባሪያ መልክን ከተወ በኋላ በሰብዓዊ ባሕርዩ የሚያደርገው የሁሉን ቻይነቱን ሁሉንም ሥራዎች ሳይሆን፣ ሰብዓዊው ባሕርይ በሚገኝበት በተወሰነ ስፍራ ጥቂትና ውሱን ነገሮችን ብቻ ነው ሲሉ፤

34 15. በ(ማቴ 28፡18) «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» በማለት ክርስቶስ በግልጽ ከተናገረው፣ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ «በእርሱ የመለኮቱ ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይገኛልና» (ቈላ 2፡9) ከሚለው ጋር የሚቃረነውን በሰብዓዊው ባሕርይ መሠረት ሁሉን ቻይነቱንና ሌሎች የመለኮታዊ ባሕርዩ መለያ ጠባያትን በጭራሽ ሊለማመዳቸው አይችልም ሲሉ፤

35 16. ለእርሱ [ለክርስቶስ] በእርግጥ በሰማይና በምድር ታላቅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፤ ማለትም ከመላእክትና ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ታላቅና የበለጠ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት አይካፈልም፤ በተጨማሪም እንዲህ ዓይነት መለኮታዊ ሥልጣን ለእርሱ አልተሰጠ ውም:: በዚህ መንገድ ሚዲያ ጠቴንሺያ (*media potentia*) በእግዚአብሔር የሁሉን ቻይነት ሥልጣንና በሌሎች ፍጥረታት ሥልጣን መካከል ያለውን ዓይነት ሥልጣን በመፍጠር ክርስቶስ በሰብዓዊ ባሕርዩ መሠረት በእርገቱ ጊዜ የተሰጠው፣ ይህ ክብርና ሥልጣን ከእግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ሥልጣን ያነሰና ከሌሎች ፍጥረታት ሥልጣን ግን የበለጠ ነው ሲሉ፤

36 17. ክርስቶስ በሰብዓዊ መንፈሱ መሠረት ምን ያህል ማወቅ እንደሚችል የተገደበ ወሰን አለው፣ እንዲሁም ሥልጣኑን እንደ ዳኛ እንዲተገብር ማወቅ ከሚገባውና ከሚያስፈልገው በላይ ሊያውቅ አይችልም ሲሉ፤

37 18. እርግጥ ነው ምንም እንኳ «የተሰወረ ጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና» (ቈላ 2፡3) ተብሎ የተጻፈ ቢሆንም ክርስቶስ ገና የእግዚአብሔር እና የሥራዎቹ ፍጹም እውቀት የለውም ሲሉ፤

38 19. በሰብዓዊነቱ መንፈስ መሠረት ክርስቶስ ከዘላለም የነበረውን፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለም በሁሉ ስፍራ እየሆነ ያለውንና ለወደፊት ለዘላለም ምን እንደሚሆን ለማወቅ አይቻለውም ሲሉ፤

39 20. ማንም ሰው በማቴዎስ 28[፡18] «ሥልጣን ሁሉ ... ተሰጠኝ» የሚለውን ምንባብ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ ባደረገበት ሁኔታ በመለኮቱ ባሕርይ መሠረት እንኳን ወደ ጎን የጣላቸውና የተዋቸው ይመስል በትንሣኤውና በዕርገቱ በመለኮታዊ ባሕርዩ መሠረት ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ለክርስቶስ እንደገና እንደታደሱለት ወይም እንደተመለሱለት ሲያስተምርና እንደዚያ ሲተረጉም እና እግዚአብሔርን በሚያሰድብ መንገድ ክፍሉን ሲያጣምም፣

እንዲህ ያለ ትምህርት የሚቀለብሰው የክርስቶስን የኪዳኑን ቃል ማጣመም ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በመጨረሻም የክርስቶስን ዘላለማዊ መለኮታዊነት ወደሚክደው ወደ ተረገመው አርዮሳዊ ኑፋቄ ለመመለስ መንገድ የሚጠርግ ነው፤ እንዲህ ዓይነቱን የሐሰት ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ጽኑ መሠረት እና ግልጽ በሆነው የክርስትና እምነት መግለጫችን ካልተቃወምነው በዚህ መንገድ ክርስቶስ ከደኅንነታችን ጋር ሙሉ በሙሉ ጠፍቶአል ማለት ነው::

## IX. (9)
## ስለ ክርስቶስ ወደ ሲኦል መውረድ

### የውዝግቡ ሁኔታ
### ይህን አንቀጽ በተመለከተ ዋና ጉዳይ[69]

1 ግልጽ በሆነ የክርስትና እምነት መግለጫችን መሠረት፣ ጌታ ክርስቶስ መቼና እንዴት ባለ ሁኔታ ወደ ሲኦል እንደ ወረደ፣ እንዲሁም ይህ የሆነው ከመሞቱ በፊት ወይስ በኋላ ነው በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ፣ በተጨማሪም ለኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ራሳቸውን በሰጡ አንዳንድ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል ይህንን አንቀጽ በተመለከተ ደግሞም ወደ ሲኦል የወረደው በነፍሱ ብቻ ነው ወይስ በመለኮትነቱ ብቻ፣ ወይም በሥጋና ነፍስ፣ በአካልም በመንፈስም እንደ ሆነ፣ እንዲሁም ይህ የእምነት አንቀጽ የሚመደበው ወደ ክርስቶስ መከራ ወይም ወደ ክብሩ ድልና አሸናፊነት እንደ ሆነ አንዳንድ ክርክር ነበር።

2 ይህ አንቀጽ እንዳለፈው አንቀጽ ሁሉ እውነት እንደ ሆነ በአመክንዮ ወይም በመረዳት
ሊገነዘቡት የማይቻል ስለ ሆነ በእምነት ብቻ ሊጨበጥ ይገባል። በዚህ ጉዳይ ላይ ክርክር ሊኖር
3 አይገባም፣ ነገር ግን ይህ አንቀጽ በ1533[70] በቶርጋው ስብከቱ በበለጠ ክርስቲያናዊ በሆነ ሁኔታ
የተባረከ ትዝታ ያለው ዶ/ር ሉተር እንደ ገለጸው ሊታመንና በቀላሉ በእጅጉ ትምህርት
ሊሰጥበት እንደሚገባ በሙሉ ድምፅ እንመክራለን። እዚያ ላይ የማይጠቅሙና የማያስፈልጉ
ጥያቄዎችን ሁሉ አስወግዶ፣ እንዲሁም ቅን የሆኑ ክርስቲያኖችን ግልጽ ወደ ሆነው ክርስቲያናዊ
እምነት መልሶአቸዋል።

4 ምክንያቱም ክርስቶስ ወደ ሲኦል እንደ ወረደ፣ ለሁሉም አማኞች ሲኦልን እንዳጠፋና ከሞት ከዲያብሎስ ሥልጣን፣ እና ከዘላለም የሲኦል ኩነኔ በቀል እንደ ተቤዣቸው ማወቃችን በቂ ነው። ያ እንዴት እንደሆነ ይህ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በእምነት ብቻ የምንቀበላቸው ጭፍን በሆነው ምክንያታዊነታችን ልንገነዘባቸው የማንችላቸው ነገሮች ሁሉ ግልጽ ለሚሆኑበት ለሚቀጥለው ዓለም ልናቆየው ይገባል።

## X. (10)
## ስለ ቤተ ክርስቲያን ልምምዶች

### Adiaphora (አዲያፎራ) ተብለው የሚጠሩ፡- መታዘዛቸው ወይም መከልከላቸው ተለይተው ያልታወቁ ጉዳዮች [71]

1 በኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል በእግዚአብሔር ቃል ያልታዘዙ እንዲሁም ያልተከለከሉ ነገር ግን ለመልካም ሥርዓትና ምግባር ይጠቅማሉ ተብለው የተጀመሩ ልምምዶችን በተመለከተ ክርክር ተከስቶአል።

### *የውዝግቡ ሁኔታ*
### *ይህን አንቀጽ በሚመለከት ዋናው ውዝግብ*

2 ዋናው ጥያቄ የወንጌሉ ጠላቶች ከእኛ ጋር ለመስማማት የማይፈቅዱበትና የእምነት መግለጫ የሚያስፈልግበትን የስደት ጊዜ ሁኔታ ይመለከታል፤ ጥያቄው በዚያ ሁኔታ ውስጥ በመልካም ሕሊና የተወገዱ የተወሰኑ ሥነ ሥርዓቶች (በራሳቸው ልዩነት የማያመጡ ነገሮች በእግዚአብሔር ያልታዘዙ ወይም ያልተከለከሉ) በተቃዋሚዎቹ ግፊትና ፍላጎት እንደገና

---

[69] ስለዚህ አንቀጽ ዳራ ከታች SD IX, 634-35 ቁጥር 305 ተመልከት።
[70] WA 37:62-67.
[71] በዚህ ክርክር ስለ ተሳተፉ ቡድኖች ከታች SDX, 635-36 ቁጥሮች 308-309 ተመልከት።

ሕይወት ሊዘሩ መቻል አለመቻላቸው እንዲሁም በእንዲህ ዓይነት ሥነ ሥርዓቶችና ልዩነት የማያመጡ ነገሮች መደራደሩ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ነበር። ለዚህ ጥያቄ አንደኛው ቡድን አዎን ሲል፣ ሌላኛው አይደለም ብሏል።

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

*ይህን አንቀጽ በተመለከተ ተገቢ፣ እውነተኛ ትምህርትና የእምነት መግለጫ*

3 1. ይህን ክርክር ለመቋጨት፣ በእግዚአብሔር ቃል ያልታዘዙ ወይም ያልተከለከሉ ነገር ግን ለመልካም ሥርዓትና ምግባር ብቻ የተመሠረቱ ሥነ ሥርዓቶች ወይም ቤተ ክርስቲያናዊ ልምምዶች በራሳቸውና ለራሳቸው መለኮታዊ አምልኮ ወይም በትንሹ እንኳ የዚህ አምልኮ ክፍል አለመሆናቸውን እናምናለን፣ እናስተምራለን፣ እንመሰክርማለን። ይኸውም «የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል» (ማቴ 15[:9]) ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

4 2. በማንኛውም ቦታና ጊዜ የሚገኝ የእግዚአብሔር ማኅበረ ሰብ እንዲህ ያሉ ሥነ ሥርዓቶችን ለእግዚአብሔር ማኅበረ ሰብ እጅግ በጣም ጠቃሚና የሚያንጹ ሆነው ከተገኙ እንደየሁኔታዎቹ ለመለወጥ ሥልጣን እንዳለው እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም።

5 3. በእርግጥ፣ ጨዋነት የጎደላቸው ቧልቶችና አሰናካይ ንግግሮች ሁሉ መወገድ አለባቸው። በተለይ በእምነት ለደከሙት የተለየ ጥንቃቄ ሊሰጥ ይገባል።

6 4. ከእኛ የማያወላውል የእምነት መግለጫ በሚፈለግበት በስደት ጊዜ እንደዚህ ባሉ ልዩነት በማያመጡ ጉዳዮች ለተቃዋሚዎቹ እጅ አንሰጥም ብለን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም። እርሱም ሐዋርያው እንደዚህ ሲል እንደ ጻፈው ነው፡- «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» [ገላ 5፡1]። ደግሞም «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ... ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» ይላል (2ቆሮ 6፡14)። እንደገናም «የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቀቀን አልተገዛንላቸውም» ይላል (ገላ 2፡5)። ምክንያቱም እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ አሳሳቢዎቹ ጉዳዮች ልዩነት የማያመጡት ነገሮች መሆናቸው ይቀርና የወንጌሉን እውነትና የክርስትና ነጻነትን የሚመለከቱ ይሆናል። ይኸውም ገሃዳዊ የጣዖት አምልኮን ከመደገፍና በእምነት የደከሙትን ከመሰናክል የመጠበቁ ጉዳይ ነው። እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ምንም ዓይነት ማካካሻ አንሰጥም፤ ዳሩ ግን የማያወላውል የእምነት መግለጫ መስጠትና እግዚአብሔር የቃሉ ጠላቶች በእኛ ላይ እንዲፈጽሙት የሚልካቸውንና የሚፈቅድላቸውን ማንኛውንም ነገር መሸከም ይገባናል።

7 5. «በጾም ጉዳይ አለመመሳሰል የእምነትን አንድነት ማናጋት የለበትም»[72] በሚለው በታወቀ አነጋገር መሠረት በትምህርትና በሁሉም የእምነት አንቀጾች እንዲሁም በትክክለኛው የቅዱሳት ምሥጢራት አጠቃቀም አንድነት እስካለ ድረስ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ከሌላው ያነሰ ወይም የበለጠ በእግዚአብሔር ያልታዘዘ ውጪአዊ ሥርዓት ያለው በመሆኑ ሌላውን መኮነን የለበትም ብለን እናምናለን፤ እናስተምራለን፤ እንመሰክራለንም።

*አሉታዊ ዐሳቦች*

*ይህን አንቀጽ በተመለከተ ያለው የሐሰት ትምህርት*

8 ስለዚህ የሚከተሉትን ትምህርቶች ስሕተትና የእግዚአብሔር ቃል ተቃራኒ ናቸው በማለት እንቃወማቸዋለን፤ እናወግዛቸውማለንም፡-[73]

---

[72] Irenaeus, በEusbius, Church History v. 24,13 (MPG 20-506; NPNF, ser., 1:243) ጠቅሶአል።

[73] እነዚህ አቋሞች ሜላንክተንና ሌሎች የሳክሶን የምርጫ ክልል የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች የለይፒዚግ ሽግግር (ለይፒዚግ ኢንተሪም) Leipzig Interim በተሰኘው ውስጥ ለማራመድ የሚሞክሩትን በተመለከተ የእውነተኞች ሉተራውያን ግንዛቤን የሚወክሉ ናቸው።

9 1. *ማንም ሰው በቤተ ክርስቲያን ያሉት የሰው ትእዛዛትና ሕግጋት በራሳቸውና ከራሳቸው እንደ አምልኮ በእግዚአብሔር የተደነገጉ ወይም የዚሁ አካል የሆኑ አምልኮዎች ተደርገው መቈጠር አለባቸው ብሎ በሚያስተምርበት ጊዜ፤*

10 2. *ማንም ሰው ውጪአዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለውን ክርስቲያናዊ ነጻነት በመቃረን እንደዚህ ያሉት ሥርዓቶች፣ ትእዛዛትና ሕግጋት አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ በመቊጠር በኃይል በእግዚአብሔር ማኅበረ ሰብ ላይ በሚጭንበት ጊዜ፤*

11 3. *በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ማንም ሰው በስደት ሁኔታ ገሃድ መግለጫ መስጠት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እነዚህን ልዩነት የማያመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ከቅዱሱ ወንጌል ጠላቶች ጋር መስማማት ወይም ድርድር ማድረግ ይችላል ብሎ በሚያስተምርበት ጊዜ፤ (እንደዚህ ያሉት ድርጊቶች የእግዚአብሔርን እውነት ለመጕዳት ያገለግላሉ)።*

12 4. *በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔር ማኅበረ ሰብ በማንኛውም ጊዜ ነጻነት እንደሌለው በሚያመለክት መንገድ እርሱ በሚገኝበት ልዩ ሁኔታ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ በሆነው በክርስቲያናዊ ነጻነት በመጠቀም ከእነዚህ ሥርዓቶች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት ለመጠቀም እንዳይችል እንደዚህ ያሉት ውጪአዊ ሥርዓቶችና ልዩነት የማያመጡ ጕዳዮች በሚወገዱበት ጊዜ ነው።*

## XI. (11)

## *ስለ ዘላለማዊ ቅድመ ውሳኔና ስለ እግዚአብሔር ምርጫ*

1 *በዚህ አንቀጽ ላይ በኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች መካከል ምንም ዓይነት የአደባባይ ግጭት አልነበረም።*[74] *ይሁን እንጂ፣ ይህ አንቀጽ በአግባቡ በሚያዝበት ጊዜ የመጽናኛ አንቀጽ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ፊት እንቅፋት የሚሆን ክርክር እንዳይነሣ እርሱም ደግሞ በዚህ ሰነድ ተገልጾአል።*

*አዎንታዊ ዐሳቦች*

*ስለዚህ አንቀጽ ንጹሕና እውነተኛ ትምህርት፤*

2 1. *ከሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ቅድመ ዕውቀትና በእርሱ ዘላለማዊ ምርጫ መካከል ያለው ልዩነት በጥንቃቄ መታሰብ አለበት።*

3 2. *የእግዚአብሔር ቅድመ ዕውቀት ማለት፣ «ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ አለ፤ እርሱም በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታውቆታል» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ዳን 2፡28) ነገሮች ከመፈጸማቸው በፊት እግዚአብሔር ሁሉንም ያውቃል ከማለት ሌላ አይደለም።*

4 3. *ይህ ቅድመ ዕውቀት ቀኖችና ክፉ ሰዎችን በእኩልነት የሚሸፍን ነው፤ ዳሩ ግን እርሱ የክፋት ምንጭ አይደለም። ይህ ሰዎች ስሕተት በሚሠሩበት ጊዜ የኃጢአት ምንጭ አይደለም (ኃጢአት በመጀመሪያ ከዲያብሎስና ከክፉው ከተጣመመ የሰው ፈቃድ የሚመነጭ ነው) ወይም ደግሞ ይህ ማለት ሰዎች ራሳቸው ኃላፊ ለሆኑበት ለሰዎች መበላሸት ምክንያት አይደለም። በዚህ ፈንታ የእግዚአብሔር ቅድመ ዕውቀት በክፋት መካከል መልካም ሥርዓትን የሚያስገኝና ለክፋቱም ገደብን የሚያደርግ ነው። ይህም ክፋት እስከ መቼ ድረስ ሊቀጥል እንደሚችል የሚወስነውና ምንም እንኳ ክፋቱ በራሱ ክፉ ቢሆንም ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔርን ምርጦች በበጎነት ያገለግላል።*

5 4. *ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምርጫ የሚሸፍነው ጻድቃንን ወይም እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ የእግዚአብሔር ልጆችን ብቻ ነው። እርሱ እግዚአብሔር የሚያመጣው የእነርሱ ድነት ምንጭ ነው። ከዚህ ጋር የሚመደበውን ማንኛውንም ነገር*

---

[74] *በዚህ አንቀጽ ጻራ ላይ ከዚህ በታች* SD XI, 641, *ቊ.* 318*ን ተመልከት።*

ያዘጋጀው እርሱ [እግዚአብሔር] ነው። የእኛ ድነት በዚህ ላይ በጽኑው የተመሠረተ እንደ መሆኑ መጠን [ዮሐንስ 10፡26-29] «የገሃነም ደጆችም አይቋቋሙአትም» [ማቴ 16፡18] ይላል።

6 5. ይህ ምርጫ በእግዚአብሔር የተሰወረ ምክር ውስጥ የሚመረመር ሳይሆን፣ ይልቁን እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ከገለጸበት ከቃሉ ውስጥ የሚፈለግ ነው።

7 6. ይሁን እንጂ፣ «ዓለም ሳይፈጠር ... በክርስቶስ መረጠን» (ኤፌ 1፡4) ተብሎ እንደ ተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም የሚድኑት ወደ ተመዘገቡበትና ወደ ተመረጡበት «የሕይወት መጽሐፍ» ወደ ሆነው (ፊል 4፡3፤ ራእ 3፡5) ወደ ክርስቶስ ይመራናል።

8 7. ይህ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ሁሉ ወደ ራሱ በመጥራት የመታደስን ተስፋ ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ መጥተው ለራሳቸው እርዳታ ማግኘት እንደሚገባቸው ፍላጎቱ እጅግ ኃይለኛ ነው [ማቴ 11፡28፤ ከ1ጢሞ 2፡4 ጋር ይነጻጸር]። እርሱም ራሱን በቃሉ ያቀርብላቸዋል። እርሱ የሚፈልገው ቃሉን እንዲሰሙ ነው እንጂ ጆሮአቸውን እንዲደፍኑ ወይም ቃሉን እንዲንቁ አይደለም። ለዚህም ዓላማ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና አሠራር፣ እንዲሁም በታማኝነት ለመጽናትና የዘላለም ድነትን ለማግኘት እንዲቻል የመለኮትን እርዳታ ተስፋ ይሰጣል።

9 8. ስለዚህ ለዘላለም ሕይወት መመረጣችንን በሚመለከት በአመክንዮም ሆነ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ተመሥርተን ፍርድ መስጠት አይገባንም። እንደዚህ ያለው አካሄድ ወደ አውሬነት፣ ኃላፊነት ወደ ጐደለውና ወደ Epicurean ኢፒኩሪያውያን ሕይወት (ወደ ቅንጦት ሕይወት) ወይም ወደ ተስፋ መቍረጥ ይመራናል፤ ደግሞም በሰዎች ልብ ጐጂ የሆነ ዐሳብ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ ሰዎች የራሳቸውን አመክንዮ በሚከተሉበት ጊዜ «እግዚአብሔር ለድነት የመረጠኝ እስከ ሆነ ድረስ ምንም ባደርግ ልኮነን አልችልም» ወይም «ለዘላለም ሕይወት አልተመረጥኩም፤ ስለዚህ መልካም ነገር ባደርግም ጥቅም የለውም፤ ሁሉም ነገር በእውነት ከንቱ ነው» ከሚሉት እነዚህን ከመሰሉት ዐሳቦች ሊያመልጡ አይችሉም።

10 9. በዚህ ፈንታ እውነተኛውን የምርጫ ትርጒም ልንማር የሚገባው ከክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል ነው። እርሱም በግልጽ «እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ ዘግቶታልና» እንደሚል ማንም ሰው እንዳይጠፋ፣ ይልቁን ሁሉም ሰው ንስሐ እንዲገባና በጌታ በክርስቶስ እንዲያምን ይፈልጋል [ሮሜ 11፡32፤ 1ጢሞ 2፡4፣ ከሕዝ 33፡11፤ 18፡23 ጋር አነጻጽር]።

11 10. ይህ ትምህርት የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚያሳስባቸውና ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክት ላይ የሚያሳውቀውን የቅደም ተከተል ሥርዓት ለመከተል ለሚፈልጉት ሰዎች ጠቃሚና አጽናኝ ነው። በዚያ ስፍራ እርሱ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ የምርጫ ምሥጢር ከመናገሩ በፊት ሰዎች ከሁሉ አስቀድሞ ንስሐ እንዲገቡ፣ ኃጢአታቸውን እንዲገነዘቡና በክርስቶስ ወደ ማመንና ለእግዚአብሔር ወደ መታዘዝ እንዲደርሱ ይጠቁማቸዋል።

12 11. «የተጠሩ ብዙዎች የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው» የሚለው ቃል (ማቴ 20፡16) እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ለማዳን አይፈልግም ማለት አይደለም። በዚህ ፈንታ የእነርሱ ኵነኔ ምክንያቱ የእግዚአብሔርን ቃል ጭራሽ ስለማይሰሙ፣ ወይም ጆሮአቸውንና ልባቸውን በመዝጋት እርሱን ስለሚንቁት፣ ከዚህም የተነሣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ሥራውን መፈጸም እንዳይችል የተለመደውን የእርሱን መንገድ ስለሚዘጉት ነው፤ ወይም ደግሞ ቢሰሙትም እንኳ ለነፋስ ስለሚበትኑትና ትኵረት ስለማይሰጡት ነው፤ ይህ ከሆነ ጒድለቱ ከእግዚአብሔርና ከእርሱ ምርጫ ሳይሆን ከገዛ ራሳቸው ክፋት ነው [2ጴጥ 2፡9-15፤ ከሉቃ 11፡47-52፤ ዕብ 12፡15-17፣25 ጋር አነጻጽር]።

13 12. አንድ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ምርጫ የሚገልጸውን አንቀጽ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውን ያህል ብቻ ማሰብ አለበት። «አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ 8፡30)፣ ቃሉ ክርስቶስን በቅዱሱ የወንጌል ስብከት አማካይነት ለእኛ የሚከፍተውና የሚገልጠው «የሕይወት መጽሐፍ» አድርጎ በዓይናችን ፊት ያሳየናል። የአብን ዘላለማዊ ምርጫ ከክርስቶስ መፈለግ አለብን። እርሱም ለልጁ ለክርስቶስ ዕውቅና ከሚሰጡትና በእርሱ በእውነት ከሚያምኑት በስተቀር ማንንም እንደማያድን

በዘላለማዊና መለኮታዊ ምክሩ አውጆአል። ሌሎች ዐሳቦችን ወደ ጐን መጣል አለብን፣ ምክንያቱም እነርሱ የሚመጡት ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከክፉው የጠላት ዐሳብ ስለ ሆነ ነው። ክፉ የጠላት ዐሳብ እንደዚህ ያሉትን ዐሳቦች ይዞ ወደ እኛ የሚቀርበው ይህንን ክቡር የሆነ መጽናናት በእኛ ለማዳከም ወይም እርሱን ፈጽሞ ሊወስድብን ነው። በዚህ ጠቃሚ ትምህርት አማካይነት ክቡር የሆነ መጽናናት ስለ አለን ያለ አንዳች የራሳችን መልካም ሥራ ከሙሉ ጸጋ ብቻ የተነሣ በክርስቶስ ለዘላለም ሕይወት የተመረጥን መሆናችንንና ከእርሱ እጅ ማንም ሊነጥቀን እንደማይችል እናውቃለን (ዮሐ 10፡28-29)። ምክንያቱም በጸጋው እንደ መረጠን ያረጋገጠልን በቃላት ብቻ አይደለም። እርሱ ይህንን በመሐላ አረጋግጦ በቅዱሳት ምሥጢራት አትሞታል። በከፍተኛ መከራ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ስለ እነዚህ ነገሮች ማሰብ በእነርሱም ራሳችንን ማጽናናት እንዲሁም በዚህ የዲያብሎስን የፍላጻ ነበልባል ማጥፋት እንችላለን።

14 13. ከዚህም ጋር በተቻለን መጠን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር መትጋትና ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሚመክረን መመረጣችንን ማጽናት ይገባናል [2ጴጥ 1፡10]፤ በተለይም እኛን ሳይፈጽም ሊዋሽን በማይችለው በተገለጠው ቃል መጽናት ይገባናል።

15 14. ይህ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምርጫ አጭር መግለጫ ሙሉና ፍጹም በሆነ መንገድ ክብሩን ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ከእኛ አንዳች በጎ ሥራ ሳይኖር ከእርሱ ንጹሕ ምሕረት የተነሣ ብቻ «እንደ ፈቃዱ ምክር» ያድነናል [ኤፌ 1፡11]። በተጨማሪም ማንም ሰው ልቡ እንዲዝል ወይም የግዴለሽነትና ከሰብአዊነት ውጪ የሆነ ሕይወት ለመኖር ምክንያት አልተሰጠውም።

*ተቃራኒ ወይም አሉታዊ ዐሳቦች*

ስለዚህ አንቀጽ ያለው የሐሰት ትምህርት

16 በዚህም መሠረት ለዘላለም ሕይወት የሚሆነውን የእግዚአብሔርን የቸርነት ምርጫ ትምህርት የታወኩ ክርስቲያኖች በእርሱ መጽናናትን ማግኘት እንዳይችሉ ዳሩ ግን ወደ ልብ ዝለትና ወደ ተስፋ መቍረጥ እንዲነዱ፣ ወይም የማይጸጸቱ ሰዎች በትዕቢታቸው እንዲጸኑ በሚያደርግ ሁኔታ የሚያስተምሩ ሰዎች ይህንን ትምህርት እንደ ቃሉና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን በራሳቸው አመክንዮ መሠረትና በተረገመው በዲያብሎስ አነሣሽነት የሚያስተምሩ መሆናቸውን እናምናለን፤ እናጸናለንም፤ ምክንያቱም (ሐዋርያው እንደሚመሰክረው) «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» [ሮሜ 15፡4] ነው፤ ስለሆነም ከዚህ የሚከተሉትን ስሕተቶች እንቃወማለን፦

17 1. እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡና በወንጌል እንዲያምኑ አይፈልግም የሚለውን ትምህርት፣

18 2. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር እኛን ወደ ራሱ በሚጠራበት ጊዜ ሁሉም ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ በአጽንኦት ዐቅዶ አይደለም የሚለውን፣

19 3. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድን አይፈልግም፤ ይልቁን ግን ኃጢአታቸውን ምንም ሳይመለከት፦ በእግዚአብሔር ነጻ ውሳኔ፣ ዕቅድና ፈቃድ ምክንያት ብቻ አንዳንዶች ለኵነኔ የተመደቡ ስለ ሆነ፣ ሊድኑ የሚችሉበት ምንም መንገድ የለም የሚለውን፣

20 4. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የእግዚአብሔር የምርጫ ምክንያት በእግዚአብሔር ምሕረትና እጅግ ቅዱስ በሆነው በክርስቶስ በጎ ትሩፋት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ዳሩ ግን እግዚአብሔር እኛን ለዘላለም ሕይወት የመረጠበት በእኛም አንድ መነሻ ምክንያት አለ የሚለውን።

21 እነዚህ ትምህርቶች ክርስቲያኖች በቅዱሱ ወንጌልና በተቀደሱት ምሥጢራት ጥቅም ያላቸውን መጽናናት በሙሉ የሚያስወግዱና የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደቡ አስፈሪ የሆኑና የተሳሳቱ ትምህርቶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ስሕተቶች በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልንታገሣቸው የሚገቡ አይደሉም።

22 ይህ፣ የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች ለተወሰነ ጊዜ እርስ በርስ በሚጋጩ መንገዶች ያስተማሩአቸውና የተወያዩባቸው አከራካሪ አንቀጾች አጭርና ቀላል የሆነ ማብራሪያ ነው። ከዚህ እያንዳንዱ ምእመን በእግዚአብሔር ቃል መመሪያ መሠረትና ቀላል በሆነው የክርስትና ትምህርት ትክክል የሆነውንና ትክክል ያልሆነውን ለይቶ ለማወቅ ይችላል። ምክንያቱም በዚህ እኛ ንጹሕ የሆነውን ትምህርት ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒና ስሕተት የሆነውን ትምህርት አጋልጠናል፤ ተቃውመናልም። በዚህም መንገድ ተነሥተው የነበሩት የሚጐዱ ክፍፍሎች ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል፣ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክና የጌታችን የኢየሱስ አባት ሁላችንም በእርሱ አንድ እንድንሆን (ዮሐንስ 17፡20-21) እና በዚህ ክርስቲያናዊ በሆነና እግዚአብሔርን በሚያስደስት አንድነት በጽናት እንድንቆም የመንፈስ ቅዱሱን ጸጋ ይስጠን።

## XII. (12)
## የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫን ፈጽሞ ስላልተቀበሉት ሌሎች የተለዩ ክፍሎችና ቡድኖች

1 እንደዚህ ያሉት የተለዩ ቡድኖችና ክፍሎች በቀደመው የትምህርት መግለጫችን ልብ ስላላልናቸው በዘዴ ከእኛ ጋር እንዳይደባለቁ[75] እነርሱ የሚሳሳቱባቸውንና በዝርዝር እንዳቀረብነው ከእኛ የክርስትና እምነትና የእምነት መግለጫ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የሚያስተምሩባቸውን ቀላል የሆኑትን የአስተምህሮ መግለጫዎች ብቻ በዚህ መጨረሻ ለመዘርዘር እንፈልጋለን።

*የዳግም አጥማቂዎች የስሕተት አንቀጾች*

2 ዳግም አጥማቂዎች እርስ በርሳቸው በብዙ የተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍለዋል፤ አንዳንዶቹ ብዙ ስሕተቶችን የሚደግፉ ሲሆን፣ ሌሎች ጥቂቶችን ይደግፋሉ። ይሁን እንጂ፣ በአጠቃላይ እነርሱ በቤተ ክርስቲያን፣ በሕዝባዊ ጉዳዮችና በምድራዊ መንግሥት ወይም በቤተ ሰብ ሕይወት ተቀባይነት ሊኖረው የማይችለውን ወይም የማይፈቀደውን የትምህርት ዓይነት ያውጃሉ።

*በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት የሌላቸው ትምህርቶች*

3 1. ክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ከመንግሥተ ሰማያት ከእርሱ ጋር አመጣቸው እንጂ ከድንግል ማርያም አልተቀበላቸውም የሚለው፤

4 2. ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ አይደለም፣ ዳሩ ግን ከማንኛውም ሌላ ቅዱስ ሰው የበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለው የሚለው።

5 3. በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን የተመሠረተው በክርስቶስ በጎ ትሩፋት ላይ ብቻ ሳይሆን በእኛ መታደስና ከዚህም የተነሣ፣ በእኛው በራሳችን የሕይወት አካሄድ ቅንነት ላይ ጭምር ነው የሚለው፤ ይህም አብዛኛው በእኛው በራሳችን በተለየና ራሳችን በመረጥነው መንፈሳዊነት [ቈላ 2፡23] ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ እርሱም በመሠረቱ ከዐዲስ የገዳም ሥርዓት የተለየ ነገር አይደለም።

6 4. ያልተጠመቁ ሕፃናት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች አይደሉም፤ ይልቁን ግን ጻድቃንና የዋሆች ናቸው የሚለው፤ በየዋህነታቸውም አመክንዮአቸውን ሙሉ በሙሉ ወደሚጠቀሙበት ደረጃ ስላልደረሱ ያለ ጥምቀት ይድናሉ ይላሉ (ይህም ማለት በእነርሱ ዐስተሳሰብ

[75] የዚህን ጽሑፍ ዝግጅት መነሻና የእነዚህን «ክፍሎችና የእምነት ቡድኖች» አቋም በተመለከተ ከዚህ በታች SD XII, 656-59 ከ330-333 ቊጥሮችን ተመልከት።

*ጥምቀት ለሕፃናት አያስፈልግም ማለት ነው)፡፡ ስለሆነም እነርሱ መላውን የውርስ ኃጢአት ትምህርትና ከእርሱም ጋር የተያያዘውን ማንኛውንም ነገር ይቃወማሉ፡፡*

7 5. *ሕፃናት በአመክንዮ ወደ መጠቀምና በራሳቸው እምነታቸውን ወደ መግለጥ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ መጠመቅ አይገባቸውም የሚለው፤*

8 6. *የክርስቲያኖች ልጆች ከክርስቲያኖችና ከአማኞች ወላጆች የተወለዱ በመሆናቸው ያለ ጥምቀትና ከጥምቀት በፊት ቅዱሳንና የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው የሚለው፤ ይህም ደግሞ ዳግም አጥማቂዎች የሕፃን ጥምቀትን እንደ አስፈላጊ ነገር የማይቈጥሩበትና ቃል ኪዳኑን ለሚጠብቁትና እርሱን ለማይንቁት ብቻ የተዘረጋውን ግልጽ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በመቃወም እርሱን (የሕፃናት ጥምቀትን) የማያደፋፍሩበት ምክንያት ነው (ዘፍ* 17፡[4-8፡19-21])፡፡

9 7. *ኃጢአተኞች አሁንም የሚገኙበት ማኅበረ ምእመናን እውነተኛ የክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን አይደለም የሚለው፤*

10 8. *አስቀድሞ ጳጳሳዊ የቅዱስ ቊርባን ሥነ ሥርዓቶች ይካሄዱባቸውና ይደገሙባቸው በነበሩት የአምልኮ ቤቶች ማንም ሰው በአምልኮ መሳተፍ ወይም ስብከት መስማት የለበትም የሚለው፤*

11 9. *ማንም ሰው በኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ መሠረት ከሚሰብኩትና የዳግም አጥማቂዎችን ስብከትና ስሕተት ከሚያወግዙት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ የለበትም፣ ማንም ሰው እነዚህን አገልጋዮች ማገልገል ወይም ለእነርሱ አንዳች ሥራ መሥራት የለበትም፣ ዳሩ ግን እነርሱ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያጣምሙ በመቊጠር ከእነርሱ መሸሽና እነርሱን ማግለል አለበት የሚሉት ናቸው፡፡*

*በሕዝባዊ ጒዳዮች ተቀባይነት የሌላቸው አንቀጾች*

12 1. *በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት በዐዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን የሚያስደስት የሕይወት አካሄድ አይደለም የሚለው፤*

13 2. *አንድ ክርስቲያን በበጎና በንጹሕ ሕሊና በየትኛውም መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ስፍራ ሊይዝና ተግባሮችን ሊፈጽም አይችልም የሚለው፤*

14 3. *አንድ ክርስቲያን መንግሥት በክፉዎች ላይ በተገቢው ሁኔታዎች በሚያካሂደው ተግባር መጠቀም የለበትም ወይም ዜጎች መንግሥት ባለውና ለጥበቃና ለመከላከያ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን እንዲጠቀም መማጸን የለባቸውም የሚለው፤*

15 4. *ክርስቲያኖች በበጎ ሕሊና መሐላ መፈጸም ወይም ለመስፍናቸው ወይም ለአለቃቸው በመሐላ አክብሮት መስጠት የለባቸውም የሚለው፤*

16 5. *በዐዲስ ኪዳን ዘመን መንግሥት ሕሊናውን ሳይጎዳ በወንጀለኞች ላይ የሞት ፍርድ ማስተላለፍ አይችልም የሚለው፤*

*በቤተ ሰብ ሕይወት ተቀባይነት የሌላቸው አንቀጾች*

17 1. *አንድ ክርስቲያን በበጎ ሕሊና የግል ንብረት ሊኖረው ወይም ሊይዝ አይችልም፣ ዳሩ ግን ሁሉንም ነገር ለማኅበረሰብ ማስረከብ ይጠበቅበታል የሚለው፤*

18 2. *አንድ ክርስቲያን በበጎ ሕሊና የሆቴል ሠራተኛ፣ ነጋዴ፣ ወይም የጦር መሣሪያ ሠራተኛ ሊሆን አይችልም የሚለው፤*

19 3. *የተጋቡ ሰዎች ለእምነት ሲሉ ሊፋቱና የትዳር ጓደኛቸውን ትተው ተመሳሳይ እምነት ያለውን ሌላ ሰው ማግባት ይችላሉ የሚለው፤*

*የሽዌንፌልደራውያን[76] (Schwenckfelders) የስሕተት አንቀጾች*

20 1. ክርስቶስ በሥጋው መሠረት ፍጡር ስለ ሆነ በመንግሥተ ሰማያት ስለሚገዛው ንጉሥ፣ ስለ ክርስቶስ ትክክለኛ ዕውቀት የላቸውም የሚለው፤

21 2. ክርስቶስ የለበሰው ሥጋ ሁሉንም መለኮታዊ ባሕርያት በይዞታውና በመሠረታዊ ክብሩ በዕርገቱ ጊዜ ከመቀዳጀቱ የተነሣ ክርስቶስ እንደ ሰው ከአብና ከቃሉ ጋር በሁሉም አንጻር እኩል ነው፡- ይህም በሥልጣን፣ በኃይል፣ በግርማና በክብር ረገድ ሲሆን፣ በዚህም ሁኔታ ከአሁን ወዲያ በክርስቶስ ያሉት ሁለት ባሕርያት አንድ ተፈጥሮ፣ አንድ የባሕርያት ጥቅል፣ አንድ ፈቃድና ተመሳሳይ ክብር ያላቸው ሆነው የክርስቶስም ሥጋ የቅድስት ሥላሴ ባሕርይ አካል ነው የሚለው፤

22 3. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሆነው፣ የሚታወጀውና የሚሰማው ቃል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን የማዳን ዕውቀት ለሰዎች የሚያስተምርበትና በእነርሱ መለወጥን፣ ንስሐን፣ እምነትንና ዐዲስ መታዘዝን የሚያስገኝበት መሣሪያ አይደለም የሚለው፤

23 4. የጥምቀት ውሃ ጌታ እግዚአብሔር እኛን እንደ ልጆች መቀበሉንና ዐዲስ ልደትን ማስገኘቱን የሚያትምበት መሣሪያ አይደለም የሚለው፤

24 5. በቅዱሱ እራት ኅብስቱና ወይኑ ክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን በእነርሱ አማካይነትና ከእነርሱ ጋር የሚያድልባቸው መሣሪያዎች አይደሉም የሚለው፤

25 6. በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእውነት ዳግም የተወለደ ክርስቲያን በዚህ ሕይወት የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹምነት ሊጠብቅና ሊፈጽም ይችላል የሚለው፤

26 7. [ኃጢአተኞችን] በአደባባይ ማግለልን የማትለማመድ ወይም መደበኛ የሆነ የውግዘት ሂደት የሌላት ማኅበረ ምእመናን እውነተኛ የክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን አይደለችም የሚለው፤

27 8. በግልና በእውነት ያልታደሰ፣ ዳግም ያልተወለደ፣ ጻድቅና ቅን ያልሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሌሎችን ሰዎች በውጤታማነት ሊያስተምር ወይም ተገቢና እውነተኛ የሆነ ቅዱስ ምሥጢር ለእነርሱ ሊያድል አይችልም የሚለው፤

*የዐዲሶቹ አርዮሳውያን ስሕተቶች*

28 ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ዘላለማዊ ባሕርይ ያለው በተፈጥሮው እውነተኛና የባሕርይ አምላክነት የለውም፤ ዳሩ ግን እርሱ ከእግዚአብሔር አብ በታችና ጐን ለጐን በመለኮታዊ ግርማ ያሸበረቀ ብቻ ነው የሚለው፤

*የሥላሴ ተቃዋሚዎች ስሕተቶች*

29 ይህ ከዚህ ቀደም በክርስትና ተሰምቶ የማይታወቅ ፍጹም ዐዲስ የሆነ የእምነት ክፍል ነው። እርሱም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስን የያዘ አንድ ዘላለማዊና መለኮታዊ ባሕርይ የለም፤ ዳሩ ግን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት የተለያዩ አካላት እያንዳንዱ አካል ደግሞ ከሌሎቹ የእግዚአብሔር አካላት የተለየ የራሱ ልዩ ባሕርይ ያለው ናቸው በማለት ያምናል፤ ያስተምራል፤ ይመሰክራል። ወይም ሦስቱም በሌሎች በሁሉም አንጻር በባሕርያቸው እርስ በርሳቸው ፍጹም የተለያዩ እንደ ሆኑ ሰዎች፡- እኩል የሆነ ኃይል፣ ጥበብ፣ ግርማና ክብር አላቸው ወይም ደግሞ በባሕርያቸውና በጠባያቸው እኩል አይደሉም ስለዚህ አብ ብቻ ዋናውና እውነተኛው አምላክ ይሆናል የሚለው፤

30 እነዚህንና እነርሱን የመሳሰሉትን አንቀጾች፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር የተያያዙትን ማናቸውንም ሌሎች ስሕተቶችና ከእነርሱም የሚመነጩትን ሁሉ ትክክል ያልሆኑ፣ ሐሰቶች፣ ኑፋቄዎችና የእግዚአብሔርን ቃል፣ ሦስቱን የእምነት መግለጫዎች፣ የኦግስቡርግን የእምነት

[76] የካስፐር ሽዌንፌልድ Caspar Schwenckfeld ተከታዮች።

መግለጫና የእርሱን መከላከያ፣ የስማልካልድ አንቀጾችንና የሉተርን የክርስትና ትምህርቶች የሚቃወሙ እንደ ሆኑ ቈጥረን እንቃወማቸዋለን፤ እናወግዛቸዋለንም። የነፍሳቸውን በጎነትና ድነታቸውን እንደ ውድ ነገር የሚቈጥሩ በከፍተኛም ሆነ ወይም በዝቅተኛ የማኅበራዊ ደረጃ ያሉ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ክርስቲያኖች ሁሉ እነዚህን መሸሽ አለባቸው።

31 ይህ፣ በመጨረሻው ቀን ጻድቅ ዳኛ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት መልስ ለመስጠት እንደምንፈልገውና፣ በስውርም ሆነ በአደባባይ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ምንም ነገር ለመናገር ወይም ለመጻፍ የማንፈልግበት፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ጸጋ በዚህ ትምህርት ለመጽናት የምንወሰንበት እንደ ሆነ ለመቀጠር በጥንቃቄ ካሰብንበት በኋላ የእኛ ትምህርት፣ እምነትና መግለጫ መሆኑን ለማሳየት በእውነተኛ ፈሪሃ እግዚአብሔርና እርሱንም በመማጸን በግንቦት 29፣1577 በበርገን በተደረገ ጉባኤ በአንድነት ተስማምተን በራሳችን እጅ ፈርመንበታል።

ዶ/ር ያዕቆብ አንድሪያ ደግፈዋል/ፈርመዋል።
ዶ/ር ኒኮላስ ሴልኔካር ደግፈዋል
ዶ/ር አንድሪው ሙስኩሉስ ደግፈዋል
ዶ/ር ክሪስቶፈር ኮርነር ደግፈዋል
ዴቪድ ቺትሪውስ
ዶ/ር ማርቲን ኬምኒዝ